የግእዝ ቅኔያት

የሰነ ጥበብ ቅርስ

ንባቡ ከነትርጓሜው

ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ
ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር

መጽሀፉን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለማሳተም መብቱ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ ነው ።

መጀመሪያ እትም 1980

አሳታሚ
የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት
አዲስ አበባ

የስራው ፕሮግራም ተሳታፊዎች

የአካዴሚው ጉባኤ የስነ ፅሁፍ ኮሚቴ አባላት ፤

አቶ ተክለ የድቅ መኩሪያ
ዶ/ር አምሳሉ አክሊሉ
ዶ/ር ሀይሉ አርአያ
አቶ መንግስቱ ለማ (የኮሚቴው አስተባባሪ) ።

የአካዴሚው ሰራተኞች ፤

አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ
በምስጠራ ትረካና እረማ
አቶ ቀፀላ መንግስቱ ዳንኤል
በዝግጅትና ቅንብር
አቶ አእምሮ ፈረደ
በትርጎማ
አቶ መልክአ ክርስቶስ ነቢዩ
በግእዝና አማርኛ ታይፕ ስራ ።

ምስጋና

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ጉባኤ የስነፅሁፍ ኮሚቴ አባላት በተለይም የኮሚቴው ሰብሰቢ አቶ መንግስቱ ለማ ለዚህ «የግእዝ ቅኔ የስነ ጥበብ ቅርስ» መፅሀፍ ዝግጅት ላበረከቱት ዘመናዊ የአሰራር ዘዴና የስራ ክትትል ፣

መፅሀፉን በማሳተም ረገድ ብርቱ ጥረት ላደረጉት ለአካዴሚው የቋንቋና የባህል ኤክስፐርት ለጓድ ዶክተር ኢሳይያስ አለሜና ለግእዝ ቅኔያትና መፃህፍት አንድምታ ትርጓሜ ክፍል ባልደረባ ለጓድ ቀፀላ መንግስቱ ዳንኤል ፣

በአካዳሚው ፅህፈት ቤት ስም አብዮታዊ ምስጋና አቀርባለሁ ፣

ከዚህም በቀር የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሃላፊዎችና ሰራተኞች መፅሀፉ ጥራት ባለው መንገድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ታትሞ እንዲወጣ ላሳዩት አብዮታዊ ትብብር ከልብ አመሰግናለሁ ፣

አሰፋ ገብረማርያም ተሰማ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ
ዋና ፀሀፊ

ማውጫ

መልእክት	ገፅ	9
መግቢያ	»	11
መቅድም		
(የቅኔ ጥበብ አጀማመርና አረማመድ)	»	15
የግእዝ ቅኔያት ከነትርጓሜያቸው	»	31
የባለ ቅኔዎች አጭር ታሪክ	»	433
የባለ ቅኔዎቹ ስም ከቅኔዎቻቸው ተራ ቁጥር ጋር	»	457
የተዛግጅ መፃህፍት ዝርዝር	»	463

መ ል እ ክ ት

ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን እኩሪ ታሪክ ያላትና የራሷ በሆነ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህል የበለፀገች አገር መሆኗ የታወቀ ነው ። ብዙ ብሄረሰቦችን ያቀፈች አገር በመሆኗም የበርካታ ቋንቋዎችና ስነ ቃሎች ባለቤት ናት ። ከዚህም የተነሳ ኢሲፓና አብዮታዊው መንግስት ለሰፈው ሀገብ የባህል እንክብካቤ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተውታል ።

ከታላቁ አብዮታችን መቀጣጠል ወዲህ በባህል ሚኒስቴር ስር በአዲስ ይዘትና ቅርፅ ከተቋቋሙት የምርምር ዘርፎች አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ የኢትዮጵያን ብሄረሰቦች ቋንቋዎችና ስነ ቃሎች በሳይንሳዊ መንገድ በመሰብሰብ ፣ በመዝገብ ፣ በማጥናትና በመመርመር ላይ ይገኛል ።

አኩሪ ከሆነው የባህል ቅርሳችን አንዱ የግእዝ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ በመሆኑ የአንድምታ ትርጓሜና የግእዝ ቅኔያትን ምርምር ስራ የሚያካሂድ በአካዴሚው ውስጥ ከተቋቋሙት የስራ ክፍሎች መካከል «የግእዝ ቅኔና መፃህፍት ትርጓሜ ክፍል» አንዱ ነው ። ክፍሉ የአካዴሚው ፅህፈት ቤትና የአካዴሚው ጉባኤ የስነ ፅህፍ ኮሚቴ በሚሰጡት መመሪያ መሰረት በርካታ ስራዎችን በማከናወን ላይ ሲሆን ፣ ይህ የመጀመሪያ የስራ ፍሬው የሆነው «የግእዝ ቅኔያት— የስነ ጥበብ ቅርስ» የተሰኘው መፅሀፍ ታትሞ መውጣት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው ።

ባህላዊው የግእዝ ቅኔ ለብዙ ምእት አመታት በግእዝ ቋንቋ ከመነገሩ ሌላ በፅሁፍ እምብዛም አይሰፍርም ነበር ። ከቅርብ ዘመን ጀምሮ ግን የግእዝ ቅኔያት ከታወቁ ሊቃውንት ተሰብስበው እንደታተሙና ለህዝብ እንደቀረቡ አይዘነጋም ። ረቂቅ የሆነው የግእዝ ቅኔ ስነ ፅሁፋዊ ጥበብ አሁን ወደ አግርኛ ተተርጉሞ ምስጢሩ ተተንትኖና ተብራርቶ ለህትመት መብቃቱ አንድ አይነተኛ እርምጃ መሆኑ አይጠረጠርም ።

የዚህ «የግእዝ ቅኔያት—የስነ ጥበብ ቅርስ» መታተምና መሰራጨት ብዙ ጥቅም አለው። በአንድ በኩል በባህርዩና በስልቱ ረቂቅ የሆነው የግእዝ ቅኔ ወደ እማርኛ ተተርጉሞና ምስጢሩ ተብራርቶ መቅረቡ ዘመናዊው የአማርኛም ሆነ የሌላው ብሄረሰብ ስነ ግጥም ከጥንታዊው የግእዝ ቅኔ መውረስ የሚገባውን ጥበባዊ ቅርስ ሊጎናፀፍ ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ የመፅሀፉ መታተምና መሰራጨት የግእዝ ቅኔ ከሰፈው ህዝብ የተሰወረ ምስጢርና ለጥቂት ምሁራን ብቻ የሚያገለግል ጥበብ መሆኑ ቀርቶ «ቅኔ ለብዙሃን» እንዲሆን መንገድ እንደሚከፍት ይታመናል።

በዚህ አጋጣሚ ይህ መፅሀፍ ታትሞ ለመውጣት እንዲበቃ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉትን ሁሉ በአካዴሚው ጉባኤ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።

አሰፋ ሊበን

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ ጉባኤ ሊቀ መንበር

መግቢያ

ዘመናዊ የስነ ጥበብ ስራዎች ከጥንታዊው ስነ ጥበባዊ ቅርስ ደገኛውንና ገንቢውን ገፅታ እየቀሰሙ የየራሳቸውን ወቅታዊ አመርታ ሲያካሂዱ የስነ ጥበብ ባህል ይራመዳል።

የግእዝ ቅኔ ከጥንት ጀምሮ ከፍተኛ ግምት የተሰጠው፣ በምእት አመታት የሚቆጠር እድሜ ያለው ልዩ ስነ ፅሁፋዊ ቅርስ ነው። ምጥንነቱ፣ ደንቡና ስርአቱ፣ ልዩ ልዩ መንገዶቹ፣ ዜማው፣ ሰምና ወርቁ፣ ወዘተ... እነዚህ ሁሉ የስነ ጥበብ ደረጃውን ከፍ ተኛነት ይመሰክራሉ። የቅኔ ደራሲያን ባብዛኛው ሊቃውንትና ምሁራን መሆናቸው፣ ሰሚዎቹና አንባቢዎቹም እነሱው መሆናቸው፣ የድርሰት ቋንቋውም ግእዝ መሆኑ የታወቀ ነው። ቢሆንም አልፎ አልፎ በአማርኛ ወይም በኦሮምኛ የተደረሱ ቅኔያት አልታጡም። (ለምሳሌ ቅኔ ቁጥር 203 እና ቁ.303)።

የቅኔ ይዘት በሙሉ እንኳ ባይሆን ባመዛኝ በሃይማኖታዊ ርእሰ ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ መሆኑ፣ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ በገንነበት ስርአተ ማህበር የተለመደ ነው። በሌሎች አገሮች የስነ ፅሁፍ ታሪክም ይህንኑ የመሰለ ሂደት ተከስቷል። በዚሁ ክልል ውስጥ ግን በማህበራዊ ሂስና በፖለቲካ ወገናዊነት ላይ የተመሰረቱ የቅኔ ድርሰቶች ይገኛሉ። (ለምሳሌ ቅኔ ቁ. 111፣ 289፣ 306)። የቤት ባለቅኔዎችም አልጠፉ። (ለምሳሌ ቅኔ ቁ. 250)።

ለቅኔ ጥበብ ማስተማሪያ አያሌ ልዩ ትምህርት ቤቶች በኢትዮጵያ ተቋቁመው ለምእት አመታት ባለቅኔዎችንና «ቅኔ ፈጣሪዎችን» ሲያፈልቁ መኖራቸው በባህል ታሪክ በኩል የሚያስገርም ደግሞም የሚያኮራ ነው። በአለንበት የአብዮት ወቅት ግን ዘመናዊ ትምህርትን በተሰሙ አንባብያን ዘንድ ሊተኮርበት የሚገባው የግእዝ ቅኔ ገንቢ ገፅታ ይዘቱን የሚገልፅበት ቅርፅ መንገድና ቴክኒክ መሆኑ አይጠረጠርም።

በዚህ በዚህ ረገድ የግእዝ ቅኔ ከብዙ ምእት እመታት ልምድ የተነሳ በጣም ከተራቀቀ ደረጃ ደርሶ ይገኛል ። ስለዚህ ዘመናዊው የስነ ግጥም ደራሲ ከሙያው እንፃር የቅኔን ቴክኒክና መንገድ በመመርመር የሚማረው አያሌ ቁም ነገር መኖሩ አሌ አይባልም።

ደገኛ ገፅታ ያላቸውን የሀገራችንን ባህላዊ ቅርሶች ለአዲሱ ትውልድ ማስተላለፍ በባህል እድገት መስክ የማይዘለል ደረጃ እን ደመሆኑ ፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ ከሌሎች ተመሳሳይ ተግ ባራቱ ጎን የግእዝ ቅኔያትን ትርጓሜ ምስጠራና ትረካ ስራ እስ ጀመረ ። ስራው በአካዴሚው ጉባኤ የስነ ፅሁፍ ኮሚቴ አመ ራር ተደግፎ እንዲከናወን ጉባኤው በወሰነው መሰረት ፤ ኮሚቴው ለስራው ዝርዝር መመሪያዎችን አውጥቶ ፥ የግእዝ ቅኔ እውቀት ያላ ቸው ሶስት ሰራተኞች በየደረጃው በስራው ተሰማርተዋል ። ከእ ነዚህ እንዱ አለቃ አለ ወርቅ ዘውዴ የታወቁ የቅኔ መምህር ናቸው። ስለዚህ ይህ መፅሀፍ የቡድን ስራ ውጤት ነው ።

የግእዝ ቅኔያትን በአማርኛ ተርጉሞ የማሳተሙ ተግባር ከዚህ ቀደምም በመጠኑ ተጀምሯል ። መምህር ይሄይስ ወርቁ በ«ንባብ ወትርጓሜ ዘትኤያት ፤ አእማደ ምስጢራት » (1960) ፤ አለቃ ይኩኖ አምላክ ገብረ ስላሴ በ«የቀድሞ ቅኔዎች ከነትርጓሜአቸው » (19 59) ፥ እንዲሁም አለቃ ለማ ሀይሉ በ«መፅሀፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ» »(1959) ቅኔያትን ከነትርጓሜያቸው አትርፈዋል ። በዚህ ስራቸው የተጠቀሱት ሊቃውንት ይመሰገናሉ ። ሆኖም በተተረ ጎሙ ቅኔያት ብዛትና በአቀራረብ ስፋት ይህን የአሁኑን መፅሀፍ የሚያህል የትርጓሜ ፥ የምስጠራና ሀተታ ፥ የትረካ ስራ ለማሳ ተም እስከ ዛሬ አልተሞከረም ። አሁን ይህንን መፈፀም መቻሉ የባህል ሚኒስቴርን የመሰረተው የኢትዮጵያ አብዮት ለባህላዊ ቅርስ ጥበቃና እንክብካቤ ተግባር የፈጠረለትን አመች ሁኔታ በጉልህ ያንፀባርቃል ።

የዚህ መፅሀፍ የመጀመሪያ አላማ ዘመናዊ ትምህርት ያላቸ ውን አንባብያን ከግእዝ ቅኔ ቅርስ ጋር ግስተዋወቅና ደረጃ በደ ረጃ ግለማሙድ ነው ። በዚሁ መሰረት ቅኔያቱን ለመገንዘብ የሚ

ያስችሉ መረጃዎችን ለአንባቢያን ለማመቻቸት ልዩ ጥረት ተደር ጓል ። የእያንዳንዱ ቅኔ ትርጉሙ ፥ ምስጠርና ሀተታው ፥ ታሪኩ ፥ በተከታታይ ተመዝግቧል ። ከባለቅኔዎቹ የግል ታሪክ ለጊዜው የተ ገኘው በመፅሀፉ መጨረሻ ክፍል በፊደል ተራ ባጭሩ ሰፍሯል ። በዚህ መፅሀፍ ቅኔያቸው የሚገኝ ባለቅኔዎች ሁሉ ስማቸው ከቅኔ ያቸው ተራ ቁጥር ጋር ለብቻው በፊደል ተራ ተደርድሯል ። የአ ማርኛው ፅሁፍ በሙሉ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ ጉባኤ በከ ፍተኛ የድምፅ ብልጫ በ1973 ተቀባይነት ባገኘው የፊደል ቁጠባ ሀሳብና ውሳኔ ላይ የተመሰረተ ነው ። ይኸውም ባጭሩ ሀ ፥ ሰ ፥ አ ፥ ፀ ፥ እንዲሁም ኋ ፥ ሟ ፥ ኗ ፥ ወዘተ.ን ይዞ ይራመዳል ።

የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የስነ ግጥም ደራሲያን የሚፈልቁት የሀገ ራችንን የስነ ጥበባት ቅርስ ደገኛ ገፅታ ከተራማጁ አለም ዘመናዊ እሴት ጋር አዋህደው የራሳቸውን ልዩ አስተዋፅኦ ከሚያበረክቱ ታታሪዎች መሀከል በመሆኑ ፥ የዚህ መፅሀፍ መታተምና መሰራ ጨት ለስነ ግጥማችን ወደፊት እመርታ አጋዥ እንደሚሆን ተስፋ አለ ። ወጣቱ ትውልድ የአገሩን የስነ ፅሁፍ ቅርስ ደገኛ ገፅታ ገንዘቡ አድርጎ ዘመናዊውን ከጥንታዊው ጋር ሲያገናዝብና ሲያ ዛምድ ነው ከፍተኛ ደረጃ ያለው የስነ ጥበብ እሴት ለሰፊው ህዝብ ሊያበረክት የሚችለው ።

በዚህ መፅሀፍ የሰፈሩት ቅኔያት በታወቁ ሊቃውንት ተደም ሲል ከተሰበሰቡና ከታተሙት መሀከል ለእንባቢ በጣም የማይፀኑ ትን በመምረጥ የተውጣጡ ፥ ደራሲዎቻቸውም (ከአንድ በቀር) ከዚህ አለም በሞት የተለዩ ናቸው ። ለዚሁ ምንጭ የሆኑት ሀው ልታዊ መፃህፍት የብላቴን ጌታ ሀሩይ ወልደ ስላሴ « መፅሀፈ ትኔ» (1918) ፥ የመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ «መፅሀፈ ቅኔ (ዝክረ ሊቃውንት) » 1963 ናቸው ። ቅኔያቱ ቤት በሚሙቱ በት የፊደል ተራ ተደርድረዋል ። በአማርኛው ትርጉም ሰሙ ከመ ርቱ በ«»ምልክት ተለይቷል ። ስርአተ ነጥብና አሀዝ በሙሉ ዘመ ናዊ ነው ።

የግእዝ ትኔያቱ ትርጉሜ በዚህ መልክና ቅርፅ ሲዘጋጅ ይህ የመጀመሪያው ጥራዝ ነው ። ተከታዩ እትም ወደፊት በቅርቡ ለአ ንባቢያን እንደሚደርስ በባህል ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካ ዴሚ ጉባኤ የስነ ፅሁፍ ኮሚቴ ሙሉ ተሰፋ አለው ።

መንግስቱ ለማ

የአካዴሚው ጉባኤ ም/ ሊቀ መንበር

መ ቅ ድ ም

የትኔ ጥበብ አጀማመርና አረማመድ

ከአለቃ አፈወርቅ ዘውዲ የተዘጋጀ ።

በስድስተኛው ምእት አመት በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መን ግስት የተነሳው ያሬድ በግእዝ መፃህፍት ምስጠር የተራቀቀ ሊቅ በመሆኑ ፤ ከመፃህፍት ጠቅሶ ከራሱም አንቅቶ አያሌ መዝሙራ ትን ከነዜማቸው ደርሷል ። እነዚህም መዝሙራት ያመ ድጓ ፣ ምእራፍ፣ ድጓ ፣ በተባሉ መፃህፍት ሰፍረው ከትውልድ ወደትውልድ ሲተላ ለፉ እስካሁን ደርሰዋል ።

የያሬድ የመዝሙር ድርሰት በግጥም ረገድ አብዛኛውን ቤት አልባ ቢሆንም ፣ አልፎ አልፎ ቤት እየሞታ ከስድ ንባብነት ወደ ጉት ነት ያመራ ፣ በሰምና ወርቅ የተመሰጠረ ፣ በሁለትም በሶስትም አም ስትም ቤት የተወሳሰበ ነው ። ቢሆንም ሂደቱ የትኔን መንገድ የተከተለ ነው።

ቤት አልባ ትኔዎችና ቤተኛ ትኔዎች ሁለቱም በያሬድ ድርሰት ውስጥ ይገኛሉ ። ለቤት አልባው ትኔ ምሳሌ የሚከተለውን ጥቅስ ከድጓ ይመለከቷል ።

1 ወብዙኃን ኖሎት መጽኡ
ወስእኑ ከሲቶታ ለእብን እምአፈ ዐዘቅት
እስከ ይመጽእ ያዕቆብ ።
ወከግሁመ መጽኡ ብዙኃን ነቢያት
ወስእኑ ከሲቶታ ለጥምቀት
እስከ ይመጽእ ዐቢይ ኖላዊ

የዚህና የሚለጥቁት የግእዝ ጥቅሶች የእግርኛ ትርጉማቸው በዚ ፅሁፍ መጨረሻ በየተራ ቁጥራቸው ለብቻው ሰፍሯል ።

በቤተኛው የያሬድ ትኔ ምሳሌ አሁንም ከያመ ድጓ እንጠቅሰለን ።

2 ሰገረ ክርስቶስ ሐዳስ ንድቅ
ዘበውስቴታ የኀድር ጽድቅ
ጸድቃን ኪያሃ እብደሩ እምውርቅ ።

እንዲሁም አርያም ከተባለው ከፍል የሚከተለው ሊጠቀስ ይችላል።

3 እምፈልፈለ ብዕል ገነት ንጉሥ ሰቀዩ
እምነቅዐ መንጌል ገራሀተ አርወዩ ።

4 በሄመ መለኮት ቀሰሙ ዒለመ
ውስተ ቤተ መርዓ እውገዙ ሰላመ
ሐዋርያት እምሕዝብ አእተቱ ፀራዊ ርጉመ ።

5 በትድስና ወበንጽሕ ምሉዕ ሥጋሁ ነደቀ
በሠረገላ ሱባኤ ተመጥቀ
ኤልያስ ከቡር እምኅለም ዘርኅቀ ።

ከዚህ በላይ ለእይነት ያህል የተጠቀሰው የያሬድ ቅኔ ቤተኛም ቢሆን ፥ ቤት አልባም ቢሆን ፥ ጉት ግጥም ነው ። (ጉት ማለት ጎታታ ያል ተጠቃለለ ፥ በመደበኛው የቅኔ ሀረግ አሰካክ ያልተቀናበረ ማለት ነው ።) ሆኖም ያሬድ በዚህ በታላቅ ስራው በዜማው ድርሰት ውስጥ ቅኔን በማስገባቱና በማዋሀዱ የቅኔን ሙያ አጎላው ። እርግጥ ከርሱ በሁዋላ የተነሱ ሊቃውንት የያሬድን ፈለግ ተከትለው እርሱ የጀመረውን ስራ አሰፋፍተዋል ። ይህ ግን ያሬድን ከቅኔ ቀደምት መስራቾች ዋነኛው ከመሆን አያግደውም ።

አንድ የዳር ሊቅ ስለ ያሬድ የደረሱት አጭር ዘይእዜ ቅኔ አለ።

6 ተትሕተ ያሬድ ዘኢተትሕተ
ለቅኔያቲሁ ደቂቅ እስመ ኢሐነጸ ቤተ ።

ሊቁ በዚህ ቅኔያቸው ፥ ያሬድ ከእርሱ በሁዋላ እንደ ተነሱት እንደ ደቀ እስጢፋና እንደ ተዋነይ ቅኔዎች ያለ ቅኔ ባለመድረሱ

ብቻ « የያሬድ ቅኔዎች ቤት አልባ ናቸው» ለማለት ሞክረዋል ። ነገር ግን የእነ ደቀ እስጢፋና የእነ ተዋነይ ቅኔያትም ቢሆኑ ከእነ ርሱ በሁዋላ ከተነሱት ሊቃውንት ቅኔያት የተለዩ መሆናቸው አይዘነጋም ። ስለዚህ «ያሬድ ለቅኔያቱ ቤት አልሰራም» አያሰኝም ። ባይሆን ያሬድ ከዜማ ደን ገብቶ ለቅኔ ቤት መሰሪያ የመዘዘው ሀረግ ረጅምና ቀጥተኛ አይደለም ፥ በሀረጉም የተሰራው ቤት ጠባብ ነው ቢባል እንኳ ያስሄዳል ።

ቅኔ ከጉት ግጥምነት ወደ ሙሉ ቤት ግጥምነት በመሸጋገር አስፈላጊው የተሟላለት ፥ ትምህርት ቤት የተቋቋመለት ፥ ጉብኤው የሰፋለት በዮሀንስ ገብላዊ መሪነት ነው ። ዮሀንስ ገብላዊ በሞድሳ (ላስታ) ገብሱን ወይም ገብላት በተባለች ቀበሌ የተወለደ ታላቅ ሊቅ በመሆኑ ፥ በትውልድ ቦታው «ዮሀንስ ገብላዊ» ተብሏል ፤ በፈላስፋነቱ «ዮሀንስ ዘፍልሱፍ» ተብሏል ። በእዜ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት (ከ1427—1460) የነበረ ነው ።

የሀንስ ገብላዊ የያሬድን ቅኔዎች መርምሮ የያሬድን ፈለግ ተከትሎ ቅኔን በሰምና ወርቅ ለማጉላት ምስጢሩን ለማራቀቅ መንገዱን ለማስፋት ቢተቹን ለመመላለት በቅቷል ። በዚያን ዘመን የእዜ ይኩኖ አምላክ ከተማ ታቦርና አርምንኤም በተባሉ ከአ ማራ ሳይንት (ከቦረና) ክልሏን በሚዋሰኑ ሁለት ተራሮች መካከል ነበር አቀማመጧ ። ዮሀንስ ገብላዊ ከዚያች ተቀምጠ የቅኔን ምስጢር አፍታታ አራቀቀ ፥ እውቀቱን አደላደለ ፤ የቅኔ ትምህርቱን ለእነ ወልደ ገብርኤል አስተማረ ።

በእዜ ዘርአ ያእቆብ ዘመን በዮሀንስ ገብላዊ ጊዜ የተደረሱ ቅኔያት እኒህን ይመስሉ ነበር ።

7 በመዝሙር እቀኒ በዘዐውርቱ እውታር
ለዘርዐ ያዕቆብ ጎር ዕበዮ በከመ ያሬድ መምህር ።

ይህ ጉባኤ ቃና በስንኙ አቀነባበርና በሀረጉ አሰካክ እንደ አሁኑ ጊዜ ጉባኤ ቃና ነው ። የሚከተለው እጣነ ሞገር ግን ከአሁኑ ዘመን እጣነ ሞገር ጋር አንድ አይደለም ፦—

8 ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ
ቃየል አበሰ እንበይነ ሉድ በላዕለ እጉሁ ቀኒአ
ሶምሶን ተሠግረ በደሊላ ምስጢረ ነገሩ ኀቡአ ኀቢአ

ምስለ ፀጉረ ርእሱ ላጸየት ጽንፆ
ብጹዕ እምእንስት ዘጉኖ ተንሢአ
ለንጉሥነ ዘርዐ ያዕቆብ ከሙ ይርድአ ።

ይህ የዱሮ እጣነ ሞገር ቤቱ አምስት በመ ሆኑ ከእሁኑ ዘመን ባለ ሰባት ቤት እጣነ ሞገር በሁለት ቤት ያንሳል ። ይህም የሚያመለክ ተው የቅኔ ጥበብ ከዘመን ወደ ዘመን ለውጥ እያገኘና እያደገ የሄደ እንጂ ባንድ ጊዜ ተስተካክሎ የተገኘ አለመሆኑን ነው ።

የዮሐንስ ገብላዊ ደቀመዝሙር የሆነው አባ ወልደ ገብርኤል ለሰምረ አብ (ሰምረ ክርስቶስ) አስተማረ ። በእኔ በእደ ማርያም ዘመነ መ ንግስት (ከ1460—1470) ሰምረ አብ ቅኔ ሲያስተምር እርሱና ንጉስ በእደ ማርያም በቅኔ ጥበብ የተነሳ ተጣሉ ። የቅኔው መንገድ ለንጉሱ እንግዳ ስለሆነበት ፣ ንጉስ የቅኔውን አነጋገር ከድንፋታ ቆጥሮ ቅኔውን አቃለለው ፤ እንደ መቀባጠር አድርጎ ተመ ልክቶት የሰምረ አብን ሙያ አኩሰሰበት ፤ የመምህሩንም የአባ ወልደ ገብርኤልን ቅኔ ዘራፊነት ነቀፈበት ። «እንተ ከነመ ምህርህ እንዲያው ትቀባጥራለህ እንጂ ፣ ከሌላ ከማን ዘንድ አግኝተኸዋል ? » አለው ።

ሰምረ አብ ግን ለንጉሱ በጎ ቃል መልሶ ፣ «እንዲህ ካልከ ሁለታችንም ሱባኤ እንግባ ፤ ያን ጊዜ ቅኔ ደኅኖ ትምህርት ስለመ ሆኑ ምስጢር ይገለጥልናል » አለው ። ሁለቱም ለየብቻቸው ሱባኤ ገቡ ። ከሱባኤ ሳሉ ለንጉሱ ምስጢር ተገለጠለትና ፣ እንደ ቅኔ መ ምህሩ እንደ ሰምረ አብ ሁለት ቤት ቅኔ ዘረፈና ተቀኘ ይባላል ። ቅኔውም የሚከተለው ነው ።

9 ድኅረ ተሰብረ አጽንፆ ለሰብእናነ ልሕዙት
ለብሐዊ ክርስቶስ በግየ ሐዲስ ጥምቀት ።

ንጉስ በእደ ማርያም ይህን ቅኔ የዘረፈበት ቀን የቃና ዘገሊላ እለት ነበርና ፣ በዚህ ሳቢያ የቅኔው ስም «ጉባኤ ቃና » ተባለ ይባላል ።

ዘረፋ ማለት ፥ አልቃሾችና ዘፋኞች ሳያወጡና ሳያወርዱ በቱ ማታ (በፍጥነት) እንደሚገጥሙት ግጥም ቅኔን ለተቀባይ (ከፍ ባለ ድምፅ ለሚያሰማ) መንገር ነው ። አፍጣኝ ዘራፊ ሁለትም ሶስትም አራትም ተግሪዎች (አዚያሚዎች) አቁሞ ለሁሉም በተራ ልዩ ልዩ ቅኔያትን ያቀብላል ። እንደ መምህር ሰረገላ ብርሃን ፤ ዳተኛ ዘራፊ ግን ሀሳብ ማውጣትና ማውረድ ስላለበት ከአንድ ተቀባይ አያልፍም።)

ሰምረ አብ ለልጄብ ፥ ልጄብ ለኤልያብ ፥ ኤልያብ ለተዋነደና ለድያቅ ወልደ ማርያም አስተማረ ። ከዚህ በሁዋላ መንግስት ታወ ከና ግራኝ ተነሳ ። ድድቅ ወልደ ማርያም በዳሞ ንት (ጎንደር) የጨ ረቃ ከሚባል ቀበሌ ገባ ፤ ተዋነይ በጣና ባህር ውስጥ ደቀ አስጢፋ ከሚባል ደሴት ገብቶ ተቀመጠ ።

ከድድቅ ወልደ ማርያም ቀጥሎ የጨረቃ በሚባለው ቦታ ድድቅ ድድቅ ተብለው የተሰየሙ ስደስት መምህራን አስተምረዋል ። (ድድቅ ማለትም የእውቀት የምስጢር ጀግና ማለት ነው ።) በስድስ ተኛው ድድቅ ጊዜ የቅኔ ጉባኤ ሰፋ ። ስድስተኛው ድድቅ ሶልያና ወልደ ማርያምን አስተማረ ። ሶልያና ወልደ ማርያም ለሚጫው (ጎጃም) ማእበል ወልደ ሀይወት አስተማረ ፤ ማእበል ወልደ ሀይ ወት ለደብረ መዊእ (ጎጃም) ሊቀ ሀሩያን ዘገየና ለሚካኤል ደብር (ጎንደር) ጌቴ ገሞራው (አለቃ ጌታነህ) አስተማረ ። «ማእበል ፣ ገሞ ራው» የሙያ መጎሳ ስም ነው (ቅኔውን የሚያነርፍ ማለት ነው ወይም እሳት የሆነ) ። እስከዚህ የተወሳው በቅኔ ሊቃውንት በኩል ስለቅኔ አመጣጥ የሚተረከው ነው ። በሌሎች የቅኔ ሊቃውንት በኩል ደግሞ እንደ ሚከተለው ይተረካል ።

ደቀ አስጢፋ የተባለ ሊቅና ፈላስፋ በእኔ በእደ ማርያም ዘመን ወደ ዕርእ (ግሪክ) አገር ወርዶ ሰባት አይነት እውቀት ተምሮ መጣ ። ከዚህ ውስጥ ሰባተኛው ቅኔ ስለሆነ በሊቃውንት ዘንድ ተወዶ ትምህርት ሆኗል ። ደቀ አስጢፋ የቅኔን ጥበብ ለእኔ እስከንድር (1470—1486) እንዲሁ ም ለሀዊራ ፣ ለመንክራ ፣ ለብሁርና ለሌላው እስከንድር አስተማራቸው ።

ደቀ እስጢፋ በንጉሱ ግቢ ቤተኛ በመሆኑ ከንግስቲቱ ታማ 1 ታማኝ አሽከርም በዘዲ ለንጉሱ ነገረበት ። እዜ እስክንድር አሽኩሩ እንደመከረው እንድ ቀን ድንገት ሳይታሰብ ሄዶ ከነበረበት ቢመ ለስ ፡ ቤት ተዘግቶ ደቀ እስጢፋ ከእቴጊይቱ ጋር የፍልስፍናን ነገር ሲጨዋወት ንጉሱ ሰማ ። ቤቱ ስለተዘጋበት ንጉሱ እውቂ ሆኖ እየር ከረ ፡ ደቀ እስጢፋም እውስጥ ሆኖ ፈርቶና ደንግጦ 1 ሁለቱ የሚከ ተሉትን ቅኔዎች ተዛርፈዋል ይባላል ።

10 ሥላሴ

ዘእስክንድር (እዜ)

ምንት አገበረከ
ቍንጽለ ገዳም አንተ ቤተ አንበሳ በዊአ ?
ኢትሰምዕኑ ጥሕረቶ በአፍአ ?
አስሙ እምኀቤየሰ ተጋንዮትከ ጠፍአ ፡
አንበሳ በኀይሉ እምድኅረ ሞአ
ኅድግሰ ዘለከ ብፅዐ
ጽንሐ ለእሳት ከሞነከ ብርዐ

(የዚህ ቅኔ ትርጉሙ ከነሀተታው በቁ. 286 ይገኛል ።)

11 ሥላሴ

ዘደቀ እስጢፋ

አጋግ ይቤ «ከመዝኑ ሞት መሪር ፡»
በጊዜ ረገዞ ሳሙኤል መምህር
ወሰራቁ ንግሥት አነ ደቀ እስጢፋ ሕሱር ፡
አንበሳ እስክንድር ፡
እግለ አንበሳ እንዘ ትጥሕር
እምእርአይከ ተኅጠኒ ምድር ።

(ይህ የጻር ጊዜ ስሳሴ ቅኔ ነው ፡ በሁሞላ በጎንደር ሊቃውንት ቅኔ በጉ ባኤ ሳይሻሻል የነበረው አይነት ትርጉሙ ከነሀተታው በቁ. 197 ይገኛል ።)

እዜ እስክንድር በዚህ ጊዜ ደቀ እስጢፋ ከንግስቲቱ ጋር የነ በረበትን እልፍኝ በአሳት አጋያት ። ደቀ እስጢፋ ግን ከነእቴጊይቱ ከታስሎሙ ወጥቶ ፡ ወደ ማና ባህር ገብቶ ፡ የሰፈረባትን ደሴት በም ትሀት ሰውር ተቀመጠ ። ቦታዋንም ደቀ እስጢፋ ብሎ በስሙ ግስጠራቱ ይነገራል ።

የንጉሱ እዝማሪ ስለንግስቲቱ መሰወር ሲያመሰጥር ፡

«እጅዋን ተሰብራ ከመሀሉ
ደቃለች አሉ » ብሎ ዘመረ ይባላል ።

ደቀ እስጢፋ በጎጃም እገው ምድር ፡ በበለያ ምድር አካባቢ የምትገኝ ቦታ ናት የሚሉም አሉ ።

ደቀ እስጢፋ ስለተባለው የቅኔ አባት ከአንድ የጻር ሊቅ የሚከተለው መወድስ ቅኔ ተደርሷል ።

12 መወድስ

ደቀ እስጢፋ ጻድቅ አመ እስክንድር
በመንፈስ ቅዱስ ነበበ ሐሳባተ ነቢይ ቅኔያተ
እምቅኔያቲሁ ለያሬድ እንበለ ያትርፍ አሐተ ።
ወከመ ኢይሳድሩ ውስተ አፍአ
ለቅኔያቲሁ ሐነጸ አብያተ
ሰብዓ ወሰማኒተ ፤
ወጠረረ እሙን አብያት እስከነ ይእዜ ኢተነስተ ።
ሐዊራሰ ወመንከራ ዘተጋብኡ ድርገተ
ዘምስለ ብሑር ወእስክንድር አስተጋብኡ መንክራተ

መንከራተቷ ሙትሩ ወተመሰሉ መጥባሕተ ፤
ለመጥባሕት እስመ ልግዱ ከፈለ ዋሕድ እርባዕተ ።

(ትርጉሙ በቁ. 226 ይገኛል)

ሊቁ በቅኔው የሚገልጠው በአዴ እስክንድር ጊዜ ደቀ እስጢፋ ቅኔያትን እንዳስተማረና ፣ ያስተማረውም ከያሬድ ቅኔዎች ሌያይዘ እንደሆነ ፣ ሀዊሬ መንክራ ፣ እስክንድርና ብሁር የተባሉ የደቀ እስ ጢፋ ደቀ መዛሙርትም የያሬድን የድጓ ድርሰት በአራት ክፍል መድ በው እንዳደራጁት ነው ።

ባጠቃላይ ሲታይ ግን ፣ የቅኔ ጥበብ ከቀድሞ ሊቃውንት ወደ ያሬድ ከያሬድ ወደ ዮሀንስ ገብላዊ ሊወርድ ሲዋረድ በመጣው እንዃር፡ ደቀ እስጢፋም በግል ስጦታው ከፍተኛነት መጠን ቅኔን ዘየነው ፤ አጭሙ መልካም አደረገው ቢባል እንጂ ፣ የመጀመሪያው የቅኔ ደራሲ እሱው ደቀ እስጢፋ ነው ቢባል የሚታመን ታሪክ አይመስልም። በጠቅላላ ሊባል የሚገባው ፣ ያሬድ የጀመረውን ቅኔ ዮሀንስ ገብላዊ ጨረሰው ፡ የዮሀንስ ገብላዊን ቅኔ ተዋነይ እንዲሁም ደቀ እስጢፋ ዘየኑት ፡ በሁዋላም የነንደር ሊቃውንት በጉባኤ አሻሻሉት ማለት ይመስለናል ።

በዚህ አይነት ካደገና ከደረጀ በሁዋላ ቅኔ በሰባት ቤት ተከፍሏል። (እዚህ ላይ «ቤት» ማለት መገን ወይም አይነት ነው)። ሰባቱ የቅኔ ቤቶች ፡ ማለትም ቅኔ የተስፋፋባቸው ቦታዎች የሚከተሉት ናቸው። የታቦር (ሳይንት ፡ ወሎ) ፡ የጨረቃ (ጻውንት ፡ ጎንደር) ፤ የአብጺቆም (ዋድላ ፡ ላስታ) ፤ የነንደር (በጌምድር) ፤ የነንጅ ፡ የዋሸራ ፡ የሚጣ (ጎጃም) ።

ይሁን እንጂ ከእነዚህ ቤቶች ውስጥ በጣም የጎሉት የዋድላ ፡ የነንደር ፡ የነንጅ ፡ የዋሸራ ቅኔ ቤቶች ናቸው ። ሆኖም የቅኔ ስሩ አንድ ነው ፤ በየቦታው ስሩ አይለያይም ። እርግጥ ያነዳንዱ የቅኔ መንገድ ጉላቱ ከቦታ ቦታ ሊለዋወጥ ይችላል ።

የቅኔ መስመር በሀረግ ይከፈላል ፤ ሀረግ በስንኝ ይከፈላል (ይመደባል) ። ቅኔው ደግሞ በሚዜምበት የዜማ አይነት መሰረት ግእዝ ፡ እዝል ፡ አራራይ ቅኔ ተብሎ ይለያል ።

ዋናዎቹ የቅኔ አይነቶች ከሀረግና ከቤታቸው ቁጥር ጋር ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል ። የዝርዝራቸው ቅደም ተከተል በቅኔ ትምህ ርት ቤቶች ደረጃ በደረጃ በትምህርትነት በሚቀርቡበት ተርታ ነው ።

የቅኔው ስም	የሀረጉና የቤቱ ልክ	
	ሀረግ	ቤት
ግእዝ ጉባኤ ቃና	4	2
ዕዝል ጉባኤ ቃና	4	2
ዘአምላኪየ	5	3
ሚበዝኁ	8	3
ዋዜማ	9	5
ሥላሴ	11	6
ዘይእዜ	11	5
አጭር ዘይእዜ	4	2
ግህልከ	7	3
መወድስ	18	8
ኵልከሙ (መወድስ)	20	9
ግእዝ ክብር ይእቲ	8	4
ዕዝል ክብር ይእቲ	8	4
ግእዝ እጣነ ሞገር	18	7
ዕዝል እጣነ ሞገር	18	11
ሐዋርያቲሁ ከበበ	4	2
ሕንጸሃ	3	2
ድምር	160 ሀረጎች	78 ቤቶች።

የቅኔ ቤቶች ጠቅላላ ድምር 78 ነው ። እላይ ከተዘረዘሩት በተ ጨማሪ ባለሶስት ቤት አጭር ዋዜማ ፡ ባለ ሁለት ቤት አጭር ዋዜማ ፡ እንዲሁም ባለ ሁለት ቤት አጭር ኩልከሙ አሉ ። ቢኖ ሩም ፡ ከላይ በተጠቀሱት መደበኛ የቅኔ አይነቶች ይጠቃለላሉ እንጂ በተለይ አይቆጠሩም ። (ስለቅኔያቸው ስምና አግባብ በመፅሀፈ ቅኔ (ዝክረ ሊቃውንት) ከገፅ 17—24 የተግፈውን ይመለከቷል።)

የቅኔ ዋነኛ መሰረቱ የሰምና ወርቅ ምሳሌ ነው። የሰምና ወርቅ አውራ መንገዶች የተወሰኑ ናቸው፤ በአውራ መንገዶቹ ውስጥ ግን ከሶስት መቶ በላይ የሚሆኑ ስላች መንገዶች መኖራቸው የታወቀ ነው።

በቅኔ ትምህርት ቤት ጀማሪው ተማሪ በጉት ግጥም ሲለማመድ ይሰነብትና ጉባኤ ቃና ይቀጥራል (ይደርሳል)፤ ሰምን ከወርቅ ምሳሌን ከምስጢር ያጋጥማል። ሆኖም የቅኔውን ዜማ (የሀረግና የስንኝ ልክ)፥ እንዲሁም ሰዋስውን በተሉ አይጠነቅቅም። መምህሩ ያርሙለታል ያስተካክሉለታል፤ ያን የታረመውን ደግም በትምህርት ከእርሱ ከፍ ያሉ ተማሪዎች ያስቀጥሉታል (ያሰጠኑታል)። መምህሩ የሚዘርፉለትን (ከልባቸው አንቅተው የሚያወጹለትን) ቅኔ እየቀጠለ (እያሰላሰለ፥ እያጠና) ከሌሎቹ ተማሪዎች ጋር ያስተያያል ያመዛዝናል። ጀማሪው የመምህሩን ቅኔ እስመ ስሎ የራሱን ቅኔ ለመድረስ ይጥራል። በብዙ ጥረትም ጉባኤ ቃናን ይለያል (ያውቃል)። ምስጢሩን ዜማውን ጠንቅቆ ሲያውቅ፥ ከጉባኤ ቃና ወደ ዘለግ ያለ ይሸጋገራል። ይህን በመሰለ ጥረት ከደረጃ ወደ ደረጃ እየተሸጋገረ ሲሰለጥን፥ እንደ ትምህርት ስጦታው፥ በዘጠኝ ወርም፥ በአመትም፥ በአመት ከመንፈቅም ከብር ይደቲን ከአጣነ ሞገር ጋር ይቀኛል። ከሁለት አመት እስከ ሶስት አመት እስከሚሞላው ድረስ እውቀቱን ያጠናክራል።

ከዚህ በሁዋላ የቅኔ አስተማሪ መሆን የፈለገ እንደሆን፥ ከመምህሩ ጉባኤ ሳይለይ ሌሎችን ተማሪዎች እያስጠና ይቆያል። እያደር መምህሩ በሚዘርፉበት ጊዜ የመምህሩን ቅኔ ነጠቃ ይጀምራል፤ ግለትም መምህሩ በጀመሩት ቅኔ ላይ የራሱን እየተካ ቅኔያቸውን ይሞላል። ቢቀናውም ባይቀናውም መገሰሱን (መርከሩን) አይተውም።

ነጠቃ፥ ባለቅኔው ገና አንድ ቤት ሲመታ፥ የቅኔውን የምስጢር ፈለግ ተከትሎ የሚቀጥለውን አንዱን ቤት ወይም ሁለቱን ቤት ከራስ በመተካት ቅኔውን መሙላት ነው። ሆኖም፥ አገኘ አጣ

ውን በነጠቃ የሚናገረው ምክሪ ብዙ ሲሆን፥ የባለ ቅኔው የልቡን የሚነግረው ከስንት አንዱ ነው። ለምሳሌ ያህል የደብረ ወርቅ ማር ያም (ጎጃም) ባለቅኔ መጋቢ አይቼህ

« እስከነ ይቤ እጽፍክ ዘበእምሳለ ርግብ ፈነውኮ »

በማለት የዋዜማ ቅኔያቸውን ሶስተኛ ቤት ሲናገሩ፤ የጎንጅ የቅኔ መምህር ቄሰገበዝ ካሳ

«አይቴኑ ባቢሎን ኢያሪኮ
ወአይቴኑ ጻንኤል ተሀውኮ ?»

ብሎ በመናገር ሁለቱን ቤቶች ከባለ ቅኔው መንጠቃቸው ይጠቀሳል፤ ሙሉው ቅኔ ከነትርጉሙ በቁ. 296 ይገኛል።

ቅኔው መልካም ሲሆን ለነጠቃ ያመረታል፤ ምስጢረ ቢስ ሲሆን ነጣቂን አያነሳሽም። እዋቂ ባለ ቅኔም ሲነጠቅ አይከፋውም። በዚህ አይነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥም በትምህርት ቤትም ሁለት ሶስት አራትም ነጣቂዎች በአንድ ጊዜ በነጠቃው ተግባር ይራኮቱበታል።

(ነጠቃ ስርቆት አይደለም። አንዳንድ ደካማ ባለቅኔ በሌላው ሰው ስራ ለመሰነን፥ ከሚደነቁት ቅኔዎች በከፊል ወይም በሙሉ ይሰርቅና ይቀኛል። ስርቆቱ የታወቀበት እንደሆነ፥ ስሚዎቹ « ተብሎብሃል » ይሉና ያሳፍሩታል። ለምሳሌ የዋሸራውን የመምህር ተክሌን (የዋሸራ ተክሌን) ቅኔ እንዱ ደብተራ ሰርቆ በትግሬ አገር ሲቀኝ የሰሙት ደብተሮች « ቅኔውስ ደረሰን፥ የኔታሳ (ተክሌ) ደህና ናቸው ወይ ?» አሉት ይባላል። የቅኔ ስርቆት እንደ ገንዘብ ሌብነት የሚያስደበድብና የሚያስወነጅል ነበር። ልባሞቹ ባለቅኔዎች ግን እንደዚህ ካለው ነውር የነጹ ናቸው።)

ለእጩው የቅኔ መምህር ነጠቃው በተናው ጊዜ በመምህሩ ትእዛዝ ቅኔ ተቀባዩ (ድምፁን ከፍ አድርጎ ቅኔ ለጉባኤው የሚያሰማው ተረኛ ተማሪ) እየቀጠለ በጎላ ድምፅ ቅኔውን ያንብለታል። እጩው መምህር ከዚህ እያይዞ መምህሩ ግታ ግታ የሚዘርፏቸውን ቅኔዎች ግልበጣ ይጀምራል። (ግልበጣ የሌላውን ሰው ቅኔ ቤቱንም ምስጢሩንም አፍርሶ የራስን ቅኔ መተካት ነው።



አብዛኛውን ጊዜ የሚገለበጠው ቤቱ ብቻ ነው ፤ ዋናው ግን የምስጢር ግልበጣ ነው ።)

እጩው መምህር በዚህ ሁኔታ ጥቂት ከቆየ በሁዋላ ከመምህሩ ጋር ተራ ገብቶ በፈረቃ ለተማሪዎች ትኔ ይዘርፋል ፤ የተዘረፈውን እየፈታ ያስረዳል ፤ ተማሪዎች የቆጠሩትን ቅኔ ያስነግራል (ይሰ ግል) ፤ ዘረፋውም ግስነገሩም በደረጃ ነው ፤ ቅኔውን ሁሉ በአንድ ጊዜ አይደለም ። ለምሳሌ መጀመሪያ ከጉባኤ ቃና እስከ ዋዜማ እንዲዘርፍና እንዲያስነግር ከመምህሩ ይፈቀድለትና በዚህ ሂደት ሲያዘግም ይቆያል ። ቀጥሎ እስከ እጣነ ሞገር ይዘርፋል ፤ ያስነግራል ።

ከዚህ በሁዋላ እጩው አስተማሪ ከመምህር ወደ መምህር እየተዛመተ የቅኔን መንገዶች ፣ የሰዋስውን ጠባቦች ይቀጥላል ። እንዲህ እያለ ከአምስት እስከ ሰባት አመት ፣ ከዚያም በላይ በእጩነት ይቆይና ፤ በቅኔ መምህርነት ይመረቃል ። ግለትም መምህሩ ይመርቁትና እንዲያስተምር ይፈቀድለታል ።

ከተመረቀ በሁዋላ አምስት ፣ አስርም ፣ አስራ አምስትም ተማሪዎች ከመምህሩ ተሰጥተውት በአንድ ገጠር (አነስተኛ ቤተ ክርስቲያን) ወይም በደብር (ከፍ ያለ ቤተ ክርስቲያን) ወንበር ዘርግቶ ጉባኤ አስፍቶ ማስተማሩን ይቀጥላል ። ብር ነቀል (አፍለኛ) ከመሆን አልፎ ስመጥር ሲሆን ተማሪውን ያንጋጋዋል ። አስተማሪው በመኖሪያ ቤቱ ዙሪያ ለተማሪዎቹ መኖሪያ የሚሆኑ ጎጆዎችን በቅድሚያ አሰርቶ ነው ማስተማሩን የሚጀምረው ። ተማሪው እየለመነ ምግቡን ያገኛል ።

ተማሪው ሁሉ ለልመና ከየተሰማራበት ሲመለስ ፤ ሰሞነኛው (ተረኛው) ተማሪ ግለት ለአንድ ሳምንት እሳት ማንደድ ተራው የሆነው ተማሪ ከማህበር ቤት (ትምህርት ከሚሰጥበት ቤት) ይገባና ያጨበጭባል ። በዚህ ጊዜ ተማሪዎቹ ከየጎጆአቸው እየወጡ በማህበር ቤት ይሰበሰባሉ ። ወዲያው የዘወትሩን ግህበራዊ ፀሎት አድርሰው በትናንትናው ግታ ከመምህሩ የተዘረፉላቸውን ቅኔዎችና እነሱም ለመምህሩ የነገሯቸውን ቅኔያት ሲቀጣጥሉ ይቆያሉ ።

መምህሩ ሲገቡ ተማሪው ሁሉ ግር ብሎ ይነሳል ። መምህሩ በከፍተኛ የእንጨት አልጋ ላይ ተቀምጠው «ይግለጥልን» ይሉና አቡነ ዘበሰማያትን ያስደግማሉ ። ለጥቆ «ተቀበል ፤ ባለተራ» ይላሉ ። በዚህ ጊዜ ባለተራው (ግስ መቀበል ተራው የሆነው ተማሪ) ይቆምና በትናንቱ ካረፈበት እንስቶ እንድ ባንድ ያጠናውን ግስ በቃሉ ይወጣዋል (ያነበዋል) ። መምህሩም ተረኛው ተማሪ ካነበበው ሌላ የገደፈውንም (ያላነበበውን) ተጨማሪ ግስ ያውርዱለታል ። በዚህ አይነት ከነገው ክፍል ግስ ሲደርስ «በቃ» ይሉና ባለተራው ተቀምጦ ከጓደኞቹ ጋር እየተቀባበለ (እየተረዳዳ) ያጠናል ።

ቀጥሎ ሶስት ተማሪዎች ተራ በተራ በመፈራረቅ ሶስት ጊዜ ወደላይና ወደታች (ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ፤ ደግሞ ከመጨረሻ ወደ መጀመሪያ) የግእዙን ቃላት ዝርዝር ከነፍቺው ሲዘልቁት ሌሎቹ ተማሪዎች በህብረት አማርኛውን ይቀበላሉ (ይናገራሉ) ። በመምህሩ የተዘረፈውን ቅኔ ተማሪው ሁሉ በጓድ በጓዱ እየሆነ ንባቡን አፈታቱን ትንተናውን ከአጠናና ምስጢሩን ከተረዳ በሁዋላ የመምህሩ ዘረፋ ደረጃ በደረጃ (ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ) ይቀጥላል ። ዘረፋው ሲፈፀም መምህሩ «የሰማነውን በየልቡናችን ያሳድርብን » ብለው አቡነ ዘበሰማያትን ደግመውና አስመርቀው ፤ እሳቸውም ተማሪዎቹም ወደየቤታቸው ይሄዳሉ ።

ይህን በመሰለ ሂደት ግሱ ከሀ እስከ ፐ ድረስ እየተገሰሰ ፤ ቅኔውም ከጉባኤ ቃና እስከ እጣነ ሞገር ድረስ እየተዘረፈ ይጠናል ። በየቀኑ ከአምስት ሰአት እስከ ዘጠኝ ሰአት ቅኔ ነገራው ይካሄዳል ፤ ቅጠላውም ይቀጥላል ። በየሳምንቱ አርብ ግታ የቅኔ ዜማ ይጮሃል ፣ ቅኔዎችም ለተማሪዎቹ እየታደሉ ቅዳሜ ጠዋት በማህበር ቤት ተማሪ ለተማሪ መሪና ተመሪ ሆነው ይቀኟቸዋል ። ጀማማሪዎች በትምህርት ቤት ራሳቸው የደረሷቸውን ቅኔዎች እንዲቀኙ መደረጉ በጉባኤ ፊት ቀርቦ ቅኔ መናገርን ለማስለመድና ፍራትን ለማስወገድ ነው ። ተመራቂ (እንዲቀኝ ከመምህሩ የተፈቀደለት) በቤተ ክርስቲያን ቅኔውን ለማህበሩ እንዲፈታ የሚገደድበት ጊዜ ይመጣል ። በዚህ ጊዜ የጋለ ክርክር ይቀጥላል ፤ መምህሩ ችግሩን በመፍታት ያስረዳሉ ።

እንግዶች ተማሪዎችን ኗሪዎቹ ተማሪዎች ተቀብለው ፤ በየ ጎጆአቸው አሳርፈው በሽሚያ እግራቸውን አጥበው ምግብ መግበው፡ በራሳቸው መኝታ አስተኝተው፡ሲያስተናግዷቸው ይሰነብቱና «ጓዴ»፡ «አይዋ» እያሉ በማናቸውም ነገር ያላምዷቸዋል ። እንግዶቹም ከሰዓዱ በሁዋላ የራሳቸውን ጎጆ ይሰራሉ ።

የጥቅሶቹ ትርጓሜ ።

1 ብዙ እረኞች መጡና
ደንጊያይቱን ከውሃ ጉድጓድ
አፍ ማንሳት ተሳናቸው
ያእቆብ እስኪመጣ ድረስ ።
እንደርሱም (እንደዚሁም) ብዙ ነቢያት መጡና
ጥምቀት ማጥመቅ አልቻሉም
ታላቅ ጠባቂ (ክርስቶስ) እስኪመጣ ድረስ ።

2 የክርስቶስ አገር አዲስ ቤት
ፅድቅ/ እንግዳ የሚያድርባት ናት ፤
የድኃን (እውነተኞች) እርሷን ከወርቅ መረጡ ።

3 ከብልፅግና/ ኗኗቴ የንጉስን (የክርስቶስን) ጓሮ አጠጡ ፤
ከወንጌል/ ምንጭ እርሻውን አረሱ ።

4 በመለኮት ጨው አለምን አጣፈጡ
በሙሽራ ሜጉላ ቤት ሰላምን አርከፈከፉ ፤
ሀዋርያት የተረገመ ጠላትን
ከሀዘብ አስወገዱ ።

5 በትድስናና በንፅህና አዳራሽ ስጋውን ገነባ
በሰረገላ ወደ ላይ መጠቀ
ከአለም የራቀ ክቡር ኤልያስ ።

6 ያልተዋረደ ያሬድ ተወረደ ፤
ለቅኔዎቹ/ ልጆች ቤት አልሰራምና ።

7 በአስር አውታር መዝሙር እቀኛለው
የቸር ዘርአ ያእቆብ ገናናነቱን ፤ እንደ መምህር ያሬድ ።

8 ቃየል ስለሱድ በወንድሙ ላይ ቀንቶ በደለ ።
ሶምሶን ስውር የነገሩን ምስጢር ሰውሮ በደሊላ ተጠመደ
እርሷ ከራሱ ጠጉር ጋር ሀይሉን ላጨች ።
ተንስቶ ከሌቶች የሸሸ ምስጉን ነው ፤
ንጉሳችን ዘርአ ያእቆብን ይረዳው ዘንድ ።

9 ከተሰበረ በሁዋላ ሰውነታችን/ ገንቦን አጠናው
ሸክለኛው/ ክርስቶስ በአዲስ ጥምቀት ውሀ ።

የግዕዝ ቅኔያት
ከነትርጓሜያቸው

1 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘአድግሱ (መልክ ብርሃን)

ባሕቲቶ ነቢረ እግዚአብሔር ፈርሀ ፤
እምኢሀልዎ ንዋም እስመ ዓለመ አንትሀ ።

ትርጉም

እግዚአብሄር ብቻውን መቀመጥን ፈራ ፤
ከአለመኖር/ እንቅልፍ አለምን አንቅቷልና (ቀስቅሷልና)

ምስጢር

ብቻውን መቀመጥ የፈራ ሰው ጓደኛውን (አቀማማጭን)
እንደሚሻ ሁሉ ፤ እግዚአብሄር ከብሩ በባህርዩ (ለብቻው ሆኖ)
እንዳይቀር ሰውንና የሚኖርበትን አለም ፈጠረ ይላሉ ባለቅኔው።

2 ግእዝ ጉባኤ ቃና

መርቆሬዎስ አብ ይደልዎከ ፍሥሓ ፤
ሃይማኖት ወልድከ አምጣነ ለፈረስ በጽሐ ።

ት ር ጉ ም

አባት/ መርቆሬዎስ ደስታ ይገባሃል ፤
ልጅህ/ ሃይማኖት ለፈረሰ ደርሷልና

ም ስ ጢ ር

አንድ ሰው ልጁ ለፈረሰ ግልቢያ ሲደርስለት «ልጅህ ለፈረሰ ደረሰልህ ደስታ ይገባሃል» ይባላል ። አንደዚሁም የአባት ምሳሌ የሆነው ስማእቱ መርቆሬዎስ ከሞተ በሁዋላ ፈረሱ እየዞረ ሃይማኖትን አስተምሯል የሚባለውን በመግለጥ ባለትኔው ሃይማኖት ልጅህ ለፈረሰ ደረሰ ብለው ተቀኝተዋል ።

ታ ሪ ክ

መርቆሬዎስ ከክርስቲያኖች አባትና እናት ተወልዶ በሮሜ ያደገ የመኮንን ልጅ መኮንን ነበር ። ጥንታዊ ስሙ ፒሉፓዲር ሲሆን ፥ በሁዋላ መርቆሬዎስ ተብሏል ። እርሱን የሾመው ንጉስ ክርስቶስን ክዶ የሰው እጅ ስራ የሆነ ጣእትን እምላኪ ስለሆነ ፥ መርቆሬዎስን ለጣእት እንዲንበረከክ አስገደደው ። መርቆሬዎስ ግን ሲሾም የተሰጠውን የክብር ልብሱን ለንጉሱ አሽቀንጥሮ ጥሎ ፥ እኔስ «ክርስቶስን ከጂ ለሰው ስራ ጣእት አልሰግድም » አለ ። ከዚህም የተነሳ የንጉሱ አሽከሮች መርቆሬዎስን በልዩ ልዩ ግርፋትና እስራት አሰቃይት ። የደሙም እንጥፍጣፊ እሳቱን አስኪያጠፋው ድረስ በብረት አልጋ ላይ አስተኝተው በበታቹ እሳት አንደዱበት ። በመጨረሻም በሰይፍ አንገቱን ተቆርጦ በሰማእትነት ሞተ ።

እርሱ ከሞተ በሁዋላ በህይወቱ ሲገለገልበት የነበረው ፈረስ በስሬው ተተክቶ ሃይማኖት በሰብእዊ ልሳን ሰብኳል ይባላል (ስንክ. ህዳር 25) ። (ስንክ. ግለት መፅሀፈ ስንክሳር ግለት ነው) ።

—❦—

3 ዘአምላኪየ

ንቅወተ ዶርሆ መስቀል ድኅረ ዓለመ አብጽሐ
ጎሐ ገጸ ዕውራን ፥ ወኮነ ጽባሐ ፤
ወአፈ በሃማን አዕዋፍ በዘተከህሉ ሰብሐ ።

ት ር ጉ ም

የዶሮ ጩኸት/ መስቀል አለምን ካዳረሰ በሁዋላ
የእውራን ፊት/ነህ ቀደደ ፥ ንጋትም ሆነ ፤
የዲዳዎች/ ወሮች አፍም በተቻለው አመሰገነ ።

ም ስ ጢ ር

ዶሮ ደጋግሞ ከጮኸ በሁዋላ ጎህ ይቀዳል (የብርሃን ውጋጋንም ይታያል) ፤ ቀጥሎም ይነጋል ፤ ወፎችም ይንጫጫሉ ። እንደዚህም ሁሉ የክርስቶስ መስቀል የእውሮችን አይን አበራ የዲዳዎችንም አፍ ፈታ ፤ አለምንም ሁሉ እዳን ይላሉ ባለትኔው ።

4 ሚበዝኁ

ዘገብረ ኢየሱስ (መምህር)

ብዑሳን ወርቅ ጸድቃን
ውስተ ቤተ ክብካብ ቦኡ ወአተዉ በፍሥሓ ፤
ለበዓለ ክብካብ ወልድ አሰመ አኀዙ እምኃ ፥
ኀጥአንሰ አዝማድ አለ አምኃ አልቦሙ ኢተመነዩ ኪያሃ ።

ት ር ጉ ም

የወርቅ ባለፀጎች/ የጸድቃን
ወደሰርግ ቤት ውስጥ በፍፁም ደስታ ገቡ ፤

ለባለ ሰርጉ/ ከርስቶስ ስጦታን ይዘዋልና ፤
ስጦታ የሌላቸው ዘመዶች/ ሀጥአን ግን እርቧን (የሰርግ ቤትን)
አልተመኙም

ም ስ ጢ ር

ለባለ ሰርግ (ለሙሽራ) ስጦታ የያዙ ሰዎች ወደ ሰርጉ በደ
ስታ ሲገቡ ያልያዙት ግን ወደ ሰርግ ቤት ለመግባት ቅር ይሰኛሉ ።
እንዲሁም በዚህ አለም መልካም ስራ የሰሩ ሰዎች ወደ መንግ
ስተ ሰማያት በደስታ ይገባሉ ። መልካም ስራ ያልሰሩ ሀጢአተ
ኞች ግን ወደ መንግስተ ሰማያት የመግባት ተስፋ የላቸውም በግ
ሉት ባለቅኔው ስለ ፅድትና ኩነኔ ያላቸውን እምነት ገልጠዋል ።

ታ ሪ ክ

ከርስቶስ ለልባሞች የድካማቸውን ዋጋ ፣ ለሰነፎችም የስንፍና
ቸውን ፍዳ ለመክፈል በግርማ መንግስት ዳግመኛ ይመጣል ፣ ይህን
አለም ከመናር ወዳለመናር ያሳልፈዋል ፣ ሙታንን ከመቃብር እንሰቶ ፣
ነፍስንና ስጋን እየሠዶ ፃድቃንን በቀኙ ሀጥአንን በግራው ያቆማቸ
ዋል ። በስጋ ህይወት ሳሉ በጎ የሰሩትን ፃድቃን «ወደእኔ ኑ» ብሎ
ወደደስታ መንግስቱ ያገባቸውና ፣ ፈጣሪያቸውን እያመ ሰገኑ ዘላለም
በደስታ ይኖራሉ ። በዚህ አለም ሳሉም ክፉ የሰሩትን ግን «ከእኔ
ወግዱ» ብሎ ወደዘላለም እሳት ቦታ ያገባቸውና በዚያው ይኖራሉ
ይባላል (ማቴ. 25 ፣ 31—46) ።

5 ዋዜማ

ዘወልደ ጊዮርጊስ (መምህር)

የብሱት በየወሃታ
ዕፀ ደብረ ሲና በለስ እመ ኢክነ ጊዜሃ ፤
እስመ ሞት ማኅፄ ተሠይመ ዲቤሃ
ፈዋሲተ ቁስሉ ለናሆም እንዘ ትሰመይ ለሲሃ ።
እንከሰ ሞታ ለዕፅ ሄኖክ ፈርሀ ፣
ወደንገፀ ኤልያስ ብዙኀ ።

ት ር ጉ ም

የደብረ ሲና እንጨት በለሰ
ጊዜዋ ባይሆን በየዋህነቷ ደረቀች ፣
እርስዋ የናሆምን ቁስል ፈዋሽ ስትባል ፣
ሞት/ መጥረቢያ (ምሳር) በላይዋ ተሹሟልና (ተሰንዝሯልና) ።
እንግዲህማ የእንጨትን ሞት ሄኖክ ፈራ ፣
ኤልያስም ብዙውን ደነገጠ ።

ም ስ ጢ ር

በመጥረቢያ(በምሳር) የተቆረጠች ዛፍ ያለጊዜዋ እንደምትደርቅ ፣
የስጋ ሞት የተፈረደባት ቅድስት ማርያም በ64 ዘመንዋ ከዚህ
አለም በሞት ተለየች ። ደግሞ እንጨቲቱ ስትቆረጥ የሚያድሩባት
ወፎች ይበተናሉ። ሄኖክና ኤልያስም ገና ስላልሞቱ የሞተችው ማርያ
ም ከመቃብር ተነስታ ወደ ነርሱ በማርጓ ሞትን ወደነርሱ ይዛባቸው
እንደሄዶች አድርጎ የቅኔው ምስጢር ያመለክታል ። የናሆምን ቁስል
ፈዋሽ የተባለች ቅድስት ማርያም የመድሀኒት እንጨት ስትባል ራስ
ዋን ከሞት አላዳነችምና ማርያም ከሞተች ሄኖክና ኤልያስም ሞት
እንዳለባቸው ቅኔው ያስገነዝባል ።

ታ ሪ ክ

ኢየሱስ በቢታንያ አድሮ በማለዳ ወደከተማ ተመለሰ ፤ ሲመ
ለስም በመንገድ ተራበና ፍሬን ለመብላት ወደአንዲት በለስ ሄደ ፣
ግን ፍሬን አላገኘባትም ፤ ስለዚህ « ዘላለም ፍሬ አይገኝብሽ »
ብሎ ረገማት ። በለሲቱም ወዲያውኑ ደረቀች (ማቴ. 21 ፣ 17—20) ።

ነቢይ ሙሴ በደብረ ሲናና በኮረብ መካከል በጎቹን አሰማርቶ
ሳለ የእሳት ነበልባልና ልምላሜ በአንድ እንጨት ላይ ተዋህደው ፤
ነበልባሉ ልምላሜውን ሳያቃጥለው ልምላሜውም ነበልባሉን ሳያ
ጠፋው አይታል ።

እንጨቱቲቱ የቅድስት ማርያም ምሳሌ ስትሆን ፥ የእንጨቲቱ ልምላሜ የማርያም ሰውነት (ድንግልናዋ) ነበልባሉም የመለኮት ምሳሌዎች ናቸው ይባላል ። ልምላሜው ነበልባሉን እንዳላጠፋው ና ነበልባሉም ልምላሜውን እንዳላቃጠለው በመለኮትና በትስብእት ተዋሀዶ መለዋወጥና መጠፋፋት እንደሌለ ይነገራል (ዘፀአ . 3 ፥ 1—7)።

6 ዋዜማ

ዘፈንታ ገብርዬ (መልአከ ብርሃን)

ኢትፈቅድ ደብረ ፀሐይ
ሀገረ እጋዕዝት ዐይነ እንተ የሀይድ ሕንፂሃ
ያብርሁ ላቲ ፀሐየ ወወርኀ ፣
እስሙ ፀሐየ ግብጽ ማርቆስ ወወርኀ ነቢያት ምስሌሃ ።
ወይቤ ዮሐንስ ነጻሪሃ
ዘከመዛ ኢርኢኩ ጽርሐ ።

ትርጉም

ሀንፃዋ የጌቶች
ሀገር እይንን የሚያንፀባርቅ ደብረ ፀሀይ
ያበሩላት ዘንድ ፀሀይንና ጨረቃን እትሻም ፣
የግብፅ ፀሀይ ማርቆስና የነቢያት ጨረቃ ከርሷ ጋር
ናቸውና ።
ተመልካቿ ዮሀንስም « እንደዚች
ያለ . . . አዳራሽን አላየሁም» አለ ።

ምስጢር

መንግስተ ሰማያት ፀሀይና ጨረቃ እንዲያበሩላት እትሻም ፀሀይዋም ጨረቃዋም እግዚአብሄር ነውና ። ባለራእዩ ዮሀንስም እንደዚች ያለች አዳራሽን አላየሁም ብሏል ። እንዲሁም በጎጃም

ደብረ ፀሀይ የተባለች የማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሀንፃዋ እጅግ እጅግ ይላል ፣ ያንፀባርቃል ። የነቢያት በእሱችም ተስለውባታል ። ይህችንም ደብር አፂ የሀንስ በጎበኙዋት ጊዜ አክብረው አልቀዋታል።

ታሪክ

መዲያኖቱ አለም ፀሀይ በቀን ፣ ጨረቃ በሌሊት እንደዚች አለም እንዲያበሩላት እትሻም ። ፀሀይዋ አይጠልቅም ፣ ጨረቃዋም አይጨልምም ፀሀይዋም ፣ ጨረቃዋም እርሱ ራሱ ፈጣሪዋ ነውይባላል ።

አቡቱለምሲስ የሀንስም በራእዩ ስለርሷ ሲናገር ፣ ከወፀቷ ብዛት የተነሳ እንደዚች ያለች ቤተ መንግስት ከቶ አላየሁም ብሏል ። ቅዱስ ጴጥሮስም ዘላለማዊት መሆኗን ሲያስረዳ « በውስጣቸው ፅድት የሚያድርባቸው አዲስ ሰማይንና ምድርን ተስፋ እና ደርጋለን» በማለት ተናግሯል (ራእ. 21 ፥ 1—27 ። 2 ጴጥ. 3፥8—15) ።

7 ሥላሴ

ይብልው ሥጋ ገሞራ
ሥላሴ እንደዱ ፍሕመ እሳት ፣
መዓቱሂ መብልዕ ከመ እይኩን ልሱሐ
ፄወ ብእሲተ ሎጥ ረሰዩ ሶቤሃ ፣
ሥጋ ገሞራ መግዘእ እስመ በጎጢአት ሠብሐ ፤
ፍትሐ ጽድቅ ይግበሩ ከመ እሚሃ ።
ወበሱቦአ ትካት ዘገብሩ ዐመፃ ብዙኀ ፣
መ ዓቱሙ ማየ አይኅ ፈልሐ ።

ትርጉም

የገሞራ ስጋን ሊበሉ
ስላሴ የእሳት ፍምን እነደዱ ፣
መ አታቸው መብልም እልጫ እንዳይሆን

ያን ጊዜ የሎጥን ሚስት ጨው አደረጉ ፤
የነሞራ/ ዝሆር (ፍሪዳ) ስጋ በሀጢአት ሰብቷልና ፤
የእውነት ፍርደን እንደዚያው ጊዜ ያደርጉ ዘንድ ።
ብዙ በደልን ባደረጉ በቀድሞ ሰዎችም
በቁጣቸው የጥፋት ውሃ ፈላ ።

ም ስ ጢ ር

ፍሪዳ ያረዱ ሰዎች ስጋ ጠብሰው ሊበሉ እሳት ያነዳሉ ። ስላሴም ሰዶምና ገሞራን ሊያጠፉ እሳትን አዘነሙ ። ወጥ እንዳ ያልጥ (አልሚ እንዳይሆን) ጨው እንዲጨምሩበት ፥ ስላሴም መአ ታቸው እንዳይዘነጋ የሎጥን ሚስት የጨው ሀውልት አደረጉ ። እንዲሁም ወጥ ሰሪዎች ምጥናቸው ይታወቅ ዘንድ በስራቸው እንደሚጠነቀቁ ስላሴም (አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ) እምላክነ ታቸው እንዳታወቅ የፍርድ አድልዎ የለባቸውም ።

ከብት ተቀልቦ እንዲሰባ የሰዶምና የገሞራ ሰዎችም በሀጢ አት ልበ ደንዳኖች ሆነዋል ። በወጥ ምጥን ጥንቃቄ ባላደረጉ ሴቶች ላይ የባለቤቶቻቸው ቁጣ እንዲበዛ ስላሴም በሰብአ ትካት (በቀድሞ ሰዎች) ላይ የጥፋት ውሃን አዘነሙባቸው ይላሉ ባለቅኔው ።

ታ ሪ ክ

የሰው ልጆች መባዛት በጀመሩ ጊዜ የአመፅ ስራቸው እንደ መልካቸው ሀብረ ቀለም ልዩ ሆነና የእግዝአብሄር ልጆች (የአ ዳም ልጅ የሴት ልጆች) የሰውን ሴቶች ልጆች (የቃየልን ልጆች) ባዩ ጊዜ መልክ መልካሞቹን ወሰዱና ሚስቶች አደረጉ ። ቃየል በሴት መልክ ውበት የተነሳ በግፍ ያፈሰሰው የአቤል ደም ወደ እግዚአብሄር እየጮኸ ከሰሳቸው ። ስለዚህ « በእንቅርት ላይ ጀር ደግፍ » እንዲሉ በዝሙታቸው ሀጢአት ላይ የአቤል ደም ከስ ተጨምሮ ፥ ሰብአ ትካት (የድሮ ሰዎች) ከገፀ ምድር እንዲ ጠፉ የጥፋት ንፍር ውሃ ከሰማይ ዘነበባቸው ፤ ከምድርም ፈላ ባቸው ። ከፃድቁ ኖህና ከቤተሰቦቹ በቀር ሁሉንም ደመሰሳቸው ።

እንዲሁም የሰዶምና የገሞራ ሰዎች ሰይጣናዊ ቅኝትን ተቃኝ ተው ከተፈጥሮ ህግ ወጥተው ግብረ ሰዶም የሚባለውን ዝሙት ከመፈፀም አንመለስ ስላሉ እግዚአብሄር ተቆጣ ። የአብርሃምን የወ ንድሙን ልጅ ሎጥን ብቻ ስለመልካም ስራው በጉስጓሳ (በጉት ጎታ) አውጥቶ የሰዶምንና የገሞራን ሰዎች ከሰማይ ባዘነበባቸው እሳት አቃጠላቸው ። ያን ጊዜም ታጠሎውን ዙረው እንዳያዩ ለሎ ጥና ለሚስቱ ከአምላክ የተሰጠውን ማሰጠንቀቂያ ጥሳ የሎጥ ሚስት ዘወር ብላ ስላየች ሀውልተ ጌው (የጨው ሀውልት ፥ ትክል ድን ጋይ) ሆና ስትቀር ሎጥ ከሁለት ሴቶች ልጆቹ ጋር ወጥቷል (ዘፍጥ. 6 ፥ 1—22 ፤ 7 ፥ 1—23 ፤ 8 ፥ 1—22 ፤ 19 ፥ 1—38) ።

8 ሥላሴ

ክብቱ (ወቃቤ ሰዓት)

ድንግል ማርያም
ለድንግልናሃ ኢበከየቶ ፥
አመ ተወለደ ሞተ መንግሥቶ እግዚአ ሕያውን ሥጋሃ
ግኅለትቱ ትንግኤ አኮኑ አሜሃ ።
ድንግለ የፍታሔሰ ትምህር ትንግኤ ጊዜ ሰዓተ ሞት በጽሓ
አኮኑ መጽሐፍ ኢያበው�
ለዘሞተ ሰብእ ድንግልናሃ
በከየቶ ክልኤተ አውራጎ ።

ት ር ጉ ም

ድንግል ማርያም
ለድንግልናዋ አላለቀሰችለትም ፥
የህያዋን ጌታ/ሲጋዋ ሞት/ መንግስቱን በተቀበለ ጊዜ
ማለቂያው (የአለም ፍፃሜ) ትንሳኤ ያንጊዜ ነውና ።
የዮፍታሄ ድንግል ግን የሞት ሰአት በደረሰባት ጊዜ

ትንሳኤን ታስተምር ዘንድ መፅሀፍ እልፈቀደላትምና
ለሞት ሰው ድንግልናዋ
ሁለት ወሮች አለቀሰችለት ።

ም ስ ጢ ር

ክርስቶስ ወደዚህ አለም ዳግመኛ በግርማ ሲመጣና የአለምን መንግስት ሲረከብ ወዲያውኑ የአለም ፍፃሜ ይሆናል ይባላል ። የክርስቶስ ምሳሌ የሆነው የድንግል ማርያም ስጋም በሞተ ጊዜ ወዲያውኑ የመንግስት ምሳሌ መነሳትን ስላገኘ ፣ በድንግልና ኖራ መሞቷ እንደ ዮፍታሄ ልጅ ቅድስት ማርያምን አላሳዘናትም ። ድንግሊቱ የዮፍታሄ ልጅ ግን በድንግልናዋ ሳለች ከተሰዋችና ከሞተች በሁዋላ እንደቅድስት ማርያም በፍጥነት መነሳት ስለማትችል ፣ ለሞተ ሰው እንደሚለቀሰለት ሁሉ በደንግልናዋ ስለመሞቷ ሁለት ወር በግልቀስ አዘነች ይላሉ ባለቅኔው ።

ታ ሪ ክ

የፍታሄ የእስራኤል መስፍን ነው ። ወደአሞናውያን ሲዘምት በቅድሚያ የተቀበለውን እንዲሰዋለት ለእግዚአብሄር ተስሎ ነበር ። ምክንያቱም ከዘመቻ ሲመለስ በፊት የሚቀበለው በግ ስለነበር ነው። ድንግሊቱም ልጁ በቅድሚያ ከሚቀበለው ከበጉ ቀድማ ተቀበለችው ። ስለዚህ « ልጄ ሆይ! አሰናከልሽኝ!» እለና ምስጢሩን ገለጠላት ። እርስዋም « እንኪያስ ለድንግልናየ የማለቅስበት ጊዜ ስጠኝ » ብላ ከመሰዋቷ በፊት ስለድንግልናዋ ከጓደኞቿ ጋር ሁለት ወር አልቅሳለች ። ከዚህ በሁዋላ ከልጁ ለእምላኩ እድልቶ ልጁን ሰውቷታል ። ስለዚህ ነው ባለቅኔው ከድንግል ማርያም ጋር እነፃፅረው የተቀኙላት (መሳ.11 ፣ ማቴ.22፤ ስንክ.ነሃሴ 16) ።

9 ሥላሴ

ዘአድግሉ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)

ዳዊት በኢያድልዎ
ፍትሐ ሞት ፈትሐ ላዕለ ካልኡ ፣
ፍትሐ ሞት በርትዕ ዘፈትሐ እመ በላዕሌሁሰ በጽሐ
ከመ ይሚጥ ፍትሐ ቃለ ጽድቁ ፍጹመ ነስሐ ፣
በደመ ፍጡራን ለርእስ አኖልዎ አምጣነ ውእቱ ረስሐ ።
እምደመ አድልዎስ እንተ ነጽሐ
ይትወከፍ ሞተ በአዳም ዘፈትሐ
እደዊሁ በመስቀል ሰፍሐ ።

ት ር ጉ ም

ዳዊት ባለማደላት
የሞት ፍርድን በሌላው ላይ ፈረደ ፣
በእግባብ የፈረደው የሞት ፍርድ ግን በርሱ ላይ በደረሰ ጊዜ
የእውነቱ ቃል ፍርድን ይመልስ ዘንድ በፍፁም ተፀፀተ ፣
በፍጡሮች ዓም ለራስ ማደላት እርሱ (ዳዊት) አደኛልና።
ከማደላት ደም የነፃ (ክርስቶስ) ግን
በአዳም የፈረደበትን ሞት ይቀበል ዘንድ
እጆቹን በመስቀል ላይ ዘረጋ ።

ም ስ ጢ ር

ነቢዩ ናታን የዳዊትን በደል ስራ ለራሱ ለዳዊት በምሳሌ ቢነግረው ፣ የጨከተኛው ሌላ ሰው መስሎት « ይህስ ወንዝ (የክብት መንጋ) ይነዳበት » ብሎ ፈርዶ ነበር ። በደለኛው ራሱ እንደሆነ በተረዳ ጊዜ ግን ፣ ለራሱ አደልቶ ራሱን ለማዳን ንስሃ የገባ ሲሆን ክርስቶስ ግን ለራሱ ሳያዳላ በአዳም ላይ የፈረደውን የሞት ፍርድ ራሱ መቀበሉን ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

ልበ አምላክ የተባለው የእስራኤል ንጉስ ዳዊት ያመፁበትን የአሞንን ልጆች በጦር ሀይል እንዲያጠፋቸው የጦር አበጋዙን ኢዮአብን ከነሰራዊቱ ላከው ። ሀቀኛው አሽከሩ አርዮም አብሮ ዘመተ ። እነርሱ ከጠላቶቻቸው ጋር ተሰልፈው በጦር ሜዳ ሳሉ ዳዊት በቤተ መንግስቱ ነበር ። ወደግታ ጊዜ ከምንጣፉ (ከመኝ ታው) ተነስቶ በሰገነቱ ሲመላለስ ፣ አንዲት በጣም የተዋበች ቤት ገላዋን ስትታጠብ አየና አስመጥቶ ከርሷ ጋር ተኛ ። ይህችውም ቤት የታማኝ አሽከሩ የአርዮ ሚስት ቤርሳቤህ ናት ። በእደፍ ጥራቷ ስለተገናኛት ፀነሰችና ይህንኑ ለዳዊት ገለጠችለት ። ስለዚህ በአፈ ፃፎሙ አፍሮ ከባሏ ፀነሰች እንዲባልለት አስቦ አርዮን ከጦር ሜዳ አስመጣው ፤ አብልቶና አጠጥቶ ከሚስቱ ጋር እንዲተኛ ፈቀደለት ። አርዮ ግን ምንጊዜም የእግዚአብሄር ሰው በመሆኑ « እነኢዮአብ በጦር ሜዳ ሰፍረው በሞት አፋፍ ላይ ሳሉ ፣ እኔ ከሚስቴ ጋር መደሰት አይገባኝም» ብሎ በቤተ መንግስቱ ከዘበኞቹ ጋር ሁለት ሌሊት አደረ ።

ዳዊት የአርዮን አለመታለል በምር ስላወቀ ፣ የራሱን ነውረ ዝሙት በአርዮ ሞት ሊሸፍን ፈለገ ፣ ስለዚህ « አርዮን ባየለው ጦር ግምባር አሰልፈው ፣ ውጊያውም ሲፋፋም ትታችሁት ወደ ሁዋላ ሽሹ » የሚል የሞት ደብዳቤ በባለጉዳዩ በአርዮ እጅ ወደኢዮአብ ላከ ፣ አርዮም እንደተባለው በበረታው ጦር ግንባር ተሰልፎ ሲዋጋ ትተ ውት ሸሹና « የእስራኤል አርበኞች ! ዛሬስ አለወትሯችሁ ምን ሆናችሁ ? » በማለት ብቻውን ተገድግዶ ሲዋጋ ሞቷል ።

ስለዚህ ዳዊት የፈፀመው ግፍ አምላክን ስላስቆጣው ፣ ነቢዩ ናታን የግፉን አፈፃፀም ለዳዊት በምሳሌ ቢነግረው «በእኔ ግዛት ይህን ግፍ የፈፀመ ካለ የሞት ሞት ይሞታል » አለ ። በዚህ ጊዜ ነቢዩ « አንተው ራስህ ነህ ፤ ያሸከርህን የአርዮን ሚስት ቀምተህ ፣ በዚህ ላይ ደግሞ እርሱን በግፍ አስገደልኸው » አለው ። በአመፅ የተወለደው ህፃን ታመመ በዚህ ጊዜ ዳዊት ተፀፀተ ፈራ ፣ ደነገጠ ፣ ፆመ ፣ ፀለየ ፣ በትቢያ ላይ ተኛ ፣ አለቀሰ ፣ ባለሟሎቹም እንዲነሳና እህልና ውሃ እንዲቀምስ ቢማልዱት እንቢ አለ ።

ነቢዩ ናታንም ዳዊት ይቅርታን በንስሃ ከአምላኩ እንዳገኘና በእርዮም ላይ የፈፀመው የግፍ ግፍ የሁዋላ ሁዋላ በሚስቶቹና በቤተ ሰቦቹ ላይ እንደሚፈፀምበት ነገረው ።

ህፃኑንም አምላክ ቀሰፈውና ሞተ ። በዚህ ጊዜ ዳዊት ቁርጥ አውቆ ከትቢያው ላይ ተነሳ ፣ ልብሱን ለወጠ ፣ እህልና ውሃንም ቀመሰ (2 ሳሙ. 11—12) ።

አዳም አትብላ የተባለውን በለስን በመብላት አምላካዊ ህግን ስላፈረሰ አምላክ በሞተ ስጋ ላይ ሞተ ነፍስን ፈረደበት ። ስለዚህ ከገነት ወጥቶ ወደምድረ ፋይድ ወረደ ፣ በዚህም እዘን ፣ ተከዘ ፣ አለቀሰ ፣ በወንጀሉ ንስሃ ገባ መሰዋእትንም አቀረበ ። የቢጋውን ሞት ሞተ ፣ በነፍስም ሞት ወደሲኦል ወረደ ። አምላክም አዘንና ንስሃውን ተቀበለውና ፤ እርሱን ለማዳንና ነፃ ለማውጣት ከትድስት ድንግል ማርያም ያለዘርአ በድንግልና ተወንሶ በድንግልና ተወለደ ። በአዳም ፈንታ ፀዋትወ መከራን በፈቃዱ ተቀበለ ፣ በስጋው በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ ። ይህን አለም ለማላለፍና በህያዋንና በሙታን ላይ ለመፍረድ ዳግመኛ በጌትነት ይመጣል ይባላል ።

10 ዋዜማ

ዘአባተ (መሪጌታ)

ጌጋይ ሐጸ ጌጋይ
ኢቀተለኑ ለስምዖን እንዘ ትረግዝ ገቦሁ ፤
ሥጋ በሥጋ እስመ ሐረት ናሁ ።
ወዘኢያስቈርር ደመ ኪዳነ ድንግል እኁሁ ፣
በማይ ጎፀበ አልባሲሁ ፣
ዘበሞቱ ለምውት ተንዝሁ ።

ትርጉም

የበደል ፍላፃ በደል
ስምእንን ጎኑን ስትወጋው አልገደለችውም ፤
እነሆ ስጋ ለስጋ ሄዳለችና ።
ደምን የማይፀየፍ የድንግል ቃል ኪዳን ወንድሙም ፥
በሟች ሞት ጊዜ በደም የተረጨትን
ልብሶቹን በውሀ አጠበ ።

ምስጢር

ስጋ ለስጋ የሄደች ፍላፃ የወጋችውን ሰው እትገድለውም ፤ እን ዲሁም በላኤ ሰብእ የሰው ስጋን በመብላቱ የፈፀማት በደል እላስኮ ነነችውም ። ደግሞ በፍላፃ የተነደፈው (የተወጋው) ሰው ልብሶቹ በደ ም ቢበከሱ ደምን የማይፀየፍ ወንድሙ በውሃ እንደሚያጥብለት ሁሉ ፤ የማርያም ቃል ኪዳን የሰውን ደም በማፍሰስ የተመረዘውን የበላኤ ሰብእን አእምሮ ለድህው ውሃን በማጠጣት ወደበጎ ምግባር መለ ሰው ። «ስጋ በስጋ» የተባለው ህብረ ቃል የፍላፃይቱን በስጋ ውስጥ ማለፍንና የሰው ስጋ መብላትን በደል ያስተባብራል ።

ታሪክ

ስሞአን የተባለ ሰው ነበር ። መንፈሱ በርኩስ መንፈስ ተለ ውጦ ሚስቱን ልጆቱን ፥ የቤቱንም የውጪውንም ሰባ ስምንት ሰዎች እስከመብላት ደረሰ ። ከእለታት በአንድ ቀን አንድ በሽተኛ እርኩቱን ይዞ ሰላየው ውሃ ከርሱ ለመለመን ቸኮለ ። በተጋጠውም ጊዜ «ስለድንግል ማርያም ብለህ ከያዝከው አጠጣኝ» በማለት ተቅ ለብልቦ ለመነው ። በዚህ ጊዜ ቀድሞ ርኩስ መንፈስ ሳይዋሀደው ደሀና ሳለ ፥ የሚያውቀው ስሟ ተሰማውና ጥርኝ ውሃ ለበሽተኛው በእፍኙ አፈሰሰለት ። የበሽተኛው የእጁ ንቃቃት ውሃውን መጠጠው ፤ በሽተኛውም በአንድ እፍኙ ያፈሰሰለትን ውሃ በምላሱ ቢልሰው ጉሮ ሮውን እንጣጣው እንጂ ጥሙን አላረካውም ። ከዚህም በሁዋላ በላኤ ሰብእ በዋሻ ውስጥ ገብቶ ስንኳን የሰው ስጋና እህልና ውሃ ሳይቀ

ምስ ሞተ ። መላእክተ ፅልመትም ነፍሱን ወደሲኦል ሊያወርዷት ሲሉ ቅድስት ማርያም በተሰጣት ቃል ኪዳን መሰረት እምላክን ማለደች ። ስለዚህም የሰባ ስምንት ሰዎች ነፍሶችና እፍኝ ውሃ በግራና በቀኝ ሆነው በሚዛን ቢመዘኑ እፍኙ ውሃ አደፋ (በክብደቱ በለጠ) ።

ስለዚህ የሃጢአተኛው የበላኤ ሰብእ ነፍስ ለድንግል ማርያም በተሰጣት ቃል ኪዳን ምልጃ እማካይነት በእምነትና በምፅዋት ፥ በንስሃም ወደ ሲኦል ከመውረድ ድና ወደገነት እንደገባች በተአም ረ ማርያም ተፅፏል ። ከዚህም የተነሳ ባለቅኔው « ወዘኢያስቈርር ደመ ኪዳነ ድንግል እኁሁ በማይ ጎፀበ አልባሲሁ» ብለው ተቀኝተ ዋል ።

11 ዋዜማ

ዘዝግነህ (ደብተራ)

አልሕምተ ጎል ኢያደንገፀ
ዕጓለ እንበሳ ስኩብ በጎለ እንስሳ ዘበዝኁ ፥
ወዘንተ እንበሳ አልሕምት ኢፈርሀ ፤
አኮኑ እምጥንት ወእመሠረት እቡሁ
እንበሳ በሰማይ ለመደ እንስሳሁ
ወእንስሳ ለመዱ ኪያሁ ።

ትርጉም

የበረት ላሞችን አላስደነገጠም
በብዙ ክብቶች በረት የተኛ የእንበሳ ልጅ ፥
ላሞችም ይህን እንበሳ አልፈሩም ፤
ከጥንትና ከመሰረት አባቱ / እንበሳ
በሰማይ እንስሶችን ለምዷልና
እንስሶችም እርሱን ለምደዋልና ።

ም ስ ጢ ር

በቅርብ አብረው ያደጉ ጓደኛሞች ስለተለማመዱ አይፈራሩም አይተፋፈሩም ። እንዲሁም በእንስሳት ስም በሚጠሩ በኪሩቤል ላይ የሚቀመጥ የእንበሳ ምሳሌ የሆነ የአምላክ ልጅ በእንስሶች በረት ተወለደ ፤ አህያና ላም በእስትንፋሻቸው (በትንፋሻቸው) እሚቁት ። በበረትም ሲወለድ ከባህርይ አባቱ ከአብና ከዙፋኑ ተሸካሚዎች ከኪሩቤል አልተለየም እየተባለ የሚተረከውን ቅኔው ያስረዳል ።

ታ ሪ ክ

እጓለ እንበሳ (የእንበሳ ልጅ) የተባለ ክርስቶስ ነው ። እንስሳ የተባሉ መንበሩን ተሸክመው የሚኖሩ አራቱ ኪሩቤል ናቸው ። ክር ስቶስ በእንስሶች በረት በተወለደ ጊዜ አህያና ላም በትንፋሻቸው አሟሙቀውታል ። በሰማይ በአራቱ እንስሶች ላይ እንዳለ ሆኖ በበ ረት እንስሶች እየተሟሟቀ የእረኞችንና የመላእክትን ምስጋና ተቀ ብሏል (ኢሳ. 1 ፥ 1—14 ፤ 6 ፥ 1—5 ፤ 8 ፥ 1—5 ፤ 11 ፥ 1—16) ።

12 . ሥላሴ

ዘአድግሱ (መልአከ ብርሃን)

ውሉደ ዘረከቡ
በጎጢአ ብእሲት ይቴከዙ ፥
ወዘረከበ ብእሲተ በጎጢአ ውሉድ ይላሑ ፤
እስመ ባዕድ ፍና ብእሲት ወለወልድ ፍናሁ ።
እምትካዘ እሉሰ ለምጽ ሕሊናተ ሎጥ ይንጽሑ
አዋልድ ለሎጥ ተራድኦሁ ፤
አምጣነ አዋልድ በለፌ አዋልዲሁ
ወበለፌ አንስተ ኮናሁ ።

ት ር ጉ ም

ልጆችን ያገኙ
ሚስትን በማጣት ያዝናሉ ፥
ሚስትን ያገኙ ደግሞ ልጅን በማጣት ያለትሳሉ ፤
የሚስት መንገድና የልጅ መንገድ ልዩ ናቸውና ።
ግን የሎጥ አሳቦች ከነዚህ ትካዜ/ ለምፅ ይነፁ ዘንድ
ሴቶች ልጆቹ ሎጥን ተራዱት ፤
ሴቶች ልጆች በዚህ በኩል ልጆቹ ናቸውና
በዚያ በኩል ደግሞ ሚስቶቹ ሆነውታልና ።

ም ስ ጢ ር

ተስማሚ ሚስቶችን ያገኙ ሰዎች ሲመክኑባቸውና ልጅ ሲያጡ ያዝናሉ ። ልጅ የወለዱትም ሚስቶቻቸው ሳይስማሟቸው ሲቀሩ ይተከዛሉ ። ምክንያቱም የሚስትና የልጅ ውኔታዎች ስላልተባበሩ ነው ። ሎጥ ግን ከሰዶምና ከገሞራ ቃጠሎ ሸሽቶ ከዋሻ ውስጥ በተሸሸገ ጊዜ ልጆቹ በወይን ጠጅ አስክረውት ከነርሱ በመውለዱ ሁለቱ ልጆቹ የልጅና የሚስትን እጦት (ችግር) እንዳታለሉለት ባለ ቅኔው ያስገነዝባሉ ።

ታ ሪ ክ

ሎጥ ከሰዶምና ገሞራ ቃጠሎ አምልጦ በዋሻ ውስጥ ተቀምጦ ሳለ ፤ ሁለቱ ሴቶች ልጆቹ በዚያው ቦታ ከአባታቸው በቀር ሌላ ወንድ ሰው አለመኖሩንና ሌላ ወንድም ከሌለ እነርሱ ያለዘር መቅ ረታቸውን አጤኑ ። ስለዚህም እርስ በርሳቸው አሳብ ለአሳብ ተስ ማሙና በአባታቸው ላይ መከሩበት ፤ የሚያሰክር የወይን ጠጅ አጠጡትና ሁለት ጊዜ አሰከሩት ። ሰክሮ እንደተኛ ተገናኝቸውና ሁለቱም ሴቶች ልጆቹ ከአባታቸው ወለዱ (ዘፍ. 19 ፥ 30 —38) ።

13 ሥላሴ

ዘአድግሱ (መልእክ ብርሃን)

አእዱን ዘአጥረዩ
በጎሚሠ መሥጎትት ይጸምው ፡
ወዘአጥረዩ መሥጎትት ለአጥርዮተ አድግ ተግሁ ፤
እስመ ባዕድ እምረባሐ አድግ ለመሥጎትት ረባሔ ።
በቅዔቱስ ለተግስ በቋሚ ለእመ አኮ ከግሁ
እለ አጥረይዎ ይትፈሥሑ ፤
እስመ መሥጎትተ ጽድቅ ይከውን ማዕሰ ሥጋሁ
ወመሥጎትቶ ይጸወን ለሊሁ ።

ትርጉም

አህዮችን የገዙ
አትግላን በመፈለግ ይደክማሉ ፡
አትግላን የገዙ ሰዎች ደግሞ አህያን ለመግዛት ተጉ ፤
የአትግላ ጥቅም ከአህያ ጥቅም የተለየ ነውና ።
የጢቃሚ ተግስ ጥቅም ግን እንደርሱ ሳይሆን
የገዙት ይደሰታሉ ፤
የስጋው ቆላ የእውነት አትግላ ይሆናልና
አትግላውንም እሱ ራሱ ይጫናልና (ይሸከግልና) ።

ምስጢር

አህያ ያለ አትግላ አትግላም ያለ አህያ ስለግይሆን ፡ ገበሬ ዎች ሁለቱንም ለግግኘት ይደክማሉ ። ሀዋርያው ተግስ ግን የክርስቶስን አምላክነት ሲመሰክር የትምህርቱ ተቃዋሚዎች ቆላውን ገፈው አትግላ አወጡ ። በአትግላውም ውስጥ አሸዋ ሞልተው

አሸክመውታል ። ስለዚህ ተግስ የአህዮቹንና የአትግላን አገልግሎት ስለፈፀመ በሁለት በኩል ጠቃሚነት አለው ግለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

ታሪክ

ከሀዋርያት አንዱ የህንደኬው ተግስ ነው ። በህንድ ወንጌልን ስለክርስቶስ ሲሰብክ ክርስቶስን ያልተቀበሉት ካጆች ቆላውን ከስጋው ገፈው አትግላ አውጥተው በአትግላው ውስጥ አሸዋ ሞልተው ያን አሸክመው አሰቃይተውታል ፤ በስጋውም ጨው ነስንሰውበታል ይባላል ።

14 ዘይእዜ

ዘተክሉ (መምህር ፡ ዘሞቪራ)

ለምንት ወልድ እንተ ጸውዖ
ለነቢይ ኤልያስ ነቢ ደብረ ታቦር ጽርሑ
እንዘ ወልድ የአምር
ከመ በደመና ይመጽእ አቡሁ
አኮኑ ኤልያስ ለደመና ሰማይ ጸላኢሁ ።
እመ ደመናሰ መጽአ ምስለ ረዳኢሁ
ኤልያስ ጉየ እስመ የአምር ፍናሁ ።
እመ ደመናሰ መጽአ ምስለ ረዳኢሁ

ትርጉም

ወደደብረ ታቦር / አዳራሹ
ወልድ ነቢይ ኤልያስን ለምን ጠራው ?
አባቱ በደመና እንደሚመጣ እያወቀ ፤
ኤልያስ የሰማይ ደመና ጠላት ነውና ።

ደመና ግን ከረዳቱ ጋር በመጣ ጊዜ
ኤልያስ ሸሸ ፤ ብድራቱን ያውቃልና ።
ደመና ግን ከረዳቱ ጋር በመጣ ጊዜ

ም ስ ጢ ር

አንድ ጋባኝ ሰው ተጋባዥን ባላጋራው ባለበት ቢጠራው ፥ የተጠራው ሰው ባላጋራውን ከሩቅ ሲያየው ይሸሻል ። እንዲሁም ኤልያስ ሶስት አመት ከስድስት ወር ደመና ዝናብን እንዳያዘንብ የከለከለ ሲሆን ፥ የደመና ጠላት ኤልያስ ወደ ደብረ ታቦር ከመጣ በሁዋላ ፥ እግዚአብሄር አብ በደመና ሆኖ «ይህ ልጄ ነው ስሙት» ባለ ጊዜ ደንግጦ ወደ ነበረበት ሄዷል ። ስለዚህ ባለትዳው ኤልያስ የደመናን በቀል በማስታወስ ፈርቶ እንደሸሸ ቆጥረው ወልድ ኤልያስን ወደ ደብረ ታቦር እንዲመጣ ሊጠራው ባልተገባም ነበር ብለዋል ።

ታ ሪ ክ

ኢየሱስ ከሀዋርያት ሶስቱን ጴጥሮስንና ያእቆብን ፥ ዮሀንስ ንም ይዞ ወደ ታቦር ተራራ አውጥታቸው ላለ አርእያው በፊታቸው ተለወጠ ፥ ፊቱም እንደ ፀሀይ አበራ ፥ ልብሱም እንደበፊዶ ነጭ ሆነ ። ከነቢያትም ሁለቱ ሙሴና ኤልያስ እየተነጋገሩ መጡና ታዩ አቸው ።

ጴጥሮስ «ጌታ ሆይ በዚህ መኖር መልካም ነው ። ብተፈቅ ድስ ሶስት ማደሪያ (ዳስ) እንዱን ለአንተ ፥ አንዱን ለሙሴ ፥ አን ዱን ለኤልያስ እንስራ» ሲለው ወዲያውኑ ዳመና ጋረዳቸው ። ወዲያውም «በርሱ ደስ የሚለኝና የምወደው ልጄ ይህ ነው ፥ እር ሱንም ስሙት» የሚል ድምፅ ከዳመናው መጣ ። ደቀ መዛሙር ቱም ሰምተው በፊታቸው ወደቁ ። ኢየሱስም ቀርቦ ሲዳስሳቸው ተነሱና ከኢየሱስ ጋር ከተራራው ወረዱ ። ሙሴና ኤልያስ ግን ወደ እየነበሩበት አለም ተመልሰዋል ይባላል (ማቴ. 17) ።

15 ዘይእዜ

ዘፈንቱ (መሪጌታ)

ኢጼሐ ቶማስ ከናፍሪሁ
በማየ ተመትሮ ቄሪር ድኅረ ተነፅበ እዴሁ ፤
በከናፍሪሁ እስመ ተርእየ
ምሂር ቃለ ሃይማኖት ለጳውሎስ ጸብጹ ።
ወእስይፍተ ፀር አብያጽ ተግለቱ ላዕሌሁ ፤
አኮኑ አተወ እስከ አጽፋሪሁ
ውሳጤ ምትረት ጸብኅ ጥዑመ ከናፍር ሥጋሁ ።
አኮኑ አተወ እስከ አጽፋሪሁ

ት ር ጉ ም

በቀዝቃዛ ውሃ/ መቆረጥ እጁን ከታጠበ በሁዋላ
ቶማስ ከንፈሮቹን አልጠረገም ፤
የሃይማኖት ቃልን ማስተማር/የጳውሎስ ወጥ በከንፈሮቹ
ይታያልና
የጠላት ሰይፎች/ጓደኞቹም በርሱ ላይ ተሳሳቁ
ስጋውን ለከንፈሮች ባጣፈጠ በመቁረጥ /ወጥ ውስጥ ፥
እስከ ጥፍሮቹ ገብቷልና
እስከ ጥፍሮቹ ገብቷልና ።

ም ስ ጢ ር

እጆቹን ታጥቦ የተመገበ ሰው በዝንጋታ ከንፈሩን ላይጠርግ ይቀርና ፥ ከከንፈሩና ከጣቱ ላይ ወጥ ሲታይበት ጓደኞቹ ይሳሳቁ በታል ። «ወጡን እስከ ጣቱ ገብቶበታል» እያሉ ይዘባበቱበታል።

እንዲሁም የክርስቶስን ትምህርት የሚቃወሙ ሰዎች በሰይፎች የክርስቶስ ምስክር የሆነ የቶማስን ከንፈሩን ፣ እጆቹንና እግሮቹን በመቁረጥ አሰቃዩት ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

ታሪክ

በ325 አ. ም. አርዮስን ለማውገዝ በኒቅያ ከተሰበሰቡት ከሶስት መቶ አስራ ስምንት ሊቃውንት አንዱ የመርእስ ኤጲስ ቆጶስ ቶማስ ነው ። ክርስቶስን በተቀበሉት ሰዎች ዘንድ የተወደደው ትምህርቱ ክርስቶስን ባልተቀበሉት ከሃዲዎች ዘንድ አስጠላው ። ከዚህም የተነሳ ስቃይ ሲበዛበት ክርስቶስን ክዶ ለጣኦት እንደሚሰግድ የገመቱ ከሃዲዎች ሃያ ሁለት አመት አስረውታል ። እያንዳንዱን ሰውነቱን በያመቱ በሰይፍ እንዲቆረጥ ወሰኑበት ። የእጆቹንና የእግሮቹን ጣቶች አፅቅ አፅቃቸውን ፣ ጆሮዎቹንና አፍንጫዎቹን ከንፈሮቹንም ተራ በተራ በያመቱ ቆረጡበት ፣ ጥርሶቹንና መንጋጋዎቹን አወለቁበት ።

ከዚህ ስቃይ በሁዋላ ተማሪዎቹ በቅርጫት ውስጥ አድርገው በአህዮቹ እየጫኑ ያጉዙት ጀመር ። የቶማስን አካላት በሰይፍ የቆራረጡ ሰዎች በአህዮቹም እየተጓዘ እንዳይጠቀም አስበው የአህዮቹንም አንገት አንገታቸውን ቆረጡበት ። እርሱም ተማሪዎቹ ቁራጮቹን የአህዮቹን አንገቶች በእየነበሩባቸው ጉምዶች እንዲገጣጥሟቸው አዘዛቸውና ቢያገጣጥሟቸው አህዮቹ ቀድሞ በህይወት እንደነበሩ ሆነዋል ይባላል (ስንክ. ህዳር 9) ።

16 ዘይእዜ

አመ ነግሡ ሰይፍ ሰብአ ገሊላ
መጸብሕ ቶማስ ዘኢየጎልቅ ዕዳሁ
ንብረቶ ፈጺሞ ተአጎዘ እዴሁ ፤
እንዘ ይብል አመጽእ ትሩፋነ አእዱጊሁ

ለእመ መዓር ውእቱ ንባበ አፉሁ
አምጣነ አልቦ ፍጥረት ዘኢይሰምዕ ዜናሁ ።
ለእመ መዓር ውእቱ ንባበ አፉሁ

ትርጉም

የገሊላ ሰው/ ሰይፍ በነገሰ ጊዜ
እዳው የማያልቅ ገበሬ / ቶማስ
ንብረቱን ጨርሶ እጁን ተያዘ ፤
የቀሩ አህዮቹን አመጣለሁ ሲል
የአፍ ንግግሩ ግር (ጣፋጭ) ቢሆን
ወሬውን የማይሰማ ፍጥረት የለምና ።
የአፍ ንግግሩ ግር (ጣፋጭ) ቢሆን

ምስጢር

ለመሬቱ የሚከፍለው ግብር ያጣ ገበሬ እጁን ይያዛል ፤ ሌላ ንብረት ከሌለው አህዮቹንም መያዣ አድርጎ እስኪሰጥ ድረስ ይገደዳል ። እንዲሁም የጠላት ሰይፍ በተመዘዘ ጊዜ የመርእስ አገር ሰማእት ቶማስ እግሩንም ፥ እጁንም ፥ ከንፈሩንም መቆረጡንና አህዮቹም ጭምር መቆረጣቸውን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

17 መወድስ

መኑ የአምር ዕለተ ሥቃዩ ?
ወመኑ የአምር ዘይመጽእ መከራው ?
እስመ ሕሊና ሰብእ ኮነ ሕሊና እንስሳት ዘበዝኁ ።
ምሳሌ ዝኒ ከመ ናእምር
ቃየል አመ ተበቀሎ ለአቤል እኁሁ
እንዘ አቤል ቤተ መዉ
ኢያእመረ አቤል ምክረ ቃየል ቀታሊሁ ።

አዳምን እንዘ በሰኡ በዓለ አእምሮ ሰሊሁ
አዳም ኢያምሠጠ እመሥገርተ ቤልሆር ጸላኢሁ ።
ወለእመ ነሐትት ንሕነ እምላከ አግልክት ኪያሁ
ጠቢብ ወግእምር አልቦ ዘእንበሌሁ ።

ትርጉም

የስቃዩን ቀን ማን ያውቃል ?
የሚመጣ መከራውንስ ማን ያውቃል ?
የሰው አሳብ የብዙ እንስሳት አሳብ ሆኗልና ።
የዚህንም ምሳሌ እናውቅ ዘንድ
ቃየል ወንድሙ አቤልን በተበቀለ ጊዜ
አቤል የሙሴ ወገን ሲሆን
አቤል የገዳዩ ቃየልን ምክር አላወቀም ።
አዳምም በሁሉ እርሱ ባለእውቀት ሲሆን
አዳም ክጠላቱ ቤልሆር ወጥመድ አላመለጠም ።
እኛም እርሱን የአግልክት አምላክን ብንመረምር
አዋቂና ብልሃተኛ ከርሱ በቀር የለም ።

ምስጢር

ሰው ምንም ባለ አእምሮ ቢሆን የሚደርስበትን ነገር አያውቅም ፤ በተፈጥሮውም ከእንስሳት የተለየ ሲሆን እንስሳዊ ስራን ይሰራል ። ለዚህም ማስረጃ ቃየል ታናሽ ወንድሙ አቤልን በድን ጋይ ገደለ ፤ አቤል ግን «ያልጠረጠረ ተመነጠረ» እንዲሉ የዋህ በመሆኑ ቃየል ሊገድለው ማሰቡን አላወቀም ።

አዳምም ጠላቱ ሰይጣን ከክብሩ ሊያዋርደው ባሰበ ጊዜ በበለስ መብል አምላክነትን የሚያገኝ አድርጎሎ ሲነግረው በተፈጥሮ እውቀቱ አሰቦ ከውድቀት አላመለጠም ። ስለዚህ ባለቅኔው ሰው በራሱ የሚደርስበትን ነገር ሁሉ አስቀድሞ ማወቅ አለመቻሉን በትኔያቸው ምስጢር ያስገነዝባሉ ።

ቃሪክ

አዳም አምላኩ « አትብላ » ያለውን በለስ በሄዋን መሪነት በመብላቱ ሳተ ፤ ህግን አፈረሰ ፤ በዚህም ምክንያት ተዋረደ ፤ ከገነትም ወጣ ። አዳም በተፈጥሮ እውቀት ከውድቀት አላመለጠም (ዘፍጥ. 3 ፥ 3—24 ፤ 4 ፥ 1—15) ።

18 መወድስ

ዘንብረ መድኀን (አለቃ ፥ ዘልማን ሥላሴ)

በአፈ ዕዒያት ይሴባሕ አካለ መርዓዊ ፤
እስመ ለዕዒያት ሠሉሙ እርእዮሙ እደዊሁ
ትንግሌ ምትረት ያእምሩ እምግዚሠ እሳት ገቦሁ ።
ወይቤ ሕማም በዙረ ኢዮብ
ይፃእ መርዓዊ እምሕይወት ጽርሑ ፤
ተመትሮ ቃለ ኢዮብ
እኮኑ ጸሐፈ በውስተ ጽላት እጓሪሁ ።
ኢንክልሂ ከመ ንንብብ ለንብረ መርዓዊ ዜናሁ ፤
እኮኑ ኢይትፈጸማ አሀጉረ እስራኤል ሥቃያቲሁ ።
እመሰ ተጽሕፈ ሕማመ ዙሉ ሥጋሁ
ዓለም እምኢያግመሮ ፤ ከመ ያእምር ልቡናሁ ።

ትርጉም

የመርአዊ ሰውነት በትሎች እፍ ይመስገናል ፤
ወገቡ/ እሳትን ከመዳሰስ የተነሳ መቆረጥ/ ትንሳኤን
ያውቁ ዘንድ
እጆቹን ለትሎች ሁሉ አሳይታቸዋልና ።
የኢዮብ በኩር / ሀማም
«ሙሽራ ከሀይወት/ አዳራሹ ይውጣ» አለ ፤

መቀረጥ/ የኢዮጣ ቃልን
በእግሮቹ / ፅላቶች ፅኽልና ።
የገብረ መርአዊንም ዝና እንናገር ዘንድ አንችልም ፤
ሲቃዮቹ/ የእስራኤል አገሮች አይረፀሙምና (አያልቁምና)።
የሰጋው ሁሉ መከራ ቢነፍ ግን
ልቡ ያውቅ ዘንድ አለም በሙሉ ባልቻለውም ነበር ።

ም ስ ጢ ር

ከፍተኛ የፈጠራ ችሎታ ያለውን ሰው ስራ የተመለከቱ ሰዎች ባለሙያውን እንደሚያመሰግኑት የገብረ ክርስቶስም አካል በሀ ሙም ተያዘ ፥ እጆቹ ቆሰሉ ፥ ተቆራረጡ ፥ ጠቅላላ አካሉ ተላ ። ቁስሉም እንደ እሳት ፈጀው ፥ አቃጠለው ። ትሉም በሰውነቱ ላይ ተርመሰመሰ። «የእስራኤል ሀገር ስፋት ቢሄዱት አያልቅም» ተብሎ እንደተነገረ የገብረ ክርስቶስም ስቃይ ተነግሮ አያልቅም ማለት በቅኔው ተገልጧል ።

19 መወድስ

ዘውብዝት (ቁሰ ገበዝ ዘብሥና)

ከፍለ ጊዮርጊስ ኮነ ክፍለ አርባዕቱ
እሰመ ክልኤቱ እፍላግ ተረከቡ በኀቤሁ ።
መመፍትው ይኅዝን ወልደ ነጐድጓድ እጉሁ ፤
ኤፌሶን አኮኑ ለሰማዕት ዕፃሁ ፥
ወምድረ ከነዓን ተካፈለ ፤
አምጣነ አውረሶ ለሰምዕ ሰይፈ ነበልባል ወላዲሁ ።
ለሞትሂ አመ አብጽሐ ሰይፈ ነበልባል ደዌሁ
አኀዙ ይትጋብኡ አክሊላተ ሰማይ አዝማዲሁ ፤
ወበሕማመ ሰዶም ነድ ለእመ ኀልቀ ሥጋሁ
ሞሠርት አበ ነፍሱ ሐተተ ልቡናሁ ።

ትርጉም

የጊዮርጊስ ክፍል የአራት (ወንዞችን) ክፍል ሆነ
ሁለቱ ወንዞች በርሱ ዘንድ ተገኝተዋልና ።
ወንድሙ ወልደ ነጎድጓድም ያዝን ዘንድ ተገቢው ነው ፤
የሰማእት አጣው ኤፌሶን ነውና ፥
የከነአንን ምድርም ተካፈለ ፤
አባቱ /የነባልባል ሰይፍ ለሰማእት(ጊዮርጊስ)
አውርሶታልና ።
በሽታው/ የነበልባል ሰይፍም ለሞት ባደረሰው ጊዜ
የሰማይ አክሊሎች/ዘመዶቹ ይሰበሰቡ ዘንድ ጀመሩ ፤
በሰዶም ሀማም / እሳትም ስጋው ቢያልቅ
የነፍስ አባቱ / መጋዝ ልቡናውን መረመረ ።

ም ስ ጢ ር

ከአራቱ ወንዞች (ጤግሮስ ግዮን ኤፌሶን ኤፍራጥስ) ሁለቱ ጤግሮስና ግዮን ግርና ውተት ናቸው ይባላል ። ጊዮርጊስም በሰማ እትነት አንገቱን በተቆረጠ ጊዜ ግርና ውተት ከአንገቱ ፈልቀዋል ይላሉ ።

ወልደ ነጎድጓድ ዮሐንስ ግን በሰይፍ አልተቆረጠም ። በጹር ዘመን አባት ለልጁ ርስቱን እንደሚያወርሰው ቅዱስ ጊዮርጊስም አክሊል ያገኘው (የተቀዳጀው) በሰይፍ በመቆረጡ መሆኑን ቅኔው ያስረዳል ። ሀመምቱኛ ሰውም በሽታው ለሞት ባደረሰው ጊዜ ዘመ ዶቹ እንደሚሰበሰቡ ፥ ጊዮርጊስም በሰይፍ በተቆረጠ ጊዜ አክሊሎች ወርደውለታል ። በሽተኛ ሰው ሰውነቱ በህማም ሲያልቅ እና ሲደ ክም የነፍስ አባቱ ቀርቦ በመስቀሉ እንደሚዳስሰው ፥ ጊዮርጊስም በመጋዝ ሰ ተርተሩንና በእሳት መ ቃጠሉን ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

አራት ታላላቅ መንዞች ከኤዶም (ከኤድን) ገነት ስር መንጭተው የተለያዩ ቦታዎችን ያጠጣሉ ። ኤፈሶን ፣ ግዮን ፣ ጤግሮስ ፣ ኤፍራጥስ ይባላሉ ። እነዚህ መንዞች ፈለገ ወይን ፣ ፈለገ ሀሊብ ፣ ፈለገ መአር ፣ ፈለገ ዘይት ናቸው ይባላል (ዘፍጥ. 2፡ 10—14) ።

ከነአን አብርሃም በእምላካዊ ጥሪ ከካራን ወጥቶ የወረሳት አገር ናት ፤ ከነአን ማለት ፣ የወተትና የማር አገር ማለት ነው ። ከዚህም የተነሳ « እንተ ታውኅዝ ሀሊበ ወመዓረ (ወተትንና ማርን የሚታፈስ ናት)» እየተባለ ይነገርላታል (ዘፍጥ.12፡ 1—8) ።

ጊዮርጊስ የልዳና የፋርስ ተወላጅ ከሆኑት ከዞሮንቶስና ቴዎብስታ ተወልዶ ካደግ በሁዋላ የክርስቶስን ጹካ (ፍሊጋ) ተከተለ ፤ ከዚህም የተነሳ በቢሩት አገር እያንዳንዱ ሰው አንዳንድ ልጁን ለዘንዶ ይገብር ስለነበር ጊዮርጊስ ዘንዶውን በጦር ወግቶ ገድሎ ፣ የዘንዶው ግብር ልትሆን በዛፍ ላይ የወጣችውን ቢሩታዊትን አድኗታል ። ከዚህም አያይዞ በከሃዲዎች ነገስታት ፊት ክርስቶስን እየሰበከ ፣ ሰባት አመት ሙሉ በአረመኔዎች ተሰቃይቷል ። ወገቡን ቀጭተው ከብረት በተሰራ በሬ ውስጥ አግብተው የእንኩትት እንደከብት አስሂደውታል ፣ በእሳት አቃጥለውታል ። በመጋዝ መግ ዘውታል ፤ አካላቱንም በስለት ለአስር ቆራርጠው ቁርጥራጩን ደቁሰውና ጹቄት እድርገው በይድራስ ተራራ ላይ በነፋስ አዝርተውታል ። ከዚህ ስቃይ በሁዋላ በእምላካዊ ተአምር ሶስት ጊዜ እየሞተ ተነስቷል ። በእንዲት ሴት ቤት ግሰሪያውን በግንድ ብስ ውስጥ አግብተው ከግንዱ ጋር ጠፍረው አስረው ቢያሳድሩት ደረቁን ግንድ በእምላካዊ ተአምር አለምልሞታል ። መቃብሩን በእግሩ ቢረግጠው በእግዚአብሄር ስም ሙትን አስነስቷል ። በመጨረሻው አንገቱን በሰይፍ ተቆርጦ ሞቷል ። በዚህ ጊዜ በሰባት አመት ስቃዩ ልክ ሰባት የክብር አክሊሎች ወርደውለታል ይባላል (ስንክ. ሀዳር 7 ፣ ጥር 18 ፣ ሚያዝያ 23 ። ገድለ ጊዮርጊስ) ።

20 መወድስ

ዘይትባረክ ቂርቆስ (መሪጌታ)

መድኃኔ ዓለም መገዝአ አመ ይጠባሕ
አንስርተ ሰማይ አስዋጥ የወዱ ላዕሌሁ ፤
አምጣነ ሙሉ ያጸግብ ዘያስተፈሥሕ ሥጋሁ ።
ወመጠነ ይክል አፈጋዊ
ኩናተ ሐራዊ አጥረየ ገቦሁ ፤
ባሕቱ ነጋድያን
ቅሥፈታተ ሥጋ ወዐፅም ተካፈሉ አነጻሁ ።
ደመ ወልድሂ መግዝአ ሳሕም አመ ተከፅወ እፍአሁ
ይጥሕሩ ላዕለ ደሙ ከዋክብት እሊአሁ ።
ባሕቱ ነፍሳት ገባእተ ሲኦል ዘበዝኁ
ይወፅኡ በጽባሕ ወሠርከ ይትፈሥሑ ።

ትርጉም

ፍሪጻ/ መድሃኔ አለም በታረደ ጊዜ
የሰማይ አሞሮች /ጅራፎች በላዩ ይዘረጉ ፤
ደስ የሚያሰኝ ስጋው ሁሉን ያጠግባልና ፥
የሚችለውንም ያህል
ሽግግሉ / የወታደር ጦር ጎኑን ገዛ ።
ነገር ግን ነጋዴዎች /
የስጋና የአጥንት ግርፋቶች ቆዳውን ተካፈሉ ።
የበሬ ፍሪጻ /ወልድ ደምም በውጭ በፈሰሰ ጊዜ
ኮከቦች /ወገኖቹ በደሙ ላይ ይጮሃሉ ።
የሲኦል ገበሬዎች / የበዙ ነፍሶች ግን
«በጠዋት ይወጡና በምሽት ደስ ይሰኛሉ ። »

ም ስ ጢ ር

የፍሪጻ ከብት በተጣለ ጊዜ አሞሮች በላዩ ይዘራሉ ፤ ከርሰቱ ስም በእይሁድ እጅ በተያዘ ጊዜ ያሞሮች ምሳሌዎች የሆኑ ጅራፎች በሲጋው ላይ ተጣሉ ። የፍሪጻ ከብቱንም ስጋ ተቀራማኞች (ቱታ ራሮች) እንደሚካፈሉ የተቀራማች ምሳሌ የሆነው የወታደር ጦር የክርስቶስን ጎን ወጋው ። ነጋዴዎችም የከብቱን ቁርበት ገዝተው እንዲከፋፈሉ ጅራፎችም የክርስቶስን ቆዳ አባዘቱት ።

የፍሪጻም ደም በፈሰሰበት ቦታ ላይ የታረደው ከብት ወገኖች ይጓጉራሉ ። እንዲሁም በከብቶች የተሠሉ የሰማይ ከዋክብትም የክርስቶስ ደም ሲፈስ ረግፈዋል በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አስመጥረዋል ።

በተጨማሪም ገበሬዎች በጠዋት ወጥተው ጥሩ ምርት አምርተው ከቤታቸው ሲገቡ ደስ እንደሚሰኙ ፣ በአጻም በደል ወደ ሲኦል የወረዱ ሰዎች ነፍሳትም በክርስቶስ ሞት ነፃነትን ሳግኝተው መደሰት መቻላቸውን ባለቅኔው ያስገነዝባሉ ።

21 መወድስ

አይሁድ ፈቅሑ በርእሰ ፈታሒ
በርእሰ አርዌ ምድር ዝብጠተ ዝብጠተ አርዌ ምድር ጸላኢሁ ፣
እምነ አርዌ ብርት አምላለ አመ ይነሥእ ለሊሁ
ይትጎፈር ጸላኢ ዘጸልአ አባሁ
እስመ ይቤልዋ ዘከማሁ
ለአርዌ ዘብርት ዕቀቢ ሰኰናሁ ።
ኢተወውቀሂ ከሞኔ ወርብ ለዘየሐትት ኪያሁ ፣
እስመ ከመ መዓልት ኢያብርህ ፀሐይ ዘላዕሌሁ ፣
ወኢንስምዮ ሌሊተ ነጸርያኒሁ
ውስተ ገጸ ሰማይ ኢረከብነ እንዘ ከዋክብት ይትዋሀውሁ ።

ት ር ጉ ም

እርሱ ከብረት እባብ አምሳያን ቢይዝ ፣
በምደር እባብ ራስ ላይ መመታትን (መቀጥቀጥን) በፈረደ በአምላክ ራስ
የጠላቱ ምድር እባብን መመታት አይሁድ ፈረዱ ፤
አባቱን የጠላ ጠላት ያፍር ዘንድ
የብረት እባብን እንደርሱ ተረከዙን ጠብቂ ብለዋታልና ።
የአርብ ሁኔታም እርሱን ለሚመረምር አልታወቀም ፤
በላዩ ያለ ፀሀይ እንደ ቀን አላበራምና ፣
ተመልካቾቹ ሌሊትን እንዳንለውም
በሰማይ ፌት ኮከቦች ሲብለጨለጭ አላየንምና ።

ም ስ ጢ ር

ባለቅኔው « ስራ ለሰሪ እሾህ ላጣሪ » እንዲሉ አዳምና ሄዋንን በአሳሳተች እባብ ላይ አምላክ በበትር መቀጥቀጥን ስለ ፈረደ ብድራት አይሁድም በልጁ በክርስቶስ ላይ እንደ እባብ በበትር መቀጥቀጥን ፈረዱበት ይላሉ ። ይህም የሆነው ክርስቶስ ሙሴ ስለእስራኤል ደህንነት የሰቀለው የብረት እባብ ምሳሌ ከመሆኑ የተነሳ ነው ። ደግሞ « እባብን የአዳምን ተረከዝ እየጠበቅሽ ንደፊ » እንዳላት አይሁድም እግሮቹን በችንካር ቸንክሩት በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

ታ ሪ ክ

አዳምና ሄዋን እፀ በለስን በበሉ ጊዜ ያሳትቻቸው እባብን ራስ በበትር እንዲቀጠቅጡና እርሷም እግራቸውን እንድትነደፍ ከአምላክ ተፈርዶባቸዋል ።

አዳምም ጠላቱ ሰይጣን ከክብሩ ሊያዋርደውና ተገዢው ሊያደርገው አስቦ በበለስ መብል አምላክነት የሚገኝለት አስመስሎ መሞቻውን ሲነግረው አምላክ « አትብላ » ያለውን በለስ በሄዋን መሪነት

በመብላት ሳት ፡ ህግ አፈረሰ ፡ በተፈጥሮ እውቀቱ ከውድቀት አላ መለጠም ። በዚህ ምክንያት ተዋረደ ከገነት ወጣ ተብሎ ይነገራል (ዘፍጥ. 3 ፡ 3—24 1 4 ፡ 1—15) ።

ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለ እለት አይሁድ እጅጉንና እግሮቹን ከመስቀሉ ጋር በችንካሮች ጠርቀው ቸንክረውታል ፡ ራሱንም በዘ ንግ ፈንክተውታል ። ፀሀይ ከስድስት እስከ ዘጠኝ ለእት ጨል ጧል ፡ ከዋክብትም ረግፈዋል ፡ ሙታን ተነስተዋል ፡ ድንጋዮች ተፈ ትተዋል ። ከመቃብር የተነሱት አምላክነቱን ለዘመዶቻቸው መስክ ረዋል ይባላል (ሰንክ. መጋቢት 27) ።

22 መወድስ

ዘንብረ ሙስቀል (መምህር)

አጽንዖሙ ቶማስ መምህረ ቡራኬ
በክልኤ አእጋር ወበ ጎምስቱ እጻብኢሁ
ለጎምሳ ምእት ሥቃያቲሁ ፡
ዘትከልት በሙሐዘ ደም ገለዓድ ገቦሁ
ዕፀ ዘይት ሰብእናሁ
ፍሬሃ ምትረተ እስመ ትሁብ በበጊዜሁ ።
ሰይፍኒ ዕፀ ክርካዕ ለእመ ጸገየ ናሁ
ለቶማስ ሐዋርያ መሀበ መዐዛሁ ፡
እስመ ኢይሌሊ ዘንተ እምነ እዴሁ
መዋዕለ ምትረት ጽጌረዳ እስከነ የኅልፍ እምኔሁ ።

ትርጉም

የቡራኬ መምህር /ቶማስ
በሁለት እግሮቹና በአምስት ጣቶቹ
አምስት ሽህ ሰዎች / ስቃዮችን እጠገባቸው ፤

የደም ውሃ መፍሰሻ በሆነ በጎለአድ ጎኑ የተተከለች
የዘይት እንጨት ሰውነቱ
ፍሬዋ መቆረጥን በየጊዜው ትሰጣለችና ።
ሰይፍ የሎሚ እንጨትም አሁን ቢያብብ
ለቶማስ ሀዋርያ ሽታውን ሰጠ ፤
የመቆረጥ ፅጌረዳ ወቅት ከርሱ (ከቶማስ ዘንድ)
እስኪያልፍ ድረስ ይሀን (ሰይፍ ሎሚን) ከእጁ አይለይ
ምና ።

ምስጢር

ክርስቶስ አምስት ሽህ ሰዎችን በሁለት አሳና በአምስት እን ጀራ እንዳጠገባቸው ሀዋርያው ቶማስም በእጆቹና በእግሮቹ ስቃይ ትን ተቀበለ ። በውሃ መፍሰሻ ጻር የተተከለች ተክልም ዐየጊዜው እንደምታራራ ቶማስም በተቆረጠ ቁጥር ደሙ ፈሰሰ ።

እንጨት ሲያብብ መአዛው ከሩቅ ይሸታል ፡ የአበባም ወቅት እስኪያልፍ ድረስ አበባው ከሚወዱት ሰዎች እጅ አይለይም ፤ እንደ ዚህም ሁሉ ቶማስም የስቃይ ዘመኑ እስኪያልፍ ድረስ በሰይፍ በመ ቆራረጥ እጁን አጣ ማለት በቅኔው ተገልጧል ።

ታሪክ

ኢየሱስ ክርስቶስ በመጥምቁ ዮሀንስ የተፈፀመበትን ሁሉ በሰማ ጊዜ ፡ ብቻውን ወደምድረ በዳ በታንኳ በባህር ላይ ፈቀቅ አለ። ህዝቡም በእግር ተከትሉት ፤ በዚህ ጊዜ ከታንኳው ወጥቶ ብዙ ህዝብ አየና አዘነላቸው ። በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው ስለምግብ እጦት ህዝቡን እንዲያሰናብታቸው ኢየሱስን አሳሰቡት ። ኢየሱስ ግን ለጊዜው በተግሪዎቹ ዘንድ የነበሩትን ሁለት አሳዎች ንና አምስት እንጀራዎችን አበርክቶ አምስት ሽህ ሰዎችን አጥግ ቧል ። አምስት ሽህ ሰዎች ከተመገቡ በሁዋላ አስራ ሁለት ቅርጫት ትራፊዎችን ደቀ መዛሙርቱ አንስተዋል ይባላል (ማቴ.14፡12—26) ።

23 መወድስ

ዘደስታ (አለቃ ፡ ዘተድባበ ማርያም)

ገብረ መርዓዊ ሰገደ በጊዜ ሕማሙ
ለምስል ዘወርቅ ድኅረ ቆመ በቅድሜሁ ፤
እስመ እንዘ ልሕኵት ነዮሙ አጸብኢሁ
ዘእብን እግሩ ወዘብርት ሐቌሁ ፡
ወእብን ደዌ ሥጋሁ
ዘእንበለ እድ ተበትከ እምእድባረ ኢዮብ ከናፍሪሁ ።
ቅዱሳንሂ አኀወ ሥጋ ሕዋሳቲሁ
አመ በፍኖት ተራከቡ በበይናቲሆሙ ይትአምኑ ፤
እስመ ለረቢ ትጉህ ሥጋ ዚአሁ
በስዒመ እግር ያገብእ ይሁዳ ደዌ ሥጋሁ ።

ትርጉም

ገብረ መርአዊ በሀማሙ ጊዜ
በፊቱ ከቆመ በሁዋላ ለወርቅ ምስል ሰገደ ፤
እጣቶቹ ሽህላ ሲሆኑ
እግሩ የድንጋይ (ምስል) ነውና ፡ ወገቡም የብረት (ምስል) ነውና ፡
የስጋ ሀማም /ድንጋይም
ከኢዮብ ተራሮች /ከንፈሮቹ ያለ እጅ ተፈንቅሏልና ።
የተመረጡ የስጋ ወንድሞቹ/ ሰውነቶቹም
በመንገድ በተገናኙ ጊዜ እርስ በራሳቸው እጅ ይነሳሳሉ ፤
ትጉ መምህር /ስጋውን
የስጋ በሽታ /ይሁዳ እግርን በመሳም ያስይዘዋልና ።

ምስጢር

ናቡከደነፆር ለወርቅ ምስል እንደሰገደና « ራሱ የወርቅ ደረቱ የብር ፡ ወገቡ የናስ ፡ ጭንና ጭኑ የብረት የሆነ ምስልን ከተራራ የወረደ ድንጋይ ሲቀጠቅጠው » እንዳየ ገብረ ክርስቶስ ለወርቅ ምስል ሰገደ ማለትም ፡ ከሙሽራ ቤቱ ወጥቶ ሲመንን በያዘው ደዌ ስጋ አካሉ ሁሉ ቀለጠ ፡ ፈራረሰ ፡ ተቆራረጠ ማለት ነው ።

በዚህም ላይ ይሁዳ እግሩን በመሳም ምልክትነት ክርስቶስን እንዳስያዘውና ድንገት በመንገድ የተገናኙ ሰዎች ሰላምታ እንደሚሰጣጡ የገብረ ክርስቶስ ሰውነት በደዌ የተለወጠና እግሩንም ደዌው ያሳበጠው ነና በጉዞ ላይ ሳለ ነው ይላሉ ባለቅኔው ።

ታሪክ

ገብረ ክርስቶስ (ገብረ መርአዊ) የቁስጥንጥንያ ንጉስ የቴዎዶስዮስና የንግስት መርኬዛ ልጅ ነው ፤ ይሁን እንጂ ልጅ አጥተው ሲኖሩ በብዙ ያምና ፀሎት ያገኙት ወላዶቹ የእግዚአብሄር ሰዎች ከመሆናቸው የተነሳ ልጃቸው ገብረ ክርስቶስ «ምንት ይበቁየ ለሰ ብእ ለእመ ኮሎ ዓለመ ረብሐ ፤ ወነፍሶ ሀጕለ » (ሰውን ምን ይጠቅመዋል አለምን ሁሉ ቢገዛና ነፍሱን ቢያጠፋ) » በሚለው በክርስቶስ ቃል ተመርቶ የአባቱን መንግስት እንደጉድፍ ቆጠረው ፤ የክርስቶስንም መንግስት ሽቶ ክርስቶስን ለመከተል ቁርጥ አሳብ አደረገ ። ገብረ ክርስቶስ በዚህ ቁርጥ አሳብ ላይ ሳለ አባቱ ያለ ፈቃዱ አቻውን የሮምን ንጉስ ልጅ አጋባው ። እርሱን ሙሽራውንና ሙሽራይቱን ስርአቱ ጋብቻ ያድርሱ ብለው ሚዜዎች እጫጉላ አገቧቸው ። በዚህ ጊዜ ከሙሽራይቱ ጋር ሳይተኛ የአለሙን ከንቱነትና የምናኔወን ነገር በመግለጥ ሙሽራይቱን በቃል ኪዳን አግላትና« እህቴ ሆይ እኔ ለሰማያዊው ሙሽራ አጭቼሻለሁ ፤ አንቺም ራስሽን ለርሱው አስገዥ» ብሎ እድምተኞቹ ሁሉ በውድቅት እንደተኙ ፡ ራሷን ስሟትና ተሰናብቷት በሌሊት ከሜንላ ቤት ወጥቶ መነነ ።

ስለዚህም ሙሽራይቱ «እኔን ለማን ትተወኛለህ» እያለች ስታ ለቅስ አደረች ። ሲነጋም ሙሽራይቱ ብትጠየቅ «ራሴን ስሞኝና ተሰናብቶኝ በሌሊት ወጥቶ ሄደ ፤ የሄደበትን ግን አላውቅም»አለች ።

እርሱ ግን ከነጋዴዎች ጋር ባህር ተሻግሮ አንድ አመት ያህል ተጉዞ አርማንያ ደረሰ ። በዚያም አገር የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ስለነበረች ፥ በዚያች ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ተጠግቶ ራሱን ከነዳያን አስቆጥሮ (እንደችግረኞች ሆኖ) በያምና በፀሎት አምስት አመት ተቀመጠ ። ወላጆቹ ለነዳያን የሚሰ ፀውት ብዙ ገንዘብ አስይ ዘው ከላኳቸው አምስት መቶ ፈላጊዎች ሁለቱ እርሱ ከነበረባት ቤተ ርስቲያን ደርሰው ለነዳያን ሲመፀውቱ የወላጆቹን ገንዘብ አብሮ በመመፅወት ራሱን ነዳይ ስላደረገ ፈላጊዎች ሳያገኙት ተመልሰዋል።

ከዚህ በሁዋላ ቅድስት ማርያም ለአንዱ ቄስ በህልም ታየቸውና ያን በውጭ ወድቆ የሚኖረውን የእግዚአብሄርን ሰው ወደ ወ ስጥ አስገባው አለችው ። ካህኑም ወደ ቤተ ክርስቲያን ወ ስጥ ካስገባው በሁዋላ በማርያም ስእል ስር «እየሰገደ ፤ እመቤቴ ለምን ድብቄን ገለጥ ሽብኝ » ብሎ ሌሊት ወጥቶ ሄደና በወላጆቹ ደጃፍ ወድቆ ተጋድሎ ውን ቀጠለ ። አሰራ አምስት አ ት በዚያው ሲኖር ሰውነቱ በህ ም ቆስሎ ስለነበር እርሱ መሆኑን ያወቀው የለም ። ስለዚህም የወላ ጆቹ አገልጋዮች «ይህን ክርፋታም ከዚህ ማን ባነሳልን ግማቱ ገደ ለን » በማለት ተ ሮ እንዲሄድላቸው የምግብ እጣቢ ን ያፈሱበ ትና አጥንቱን ይጥሉበት ጀመር ። ወ ሾቱም አጥንቱን ሲሉ በላዩ ላይ እየተናከሱ ይረፋረፉበት ነበር ።

በዚህ የተነሳ «ፈጣሪዬ ሆይ! በአባቴ ቤተሰቦች ፍጻ እንጻላ በዛባቸው ነፍሴን ከሲጋዬ ለይና ወደአንተ ጥራኝ» እያለ ይፀልይ ጀመር ። ስለዚህም ከዘህ አለም በሞት ተለየ ። በመ ሃል እጁ ተጨ ብጦ የተገኘው ፅሁፍ ቢነበብ «እኔ የቴዎድስዮስና የመርኬዛ ልጅ ገብረ ክርስቶስ ነኝ» የሚል ስለሆነ ወላጆቹ በግንባራቸው እየተ ከሰከሱ አለቀሱለት ። በረከቱን የሚሹት ህዝቡም አስከሬኑን ወደ መቃብር አላስሄደው ብለው ነበር ። ብርሃንም በመቃብሩ ላይ እንደ ቀስተ ደመና ተተከለበት ይባላል (ስንክ. ጥቅምት 14) ።

ናብከደነጾር በሌሊት ተኝቶ ሳለ ራሱ የወርቅ ፥ ደረቱና እን ገቱ የብር ፥ እንድ እግሩ የሸክላ ፥ አንድ እግሩ የብረት የሆነ ትልቅ ምስል በፊቱ ቆሞ እርሱ እርሱን ሲመለከተውና እርሱም እርሱን ሲመለከት ፤ ታላቅ ድንጋይ ከረዥም ተራራ የሰው እጅ ሳይነካው ወርዶ ቀጥቅጦ ሲያጠፋውና ተመልሶ ተራራ ሲያህል ያንንም ነፋስ ሲያጠፋው በህልሙ አይቷል (ዳን. 2 ፥ 1—49) ።

ከዘመድ ተለይተውና ከአገር ወጥተው ፥ ዳዋ ጥሰው ፥ ጤዛ ልሰው ፥ ድንጋይ ተንተርሰው ፥ ሌጦ ለብሰው ፥ የሌሊት ጭንቅና የአራዊትን ግርማ የፀሀይን ቃጠሎ ታግሰው ፤ በዱርና በዋሻ የሚ ኖሩ ው ናኞች ሰዎች ቅዱሳን ይባላሉ ። እነርሱም በመንገድ ሲገናኙ እንዲያው እይተላለፉም ው ንፈሳዊ ሰላምታን ተሰጣጥተውና እም ላካቸውን እመ ስግነው ይሄዳሉ ። ቅዱሳን ማለት ልዩዎች ፥ ምስጉ ኖች ፥ ንፁሆች ማለት ነው ።

ኢየሱስ በዚህ አለም ሰው ሆኖ ሲመላለስ አስራ ሁለት ተከታዮች ሰዎችን በቅደሚያ ሠ ርጧል ። ከአስራ ሁለቱም እንዱ ይሁዳ ነው ። ኢየሱስ የማህበሩን ገንዘብ ያዥ አደርጎት ነበር።ግርያም እንተ እፍረት ኢየሱስን የከበረ ሽቶ በቀባቸው ጊዜ « እየ ጉድ ! ምን ያህል ሽቶ እበ ላሽች!ብዙ ገንዘብ ያወጣ ነበር! » ብሎ ተቆረቆረ። ስለዚህም ኢየሱስን በአይሁድ ለማስያዝ በገንዘብ ተገዛ ፤ እርሱ በተግሪ ደንብ እግሩን የሚሳሠወ ኢየሱስ መሆኑን ምልክት በማድረግ አሳልፎ ሰጣቸው (ማቴ. 26 ፥ 14—25) ።

24 መወድስ

ዘገብረ ጻድቅ (መሪጌታ ፥ ዘፍቼ ጊዮርጊስ)

ለእመ ሐተታ ሐተትነ ጠበብተ ሐተታ
አልቦ በምድር ዘይትአመን እስከናሁ ፤
እመ ኮነ ወልደ ወዘመደ ሥጋ ከማሁ
ወደቂቀ እም ለእመ ኮነ
ቃየል አምጣነ ቀተሎ ለአቤል እኁሁ ፤

አቤሴሎምኒ ለአምናን
ወቀዳግዊ ሶርሶር ለሰናክሬም አቡሁ ።
ለሰብአሰ ዘይኄይሶ ዘኢተዘምደ ምስሌሁ ፤
ጲላጦስ ዘኢተዘምደ እንዘ ይትራኅራኅ ላዕሌሁ
ለዝንቱ ምሳሌየ ወይን ከመ ይቅሰሙ ፍሬሁ
አምጣነ ለወልድ ናላዌ ዙሱ ቀተልዎ አዝማዲሁ ።

ት ር ጉ ም

የምርምር ጥበበኞች ምርምርን ብንመረምር
እስከ አሁን ድረስ በምድር የሚመታን የለም ፤
ልጅም ቢሆን እንዲሁም የስጋ ዘመድ ቢሆን
የእናት ልጅም ቢሆን
ቃየል ወንድሙ አቤልን ገድሎታልና ፥
አቤሴሎምም አምናንን ገድሎታልና
የቀደመ ሶርሶርም አባቱ ሰናክሬምን ገድሎታልና ።
ለሰውስ የሚሻለው ከርሱ ጋር ያልተዛመደው ነው ፤
ያልተዛመደው ጲላጦስ በርሱ ላይ ሲራራ ፥
የዚህ ምሳሌየ/ የወይን ፍሬን ይለቅሙ ዘንድ
ዘመዶቹ የሁሉ ጠባቂ ወልድን ገድለውታልና ።

ም ስ ጢ ር

ልጅም ዘመድም ፥ ወንድምም ቢሆን በዚህ አለም ላይ የሚ
ታመን የለም ። ይህንንም ለመረዳት ቃየል ታናሽ ወንድሙ አቤ
ልን ገድሎታል ፤ አቤሴሎምም ወንድሙን አምናንን ፥ ሶርሶርም
አባቱን ሰናክሬምን ገድለዋል ።

ባለቅኔው ከዘመድ ባእድ መብለጡንና ዘመድ አለመታመኑን
አመልክተው የግይዘመደው ጲላጦስ ሲራራለት የእናቱ የድንግል
ማርያም ወገኖች (ዘመዶች) አይሁድ ክርስቶስን ሰቅለውታልና
ከዘመድ ባእድ ይሻላል ይላሉ ።

ታ ሪ ክ

አቤልና ቃየል ከአዳምና ከሄዋን የተወለዱ ወንድማማቾች
ናቸው ። እግዚአብሄር የቃየል መስዋእት ባለመበጀቱ ሳይቀበል
ለት የአቤልን መስዋእት ስለበጀ ተቀበለለት ። ስለዚህም ቃየል
ተናደደ ።

በዘመናቸው ባእድ ሰዎች ስለሌሉ ፥ የአቤልን መንትያ ቃየል ፥
የቃየልን መንትያ አቤል እንዲያገቡ በአዳም ተወሰነ ። የቃየል
መንትያ መልከ መልካም ስትሆን የአቤል መንትያ መልከ ጥፉ
ነበረችና ቃየል በውሳኔው አልተስማማም ፥ በጣም ተቆጣ ፥ አቤል
ንም ተበቀለው ። «ወንድሜ አቤል ፤ ና ውሃ ጠጥተን እንምጣ» በማ
ለት አታለለው ። እርሱ በቅድሚያ ጠጣና አቤል በሁዋላ ተጎንብሶ
ውሃ ሲጠጣ በድንጋይ መትቶ ገደለው (ዘፍጥ. 4 ፥ 3—15) ።

አቤሴሎምና አምናን በእናት አንድ ሳይሆኑ ከዳዊት የተወ
ለዱ ወንድማማቾች ናቸው ። አምናን አባቱ ዳዊት ከአቤሴሎም
እናት የወለዳትን እህቱን ትእማርን ባዝሙት መንፈስ ወደዳት ፥
ከብረ ድንግልናዋንም ከማጥፋት ያረሰ ። በሁዋላ አቤሴሎም ተናደ
ደና የልቡን በልቡ አድርጎ ፥ አምናንን የሚበቀልበትን አመቺ
ጊዜና ምክንያት ፈለገ ። ስለዚህም ለበጎች ጠጉር ሽለታ በአል
ድግስ ደገሰና አባቱ ዳዊት ከእነልጆቹ በግብጥው እንዲገኝለት
ጠየቀ ፥ አባትየው ለግብጥው ፈቃደኛ ባለመሆኑ አምናን ከእነወ
ንድሞቹ በግብጥው እንዲገኝለት አቤሴሎም ከአባቱ አስፈቀደና
እርሱን ለመበቀል አመቺ ጊዜና ምክንያት አገኘ ። አምናን በወ
ይን ጠጅ ደስታ ሲዘናጋለት አቤሴሎም ከታዛዣቹ ጋር ተመሳ
ጥሮ አስገደለውና ኮበለለ ።

የቀሩት ወንድሞቹ ሸሽተው ወደዳዊት ሄዱና ከአባታቸው
ጋር ለወንድማቸው አምናን አለቀሱለት ። ይልቁንም ዳዊት አም
ናን የበኸር ልጁ እንደመሆኑ መጠን እጅግ በጣም አዝኖ ነበር
(2 ሳሙ. 13 ፥ 1—39) ።

የአሶር ንጉስ ሰናክሬም ወደእስራኤል ንጉስ ወደ ህዝቅያስ ዘምቶ በህዝቅያስ ላተበት ፥ ተመካበት ፥ አስጨነቀው ፥ እስከ መሰ ግመጥም አደረሰው ። በእግዚአብሄር ስም ላይ ተሳንደ (ተቀጣጠበ ፥ ተዘባበተ) ። ህዝቅያስም እዝግሚያውን አይቶ የሚያዋጣውን አሰቦ ወደ እግዚአብሄር ቤት ገባ ፥ ማቅ ለበሰ ፤ ትቢያ ነሰነሰ ። ያመ ፀለየ ፥ በሀጢአቱና በህዝቡ በደል ተፀፀተ ። አምላኩም አዘ ነለት ፥ ንስሃውንም ተቀበለው ።

ስለዚህም መልአኩ ቅዱስ ሚካኤልን እንዲረዳው ላከለት ። መልአኩም የአሶር ንጉስ ሰናክሬም ህዝቅያስን በጦር ሃይል ሊመ ታው በሰፈረበት ቦታ ሴሊቱን ሰራዊቱንና የጦር መሪዎቹን እው ድሚቸው አደረ ። ንጉሱ ሰናክሬም ከጥቂት ተከታዮቹ ጋር ተባ ብሮ እቤቱ እንደገባ ፥ ሁለቱ ልጆቹ ሶርሶርና አድራሜሌክ ሀብቱን ጥሎ ባዶገሬውን (ባዶ እጁን) በመምጣቱ ተበቀሉት ፤ በጣኦቱ ቤት ገብቶ ሲሰግድ በዘንዘና ራስ ራሱን ብለው ገደሉት (2 ነገስ. 18 ፥ 1—37 ፤ 19 ፥ 1—37) ።

25 ዕዝል ጉባኤ ቃና

የእምር ተግስ በበዕለቱ ግዕደ ሳውል ጸናሒ
ጣዕመ ጸብኅ ምትረተ እንዘ በእንፉ ያርሒ ።

ትርጉም

በየቀኑ የጳውሎስን ግእድ ተጠባባቂ ተግስ
የወጥ ጣእም /መቆረጥን በአፍንጫው እሽትቶ ያውቃል።

ምስጢር

ግብረ በላ የወጡን ጣእም በአፍንጫው እያሸተተ እንደሚ ያውቅ ፥ የክርስቶስን መንግስት ድጅ የሚጠና ተግስም አፍንጫ ውም ሳይቀር መላ አካሉን በሰይፍ ተቆራረጠ ይላሉ ባለቅኔው ።

26 ግዕዝ ጉባኤ ቃና

ይቤለነ ጸም ካህነ አሪት ስባሔ
ሀገረ ሰቆቃው ይእቲ ዐይነ ባሕታዊ ቴቁሔ ።

ትርጉም

የአሪት /ምስጋና ካህን/ ያም
የባህታዊ አይን/ ቴቁሄ የልቅሶ አገር ናት አለን ።

ምስጢር

ልቅሶ ተመልካች «ይቶ ሀገር የሙሾ ሀገር ናት» እንደሚል ፥ የምስጋና ተባባሪ የሆነ ያም የባህታውያን አይን እንድታነባ (እንድ ታለቅስ) አደረገ በማለት ባለቅኔው አመስጥሮዋል ።

27 ዋዜማ

ዘገብረ መድኀን (አለታ)

አብርሃም ኢረከበ
አሐተ ምስጋረ እምድረ ከነዓን ጽርሕ
ለከነዓን እንዘ ምጣኔሃ እስከ ዕፅ ነዋኅ ፤
ደብረ ሊባኖስ ባሕቱ ሕጽርተ አድማስ ኰኵሕ
ምስጋረ አእጋር ኮነት ለሐንካስ የዋህ ፤
ወምልእተ ለሕጹጽ ወርኅ ።

ትርጉም

የከነአን ልክ (መጠን)
እስከረጅሙ እንጨት ድረስ ሲሆን አብርሃም
ከከነአን አዳራሽ ምድር አንድ እርምጃን አላገኘም ።

ነገር ግን በጭንጫ አድግስ የታጠረች ደብረ ሊባኖስ
ለእግረ አንካሳ የእግሮች መራመጃ ሆነች ፣
ለጎደሉ ጨረቃም መሙያን ሆነች ።

ም ስ ጢ ር

አብርሃም በከነአን ምድር ከደጁ አጠገብ ባለች አንድ ዛፍ ስር ብቻ የተወሰነ ሲሆን ከዚች ሌላ አንድ መራመጃ ስንኳን አላገ ኘም ነበር ። ደብረ ሊባኖስ ግን ከአለት በሚወርደው ውሃ አንካ ሳዎችን አረታች ፣ እውሮችንም አበራች ፤ ለአንካሳም የእግር መራ መጃ ሆነች በማለት ደብረ ሊባኖስ ከርቷ በፈለቀው ፀበል የአን ካሶችን እግር ያረታች (ያቀናች) መሆኗን ለጎደለው ጨረቃ ምል እት (ሙላት) ሆነች በማለት ደግሞ ደብረ ሊባኖስ የጠፋውን የእ ውር አይን ማብራቷን ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

ታ ሪ ክ

አብርሃም ከወንድሙ ልጅ ከሎጥ ጋር በከነአን ምድር ሲኖር ፣ የሁለቱም መንጋዎች በጣም በዙላቸው ። የመንጋዎቻቸው መሰማ ሪያ ምድር ጠበባቸውና ተለያዩ ። አብርሃም በመምረ የአድባር ዛፍ ስር በቀትር ጊዜ ይቀመጥ ነበር ።

የደብረ ሊባኖስ አበምኔት (የገዳም አባት ፤ አስተዳዳሪ) ፃድቅ ተክለ ሃይማኖት የአንካሶችን እግሮች በአምላካዊ ተአምር አርትተ ዋል (አቅንተዋል) የእውሮችን አይናቸም አብርተዋል እየተባለ በገድላቸው ተተርኳል ።

28 መ ወድስ

ዘሙሽት (ቁስ ገበዝ፡ዘብኖና)

ግርያም ሥርጉት ፀምረ ተደንግሉ
ግርም ገዳም ገዳመ አንበሳ መፍርሀ
ግርያም በግዕት ወላዲት በግዕ ቀይሕ

ለፀሐይ ሙሳአ ዚአሁ ግርያም ጽባሕ
ተቅዋመ ዘካርያስ ግርያም
ጸወዳ ብርሃን ዘበላዕሌኪ ያበርሀ
ግርያም መሰንቆሁ ለወልደ እሴይ መሲሕ
ገነተ ኤልያስ ግርያም ዘበውስቴትኪ ፍሬ ንጽሕ
ግርያም ሐመር ሐመረ ቀዳማይ ኖኅ
ኢንብረ ሙስናኪ ልግደ እንስት ግየ አይኅ ።

ት ር ጉ ም

ግምጃ/ ድንግልናን የተሸለምሽ ግርያም
የሚያስፈራ አንበሳ ዱር የሆንሽ ግርያም/ገዳም
ቀይ በግን የወለደሽ ግርያም/በግ
የፀሀይ መውጫ የሆንሽ ግርያም/ ንጋት (ምስራቅ)
ነጭ ብርሃን በላይሽ ላይ የሚያበራ
የዘካርያስ መቅረዝ/ግርዮም
የንጉስ የእሴይ ልጅ መሰንቆ/ ግርያም
ንፅህና/ ፍሬ በውስጥሽ ያለ የኤልያስ ገነት /ግርያም
የቀደመ ናህ መርከቡ የሆንሽ መርከብ/ግርያም !
የጥፋት ውሃ/ የሴቶች ልግድ ጥፋትሽን አላደረገም (አላ ጠፋሽም ።)

ም ስ ጢ ር

ግምጃ በልዩ ልዩ ህብረ ቀለም እንደምታጌጥ ቅድስት ግር ያም ስለቅድስናዋ በልዩ ልዩ ምስጋና ትመሰገናለች ። ጫካ (ደን) የሚያስፈራ አንበሳ መዋያ እንደሆነ ሁሉ ግርያምም የአንበሳ ምሳሌ ክርስቶስ እናት ሆነች ። በጊቱ ቀይ በግን እንደምትወልድ የሴት በግ ምሳሌ የሆነች ግርያም የወንድ በግ ምሳሌ የሆነ ክርስቶስን ወለደች። ፀሀይ በንጋት እንደሚወጣ የንጋት ምሳሌ ከሆነች ግርያምም

የፀሀይ ምሳሌ የሆነ ክርስቶስ ተገኘ ። በዘካርያስ መቅረዝ መብራት ይበራ እንደነበር ፣ የመብራት ምሳሌ የሆነ ክርስቶስም የዘካርያስ መቅረዝ ምሳሌ በሆነች ማርያም ማህፀን ተፀንሶ ተወለደ ።

የሳኦልን ህመም ያስታገሰችለት የዳዊት መሰንቆ ምሳሌ የሆነች ማርያም ህይወትን አስገኘች ። በገነት ጥሩ ፍሬ እንደሚገኝ በማርያምም ንፅህና ተጠበቀ ። የጥፋት ውሃ የናህን መርከብ እንዳላጠፋት ማርያምንም የሴቶች ልማድ አላገኛትም ይላሉ ባለቅኔው ።

ታሪክ

ቅድስት ማርያም በጌዴዎን ግምጃ ትመሰላለች ። ጌዴዎንን ምድያምን ለመምታትና እስራኤልን ከምድያም እጅ ለማላቀቅ እምላክ መረጠው ፣ ስለዚህም በመልአክ ነገረው ። ጌዴዎንም ይህ ነገር በርሱ እንደሚፈፀም የሚያረጋግጥበትን ምልክት ለማግኘት ፈለገና አምላኩን ጠየቀ ። ይኸውም «ከተባዘተ የበግ ጠጉር የተሰራት ፀምር (ግምጃ) በአውድማ ላይ ልዘርጋና በመካከሏ የሰማይ ጠል ይውረ ድልኝ ፣ ዙሪያዋ ደረቅ ይሁንልኝ ፣ ሁለተኛም በዙሪያዋ ጠል ይው ረድና መሃሏ ደረቅ ይሁን» በማለት ጠይቆ አሳቡ ተፈፅሞለታል ። በዚህም ምልክት ምድያምን በአምላካዊ ሀይል እንደሚመታና እስ ራኤልን ነፃ እንደሚያወጣቸው አውቋል ።

የጌዴዎን ፀምር የቅዱስት ማርያም ምሳሌ ስትሆን ፣ ጠሉ የክ ርስቶስ ምሳሌ እንደሆነ መምህራን ይተረጉማሉ (መሳ. 5 ፣ 36—40)።

ከዚህም ሌላ ማርያም በገዳም ስትመሰል ፣ ክርስቶስ በአንበሳ ይመሰላል ። ስለዚህም እዝራ «አንበሳ ተንሥእ እምገዳሙ ውእቱኬ ዋሕድ ውእቱ ። አንበሳ ከደኑ ተነሳ እርሱም ያው አንድ ነው» ብሏል።

ነቢይ ዘካርያስ ሁለንተናዋ ወርቅ የሆነ መቅረዝን አይቷል ። የዘይት ማሰሮ በራሷ ላይ ሆኖ ሰባት መብራቶች ያበሩባት ነበር ። መቅረዟቱ የማርያም ፣ መብራቱ የወልደ ምሳሌዎች ናቸው ተብሎ ይነገራል (ዘካ.4 ፣ 1—3) ።

29 አሞር ኩልክሙ

ዘንብረ ጊዮርጊስ (መምህር)

ኢተመይጠ ቋዕ መንገለ ጻድቅ ኖኅ
እስከ ነትገ እምነ ምልአቱ ማየ ዐይን አይኅ ።

ትርጉም

የእይን ጥፋት/ ውሃ ከሙላቱ እስከጎደለ ድረስ
ቁራ ወደእውነተኛ ናህ አልተመለሰም ።

ምስጢር

የጥፋት ውሃ እስኪጎድል ድረስ ቁራ ወደ ናህ እንዳልተመለሰ የንብረ መንፈስ ቅዱስንም አይን ቁራ (አሞራ) አነቆረወ ና አፈሰሰው በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

ታሪክ

አቡነ ንብረ መንፈስ ቅዱስ (አቦ) በአምላክ ፈቃድ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው መንፈሳዊ ተግባራቸውን ያካሄዱ ፃድቅ ናቸው ። በዝቋላ ገዳም በባህሩ ውስጥ ተዘቅዝቀው ሲፀልዩ ፣ መና ፍስት ርኩሳን በልዩ ልዩ አመጣጥ እንደተፈታተኗቸው በገደላ ቸው ተፅፏል ። በጫካ ውስጥ ቆመው ሲፀልዩ አንድ ቁራ አይና ቸውን መንጥሎ ጠጣው ።

ይሁን እንጂ በፀሎት ሰአት መነቃነቅ ስለማይገባ በትእግስት ፀሎታቸውን ከጀመሩበት ቦታ መፈፀማቸው ይነገራል ። ራብና ጥም አልተቃወማቸውም ነብሮችንና አንበሶችንም አሰግደዋቸዋል ይባ ላል ። ንብረ መንፈስ ቅዱስ ገደላቸውን ፈፅመው መጋቢት 5 ቀን አርፈዋል (ገድለ ንብረ መንፈስ ቅዱስ) ።

30 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ቆመ ጴጥሮስ ቅብዐ እንስሳ ፈሪሆ ፡
እስመ ሥልስ ክሕደ እስከነ ይነቁ ዶርሆ ።

ትርጉም

የእንስሳ ቅቤ/ጴጥሮስ ፈርቶ ቆመ ፡
ዶሮ እስኪጮህ ድረስ ሶስት ጊዜ ክዷልና ።

ምስጢር

ሀዋርያው ጴጥሮስ ዶሮ ሳይጮህ ሶስት ጊዜ እንደ ካደ የላሞች ቅቤም የፋሲካ ዶሮ እስከሚታረድ ድረስ በሶስቱ የምግብ ሰአቶች (በቁርስ ፡ በምሳና በራት) ከወጥ ገብቶ አልቀረበም ። ዳግ መኖም ባለቅኔው ስልስ በሚባለው ወጥ ቅቤ አለመጨመሩን ያመ ለክታሉ ።

ታሪክ

ሀዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስን ኢየሱስ ክርስቶስ «ዶሮ ከመጮሁ በፊት ሶስት ጊዜ ትክደኛለህ» ባለው መሰረት ክርስቶስ ሀሙስ ማታ ለአርብ አጥቢያ ተይዞ ሳለ አይሁድ ቢጠይቁት «አላወቀ ውም» እያለ ሶስት ጊዜ ክዷል ።

31 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ተክለ ሃይማኖት ይትፈሣሕ በተጠብሖ ቶማስ ዶርሆ ፤
ጎጺር እግር እስመ ለተክለአብ በጽሖ ።

ትርጉም

ተክለ ሃይማኖት በቶማስ/ ዶሮ መታረድ ደስ ይሰኛል ፤
አጭር እግር ለተክለ ሃይማኖት ደርሶታልና ።

ምስጢር

በተሰራ ዶሮ ወጥ አጭር እግር (የዶሮ ጭን) የደረሰው ልጅ ደስ እንደሚለው ተክለ ሃይማኖትም የፀሎት ቁመትን ከማብዛት የተነሳ አንድ እግራቸው በመሰበሩ እግሩ የተቆረጠ ቶማስን መሰሉ ማለት ነው ።

ታሪክ

አቡነ ተክለ ሃይማኖት በደብረ ሊባኖስ ዋሻ ቆመው ሲፀልዩ ለፀሎት ከመቆም ብዛት የተነሳ አንድ እግራቸው እንደ እንጨት ተሰብሯል የሚል በገድላቸው ተፅፏል ። ስለዚህ ባለቅኔው «ጎጺር እግር በጽሖ » ብለዋል ።

32 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ባሕታዊ ተመይጠ ጎበ ተአምኖ ጸበለ ፤
እስመ እምደዌሁ ኢድኀነ ለእመ አብዝኀ ቈጽለ ።

ትርጉም

ባህታዊ ጠበልን ወደመታመን ተመለሰ ፤
ቅጠልን ቢያበዛ ከደዌው አልዳነምና ።

ም ስ ጢ ር

በሽተኛ ሰው የቅጠላ ቅጠል መድሀኒት ሲያደርግ ቆይቶ የሚድን መሆኑን ሲረዳ ጠበል ወደመጠመቅ እንደሚመለስ ፣ ባህ ታዊም በያምና በፀሎት ወራት ቅጠል እየበላ በእንባ እየታጠበ ሰገደ ይላሉ ባለቅኔው ።

33 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘተክሉ (መምህር ፣ ዘየሸራ)

ደመና ቢታቦር ለእመ አዝነመ ቃለ
ሙሴ እምድር እንበለ ጊዜሁ በቁለ ።

ት ር ጉ ም

ደመና በደብረ ታቦር ቃልን ቢያዘንብ
ሙሴ ከምድር ያለ ጊዜው በቀለ ።

ም ስ ጢ ር

ደመና በምድር ላይ ዝናብ ሲያዘንብ ያለወቅቱ የሚበቅል ቡቃያ አለ ፤ እንዲሁም ደመና በደብረ ታቦር «ይህ የባህርይ ልጄ ነው» የሚል የአብ ቃልን ቢያሰማ ሙቶ ከተቀበረ ብዙ ዘመን የሆነው ሙሴ በአካለ ነፍስ ወደ ደብረ ታቦር መጣ ይሉኑ ባለ ቅኔው ።

34 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘተክሉ (መምህር ፣ ዘየሸራ)

ካህን ገብርኤል ይመስለነ ቀሊለ ፤
ሳዕሌሃ ለያፍ አምጣነ አጎደረ ቃለ ።

ት ር ጉ ም

ካህን/ገብርኤል ቀላል ይመስለናል ፣
ቃልን በወፍ ላይ አሳድሯልና ።

ም ስ ጢ ር

እንዳንዱ ቄስ አለአግባብ ሲገዝት «ቀላል ወፈ ገዝት» ይባላል ። በዚህም አንባር ቃል የተባለ እግዚአብሄር ወልድ የወፍ ምሳሌ በሆነች ቅድስት ማርያም ማህፀን እንዲፀነስ ቅዱስ ገብርኤል አበሰራት ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

35 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ዘአበባ (አለቃ ፣ ዘሐመረ ኖኅ ጎንደር)

እኮ ፍጡን ጊዮርጊስ እንተ ይጽሕፍ ወንጌለ ፤
በዋሕድ ዐምድ እስመ ውእቱ ወዐለ ።

ት ር ጉ ም

ወንጌልን የሚፅፍ ጊዮርጊስ ፈጣን አይደለም ፤
እርሱ በአንድ አምድ ውሏልና ።

ም ስ ጢ ር

በአንድ አምድ ብቻ የሚውል ቁም ፀሀፊ አያረጥንም ጻተኛ ነው እንደሚባል ቅዱስ ጊዮርጊስም በአምደ መበለት(በመበለቷ ቤት ምሰሶ) ታሰረ ። አምድ የተሰኘው ሀብር ቃል ሰምና ወርቁን አስተባብሯል ።

ትዱስ ጊዮርጊስ የታሰረበት ያንዲት መበለት ቤት ምሰሶ በእምላካዊ ተአምራት ለምልሟል ይባላል (ገድለ ጊዮርጊስ) ።

36 ዋዜማ

አንስት ወላድያት
ለእመ ሐማ ይለዳ ዘይንእሶን እካለ
እምልማድ ዝንቱ ይደክማ ጎይለ ፤
መርፍኤሰ ወላድ ዘየዐብያ ገመለ
እንዘ ለሊሃ ትወልድ ኢያስምዐት ቃለ
ወመሰላ ዘትወልድ ፈትለ ።

ት ር ጉ ም

ወላጆች ሴቶች
የሚያንሳቸው አካልን ይወልዱ ዘንድ ቢታመሙ
ከዚህ ልማድ የተነሳ በሀይል ይደክማሉ ፤
ወላድ/መርፌ ግን የሚበልጣት ገመልን
እርሷ ስትወልድ ቃልን አላሰማችም ፤
ፈትልን የምትወልድም መሰላት ።

ም ስ ጢ ር

ወላጆች ሴቶች ልጅ ሲወልዱ ይደክማቸዋል ፤ የሀዋርያ ታዴ ዎስ መርፌ ግን እርሷ ትንሽ ስትሆን ታላቁን ግመል እንደከር በተ እምር እሾለከችው ይላሉ ባለትኔው ።

ኢየሱስ የባለፀጎችን ለማንዘብ መስገብገብ ሲያስረዳ ፣ «ባለፀጋ ወደ መንግስት ሰማይ ይገባል ከማለት ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ይሾልካል ማለት ይቀላል» ብሏል ። ይህንም ሀዋርያው ታዴ ዎስ በተግባር አሳይቷል ተብሎ ይተረካል (ማቴ. 19 ፣ 16—25 ። ስንክ. ሆሎ 2) ።

37 ዋዜማ

ዘስሙኒ (መሪጌታ)

ስምዖን አረጋዊ
እምነ ኩሉን አንስት መርዓት ዚአሁ አልዐለ ፤
ውእቱ እስመ እንበሌሃ ኢይጥዕም እክለ ፣
ውኀበ አፍአ ኢትሃእ በጽርሐ ሥጋሁ መሐለ ፣
በጸውዖ ስማ ለእም ነሢአ መስቀለ
ምስለ ዛቲ እስመ ቦአ ቃለ ።

ት ር ጉ ም

ሽማግሌ / ስምኦን
ከሴቶች ሁሉ የርሱ ሙሽራን ከፍ አደረገ (አበለጠ) ፤
እርሱ ያለርሷ እህልን አይቀምስምና ፣
ወደውጭም እንዳትወጣ በአዳራሽ ሲጋው ማለ ፤
መስቀልን ይዞ የእናት ማርያምን ስም በጮኸራት
ከርሷ ጋር ቃልን ገብቷልና ።

ም ስ ጢ ር

አንዳንድ ወንድ ጊስቱን ከመውደዱ የተነሳ ከሌሎች ሴቶች ያበልጣታል ፣ ያለርሷም ብቻውን እህል አይቀምስም ፣ ወደውጭ

እንዳትወጣ መስቀል ጨብጠ በማርያም ይምላል ። ይህንም ማድረጉ የገቡት ቃል ኪዳን በመሃላ የሚፀና ስለሚመስለው ነው ።

በአንፃሩም ስምአን በላሌ ሰብአ እህልን ትቶ ሌሎቹን ሰዎችና ሚስቱን በላ በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመሰጥረዋል ።

38 ሥላሴ

ዘበዓብይ ወንድም (አለቃ)

ጐየ ሐራውያ
በጸዳለ ዕንቊ እምአርአያሁ ፣
በጸዳለ ዕንቊ ደንግል ባሕቱ ሶበ ነጸረት አምሳለ
ተለወት አርአያ ዚአሃ አማነ ድንግለ ።
ምኒልክኒ አውልዕ ድኅረ ተጥዘመ በቁለ
ላዕለ ዕፀ ሕይወት ኀበ ተተክለ ፤
አስመ በላዕለ ሥን ሥነ በዘአሕመልመለ
ተገዚሞ ፈረየ አስካለ ።

ት ር ጉ ም

እሪያ በእንቁ
ብርሃን ከአምሳያው ሸሸ ፤
ነገር ግን ድንግል በእንቁ ብርሃን እምሳያን ባዮች ጊዜ
እውነተኛ ድንግል አርአያን ተከተለች ።
በህይወት / እንጨትም ላይ ከተተከለ ዘንድ
ወይራ / ምኒልክ ከተቆረጠ በሁዋላ በቀለ ፤
በወጡት ላይ ውበትን ከአለመለመ ዘንድ
ተቆርጦ ፍሬን አፍርቷልና ።

ም ስ ጢ ር

እሪያ (ከርከሮ ፣ አሳማ) በጨለማ ሲሄድ የእንቁ ብርሃን የገዛ መልኩን ያሳየዋል ፣ ስለዚህ እርሱ ምን መጣብኝ ብሎ ከገዛ መልኩ ይሸሻል ። ቅድስት ማርያም ግን የእንቁ ምሳሌ በሆነ በእግዚአብሄር መንፈስ የተመሰለላትን ምሳሌና የተተነበየላትን ድንግልና በተግባር አፀደቀች ። ደግሞም ወይራ ከተቆረጠ በሁዋላ ከዘይት ጋር ሲዋሃድ እንደሚበቅልና ፍሬን እንደሚያፈራ ፣ እዜ ምኒልክም ከሞቱ በሁዋላ በጥምቀት ስያሜ (ከርስትና ሲነሱ) አስካለ ማርያም የተባሉት ልጃችውን ንግስት ዘውዲቱን በመንግስታቸው ተኩ ።

ወይራም በቅጠል ላይ ቅጠልን እንደሚያለመልም የእዜ ምኒልክ ወራሾች ልጅ ኢያሱና ንግስት ዘውዲቱ በተራ ገዙ በማለት ባለቅኔው ስለእዜ ምኒልክ ዘር መባረክ ያላቸውን አመለካከት በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

ታ ሪ ክ

የቀን ዋእየ ፀሀይ (የፀሀይ ቃጠሎ) በሚፀናበት አገር የሚኖሩ ሰዎች በቀን አይሰሩም ። ሌሊት በእንቁ ብርሃን እያዩ ይሰራሉ ። እንቁ በሌሊቱ ለአት በከፍተኛ ቦታ ላይ ተደርጎ ያበራል ። በዚህ ጊዜ መልከ ክፉ የሆነ እሪያ የገዛ መልኩን አይቶ ሌላ አውሬ የመጣበት መስሎት ከራሱ አርአያ ይሸሻል ። ቅድስት ማርያም የእግዚአብሄር አብን ቃል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና እንደምት ወልደው ፣ በብዙ ህብረ አምሳልና በብዙ ህብረ ትንቢት በነቢያት እንደተነገረላት ለዚሁ ብቁ ሆና ተገኝታለች ይባላል ።

የውጭ ሰዎች ወይራውን ቆርጠው በዘይት እንጨት ፍልፍል ው ስጥ ከዘይቱ ጋር አጣብቀው ያዳቅሉታል ። ስለዚህ ዘይቱ የወይራውን ጥናት ሲወርስ ወይራው የዘይቱን ጣእም ይወርሳል እየተባለ ይተረከል ።

እዜ ምኒልክ ንግስት ዘውዲቱን ወልደው አሳድገውና ድረው ከሞቱ በሁዋላ ንግስት ዘውዲቱ በኢትዮጵያ መንበረ መንግስት

ተተክተዋል። ታእካ ነገስት የተባለችውን የበኢታ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን በአባታቸው ቤተ መንግስት አጠገብ አሰርተው የአባ ታቸውን አስከሬን (አፅም) በዚያው በክብር አሳርፈዋል ። እርሳ ቸውም ሲሞቱ አስከሬናቸው በዚያው አርፏል ።

39 ሥላሴ

ታሰምዕ ለእዝነ ኵሉ
ፅንስት ያፍ ድምፀ አእባን ፤
እስከነ ሕግማ ትረስዕ እምከርሣ ጊዜ ወሊዶታ ዕጓለ
ከመትርከብ በሰሚዐ ዝንቱ ዕረፍተ ወሣህለ ።
ርግብ ነጋሢ ሰሎሞን ባሕቱ በዘተረኮቦታ ድንግለ
እከምርሣ ሕግም እስመ ሰሰለ ፡
ጊዜ ወሊዶታ እምከርሥ ሕፃና ልዑለ
ለጸታሃ ኢያስምዐት ቃለ ።

ት ር ጉ ም

የፀነሰች ወፍ የድንጋዮች
ድምፅን ለሁሉ ጆሮ ታሰማለች ፤
ከሆዲ ልጅን በመውለዲ ጊዜ ህመሟን እስከትረሳ ድረስ
ይህን በመስማት እረፍትንና ይቅርታን (ሰላምን) ታገኝ
ዘንድ ።
ነገር ግን የነጋሽ ሰሎሞን ርግብ ድንግልን ሆና በመገኘቷ
ምጥ ከሆዲ ተወግዲልና ፡
ከፍተኛ (የከበረ) ልጅዋን በመውለጃዋ ጊዜ
ለወገናችዋ ቃልን አላሰማችም ።

ም ስ ጢ ር

እንደ ግንደ ቆርቁር ያለች አንድ ወፍ አለች ፤ ይህች ወፍ ፀንሳ በምትወልድበት ጊዜ የድንጋይ ድምፅ ስታሰማና ስትሰማ ህመሟ

(ምጥ) ይቀልላታል ይባላል ። ርግብ የተባለችው ቅድስት ማር ያም በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ልጅዋ ክርስቶስን ስትወልድ እን ደሌሎቹ ወላድ ሴቶች ምጥ የሌለባትና የምጥ ቃልን ያለሰማች ተባት የሌላት ርግብ ሆነች ይላሉ ባለትኔው ።

ታ ሪ ክ

አንዲት አፈ ያሬድ የምትባልና ሶስት አይነት ድምፅ የም ታሰማ ወፍ አለች ፤ በምጥ ጊዜ ኪል እንደምትል ስለ ድንጋይ ያለ ድምፅን ለሌሎቹ ሁሉ ታሰማለች ። በዚህ ጊዜ ምጥ ይቀልላትና በቶሎ ትወልዳለች ። ሌሎቹም በድምፁዋ ቶሎ ይወልዳሉ ይባላል ።

40 ሥላሴ

ዘአብርሃ (አፈ ንዑረ እድ ፡ ዘአክሱም)

ኢይባእ ቤተ መቅደስ
ተከልአ ዕፅ በአበሳሁ ፤
አምጣነ በዕፅ አዳም መዋቲ እመንበረ ክብሩ ሰሰለ
ወሕያው አምላከ አዳም ዲበ ዕፅ ተሰቅለ ።
ወኢይምሰሎ ለእብን ገፋሂ ከበደ ጌጋዩ ቀሊለ
ውስተ ቤተ መቅደስ እመ ተልዕለ ፤
አምጣነ የዋህ አቤል በእብን ተቀትለ
ወበእብን ኤርምያስ ተሠጥለ ።

ት ር ጉ ም

ቤተ መቅደስ እንዳይገባ
እንጨት በበደሉ ተከለከለ ፤
ሟች አዳም በእንጨት ከክብር ወንበሩ ተወግዲልና
ህያው የአዳም አምላክም በእንጨት ተሰቅሏልና ።

በቤተ መቅደስም ከፍ ቢል ለገፈ ድንጋይ
የበደሉ ክብደት ቀላል አይምስለው ፤
ተሳላ (ገር) አቤል በድንጋይ ተገድሏልና
ኤርምያስም በድንጋይ ጠፍቷልና ።

ም ስ ጢ ር

ነውረኛ የሆነ ካህን ቤተ መቅደስ እንዳይገባ ይከለክላል ፤ እን ዲሁም የቅድስት ማርያም ቤተ መቅደስ ያለ እንጨት በድንጋይ ብቻ ተሰራ። አዳም በበለስ እንጨት ምክንያት በመጎዳቱና ከርስቶስም በእንጨት ላይ በመሰቀሉ እንጨት ለቤተ መቅደስ ስራ አልዋለም ።

«ሌላው ካህንም በቤተ መቅደስ ከፍ ቢል ደህና የሆንሁ አይ ምስለው ። በሱ ምክንያት ንፁህ ሰው ተገድሏል ፤ የዋሁ ሰው ጠፍቷል» እንደሚባል ፤ ድንጋይ ደግሞ ያለ እንጨት ብቻውን ቤተ መቅደስ ሆኖ ስለተሰራ አቤልና ኤርምያስ በዚሁ በድንጋይ በመገ ደላቸው እንደ እንጨት መወገድ ነበረበት በማለት ባለቅኔው ፍርድ ነክ አስተያየታቸውን በምስጢር ሰንዝረዋል ።

ታ ሪ ክ

ንጉስ ላሊበላ በላስታ ያሳነፀው ቤተ መቅደስ እንደሌሎቹ ቤተ መቅደሶች በድንጋይና በጭቃ የተገነባና የእንጨት ጣሪያ ያለው ሳይሆን ፤ ገሃው መሬት እየተፈለፈለና ውስጡ እየተከፈለ የተሰራ አስደናቂ ስራ ነው ።

ነቢዩ ኤርምያስ ልዩ ልዩ መከራን ከመቀበሉም በላይ በድ ንጋይም ተወግሯል (ኤርም. 20 ፥ 2) ።

41 መወድስ

ዘጀንበረ (መረጌታ)

ኢይተርፍ ሰብእ በከመ ጌገየ
ዳዕሙ ይጸውር ጌጋየ ርእሱ መስቀለ ፤

ፍዳ በጽምዐ ግይ ወልድ ጸላኢተ ነቢይ አህጉለ
አምጣነ አስምዐ ጊዜ ሞቱ
ጎበ ደቂቆሙ ጸግዕኩ ብሂለ ፤
ወበግየ አይጎ አዝግደ ኖኅ
ፍዳ ዘቀተለ ወልድ በምክንያተ ግይ ተቀትለ ።
ለአዳምኒ አመ አግጎሥ ከመ ኢይብላዕ እስካለ
ፍሬ ዕፀ በለስ ኢረከበ እስከነ ረገመ ሐመልግለ ፤
እመኒ አሥዋከ በከርሠ አዳም አብቈለ
በጌጋየ አዳም ልሳነ ሥክ ላዕለ ርእሰ ወልድ ተለዐለ ።

ት ር ጉ ም

ሰው እንደበደለ አይቀርም
የራሱ በደል/ መስቀልን ይሸከማል እንጂ ፤
ወልድ የነቢይ ኤልያስ ጠላቶችን በውሃ ጥም ስላጠፋ ብድራት
በሞቱ ጊዜ ተጠማሁ ግለትን
ወደልጆቻቸው አሰምቷልና ፤
የናህ ዘመዶችንም በጥፋት ውሃ
ስለገደለ ብድራት (ፈንታ) ወልድ በውሃ ምክንያት ተገድ ሏልና ።
አዳምንም ፍሬን እንዳይበላ ቢያስወግደው
ልምላሜን እስከ ረገመ ድረስ የበለስ እንጨት ፍሬን አላ ገኘምና ፤
እሾሆችንም በአዳም ሆድ ባበቀለ ጊዜ
በአዳም በደል የእሾህ ጫፍ በወልድ ራስ ላይ ወጥቷልና ።

ም ስ ጢ ር

«ብድር ውሉ አያድር» እንዲሉ በነቢዩ ኤልያስ ቃል የእስራ ኤል ወገኖችን በውሃ ጥም እንዲያልቁ በማድረጉ ፤ በእግዚአብሄር ወልድ በውሃ ተጠምቶ መሞት መጣበት ። ሰብአ ትካትንም በጥ

ፋት ውሃ በመግደሉ ፥ መጣጣና አሞትን ጠጥቶ ከመሞት ደረሰ ። አዳምንም «እሾህ ይብቀልብህ» ብሎ በመርገሙ ፥ አይሁድ በራሱ ላይ የሾህ አክሊልን ደፉበት በማለት ባለቅኔው ሰው የእጁን የማ ያጣ መሆኑን አስረድተዋል ።

ታ ሪ ክ

አክአብ የእስራኤል ንጉስ ከነሚስቱ ጣኦትን እያመለከ የግፍ ግፍ ሰራ ፤ ነቢዩ ኤልያስ ቢመክረውና ቢያስተምረው ከክፉ ስራው አልመለስም አለ ። ነቢዩ ኤልያስ « ይህ ሁሉ መሆኑ ጥጋብ ቢበዛ አይደለምን ? » ብሎ ሰማይ ዝናብ ለዘር ፥ ጠል ለመከር እንዳይ ሰጥ እንዲያደርግለት አምላክን ለመነ ፤ እንዳለውም አደረገለት ። ሶስት አመት ከስድስት ወር ድርቅ ሆነ ። ሰውም ከብትም በውሃ ጥም አለቀ ። ንጉሱ አክአብም ከአብድዩ ጋር ለበቅሎቹ ሳር ፍለጋ ወንዝ ለወንዝ እሽኪንከራተት ድረስ ተቀጣ ። ኤልያስ ግን በአምላኩ ትእዛዝ ሁለት ቁራዎች በጧትና በማታ የሚያመላልሱለትን ስጋ እየበላና እንደወተትና ማር የሆነችለትን ምንጭ እየጠጣ ምህረት የማ ይለምን ቢሆን አምላክ ምግቡን አስቀረበት ። ከዚህ በሁዋላ ዝናብ እንዲዘንብ ለመነና ዝናብ ዘነበ ፥ ዘሩም በቀለ ፥ ቡቃያው በፍጥነት አድጎ አፈራ ፥ ፍርቱ ተትረፈረፈ ፥ ጥጋብ ሆነ ይባላል (1 ነገስ.17 ፥ 2—7 ፤ 18 ፥ 1—46) ።

42 መወድስ

ደመ ዘካርያስ ዘንመ ውስተ ቢታንያ
ሆሳዕና ዓለም ይዝራዕ መልዕልተ አእባን ቃለ ፥
እመኒ ለቃል እንተ በደመ ዝ በቁለ
እድግተ በለዓም ትበልዖ ፥
ወበለዓም አመ ሆሳዕና ኢኮነ ቀሊለ ፤
ተረፈ እድግቱ ለበለዓም
እስመ ዕጓለ ሰብእ በልዐ ፥ ወኢተሰምየ ዕዋለ ።

ተወለጠሂ በሆሳእና ምግባረ ሙሴ ዘብዕለ ፤
እስመ እምአእባን ሆሳዕና ጥበበ አፈልፈለ ፥
ወእንዘ ይሰቂ ዘንተ መስቀለ ይሁዳ አጥለለ ፤
እስመ ንባበ እብን አዘከሮ ፍቅረ ወበቀለ ።

ት ር ጉ ም

የአለም ሆሳእና በድንጋዮች ላይ ቃልን
ይዘራ ዘንድ የዘካርያስ ደም በቢታንያ ውስጥ ዘነበ፥
ምንም በዚህ ደም የበቀለ ቃልን
የበለአም አህያ ብትበላው ፥
በለአምም በሆሳእና ጊዜ ቀላልን አልሆነም ፤
የበለአም የአህያውን ትራፊ
የሰው ልጅ በልቷልና ፥ ውርንጫም አልተባለምና ።
የበለፀገ የሙሴ ስራም በሆሳእና ተለወጠ ፤
ሆሳእና ከድንጋዮች ጥበብን አፍልቋልና ፥
ይህንም ሲጠጣ የይሁዳ መስቀልን አለመለመ ፤
የድንጋይ ነገር በቀልንና ፍቅርን አሳስቦታልና (አስታ ውሶታልና) ።

ም ስ ጢ ር

ዝናብ ሲዘንብ ገበሬ ዘሩን ይዘራል ፤ እንዲሁም እንደዝናቡ የዘካርያስ ደም ሲፈስ ፥ ሆሳእናም እንደገበሬው ዘር ድንጋዮችን ቃል አናገረ ። የበቀለውን የገበሬ አህልንም አህያ እንደሚበላው የበለአም አህያም እንደሆሳእና ድንጋዮች ቃልን ተናግራ ነበር ። ህፃናትም የአህያ ትራፊ የሆነ የሆሳእናን ምስጋና አመሰገኑ ። ከድ ንጋይም ስር ውሃ እንደሚመነጭ የሆሳእና ምስጋና በድንጋዮች ተነገረ ፤ ውሃውም እንጨትን እንደሚያለመልመው ሁሉ ፥ ይሁዳ ሆሳእናን በማመስገን ፈንታ በመስቀል በቀልን ተበቀለው በማለት ባለቅኔው ትኔያቸውን አመስጥረዋል ።

ሆሳእና የተባለ ከርስቶስ ነው ። አህያዋንና ውርንጫዋን በግ
ፈራረት ጋልቦ ከቢታንያ ኢየሩሳሌም ሲገባ ብዙዎች ህዝቦች
ተቀበሉት ። ህፃናትና ሽማግሌዎች «በእርያም (ሰማይ) ያለህ መድ
ሀኒት» እያሉ አመሰገኑት ። አይሁድ በቅናታቸው እንዳያመሰግኑት
ህፃናትንና ሽማግሌዎችን ቢከለክሏቸው ድንጋዮች እንደሰው በመ
ጮህ አምላክነቱን መሰከሩለት ። አይሁድ ግን በዚህ ቀንተው በመ
ስቀል ላይ ሰቀሉት (ማቴ. 25 ፣ 9—17 ፣ 27 ፣ 1—66) ።

ዘካርያስ ከነቢያት አንዱ ነው ። የእግዚአብሄርን ነገር ሲሰ
ብክ ፣ በቤተ መቅደስ መካከል ተገድሉ ደሙ በግፍ ፈሷል (ማቴ.
23 ፣ 29—39) ።

እስራኤል ከግብፅ ሲወጡ የሶርር ልጅ ባላት ብዛታቸውን
አውቆ በእገሩ እንዳይሄዱበት በተራጋሚ ሰው አስረግሞ ሊያጠፋ
ቸው ወደደ ፣ ስለዚህ የመርገም ስጦታ ያለውን በለአም የተባለውን
ሰው « ናና ረግመህ አጥፋልኝ» አለው ። እርሱም ከቤቱ ተነስቶ
በአህያው ላይ ሆኖ ሲሄድ ግሩም የሆነ (የሚያስፈራ) መልአክ ታያ
ትና ፈራችው ። ወደሁዋላ እያፈገፈገች ወደፊት አልሄድ አለች ።
በዚህ ጊዜ በለአም ተናዶ ቢመታት «ከእንተ የበለጠ ግሩም መል
አክ ቢታየኝ ነው ፣ ምን ትለኛለህ ? » በማለት በሰብአዊ ቃል ተና
ገረችው ይባላል (ኢያ. 13 ፣ 22 ። ዘሁል. 22—24) ።

ሙሴ እስራኤልን እየመራ በሲና በረሃ ሲጓዝ ህዝቡ በውሃ
ጥም ስለተጨነቁ ፣ ወደአምላኩ ፀልዮ ውሃ ከድንጋይ አፍልቆ እጠ
ጥቷቸዋል ይባላል ።

43 አጭር ኩልክሙ

ግርያም ከርካፅ እንተ አሕመልመለት ቈጽለ
ጸገየት ድንጋሌ ወፈረየት ቃለ ።

ቅጠልን ያለመለመች ግርያም/ሎሚ
ድንግልናን አበበች ፣ ቃልንም አፈራች ።

ምስጢር

የለመለመች የሎሚ እንጨት ፍሬን እንደምታፈራ ከሴቶ
ች መካከል የተመረጠች ቅድስት ግርያም ቃል የተባለ ኢየሱ
ስን በድንግልና ፀንሳ ወለደች በማለት ባለቅኔው እምነታቸውን በቅኔ
ያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

44 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ካህነ ደብረ ዘይት እብን ለባዌ መጽሐፍ ኵሉ ፣
እኵኑ ጸሐፈ ቅዳሴ እግዚእ በቃሉ ።

ትርጉም

የደብረ ዘይት ካህን/ድንጋይ መፅሀፍን ሁሉ አስተዋይ ነው ፣
የጌታን ቅዳሴ በቃሉ ፅፏልና ።

ምስጢር

ቅዳሴውን በቃሉ አጥንቶ የሚፅፍ ካህን (ቁም ፀሀፊ) አስተ
ዋይ ይባላል ፣ እንዲሁም ባለቅኔው የደብረ ዘይት ድንጋይ ከርስቶስን
አመሰገነ ፣ እንደ ሰው ሆነ ይላሉ ።

45 ዕዝል ጉባኤ ቃና

መርዓተ ፃግ ታፈቅር ዘምስለ ስምዖን ተሀሉ ፣
እስመ ስምዖን አብ ፈጸሜ ግብረ ሰብእ ኵሉ ።

ት ር ጉ ም

የድካም ሙሽራ ከስምአን ጋር ትኖር ዘንድ ታረቅራለች ፤
አባት ስምአን የሰውን ሰራ ሁሉ ፈፃሚ ነውና ።

ም ስ ጢ ር

ባል ፈቃድ ፈፃሚ ሲሆን ሚስት ልትለየው እንደማትሻ ሁሉ
የበላኤ ሰብ ሚስትም ባሏ ሌሎቹን ሰዎች በበላ ጊዜ አልተለየች
ውም እርሷም ተበላች ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

46 ዕዝል ጉባኤ ቃና

መደልው ትብዕ ለገጸ ባዕል ያደሉ
ከርሠ ባሕታዊ አልዓዛር ዕራቆ እንዘ በዲዲሁ ይሄሉ ።

ት ር ጉ ም

የባህታዊ ሆድ/አልአዛር ራቁቱን በደጃፉ እያለ
የሚያዳላ/ቅቤ ለሀብታም ሬት ያደላል ።

ም ስ ጢ ር

ግብዝ ዳኛ ከድሀው ይልቅ ለባለፀጋው ፍርድ እንደሚያደላ
ባለፀጋ የበላው ቅቤም ራቁን ማውዛቱን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

ታ ሪ ክ

ባህታዊ ከትውልድ አገሩና ከወገኑ ተለይቶ ፈጣሪውን በያምና
በፀሎት እያገለገለ ድምፀ አራዊትንና ግርማ ሌሊትን ታግሶ በበረሃ
የሚኖር መናኝ ነው (ሉቃ. 16 ፡ 18—41) ።

አልአዛር የተባለ በሽተኛ ሰው ነዌ በሚባል ባለፀጋ ሰው በር
ወድቆ ይኖር ነበር ። ነዌም በግብዝነቱ ንፋግ ስለነበር ምንም ሳይዘ
ከረው ኖረ ። መቼም ለክፋውም ፡ ለበጎውም ሞት አይቀርምና
ሁለቱም ሲሞቱ አልአዛር በነዌ አስፈረደበት ይባላል (ሉቃ.16 ፡
19—31) ።

47 ዘአምላኪየ

ሕፃን ማርያም ኢትበል በጎለ እንስሳ እሄሉ ፤
ድኅረ ቦአ ቤቶ ወአተወ ኵሉ
ይቀትሉከ ፈያት አኮኑ እንዘ ለጸርትከ ይብሉ ።

ት ር ጉ ም

የማርያም ህፃን በእንስሳት በረት እኖራለሁ አትበል ፤
(ሰው) ሁሉ ፈፅሞ ወደቤቱ ከገባ በሁዋላ
ሽፍቶች ለልብስህ ሲሉ ይገድሉሃልና ።

ም ስ ጢ ር

ሰው ሁሉ ወደቤቱ ከገባ በሁዋላ በከብት መዋያ (መሰማሪያ)
ብቻውን የተገኘውን ሰው ሽፍቶች ለልብሱ ሲሉ ይደበድቡታል ።
በዚህ እንዳር የቅድስት ማርያም ልጅም በከብቶች በረት መወለዱ
ንና በጨርቅ መጠቅለሉን ከብት ጠባቂዎችም ያመሰገኑት መሆኑን
ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

48 ሥላሴ

ዘወልደ ማርያም ጉታ (መምህር)

በባቢሎን አመ ተሠርዐ
መሥዋዕተ ገሞራ ነደ እሳት

እሳታውያን ደቂቅ ለኪፎተ ዝንቱ ኢክህሉ ፤
እሳት አምጣነ በላዒ ወመፍርህ ለኵሉ ።
ላእካነ ባቢሎን ሕዝብ ባሕቱ አመ በእከይ ወዐሉ
መቅሠፍቶሙ በልዑ ወተካፈሉ ፤
ላእከ ቤተ መቅደስ ገብርኤል ጊዜ በዓሉ
እስመ ሠርዐ እሳተ ለዝኩ ።

ት ር ጉ ም

የገሞራ መስዋእት / የእሳት ነዲድ
በባቢሎን በተሰራ ጊዜ
እሳተኞች (እሳት የሆኑ) ልጆች ይህን መንካት አልቻሉም፤
እሳት በላተኛና ለሁሉም አስፈሪ ነውና ።
ነገር ግን የባቢሎን መልእክተኞች ህዝቦች በከፋት
በዋሉ ጊዜ
መቅሰፍታቸውን ተካፍለው በሉ ፤
የቤተ መቅደስ መላክተኛ/ ገብርኤል በበአሉ ጊዜ
(ግእድ) እሳትን ለሁሉ ሰርቷልና ።

ም ስ ጢ ር

መስዋእት በሚሰራበት ጊዜ የማይገባቸው ወገኖች (መስዋእ ቱን ለመብላት ብቁ ያልሆኑ) እንደማይነኩት ፥ በባቢሎን ሶስቱ ልጆች (አናንያ ፥ አዛርያ ፥ ሚሳኤል) እሳቱ በሚነድበት ጉድጓድ ሲጣሉ በእሳቱ እንዳልተቃጠሉ ቅኔው ያስረዳል ። የሚገባቸው ወገ ኖች (መስዋእቱን ለመብላት ብቁ የሆኑ ካህናት) መስዋእቱን እን ደሚበሉ ፥ የባቢሎን ሰዎችም ራሳቸው ባነደዱት እሳት ተቃጠሉ፤ መስዋእቱን የቤተ መቅደስ አገልጋይ እንደሚሰራውም ቅዱስ ገብር ኤል እሳቱን ለሰለስቱ ደቂቅ ማብረዱን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ።

49 ሥላሴ

አልዓዛር ምሥጢረ ቅኔ
ግዱፈ ኮነ አምሳለ በድን
በእንቀጸ ነዌ ባዕል ጎጢአ ዘያሐይዎ በቃሉ ፤
ለውእቱ አምጣነ ጎለፈ ጊዜሁ ወብዕሉ ።
ባሕቱ ልብነ ማርታ እንተ ትሰርሕ ለዝኩ
በአስቆቅዎ እመ ትሄሉ ፥
ለቅኔ አልዓዛር እግዚአ ላዕሉ
እምአንሥአ ዳግመ በጎይሉ ።

ት ር ጉ ም

የቅኔ ምስጢር / አልአዛር
በቃሉ የሚያድነው አጥቶ
በባለፀጋ / ነዌ ደጃፍ (በር) እንደ በድን ወደቀ ፤
የርሱ ጊዜውም ፥ ብልፅግናውም አልቆልና ።
ነገር ግን ለሁሉ የምትደክም ማርታ/ ልባችን
በማልቀስ ብትኖር ፥
የላይኛው ጌታ አልአዛር / ቅኔን
በሀይሉ ዳግመኛ ባነሳው ነበር ።

ም ስ ጢ ር

አልአዛር የተባለው በሽተኛ በባለፀጋው ነዌ ደጅ አስተዋሽ አጥቶ ወድቆ ይኖር ነበር ። እንደዚሁም ሁሉ አንድ ባለቅኔ ለጎንደሩ አለቃ እንግዳ ወርቅ ሀይሉ ያበረከቷቸው ቅኔ ሳያሸልማቸው ቀር ቷል ። ዳግመኛም የሌላው አልአዛር እህት የሆነችው ማርታ በወ ንድሟ ሞት ስላዘነች ክርስቶስ ወንድሟን እንዳነሳላት ፥ እንዲሁም ባለቅኔዎች ቢያዝኑ የወደቀውን የግእዝ ቅኔ በአለቃ እንግዳወርቅ

ሀይሉ እንዲወደድና ዋጋ እንዲያሰጥ ማድረግ የአምላክ ፈቃድ ይሆን ነበር በማለት ባለቅኔው በጊዜው የቅኔ ሙያ ዋጋ የሚያገኝ በትን መንገድ በቅኔያቸው ምስጢር ቀይሰዋል ።

ታሪክ

ማርታ በክርስቶስ ግህበር ውስጥ ትረዳ የነበረች ሴት ናት ። «እህቴ ማርያምን እርጃት አትላትምን ? እኔ ለብቻዬ ይህን ያህል ስደክም » ብላ ለኢየሱስ ነግራዋለች ። እርሱም «ማርታ ማርታ ለምንት ትሰርሒ በእስተዳልዎ ብዙኀ ? ማርያምሰ ጎርየት መከፈልተ ሠናየ ዘኢየሀይድዋ (ማርታ ማርታ ለምን ብዙን በማዘ ጋጀት ትደክሚያለሽ ? ማርያምስ የማይቀሟት እድልን መርጣለች)» ብሏል (ሉቃ.10 ፡ 38—40) ።

50 ዘይእዜ

ዕብራዊ ያዕቆብ ኢትይመካሕ ፡
እንዘይብል ወለድኩ እምአንስተ ግብራት ዘብዕሱ
ዐሠርተ ደቂቀ ምስለ ክልኤቱ ፤
ዓለም እስመ ኢረከበ ጥዒና በእሱ ።
ይትመከሑሰ ኢያቄም ወሐና ንግሥተ ላዕሱ ።
ወለድነ እልፈ እንዘ ይትባህሱ ፤
እስመ ወለቶሙ ኮነት መድኀኒተ ዓለም ዙሱ ።
ወለድነ እልፈ እንዘ ይትባህሱ ፤

ትርጉም

የኤቦር ወገን ያእቆብ
ከበለፀጉ የሰራዎች ሴቶች አስራ ሁለት ልጆችን
ወለድሁ እያለ አይመካ ፤
አለም በነርሱ ጤናን አላገኘምና ።

የላይ ንግስት ሀናና ኢያቄም ግን
እልፍን ወለድን እየተባባሉ ይመኩ ፤
ልጃቸው የአለም ሁሉ መድሀኒት ሆናለችና
እልፍን ወለድን እየተባባሉ ይመኩ ፤

ምስጢር

ያእቆብ አስራ ሁለት ልጆችን ከሁለት ሴቶች ቢወልድ በእነርሱ የአለም ሰላም ያልተገኘ ሲሆን ፤ እንዲቱ የኢያቄምና የሀና ልጅ ትድስት ማርያም ግን (ኢየሱስን በመውለዷ ምክንያት) ከእልፍ አእላፋት በላይ የምትቆጠር ናት በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

51 መወድስ

ዘወምዶ ሚካኤል (አለቃ)

አልቦ ሠናይ እንበለ ዘበልዐ ፤
እስመ እንዘ አርዌ ጠቢብ በበሊዐ መሬት ይሄሱ
ሥነ መልክኡ አዳም ወጸዳለ ፀሐይ ጸዳሉ ፤
ወዕዜ ዘበልዐ ዕጥለ ቋዓት
በበሊዐ ዕዜ ይትሔደስ አካሉ ።
በበሊዕሰ ዘኢይደሉ
ነቢየ ይሁዳ ተሀጉለ ለነቢየ ሐሰት እምቃሉ ፤
አዳምሂ ድኅረ ተፈጥረ ለበሊዐ መብልዕ ዙሉ
አጋዕዝቲሁ ተበቀልዎ በላዕከ እንዘ ይብሉ ።
እመሰ ዙሉ ነሐትት ወፍና ጥያቄ ንተሉ
እለ ይጸውሙ በሊያሙ በመልአከ ብርሃን ይትሜሰሉ ።

ትርጉም

ከበላ (ሰው) በቀር ጥሩ የለም ፤
ጥበበኛ እባብ መሬት በመብላት ሲኖር
የመልኩ ደም ግባት መልካም ነውና ፥ ፀዳሉም የፀሀይ ፀዳል ነውና ፥
ትልንም የበላ የቁራዎች ጫጩት
ትልን በመብላት አካሉ ይታደሳልና ።
የማይገባውን በመብላት ግን
ከአሰት ነቢይ ቃል የተነሳ የይሁዳ ነቢይ ጠፋ ፤
አዳምም መብልን ሁሉ ለመብላት ከተፈጠረ በሁዋላ
በላህ ብለው ጌቶቹ (ስላሴ) ተበቀሉት ።
ሁሉን ግን ብንመረምር ፥ የመረዳትንም መንገድ ብንከተል
በልተው የያሙ በብርሃን መልአክ ይመሰላሉ ።

ምስጢር

ባለቅኔው የሰው ልጅ ሊበላ የሚገባውን መብላቱ ሀይወት ሲሆነው ፥ ሊበላ የማይገባውን መብላቱ ደግሞ ሀግም ይሆነዋል ይላሉ ። በመሆኑም እባብ መሬት በልቶ ሲያምርና የቁራ ጫጩትም ትል በልቶ ሲታደስ ፥ የይሁዳ ነቢይና አዳም ግን የማይገባቸውን በመብላታቸው ተነዱ በማለት ባለቅኔው በቅኔያቸው የመታዘዝን ጠቃሚነትና ያለመታዘዝን ጎጅነት አስረድተዋል ።

ታሪክ

እባብ መሬት ለመሬት በደረት እየተንሻለለ (እየሄደ) አፈርን እየበላ ይኖራል ፥ ሲኖርም መልኩ ያምራል ፥ አይኑ ይቁለጨለጫል (ይንቦገቦጋል) ።

ቁራዎች (በጠቅላላው ወፎች) በአፋቸው ከመሬት ትሎችን እየለቃቀሙ ልጆቻቸውን በትሎች ያሳድጋሉ ።

በይሁዳ የሚኖር አንድ የእግዚአብሄር ሰው ነበር ። እርሱም ኢዩኤል ይባላል ። እግዚአብሄር በኢዮርብአም ሲፈፅምበት ያሰበውን ወደፊት ኢዮስያስ የጣኦቶችን መሰርያን (ጠንቋዮች)ና ጣኦት አጣኞቻቸውንም እንደሚያጠፋቸው እንዲነግር ከእግዚአብሄር ተላከ፤ የታዘዘውንም በእስራኤል ንጉስ በኢዮርብአም ፊት ተናገረ ። የተናገረውም ተፈፀመ ፤ መሰዊያውም ለምልክት ተሰነጠቀ ። በዚህ ጊዜ ኢዮርብአም እጁን ከመሰዊያው ላይ አንስቶ ጣቱን ቀስሮ «ያዙት» አለ ። ይህን ሲናገር የኢዮርብአም እጅ ደረቀች ። ኢዮርብአም ነቢዩን ፀልዮ እንዲያድነው ተለማመጠው። እርሱም ፈጣሪውን ለምኖ አዳነው ። ስለዚህም ንጉሱ ኢዮርብአም ነቢዩ በቤቱ እንዲመገ ብለት ቢለምነው «በግንም ቤት እንዳልገባና እንዳልበላ ፥ እንዳልጠጣም በእግዚአብሄር ቃል ታዘዣለሁ አይቻልም» ብሎት ሄደ ። ይህን የሰማ አንድ ነቢየ ሀሰት ተከተለውና በአድባር ዛፍ ስር እንዳረፈ አገኘው ። እኔም እንደአንተ ነቢይ ነኝ ፥ መልአክ መጥቶ « ያን የእግዚአብሄር ሰው መልሰውና ከአንተ ጋር እህልና ውሃ ቀምሶ ይሂድ » ብሎኝ ነው የመጣው በማለት በአሰት አታለለው ። ነቢዩም ሰው መሆን አይቀርምና አብሮት በላ ጠጣ የእግዚአብሄርን ትእዛዝ በመጣሱ መቅሰፍት ታዘዘበት ። አህያውን ጭኖ ወደ መጣበት በሌላ መንገድ ሲሄድ አንበሳ ገደለውና ያው ነቢየ ሀሰት ሬሳውን አንስቶ ቀበረው ። ነቢዩ ኢዩኤል በተነባው ትንቢት መሰረት ኢዮስያስ ነገሰና የተተነባውን ሁሉ ፈፀመ ። ያን ጊዜ የኢዩኤልን መቃብር መታሰቢያ አየና የነቢዩ መታሰቢያ መሆኑን ተረዳ። ስለዚህ የካሀናተ ጣኦትን አጥንቶች ከመቃብራቸው እያስወጣ ሲያቃጥላቸው የነቢየ እግዚአብሄር መቃብር እንደተከበረ እንዲኖር አድርጓል ። ያም አታላይ ነቢይ ከደገኛው ነቢይ ከኢዩኤል መቃብር ስለተቀበረ ደገኛ ጥግ ሆኖት ከእሳት ቃጠሎ መዳኑ ተፅፏል (1 ነገስ. 13 ፥ 1—34 ፤ 2 ነገስ. 23 ፥ 1—23) ።

51 መወድስ

ዘተበቡ (መሪጌታ)

ሶበ ሞተ ባዕድ ነደ ነበልባል
ቅብዐ አልሕምት ሕይወተ ተቀቢያሙ ወዐሱ
ሠለስቱ ደቂቅ በጥቃ በድኑ ዘዓሉ ፣
ወለዐይነ ንጉሥ ዘተስእሎሙ
ንስቲት ተዘምዶ አልብነ ይቤሉ ።
ባሕቱ መልአከ ራማ
መቃብሪሁ መጠነ በነዋኅ በትረ መስቀሉ ።
ተኅይንሂ ዘቢባሉን ዘአሕሙምዎ በዙሉ
ሥቃየ ወመከራ ንዋያተ እሳት ተካፈሉ ፤
መዋቲ እሳት እስመ አዘዘ ለእሉ
ዘቦ በውስተ እፍኣ ወዘቦ ውስተ መርጡሉ ።

ትርጉም

ባእድ የነበልባል እሳት በሞተ ጊዜ
በእስከፊኑ አጠገብ የሚዞሩ ሶስት ልጆች
የላሞች ቅቤ/ህይወትን ተቀብተው ዋሉ ፤
ለጠየቃቸው (ሰው) የንጉስ አይንም
ትንሽ ዝምድና የለንም አሉ ።
ነገር ግን የሰማይ መልአክ (ቅዱስ ገብርኤል)
መቃብሩን በረኽም መስቀሉ በትር ለካ ።
በሁሉ ያስታመሙት የባቢሉን ከተሞችም
የእሳት ገንዘቦች /ስቃይና መከራን ተካፈሉ ፤
በውጭ ያለውንና በአዳራሹ ውስጥ ያለውን
ሟች/ እሳት ለነርሱ አዟልና ።

ባእድ ሰው ሲሞት ጠላቶቹ ቅቤ ተቀብተው በደስታ እንደሚ ውሉ ፣ ሶስቱ ልጆችም (አናንያ ፣አዛርያ ፣ ሚሳኤል) እሳት ቀዘቀ ዘላቸው ። ቅቤ የተቀቡትንም ሰዎች ሌላው ሰው « ለምን ተቀባ ችሁ?» ሲላቸው « ከሟቹ ጋር ዝምድናም የለንም » እንደሚሉ ሶስቱ ልጆችም እንኳን ሰውነታቸው ልብሳቸው በእሳት አለመቀን በሩን (አለመለብለቡን) ያመለክታል ።

እንዲሁም በህይወት ያለ ሰው የሞተ ሰውን መቃብር በበትሩ እንደሚለካ ቅዱስ ገብርኤልም እሳቱን በመስቀል በትሩ ባረከ ፤ በዚ ህም ላይ ሟች ሰው በቤትና በውጭ ያለ ንብረቱን ለቤተሰቦቹ እንደሚናዘዝና እነርሱም ሀብቱን እንደሚካፈሉ ፣ የባቢሉን ሰዎችም የእሳት ቃጠሎንና ስቃይን ተቀበሉ በማለት ባለቅኔው ተቀኝተዋል።

ታሪክ

ሶስቱ የመንግስት ልጆች (አናንያ ፣ አዛርያና ሚሳኤል) በባ ቢሎን በምርኮኝነት ሲኖሩ ፣ ሁሉን በፈጠረ አምላክ ማመናቸውን አጥንተው የሰው እጅ ስራ ለሆነ ጣኦት አንሰግድም መስዋእ ቱንም አንበላም ስላሉ ናቡከደናዖር በእሳት ውስጥ አስጣላቸው ።

የእሳቱ ነበልባል ምጥቀቱ (ርዝመቱ) እስከ አርባ ዘጠኝ ክንድ ዘልቆ ሳለ የእሳቱ ባህርይ በእነርሱ ዘንድ የውሃ ባህርይ ሆኖ ላቸው በአምላካዊ ተአምራት ልብሳቸው እንኳ ሳይቀር ከመቃ ጠል ድኗል ። የእሳቱ ነበልባል ከእነርሱ አልፎ በእሳት ላይ የጣ ሏቸውን ሰዎች አቃጥሏቸዋል ይባላል (ዳን.3 ፣ 1—30) ።

53 መወድስ

ዘንጉሤ ይመር (አለቃ ፣ ዘጸጋ)

አይቱኑ ለነውር ብሔረ ሙላዱ
በውስተ ዙሉ ብሔር እስመ ከመ ነግድ ይሄሉ ።
ጠይቶተ ዝኒ ነገር ከመ ይትገሀድ ለዙሉ

ጎጥእ ይግለት ላዕለ ጻድቅ
ከመ ዘንጹሕ ወሠናይ ባህሉ ፡
እስመ እንዘ ሠርዌ በውስተ ዐይኑ
እምዐይነ ቢጹ ብሩህ አውፅኦት ሠርዌ ያስተዴሉ ።
እይሁድኒ ሐዋርያት በጽዕለቶሙ ጸዐሉ
ጊጉያነ ወአብጻነ ወሐሳውያነ እንዘ ይብሉ ፡
ወእንዘ ብእሴ ጻደቀ ዘህለዎሙ ይስቅሉ
እንዘ ወቅአን እምነ ጽድቅ በጽደቀ ርእሶሙ ተለዐሉ ።

ት ር ጉ ም

የነውር መወለጃ አገር የት ነው ?
በአገሩ ሁሉ ውስጥ እንደ እንግዳ ይኖራልና ።
ይህንንም ነገር መረዳት ለሁሉ ይገለጥ ዘንድ ፡
ባህሉ ንፁህና መልካም እንደሆነለት ሰው ሁሉ
ሀጢአተኛ በእውነተኛ ላይ ይዘባበታል ፤
ጉደፍ በአይኑ ውስጥ ሳለ ከባልንጀራው ብሩህ አይን
ጉደፍን ፣ወጣት ያዘጋጃልና ።
በደለኞችን ፡ ሰነፎችንና አሰተኞችንም ብለው
አይሁድ ሀዋርያትን በስደባቸው ሰደበዋልና ፤
እውነተኛ ሰውን ይሰቅሉ ዘንድ ያላቸው አይሁድ
ከእውነት ወጭ ሲሆኑ በራሳቸው እውነት ከፍ ብለዋልና ።

ም ስ ጢ ር

«አንዱ በአንዱ ሲሰቅ ፡ ጅንበር ጥልቅ» እንዲሉ ነውረኛው በንፁሁ ሀጥኡ በፃድቁ ፡ አላዋቂው በብልሁ እርስ በርሱ ሲዘባበትና ሁሉም በግብዝነት ራሱን በገዛ እጁ ሲያልቅ ይናገራል ካሉ በሁዋላ ባለቅኔው ትላልቁን ሀጢአት በአይን ውስጥ ባለ ትልቅ ጉደፍ፡ ጥቃቅኑን ሀጢአት ደግሞ በአይን ፀ ስጥ ባለ ትንሽ ጉደፍ መስለ ውታል ። የእውነት ምስክሮች የተባሉ ሀዋርያት በአሰተኞች አይ

ሁድ ዘንድ መናቃቸውንና ፣ ፃድቅ የሚባል ከርስቶስም ሀጥእ መባ
ሉን በትኔያቸው ገልጠው ይህ እንዲህ ከሆነ « የነውር አገሩ የት
ነው ? » ይላሉ ባለቅኔው ።

54 ዕዝል ዕጣነ ሞገር

ዘእድግሱ (መልእክተ ብርሃን)

ሀየንተ አባግዕ ዘሞትከ ኖላዊ ታሕቱ ወላዕሉ
አባግዕ ብከ ኢተሀጕሉ ፤
ሙሴሰ ወዳዊት እምትጥስዮሙ ለእሉ
ጠስየነ እመ ይብሉ
ላዕለ አባግዕ ተንሥኡ ወአባግዐ ቀተሉ ፤
ከማከ እስመ እምአበሳ ነጺሐ ኢይክሉ ።

አመረ ንጉሥ

ለዘበድኅሬነ ጸርሐት ብእሲት ታስተፋትሓ ይደሉ
ሰግዕተ ከሐ ወዝየ ፤ አመረ እግዚእከ ትትሉ ፤
ላዕለ ወለታ እስመ ኅየሱ
ዕደወ አመግ ወግፍዕ ዘገዳመ ዔሉ ፤
ወይእዜ ተረጸመ ኰሉ ።

ት ር ጉ ም

በበጎች ፈንታ የሞትህ የታችና የላይ እረኛ
በጎች አልጠፉብህም ፤
ዳዊት እና ሙሴ ግን እነርሱን (በጎቹን) ከምታጠፋቸው
አጥፋን ቢሉ
በበጎች ላይ ተነሱና በጎችን ገደሉ ፤
ከበደል መንግስትን እንዳንተ አይችሉምና ።

የጌታህን ፈለግ ትከተል ዘንድ የወዲያና የወዲህ ምስክር
ጊዮርጊስ !
በሁዋላችን የጮኸች ሴትን ታፈራርዳት ዘንድ ይገባል ፤
ዱርን የዞሩ የግፍና የበደል ወንዶች
በልጅዋ ላይ አይለዋልና (በርትተዋልና) ፥
ዛሬም ሁሉ ተፈፀመ ።

ም ስ ጢ ር

መልካም ጠባቂ ከበጎች ፊት ጠንክሮ አውሬውን ከተከላከለ ላቸው ፤ በጎቹ እንደማይበሉ ክርስቶስም መሞቱ አዳምንና ልጆቹን ከዲያብሎስ ቁራኛነት ነፃ ለማውጣት ነው ።

የበጎች እረኞች የነበሩ ሙሴና ዳዊት ግን በበጎች የተመሰሉ እስራኤልን ከበደላቸው የተነሳ አምላክ ሊያጠፋቸው ሲል ፥ «እነር ሱን ከምታጠፋብን እኛን ጠባቂዎቻቸውን አጥፋን » ብለው አም ላክን ቢማለዱላቸውም እነርሱ እራሳቸው እስራኤልን ከማጥፋት አልተቆጠቡም ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

የአሰረ ነጋሲው ምስጢር ደግሞ ፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያ በገባበት ወቅት የሀገር ፀጥታ ስለተበላሸ ፥ ወንበዴዎች ሌሊት ደብ ድበውና አፍነው ልጅዋን የወሰዱባት አንዲት ሴት ስትጮህ የሚ ረዳት አጣች ። ስለዚህም ከዲግ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን መስክ (ከግርገጃው ቆማ) እየጮኸች አለቀሰች ። ይህንም ራሳቸው የቅኔው ባለቤት በማየታቸው ሰው የጨከነባት ያችን ሴት የዲግው ቅዱስ ጊዮርጊስ ፈጥኖ እንዲረዳት በቅኔያቸው (ሰማእቱን) ተማፅነዋል ።

ታ ሪ ክ

ዳዊት የእስራኤልን ህዝብ አንድ ባንድ አስቆጥሮ የብዛታቸ ውን መዝገብ ከኢዮአብ ከተረከበ በሁዋላ በስራው ተፀፀተ ፤ እግዚአ ብሄርንም ይቅርታ ጠየቀው ። እግዚአብሄርም በነቢዩ በጋድ ቃል

ከሶስት መቅሰፍቶች አንዱን እንዲመርጥ አመለከተው ። እርሱም ይቅር ባይ እንደመሆኑ መጠን በሰው እጅ ከመውደቅ በእግዚአ ብሄር እጅ መውደቅን መረጠ ። ይሽውም ቸነፈር በስንዴ መከር ጊዜ ህዝቡን መግደል ጀመረ ፤ በመቅሰፍቱ ሰባ ሺህ ሰው ሞተ ።

ቀሳፊው መልአክም ኢየሩሳሌምን ሊያጠፋት ሲል ፥ እግዚ ብሄር ስለህዝቡ እልቂት አዘነ ፤ መልአኩን «ከእንግዲህ በቃህ እጅህን መልስ» አለው።ዳዊትም ቀሳፊውን መልአክ በአርና አውድግ አጠገብ ባየው ጊዜ አምላኩን ለመነ ፤ በደሉንም ገልጦ «የበደልሁ እረኛቸው እኔ ስሆን ፥ እሊህ በጎች ምን አደረጉ ? በእኔና በአ ባቴ ቤት ላይ የቁጣህን እጅ ዘርጋ» አለ ። በዚህ ጊዜ ነቢዩ ጋድ መጥቶ መስዋእት እንዲሰዋ አዘዘውና እንዳዘዘው አደረገ ። መቅሰ ፍቱ ተግ አለ (2 ሳሙ. 24 ፥ 1—25) ።

ክርስቶስ ራሱን በቸር ጠባቂ ፥ አማኞችን በበጎች ዲያብ ሎስን በአውሬ መስሎ ተናገሯል ። « ለዘመጽአ ጎቤየ ኢይሰድዶ ወኢያወፅአ አፍአ (ወደእኔ የሚመጣውን አላባርረውም ፤ ወደውጭም አላወጣውም)» ባለው መሰረት በመጠበቁ ማጥፋት እንደሌለበት አረጋግጧል (ዮሀ. 10 ፥ 1—42) ።

በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ በዲግ ጊዮርጊስ ደብር የሰው ግዙ የሆነች አንዲት ሴት ነበረች ። በበረሃ የሚኖሩ ሽፍቶች ሌሊት መጥተው የዚያችን አገልጋይ ሴት ልጅ ነጥቀዋት ሄዱ ። ቀኑ እሁድ ስለነበረ መወድስ ተቁሞ ሳለ ፥ በቅኔ ማህሌቱ ውስጥ መጥታ «ልጄን ወሰዱብኝ ወይኔ ! ወይኔ ! » እያለች ስታለቅስ አደረች ። ስለዚህ ነው ባለቅኔው «ላዕለ ወለታ እስመ ጎየሉ» ያሉት ።

55 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ኢጸግበ ሰይፍ ዘዘካርያስ ወዓሊ ፤
ዘይሴሰዮ ዮሐንስ እስመ ውእቱ አቦሊ ።

ት ር ጉ ም

የዘካርያስ አሽከር / ሰይፍ አልጠገበም ፤
የሚመገበው የሀንስ ክፋይ (ግማሽ) ነውና ።

ም ስ ጢ ር

ግማሽ ወይም ኩርማን እንጀራ የቀረበለት ሰው እንዳይጠግብ ሰይፍ የመጥምቁ ዮሀንስን አባት ዘካርያስን በመቁረጥ ብቻ አልቀረም ፤ መጥምቁ ዮሀንስንም ለሁለት ቆረጠ በማለት በሰይፍ መሞት የዘካርያስና የልጁ የዮሀንስ እጣ መሆኑን ባለቅኔው ያስገንዝባሉ ።

ታ ሪ ክ

ዮሀንስ ክርስቶስን በዮርዳኖስ ያጠመቀ የዘካርያስ ልጅ ነው ። የገሊላ ንጉስ ሄሮድስ ሰቤተ ልሄም የተወለደውን የድንግል ማርያምን ልጅ ለመግደል ሲያስፈልገው ፣ በርሱ ምክንያት አባቱን ዘካርያስን ካስገደለበት በሁዋላ ሄሮድያዳ የተባለች ዘማ አንተቱን በሰይፍ አስቆርጣዋለች ። ራሱም ክንፎችን አውጥቶ በአየር መጥቆ ፣ ዮሀንስ በሀይወት ያወገዘውን ሄሮድስን እያወገዘ አስራ አምስት አመት ቆይቶ በፍና አረቢያ ውድቆ ተገኝቷል ፤ ዘማይቱንም መሬት ውጧታል ይባላል (ማቴ. 14 ፥ 1—12) ።

56 ዙልክሙ

ዘንጉሤ ይመር (አለቃ ፣ ዘዲግ)

ሕዝበ እስራኤል ወአርን ለእመ አበሱ
ቅድመ እግዚኡ ሰገደ ሙሴ እንዘ ይጼሊ ፤
ለአድኅኖ አሉ እሞት እስመ በጸሎቱ ከሃሊ
እስከ ጊጋዮሙ ከመ ልብስ ይብሊ ።
ዘመነ ሣህልሰ ወተበቅሉ

ከመ ኢይኩን ሕውሰ ፥ ንፍልጥ ወንሌሊ
ተምዐ ከመ ያስጥሞ ለንጉሠ ግብጽ ማህጉሊ
ሚካኤል ፤ እንዘ የዋህ እስመ ላዕለ ፈርዖን ተበቃሊ ።
ጊዮርጊስኒ ጎያል ዘተራድኦ ይሔሊ ፥
ምስለ ነገሥተ ሮም ዐላውያን በፍቅረ ምኒልክ ተጋዳሊ ፥
ወእምቅድመ ዝ ውእቱ ሰብአ ነገሥተ ፋርስ ቀታሊ ።
ምስለ ነገሥተ ሮም ዐላውያን በፍቅረ ምኒልክ ተጋዳሊ ፥

ት ር ጉ ም

የእስራኤልና የአርን ወገኖች ቢበድሉ
ሙሴ በጌታው ፊት እየፀለየ ሰገደ ፤
በደላቸው እንደ ልብስ እስኪያረጅ ድረስ
በፀሎቱ እነርሱን ከሞት ለማዳን ቻይ ነውና ።
የይቅርታና የመበቀል ዘመን ግን
ቅልቅል እንዳይሆን ፥ በፍፁም እንለይ ዘንድ
ሚካኤል አጥፊ የግብፅ ንጉስን ሊያስጥመው ተቆጣ ፤
(እርሱ) የዋህ (ቸር) ሲሆን በፈርኦን ላይ ተበቃይ ሆኗልና ።
መራዳትን የሚያስብ ሃይለኛ ጊዮርጊስም
ከወንጀለኞች የሮም ነገስታት ጋር በምኒልክ ፍቅር
ተጋዳይ ነውና ፥
ከአሁን ቀደምም የፋርስ ነገስታትን ገዳይ ነበር ።
ከወንጀለኞች የሮም ነገስታት ጋር በምኒልክ ፍቅር ተጋ
ዳይ ነውና ፥

ም ስ ጢ ር

የከብቶች አረኞች አህል ባስበሱ ጊዜ የጎረቤት ሽማግሌ እንደ ሚያያስታርቅ አስራኤል ጣኦት አምልከው እርሱን በመበደላቸው ፥ እግዚአብሄር አስራኤልን እንዳያጠፋቸው ሙሴ በፀሎት መግለጹ ንና ልብስም ሲያረጅ እንደሚበጣጠስ በደላቸው መፋቱን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ።

ነገር ግን ለመበቀልም ፣ ለይትርታም ጊዜ እንዳለው ፣ ሚካኤል ርሀሩህ ሲባል የእስራኤል ጠላት ፈርኦንን በኤርትራ ባህር አሰጠመው ። ቅዱስ ጊዮርጊስም የፋርስ ነገስታትን በእሳት ማጥፋት እንደለመደ ፣ ለእዬ ምኒልክ ረዳት ሆኖ በአድዋ ከርሞ የመጣውን የፋሽስት ኢጣልያ ጦር ድል እንዲሆን አደረገ በማለት ባለቅኔው በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ዘንድ የሚነገረውን በትኔያቸው ምስጢር አመልክተዋል ።

ታሪክ

ሙሴ ወደ ደብረ ሲና ሄዶ ስለዘገየ የእስራኤል ህዝብ ተሰብስበው ሄደው ወንድሙን አሮንን «ሙሴ ወደደብረ ሲና ሄዶ ቆየብን የሆነውን አናውቅምና ጠላቶቻችንን የሚያጠፉልን ጣኦቶችን ስራልን» አሉት ። አርሱም ቢሰራላቸው አምላክ እንደሚጣላው ቢያውቅም ፣ አይሆንም ቢላቸው እነሱ ስለሚጣሉት ነገሩ የሚሰናከልበትን ዘዴ የፈጠረ መስሎት «በሚስቶቻችሁ ጆሮዎችና አንገቶች ያሉትን የወርቅ ጌጦች አምጡ ፣ እሰራላችሁዋለሁ» አላቸው ። ምክንያቱም እስራኤል ገንዘብ ስለሚወዱ ፣ ዛሬ ነገ ሲሉ ሙሴ ይመጣልኛል በማለት ነበር ።

እነሱ ግን አሮን የጠየቀውን ወርቅ ሰብስበው ወዲያውኑ አመጡለት ፤ ዘዴ ቢፈጥርም አልተሳካለትም ፣ ያሉትን ሰራላቸው ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሄርም ሙሴን « ወንድምህ አሮንና ህዝብህ በደሉኝ ፣ ተወኝ ላጥፋቸው » ቢለው እነሱን ከምታጠፋቸው እኔን እጥፋኝ» ብሎታል ። « እንኪያውስ ፈጥነህ ውረድና ስራ ፣ ቅጣ» አለው ። ሄዶ የወርቁን ጣኦት በእሳት አቃጠለው ያን አድቅቆና አልሞ በውሃ በጥብጦ አጠጣቸው ። የጣኦት ፍቅር ያለበት ሰው ሁሉ በከንፈሩና በግንባሩ የጣኦት ስም እየተቀረፀበት ተገኘ ። ስለዚህም ያን ምልክት አድርጎ ሌዋውያንን አዝዞ ሶስት ሽህ ሰዎችን እንዳስገደለ ተፅፏል (ዘፀአ. 32 ፡ 1—32) ።

ሚካኤል የሚባለው የመላእክት አለቃ እስራኤልን ቀን በደመና ሌሊት በእሳት ብርሃን እየመራቸው በሙሴ አማካይነት ከግብፅ አውጥቷቸዋል ። ባህር ከፍሎ ወንዝ አሻግሮ ወደ ከነአን እንዲገቡ ሲያደርግ ፤ በባርነት ቀጥቅጦ ሲገዛቸው የኖረው የግብፅ ንጉስ ፈርኦን ጋት በጋት (እግር በእግር) ተከታትሏቸው በተከፈለው ባህር መካከል ጥልቅ ሲል እንደ ግድግዳ የቆመውን ውሃ ሙሴ በበትር እንዲመታው ታዘዘ ። ሙሴም ሲመታው ጊዜ ማእበሉ በራሱ (በፈርኦን) ላይ ተከንብሎ ንጉሱን ከነሰራዊቱ ፣ ከነሰረገሎችና ከነፈረሶቹ በባህር ውስጥ አስጥሞ አስቀርቶታል ይባላል(ዘፀአ. 41 ፡ 1—15)።

የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት አፄ ምኒልክ የቅዱስ ጊዮርጊስን ታቦት በካህናት አስይዘው አድዋ ዘምተው ከርሞውያን ጋራ ሲዋጉ በሰራዊታቸው ጀግንነትና በቅዱስ ጊዮርጊስ ተራዳኢነት በድል አድራጊነት ተመልሰዋል እየተባለ ይተረካል ። ደግሞ ቅዱስ ጊዮርጊስ በህይወቱ ሳለ በሰባ ነገስት ከተሞች የክርስቶስን ስም ሲሰብክ ፣ በልዩ ልዩ ሲቃይ ሰባት እመት ሙሉ ተሰቃይቶ በሰባተኛው እመት በሰይፍ ተከልሎ ከመሞቱ በፊት ፤ ሊቆርጡት የመጡትን ወገኖች ትንሽ እንዲታገሱት በትህትና ለምኖ ከሰማይ እሳት እንዲዘንብለት ስለፀለየ ሰባውን ነገስታት በአምላካዊ ተአምራትና ሀይል በእሳት እጋይቷቸዋል ይላሉ (ስንክ. ሚያዝ 23) ።

57 ግእዝ ክብር ይእቲ

ዘንብረ መድኅን (ግራጌታ)

ናላዌ እባግዕ መስቀል ሠናያተ ዘይሔሊ
መራዕየ ጠሊ አእላፈ እምአባግዒሁ ይሴሊ ፤
እስመ እምአጣሊ በግዐ ዘኢሴለየ ወዓሊ
ሙፋረ አባግዕ ረሰየ ሙፋረ ግብሮሙ ለአጣሊ ።

ትርጉም

ጥሩዎችን የሚያስብ የበጎች እረኛ /መስቀል
ብዙዎችን የፍየል መንጋዎች ከበጎች ይለያል ፤
በጎችን ከፍየሎች ያልለየ ጠባቂ
የበጎችን መሰማሪያ የፍየሎች መሰማሪያን አድርጓልና ።

ም ስ ጢ ር

የበጎች እረኛ ፍየሎችን ከበጎች ለይቶ እንደሚያስገባ የክርስቶስ መስቀልም ለምእመናን ድህነት ሲሆን ለአይሁድ ጥፋት ሆነባቸው ። ደግሞ በጎችን ከፍየሎች ያልለየ እረኛ አብር እንደሚያሰግራቸው በዚህም አለም ደገኞችና ክፉዎች ተቀላቅለው ይኖሩበታል ግለትን ቅኔው ያሳያል ።

58 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘስሜን (መሪጌታ ፡ ዘጠለዛሞ)

ኢትእመኑ ሕዝብ ዘወለድከሙ በተድላ ፤
እስመ ለግርያም ድንግል ዘወለደቶ ቱተላ ።

ት ር ጉ ም

ወገኖች (ህዝብ) በደስታ የወለዳችሁትን አትመኑ ፤
ድንግል ግርያምን የወለደችው ገድሏታልና ።

ም ስ ጢ ር

አንዳንድ እናቱን የሚገድል ልጅ እንደግይታጣ ሁሉ ፡ በሰውሬት የግያዳላ አምላክ በእጻምና በሄዋን የፈረደውን የሲጋ ሞት እናቱ ቅድስት ግርያም እንድትቀምሰው አደረገ ይላሉ ባለቅኔው ።

59 ዋዜማ

በያሬድ ቂርቆስ (መሪጌታ)

መነነቶ ወጎደገቶ
ለተክለ ሃይማኖት አብ ጽጉዐ ሃይማኖት መሐላ
ብእሲት እግሩ ዘዐቢይ ጎይላ ፡

ወኢፈቀደት ነቢረ ውሳጤ ቀዊም መርጡላ
ስድስተ አከናፈ ደቂቀ ተድላ
በላዕሌየ ወለደ ብሂላ ።

ት ር ጉ ም

ሃይሏ ትልቅ
የሆነ እግሩ / ቤት የሃይማኖት መሃላን ያጠና
አባት/ተክለ ሃይማኖትን ናቀችውና ተወችው ፤
ስድስት ክንፎች / የምችት ልጆችንም በላየ ላይ
ወለደ ብላ በመቆሚያ / ቤቷ
ውስጥ -መኖርን አልወደደችም ።

ም ስ ጢ ር

የጎልማሳ ሚስት ባልዋ በላይዋ ላይ ከሌላ ቤት ልጅ ሲወልድ ቀንታ እንደምትፋታ ሁሉ ፡ ዓድቅ ተክለ ሃይማኖትም ሰባት አመት ቆመው ሲፀልዩ አንድ እግራቸው ተሰብሮ ስድስት የፀጋ ክንፎችን አገኙ ይላሉ ባለቅኔው ።

ታ ሪ ክ

ተክለ ሃይማኖት የተባሉት ዓድቅ ሸዋ ፡ በቡልጋ ውስጥ ከፀጋ ዘአብና ከእግዚእ ሀረያ ተወልደው ካደጉ በሁዋላ እየተዘዋወሩ ህዝቡን በክርስቶስ አሳምነዋል ። በያምና በፀሎት ከመቆማቸው ብዛት የተነሳ እንዱ እግራቸው ተሰብሯል ። ስለመንፈሳዊ አገልግሎታቸውም ስድስት የፀጋ ክንፎች ተሰጥተዋቸዋል ማለት ይተረካል ። ስለዚህ ባለቅኔው እግራቸውን በተፈታች ሴት ፡ ክንፎችን በውጭ ልጆች መስለው ተቀኝተውላቸዋል (ገድለ ተክለ ሃይማኖት) ።

60 ዋዜማ

ዘስመኘ (መሪጌታ ፡ ዘጠላዛሞ)

ስምዖን ለመርዓቱ
እምነ ዘሱ እክበራ ፡ መልምነ ዘሱ አልወላ ፡
ሊትፃኢ እፍኣ እኮኑ ይቤላ ፡
ኪያሃ ኢይርአይ ጸዳለ ፀሐይ ወፅብላ ።
ወይቤ በፍጽም ወበከሞላ
ይትልውኪ ሰብእ ምድር ዙላ ።

ት ር ጉ ም

ስምኦን ሚስቱን
ከሁሉም አብልጦ እክበራት ፡ ከሁሉም አብልጦ ከፍ አደ
ረጋት ፡
የፀሀይና የጨረቃ ብርሃን
እንዳያያት ወደውጭ አትውጭ ይላታልና ።
በፈትና በሁላዋም የምድር
ሰዎች ሁላ ይከተሉሽ ብሏልና ።

ም ስ ጢ ር

እንዳንድ ሰው የሚወዳት ሚስቱን «ወደውጭ አትውጭ ነፋስ አይንፈስብሽ ፡ ፀሀይም አያቃጥሽ» እያለ አፍኖ እንደሚያኖራት ሁሉ ፡ በላኤ ሰብእም መጀመሪያ ሚስቱን በመጨረሻም ሌሎችን ሰዎች መብላቱንና ሚስቱም ከፀሀይና ከጨረቃ አለም መለየቷን ባለትኔው አመስጥረዋል ።

61 ዋዜማ

ዘዮፍታሔ ንጉሤ (ቀኝ ጌታ)

ቆመ የስኳር ጠጅ
ውስተ ደብረ ማኅው ልብነ ሀገረ ሥቃይ ወተድላ ፡
ወወደይነ በበተራሆሙ አረቄ ወጠላ ።
ወበውስተ በርሜል ልብነ ምስትፋቡአ በቀል አተላ
እሳተ አራዳ ኮኛክ እርቧው ተቃጥላ ፡
አውዐየታ ለባቢሎን ገላ ።

ት ር ጉ ም

የመከራና የምኞት አገር
በሆነ በብርጭቆ ተራራ / ልባችን የስኳር ጠጅ ቆመ ፡
በየተራቸውም አረቄና ጠላን ጨመርን ።
የበቀል/ አተላ መከማቻ በሆነ በርሜል/ልባችንም ውስጥ
የአዳራዳ ኮኛክ/ እሳት እቧው ተቃጥላ
ባቢሎን/ ገላን አቃጠለች ።

ም ስ ጢ ር

አንድ ሰው በአካባቢው የሚደረገውን ለመመልከት በተራራ ላይ እንደሚቆም በስኳር የተጠጀ ጠጅም በጠጭዎች ልብ ፈላ ። ለግብር የሚኮለኮሉ ሰልፈኞችም በየተራቸው እንደሚገቡ ጠጭዎች በጠላ ላይ አረቄን ፡ በአረቄም ላይ ጠላን መጠጣት አበዙ ።

ደግሞ እሳት ተቃጥላ ሌላውን እንደምታቃጥል ፡ አረቄም የእሳት ባህርይ ስላላት የጠጭዎችን ገላ ትኩሳታም ማድረጓን የቅኔው ምስጢር ያመለክታል ።

ዘዓለሙ (መጋቢ ፡ ዘጎንጅ)

ለኤልያስ ሐዋርያ
አይቴ ተሐውር እመ ትቤሎ
አሐቲ ብእሲት ዓለመ ሐሰት ወተድላ
አሐውር ጎፀ እንተ አልቦ ሞተ ሰብእ ይቤላ ።
አመኒ ተመይጠ እምሀገረ ባዕድ ጌልጌላ ፡
ሰይፈ ብርት እጎት ዘይትዌከላ
ላዕለ ከሣዱ ትወድቅ ፡ አስመ ዐልወላ
እምአንስት ሕማማት ሠላ ።

ትርጉም

ኤልያስ / መንገደኛን
አንዲት ሴት / የደስታና
የምችት አለም ወዴት ትሄዳለህ ? ብትለው
«የሰው ሞት ወደሌለበት እሄዳለሁ» አላት ።
ከባእድ አገር ሰማይም (ኤልያስ) በተመለሰ ጊዜ ፡
የሚተማመናት የብረት ሰይፍ / እህት
በአንገቱ ላይ ትወድቃለች ፡
ከሴቶች / ሀማሞች ሁሉ አልቋታልና ።

ምስጢር

አንዲት ሴት በአጠገቧ የሚያልፍ መንገደኛን «ወዴት ትሄዳለህ?» ስትለው « ሞት ወደሌለበት እሄዳለሁ» በማለት እንደሚቀልድ ነቢዩ ኤልያስም ከሞት አለም ወደ ህይወት አለም አረገ ይላሉ ባለቅኔው ። መንገደኛውም ከሄደበት ሲመለስ እህቱ በናፍቆት ከአንገቱ ላይ እንደምትጠመጠም ፡ ኤልያስም በመጨረሻ በሰይፍ የሚቆረጥ መሆኑን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

ከማቴ ብርሃን
እንዘ ሊቅ ፈጸመ ሕገ ተልእኮ
ወለቀዳሚት ድግጎ ደብተራ እንተ እግዚአብሔር ተከላ
ምዕራፍየ ዛቲ ለዓለም ይቤላ ፤
አኮኑ ቀደመ እምኵሉ ለበዊአ ድግጎ ገሲላ
በትእምርተ መስቀል ሠረገላ ።
ወፈቀደ ይምላሕ እግእከላ
ሥረዊሃ ለአመት ሰገላ ።

ት ር ጉ ም

ከሳቴ ብርሃን
ሊቅ ሲሆን የመልአክን ሀግ ፈፀመ (ጨረሰ) ፤
እግዚአብሄር የተከላት መጀመሪያይቱን ድንኳን / ድግ
ሀንም
«ይች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት » ይላታል ፤
በሰረገላ / የመስቀል ምልክት ወደገሊላ / ዲግ
ለመግባት ከሁሉ ቀድሚልና ።
የዛር ውላጅ/ ሾላ ስሮችንም
ከመሃሏ ይነቅል ዘንድ ወዲልና ።

ም ስ ጢ ር

ክርስቶስ በሰውነቱ የአገልግሎትን ስራ እንደፈፀመ ፡ አባ ተክ
ስተ ብርሃን የተባሉ የዲግ ጊዮርጊስ ገዳም አበ ምኔት የነበሩ ፃድቅ
በያንሩ እየተዘዋወሩ ሰብከዋል ፤ አስተምረዋል ።

በዚህም ላይ ሙሴ በደብተራ አሪት እንዳገለገለ አባ ተክስተ ብርሃንም ብዙ ካገለገሉ በሁዋላ በደብረ ድግሀ ማረፋቸውን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ።

በተጨማሪም ከርስቶስ ከሀዋርያት ቀድሞ በገሊላ እንደተገኘ አባ ተክስተ ብርሃንም አስቀድመው ዲማን ማትኒታቸውን ፤ በሰረገላም ቀድሞ መንዝ እንደሚቻል ፥ አባ ተክስተ ብርሃንም በመንፈሳዊ ሥራ ቀዳሚ መሆናቸውን ያመለክታል ። ከዚህም ሌላ ባለቅኔው የሾላ ስር እንደሚነቀል ፥ በዲማ ጊዮርጊስ አካባቢ በሚገኘው ገደ በሚባለው ወንዝ መጣያ ገደል ትናር የነበረችውን የዛር ውላጅ (ሰይጣናዊት) እመ ውላድ አባ ተክስተ ብርሃን ከገደ ወንዝ አስለቀቋት ይላሉ ።

64 መወድስ

ዘእንግላ ወርቅ ጎደሉ (አለቃ)

ነቢያተ አሪት ረኃብ ወግብረ ተሰዶ
ውደተ መከራ አርአዩ በአፍራስ ወሠረገላ ፤
መምጽአተ ደዌ ሰበኩ ለሰዓተ ንዴት በክፍላ
እምከነዓን ፍጽመ ተዋርዶ እስከ ግብጽ ከዋላ ።
ውተሀውከት ሰብእናን
ሀገር ቅድስት ኢየሩሳሌም ኮላ ፥
እስመ ቦአ ለገፍትዖ ግእደ መወልጥ ግእከላ
ረኃብ ወልደ ዳዊት በተፅዕኖ እድግት ወፅዋላ ።
ወግዘፈ መብልዕ ይርአይ እምድኅረ ጎለፈ ተድላ
ከርሠ ርኁባን መጸብሐዊ ወርኀ ዲበ ሰግላ ።

ት ር ጉ ም

የአሪት ነቢያት /ራብና የመሰደደ ግዴታ
የመከራ ዙረትን በፈረሶችና በሰረገላ አሳዩ ፤
ከከነአን/ መዋረድ ፈት እስከ ግብፅ / ሁዋላ ድረስም

የደዌ አመጣጥን በችግር ሰአት አስተማሩ ።
መላዋ ቅድስት
አገር ኢየሩሳሌም/ ሰውነታችንም ታወክች ፤
ራብ/ የዳዊት ልጅ በአሀያይዙና በውርጋጧዋ በመቀመጥ
(በመጋለብ) የሰዋሟን ማእድ ለመገልበጥ (ለመድፋት)
በመካከሏ ገብቷልና ።
ምኞትም ካለፈ በሁዋላ የመብልን ፈት ያይ ዘንድ
የተራቡ ሰዎች ሆድ / ዘኬዎስ በሾላ ላይ ወጥቷልና።

ም ስ ጢ ር

የአሪት ዘመን ነቢያት ኢየሩሳሌም በፈረስና በሰረገላ እንደ ምትወረር እንደተናገሩና አገር ላገር መዞርን እንዳበዙ ፥ በክፉ ቀን የነበሩት ራብና የመሰደድ ግዴታ መንከራተትንና መከራን አበዙ ። ነቢያት የእግዚአብሄርን ልጅ ወደዚህ አለም መምጣት ከከነአን እስከ ግብፅ እንደ ሰበኩ፥ ራብና መሰደደም መዋረድን ፥ ችግርን ፥ ሀሜንና ሞትን በፊትና በሁዋላ አከታትለው አመጡ ። የዳዊት ዘር ከርስቶስም በአሀያይዙና በውርጋጧዋ በመቀመጥ የሽቃጮችን ድብር (መደብር) በገለበጠው ጊዜ አገሪቱ እንደተሸበረች የክፉ ቀን ራብ የአህያ ስጋን እስከ ማስበላት ደረሰ ። በህይወትም ያለው የሰው ሰውነት መነመነ ፥ ራብን መቋቋም ያልቻለው ሰውም ራብ ባስከተለው ቸነፈር አለቀ ። ዘኬዎስ ክርስቶስን ለማየት በሾላ ዛፍ ላይ እንደወጣ፥ ራብተኞች ሰዎችም የሚበሉት አህል ጠፍቶ ቅጠልና ፍሬን በሉ በማለት በዘመናቸው የነበረው ራብ ያስከተለውን አልቂት ባለቅኔው በትእያቸው አስገንዝበዋል ።

65 መወድስ

ዘምሥራት (አለቃ ፥ ዘኤልሻማ)

እመ ውስተ ፍና ተተከለት ዕፀ ደብረ ሲና
አዕዋፈ ግብጽ እሥዋከ በላዕሌሃ አጽለላ ፥
አኮኑ ለዕፅ እንተ ኢትትነገፍ ቁጽላ

ጎዘን ገባኢ ጽንፈ ማይ ተከላ ።
ወታንሶሱ በገሊላ
ንግሥተ እስራኤል ስደት አክሊለ ሰሎሞን ተቀጺላ ፤
ዮሴፍሂ ማፍዐ ናቡቴ ንቡረ ምድረ ግብጽ ሰግላ
ለያዕቆብ ተዋርዶ ፈነወ ሠረገላ ፤
ወመስተገብር ጎዘን ለገራሀተ አብርሃም ኮላ
እክል እንዘ አልባቲ ሐጸራ በአሜክላ ።

ት ር ጉ ም

የደብረ ሲና እንጨት በመንገድ በተተከለች ጊዜ
የግብፅ ወፎች እሾሆች በላይዋ ላይ ሰፈሩ ፤
ቅጠሏ የማትረግፍ እንጨትን
አዘን ገበሬ በውሃ ዳር ተክሏታልና ።
የእስራኤል ንግስት ስደትም
የሰሎሞን አክሊልን ተቀዳጅታ በገሊላ ትመላለሳለች ፤
በግብፅ ምድር ሾላ የተቀጠጠ የናቡቴ ግፍ ዮሴፍም
ለመዋረድ ያእቆብ ሰረገላን (ጋሪን) ላከ ፤
አዘን ገበሬም የአብርሃም እርሻን ሁላ
እህል ሳይኖርባት በእሾህ አጠራት ።

ም ስ ጢ ር

በመንገድ ዳር በተተከለች እንጨት ወፎች ይሰፍራሉ ፤ እን ዲሁም በመንገድ የምትንከራተት ቅድስት ማርያምን እሾሆች ወጉት ። እንጨቲቱ በውሃ ዳር እንደምትተከል የእንጨቲቱ ምሳሌ ማርያም በስደቷ ጊዜ እንባ በእንባ ሆነች ። ንግስትም አክሊልን ተቀዳጅታ (ዘውደን በራሷ ላይ ደፍታ) እንደምትመላለስ የሰሎ ሞን አክሊል ምሳሌ የሆነችው ማርያም በስደት ተጉላላች ።

ዮሴፍም አባቱን ያእቆብን ለማስመጣት ሰረገላን ወደ እስራ ኤል አገር እንደላከ መገፋት የሰረገላ ምሳሌ የሆነችውን ማርያምን አዋረዳት ። ገበሬም እርሻውን በእሾህ አጥር እንደሚያጥራት ፤

በእርሻ የተመሰለችውን ማርያምን የገበሬው ምሳሌ የሆነ ለልጁዋ ማዘን እሾህ ለእሾህ አስሄዳት ፤ ስንቅንም አሳጥቶ እህልንና ውሃን እስከመለመን አደረሳት በማለት ባለቅኔው ከአገሯ ከገሊላ ውጭ በመሰደዷ ምክንያት በማርያም ላይ የደረሰውን መከራና ስቃይ በቅኔያቸው ምስጢር ያስረዳሉ ።

ታ ሪ ክ

የያእቆብ ልጆች በወንደማቸው በዮሴፍ ስለቀኑበት ለግብፅ ነጋዴዎች ሸጡት ። ዮሴፍ ግን በተሸጠበት በግብፅ አገር ባለሟልን ትን አገኘ ፤ ተሾመ ፤ ተሸለመ ። በትውልድ አገሩ በከነአን ራብ ስለሆነ ወንድሞቹ እህል ሊሸምቱ እርሱ ወዳለበት አገር ወረዱ ። ወንድማቸው መሆኑን ሳያውቁ ስለእህል ሸመት ጉዳይ ሲያነጋግሩት እነርሱ ያንድ ሽማግሌ ልጆች መሆናቸውንና አባታቸው በህይወት መኖሩን ነገሩት ። በዚህ ጊዜ አወቃቸውና እህሉን በየስልቻቸው ሞላላቸው ። በሁዋላም ከንጉሱ አስፈቅዶ አባቱን ያእቆብን በሰረ ገላ ወደ ግብፅ አስመጥቶታል (ዘፍጥ. 42—45 ፤ 47 ፤ 13—26) ።

እነሆ ቅድስት ማርያም ከኢያቄምና ከሀና በአዘንና በልቅሶ በያም በፀሎትና በስእለት ፤ በራእያም ተወለደች ። በተወለደች በሶ ስት አመቷ በስእለቱ መሰረት ቤተ መቅደስ ገባች ። ከሰማይ በመ ልአክ የወረደ መናንና ወይንን እየተመገበች በቤተ መቅደስ አስራ ሁለት አመት ኖረች ። አስራ አምስት አመት ሲሆናት በዘመድዋ በዮሴፍ ቤት እንድትጠበቅ ተደረገ ። በትህትና ተልእኮ ውሃን ስት ቀዳ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከወይሁዋላዋ መጥቶ በሽበታም አዛ ውንት አምሳል «ትፀንሻለሽ» አላት ፤ ዘወር ስትል ምንም ሰው የለም ። አሳሳች ሰይጣን ነው መሰለኝ ብላ ፤ ከእግሯ ነጠቅ ነጠቅ እያለች ሄዳ እቤት እገባለሁ ስትል ዳግም «ትፀንሻለሽ» አላት ። ስለዚህ ወደቤተ መቅደስ ሄደችና በቋምጤ (ድንክ) ወንበር ላይ ተቀ ምጣ ሀርንና ወርቅን ስትፈትል ሶስተኛ ጊዜ ያንኑ ቃል ነገራት ። ቃል ለቃል ከተሟላለት በሁዋላ ነገሩን አመነችውና ፤ እግዚአብሄር ወልድን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወለደች ይባላል ። የገሊላው

ንጉስ ሄሮድስ መንግስቴን ይነጥቀኛል ብሎ ልጅዋ እግዚአብሄር ወልድን ሊያስገድለው ስላሰፈለገው ፡ ያበሰራት መልአክ ሀሳኑን ከዮሴፍና ከሰሎሜ ጋር ይዛው ወደግብፅ እንድትሰደድ ለዮሴፍ በህልም ነገረው ። ሶስት አመት ከስድስት ወር ከኖሩም በሁዋላ ከግብፅ ተመለሱ (ማቴ. 1 ፡ 17—25 ፡ 2 ፡ 1—23) ።

66 ግእዝ ክብር ይእቲ

ለመርዓተ ፀርነ ሲኦል ኢሳይያስ መሰግላ
እመ ተስእለቶ ቅድመ ወጠየቀቶ ቢቃላ
ዘመነ ሥጋዌ ማቴዎስ ያፈረርሀኪ ይቤላ ፡
ወይትበአሰኪ ደም ዘተክዕወ በመሐላ ።

ት ር ጉ ም

በመጀመሪያ ብትጠይቀውና በቃሏ ብትረዳለት
ኢሳይያስ ጠንቋይዋ የጠላታችን ሙሽራ ሲኦልን
የሰጋዌ ማቴዎስ ዘመን ያስፈራሻል ፡
በመሀላ የፈሰሰም ደም ይጣላሻል አላት ።

ም ስ ጢ ር

አንዲት ሴት ጠንቋይን ስትጠይቅ « በዘመነ ማቴዎስ ያስፈራሻል ፡ ደምም ይጣላሻል » እንደሚላት ፡ ነቢይ ኢሳይያስ በተና ገረው ትንቢት መሰረት እግዚአብሄር ወልድ ሰው በሆነበት በዘመነ ስጋዌ ለአዳም በሰጠው ቃል ኪዳን ተስፋ ያፈሰሰው ደም ነፍሳትን ከሲኦል አወጣ ይላሉ ባለቅኔው ።

67 ዘአምላኪየ

ጎቡረ ልህቱ በገራህተ ወንጌል ሉዓሌ
ክርዳድ ይሁዳ ወኤጥሮስ ስንዳሌ
እስከ ይበጽሕ ግእረር ዘዕለተ ዐርብ ወይሌ ።

ት ር ጉ ም

እንክርዳድ/ ይሁዳና ኤጥሮስ/ ስንዴ
የአርብ ቀን እዝመራ / ልቅሶ እስኪደርስ ድረስ
በወንጌል / እርሻ ወደላይ አብረው እደጉ ።

ም ስ ጢ ር

«የእዝመራ ወራት እስኪደርስ ድረስ እንክርዳድና ስንዴ አብረው ይደጉ» ብሎ ኢየሱስ እንደተናገረ ፡ የእንክርዳድ ምሳሌ ይሁዳና የስንዴው ምሳሌ ኤጥሮስ በመንፈሳዊ ሹመት አንድ ሲሆኑ ፡ ይሁዳ በእለተ አርብ (አርብ ቀን) ክርስቶስን በማስቀሱ ከሀዋርያው ኤጥሮስ በክርስቶስ በሰራው ክፉ ስራ ተለየ ። ኤጥሮስ ግን « ክርስቶስን አላውቀውም» ብሎ በአፉ በመካድ በፈፀመው በደል ተፀፅቶ በግልቀሱ ከይሁዳ ቢለይም ከክርስቶስ አልተለየም ይላሉ ባለቅኔው ።

ታ ሪ ክ

ይሁዳና ኤጥሮስ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ናቸው ። ይሁዳ መምህሩ ክርስቶስን በገንዘብ ለውጠ ከእነቀያፋ ጋር ተመሳጠረበትና ለሰላሳ ብር ሸጠው ። ለሞት አሳልፎ ሰጠው ፡ አሰቀለው ። ከዚህም ሌላ የማይረባና የማይጠቅም ፀፀትን ተፀፀተና ፡ የተቀበለውን ብር በትኖ ለመታነቅ መንጠልጠያን አዘጋጀ ። ሊሰቀልባት ያዘጋጃት እንጨት « እንደ ወንድምህ ኤጥሮስ ንሰሃ ግባ» እያለች በሰብአዊ ሁኔታ ብትመክረው አልሰማም ፡ ተሰቅሎ ሞቷል ይባላል (ማቴ. 27 ፡ 3—5 ። የሀዋ. 1 ፡ 15—19) ።

ጴጥሮስ ደግሞ የሀዋርያት አለቃ ሆኖ የኖረ ሀዋርያ ነው ፤ ክርስቶስ በተያዘ ጊዜ አሙስ ግታ ለአርብ አጥቢያ የክርስቶስን ሁኔታ ለማየትና ለመስማት ራት እያለ ክርስቶስን በመከተል በሊቀ ካህናቱ በር ቆሞ ነበር ። «እንተስ ከናዝሬቱ ከኢየሱስ ጋር አልነ በርሀምን ?» የሚሉ ሶስት ጥያቄዎች ቢገጥሙት ፤ « የምትሉትን አላውቀውም » በማለት ራሱን በራሱ ይረግም ጀመር ። ይሆን ብሎ ከእነሱው ጋር ፍሙን እየሞረ እሳቱን ሲሞቅ አድሯል (ማር. 14 ፡ 66—72)።በሁዋላ ግን ንስሃ ገብቶ በምር ስላለቀሰ ይቅርታን ከአምላኩ አግኝቷል ። ስለዚህ ባለቅኔው «ጎቡረ ልህቁ እስከ ይበጽሕ»ብለዋል ።

68 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘወልደ ማርያም ሀብቱ (አለቃ)

ተዘከር ወልድ ፍተ ርኅራኄከ እክል ፤
እስመ ቅድመ ገጽከ ቆመት ሰአሊተ ምሕረት ድንግል ።

ት ር ጉ ም

ወልድ የርህራሄ/እህል ቁራሽን ተዘከር(አስብ) ፤
ምህረትን ለማኝ ድንግል በፊትህ ቆማለችና ።

ም ስ ጢ ር

እንጀራ ለማኝ ሴት ከሰው ፊት ስትቆም « ቁራሽ ተዘከሯት» እንዲባል ወልድ ሆይ ! ለእናትህ ድንግል ማርያም በሰጠሀት ቃል ኪዳን መሰረት በፊትህ ቆማ ስትግልድ ራራ ። ባለቅኔው « ተዘ ከር » በተሰኘው ህብር ቃል ለሰሙ ስጥ ፡ ለወርቁ ግን የሰጠሀ ትን ቃል ኪዳን አስታውስ ማለትን አስተባብረዋል ።

69 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ዘተክሌ (መምህር፡ ዘጥሬራ)

ጎፍረት ይደሉ ለዘግ ወለቢሰ ዘምድር ጸበል ፤
እስመ በዓለ ክንፍ ተረክበ በዘአቅረበቶ ጼሐል ።

ት ር ጉ ም

ለዘግዊት ሴት ግፈር ይገባል ፡ የምድር ትቢያንም መልበስ ይገባል ፤
ባቀረበችው ወጭት (የወጥ ግትረቢያ) ባለክንፍ ተገኝ ቷልና ።

ም ስ ጢ ር

አንድ ሴት ሰርታ ባቀረበችው ወጥ ውስጥ የእሳት ራት ገብቶ ሲገኝ በባሏና በሌሎች ተጋባዦች ፊት ታፍራለች ። እንዲሁም ሄሮ ድያዳ የተባለችው ዘግዊት ያስቀረጠችው የመጥምቁ ዮሀንስ ራስ ክንፍ አውጥቶ በረረ በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

70 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ዘገብረ ሥላሴ ክንፉ (መምህር ፡ ዘኤልያስ)

አቤል ግእዝ ቀዳሚሁ ለሞተ ሥጋ ፈደል ፤
ወፍጻሜሁ ሳብዕ ሞተ ኤልያስ ድንግል ።

ት ር ጉ ም

የስጋ ሞት ፈደል መጀመሪያ አቤል / ግእዝ ነው ፤
የድንግል ኤልያስ ሞት / ሳብእም መጨረሻው ነው ።

ም ስ ጢ ር

ባለቅኔው የፈደል መጀመሪያው ግእዝ ፡ መጨረሻውም ሳብእ እንደሆነ ሁሉ በአቤል የተጀመረው ሞት በኤልያስ ይፈፀማል ይላሉ ።

71 ሚበዝኑ

ሳይጻ ገሞራ እሳት
በወረዛ እንጌቤን ቂርቆስ ዘሐመይዋ አህባል
በስመ አቡሃ መልአክ መሐለት እንዘ ትብል
ኢየአምር ባዕደ ዘንእበለ ጽሩይ ማይ ወእንበለ ምትየቈጽል ።

ት ር ጉ ም

ወገኖች በእንጌቤን
ጎልማሳ ቂርቆስ ያሚት የገሞራ ቆንጆ እሳት
ከጥሩ ውሃና ከባሌ ቅጠል በቀር
ሌላ አላውቅም እያለች በአባትዋ መልአክ ስም ማለች ።

ም ስ ጢ ር

ወገኖችዋ በጎልማሳ ያሚት ሴት « ከውሃና ከባሌ በቀር ሌላ አላውቅም» እያለች በአባትዋ ስም እንደምትምል ፣ በፊት ገሞራን ያቃጠለች እሳት ለቂርቆስ ስቃይ ከተዘጋጀች በሁዋላ በቅዱስ ገብርኤል ተአምር እንደ ውሃ መቀዝቀዝዋንና የእሳት አደጋም በቅጠል የሚጠፋ መሆኑን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ።

72 ዋዜማ

ዘአድግሱ (ንቡረ እድ)

ጎብእት ምድረ ኤርትራ
ግሀደ ኮነት ቅድመ ገጸ ሙሴ ጽዱል ፣
እሙሴ ተከብቶ አኮኑ ኢትክል ።
እመ ይከይዶሰ ፈርአን እንበለ ሚካኤል በጎይል
ምስለ ሠራዊቱ ተገምረ በኵናት ማዕበል
እስመ ኮነ መፍቅዱ ቀቲል ።

ት ር ጉ ም

ሸሽግ የኤርትራ ባህር
በሚያበራ ሙሴ ፊት ግልፅ ሆነች ፣
ከሙሴ መሸሸግን አትችልምና ።
ፈርኦን ግን ያለ ሚካኤል በሀይል ቢረግጣት
በማእበል ጦር ከሰራዊቱ ጋር ጠፋ ፣
ውዴታው (ፍላጎቱ) መግደል ሆኗልና ።

ም ስ ጢ ር

የተሸሸገች ሴት ከዘመዶችዋ መሰወርን እንደማትችልና እንደ ምትገለጥ ፣ የኤርትራ ባህር ምድርም ውሃው ለነሙሴ ሲሸሽላቸው ያን ጊዜ ታየች ። ደግሞ ጠላት ሲመጣ ሀይለኛው ተዋጊ ከእነሰ ራዊቱ በጦር እንደሚዋጋ ፣ ፈርኦን ከነሰራዊቱ እባህሩ ሲገባ በውሃው ሰጠመ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

ታ ሪ ክ

እስራኤል የኤርትራን ባህር በሙሴ መሪነት ሲሻገሯት ፡ ውሃዋ መሬቱን ለቆ በግራና በቀኝ እንደግድግዳ ቆመላቸው ፡ እስ ኤራልን ያሰቃይዋቸው የነበሩ የግብፅ ንጉስ ፈረኦንን ና ሰራዊቱን ግን አሰጠማቸው (ዘፀአ. 14 ፡ 1—15) ።

73 ዋዜማ

ዘለግ ጎይሉ (አለቃ)

ኢይበቁዕ ክብረ አዝማድ ፡
እስመ ወልደ ባዕል ወድቀ በእደ ረታብ ጎያል ፣
አግብርት እንዘ ጽጉባን ወይተርፍ እክል ።

ምሳሌ ዝኒ ነገር አጠየቀተነ ጎል ፤
እምጣነ ወልዳ ኢድነነ እምለቢሰ ቁጽል
እንዘ ወርቀ ትፈትል ድንግል ።

ትርጉም

የዘመዶች ክብር አይጠቅምም ፤
አገልጋዮች የጠገቡ ሲሆኑ እህልም ሲተርፍ፥
የባለፀጋ ልጅ ገብረ ክርስቶስ በብርቱ ራብ እጅ ውድቋልና ።
የዚህንም ነገር ምሳሌ በረት አስረዳችን ፤
ድንግል ወርቅን ስትፈትል
ልጅዋ ቅጠል ከመልበስ አልዳነምና ።

ምስጢር

ገብረ ክርስቶስ የንጉስ ልጅ ሲሆን መንና (አለምን ንቆ) በመቸገሩና በስቃይ በመሞቱ ፥ ክርስቶስም እናቱ ድንግል ማርያም ሀርና ወርቅን አስማምታ ስትፈትል በተወለደ ጊዜ በቅጠልና በጨ ርቅ በመጠቅለሉ እንዳር የወገን ክብር ጠቃሚ አለመሆኑን በመግ ለጥ ቅኔው ተመስጥሯል ።

74 ሥላሴ

ዘወልደ ጊዮርጊስ ዘዱ (አለቃ)

ለንጽሕት መሶበ ወርቅ
ርደተ መና ውስተ ገዳም
ወለእስራኤል ኢኮነ ፤ አኮኑ ጽጉብነ ቅንአት እክል ፥
ወይትዐወቅ እምድምፀ ንባቡ ለፋኑኤል ቃል ።
ዝኒ ነገረ ከመ ያጠይት እምሳል
መስተጉበረ ምድር ዕፀመ ሐቅል
ዘግየ ቀላይ ያሰቲ በላዕለ አስካል ፥
ያገዘር ለልምለም ቁጽል ።

ትርጉም

የመና በገዳም ውስጥ መውረድ
ለንፅህት መሶበ ወርቅ ነው ፥
ለእስራኤል ግን አልሆነም ፤ ቅናት/እህልን የጠገቡ ናቸውና፥
ከፋኑኤል ቃል ንግግር ድምፅም የተነሳ ይታወቃልና ።
ይህንም ነገር ምሳሌ ያስረዳ ዘንድ
የዱር እንጨቶችን በፍሬ ላይ
የወንዝ ውሃን የሚያጠጣ የምድር ገበሬ
ለምለም ቅጠልን ያወፍረዋል (ያንሰራፋዋል) ።

ምስጢር

ቀድሞ መና ለእስራኤል ይወርድላቸው ነበር ይባላል ። መል አኩ ፋኑኤል ያመጣው መና ግን በመሶበ ወርቅ ለምትመሰለው ቅድስት ማርያም መውረዱንና ለእስራኤል ልጆች ለነዘካርያስ አለ መሆኑን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ። የአትክልቶችን ስር ውሃ የሚያጠጣ ገበሬ በፍሬው ላይ ቅጠሉን እንደሚያንሰራፋው ፥ የእ ሴይ ስር የሆነች ሀሳኒቱ ማርያም የመልእክን መና እየተመገበች አድጋ አምላክን በመውለዷ ለእነርሱም ለትንርሜሮች ሰዎች ትበ ጃቸዋለች ይላሉ ባለቅኔው ።

ታሪክ

ቅድስት ማርያም የስእለት ልጅ እንደመሆኗ በተወለደች በሶ ስት አመቷ ለቤተ መቅደስ ተሰጠች ። የቤተ መቅደሱ ሊቀ ካህ ናት ዘካርያስ ይባላል ፤ እርሱም መጥቅእ መትቶ (ደወል ደውሎ) የእስራኤልን ሽማግሌዎች ሰብስቦ ሲመካከር የእግዚአብሄር መል አክ ፋኑኤል በቤተ መቅደሱ ረቦ ታየ ። ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ ለርሱ የመጣ ሀብት መስሎት ቀረብ ቢል ወደላይ ሰቀቀበት ። እንዲ ሁም ሽማግሌቹ በተራ ቀረቡ ፤ ራቱ ። ስለዚህም ወላጆችዋ ኢያ ቄምና ሀና እንዲቀርቡ ታዘዙና ቢቀርቡ ፥ እጅግም አልቀረባቸ

ውም ፡ እጅግም አልራቃቸውም ። ከዚህም በውጭ ሀገኒቱን ትተ
ዋት እልፍ እንዲሉ ተደረገና ትተዋት እልፍ አሉ ። ሀገኒቱም ወደ
እነርሱው ድንኩል ድንኩል ስትል መልእኩ ወረደና በክንፉ ውስጥ
አድርጎ ሰግያዊውን ህብስት መግቢትና ሰግያዊውን ወይን አጠጥ
ቷት እንዳረገ ተዕቹል (ነገረ ማርያም) ።

75 ሥላሴ

ዘመኩንን ሰሎሞን (አለቃ)

ለምንት አንገለጉ
ዕዜያተ ምድር አሕዛብ ?
በጌቴሴማኒ ወረበት እኮኑ ፋሲካሆሙ ድንግል ፡
ወገፍትዐ ማዕዳቲሆሙ ደመና ቀሊል ።
ወተመሥጠ ሄኖክ ሥጋሃ በመዐዛ ኤልያስ ኮል
ይቤሎሙ ቶማስ መስተበቅል ፤
ወበሥጋ ድንግል ታቦር መጽአ ቃል
እምደመና ወልደየ ዘይብል ።

ት ር ጉ ም

የምድር ትሎች / አህዛብ
ለምን ተሰበሰቡ ?
በጌቴሴማኒ ፋሲካቸው / ድንግል ደርሳለችና ፡
ቀላል ደመናም ማእዳቸውን ገልብጧልና ።
ቶማስ ተበቃይም ስጋዋ / ሄኖክ በኤልያስ / ሽቱ
መአዛ ተመሰጠ አላቸው ፤
ከደመናም « ልጄ» የሚል ቃል
በድንግል ስጋ / ታቦር መጣ ።

ም ስ ጢ ር

«በእግዚአብሄር ልጅ ላይ አህዛብ ለምን ተሰበሰቡ » እንደተ
ባለው ሁሉ የመቃብር ትሎች በጌቴሴማኒ በተቀበረች በማርያም
መቃብር አልተፈጠሩም ። ደግሞ ፋሲካ እንደሚደርስ ድንግል ማር
ያም ከጌቴሴማኒ መቃብር ተነሳች ። ከርስቶስም የሸቃጮችን መደ
ብር እንደገለባበጠባቸው የማርያምን ስጋ ትሎች እንዳይበሉ ደመና
ወደሰማይ አሳረገባቸው ። በሎሚ ሽታም እንደመመሰጥ የማርያም
ስጋ እንደሄኖክና እንደ ኤልያስ ተመሰጠ (አረገ) ።

ሽቱንም ያሸተተው እንደሚያደንቅ ቶማስ ሀዋርያ ማርያምን
ስታርግ አገኛት ። ከደመናም ብታቦር ሰማይ ቃል እንደመጣ ሁሉ
(እንደተነገረ ሁሉ) ፤ የማርያም ስጋ በእርገቱ ጊዜ በመላእክት
ቃል ተመሰገነ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

76 ዘይእዜ

ይሄሉ ቃል በተቃውሞ ፡
ወለድኩ ቃለ ለእሙ ትቤ ድንግል
ለአዝማድ ዮሴፍ ወሰሎሜ
እስመ አብ እምቅድመ ዓለም ወለድከዎ ይብል ፡
ወከመ ኢይትከሐድ አብ ከሙ መልክአ አብ መልክአ ቃል
ወከመ ኢትትከሐድ እም ገባሪተ ጎይል
ኢሀሉ እምቅድም ከሒደ ወላዲት ዘይክል ።
ወከመ ኢትትከሐድ እም ገባሪተ ጎይል

ት ር ጉ ም

ቃል በተቃውሞ ይናራል ፡
ለሰሎሜና ዮሴፍ ዘመዶቹ
ድንግል ቃልን ወለድሁ ብትል
አብ ከአለም በፊት (አስቀድሞ) ወለድሁት ይላልና ፡
አብም እንዳይካድ የቃል መልክ እንደ አብ መልክ ነውና ፡

ታምር አድራጊዋ እናትም እንዳትካድ
ከቀድሞ ጀምሮ እናትን መካድ የሚችል የለምና ።
ታምር አድራጊዋ እናትም እንዳትካድ

ም ስ ጢ ር

ከአለም መፈጠር በፊት እግዚአብሄር ወልድ ከእግዚአብሄር አብ በባህርይ ያለ እናት ተወለደ ። አለም ከተፈጠረ በሁዋላ ወልድ ከድን ግል ግርያም ያለ አባት ተወለደ ፤ ከባህርይ አባቱ አብ ጋር ትክ ክል መሆኑ ግን የማይመረመርና ይህም ሁለት ልደት የሚባል መሆ ኑን ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

ታ ሪ ክ

ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃላቸው የሆነው እግዚአብሄር ወልድ ከአለም መፈጠር በፊት ያለእናት በማይመረመር ምስጢር ከአብ ባህርይ ተወልዷል ። ቢወለድም አብ አይበልጠውም ፤ አይቀድ መውም ። በፍፁም መልክ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ትክክል ነው ። ከአለም መገኘት በሁዋላ ከኪሩቤል መንበሩ ሳይለቅ በም ላት ወልድ ወደዚህ አለም መጣ ። ያለአባት ከቅድስት ማርያም በድ ንግልና ተፀነሰ ፤ ከስጋዋ ስጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሳ (ወሰደ) ። ፍፁም ሰው ሆነ ። ቃል በድንግልና ስጋ ያለ ሴቶች ልማድ ተወለደ ፤ ከሀጢአት በቀር የሰውን ህግ ፈፀመ ። «ነአምን ክልኤተ ልደታተ (ሁለቱን ልደቶች እናምናለን) » በተባለው መሰረት ቀዳማዊ ልደ ቱና ደህራዊ ልደቱ ከዚህ በላይ ተገልጧል ።

77 ዘይእዜ

ዘለፋ ዘወድቀ ላዕለ መካን
ቅድመ ልደተ ቃል ሕያው ወድኅረ ልደቱ ለቃል ፣
እመ ላዕሌኪ ነበብነ ድንግል

በበዕለቱ ኪያኪ ዕጹተ ግሕፀን እንዘ ንብል ፣
ነፍሰ ድንግልና ጸድቅ ከመ ኢንትትል
ዘለፋ አልብነ ፤ ወንስሐነ ቀሊል ።
ነፍሰ ድንግልና ጸድቅ ከመ ኢንትትል

ት ር ጉ ም

በመሃን ላይ የወደቀውን ዘለፋ (ስድብ)
ከሀያው ቃል ልደት በፊትና ከቃል ልደት በሁዋላ ፣
አንቺን በየቀኑ ማህፀነ ዝግ እያልን
ድንግል ! በአንቺ ላይ በተናገርን ጊዜ ፣
የድንግልና / የድቅ ነፍስን እንዳንገድል
ዘለፋ (ስድብ) የለብንም ፤ ንስሃችንም ቀላል ነው ።
የድንግልና / የድቅ ነፍስን እንዳንገድል

ም ስ ጢ ር

ባል አግብተው ያልወለዱ መሃኖች ሴቶች ካለመውለዳቸው የተነሳ ፣ ማህፀነ ዝግ እየተባሉ በአሪቱ ዘመን ይሰደቡ ነበር ፤ ማር ያም ግን በድንግልና የእግዚአብሄርን ቃል ፀንሳ በድንግልና በመ ውለዷ ማህፀነ ዝግ መባል እንደነርሱ አያሰድባትም ። ስለዚህ ማህፀነ ዝግ መባል ምስጋናዋ ነው ። ማህፀነ ዝግ ባዮችም እውነ ተኞች አመስጋኞች ናቸው ይላሉ ባለቅኔው ።

ታ ሪ ክ

በአሪት ዘመን ምክንት የሚመጣው በሃጢአት ነው ስለሚባል ያልወለዱ ሴቶች ሁሉ « ዕጹተ ግሕፀን (ማህፀነ ዝግ) » እየተባሉ ይሰደቡ ነበር ።

78 መወድስ

ይትረከብ ምክር እምድኅረ መከራ ፣
ወይስግዕ ዘንተ ዘቦ እዝነ አምላክ ፤
እምጣነ ይቤ እግዚእ በዘኢይትሔሰው ቃል
በላዕለ እሥራኤል ድኅረ አንገሥ
ነሳሕኩ እስመ አንገሥክዎ ለሳኦል ቀሲል ፤
ወጸልእ እምናን
ግብረ ሙስናሃ ለትእግር ድኅረ አግሰና በጎይል ።
በለሰኒ ድኅረ መተረ እምጎዲገ ትእዛዝ በቀል
አስቆቀወ አረጋዊ ወይልየ እንዘ ይብል ፤
ወዳዊት በከየ በሞተ ኦርዮ ባዕል ፤
አንቀጸ ምንዳቤ አምጣነ ቦአ ርእሶ ከመ ይትትል ።

ትርጉም

ምክር ከመከራ በሁዋላ ይገኛል ፣
የምሳሌ ጀሮ ያለውም ይህን ይስማ ፤
በእስራኤል ላይ ካነገሰው በሁዋላ
ጌታ በማይዋሽ ቃል ቀላል
ሳኦልን ስላነገስሁት ነደምሁ (ተፀፀትሁ) ብሏልና ፤
በሀይል ካጠፋት
በሁዋላም የትእግር ጥፋት ስራን እምኖን ጠቷልና ።
ትእዛዝ/በቀልንም ከመተው የተነሳ በለስን ከቆረጠ በሁዋላ
ሽግግሌ/አዳም «ወይኔ» እያለ አለቀሰ ፤
በኦርዮ/ባለጠጋ ሞትም ዳዊት አለቀሰ ፤
በመከራ/በር ራሱን ይገድል ዘንድ ገብቷልና ።

ምስጢር

«ምክረው ምክረው ፣ እምቢ ካለ መከራው ይምክረው » እንደ ሚባል የሰውን ምክር የማይቀበል ሰውን መከራ ያርማል ፣ ያስተካክላል ፤ ይህም በአምላክና በሳኦል በአምናንና በትእግር ፣ በአዳምና በበለስ ፣ በዳዊትና በኦርዮ ታሪክ ተፈፅሟል በማለት ባለቅኔው በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ያለውን ሁኔታ በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

ታሪክ

እግዚአብሄር ሳኦልን በእስራኤል ላይ ካነገሰው በሁዋላ አግሌቅን እንዲበቀልና ጨርሶ እንዲያጠፋቸው ቢያዝዘው ሳኦል የእግዚአብሄርን ትእዛዝ ጥሶ የአግሌቅ ንጉስ አጋግንና ሌሎችንም ግርኮ በመያዱ ፈንታ ወደ ሀገሩ አውጥቷቸዋል ። ስለዚህ እግዚአብሄር እርሱን በማንገሱ ተፀፅቷል (1 ሳሙ. 15 ፣ 1—12)

አምናን በዝሙት አስተሳሰብ እህቱ ትእግርን ለሩካቤ ስለአሰባት እርሷን የሚያገኝበትን ዘዴ ፈጥሮ በፈጠረው የተንኮል ዘዴ ብትመጣለት ድንግልናዋን ገፏታል ። ነገር ግን ድርጊቱ ከተፈፀመ በሁዋላ በወደዳት ልክ እርሷን ጠላት (2 ሳሙ. 13 ፣ 1—22)።

79 መወድስ

ዘመርሻ (መጋቢ ፣ ዘጻማ ጊዮርጊስ)

በርቀተ ነፍስ ተነብአ ግዘፈ ሥጋነ ፤
እስመ ዓለመ ነፍስ ኮነ ዓለመ ሥጋ ብሔረ እክል ።
ወነገረነ በየውጣ ቅርፀተ እክል
ዙሉ ዘርእየ ከመ ሠናይ
ረኃብ ጼዊ ለልሱሕ ቄጽል ፤
አምጣነ ዙሉ ዘይቄስም
ለእሰ ይረፍቁ ሕዝብ ዲበ ማዕር ወሐመልግል ።
ወፅአሂ በዘመንነ ለገቢረ ምሳሕ በዓል
ሞት ዘይጼአኖ ፈረሰ አክዓብ ሐመልሚል ፤
ወለናዝራዊ ሶምሶን ንዋየ ሐቅሉ ዕዋል
ለመልድ ልብሰ ልደቱ መሥብሐ መሥዋዕቱ ለእስራኤል ።

ት ር ጉ ም

የስጋችን ውፍረት በነፍሳችን ርቀት ተሸሸገ ፤
የእሀል አገር የሆነ የስጋ አለም የነፍስ አለምን ሆኗልና ።
ሁሉንም ጥሩ እንደሆነ ያየ
የአልጫ ቅጠል ጨው/ ራብ
የአካልን ቅርፅ (እዝልና ቅፅል በሌላት) በየውጣ ነገረን ፤
በሳርና በቅጠላ ቅጠል ላይ
ለተቀመጡ ህዝብ ሁሉን የሚያጣፍጥ ነውና ።
ሞት የሚጋልበው ሹጉርጉር የአከአብ ፈረስም
ምሳ/ በእልን ለግድረግ በዘመናችን ወጣ ፤
የናዝራዊ ሶምሶን የጦርነት እታ የሆነ እሀያም
ለወልድ የልደቱ ልብስ ነው ፤ ለእስራኤልም የሰባ መስዋ
እቱ ነው ።

ም ስ ጢ ር

እንድን አገር ጠላት ሲወር ፈሪ ቦታ መርጦ እንደሚሸሸግ ፤ በክፉ ቀን ራብ ጊዜም እሀል ጠፍቶ የስጋ ውፍረት እንደ ነፍስ ረቀቀ ። እዝልና ቅጥል እንደሌላት እንደ ግሪክ ፊደል የውጣም (እይ) ሰው ሁሉ ቀጠነ ፤ መነመነ ። ምግብ በጨው እንደሚጣፍጥ ፤ በክፉ ቀን ራብ ጊዜም ማንኛውም ቅጠላ ቅጠል ጣፈጠ ሰውም ምግብ ሳያማርጥ እንደ ከብት ቅጠል በላ ። ዳግመኛም በበአል ጊዜ ሰው በፈረስ ተቀምጦ እንደሚወጣ ፤ ሞትን ያስከተለ ራብ በእስራኤል ንጉስ አከአብ ዘመን እንደ በረታ በኢትዮጵያም በክፉ ቀን በጣም ፀና ። የፈረሱ መልክ ሹጉርጉር እንደሆነ ራብም የሰውን መልክ ለዋወጠው ። ሶምሶን ጠላቶቹን በእሀያ መንጋጋ አጥንት እንደጨረ ሳቸው እግዚአብሄር ወልድ ከቅድስት ማርያም በቤተ ልሄም በከ ብቶች በረት ሲወለድም በእሀዮች ትንፋሽ ተሟሟቀ ። በመልካምም ቀን የሰባ ከብት ለመስዋእት እንደሚመረጥ ሁሉ ፤ የክፉ ቀን ራብተኞ ችም የእሀያን ስጋ በመብላት በራብ ምክንያት ከሚመጣ ሞት ለመዳን መሞከራቸውን በመግለጥ ባለቅኔው የራብን አስከፊ ገፅታ ያሳያሉ ።

80 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዜናዊ ረኃብ እመ ተዝያነወ ሠሉ
ባሕታዊ ልሂት ኢታድክመኒ ይቤሉ ።

ት ር ጉ ም

ወሬኛ/ ራብ ሁሉን በአወራ ጊዜ
ሸግሌ/ መናኝ (ባህታዊ) «አታድክመኝ» አለው ።

ም ስ ጢ ር

ወሬኛ ሰው የሆነ ያልሆነውን ሲቀባጥር ፤ ሰሚው ከመሰልቸቱ የተነሳ «እባክህ አታድክመኝ» እንደሚለው ፤ ባህታዊን (መናኝን) ራብ እደክመው ይላሉ ባለቅኔው ።

81 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ነገረ ሐሜት ኢይንብብ ደመና መልዕልተ ኢዮር ዘሀሉ ።
አምጣነ ይሰምዕ ወይን ዘኢይሰምዕ መሲሉ ።

ት ር ጉ ም

በሰማይ ላይ ያለ ደመና የሀሜት ነገርን አይናገር ፤
ወይን የማይሰማ መስሉ ይሰማልና (ያጻምጣልና) ።

ም ስ ጢ ር

አሜተኛ የተኛውን ሰው ሲያማ የሚታማው ሰው እንቅልፍ የወሰደው መስሉ እያንኮራፋ ያጻምጠዋል ፤ እንዲሁም ወይን በደመ

ናና በዝናብ ጊዜ (በክረምት) የደረቀ ቢመስልም ውስጡ ለምለም ነት ያለው መሆኑን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

82 ዘአምላኪየ

ያስተጋብእ ጠለ ንዋየ ዘመን ኵሉ
ጕንደ ወይን ብእሲ ዕራቁ ዘሀሉ
ለዘይመጽእ ዘመን ይከውነኒ ብሂሉ ።

ት ር ጉ ም

ራቁቱን ያለ የወይን ግንድ / ሰው
ለሚመጣው ዘመን ይሆነኛል ብሎ
የዘመን ገንዘብ/ልምላሜን ሁሉ ይሰበስባል ።

ም ስ ጢ ር

አንዳንድ ሰው እየተራበና እየተራቆተ ለወደፊት እጦርበታለሁ በግለት ብዙ ገንዘብ ያጠራቅማል ። ወይንም በበጋ ወራት በግልጥ የያዘውን ልምላሜ በክረምት ወራት በውስጡ ደብቆ እንደያዘ ይዘ ልቃል ግለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

83 ሚበዝኁ

በተክለ ጊዮርጊስ

በመዐዛ ሥቃይ ወገድል
ለዐፅመ ጊዮርጊስ አፈው አልቦ ዘይመስሎ ፤
እስመ እስከ አድማስ በጽሐ በመትከፈ ነፋስ ወዐውሎ ፡
ወበመዐዛሁ ሰሐበ ዘግ ቶማስ ሰይፈ እንተ ታስተቃትል
ኵሉ ።

ት ር ጉ ም

የጊዮርጊስ አጥንት/ሽቱን
በገድልና በስቃይ ሽታ የሚመስለው የለም ፤
በነፋስና በአውሎ ትከሻ እስከ አድማስ ደርሷልና ፡
በሽታውም ሁሉን የምታጋድል የቶማስ ሽርሙጣ/ሰይፍን
ስቧልና ።

ም ስ ጢ ር

በመአዛው ወደር የሌለው ሽቶ በነፋስ ተወስዶ ከሩቅ ቦታ ሲሸት ሽርሙጣን ያስደስታል በማለት ፡ ከዚህ አንፃር ጊዮርጊስም ብዙ ስቃይና መከራን ከተቀበለ በሁዋላ በሰይፍ መቆረጡን ባለቅኔው መስክረዋል ።

84 ዋዜማ

መኑመ ይሰትዮ
ለዘበጽሐርት ወረደ ነደ ነበልባል ጼተሎ ?
ቂርቆስ እምጣነ ተንሥአ ጸገብኩ ብሂሉ
ወደመ ደመ ለመርቆሬዎስ ይቤሉ
ባሕቱ ዘጸምዐ ነፋስ ዐውሎ
ጊዮርጊስ ኢጎደገ ጣሕሉ ።

ት ር ጉ ም

በጋን የወረደ
የነበልባል ነዲድ/ ጉሽ ጠጅን ማን ይጠጣዋል ?
ቂርቆስ «ጠገብሁ» ብሎ ተነሥቷልና
መርቆሬዎስንም ደም ደም ብሎታልና ።
በአውሎ ነፋስ የተጠማ ጊዮርጊስ ግን
አተላውንም አልተወም ።

በጋን የወረደ (የቀረበ) ጠጅ ሀይለኛ ሲሆን ፣ አንዱ ሰው ቀምሶ ሲተወው ፣ ሌላው ደግሞ «ደም ደም አለኝ» ብሎ ይተወዋል ። የተጠማ ሰው ግን እስከ አተላው ያንጫልጠዋል ። እንዲሁም የጠጁ ምሳሌ በሆነው በፈላ የጋን ውሃ ውስጥ ቂርቆስ በገባ ጊዜ አልተቃጠሰም ። መርቆሬዎስም በሰይፍ በተቆረጠ ጊዜ ደሙ ተንጠባጥቧል ፤ በነፋስ የተዘራ ጊዮርጊስ ግን በእሳቱ ተቃጠለበት ግለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

85 ዘይእዜ

ዘመንግሥቱ (መሪጌታ)

ተናዘዘ ስምዖን ብዝኀ ዕዳሁ ፤
በውስተ ሀገር ምንት ያነብረኒ ብሂሉ
ለስደት እምድኅረ ተንሥአ አኮኑ ትቤሉ
ግርያም አነ ለዕዳከ እከፍሉ ፤
ዕዳሁሰ ትክፍል እመ ትምህሉ
ከመ ልቡናሁ ሀለወ ኢሀልወ ዕዳ መሲሉ ።
ዕዳሁሰ ትክፍል እመ ትምህሉ

ትርጉም

ስምኦን የእዳውን ብዛት ተናዘዘ ፤
«በሀገር ውስጥ ምን ያስቀምጠኛል» ብሎ
ለመሰደድ ከተነሳ በሁዋላ ግርያም
«እኔ እዳህን እከፍላለሁ» ትለዋለችና ፤
እዳውን ግን ትከፍልለት ዘንድ ብትምልለት
እዳ የሌለበት መስሎ እንደ ልቡ ኖረ ።
እዳውን ግን ትከፍልለት ዘንድ ብትምልለት

እዳ የበዛበት ሰው ከአጉሩ ሊሰደድ ሲነሳ ፣ «እዳህን እኔ እከፍ ልልሃለሁ» ብላ እናቱ እንደምትምልለት ፣ የባለእዳው ምሳሌ የሆነ በሳኤ ሰብእም ሀጢአቱ በዝቶ ወደ ገሃነመ እሳት የሚያወርደው ቢሆንም ቅድስት ግርያም በቃል ኪዳንዋ ሀጢአት እንዳልሰራ ሰው ያደረገችው መሆኑን የቅኔው ምስጢር ያስገነዝባል ።

86 መወድስ

ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፣ ዘኤልያስ)

መኑ ሰብእ እንተ የሐምዮ
ለባዕል ሞት እምቅድመ ዓለማት ዘሀሉ ?
አኮኑ ይጼውዕ እንዘ ያስተዔሪ ሙሉ
ለውሉዶ ሰብእ አመ አቅረበ
ዕዴ ምድር ዘቦ መቃብረ እክሉ ።
ግርያምኒ ንግሥተ ሴሎ
ኢተርፈት ድኅረ በርኀቀተ ሀገር ተደንግሎ ፤
አኮኑ በዙረ ዚአሃ አመ ይገብር በዓሉ
ወይነ ሥጋዌ አስተዳለወ ኪያሃ ለተቀብሉ
ባሕቱ ኤልያስ ተርፈ እምነ ምሳሁ ተገንሉ
መድኀኒተ ሠረገላ ሰተይኩ እንዘ ይብሉ ።

ትርጉም

ከአለማት በፊት ያለ
ሞት/ባለፀጋን የሚያማው ማን ነው ?
ሁሉን እያስተካከለ ይጠራልና
የምድር ትል ያለበት እሁሉ/መቃብርን
ለሰው ልጅ ባቀረበ ጊዜ ።
የሴሎ ንግስት ግርያምም

በድንግልና/አገር ርቀት ወደሁዋላ አልቀረችም ፣
የበኩር ልጅዋ በአሉን ባደረገ ጊዜ
እሷን ለመቀበል የወይን ጠጅ/ሰው መሆንን አዘጋጅቷልና
ኤልያስ ግን ሰረገላ/መድሀኒትን
ጠጣሁ ብሎ ከግብዣው ቀረ ።

ም ስ ጢ ር

ሁሉን አስተካክሎ የሚጠራና ነቀዝ የሚበላውን እህል የሚ መግብ ባለፀጋን የሚያማው ሰው የለም ። እንዲሁም የባለፀጋው ምሳሌ የሆነ ሞት ሁሉን ትል ወደሚፈጠርበት መቃብር ያወርዳል ። ባለፀጋው በሩቅ አገር የምትኖረውን ወዳጁን እንደሚጠራት በድን ግልናዋ አምላክን የወለደች ቅድስት ማርያምም ከሞት አላመለጠ ችም ። ባለፀጋው የበአል ግብዣን ሲያደርግ ወይን እንደሚያዘጋጅ ወልድ የሚሞት ስጋዋን ለበሰ ። መድሀኒት የጠጣም ሰው ከባለፀ ጋው ድግስ ገብቶ እንደማይጋበዝ ነቢዩ ኤልያስ በሰረገላ ወደሰማይ ስለአረገ ከሞት ጥፋት ለጊዜው ዳነ በማለት ባለቅኔው ግንኛውም ፍጡር ከሞት እጅ የማያመልጥ መሆኑን በቅኔያቸው ምስጢር ያስረዳሉ ።

87 መወድስ

ዘመንሥግቴ (መሪጌታ)

ብእሲት ባሕር ምልእተ ዕመግ
ለብእሲሃ ምልከግም እፎኑመ ታቀልሉ ?
እመ እገሪሁ ያቀርብ ተጎፅበኒ ብሂሉ
እግረከ ኢየጎፅበከ አኮኑ ትቤሉ ፤
ወአምጽአት ምክንያተ
እንዘ ትብል ግይ ውስተ ቤትየ ኢሀሉ ።
ለፈርዖንሰ እመ ሠምረቶ እንበለ ንስቲት ተሀጕሉ

ሐዊራ ውስተ ፍናቱ ፈረሰ ትትቄበሉ ፤
ወበተዋንዮ ብዙኀ እንዘ ታስተሚኒ ኵሉ
ምዕረ ትጸዐኖ ወምዕረ ትሰቀሉ ።

ት ር ጉ ም

በደልን የተመላች ባህር /ሴት
ሙሴ / ባልዋን ምንኛ ታቀለዋለች ?
ታጥበኛለች ብሎ እግሩን ቢያቀርብ
እግርህን አላጥብም ትለዋለችና ፤
ምክንያትም እመጣች
በቤቴ ውስጥ ውሀ የለም ስትል ።
ያለ ትንሽ ጥፋት ፈርአንን ግን ብትወደው
ከመንገዱ ሂዳ ፈረሰን ትቀበለዋለች ፤
በብዙም ጨዋታ ሁሉን እያስመኘች
አንድ ጊዜ ትጫነዋለች አንድ ጊዜም ትሰቀለዋለች
(ትቀመጥበታለች) ።

ም ስ ጢ ር

ሴት ባልዋን ስትንቅ ፈውሀ የለኝም ፣ እግርህን አላጥብም » ትለዋለች ፤ ባልዋን የምትወደው ከሆነ ግን ፈረሱን ከመንገድ ትቀ በለዋለች ። በሴት የተመሰለች የኤርትራ ባህርም ለነሙሴ መን ገድ ስትሰጥ ፈርአንን ግን ከነፈረሱና ከነሰራዊቱ ማስጠሟን ባለቅ ኔው ያስገነዝባሉ ።

88 ዋዜማ

ዘሰግ ጎይሉ (አለቃ)

ሰሎሞን በብዝኀ ክብሩ
ድኅረ ቤተ ርእሱ አፅበየ ወቤተ እግዚኡ ፈጸመ
ኢጸመወ ለቤተ ባዕዳን ከመ ያትርፍ ስመ ።

ሥርዐተ ሕንጻ ዓለም እመ ከመዝሰ ቆመ
ለቤትከ ጴጥሮስ አሠኒ ቅድመ ፡
ወለሙሴ ትሔሊ ዳግመ ።

ት ር ጉ ም

ሰሎሞን በክብሩ ብዛት
የራሱን ቤት ከፍ ካደረገና የጌታውንም ቤት ከጨረሰ በሁዋላ
ስምን ያተርፍ ዘንድ ለሌሎች ቤት አልደከመም ።
የህንፃ ስርአት አለም እንደዚሁ ቢቆም ግን
ጴጥሮስ መጀመሪያ የቤትህን ህንፃ አሳምር ፡
ለሙሴ ግን ሁለተኛ ታስባለህ ።

ም ስ ጢ ር

ሰሎሞን የራሱን ቤተ መንግስትና የእግዚአብሄርን ቤተ መቅደስ በመስራት ስሙን አስጠራ እንጂ የሌሎች ሰዎች ስራን የስሙ መጠሪያ አላደረገም ፤ ሀዋርያው ጴጥሮስ ግን በደብረ ታቦር ለራሱ ሳይል ፡ ለአምላክና ለሁለቱ ነቢያት ለሙሴና ለኤልያስ ቤት ለመስራት መመኘቱን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

ታ ሪ ክ

ሰሎሞን አባቱ ዳዊት ሲመኘው የኖረውን ቤተ መቅደስ ለመ ስራት አጋጣሚ ጊዜ አግኝቶ « ወልድ ወሕንጻ ያዐብዩ ስመ (ልጅና ህንፃ ስም ያገናሉ ፡ ያስጠራሉ) » በማለት በሲራክና በሰሎሞን እንደተነገረ አስደናቂ ቤተ መቅደስን ለአምላኩ ሰርቷል (1 ነገስ.8) ። የራሱንም ቤተ መንግስት አሳምሯል ። ይሁን እንጂ ዝናን ለማት ረፍ የሌሎችን ቤት ለመስራት አልተጋም ነበር ።

ጴጥሮስ በደብረ ታቦር ከክርስቶስ ጋር ሳለ ለክርስቶስና ለሙሴ ለኤልያስም አንዳንድ ቤት እንዲሰራ ተመኘ እንጂ ለራሱ አላሰ በም ነበር (ማቴ. 17) ።

89 ዋዜማ

ዘአድግሉ (ንፁረ እድ)

ሕንፃ ቤተ ሰማዕት እለ ነጸሩ
ወወልደ ነጋሢ ዘርእዩ ያስተበፅው ፍጹመ
እስመ ወልድ ወሕንጻ ያዐብዩ ስመ ።
ወከመ ኢይትሀጐል ድኅረ በሕንጻ ቤቱ ዘደክመ
ምስለ እግዚኡ ኪዳነ ጊዮርጊስ አቀመ ፤
ተጋድሎ አኮኑ አቅደመ ።

ት ር ጉ ም

የሰማእት ቤት ህንፃን ያዩ ሰዎችና
የንጉስንም ልጅ ያዩ ሰዎች ዘፍፁም ያመሰግናሉ ፤
«ልጅና ህንፃ ስምን ያስጠራሉና »
በሁዋላም በቤቱ ህንፃ የደከመ እንዳይተጓጎል
ጊዮርጊስ ቃል ኪዳንን ከጊታው ጋር አቆመ ፤
መጋደልን አስቀድሟልና ።

ም ስ ጢ ር

መልክ መልካም ነልግላ ሲታይ ፡ ጹር « ይህስ የንጉስ ልጅ ይመስላል » ይባላል ። እንደዚሁም ሁሉ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ መቅደስ ህንፃ እጅግ የተዋበ መሆኑንና ፡ ልጅም ስምን እንደሚ ያስጠራ ህንፃው የአሰሪው ስም መታሰቢያ መሆኑን ቅኔው ይገልጣል ። በዚሁም ላይ ልጅ እንዲወጣ የሰራ መበጀት እንደሚ ያስፈልገው ፡ የጊዮርጊስንም ቤተ መቅደስ የሰራው ሰው ዋጋ ውን እንዲያገኝ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአምላኩ ጋር ቃል ኪዳን መግባ ቱን ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

ያራዳ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ከአድዋ ዘመቻ በሁዋላ አፄ ምኒልክ አሰርተዋል ። በዘመኑም ከነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በአሰራሩ በጣም አስደናቂ ሆኖ ተገኝቷል ። አስደናቂ ስራውም ከአድዋ ድል ጋር ተጣምሮ አሰሪውን አፄ ምኒልክን ስመጥር አድርጓቸዋል ።

90 ዋዜማ

ለመልአክ ኢናከብሮ
ለእመ አሥረፀ ክንፈ በመጠነ ነዊኅ ቆሙ ፤
ለዖፍ ወለትንንያ እስመ ክንፍ ቦሙ ።
ወበሚበቱ ለሰብእ ኢናከብሮ ቀዲሙ ፤
ጸወዳ ሚበት እስመ ሀለምሙ
ለዕፀው ወአእባን ዙሉሙ ።

ትርጉም

በረኸም ቁመቱ ልክ
ክንፍን ቢያበቅል መልአክን አናከብረውም፤
ለወፍና ለትንኝ ክንፍ አላቸውና ።
በመጀመሪያም ሰውን በሸበቱ አናከብረውም ፤
ለድንጋዮችና ለእንጨቶች ሁሉ
ነጭ ሽበት አላቸውና ።

ምስጢር

መልአክ የሚከበረው ለወፎችና ለትንኞች ተፈጥሮ ያደለቻቸው ክንፍን በማብቀሉ እንጻልሆነ ፥ ሰውም የሚከበረው በስራውና በቁም ነገሩ እንጂ በድንጋዮችና በእንጨቶች ላይ የሚታይ ሽበትን

በማብቀሉ አይደለም በማለት ያለምንም ተግባር በልብስና በማእረግ ብቻ መከበር የሚሹ ሰዎችን ባለትኔው በትኔያቸው ምስጢር ይገስፃሉ ።

91 ዘይእዜ

ዘተሰግ (አለታ)

ሄዋ ፋርስ ይሚጥ መንገለ ሮሐ
ትሩፋን ቤቱ ዕፀው በአንቀጸ ብልጣሶር ቆሙ ፤
እምጣነ አልቦ ዘየዐብዮ
ለዮሐንስ ሕንጻ ላሊበላ ዘመካን እሙ ።
ወመንገለ እሳት ሑሩ እምኔየ ይቤሎሙ
ለጎጥአነ ምድር ዕፀው እለ በፀጋሙ
እደ ላሊበላ ዘሠርዐ ሚጠት ብርሃናት በወቅሙ ።
ለጎጥአነ ምድር ዕፀው እለ በፀጋሙ

ትርጉም

የፋርስ ምርኮን ወደ ርሀ ይመልስ ዘንድ
የቤቱ ትራፊዎች እንጨቶች በብልጣሶር በር ቆሙ ፤
እናቱ መሆን የሆነች
የላሊበላ ህንፃ / ዮሀንስን የሚበልጠው የለምና ።
የብርሃናት ምልልስን በልኩ የሰራ የላሊበላ እጅም
በግራው ያሉትን ሀጢአተኞች / እንጨቶችን
ከእኔ ወደእሳት ሂዱ አላቸው ።
በግራው ያሉ ሀጢአተኞች/ እንጨቶችን

ምስጢር

ተግርከው ወደፋርስ ባቢሎን ከወረዱት እስራኤላውያን ብዙ ምቹ በሁዋላ ወደአገራቸው ተመልሰዋል ፤ ጥቂቶችም ከመግረክ ቀር ተው በብልጣሶር እደባባይ ተገኝተዋል ። ንጉስ ላሊበላም የክርስ

ቲያንን ወገኖች ወደርሃ ለመሳብ ቻለ ። እንጨቶችም ከላሊበላ ሀንፃ ተገለሉ ፤ እናቴ መከና የናረች ዮሀንስን የሚበልጠው እን ደሌለ ቦታው የተለየች የላሊበላን ሀንፃም የሚመስል ቤተ መቅ ደስ የለም ። ክርስቶስም ሀጥአንን ወደ እሳት ሂዱ እንደሚላቸው ከላሊበላ ሀንፃ የተገለሉት እንጨቶች ግፃዱ ሆኑ ። ብርሃናችም (ፀሀይ ጨረቃ ከዋክብት) እንደሚመላለሱ የላሊበላ ሀንፃም እንደ ፀሀይ ጨረቃና ከዋክብት ያበራል በግለት ባለቅኔው ለላሊበላ ሀንፃ ያላቸውን አድናቆት በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

92 መወድስ

ዘደስታ (አለቃ ፡ ዘተድባበ ማርያም)

ዐቀብተ መቃብር ሕዝብ ዕዴያተ ሥጋ
እምግርማ ዮሐንስ አብ ርኁቀ ይቅውሙ ፤
ወግርማ ዮሐንስ ገጽ አመ ተወለጠ ቦሙ ፤
ዮሐንስ ፍሥሓ ኀዘነ ኮኖሙ ፤
እንዘ በመቃብር የሐልሙ
አምጣነ ሐሰተ ኮነ ሥጋ ዮሐንስ ሕልሞሙ ።
በሊሕኒ እምቀዳሚ ለክሢወ ደም እግሮሙ
አምጣነ ጎሳር ወቅጥቃጤ ውስተ መቃብር ፍኖቶሙ ።
ወከመ መቃብር ከሡት ጐራዒቶሙ ፤
ጎምዘ አርዌ ምድር ዘአመ ኖኅ እስመቦ በአፉሆሙ ።

ት ር ጉ ም

መቃብር ጠባቆች የስጋ ትሎች / ወገኖች
ከአባት / ዮሀንስ ግርማ / ፊትም በተለወጠባቸው ጊዜ

ደስታ / ዮሀንስ እዘን ሆነባቸው ፤
በመቃብር ውስጥ ሲያልሙ
የዮሀንስ ስጋ/ ህልማቸው ውሸት ሆኗልና ።
እግራቸውም ደምን ለማፍሰስ ከቀድሞ ፈጣን ነው ፤
በመቃብር/ መንገዳቸው ውስጥ መከራና ችጥቃጤ አሉና ።
ጉረሮአቸውም እንደ መቃብር የተከፈተ ነው ፤
በናህ ጊዜ የነበረ የምድር እባብ መርዝ በአፋቸው አለና ።

ም ስ ጢ ር

ጠባቂዎች የክርስቶስን መቃብር ርቀው እንደቆሙ ፡ ወልደ ነጎድጓድ ዮሀንስ የተባለውንም ሀዋርያ የመቃብር ትሎች አላገኙ ትም ። ክርስቶስም በደብረ ታቦር በተለወጠ ጊዜ ያዩት ሰዎች እንደ ደነገጡ ትሎችም በዮሀንስ አካል ላይ አልተገኙም ። ምክንያቱም የሌሊት ህልም ሲነጋ እንደማይገኝ ዮሀንስ ወልደ ነጎጓድንም ከመ ቃብር ውስጥ ሊያገኙት ባለመቻላቸው ነው ። የክፉ ሰዎች እግር ደምን ለማፍሰስ እንደሚፋጠን ፡ አንደበታቸውም መርዝን እንደ ሚናገር ትሎችም ሌሎችን ሚች ወገኖች ይበላሉ ፤ ደማቸውንም ያፈሳሉ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

93 ግእዝ ክብር ይእቲ

ተመነየ ሞተ አምላክ ኖላዊሆሙ
ለአዳም ወሔዋን አባግኢሁ ዘሎሙ
አርዌ እኩይ እስመ በልዖሙ ቀዲሙ
ቈጽለ ቈጽለ እንዘ ይሬእዩ በዐይኖሙ ።

ት ር ጉ ም

እረኛቸው/ አምላክ ሞትን ተመኘ ፤
ሁሎች በጎቹ/ አዳምና ሄዋንን
ክፉ አውሬ ቀድሞ በልቷቸዋልና
በአይናቸው ቅጠል ቅጠልን ሲያዩ ።

ምስጢር

ቅጠል ቅጠል ሲያዩ በጎቹን አውሬ የፈጀበት ጠባቂ ሞቱን እንደሚመኝ ፣ የአውሬ ምሳሌ የሆነ ሰይጣንም የበጎች ምሳሌ የሆኑ አዳምና ሄዋንን በበለስ ቅጠል መብል የተነሳ ያሳተበት የጠባቂ ምሳሌ ክርስቶስ ስለ ሰው ብሎ መሞቱን ባለቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

ታሪክ

አዳምና ሄዋን የሰው ፍጥረት መጀመሪያዎች ናቸው ይባላል። አዳም ያለዘር ከመሬት የተፈጠረ ተባት ሲሆን ሄዋን ከአዳም ጎን አጥንት የተፈጠረች እንስት ናት ። ሁለቱንም አምላክ የፍጥረቱ ሁሉ ገዥዎች በማድረግ አልቋቸው (ሾሟቸው) በህይወት ገነት አኖራቸው ። ከበለስ ቅጠል በቀር ሁሉንም ፣ እንዲበሉና እንዲጠጡ ፈቀደላቸው (ዘፍጥ. 1 ፡ 27—28 ፤ 2 ፡ 19—25) ። ስለዚህም ሰይጣን ቀናባቸውና አሳስቶ የበለሲቱን ቅጠል እንዲበሉ አደረጋቸው ። ሲበሉም የብርሃን ፀጋቸው ተገፈፈባቸውና ተራቆቱ ። ከዚህም የተነሳ አምላክ ንስሃቸውን ተቀብሎ ስለእነርሱ ሰው ሆነላቸው ፣ በመስቀል ተሰቅሎ ሞተላቸው ይባላል (ዘፍጥ, 3 ፡ 1—13 ። ኤፌ. 2 ፡ 4—5) ።

94 ዕዝል ክብር ይእቲ

በጽርሐ ይሁዳ ነዳይ አመ ተጠብሐ በግዐ ሙሴ ቀዲሙ
ለመኑ ይከውን እስመ ርኁባን ኮኑሙ
አዝማደ ይሁዳ ነዳይ ዘቅንአተ ልብ ማኅተሙ
ወእምነ ዝንቱ በግዕ ኢተካፈሉ እምነ ሥጋሁ ወደሙ።

ትርጉም

የሙሴ በግ በድህ/ ይሁዳ አዳራሽ ቀድሞ በታረደ ጊዜ
ለማን ይሆናል ? የልቡ ትናት ማተሚያው የሆነ

የድህ/ ይሁዳ ዘመዶች ሁላቸው የተራቡ ናቸውና፤
ከዚህም በግ ከስጋውና ከደሙ አልተካፈሉም ።

ምስጢር

ራብተኞች ሲበዙ «የአንድ በግ ስጋ ለስንት ይሆናል?» እንደሚባል የይሁዳ ወገኖች ሁሉ የበግ ምሳሌ በሆነ በክርስቶስ ስጋና ደም አለመጠቀማቸውን ባለቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል።

95 ዕዝል ዕጣነ ሞገር

ዘተከለ ጽዮን (አለቃ)

ወልጠተ ሌዊ ወሰምዖን ቃለ መሐላ ጽድቆሙ ፤
እስመ ተጐሰቈ ጽድቀ ዐመፃሆሙ ።
እመሰ ሰብአ ገሊላ ላዕለ ዮሐንስ ፈጸሙ
ሕሰመ ከናፍር መሐላሆሙ
በላዕለ ዐመፃ ወሰኩ ዐመፃ ፤ እስመ ተከሥተ ግብሮሙ
ከመ ያፍ እምድኅረ ሠረረ ዮሐንስ ክብሮሙ ።

አሠረ ንጉሥ

እስተቀጸለቶ ባዕደ አክሊለ ስምዕ ተድባበ ማርያም እሙ
ለገላውዴዎስ መሲሕ ዘበኩራ አመ ዕለተ ሞቱ ቀዲሙ ፤
ወዛቲ ተድባብ ገራኅተ ደሙ ፤
እስመ ኀበ ግብሩ ይመርሕ ጊዜ ሕማሙ
ለሰማዕት ገላውዴዎስ ስሙ ።

ትርጉም

የሌዊና ስምኦን የመሀላ ቃልን መለወጥ እውነታቸው ነው ፤
በደላቸው (አመፃቸው) ከፅድት ተቆጥሯልና ።
የገሊላ ሰዎች ግን የከንፈሮች ውሸት የሆነ

መሃላቸውን በዮሀንስ ላይ ቢፈፅሙ
በደልን በበደል ላይ ጨመሩ ፤ ክብራቸው / ዮሀንስ
እንደ ወፍ ከበረረ በሁዋላ ስራቸው ተገልጧልና ።

አ ሰ ረ ን ጉ ስ

አስቀድሞ የበኽር ልጅዋ ለሆነ ንጉስ ገላውዲዎስ በሞቱ ጊዜ
እናቱ/ተድባበ ማርያም የሰማእትነት አክሊልን አቀዳጀችው፤
ይችውም ተድባበ ማርያም የደሙ እርሻ ናት፤
ምስክር የሆነ የገላውዲዎስ ስሙ
በመከራው ጊዜ ወደ ስራው ይመራልና።

ም ስ ጢ ር

ስምኦንና ሌዊ መሃላቸውን በማፍረስ ሴኬምን በዲና ምክንያት መግደላቸው ሃጢአት ያልሆነባቸው ሴኬም የፈፀመው ስራ አመፅ ስለነበረ ነው ። የገሊላ ሰዎች ግን ለሄሮድያዳ የተሰጠውን መሃላ ጠብቀው መጥቁ ዮሀንስን ከሚገድሉ መሃላቸውን አፍርሰው ቢያድኑት ናሮ ከፅድቅ ይቆጠርላቸው ነበር በማለት ባለቅኔው የገሊላ ሰዎች በዮሀንስ ላይ የፈፀሙትን በደል አውስተዋል ።

ቤርሳቤህ ልጅዋ ሰሎሞን ዘውድ እንዲቀዳጅላት እንደ ጣረች ተድባበ ማርያምም ለእደቷት ለእዬ ገላውዲዎስ የሰማእት ገላውዲዎስን ክብር አሰጠቻቸው በማለት ባለቅኔው እዬ ገላውዲዎስ የሰማእትነት ክብር በሚያሰጥ አሟሟት የሞቱ መሆኑን በቅኔያቸው ምስጢር ይመሰክራሉ ።

ታ ሪ ክ

ያእቆብ በኤሞር አገር ሳለ ዲና የተባለች መልከ መልካም ልጅ ነበረችው ። ያገሪቱ ሴቶች ልጆች ሲጫወቱ ልታይ በወጣች ጊዜ ያገሪቱ ጌታ የኤሞር ልጅ ሴኬም አያትና ልቡ በፍቅሯ ተመሰጠ (ተነካ) ። ስለዚህ ወስዶ አስነወራት ። አባቷ ያእቆብም ስምቶ የል

ቡን በልቡ አድርጎ ልጆቹ ስምኦንና ሌዊ ከውጭ እስኪመጡለት ዝም አለ ። ስምኦንና ሌዊ የእህታቸውን መደፈር ሰምተው መጡ ። ኤሞርም ልጁ በፈፀመው ነውር ይቅርታን ሊጠይቅና ልጅቱን ለልጁ በሚስትነት እንዲሰጡት ሊለምናቸው መጥቶ ተለማመጣቸው ።ልጁ ሴኬምም አብሮት ተነናበሳቸው (እጅ በመንሳት ተለማመጣቸው) ። ስምኦንና ሌዊ ግን በእህታቸው በዲና ውርደትና በእነርሱ መደፈር በጣም ስለተናደዱ «አንተና ወገኖችህ እንድ ባንድ እንደእኛ ብት ገረዙና ብትመስሉን ዲናን በሚስትነት ለአንተ እንሰጥሃለን ፤ እኛም የእናንተን ሴቶች ለልጆቻችን እናጋባለን» ብለው የተንኮል መልስ ሰጧቸው ። ሴኬምም በዲና ፍቅር ስለተነደፈ ወዲያውኑ ተገረዘ ፤ ሌሎችም የከተማው ሰዎች በርሱ መሪነት ተገረዙ ። ቡተገረዙ በሶስተኛው ቀን ቆስለው እንደተኙ ስምኦንና ሌዊ እደጋ ጥለው በሰይፍ መታቸውና ቁሞታቸውን ተወጡ። ስለዚህም የቃል ኪዳናቸው ውል ከሀይወት ወደሞት ተለወጠ (ዘፍጥ . 34፡1—31) ።

የገሊላ ንጉስ ሄሮድስ የተወለደበትን ቀን ሲያከብርና ሹማምቱን ሲጋብዝ የዘማዪቱ የሄሮድያዳ ልጅ ዘፈነችለትና አስደሰተችው ። ስለዚህ የመንግስቱን እኩሌታ ስንኳ ቢሆን እንደሚሰጣት ማለላትና «ምን ላደርግልሽ ትፈልጊያለሽ?» አላት። እርሷም እናቷ ሄሮድያዳ የሄርድሮስ ወንድም የሆነው የፊልጶስ ሚስት ስትሆን ፊልጶስ ከሞተ በሁዋላ ሄሮድስ ስለወረሳት፤ ዮሀንስ «የወንድምህ የፊልጶስን ሚስት ማግባት አይገባህም» እያለ ያወግዝባት ነበርና ፤ «ዮሀንስ ከሞተ በእናቴ ምክንያት መንግስቱን አላጣውም» ብላ « የዮሀንስን ራስ ቆርጠህ ስጠኝ» አለችው ። ዮሀንስ በብዙ ህዝብ የታወቀ ገናና ስለነበር ንጉስ ሄሮድስ መሀላውን ለማፍረስ ተቸገረ ። ስለዚህም የዮሀንስን አንገት በሰይፍ አስቆርጦ ለዘማይቱ ልጅ ራሱን ሰጣት ። እርሷም « ንጉስና ንግስት ስትዘልፈ አትፈሪ የነበርሽ ምላስ እንዲህ ሆንሽን? » በማለት በያዘችው ነገር ስትወጋት ራሱ እንደመልአከ ክንፍ አውጥታ ጣራውን ሰንጥቃ ወደአየር በረረች ። ዘማይቱንም ከእነልጅዋ መራት ውጪታል ይባላል (ማቴ.14 ፡ 1—12) ።

96 መወድስ

ሰይፈ ጎይለ መንግሥት ትንት መጠነ ምናሴ
ጎያል ዮሐንስ ውስተ ሐቌከ ሰላማ
በውቤ ሥንከ ወበላህይከ ለማ፤
ወትቤ ድንግል ቃለ አፉከ
እስመ ርእየ ለኢትዮጵያ አመቱ ሕማማ
ለለዕለቱ ዘያደክማ ፤
ወታዐብዮ ነፍስየ ለውቤ አምላከ ራማ ።
እምአሶርሂ ዘይፈጥር ዲበ ትእዛዝከ ጸማ
ሠራዊተ ቤትከ ተካፈሉ ሰቂማ ዲበ ሰቂማ ፤
ወእመ ተራከባ ንግሥ ወቤተ ክህነት እማ
ጽድቅ ወሰላም በመዋዕሊከ ተሳለማ ።

ት ር ጉ ም

ሀይለኛ (ብርቱ) ዮሀንስ ፤ በሰላማ / ወገብህ
በውቤ/ውበትህና በለማ/ ወዝህ የመንግስት ሀይል/ ሰይፍን
በምናሴ ልክ(እንደምናሴ) ታጠቅ ፤
የአፍህ ቃል/ ድንግልም በየቀኑ
የሚያደክማት የአገልጋዩ ኢትዮጵያ ህመምን
አየ እኮ አለች፤
የሰማይ አምላክ/ውቤንም ነፍሴ ታከብረዋለች አለች ።
በትእዛዝህ ላይ ድካምን በሚፈጥር አሶርም
የቤትህ ወታደሮች ምርኮን በምርኮ ላይ ተካፈሉ ፤
መንግስትና እናቷ/ ቤተ ክህነትም በተገናኙ ጊዜ
ሰላምና እውነት በዘመንህ ተዋደዱ(ተስማሙ) ።

ም ስ ጢ ር

ሰይፉን ከወገቡ የታጠቀ አርበኛ አለባበሱና የጦር መሳሪያ እያ
ያዙ ከተፈጥሮ ውበቱ ላይ ተጨማሪ ውበት እንደሚሆንለት፤ አፄ
ዮሀንስ በእቡነ ሰላማ ተቀብተው መንገሳቸውንና ውቤና ለማ በተ
ባሉት እሽከሮቻቸው መታጀባቸውን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ።
ደግሞ ቅድስት ማርያም መከራዋን ያራቀላት አምላኳን እንዳመሰ
ገነችው ፤ የአፄ ዮሀንስ ትእዛዝም በየጊዜው የሚቃወሙትን የኢት
ዮጵያን ጠላቶች ማጥፋቷንና ሰራዊታቸውም በምርኮ ላይ ምርኮ
ማግኘቱን ባለቅኔው ተርከዋል ።

97 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ዘአድማ (መልአከ ብርሃን)

እስራኤል ዕፀው አውዕአዎ እግኅበሮሙ ልምላሜ
ለእንተ ደወየ ወይን በለምአ ከናፍር ጊሜ ።

ት ር ጉ ም

እንጨቶች / እስራኤል ከልምላሜ / ማህበራቸው
በከንፈሮች ለምጥ የታመመ ወይንን አወጡት ።

ምስጢር

እስራኤል በአሪቱ ልማድ ለምጥ የያዘውን ሰው ከአንድነታቸው
እንደሚለዩት ፤ ሌሎቹ እንጨቶች በከረምት ሲለመልሙ ወይን አለ
መለምለሙን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

98 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ደብረ ክርም ይመስል ካህነ ብዙኅ ዕድሜ ፤
እስመ ዲበ ርእሱ ይጠውም ጸዐዳ ሕሚለተ ርእስ ጊሜ ።

ት ር ጉ ም

የክረምት ተራራ የብዙ እድሜ ካህንን ያመስላል ፤
ነጭ የራስ መጠምጠሚያ / ጉምን በራሱ ላይ ጠምጥሟልና።

ም ስ ጢ ር

ካህን ሻሹን በራሱ ላይ እንደሚጠመጥም በክረምት ወራት ተራራው በጉም ተሸፈነ ይላሉ ባለቅኔው ።

99 ዘይእዜ

ታዴዎስ መሰግል
እስመ ይቤላ ለዘግ እንዘ ይሰብክ በርሜ
እምጽኢ በሐተታ
ዐጽቀ ዘነፋሰ ዐውሎ ወሥርወ ዘጊሜ ፤
ወወለተ ዘግ ጎስርት ተየውሀት ለፍጻሜ
እስመ ይመስላ ጸድቀ በብዝኀ ሱላሜ
ሊቀ መዘምራን ታዴዎስ እሱረ መንጌል መሐሜ
እስመ ይመስላ ጸድቀ በብዝኀ ሱላሜ ።

ት ር ጉ ም

ታዴዎስ ጠንቋይ ነው ፤
በርም ሲያስተምር ሽርሙጣን በምርምር
የእውሉ ነፋስን ጫፍና
የጉምን ስር እምቄ ብሏታልና ፤
ጎስቋላ የዘግም ልጅ በፍቅም ተታለለች ፡
በፍቅር ብዛት እውነተኛን መስሏታልና
በወንጌል/እግር ብረት የታሰረ የመዘምራን አለቃ/ታዴዎስ
በፍቅር ብዛት እውነተኛን መስሏታልና ።

ም ስ ጢ ር

አባይ ጠንቋይ ሴትን ሲያታልላት የነፋስን ቀንበጥና የጉም ስርን እምቄ እንደሚላትና ሴቲቱም እንደምትሞኝ ሀዋርያው ታዴዎስ ዘግይቱን በጉም መሄጃ ሀዋ ላይ በነፋስ ሰቀላት በማለት ባለ ቅኔው አመሰጥረዋል ።

ታ ሪ ክ

ታዴዎስ ከአስራ ሁለቱ የክርስቶስ መልእክተኞች አንዱ ሀዋርያ ነው ፤ ወደሀገረ ስብከቱ ስለክርስቶስ ሲያስተምር እንዳይገባ ተቃዋሚዎቹ አንዲቱን ሴት እራቁቷን በከተማው በር አቆሟት ። እርሱም ያችን ሴት በነፋስ አውታር በሀዋ ላይ ሰቀላትና ስብከቱን ቀጠለ ። በሁዋላም እርሷን ከስቅላቷ አውርዶ አሳምኗታል ይባላል (ገድለ ሀዋርያት) ።

100 ሚሀልክ

ምኒልክ ተአሰር በኀበለ ዕድሜ ፤
አንተኒ እስራ ለሀብተ ካህናት ሰሎሜ
በኀበለ እስራኤል ምድረ ርስት ፤
እስመ ወይን ልባ ኢኮነ ከራሜ ።

ት ር ጉ ም

ምኒልክ በእድሜ/ ገመድ ታሰር ፤
አንተም በእስራኤል ገመድ/ የምድር ርስት
የካህናት ሀብት/ ሰሎሜን እስራት ፤
የወይን ጠጅ/ ልቧ ከራሚን አልሆነምና ።

ም ስ ጢ ር

ባለቅኔው ለአፄ ምኒልክ ረጅም የንጉሰ ነገስትነትን እድሜ ከተ መኙ በሁዋላ ፣ ምኒልክ እርሳቸውን (ባለቅኔውን) ና ጓደኞቻቸውን ከረ ምት ከመግባቱ በፊት ባለርስት አድርገው በሰሞን መሬት እንዲ ተከሏቸው በቅኔያቸው ምስጢር ተግፅነዋል ።

101 መወድስ

ዘይኩና አምላክ (አቶ)

ኢያጸድቆ ለሰብእ እንበለ ገቢር
አንብቦ መጻሕፍት አእላፍ ወሰሚዐ ጥዩቅ ትርጓሜ ፣
እስመ እምዙኃኒ ሐዊን ወእምነ ሥቃይ መሐሜ
ኢያምሰጠት ምንተ ነፍሰ ይሁዳ
ብእሲ ነባቢ ሕገ ርትዕ ቀዋሚ፣
ወእስከ ፍጻሜሰ ታከብሮ
ትርፍት ሕግ ለዘየዐቅባ እስከ ፍጻሜ ።
አምላክነሂ አለበዎሙ ተነ ሃይማኖቶሙ ጊሜ
ለጴጥሮስ ወለሕዝቡ በይብስተ በለስ እምልምላሜ ።
ወይጼዐኑ ሕጋተ አፍራሲሆሙ በዕድሜ
መሳፍንት ዘደብረ ሲና ወነገሥተ ጽድቅ እለ በሮሜ ።

ትርጉም

ብዙ (አእላፍ) መፃህፍት ማንበብና
የተብራራ ትርጉምም መስማት ያለ ስራ ሰውን አያፀድ
ቀውም ፤
ከብረት/ ኩነኔና ከስቃይ/ እግር ብረት
ቋሚ የሆነ የቅንነት ህግን የሚናገር
ሰው/ የይሁዳ ነፍስ ምንም አላመለጠችምና ፤
ትርፍ ህግ ግን

የሚጠብቃትን (ሰው) እስከመጨረሻ ታ...
አምላካችንም ለጴጥሮስና ለህዝቡ የሃይማኖታቸው/
ጉም ትንትን በበለስ ከልምላሜ መድረቅ አንፃር አስረ
ዳቸው ፤
የደብረ ሲና መሳፍንትና በሮም የነበሩ
የእውነት ነገስታትም ፈረሶቻቸው/ ሀጎችን በዘመን ጋለቡ ።

ም ስ ጢ ር

የእንድ አገር ዜጋ እውነተኛነት (ህግ አክባሪነት) የሚረጋገ ጠው ፣ ያ ሰው የህግ መፃህፍትን በማንበቡና ትርጓሜያቸውንም ጠንቅቆ በማወቁ ሳይሆን ፣ በህግ የተደነገገውን በተግባር መተር ጎም በመቻሉ መሆኑን ባለቅኔው ያስገነዝባሉ ።

102 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘወልዶ ያረድ (አለቃ)

አጎውየ ! ንጎድግ ፍቅረ እንስሳ ዓለም ፤
በሰኑይ ዕለት እስመ ይቀሥፈነ ጾም ።

ት ር ጉ ም

ወንድሞቼ ! የእንስሳ አለም/ ፍቅርን እንተው ፤
ፆም በሰኞ ቀን ይገርፈናልና ።

ም ስ ጢ ር

ዝቡሬ በሬውን በእርሻ ስራ ቀን እንደሚገርፈው ፆም በሰኞ ቀን ይገባልና ፣ እንደ እንስሳ ሰአት ሳንለይ ምግብ ሳንመርጥ መብ ላትን እንተው በማለት ባለቅኔው በቅኔያቸው የሃይማኖት ጓዶቻ ቸውን ይመክራሉ ።

103 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘዳን (አለታ ፡ ዘሬጡኤል)

ሰብሕዎ ቅብዕ ወመብልዐ ሥጋ ለጸዎ ፤
እስመ አድኅኖሙ ጥቀ እምእቶን እሳት ግሩም ።

ት ር ጉ ም

ቅቤና የስጋ መብል ያምን አመሰገኑት ፤
ከሚያስፈራ የእሳት ግንደጃ ፈፅሞ አድኗቸዋልና ።

ም ስ ጢ ር

አናንያ አዛርያና ሚሳኤልም ከእሳት ቃጠሎ ያዳናቸውን አምላክ እንዳመሰገኑት ፡ እነርሱ የተመሰሉባቸው ቅቤና ስጋ በያዘ ጊዜ በክርስቲያኖች ቤት በእሳት ወጥ አለመሰራታቸውን ቅኔው ያስገነዝባል ።

104 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ድንግል ኮነት እመ አምላክ ሀብት ፍጹም
እንዘ ተንግአ ሚልኮል አሐደ እምከዊነ ድንግል ወእም ።

ት ር ጉ ም

ድንግል የፍፁም ሀብት አምላክ እናት ሆነች ፤
ሚልኮል ድንግልንና እናትን ከመሆን አንድን ስታጣ ።

ም ስ ጢ ር

አንዲት ሴት ከሁለት ስጦታዎች አንዱን ሳታገኝ ሌላይቱ በሀብት ላይ ሀብትን እንደምታገኝ ፡ የዳዊት ሚስት ሚልኮል እግ ብታ ሳትወልድ መቅረቷንና ቅድስት ማርያም ግን በድንግልነቷ ላይ አምላክን መውለዷን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ።

ታ ሪ ክ

ሚልኮል የንጉስ ሳኦል ልጅ ናት ። የእሴይ ልጅ ዳዊት እግ ብቷት ስትኖር ፡ ንጉስ ዳዊት ልብሰ መንግስቱን ለብሶ እንደተራ ሰው በታቦተ ፅዮን ፊት በቆነጃጅት መካከል ሲዘፍንና ሲዘል አየችው። በዚህ ጊዜ «እሁን ንጉስ እንደዚህ መሆን ? » ብላ ነቀፈችው ። በዚህ ምክንያት መክና ልጅ ሳትወልድ ሞታለች ይባላል (1 ሳሙ. 18 ፡ 22—29 ፡ 2 ሳሙ. 6 ፡ 1—23) ።

105 ሚበዝኁ

ዘንብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኤልያስ)

እመ ሰማዕከሙ ቀርነ
ውስተ ቤተ ጸሎት ኬብሮን ባሕታውያን ዘገዳም
በሉ ነግሠ መብልዕ አቤሴሎም ፤
እስመ አሜሃ ይሰደድ እንተ ልግዱ ብካይ ንጉሠ እስራኤል ጸም ።

ት ር ጉ ም

የገዳም ባህታውያን / እስራኤል
በፀሎት ቤት/ኬብሮን ውስጥ ነጋሪትን በሰማችሁ ጊዜ
አቤሴሎም/መብል ነገሰ በሉ ፤
ልግዱ ለቅሶ የሆነ የእስራኤል ንጉስ / ያም ያን ጊዜ ይሰ ደዳልና ።

እስራኤል ወደ አቤሴሎም እንደከዳለት የነዳም ባህታውያን ለምም አደሉ ። በኬብሮን የአቤሴሎም ነጋሪት እንደተሰማ በቤተ ክርስቲያንም የሆሳእና እለት ከበሮ ተመታ ። እንደአቤሴሎምም መንገስ የስጋ መብል የሚትረፈረፍበት ፋሲካ ደረሰ ፤ እንደ ዳዊት መሰ ደድም የአርባው ቀን ያም አለቀ በግለት ባለትኔው አመስጥረዋል ።

ታ ሪ ክ

አቤሴሎም የንጉስ ዳዊት ልጅ ነው ። የአባቱን መንግስት ለመገልበጥና ፍላጎቱን ለማርካት ነገረተኛውን (ባለጉዳዩን) ሁሉ ያለልቡ እያቀፈና እየሳመ አርሱ ቢነግስ ህዝቡ በነገር እንደማይጉላላና ቅን እንደሚፈርድ እያስከጀሶና እያጓጓ የእስራኤልን ልብ ከዳ ዊት ሰረቀ (አስከዳ) ። ስእለት እንዳሰበት ለአባቱ ነግሮ በስእለቱ መሰረት በኬብሮን መስዋእት ሰውቶ እንዲመለስ አስፈቀደ ። ከሄደ በሁዋላ የቀንደ መለከት ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ ፣ «አቤሴሎም በኬብ ሮን ነገሰ እያላችሁ ጩሁ » የሚሉ ጉበኞችን ወደከተማ ለከ ። ጉበኞቹም የተባሉትን ፈፀሙ ፤ በዚህ ጊዜ ብዙዎች የዋሆች ምስ ጢሩ ሳይገባቸው አቤሴሎምን ተከተሉት ። ዳዊትም ይህን በሰማ ጊዜ ከቤተሰቦቹና ከመሰሉት ህዝቦች ጋር ከቤት መንግስቱ ወጥቶ ወደውጭ ተሰደደና አቤሴሎም ሲሞት ተመለሰ (1 ነገስ 15 ፡ 1—27) ። ክርስቶስ በየርዳናስ ውሃ በዮሃንስ እጅ ከተጠመቀ በሁዋላ ሳይ ውልና ሳያድር እለቱን ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ ፣ አርባ መእልትና አርባ ሌሊት የያመውን ያም በጹርና በገደል የሚኖሩ መናኞች መላ ዘመናቸውን ይያሙታል (ማቴ. 5 ፡ 2) ። ሲያሙትም በስግደ ትና በፀሎት ፣ በእዝንና በልትለ ተወስነው እንዳንድ ጊዜ ቅጠል እየሸመጠጡ በመብላት ነው ፣ አለማውያን ደግሞ ውለው በሰባ ትም ፣ በዘጠኝም ፣ በአስራ ሁለትም ሰአት ምግባቸውን በዘይት በተሰራ ወጥ እየበሉ እንደየችሎታቸው ይያሙትና ፣ በመጨረሻው ጊዜ በህማማት ሰሞን ከሰኞ እስከ አርብ በቤተ ክርስቲያን ሲሰ ግዱ ይሰነብታሉ ። ቅዳሜ የቅንሳኤውን የምስራች ቄጠማን ከካህ ናት ተቀብለው ያለምንም ምግብ አከፍለው አድረው አሁድ በመ

ንፈተ ሌሊት እስተድሰው ሲያበቁ ፣ በስጋና በወተት በትቤም ይፈስ ካሉ (ምን ይፈታሉ) ። ከቅንሳኤው እለት እስከ አምሳ ቀን ረቡእና አርብን አይያሙም ።

106 ሥላሴ

ዘመደ ገብርኤል (ራስ)

ዓለም እስከ ጊዜሃ
በሐብለ ዝንጋኤ ትስሕበነ
ወታመርደነ ታሕተ ኀበ ዘተዳሚ መርገም
ለዘተወለድነ በሥጋ ወደም ።
ዘአእመራሰ ጠቢብ ለባዊ ለኀልፈተ ዛቲ ዓለም
ፍዳ ወይን ይሰተይ ማየ ዝናም ፣
መሀንተ ልብስ ይትከደን ቁጽለ አዕዋም ፤
እስመ ዛቲ ጽላሎት ወሕልም ፡

ት ር ጉ ም

አለም እስከ ጊዜዋ
በዝንጋታ / ገመድ ትጎትተናለች ።
ሁለተኛም ወደተደመ ርግማን ታመርደናለች
በስጋና በደም የተወለድን እኛን ፤
የዚችን አለም አስተሳለፍ ያወቃት ጥበበኛ ልበኛ ግን
ስለወይን ፈንታ የዝናብ ወሃን ይጠጣ ፤
በልብስ ፈንታም የዛፎች ቅጠልን ይልበስ ፤
ይችው (አለም) ህልምና ጥላ ናትና ።

ም ስ ጢ ር

በግን የገዛች ሴት ወደ ወደደችው እንደምትሰበው የባለቢቱ ምሳሌ የሆነችው አለም የበግ ምሳሌ ሰውን እያታለለችና እያዘና ጋች የአዳምን ፍዳ እንዲተበል ታደርገዋለች ። ከዚህም ሌላ ዮኑ ርን ልክ የሚያውት ባላገር በጠላ ፈንታ ውሃን እንደሚጠጣና ተራ

ልብስን እንደሚለብስ ፡ እንደ አለም ከንቱነት ቢሆን የዝናብ ከታሪ ውሃን (ጨረቆን) ጠጥተና ቅጠልን አገልድሞ መናር ይነባ ነበር በግለቱ ባለቅኔው የአለምን ከንቱነት ያስረዳሉ ።

107 ሥላሴ

ንጽናሕ ለለዓመቱ
በረከተ መልአክ ሚካኤል ፤
እንበለ ብእሲ ጸድቅ መምህረ ሁሉ ዓለም
ኢንበል ካህናተ ዝግራ በልሳን ድኩም
ኢይትረከብ ግይ ቡራኬ እመልአክ ሰግይ ገጻም ፡
ስዒሮ መርገመ ዘለዓለም
እስመ በረከተ ንብረ ላዕለ ብንያም
ሰግያዊ ሚካኤል ሥዩም ።

ት ር ጉ ም

የመልአክ ሚካኤልን
በረከት በየአመቱ እንጠብቅ ፤
ከአለም ሁሉ መምህር እወንተኛ ሰው በቀር
ያዝመራ ካህናት በደካማ እንደበት
ውሃ /በረከት ከሰማይ መልአክ/ ሚካ አይገኝም እንዳንል ፡
የሰማይ መልአክ ሚካኤል / ሹም
የዘላለም ርግማንን ሽር በብንያም ላይ
በረከትን (ምርቃትን) አድርጓልና ።
(ብንያምን መርቋልና)

ም ስ ጢ ር

ዝናብ ለሀጥአንና ለፃድቃን በየአመቱ ስለሚዘንብ የዝናቡን በረከት (መምጣት ስጦታ) ገበሬዎች እንደሚጠባበቁ ፡ የቅዱስ ሚካኤል በረከትም ለደጋጎች ብቻ ሳይሆን ለክፉዎች ጭምር ከዱር እንደ

ሚመጡና ድርቅትን እንደሚያጠፋው ፡ መረትንም እንደሚያለመልም ወንዝ የበለአምን እርግማን አጠፋና ወደ ምርቃት ለመጠው ። ብንያምንም አበላው፡ ከፋውን በለአምንም የእስራኤልን ተስፋ አና ገረው ይላሉ ባለቅኔው ።

108 መወድስ

ዘምኩ (ሥጋዊ)

ብሥራተ ማርቆስ ነድ ወንጌለ ገሞራ
እምገበ ፅጉሥ ተጽሕፈ በቀይሕ ሕብረ ቀለም
ወግጎተሙ ውእቱ በዘአንበሳ ግጎተም
ደቂቅ ሕዋሳቲሁ
እስመ ተሳተፉ በሥጋ ወደም
ወማርቆስ ይጸውም
ጸሙ ነነዌ እሳተ እንተ ንብረቱ ገጻም ።
ቆሚ ያስተማውቆ ለእግዚአ ልደት ላሕም
አምጣነ አኮ ላሕመ ስሕተት እንተ አቀሞ ኢየርብዓም
አድኀኒ ከማሁ ይንብር ለፈጽሞ ትንቢት ሰም
እስመ ኢሀለወት በነገሩ እድግተ ቤቱ ለበለዓም ።

ት ር ጉ ም

የማርቆስ ምስራች የሆነ እሳት/ የገሞራ ወንጌል
ከታጋሽ ዘንድ በቀይ የቀለም አይነት ተፃፈ፡
ግሀተሙም የአንበሳ ግሀተም ነው ፤
ልጆች/ ሰውነቶቹ
በስጋና በደም ተሳትፈዋልና (አንድነት አላቸውና) ።
መናሪያው ሚካ የሆነ
የነነዌ ፆም/ እሳትንም ማርቆስ ይፃግል ።
ላምም የልጆች ጌታን ሊያሟሙቀው ቆመ ፤

ኢዮርብአም ያቆመው የስህተት ላም አይደለምና ።
አህያም ትንቢት/ስምን ለመፈፀም እንደዚሁ ያደርጋል ፤
የበለአም የቤቱ አህያ በነገሩ የለችምና ።

ም ስ ጢ ር

ትርጓሜው ምስራች የሆነ መንፈል በቀይ ቀለም እንደሚፃፍ ግርቆስ የተሰቃየበት የእሳት ነበልባል በደሙ ፍሳሽ ተቀነሰ ። ደግሞ መፅሃፍ ተፅፎ በግሀተም እንደሚታተም በእሳት የተሰቃ የው ግርቆስ ገፀ እንበሳ (እንበሳ ፊት) ይባላል ። በገጻምም የተሰራ ውን የነነዌን ፆም ክርስቲያናዊው ሰው እንደሚያመው የጴር ሰደድ እሳትን ግርቆስ ታገሰ ። ህዝቡም የመሬትን ግብር ለመንግስት እን ደሚገብሩ በክብቶች በረት የተወለደ ክርስቶስን ላምና አህያ ትንፋ ሻቸውን አሞቱት ። ምክንያቱም በልደቱ ቀን የተገኘው ላም ኢዮር ብአም እንዳቆመው የላም ጣአት የማይተነፍስና የማያሸት ሳይሆን ህይወት ያለውና የሚተነፍስ ነውና ። አህያውም ከበለአም አህያ የተ ለየ እንደላሙ የማይናገር ነው ይላሉ ባለትኔው ።

ከዚህም ሌላ በእንስሳት በረት የተወለደውን ክርስቶስን ላምና አህያ ትንፋሻቸውን እንዳሟሟቱት ግርቆስን እንስሳዎች ጴር ለጴር ንተቱት ፤ እርሱንም በእንስሳዎች ለመነተት ያደረሰው የኢዮርብአ ምን አምልኮተ ላህም (ላምን ማምለክን) መቃወሙ ነው ። በእንስሳ ትም የግርቆስ መነተት እንደ በለአም በአህያ ላይ መሄድ አይደ ለም በግለት ትኔው ተመስጥሯል ።

109 መወድስ

ዘመልደ ግርያም (ሙሀር ፡ ዘጻግ)

አ ባዕል በእደ ዚአከ
ዘትዌስከ ዘልፈ ሕግመ በሕግም
ለእመ ፈቀደከ ትድነን እምሕግከ ሕሙም
ድኅረ ጸም ኩለሄ ተቤሰይ በወቅም ፡

እምጣነ በወትም ዘይሴሰይ
ጥዒና ይረክብ ወየኀድር በሰላም ።
ተትልከሂ እስመ ኢኮነ ምስለ ዘሥጋ ወደም
በጸም ወበጸሎት ዓለመ ሥጋከ ተቃወም ፤
ከመ ይቤለከ ሊቅ እንበለ ጸሎት ወጸም
እምጣነ አልቦ ዘይመውኦ ለዓለም በዓለም ።

ት ር ጉ ም

በሀመም ላይ ሀመምን
ዘወትር በገዛ እጅህ የምትጨምር ባለፀጋ ሆይ ፤
ከከፉ ሀግምህ ትድን ዘንድ ብትወድ
ከሆም በሁዋላ ሁልጊዜ በልክ ተመገብ ፤
በልክ የሚመገብ
ጤና ያገኛልና በሰላምም ያድራልና ።
ውጊያህም ከደምና ከስጋ ጋር ስላልሆነ
በፆምና በፀሎት የስጋህ አለምን ተቃወም ፤
ሊቅ እንዳለህ ያለ ፆምና ፀሎት
አለምን በአለም የሚያሸንፈው የለምና ።

ም ስ ጢ ር

አንዳንድ ሰው ያላትሙ ይሸከምና በገዛ እጁ ድካምን ይፈጥ ራል ፤ እንዲሁም አንዳንዱ ባለፀጋ ያለመጠን እየበላና እየጠጣ በሽ ታውን በገዛ እጁ ያመጣዋል ። ስለዚህም ከመጠን በላይ ላለመድ ከም በልክ መሸከም እንዲያሻ ሆድን ከበሽታም ለማዳን ቢፈለግ እየፆሙ በልክ መብላትና መጠጣት ተፈላጊ ነው ። ምክንያቱም በልክ የተሸከመ ከድካም እንደሚያርፍ ፣ እንዲሁም በመጠን መመገብ ከስጋ ሀግም ስለሚያድን ነው ። ከዚህም ሌላ የጦር ትምህርት የሚ ያውቅ አርበኛ ባላጋራውን በጦር መሳሪያ እንደሚያሸንፍ እንዲ ሁም መንፈሳዊ ሰው ሰይጣንን ድል የሚያደርገው በፆምና በፀሎት ሀይል ነው በማለት ባለትኔው በልክ መኖር ጠቃሚ መሆኑን አመ ስጥረዋል ።

110 መወድስ

ዘዳሪ (ገራጌታ ፡ ዘንኩ ጽጌ)

ኢይትመካሕ ቂሮስ በኑኅ መንግሥቱ
ላዕለ ንጉሠ ጎይል ዳርዮስ ምሳሌ ብሩር አኅዎ ፡
ጐልቈ ዕድሜ ነገሥት ነቢይ ድኅረ ነጸረ በሀልም
ንጉሠ ነገሥት ሆኅዕና
ሰበረ አትርንተ ራእዩ ለነቢይ ላህም ፤
ሆኅዕና ጻዊት ዘአርያም
እንዘ ዲበ ዕዋል ይጼወን አምላነ መንግሥቱ ዘለዓለም ።
ፍሉጥሂ ግየ ገቦሁ እግየ መፍጥዕ ሕሙም
ድኅረ ተፈወሰ እምደዌሁ ዘወረደ ይቀድም ፤
እስመ ኮነቶ እመ ለደኃራውያን አዕዋም
ዘገጻጥ የአክላ መንግሥተ ሰማይ ማርያም ።

ት ር ጉ ም

ቂሮስ በመንግስቱ ርዝማኔ የብር
ምሳሌ በሆነ በሀይል ንጉስ ዳርዮስ / አኅዎ ላይ እንዳይመካ፡
የነገስታት እድሜ ቁጥርን ነቢይ በሀልም ካየ በሁዋላ
የነገስታት ንጉስ / ሆሳእና
የነቢይ ራእይ /ላም ቀንዶችን ሰበረ ፤
የሰማይ (እምላክ) የሆነ የዳዊት ሆሳእና
በአህያ ላይ ሲቀመጥ መንግስቱ ዘላለማዊ ነውና ።
የነኑ ውሃም ከበሽታው ከዳነ በሁዋላ መውረድን
ከቀደመ ከመፃጉእ ውሃ የተለየ ነው ፤
ጥቂት የሚበታት መንግስተ ሰማይ/ ማርያም
ለሁዋለኞች ወገኖች እናትን ሆናቸዋለችና ።

ም ስ ጢ ር

የፋርስ ንጉስ ቂሮስ በሚዶን ንጉስ ዳርዮስ ላይ እንዳይመካ ነቢዩ ዳንኤል የነገስታትን እድሜ ቁጥር ካየ በሁዋላ የዕርኢ ንጉስ ነገስታትን ሰበረ (ደመሰሰ) ። እንዲሁም ዲያብሎስ በአዳም ላይ እንደሰለጠነ እንዳይቀር የሰማይ አምላክ ሆሳእና ነቢዩ ዳንኤል ባየው ራእይ መሰረት ሰው ሆኖ ንጉስ ተባለ ። የክብት እረኛ የክቶትን ክብቶች ቀንዳቸውን በድንጋይ እንደሚሰብራቸው ሆሳእና አጋንንትን አጠፋ ፤ እንደክብት እረኛ በአህያ ላይ ቢቀመጥም ነቢዩ በራእይ እንዳያቸው ነገስታት አልተደመሰሰም ።

ከዚህም ሌላ አንድ ሰው በመልከና በጠባይ ከሌላው እንደሚለይ መፃጉእ ከተፈወሰበት ውሃ የሆሳእና የነኑ ውሃ ይልቃል ። ምክንያቱም የመፃጉእ ውሃ በመልአክ በመቀደሱ የተጠማቂውን መቅደም ሲሻ የሆሳእና የነኑ ውሃ የፈተኞቹንም ፣ የሁዋለኞቹንም ተጠማቂዎች የሚያደን ነው ይላሉ ባለትኔው ።

መንግስተ ሰማይም በጥቂት ምክንያት እንደምትወረስ እንዲሁም በጥቂት ስጦታ ስምኦን በላኤ ሰብእን ያግለደች ማርያም የሀዋርያት ሞገስና የሰማእታት እናት መባሏ በትኔው ተመስጥሯል ።

111 መወድስ

ዘንበረ መድኅን (አለታ)

ገሞራ ወሰዶም አህጉረ ፍዳ
ይረክባ ሳሕተ አመ ዕለተ ቀትል ግሩም
አንቲሰ ጎስርት ትዕይንተ ርም
ለጠይቆ አቤርን ወዳታን
ተፈናኪ ውስተ መቃብር ጥብልተ በደም ፤
እምነበ ምኒልክ ቤዛ ዓለም
እስመ በጽሐ ብኪ ዘኢበጽሐ በስዶም ።
ዋሕደሂ ዘርዐ ዚአኪ ከመ ኢያትርፍ ስስም

መሐለ ተዘኪር ሳሙኤልሃ ዘትግልዮ ፤
አምጣነ ጎሳሩ ለሳኦል አድኅኖ አጋግ ሕሙም ፤
ወበእንተዝ ሰደፈ እዴሁ ጎጠተ ዘርዕኪ ይቀስም ።

ት ር ጉ ም

የመከራ አገሮች ሰዶምና ገሞራ
በሚያስፈራ በግዳይ ቀን ጊዜ እረፍትን ያገኛሉ ።
አንቺ ጎስቋላ የሮም ከተማ ግን
አቤርንንና ዳታንን ለመጠየት
በደም ተጠቅልለሽ ወደ መቃብር ተላክሽ ፤
በአለም ቢዛ ምኒልክ ዘንድ
በሰዶም ያልደረሰ ደርሶብሻልና ።
ያንችን ዘርም ለስም አንድ እንዳያስተር
የትናንት ሳሙኤልን አስቦ ግለ ፤
የታመመ አጋግን ግዳን የሳኦል አሳር (መከራ) ነውና ፤
ለዚህም የአጄ ሰይፍ የዘርሽን ትንጣት ይለትግል ።

ም ስ ጢ ር

የሮም ሀይል ከሰዶምና ከገሞራ ጥፋት ባላነሰ ሁኔታ በእኔ ምኒልክ በተመራው ጦር በአድዋ ፡ ለሙሴ እንዳልታዘዙ እንደዳታንና አቤርን መንኮታኩቱንና የእኔ ምኒልክም ጦር አድራጎት ሳሙኤል አጋግን በመግደል እንደፈፀመው አድራጎት ያልተጠበቀ መሆኑን ባለቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

112 መወድስ

ዘመልደ ተብርኤል (ራስ)

ሥነ ጽጌ ረዳ ዓለም እንተ ትትነገፈ
ወተጎልፈ ቅጽበተ አርአያ ጽላሎት ወሕልም ፤
እምነ አሐዱ አፉኪ እስመ ይመፅኡ ዮም

ለፈ ቡራኬ ወለፈ ሞርጎ ።
ወምንተ ይኤድም
ዘመነነኪ ወሖረ ፍናተ አስቴጥስ ገዳም ፤
እንሰሂ አረማዊ ወክርስቲያናዊ በስም
ለለጽባሔ ቡኀሊት እንዘ ጽንዐ ጎይልየ አደከም ፡
ዘመንየ ዙሉ ረጸምኩ እንበለ ጸሎት ወጸም
ሜኃልተ በመብልዕ ወሊሊተ በንጥም ።

ት ር ጉ ም

የፅጌ ረዳ/አለም ውበት ረጋፊ ነሽ ፡
እንደጥላና እንደ ህልምም በፍጥነት ታልፊያለሽ ፤
በወዲህ በኩል ምርታት በወዲያ በኩል እርግማን
ከአንዱ አፍሽ ዛሬ ይወጣሉና ።
የናቀሽና የአስቴጥስ
ገዳም መንገድን የሄደ ሰው ምንስ ያምር !
በስም ክርስቲያን ስሆን አረመኔ እኔ ግን
እየተኑም ሃይሌን በፃጢአት እያደከምሁ ፡
ዘመኔን ሁሉ ያለ ፆምና ያለ ፀሎት ጨረስሁ
ቀን በመብል ሌሊትም በእንቅልፍ ።

ም ስ ጢ ር

የመስከረም አበባ በፍጥነት እንደሚረግፍ አለም እንደዚሁ ጠፊ ናት ። ደግሞ ሌሊት የታየ ህልም ጧት እንደማይገኝ አለም ሲጀት አትገኝም ። በዚህም ላይ ጣፋጭ ውሃና መራራ ውሃ ካንድ ምንጭ የማይወጡ ሲሆኑ ፡ ምርታትና እርግማን በአንድ አለማዊ ሰው አንደበት መነገራቸው ባለቅኔውን አሳዝኗል ። ከዚህም ሌላ የስራ እንጂ የስም ክርስቲያንነት ከንቱ መሆኑን የተረዱት ባለቅኔ አለማዊ ኑሮን ነቅፈው በገዳም መኖርን ተመኝተዋል ።

113 መወድስ

ዘመልደ ዮሐንስ (መልክዐ ቁርጥ)

መዐዛ ትንሞት ፈለጠ በአእናፈሁ
አበ አእሩግ ቂርቆስ ሕፃነ መለስቱ አክራም ፡
ወትርጓሜ ስሙ መጽሐፍ ከሙ ኢይትረሳዕ ዮም
ጽሑፍ ስሙ በቀይሕ ተለም ፡
ወተእኅዘ በድካም ፤
እስመ ውስተ ልቡ ተሰውጠ ዘቴዎድሮስ ሕግም ።
ነሥአሂ ከናፍሪሁ አድባረ ጽዮን አጸም
ማየ ደመ ቀናት እንተ ወረደ እምነ ወይኑ አርሞንኤም ፤
ወአእናፈሁ ዐበይት አህጉረ ክርቤ ጥዑም ፤
ደመና ቀናት እስመ ተተክለ ግእክለ ወይኑ ገራህተ ደም ።

ት ር ጉ ም

የሶስት አመት ህፃን የሆነ
የሽማግሎች አባት / ቂርቆስ የችንካሮች ሽታን
በአፍንጮቹ ለየ ፡
የስሙ ትርጓሜ መፅሀፍም ዛሬ እንጸይረሳ
ስሙ በቀይ ቀለም የተፃፈ ነው ፤
በድካምም ተያዘ ፤
የቴዎድሮስ ህግም በልቡ ውስጥ ተመልሷልና ።
የመልካም ፅዮን ተራራዎች / ከንፈሮችም
ከአይኑ/ አርሞንኤም የወረደ ችንካር ደም / ውኃን ያዙ ፡
ታላላት አፍንጮቹም የጣፋጭ ክርቤ አገሮች ናቸው ፤
ችንካር / ደመና በደም እርሻ / አይኑ መሃል ተተክሏልና ።

ም ስ ጢ ር

የምገብ መአዛ ባፍንጫ እንደሚለይ ቂርቆስ አፍንጫዎቹን
በችንካር በመችንከር የደረሰበትን ስቃይ በመታገሱ ከማያምኑ

ሰዎች ተለየ ። የመፅሀፍ ትርጓሜ እንጻይዘንጋ በተለም እንደሚያዙ
የቂርቆስም ስም በመሰሉቹ ክርስቲያኖች ዘንድ መታወቁንና በቤተ
ክርስቲያን ታሪክ መፃፉን ትኔው ይገልጣል ። የልብ በሽታ ያለበት
ሰው እንደሚደክምና እንደሚታመም የቂርቆስ ልብ በችንካር ተቸ
ነከረ ። አርሞንኤም ከሚባለው ተራራ ላይ የተቆለለ በረዶ እየሟሟ
ወደ ዮርዳኖስና ወደ ገሊላ ባህር እንደሚፈስ ከቂርቆስ አይን የመ
ጣው ደም ከንፈሮቹን ግልበሱን ባለትኔው ያስረዳሉ ።

114 መወድስ

ዘተሰኘ (መልክዐ ፅሑይ)

እምሀጦሰ አባግዕ ጻዊት ናላዊ ርኅራጌ
መዊተ ጽሕቶ ፡ ወሙሴ ውስተ ገጻም
ድምሳሴ መርዔቱ ኢይሰግዕ እመጽሐፈ ሕይወት አጻም
አብደረ ድምሳሴሁ ፡
ወኢያርአይ ሙስና ብሑሩ ፈተወ እምትድም
አቤሜሌክ ዘርዐ ካም
ለእመ ኢወተበ ወልድ ትጋህ እሙንቱ እስመ ንኖም ።
እምትጋህኒ ዘመላእክት ንኖመ ክርስቶስ ጥዑም
ዘሐመረ ግዕበል ጊዘ ንኖመ ኢክህለ ይሰጠም ፤
አኮኑ ዘቦቱ ተጽሕፈ ግዕዛን ሠሉ ዓለም
ወክሡት ለባሕቲቱ መጽሐፈ ሕይወት ወሰላም ።

ት ር ጉ ም

የርህራሄ ጠባቂ ጻዊት ከበጎች ጥፋት የተነሳ
ለመሞት ተጋ ፡ ሙሴ ግን በጻር ውስጥ
ከአግረ ህይወት መፅሀፍ የወገኖቹን ጥፋት እንጻይሰማ
ጥፋቱን መረጠ ፡
ከመጀመሪያም የህጉን ጥፋት እንጻያይ

የኛም ዘር አቤሜሌክ ወደደ ፤
ወልድ ካልጠበቀ የአነርሱ ትጋት እንትልፍ ነውና ።
በእንትልፉ ጊዜ የማአበል መርከብ ሊሰጥም ያልቻለ
የክርስቶስ እንትልፍም ከመላእክት ትጋት ጣፋጭ ነው ፤
የአለም ሁሉ ነፃነት የተፃፈበት ነውና ፤
የሰላምና የህይወት መፅሀፍም ለብቻው የተገለጠ ነውና ።

ም ስ ጢ ር

ዳዊትና ሙሴ በበጎቻቸው (በእስራኤል) ፋንታ እነርሱ ራሳቸው እንዲጠፉ ማሰባቸው ፣ የእግዚአብሄር ልጅ ካልጠበቀ የነርሱ መጠበቅ እንደመተኛት ያለ ስለሆነ በዚህ በኩል አያነድሉም ። ከዚህም ሌላ ክርስቶስ በሰውነቱ ሲያንቀላፋ መላእክት በመንፈስነታቸው (ሲጋ ባለመልበሳቸው) ባይተኙ አስጠባቂውም ጠባቂውም እርሱው ራሱ ነው በማለት የቅኔው ደራሲ ያስረዳሉ ።

ታ ሪ ክ

ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ባሀርን ሲሻገር ደቀ መዛሙርቱ የተኛ መስሏቸው እንደሚሰጉ ተጠራጠሩ ፤ ከመጠራጠራቸውም የተነሳ መዝቱ ጀመሩና «ሊቅ! ንቃና አድነን» እያሉ ሙሁ ። በዚህ ጊዜ ሊያሰስ ክርስቶስ « እስከመቼ ድረስ ስትጠራጠሩ ትኖ ራላችሁንወሰ ገሰግችውና የባሀሩን ማእበል ፀጥ አደረገላቸው ይባላል ።

115 መወድስ

ምኒልክ ዝራፅ እንበለ ዕረፍት
ዘርዐ ቤተ አብርሃም አክል በገራሀትክ ዓለም ፤
ወከመ ኢትፅዋበ አንተ ምጽአተ ደመና ግሩም
አንተ ደመና ፣ ወአንተ ዝናም ፤
ለአመ ይዘራፅ በድካም
አምጣነ በክብር ይትነሣእ ሠሉ ዘርዐ ኤፍሬም ።

የምኒ ሶበ ተክይዶ እክለ ቤትክ ጥውም
ንግርሙ ለአግብርት አፈ አልሕምት ኢይትፈፀም ፤
ወእንበለ ደዊ ጽኑዕ ዘእንበለ ብዙኅ ሕማም
ያብጽሕክ ያብጽሐነ አመ ክመ የም ።

ት ር ጉ ም

ምኒልክ! ያለእረፍት
የአብርሃም ቤት / እህል ዘርን በእርሻህ / አለም ዝራ ፤
አንተም የሚያስፈራ የደመና መምጣትን(አመጣጥን)እንዳት
ጠብቅ
ደመና አንተ ነህ ፣ ዝናምም አንተ ነህ ፤
በድካም ቢዘራ
የኤፍሬም ዘር ሁሉ በክብር ይነሳልና ።
ጣፋጭ የቤትህ እህልም ዛሬ በተበራየ ጊዜ
የበረዎች አፍ እንዳይለጎጥ (እንዳይታፈን) አገልጋዮችን
ንገራቸው ፤
ያለ ብርቱ (ፅኑ) ደዌና ያለ ብዙ ህማምም
ከርሞ እንደዛሬ (ዘንድሮ) ያድርስህ ያድርሰን ።

ም ስ ጢ ር

ገበሬ በእርሻው ላይ በትጋት ዘሩን እንደሚዘራ አፄ ምኒልክ በመንግስታቸው እንደ አብርሃም ሊጋስ ሆኑ ። ደግሞ ገበሬ የዘራው ዘር ፈርሶ በስብሶ እንደሚበቅል ፣ ያጣው ሰው ሁሉ በአፄ ምኒልክ ጊዜ ያገኛል ይላሉ ባለቅኔው ። ገበሬ እህሉን በአውድማው ሲወቃ የበረዎቹን አፍ ግረን እንደማይገባው አፄ ምኒልክም በአዳራሻቸው ግብር ሲያገቡ (ሲያበሉ) አጋፋሪዎቻቸው ሰውን እንዳያንገላቱ መደረጉን በመግለጥ ባለቅኔው አፄ ምኒልክ በያሙቱ ህያው ሆነው እንዲኖሩ ተመኝተዋል ።

አቴ ምኢልክ በዘመነ መንግስታቸው ለአድባራትና ለገዳማት ለካህናትና ለወታደሮች ግብር በማብላትና የቀላድ መሬት በመስጠት ለመነኮሳት ድርጎ በመዳረግና የብር ጉርሻ በማጉረስ ሊጋስ እንደ ነበሩ ይነገራል።

ከእበው አንዱ አብርሃም ድንኳኑን በተመሳቀለ መንገድ ዳር ተክሎ ፣ የወጣውንና የወረደውን ያለፈውንና ያገደመውን እንግዳ ሁሉ ሲቀበል የናረ ሊጋስ ሰው ነበር ። ከዚህም የተነሳ የበጎ ስራ ጠላት የሆነ ሰይጣን ቀንቶበት እንግዶቹን በተንኮል ነገር ቢያስቀርበት ፣ ያለእግዚአብሄር እንግዳ አልበላም ብሎ ሶስት ቀን ሙሉ ያሙን ውሎ አደረ። ስለዚህም እግዚአብሄር በሰው አምሳል በእንግድነት ተገለጠለትና እህል ውሃ ለመቅመስ ቻለ ይባላል (ዘፍጥ. 18)

116 መወድስ

መከራ ኢርኅተ እምርእሰ ጻድቃን
ወርእሰ ጻድቃን ኢርኅተ እምነ መከራ ግሩም ፣
እስመ ኢረከቦ ለኢዮብ ነገረ አርዌ ሕማም
እስከ ተፈጸሙ ሰብዑቱ አክራም ።
ወተፈትነ አብርሃም
በሕገ እምላኩ ፈታኒ በሠሮዐ ወልዱ ሀኖንተ ላሕም ፤
ድኅረኒ አመ ለበዉ መከራሙ ዘቅድም
እንዘ መንፈስ ቅዱስ ይመርሖሙ የማነ እምፀጋም
ፈጸሙ ሀየ በድሮሙ በእንጽሖተ ደቅ እምደም ፤
ቴዎድሮስ በቀኖት ወፋሲለደስ በልዓሙ።

ትርጉም

መከራ ከፃድቃን ራስ አልራቀም
የፃድቃን ራስም ከሚያስፈራ መከራ አልራቀም ፤
ሰባቱ ዘመናት እስከ ተፈፀሙ ድረስ የአውሬ ነገር/

ሀግም ኢዮብን አግኝቶታልና።
በፈታኝ አምላኩ ሀግም
በላም ፈንታ ልጁን በመሰዋት አብርሃም ተፈተነ፣
በሁዋላም የመጀመሪያ መከራቸውን ባስተዋሉ ጊዜ
መንፈስ ቅዱስ ከግራ ወደቀኝ እየመራቸው
ቴዎድሮስ በቸንካር ፋሲለደስም በልዓም ደምን
ከደም ለማንፃት ቅድስግቸውን (ውድድራቸውን) በዚያ
ፈፀሙ ።

ምስጢር

አባትና ልጅ እንደግይራራቁ መከራና የእግዚአብሄር ሰዎችም የግይለያዩ ለመሆናቸው ኢዮብና አብርሃም ቴዎድሮስና ፋሲለደስ ማስረጃዎች ናቸው ይላሉ ባለትኔው።

117 መወድስ

ዘዘኮስን (አለቃ)

በዓለ ከልኤቱ አእጋር በአእጋሪሁ
ኢየዐርግ ምዕረ ላዕለ ከልኤቱ አዕዋም ፤
እንዘ ይብል ውእቱ በልሳነ ሥጋ ጥዑም
አእጋር ከልኤቱ ሀለዉኒ ዮም
አሐዱ እስመ ድኩም
ዘይረድኦ ካልእ እመ ኢሀሉ እምትድም ።
ወልድሰ እንተ ኢወፅአ እምዋሕድናሁ ፍጹም
ሰከበ ውስተ ጎል እንዘቦ በእርያም፣
ወእንዘ ሀሉ ሥውለ ውስተ ማሕፀና ለእም
ኪሩቤል ኢያዕረፉ ወኢያዕረፈት ማርያም ።

ት ር ጉ ም

ባለሁለት እግሮች በእግሮቹ
በሁለቱ ዛሮች ላይ በአንድ ጊዜ አይወጣም፤
እርሱ በጣፋጭ የስጋ እንደበት ዛሬ
ሁለት እግሮች አሉኝ እያለ
የሚረዳው ሁለተኛ
(እግር) ከሌለ አንዱ ደካማ ነውና።
ከናቱም አንድነቱ ያልወጣ ወልድ ግን
በሰማይ ላለ በበረት ውስጥ ተኛ፤
በእናት ማርያም ማህፀንም ውስጥ ተፀንሶ ሳለ
ኪሩቤል አላረቱም፤ ማርያምም አላረፈችም።

ም ስ ጢ ር

አንድ ሰው በሁለት እግሮቹ ከሁለት ዛሮች ላይ ሊወጣ የማይ ችል ሲሆን፥ ወልድ ግን በሰማይ ከኪሩቤል ላይ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እንዳለ ሆኖ በማርያም ሆድ ተፀንሶ በበረት ተወለደ በማለት ባለትኔው ይህ አድራጎት ለሌላ ሰው የማይቻል መሆኑን አስረድተዋል።

118 መወድስ

ዘእድጣሁ (መልክ ፀርን)

አኮ ፅፁብ ለዘይሰምዖ
እመ ያስተግሑት አድግ አንበሳ ዕዝራ ሥዩም፥
ወለእመ ይድኅን አድግ እምአፈ አንበሳ ጭሙ፤
በኀበ ኢሳይያስ ወሱታስ
ውእቱ እምጣነ በግዕ ወውእቱ ላሕም፤
ወለእመ ለፅፁ ኢያውዐያ

እንዘ ለሊሁ እሳት እስመ ውእቱ ዝናም።
ፅፁብሰ ለሰማዒሁ ልደተ ዳግማይ አዳም
አብ ዘወለዶ እስመ እምኔሁ ኢይቀድም፤
አመኒ ተወልደ እምወለተ አብርሃም እም
ሀሎኩ ይቤለነ እምቅድመ ይትወለድ አብርሃም።

ት ር ጉ ም

የሹም/ እዝራ አንበሳን አህያ
ቢያጋጭት ለሚሰግው የሚያስደንት አይደለም፥
አህያው ከሚያስፈራ አንበሳ አፍ ቢድን፤
በኢሳይያስና በሱታስ ዘንድ
እሱ/ አንበሳ በግ ነውና ላምም ነውና፤
እንጨትንም ባያቃጥሳት
እርሱ እሳት ሲሆን ዝናብ ነውና።
ለሰሚ የሚያስደንቀው ግን የሁለተኛ አዳም ልደት ነው፤
የወለደው አባት ከእሱ አይቀድምና፥
ከአብርሃም ልጅ እናት በተወለደም ጊዜ
«አብርሃም ሳይወለድ አለሁ» ይለናልና።

ም ስ ጢ ር

ክርስቶስ አንበሳ በመባሉ ላይ በግና ላም ከተባለ እንስሳት ያጋጋቱት በእንስሳነቱ ነው። እንዲሁም እንጨቲቱን 'ማርያምን' ያሳቃጠላት በእሳትነቱ ላይ ዝናብነቱን በመያዙ ነው። ይህ ድርጊት ግን ብርቅና ድንት አይሆንም። የሚያስደንቀውስ አብና ወልድ ሳይ ቀዳሥና ሳይበላለጡ እኩሎች ናቸው ሲባል፤ ወልድ በባህርይ ከአብ ተወለደ ማለትና ከአብርሃም በፊት ያለው ወልድ ከአብርሃም ልጅ በስጋ ተወለደ ማለት ነው ይላሉ ባለትኔው።

119 ሁልክሙ

ዘአድግሱ (መልአክ ብርሃን)

ሰግዕተ ሐሰት ይኩኑ በላዕለ ጽዮን
ዕጓላተ ወርቅ አቀሙ በሰማርያ ኢዮርብዓም ፣
ወበፍናተ ግብጽ አርገ ዘበዲበ አሪት ሥዩም ፤
እንዘ ሰግዕተ ጽድቅ ይከውናሃ
ለጽዮን ዘውስተ ኢሉፍሊ ዕጓላት ዘላሕም ፤
ወኢከህለት ሰማርያ
ኢየሩ ሌም ከሢነ በዓለ ፋሲካ ታስተሐምም ።
ንሕነሰ ዘረከብናሃ በያመ ምኂልክ ገዳም
ከመ ኢዮርብዓም ወአርገ ዕጓላተ ወርቅ ኢናቀውም ፤
ወአከለን ዐሪገ ኢየሩሳሌም ፤
ኢየሩሳሌም አግዓዚት እኩ ምድረ አክሱም
ወሀየ እምነ ጽዮን ጸዋሪተ ሕግ ፍጹም ።
ኢየሩሳሌም አግዓዚት እኩ ምድረ አክሱም ፤

ት ር ጉ ም

በፅዮን ላይ የሀሰት ምስክሮች ይሆኑ ዘንድ
ኢዮርብአም በሰማርያ የወርቅ ቡችሎችን አቆመ ፤
በአሪት ላይ ሹም የሆነ አርገም በግብፅ መንገድ (አቆመ)፤
በኢሉፍሊ ውስጥ ላለች ፅዮን
የላም ጥጆች የእውነት ምስክሮችን ሊሆኗት፤
የፋሲካን በአልም
ታስብ ዘንድ ሰማርያ ኢየሩሳሌም መሆንን አልቻለችም ።
በምኂልክ/ ደን ዛፍ (ፅዮንን) ያገኘናት እኛ ግን
እንደ ኢዮርብአምና እንደ አርገ የወርቅ ቡችሎችን አና
ቆምም ፤

ወደኢየሩሳሌም መውጣትም በቃን ፤
ነፃ አውጭ ኢየሩሳሌም የአክሱም ምድር ናትና ፣
ፍፁም ሀገን የተሸከሙት እናታችን ፅዮንም በዚያች አለችና ።
ነፃ አውጭ ኢየሩሳሌም የአክሱም ምድር ናትና ፣

ም ስ ጢ ር

በዳዊት አገር የፅዮን እምላክ ሳለ ኢዮርብአምና አርገ የላም ምስል ጣእትን አቆሙ ። ይህንም ያደረጉት ከኢሉፍሊ ምድር ታቦተ ፅዮንን በሰረገላ ይዘው ከዳዊት ከተማ የገቡ ውስት ጊደሮች በፅዮን እምላክ መሪነት መምጣታቸውን ባለማጤን ነው በማለት ፣ ባለት ኔው አክሱም እንደ ኢየሩሳሌም መሆኗንና ታቦተ ፅዮንም በአክሱም እያለች ወደኢየሩሳሌም ሂድ አለማለፈልጉን ገልጠዋል ።

120 መወድስ

ዘርዓየ (አለቃ ፡ ዘተንታ)

እመ አሐዱ ይሰሐብ በፍትረ ካልኡ
ገራህተ ሙቴ ትርጠት ጎበ ገራህቱ ለአብርሃም ፡
ወጽርሐ ሚልክያስ ኮነት ትርጠተ ቤቱ ለዴም ፤
ወእመ ይትነሥኡ ላዕለ ሙቴ
ነፋስ ዘዕዝራ ወዘኔናክ ፍሕም
ለረድኤተ ሙቴ ወፅንዓቶም
ጌዴዎን መጽአ ጸዊር ጠለ ገዳም ።
ይኩንሂ ግእከሌክሙ መግእከሌነ ሰላም
ደብረ ሊባናስ ወደብረ ከርቤ ግርታ ወግርያም ፤
እስመ ዘእግሄ መስተል ወመስተለ ብርሃን ዘኮ
አኳል ዘእምአኳል ወዕፀም ዘእምዕፀም።

ትርጉም

በእንዱ ፍቅር እንዱ ቢሳብ
የሙሴ እርሻ ወደ አብርሃም እርሻ የቀረበች ናት ፣
የሚልክያስ እልፍኝም ለሴም እልፍኝ ቅርብ ናት ፤
የእዝራ ነፋስና የሄናክ ፍም
በሙሴ ላይ በተነሱ ጊዜ
እንባቆምና ሙሴን ለመርዳት
ጊዴዎን የዱርን ጠል ተሸክሞ መጣ ።
ሰላምም በመካከላችሁና በመካከላችን ይሆን ዘንድ
ደብረ ሊባኖስና ደብረ ከርቤ ግርያምና ግርታ ናቸው ፤
የዚያን ጊዜ መስቀልና የዛሬው የብርሃን መስቀል
ከአካል የተገኘ አካልና ከአጥንት የተገኘ አጥንት ናቸውና ።

ም ስ ጢ ር

አንድ ሰው በሌላው ሰው ፍቅር ይሳባል ፤ ቅድስት ግርያምም በአብርሃም እርሻና በሴምና በሚልክያስ አዳራሽ ትመሰላለች ። ነፋስ ያገለበለበው እሳት በቤት ላይ ሲነሳ ባለቤቱን ለመርዳት ጎረቤት ውሀ ይዞ እንደሚመጣ ፣ እዝራ ባየው ነፋስና ሄናክ በተ መለከተው እሳት የተመሰለ ከርስቶስ በጊዴዎን ግምጃ ጠልም ይመ ሰላል ። እንዲሁም ግርታና ግርያም እህትማማች እንደሆኑ ግሸን ግርያም (ደብረ ከርቤ)ና ደብረ ሊባኖስ ተክለ ሃይማኖት ተመሳሳ ዮች መሆናቸው በቅኔው ተመስጥሯል ። ሁለት ወንድማማች ከአ ንድ አባትና እናት እንደሚወለዱም ፣ በግሸን በአኗ ዳዊት ዘመን የተቀበረው ግማደ መስቀልና ለተክለ ሃይማኖት ወረደ የሚባለው የብርሃን መስቀል የአንድ አምላክ ስጦታዎች ናቸው በማለት ፣ ባለቅኔው በሁለቱ አድባራት መካከል የነበረውን የቅደም ተከተል ክርክር በቅኔያቸው ለማስታረቅ ሞክረዋል ።

121 መወድስ

ዘሠርሐንስ (አለቃ)

ዕለተ ፍጻ መስለት ዕለተ ዚአነ ፣
ወከርሙ ነጻያን መሰለ መካነ ዙኃኔ ግሩም ፤
እስመ ዕጌሁ ለክርሥ ዘኢይነውም
ወእም አውያተ ወለታ ኢትሰምዕ የም ፣
ወምንተ ይኤድም
ለአረፍተ ሥቃይ ዘመን ዘይትዐደም በሰላም !
ሥጋ ላሕምኒ ኢንበልዕ በመዋዕለ ፍጻነ ጾም ፣
ወደመ ጠሊ ኢንሰቲ በአትርገቲሁ ለኢየራም ፤
እስመ ሥጋ ሱበአ ኮነ ከመ ሥጋ ላሕም ጥዑም
ወጥዑም ለአፉነ ዙሱ ሥነ ገጻም ።

ትርጉም

የእኛ ቀን የመከራ ቀንን መሰለች ፣
የችግረኞች ሆድም የሚያስፈራ የኩነኔ ቦታን መሰለ፤
የሆድ ትሉ የማይተኛ ነውና
እናትም የልጅዋን ለቅሶ ዛሬ አትሰማምና ፤
የስቃይ ዘመን /ጎድጓዳን
በሰላም የሚሻገር (የሚያልፍ) ሰው ማን ምን ያምር !
በመከራችን/ ያም ዘመን የላም ሲጋን እንበላም ፣
በኢየራም ቀንዶች ዋንጮችም የፍየል ደምን እንጠጣም፤
የሰው ሲጋ እንደ ላም ጣፋጭ ሲጋ ሆኗልና
የዱር ውበት (አትክልትና እንስሳት) ሁሉም ለአፋችን
ጣፋጭ ነው ።

የክርስቶስ ፍርድ ቀን አስቀድሞ ለተፈፀመ በደል ማሻሻያ ምህረት ማግኛ እንዳልሆነች የችግር ዘመንም ልትሻሻል አትችልም ። በገሃነም ውስጥ እሳቱ እንደማይጠፋ ፣ የክፉ ቀንም ራብ የችግረኞችን ሆድ እንደ እሳት ያቃጥላል ፤ እንደ ትል ይበላል ። በክርስቶስ ፍርድ ቀን እናት የልጅዋን ጩኸት እንደማትሰማ ፣ በክፉ ቀን ችግር ቀንም ልጆች እናቶቻቸውን «እንጀራ» ሲሉዋቸው እናቶች የሚሰጧቸው የለም በማለት ፣ ባለትኔው በዘመናቸው የደረሰውን የራብ አልቂት ፅናት በትኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

ኢዮራም ከአባቱ ከይሁዳ ንጉስ ኢዮሳፍጥ በሁዋላ ከ848 እስከ 841 ክክርስቶስ ልደት በፊት የነገሰ እምስትኛው የይሁዳ ንጉስ ነው ። የእስራኤል ንጉስ የአክአብን ልጅ አግብቶ ነበርና እንደ አማቱ አክአብ ለጣኦት መሰዋእት አቀረበ ። ነቢዩ ኤልያስም እርሱን በመገሰፅ ፃፈ ። ኢዮራም በሚያሰቃይ በሽታ ታሞ በዘጠኙ ሁሉ ዘንድ ተጠልቶ ሞተ (2 ዜና. 21 ። 2 ነገስ. 8 ፡ 16—24) ።

122 መወድስ

በላዕለ ደብረ ዘይት ፍትሕ አመ ተመለጠ
ማዕደ ሥጋ ከልአነ መዋዕሊሁ ለጸዎ ፤
እንዘ ደብረ ዘይት ይበልዕ ማዕደ ሥጋ ወዕፅም
አኮኑ ኢይትዐወቆ
ለሰብአ ጌጋዩ ዘሥጋ ወደም
ከመ ቀዳሚዊ አቤሴሎም
በትድመ ብእሲ መካሕ ዘይወዕእ እምኤዶም ።
በፍትሕሰ ዘይደሉ እመ ነበረ ዓለም
ኤልግዕ እምኢሐይወ እንዘ ኢዮብ የሐምም ፤
ወአመ በጌሞ ተነድፈት ኢየሩሳሌም
ዘይረውጽ እምኢሞተ እንዘ አቤሜሌክ ይነውም ።

በደብረ ዘይት ላይ ፍርድ በተለወጠ ጊዜ
የያም ዘመን የስጋ ማእድን ከለከለን ፣
ደብረ ዘይት የስጋና የአጥንት ማእድን ሲበላ
ለሰው የስጋና
የደም በደሉ አይታወቀውምና
እንደ መጀመሪያው አቤሴሎም
«ከኤዶም (ገነት) በሚወጣ በተመኪ ሰው » ፊት ።
አለም ግን በሚገባ ፍርድ ቢኖር
ኢዮብ ሲታመም ኤልሳኔ ባልዳነም ነበር ፣
ኢየሩሳሌምም በምርኮ በወደቀች ጊዜ
አቤሜሌክ ሲተኛ የሚሮጥ ባልሞተም ነበር ።

በያም ወራት ክርስቲያኖች ከስጋ ምግብ ተከልክለው በዘይት ወጥ ብቻ እንደሚበሉ ክርስቶስም በደብረ ዘይት ሲገለጥ ስጋና እጥንት ይዋሀዳሉ ። ልጆቹ ያለቁበት ኢዮብ ሲታመም የባእዶችን ልጆች በድብ ያስጨረሰ ኤልሳኔ በደህና ኖረ ። አቤሴሎምም አባቱ ዳዊትን በድብት ከድቷል ። ስለዚህ ፍርድ አለአግባብ ሲሆን ሊገኝ የሚገባው ነገር አይገኝም ይላሉ ባለትኔው ።

የእግዚአብሄር አብ የባህርይ ልጅ ቃል እግዚአብሄር ወልድ በምላት ወደዚህ አለም የመጣለትንና ሰው የሆነለትን ተግባር ፈፅሞ ወደ ባህርይ አባቱ አረገ ። ዳግመኛም ወደዚህ አለም ከመላእክት ጋር መጥቶ በደብረ ዘይት በግርማ መንግስት ይገለጣል ። ሙታንን አንስቶ ሲጋንና አጥንትን ያዋህዳል ፣ ፍፁም በድንም ያደርገዋል ፣ በበድኑ ነፍስን አሳድሮ ያንቀሳቅሰዋል ማለት ተፅፏል (ማቴ. 25 ፡ 1—46) ።

ክርስቶስ በዚህ አለም ሳለ ያምንና ፅድቱን ሰርቷል (መስር ቷል) ። ያም ከመብልና ከመጠጥ ከክፋም ስራ ተከልክሎ መዋልና ከስ ጋና ከቅቤ ከወተትና ከሩካቤ ሲጋ እስከያሙ ፍጥሜ መለየት ነው ። (ማቴ. 6፥16—19) ።

ኢዮብ እንደ አብርሃም የእግዚአብሄር ወዳጅ የሆነ ትእግስ ተኛ ሰው ነበር ። የእግዚአብሄር ወዳጅ ከመሆኑ የቱነሳ ትእግስ ቱን ሰማስዉረስና ከአምላኩ መንገድ ለማውጣት ሰያጣን ተረታ ተነው ። እግዚአብሄርም የኢዮብን ጥናትና እምነት ስለሚያውቅ ሰያጣን ከነፍሱ በቀር በኢዮብ የወደደውን እንዲፈፅምበት ፈቀደ ለትና ተንቀሳቃሾች ሀብቶቹን ፡ ቤተሰቦቹንና ልጆቹንም በድን ገተኛ አደጋ አስፈጀበት ። ሰውነቱንም ከእግሩ እስከ አናቱ በቁ ስል መታበት (አቆሰለው) ። ይሁን እንጂ ኢዮብ የሁሉንም መርዶ ዜአንድ ቀን ሲሰማና አካሉን ሲያጣ ከትእግስቱና ከእምነቱ አል ተናወጠም ። በሚስቱም ስህተት አልተመራም ፡ «እግዚአብሄር ሰጠ ፡ እግዚአብሄር ነሳ ፡ ይክበር ይመስገን» አለ እንጂ አላማረረመም። ስለዚህም ፈተናውን በትእግስቱ አለፈ ይባላል (ኢዮ.2—11) ።

123 ሕንጂሃ

ኢይትፈጸም በካልእ እንበለ ግርያም ሰላም
ግጌሌተ ጽድቁ ለሁሉ ዓለም ።

ትርጉም

የአለም ሁሉ ፅድት ግሀሌት
ያለግርያም ሰላም በሌላ አይፈፀምም (አያልትም) ።

ምስጢር

በቤተ ክርስቲያን ስርአት በክበር በውዕልና በመቋሚያ የሚ ደረሰው ግሀሌት ሰላም በሚባለው ክፍለ ዜማ እንደሚፈፀም የአ ለም ፅድትም በትድስት ግርያም ተፈፀመ ያላሉ ባለትጌው ።

124 ሥላሴ

ድንግለ እመ ጎየአ
ሞት ይጸውዕ ኤልያስሃ ፡
እስመ አመ ለዝ ኤልያስ እግዚአብሔር ጎተሞ
ኢያንከረ ዕጊ ሥጋሁ ጥጊሞ ።
መለእመ ሐለዩ ምክረ ትንሣኤ እንተ ኢይክሉ አትሞ
ዕዝራ ወሄኖክ ሰብአ አርምሞ
እስመ ቦ ኤልያስ ዘይቀድሞ
ኢያዕረፈ መታብር ፈጺሞ

ትርጉም

ሞት ድንግልን
ባጣ ጊዜ ኤልያስን ይጠራል ፡
ይህን ኤልያስን እግዚአብሄር በሰወረው ጊዜ
ትል ስጋውን ተምሶ አላደነቀምና ።
የዝምታ ሰዎች/ እዝራና ሄኖክ መወሰን የማይቻላቸው
ትንሳኤ/ ምክርን ቢያስቡም
የሚቀድመው ኤልያስ አለና
መታብር ፈፅሞ አላረፈም ።

ምስጢር

አንድ ወንድ ሙሽራ የፈለገውን ሲያጣ ሚዜውን እንደሚ ጠራ የፈላጊው ምሳሌ ሞትም ድንግል ማርያም ብትነሳበት ነቢይ ኤልያስን ገና ይጠባበቃል ። በዚሁም ላይ አንዳንድ ሰዎች የማያ ዛልታቸውን ምክር እንደሚመክሩ ፡ ሄኖክና እዝራ ኤልያስም ለጊዜው ከሞት ቢሰወሩ በሁዋለኛው ጊዜ መሞት አለባቸው በማ ለት ባለትጌው ሞት ስጋ ለለበሰ ፍጡር ሁሉ የግይቀር የተፈጥሮ ህግ መሆኑን በትጌያቸው ምስጢር ያስረዳሉ ።

125 መወድስ

በሕግም ለዲ እብነ ቢታንያ
ዘእምሆሳዕና ፀንስኪ ነገረ በቀል ወተቀይሞ ፤
ወወለደኪ ግብኢ ጎበ ምትኪ አርምሞ ።
ወቃለ ቅዳሴ መልከጼዴቅ
ንፈቅድ ከመ ያይድዐነ አባሁ ወእሞ ፤
ከመ ናይድያሙ ዘተገብረ
በነሢአ እብን አይሁድ አምጣነ ሰበሩ ዐፅሞ ።
አተወሂ ቤተ ሱራፌ እንዘ ያንጸፈጽፍ ደሞ ፤
አኮኑ ኢየዐርፍ እብነ ቢታንያ ለተቃውሞ ፤
እንዘ ለአእባን ወጢን ወለኪሩቤል ፈጽሞ
ድኅረ አጥመቆሙ ሆሳዕና በአንብሮተ እድ ባሕረ ተሰጥሞ።

ት ር ጉ ም

ከሆሳእና የበቀልና የመቀየም
ነገርን የፀነስሽ የቢታንያ ድንጋይ ! በምጥ ውለጅ ፤
ወልደሽም ወደዝምታ ባልሽ ተመለሽ ።
የምስጋና ቃል መልከጼዴቅም
አባትና እናቱን ይነግረን ዘንድ እንወዳለን ፤
የተደረገውን እንነግራቸው ዘንድ
አይሁድ ድንጋይን በመያዝ አጥንቱን ሰብረዋልና ።
ወደሱራፌ ቤትም ደሙን እያጠፈጠፈ ገባ ፤
የቢታንያ ድንጋይ ለመቃወም አያርፍምና ፤
መጀመር ለድንጋዮች መፈፀም ለኪሩቤል ሲሆን
ሆሳእና እጅን በመጫን/ መሰጠም ባህር ካጠመቃቸው
በውዋላ።

ም ስ ጢ ር

ሄኖን እምጣ ወልዳ ወደባልዋ እንደ ተመለሰች ፤ የሄኖን ምሳሌ የሆነች የቢታንያ ድንጋይ ሆሳእናን አመስግና ወደቀድሞው ዝም ታዋ መመለሷ በትኔው ተመስጥሮበታል ። በሌላ በኩል ደግሞ መ ል ከጼዴቅ ያለአባትና እናት እንደናረ የመልከጼዴቅ ምሳሌ የሆነ የድንጋይ መናገርም ያለተፈጥሮው ሆነ ። በዚህም ላይ ራሱን የተገ መሰ ሰው ደሙን እያፈሰሰ ወደቤቱ እንደሚገባ ድንጋይ እንደ ሱራፌ (መላእክት) ያለ ፍጡር ሆነ። በተጨማሪም እንዱ የጀመረውን ሌላው እንደሚጨርሰው የድንጋዮችን ምስጋና መላእክት አደነቁ ይላሉ ባለትኔው ።

126 ግእዝ ጎ ባ ኤ ቃና

መልከጼዴቅ አብ እመ ሲኦለ ያንሶሱ
ደንገፀ አቤል እስከነ ትወፅእ ነፍሱ ።

ት ር ጉ ም

አባት መልከጼዴቅ በሲኦል (በመቃብር) ቢመላለስ
አቤል ነፍሱ እስክትወጣ ድረስ ደነገጠ ።

ም ስ ጢ ር

የሚጫወት ልጅ አባቱ በድንገት ሲደርስበት እንደሚደነግጥ ፤ የልጁ ጭረሴ ፣ሆነው የመልከጼዴቅ ቤተ ክርስቲያን ያለበት መቃ ብር የአባት ምሳሌ በሆነው በመልከጼዴቅ ቃል ኪዳን የሙታንን ሕካል እስማናረሱንና አለማበሰበሱን ባለትኔው በትኔያቸው ምስጢር ይገልጣሉ ።

መልክዒያት በተባሉ ኢትዮጵያዊ ፃድቅ ሰም የተመሰረተ ቤተ
ክርስቲያን በሸዋ ክፍለ ሀገር ሚዳ በሚባለው ወረዳ በሚገኝ ዋ
ውስጥ አለ ። ያካባቢው ኗሪዎች የሞቱትን ሰዎች ሬሳዎች (አስከሬ
ኖች) በዚሁ ዋሻ ውስጥ ያኖሩበታል ። የሙታኑ አስከሬናችም ሳይ
ፈርሱና ሳይበሰብሱ ደርቀው ይኖራሉ ። ይህም ሊሆን የቻለው ለ
ድቅ መልክዒያት በተሰጠው ቃል ኪዳን መሰረት ነው እየተባ
ይተረካል ።

127 ዘአምላኪየ

ዘረንታዩ (አለቃ)

ለእመ ኀለፈ ወልድ ሐዋርያ ወንጌል በናእሱ
መቃብር እሙ ትበኪ በልብሱ ፤
ወይ ሊተ ብሂላ እንዘ ኢትመፅእ ነፍሱ ።

ትርጉም

የወንጌል ሀዋርያ ልጅ በህፃንነቱ ቢሞት
ነፍሱ ሳትወጣ ፡ ወዮልኝ ብላ
እናቱ/ መቃብር በልብሱ ታለቅሳለች ።

ምስጢር

ልጅ ሲሞት ገና ነፍሱ ሳትወጣ ጀምራ እናቱ ልብሱን ይ
እንደምታስትስ ፡ የልጅ ምሳሌ የሀገሯ ወልደ ነጎድጓድ ሲሰመር የ
ናት ምሳሌ በሆነች መቃብር ላይ ልብሱ ወድቆ ተገኘ በማለት ባ
ቅኔው ቅዱሳኖቹን አመሰጥረዋል ።

128 ዋዜማ

ዘለማ ጎይሉ (አለቃ)

መቃብር ዘይትራድኦ
ለሊቶ ካህናት ሞት በተልእኮ ድንግል መቅደሱ
ተከልአ እምበሊዐ ሥጋ ወፈትሐ በርእሱ ፤
አመ እምቀትለ ፈርያን ጕየ በጎደለ ሙሴ ፈረሱ
ነሢአ ሲጋሁ ለዳታን ምስለ ነፍሱ
አስመ መልዐ ወኢሐጸ ክርሱ ።

ትርጉም

በድንግል/ መቅደሱ
አገልግሎት የካህናት አለቃ/ ሞትን የሚረዳ መቃብር
ስጋን ከመብላት ተከለከለ ፡ በራሱም ፈረደ፤
በሙሴ/ ፈረሱ ሀይል ከፈርአን ጦርነት በሸሸ ጊዜ
የዳታን ስጋን ከነፍሱ ጋር በመያዙ
ሞዱ ሞላ እንጂ አልጎደለምና ።

ምስጢር

ንፍቁ ቂስ (ሁለተኛው ቂስ) ገባሬ ሰናዩን ቂስ (ዋናውን ቂስ)
በቤተ መቅደስ አገልግሎት ስራ እንደሚረዳው ፡ የንፍቁ ቂስ ምሳሌ
የሆነ መቃብር የገባሬ ሰናዩ ቂስ ምሳሌ ከሆነው ሞት የመቅደስ
ምሳሌ የሆነች ማርያምን አገኘ ።

ደግሞ በአሪት ህግ ስጋ አብሳዩ ያበሰለውን ስጋ ራሱ እንደ
ግይበላው የአብሳዩ ምሳሌ መቃብር የመስዋእት ምሳሌ የሆነች የማ
ርያምን ስጋ አለማፍረሱንና አለማበስበሱን ቅኔው ይገልጣል ። የተሸ
ነፈ ተዋጊም ከጦር ሜዳ በፈረሱ እንደሚሸሽ በኤርትራ ባህር የሰ

ሙሴ ፈርኦን በመቃብር ሳይቀብር መትረቱን ባለትኔው ያስረዳሉ ። በተዉግሪም በለላ ቤት ሲጋን እንደመጥንብ ዳታንን ምድር ተከ ፍቶ መዋጡን የትኔው ምስጢር ያሳያል ።

ታሪክ

በአረት ስርአት የመስየእቱን ስጋ በመተቀልና ትትሉን በሹካ በማትረብ ካህኑን የሚያገለግለው ታዛዥ ለካህኑ የሚሆነውን መቅ መስ አይችልም (ዘሁል .18) ።

የንብዕ ንጉስ ፈርኦን አስራኤልን ሊመልስ ሲገሰግስ በኤርትራ ባህር ውስጥ ሰጥም ቀረ እንጂ እንደወጉ መቃብር ተቆፍሮለት በአ ጉሉ አልተቀበረም (ዘፀአ.14፡1—15)።

ዳታንና አቢሮን በሙሴ ላይ ስላመፁበትና ከፉ ስለመከሩበት ምድር ተከፍቶ ውጧቸዋል ይላላል (ዘሁል. 16፡1—35) ።

129 ዋዜማ

ራጌል ፈትሰ እዲሃ
አግልክተ ወርቅ ሰረተቅ ውስተ ጽርሐ ነቢይ ኢያሱ ፡
ወያዕቆብ መንጦላዕተ ወርቅ ሰመረ በልብሱ ፤
ወገበ ሶስና ድንግል ዘበዐጸደ ወይን ታንሶሱ
ከልኤሆሙ ሙና ወወይን ረበናት ጌሙ
ዘርጉብ ገቦሃ ይግሥሙ ።

ትርጉም

የእጅዋ ፈትል /ራሄል
በነቢይ ኢያሱ አዳራሽ ውስጥ የወርቅ አግልክትን ሰረቀች፡
ያእቆብም የወርቅ መጋረጃን በልብሱ ሸሸገ፡
በወይን ቦታ ወደምትመላለስ ሶስና /ድንግልም
ሁለቱ ሙናና ወይን/ መምህራን ገሰገሱ
የተራብ ነፍን ይዳብሱ ዘንድ ።

ምስጢር

ያእቆብ ከአጎቱ ከላባ ኮብልሎ ወደአባቱ ቤት ሲሄድ ሚስቱ ራሄል የአባቷን የወርቅ አግልክት እንደሰረቀች የራሄል ምሳሌ የሆነች የድንግል ማርያም የእጅዋ ፈትል ወርቅ መሆኗንና ያእቆብም ነገሩን እንደሰመረ መጋረጃውም የወርቅ ልብስ መሆኑን ትኔው ያስረዳል ።

ደግሞ ሁለት ረበናት(መምህራን) በወይን ቦታ ወደምትመላለስ ወደሶስና እንደገሰገሱና እንደያዟት ፡ የረበናት ምሳሌ የሆኑ መናና ወይን ለቅድስት ድንግል ማርያም መውረዳቸውንና ምግቢና መጠጢ መሆናቸውን ባለትኔው ያስገንዝባሉ።

ታሪክ

ራሄል የላባ ልጅ የያእቆብ ሚስቱ ናት ። ባሏ ያእቆብ አባቷን ሃያ አመታት ካገለገለ በሁዋላ ኮብልሎ ወደአባቱ አገር ሲሄድ የአባ ቷን የወርቅ አግልክት ሰርቃ አብራው ሄደች ። እነርሱም በሄዱ በሶ ስተኛው ቀን ላባ መኮብለላቸውን ሰማና ተከታትሎ በሰፈሩበት ተራራ ደረሰባቸው። ያእቆብም ሚስቱ ራሄል የአባቷን የወርቅ አግ ልክት መስረቋን ስላላወቀ ላባ ድንኳናቸን እንዲበረብር ፈቀደለት። ራሄል ግን የሰረቀቻቸውን የወርቅ ምስሎች በግመል ኮርቻ ስር አድርጋ «አደፍ (የወር አበባ) ታይቶኛል» በማለት ተቃመጠችባ ቸው ። በዚሁ ምክንያት አባቷ ድንኳኗን ሲበረብር አልተነሳችም ፤ እርሱም (ላባ) ያልተቀመጠችበትን እቃ ብቻ በርብሮ ወጥቶ ሄደ (ዘፍጥ. 31፡1—35) ።

130 ዋዜማ

ዘአድግሱ (መልከ ብርሃን)

ተመስሳይያን ፈደላት
ከመ ብክሙ ሥርዐት በውስተ መጻሕፍት ቅኅሥሡ
በበቤቅክሙ በሥርዐቅ ንኅሡ ።

መኢቅፋፋሱ ቤተ በቤት ባዕዳን ቅንጭ ፤
በጎበ ግእምራን ፈታሕት እስመ ይቅውቀሱ
በኢሕግ ቤት ባዕድ ዘጌሙ ።

ትርጉም

ሞክሸዎች ፈደሉች
በመዕፀዊ ውስጥ ስርአት እንዳላችሁ ትሹ ዘንድ
በየቤታችሁ በስርአት ግቡ፣
በባእዶች ቤት ትነግሱ ዘንድ ከቤትም አትሰደዱ፤
ያለህግ ወደባእድ ቤት የሄዱ በአዋቂዎች
ፈራጆች ዘንድ ይወቀሳሉና።

ምስጢር

ባለስልጣኖች በራሳቸው ይዞታ መኖር እንጂ የሌላውን ሰው ድርሻ መውረስ እንደማይገባቸውና ቢወርሱም እንደሚወቀሱ ፤ እንዲሁም ዘጠኙ ፊደሎች ሀ ፡ ሐ ፡ ኀ ፡ ሠ ፡ ሰ ፡ ጸ ፡ ፀ ፡ አ ፡ ዐ ፡ እያንዳንዱ በልዩ ልዩ ቃል የሚገቡበት ስርአት ስላላቸው በፅሁፍ አገባባቸውን ግለዋወጥ አይገባም ። ቢለዋወጡም ፀሀፊውን ያስንቅሩ በግለት ባለቅኔው ፡ስለፊደላት አጠቃቀም ያላቸውን አስተያየት በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

131 ሥላሴ

ዘተክለ ጽዮን (አለቃ)

ወልድ ወተክለ አልፋ
ለዮኮ ገጻም ተግሰጥዎ
እስመ ተክለ አልፋ ጸድቅ ለእግሩ መመድኅን ዓለም ለርእሱ
ዮኮ በሊሐ ልሳን እምገጻም ኀሠሡ ።
ግትያስሰ ወኪርስ አሙ በዋሕድና ፈለሱ

ህዝቡ ጠላቶቻቸውን እየተከታተሉ እስኪያጠፉ ቀኑ እንዲረዝም
ወደ እግዚአብሄር አመለከተ ፤ እስራኤልም የከነአንን ነገስታት እሸ
ንፈው አገሩን እጅ እስካደረጉ ድረስ ቀኑ ረዘመላቸው ይባላል ።
(ኢያሱ. 10 ፡ 1—15) ።

163 መወድስ

ዘገብረ ሥላሴ (መምህር ፡ ዘኤልያስ)

ቦ ጎያል በዲበ ጎያል ፤
እስመ እንዘ በለሰ ይትሜካሕ በላዕለ አዳም ርእስ
መደንግፅ ዝናም ንጉሠ ጢሮስ
ነሠተ ቤተ ልምላሜሁ ለመካሕ በለስ ።
ወእንዘ ይትሜካሕ በበለስ
ውእቱ ጠል ጎፍረ በኤልያስ ።
ኤልያስሂ እንዘ ውእቱ ቀታሌ ዝናም ነፍስ
ተንሥአ በላዕሌሁ ዘይመውአ ጎይለ ተጽናስ ፤
ወእንዘ ረኃብ ይጸርሕ በዘኤልያስ መቅደስ
ለረኃብ ተበቀሎ ዘመደ መባልዕት ኢዮስያስ ።

ትርጉም

በሀይለኛ ላይ ሀይለኛ አለበት ፤
በለስ በአዳም ራስ ላይ ሲመካ
አስደንጋጭ ዝናብ/ የጢሮስ ንጉስ
የትምክህተኛ/በለስ ልምላሜ/ቤትን አፍርሷልና ።
ዝናብም በበለስ ሲመካ
ያው ርጥበት (ዝናብ) በኤልያስ አፍሯልና ።
ኤልያስም የዝናብ/ ነፍስ ገዳይ ሲሆን
የሚያሸንፈው የችግር ሃይል በርሱ ላይ ተነሳ ፤
ራብም በኤልያስ መቅደስ ሲጮህ
ራብን የመብሎች ዘመድ/ኢዮስያስ ተበቀለው ።

ም ስ ጢ ር

በአጥቂው ላይ አጥቂ አለበት ። ሃይለኛው በደካማው ላይ ሲመካ በትምክህተኛው ላይ ሌላ አሸናፊ ተነስቶ ቤቱን ይመዘብርበታል ፤ እንዲሁም በለስ ለአዳም የሞት ምክንያት ቢሆንበት የከረምት ዝናብ የበለስን ልምላሜ አደረቀበት ።

ደግሞ ቤት መዝባሪው በተሸናፊው ላይ ሲመካ ተመኪው በሌላ አሸናፊ ድል ሆኖ እንደሚያፍር ፤ ዝናብ በለስን ሲያደርቅ እርሱ ደግሞ በነቢይ ኤልያስ ጠፋ ። አሳፋሪውም ነፍስ ገዳይ ሌላ አሸናፊ እንደሚነሳበት ዝናብን ያጠፋ ነቢይ ኤልያስን ራብ ሞረሞረው። ነፍሰ ገዳዩ አሸናፊም ሲፎክር ፎካሪውን የተገዳዩ ዘመድ እንደሚበቀለው ምግቦችን ያዘጋጀ ኢዮስያስ ራብን አጠፋው በማለት ባለ ቅኔው አመስጥሮዋል ።

ታ ሪ ክ

አዳም ከክብሩ የተዋረደውና ከክብር ቦታው ገነት የወጣው ፤ በሞተ ስጋም ላይ ሞተ ነፍስ የተፈረደበት በበለስ መብል ምክን ያት ነው ። አምላክ ብላ ያለውን በልቶ አትብላ ያለውን ትቶ ቢጠነ ቀቅ ኖር ፤ ከሺህ ዘመን በውዋላ እፀ ሀይወትን በልቶ በመታደስ በመ ንግስተ ሰማይ ይኖር ነበር ይባላል ። በለስ ለአዳም የስህተት ምክ ንያት የሆነበት እፅ ሲሆን በክረምት ዝናቡ ስለማይስማማው አይለ መልምም ቅጠሉም ሁሉ ይረግፋል ።

ኤልያስ የቴስብያ ነቢይ ነው ፤ በዘመኑ የነበረው ንጉስ አክአብ ዘማዊት ኤልዛቤልን አግብቶ ጣኦት አመለከ ። ነቢዩም ቢመክረውና ቢያስተምረው ንጉሱ ከክፉ ስራው ወደ እግዚአብሄር አልመለስ አለ። በዚህም የተነሳ «ይህ ሁሉ ጥጋብ መደረጉ በዝናብ አብቅለህ በፀ ሀይ አብስለህ ብትመግባቸው አይደለምን ? ከእንግዲህ ወዲህ አት ግቸውን ይወቁት ፤ ሰማይ ዝናብ ሲዘር ፤ ጠል ለመከር አይስጥ» ብሎ ኤልያስ ወደ አምላኩ አመለከተ ። እንዳለውም ሆነለት ፤ ሶስት አመት ከስድስት ወር ዝናብ ከመዝነብ ተከለከለ ። እህል ጠፋ ፤ ራብ ጠና

ወንዞች ደረቁ ፤ ንጉሱ ከነሰራዊቱ በፀሀይ ሀሩርና በድርቅ ተቀጣ ። ይህን አድርጎ ሳለ ራሱ ነቢዩ ኤልያስ ተራበ ፤ እንዲት ሴት ጥቂት እንጨት ስትለቃቅም አገኘና ከርሷ እህልና ውሃ እስከ መለመንና ከልጅዋና ከርሷ በፊት ለመብላት እስከ መንሰፍሰፍ ደረሰ ። ሴቲቱም በቅድሚያ ሰጠችውና በልቶ ቤቷን ባረከ (1 ነገስ. 17 ፥ 1—24)

164 መወድስ

ዘደግዛው (አለቃ ፥ ዘደብረ ወርቅ)

በፈለገ ሐሊብ ወወይን ኢንቄልጦሙ
ለዘበደብረ ወርቅ ሀለዉ ማያተ ሕይወት ወፈውስ ፤
እስመ አሠነዮሙ አብ ኤዎስጣቴዎስ
እምሐሊብ ጸዐዳ ወእምወይን ሐዲስ ፥
ወኢንትሜነዮ ለዮርዳኖስ
ሰብአ ደብረ ወርቅ፣ማይኑ እስመ ይትዔረዮ ለዮርዳኖስ ።
ሀለወሂ ወኢሀለወ ቅድመ አነዳ ንኡስ
ኢይትበሀል ኢያሪኮ ፤ እምጣነ ርጡብ ወይቡስ ።
ወመልዕልታ ተሐንጸ ቤተ ኤዎስጣቴዎስ ርእስ ፤
እስመ ርእሰ እድባር ደብረ ወርቅ ወርእሰ ደብረ ወርቅ
መንፈስ ቅዱስ ።

ት ር ጉ ም

በደብረ ወርቅ ያሉ የህይወትና የፈውስ
ውሃዎችን በወተትና በወይን መንዝ አንለውጣቸውም ፤
አባት ኤዎስጣቴዎስ ከነጭ ወተትና
ከአዲስ ወይን ይልቅ አሳምሯቸዋልና ፥
የደብረ ወርቅ ስዎችም
የርዳኖስን እንመኘውም ፤ ውሃችን የርዳኖስን
ይስተካከለዋልና ።

በትንሹ አፅፍ (ቁርበት) ፊትም ኢያሪኮ
አለ ፣ የለም አይባልም ፤ እርጥብና ደረቅ ነውና ።
የኤዎስጣቴዎስ ጉልላት ቤትም በላይዋ ተሰራ ፤
የአድባራት ራስ ደብረ ወርቅ ናትና ፣ የደብረ ወርቅ ራስም
መንፈስ ቅዱስ ነውና ።

ም ስ ጢ ር

አንድ ትንሽ ነገር ትልቅ ዋጋ ካወጣ በትንንሽ ነገሮች አይ
ለወጥም ። እንዲሁም በጎጃም የደብረ ወርቅ ማርያም ፀበል የህ
ይወት ውሃ ስለሆነ ከወተት ወንዝና ከወይን ወንዝ ይበልጣል ይላሉ
ባለቅኔው ።

እንዲሁም የከበረ እቃ ያለው ሰው ሌላ እቃ እንደማይፈልግ ፣
የደብረ ወርቅ ፀበል እንደ ዮርዳኖስ ስለሆነ የዮርዳኖስ ፀበል በደ
ብረ ወርቅ ሕሰፈላጊ አለመሆኑን ቅኔው ይገልጣል ። ከዚህም ሌላ
አባይና መስላታ የሆነ ሰው መኖሩም አለመኖሩም እንደማይታወቅ
የኢያሪኮ ባህርም ሙሉ ሲሆን በኤዎስጣቴዎስ አፅፍ መርከብነት
የድቁን ከነደቀመዛሙርታቸው ማሻገሩን ባለቅኔው ያስገንዝባሉ ።

በተጨማሪም ቤት ሲሰራ በራሱ ላይ ቤተሞስ (ጉልላት)
እንደሚደረግበት በኤዎስጣቴዎስ ክብር ደብረ ወርቅ ከአድባራት
በላይ መሆኗንም ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

ታ ሪ ክ

ከጎጃም አድባራት አንዷ ገዳም ከደብር የሆነችና በማርያም
ስም የተመሰረተች ደብረ ወርቅ ናት ፤ የአባ ኤዎስጣቴዎስ በአል
መከበረም አስራ ስምንት ቀን ይከበርባታል ። ከደጄ የሚፈሰስ
የህይወት ውሃ አለባት ። በሽተኞች ከርሱ እየጠጡ ከሆድ ህመም
ይድኑበታል ። የድቁ አባ ኤዎስጣቴዎስ ስለቀዳሚት ሰንበትና ስለ
አሁድ ሰንበት ከአርማንያው ሊቀ ጳጳሳት ለመረዳት ከኢትዮጵያ
ወደአርማንያ በሄዱ ጊዜ የኢያሪኮን ባህር ከእነተማሪዎቻቸው በአፅ
ፋቸው ሲሻገሩ ባህሩ ፀጥ ብሎላቸዋል ይባላል ። ደብረ ወርቅ

የእግዚአብሄር ቃል በድንግል ማርያም ማህፀን በተፀነሰና ስጋ በሆነ ጊዜ
በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ከበረ ማለት ሲነገርባት የኖረች ደብር ናት ።
ይሁን እንጂ የጎጃም ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ አብር
ሃም «ስጋ በተዋህዶተ ቃል ከበረ» ወደ ማለት እምነት መልሰዋ
ታል ተብሎ ይነገራል ።

165 መወድስ

ዘባቱኤል

አሐዱ የጎጥአ በውስተ ዓለም
እንተ አሐዱ ዓለም ረከበ በጎሚሥ ፤
ምሕዋራተ ራትዕ ዳዊት ፍናወ መንበር ወንግሥ
ርቱዐ አምጣነ ኢሖረ ኤልያብ ሐንካስ ።
ኢፈረዩሂ ውስተ መቅደስ
ደቂቀ ቆሬ አሥዋክ አስካለ አሮን በለስ ።
አክዓብሂ ወአብድዩ እምነ ቀላይ ወየብስ
እመ ሣዕረ የጎሥሡ ለበቅል ወለፈረስ
በዓመተ ኤልያስ ጎጥኡ ሣዕረ ሊባናስ
ለኪሮስ እንዘ ልብሱ ወእንዘ ምግቡ ለማትያስ ።

ት ር ጉ ም

አንዱ አለም በፍለጋ ያገኘውን
አንዱ (ከሌላው) በአለም ውስጥ ያጣል ፤
ቅን የነበረ የዳዊት መሄጃዎች የሆኑ የንግስና የዙፋን
መንገዶችን
እንካሳ ኤልያብ ቀጥ ብሎ አልሄደምና ።
የቆሬ ልጆች/እሾሆችም
የአሮን/በለስ ፍሬን በመቅደስ ውስጥ አላፈሩም ።
አክአብና አብድዩም ከወንዝና ከየብስ

ሳር ለፈረስና ለበቅሉ ቢፈልጉ
ለኪሮስ ልብሱ ለግትያስም ምግቡ ሲሆን
የሊባናስን ሳር በኤልያስ ዘመን አጡ ።

ም ስ ጢ ር

አንዱ ያገኘውን ሌላው ሊያገኘው ባለመቻሉ እያንዳንዱ ሰው የተለያየ እድል እንዳለው ቅኔው ያስረዳል። ይኸውም ሊታወቅ እንካሳ ሰው መንገድን በቀጥታ እንደማይሄድ ኤልያብ የታናሽ ወንድሙ የዳዊትን እድል አልታደለም ። ከዚህም ሌላ እሾሆች የበለሰን ፍሬ እንደማያፈሩ የቆሬ ልጆችም የአሮንን እድል አልታደሉም ። አክ አብና አብድዩ ለፈረስና ለበቅሏቸው ያጡትን ሳር ማትያስ በላው ኪሮስም ተኛበት በማለት ባለቅኔው ስለሰው ልጅ ኑሮ ውጣ ውረድ ያላቸውን አስተያየት በቅኔያቸው አመሰጥረዋል ።

ታ ሪ ክ

ከእሴይ ልጆች ታላቁና ረገደ መልካሙ ኤልያብ ሲሆን ለመ ንግስት የተመረጠው ታናሹ ልጅ ዳዊት ነው ። ነቢዩ ሳሙኤል የፈቱን ግርማና የቁመቱን ታላቅነት በማየት ወደኤልያብ ሲመለ ከት እግዚአብሄር ወደዳዊት ተመለከተ (1 ሳሙ. 16 ፡ 1—13) ።

አሮን የሙሴ ወንድሙ ሲሆን ለክህነት ስራ ተመርጦ በደብ ተራ አሪት ሲያገለግል ኖሯል ። የቆሬ ልጆች ግን ያልተፈቀደላቸ ውን የአሮንን ስራ እንሰራለን በማለት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ሲያ ጥኑ ጢሱ ቢነካቸው ፡ ልብሰ ተክህኖው ሳይቃጠል ሰውነታቸውን የተለበለበ ግንድ አስመስሎታል (ዘሁል. 16 ፡ 1—35) ።

አክአብና አብድዩ ለፈረስና ለበቅሉ ለምለም ሳር ለመፈለግ ወንዝ ለወንዝ ሲሄዱ አብድዩ ነቢይ ኤልያስን አገኘው (1 ነገስ. 18 ፡ 3—16) ።

ዘሜልቲ ጎይሉ (አባ)

በዘመነ ንጉሥ ብልጣሶር ለእመ ሀለዉ
ገብረ መርዓዊ ወኢዮብ እርድእተ ኦሪሚ ክርስቶስ
ወእመ ርእዩ አጽባዕተ በአረፍት ቤት ይቡስ ፡
ዕፃ ንትፋሰስ እምተባህሉ ፡
ወይርከባ ለዘይረከባ በዛቲ ለንግሥ ፡
ዛቲ እስመ አሐቲ
ወኢሀለውዋ ምንተ አምትንተ ሥጋ ወሥርወ ርእስ ።
ባሕቱ እምዐጸቦሙ አስተጸንፆታ ለነፍስ ፡
እስመ ለክልኤቱ ኢተውህቦሙ ጥበበ እደ ቶማስ ዲዲ
ሞስ ፡
ወእመ እንታክቲ አጽባዕት እንተ ትገሥሥ
በዓለ አጽባዕት እምቀደሞሙ በነሢአታ እምላዕለ ናሕስ ።

ትርጉም

የንጉስ ክርስቶስ ተማሪዎች ገብረ መርአዊና
ኢዮብ በንጉስ ብልጣሶር ዘመን ቢኖሩ
በደረቅ ቤት ግድግዳም ጣቶችን ቢያዩ ፡
እጣ እንጣጣል ይችንም በንግስ
የሚያገኛት ያግኛት በተባባሉ ነበር ፡
ይችው አንዲት ናትና ፡
የስጋ ጅማትና የራስ ስርም ምንም የሏትምና ።
ነገር ግን ነፍስን ግጥናት በጨነቃቸው ነበር ፡
ዲዲሞስ የተባለ የቶማስ እጅ ጥበብ ስሁለቱ አልተሰጣቸ
ውምና ፡
ያች ጣቷም የምትዳስስ ብትሆን ኖሮ
ባለ ጣት እሷን ከግንብ ላይ በመያዝ በቀደማቸው ነበር።

ም ስ ጢ ር

ኢዮብና ንብረ ከርስቶስ ጣቶቻቸው በደዌ ስጋ ስለተቆረጡ በብልጣሶር ግድግዳ ላይ «ማኒ ቴቄልን» በፃፈችው ድብቅ ጣት እንደሚሻሙባትና ጣቲቱ የምትዳስስ ብትሆንም ሌላ ባለጣት እንደ ሚቀድማቸው በማመልከትና እነርሱም በመቆረጥ እንደ ቶማስ ሀዋ ርያ አለመሆናቸውን በመግለጥ ቅኔው ተመስጥሯል ።

ታ ሪ ክ

ብልጣሶር የናቡከደነፆር ልጅ ነው ፤ ለመኳንንቱ ታላቅ ግብዣ አደረገ ። አባቱ በኢየሩሳሌም ከእግዚአብሄር ቤተ መቅደስ ዘርፎ የወሰዳቸውን የብርና የወርቅ እቃዎች መኳንንቱና ወይዛዝርቱ እቁባቶቹና ሚስቶቹ የወይን ጠጅ ጠጡባቸው ። ያን ጊዜ አምላክ ተቆጥቶ የሰው እጅ አምሳል ጣቶች በቤቱ ግድግዳ ልስን ላይ ሲፅፉ በህልሙ አያቸው ። በዚህ በጣም ታወከ ፤ በሚስቱ ምክርና ጥቆማ ተመርቶ ነቢይ ዳንኤልን አስመጥቶ የፅሀፈቱን ፍቺ እንዲነግረው ነገሩን ገለጠለት ። ነቢዩም ፅሀፈቱ «ማኒ ቴቄል ፋሬስ» የሚልና የእጅ ጣቶችም የእግዚአብሄር ስልጣን ቅእዛዞች እንደሆኑ ፣ ፍቻ ቸውም «እግዚአብሄር መንግስትህን ፈፀመው ፣ በሚዛን ተመዝነህ ቀለልህ ፤ መንግስትህ ተከፍሎ ለፋርስና ለሜዶን ተሰጠ» ማለት እንደሆነ አስረዳው (ዳን 5 ፡ 1—31) ።

167 አጭር ኩልክሙ

ኬፋ ላዕለ አይሁድ እሳተ ረዋጺ ነፋስ ፤
ወአይሁድ ለኬፋ አዕይንት ዘጢስ ።

ት ር ጉ ም

ጴጥሮስ በአይሁድ ላይ የሯጭ ነፋስ እሳት ነው ፤
አይሁድም ለጴጥሮስ የጢስ አይናች ናቸው ።

ምስጢር

ነፋስ ያነሳሳው እሳት ቤቶችን እንደሚያቃጥል ፣ መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ጴጥሮስ አይሁድን አስፈራቸው ፤ አይናች በጢስ እንደሚታ መሙ አይሁድ በጴጥሮስ ቃል ተረቱ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

168 ግእዝ ክብር ይእቲ

በበለስ ዘሐመ አድኅነ በበለስ ።
እግዚአብሔር ዘሰብአ ወዘመላእክት አፍራስ ፤
እምቅድመ ዝኒ ተገብረ በሀገረ ሮሜ ወፋርስ ፤
በሦክ ዘሐመ አምጣነ በሦክ ይትፈወስ ።

ት ር ጉ ም

የሰውና የመላእክት/ፈረሶች እግዚአብሄር
በበለስ የታመመውን በበለስ አዳነ ፤
(ይህ) ከዚህም በፊት በሮምና በፋርስ አገር ተደርጓል ፤
በሾህ የታመመ በሾህ ይድናልና ።

ም ስ ጢ ር

« እሾህ በእሾህ ይነቀላል በደል በካሳ ይመለሳል » እንዲሉ በእንጨት የታመመው ሰው በእንጨት እንደሚድን ፤ በበለስ ቅጠል መብል የወደቀ አዳምን ከርስቶስ በእንጨት መስቀል አዳነው ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

ታ ሪ ክ

በሽተኞች የበለስን ደም እየተቀቡ ይድኑ ነበር ። ከዚህም የተነሳ ኤርምያስ አቤሜሌክን ለድውይ የሚቀባ የበለስ ቅንቡጥ እንዲያመጣ ልኮታል ። ሀማ መርዶክዮስን ለመስቀል ረኃም እንጨት በበሩ አቁሞ በዚህም ላይ የመርዶክዮስ ወገኖች ሁሉ እንዲጠፉ ከንጉስ አርጤክስስ አስፈቅዶ ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር ። የንጉሱ ሚስት

አስቴር የመርዶክዮስን ልቅሶ ስምታ የሶስት ቀን ፆምና ፀሎት ከእነወገኖቿ በጥብቅ አደረገችና ለንጉሱ በግብዣዋ ላይ ግፋን አስረዳች ። ስለዚህም ንጉሱ ልመናዋን ተቀብሎ ሀማን ለመርዶክዮስ በአዘጋጀው እንጨት ላይ ሰቅሎታል (አስቴ.3—8) ።

169 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ሐንካሳን አልዐሱ እደዊሆሙ ጎቡረ ፡
እስመ ገሠደሙ አብ ከመ ኢያንሥኡ በትረ ።

ት ር ጉ ም

አንካሶች በአንድነት እጆቻቸውን አነሱ ፡
በትር እንዲያነሱ አባት ተቆጥቷቸዋልና ።

ም ስ ጢ ር

ለመግታት በትር ያነሱ ጎበዞች እባታቸው በተቆጣ ጊዜ እጆቻቸውን ወደላይ አንስተው በትር አለመያዛቸውን ለአባታቸው ያረጋግጣሉ ። እንዲሁም የጎበዞቹ ምሳሌዎች የሆኑ አንካሶች ከበሽታቸው ከዳኑ በሁዋላ ያለበትር ሂዱ ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

170 ዘአምላኪየ

ዘገብረ ሥላሴ (መምህር፣ ዘኤልያስ)

ቀዳሚ ፈሐጠ ዘንግሥተ አዜብ እግረ
መስቀል ወሬሣ ዘይከብት ነውረ
እንዘ ይብል አመጽአ ደኃሪ ጎበ ሀሎኪ ሀገረ ።

ት ር ጉ ም

ነውርን የሚደብቅ ጎበዝ/ መስቀል
ወዳለሽበት አገር በሁዋላ እመጣለሁ እያለ
የንግስተ አዜብን እግር በመጀመሪያ ቆነጠጠ ።

ም ስ ጢ ር

አንዳንድ ዝሙተኛ ጎልማሳ የሌትየቱን እግር ቆንጥጦ (ይቆነጥጥና) «ወደ ቤትሽ እመጣለሁ» ይላታል ። እንዲሁም የአዜብ ንግስት የነበረችው ግክዳ ወደሰሎሞን ቤት ስትገባ ከሰሎሞን በር ተጥሎ የናረው እንጨት ባንቀፋት ጊዜ በእግሯ ላይ የነበረውን የሀም ተቀጥላ አወልቆ ጣለላት ። በዚህም እንጨት ክርስቶስ ከተሰቀለበት በሁዋላ በአፄ ዳዊት ዘመን ግማደ መስቀል (የመስቀል ክፋይ) ወደንግስተ አዜብ እገር ኢትዮጵያ ገባ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል።

ታ ሪ ክ

በእስራኤል ንጉስ በሰሎሞን ደጅ የሚኖር ከቤተ መቅደስ ስራ የተረፈ እንድ እንጨት ነበር ። የኢትዮጵያ ንግስት ግክዳ (ንግስተ አዜብ) የሰሎሞን ገናናነትና ጥበበኛነት ሰምታ በጀርዋ የሰማችውን በአይኗ አይታ ለመረዳት ወደኢየሩሳሌም ተጓዘች ። ከዚያም በደረሰች ጊዜ ወደሰሎሞን ቤተ መንሰግት ስትገባ እንጨቱ በእግሯ ላይ እንደ አሀያ ሸሆና የነበረውን ተቀጥላ ነገር አንቅሮ አወለቀላት ። ይህም እንጨት ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ሆኖ ተሰርቷል ። ቁራጩም በአፄ ዳዊት ዘመን ወደኢትዮጵያ መጥቶ በግሸን ማርያም አንባ ተቀብሯል ይባላል (ክብረ ነገስት) ።

171 ዘአምላኪየ

ወልደ ነጐድጓድ ተሰደ እንዘ የጎድግ ሀገረ
እምጎበ አጥፍአ ሞተ ሰብእ ሥረ ፤
ገራህቱ መቅበርት እምጣነ አብቁለት ማዕረ

ወልደ ነጎድጓድ (ዮሀንስ) የሰው ሞት /በራን
ከአጠፋ ዘንድ አገር ትቶ ተሰደደ ፤
እርሻው መቃብር ሳር አብቅላለችና ።

ምስጢር

በራ ያጣ ገበሬ እርሻው ዳዋ ለብሶ ሲቀርበት አገር ጥሎ ቁር
በት ጠቅልሎ ይሰደዳል ። በእንግሩም የገበሬው ምሳሌ ዮሀንስ
ወልደ ነጎድጓድ ከመኖሪያው አለም ተለይቶ ተሰወረ ሞትን አሸነፈ ።
ለርሱ የተቆፈረው መቃብርም መስክ ሆኖ ተገኘ ይላሉ ባለቅኔው ።

ታሪክ

ዮሀንስ ወልደ ነጎድጓድ መቃብር አስቆፍሮ ደቀ መዛሙር
ቱን ሰው እንዲጠሩ ወደ ሰፈር ላካቸው ። እነርሱም ከሄዱበት
ቢመለሱ አጡት ፤ መቃብሩም መስክ ሆኖ አገኙት ። ልብሱንና በት
ሩን ጭራውንም በዚያ ትቶ ተሰውሯል ተብሎ በአንድ ፊት ሲተ
ረክ ፥ በሌላ በኩል ደግሞ እንደሌሎቹ ሀዋርያት በመስቀል ተሰቅሎ
በሰይፍ ተቆርጦ አልሞተም እንጂ ንፁሁን ሞት ሞቶ ተቀብሯል ።
ለምልክትም ልብሱና በትሩ ጭራውም በመቃብሩ ቦታ ተገኝተ
ዋል ተብሎ ይተረካል (ስንክ.ጥር 4) ።

172 ሚበገሩ

ሚካኤል ዘፈርሀ
ባሕርያተ መሬት ወማይ ጸብአ ወነገረ
ሥጋቆ ምሕረተ ምስለ ሥጋቆ ፈርዮን ኢደመረ ፤
እስመ እንዘ ረኃብ በግብጽ እንተ ይበልዕ በሊያ ለዘይብእስ
እንበረ ።

የመሬትና የውሃ
ባህርዮች/ ጠብና ነገርን የፈራ ሚካኤል
ምህረት/ ስንቁን ከፈርኦን ስንቅ ጋር አልቀላቀለም
(አልደባለቀም) ፤
በግብፅ ራብ ሳለ የሚበላውን በልቶ ለሚብስ ጊዜ
አስቀምጧልና ።

ምስጢር

በችግር ጊዜ ያንዱ ገንዘብ ከሌላው ገንዘብ ጋር ሲቀላቀል
ስለሚያጣላ ፥ ይህን የተገነዘበ መንገደኛ ስንቁን ከጓደኛው ስንቅ
ጋር ሳይቀላቅል የበላውን በልቶ የተረፈውን ለባሰ ቀን ያኖራል ።

እንዲሁም የመንገደኛው ምሳሌ መልአክ ሚካኤል ከእሳትና
ከነፋስ እንጂ ከመሬትና ከውሃ አልተፈጠረም ። ለንሙሴ ያደረ
ገው ትድግናውንም ለፈርኦን አላደረገም ። በግብፃውያን ላይ መከ
ራን ሲያፀና በምህረቱ እስራኤልን በሙሴ መሪነት ኤርትራን ፥ በኢ
ያሱም መሪነት ዮርዳኖስን አሻግሯል ይላሉ ባለቅኔው ።

ታሪክ

መላእክት መንፈስ ናቸው ፤ ከሁለቱ ባህርያት ከነፋስና ከእ
ሳት«እምኀበ አልቦ (ያለ ምንም ጥንተ ተፈጥሮ) » ተፈጠሩ ይባላል ።

ስለዚህም በአይነ ነፍስ እንጂ በአይነ ስጋ አይታዩም ። መላእ
ክት ለምህረትም ፥ ለመአትም ከእግዚአብሄር ዘንድ ወደ ሰው
እየተላኩ የሰውን ወደ እግዚአብሄር የእግዚአብሄርን ወደ ሰው ያቀ
ርባሉ ተብሎ ይነገራል ። በሌላም ጊዜ የመላእክት አለቃቸው ቅዱስ
ሚካኤል እስራኤልን በሙሴ አማካይነት ከግብፅ አውጥቶ ቀኝ
ጎጸናን መርቶ ኤርትራን አሻግሮ ወደ ከነአን እንዲገቡ ሲያደ

ርግ ፤ በእስራኤል ላይ የግፍ አገዛዝን ያጠኑ ግብፃውያንን በሙሴ በትር ምት አማካይነት በኤርትራ ባህር አስጥሟቸዋል ይባላል (ዳን.10 ፥ 13—21 ። ስንክ.ሀዳር 12) ።

173 ዋዜማ

ዘአበበ መሸሻ (መረጌታ ፥ ዘደብረ ወርቅ)

ኢይሰዐር ሕገ ሙሴ
ማዕቀበ አልፋ ኢያሱ ጥቅመ ኢያሪኮ ሰበረ ፥
ወለሕዝብ መዋግደ ባሕር አውረሰሙ ምድረ ፥
ወእንዘ ይጼሊ ባሕር ጸሎተ ዘከርያስ ምዕረ
በዘብድወ ጠሊ ቄሪር ሐቄሁ አሰረ ፥
ወጎደገ ምስለ ሰብእ ነገረ ።

ት ር ጉ ም

የሙሴን ህግ እንዳይሽር
ማእቀበ አልፋ ኢያሱ የኢያሪኮን ህንፃ ሰበረ (አፈረሰ) ፥
ለህዝቦች የባህር አዚረቶችም ምድርን አወረሳቸው ፥
ባህር የዘካርያስ ፀሎትንም አንድ ጊዜ ሲፀልይ
በቀዝቃዛ የፍየል ሌጦ (ቆዳ) ወገቡን አሰረ ፥
ከሰው ጋርም ነገርን ተወ ።

ም ስ ጢ ር

በሙሴ ህግ እስራኤልን የሚመራቸው ኢያሱ የኢያሪኮን ቅጥር ሰብሮ እንደገባባትና የርስት ምድርን ለእስራኤል እንደ አከፋፈላቸው ሁሉ ፥ የኢያሱ ምሳሌ የሆኑት አባ ኤዎስጣቴዎስ እንደ ሙሴ የኢያሪኮን ባህር በደህና ተሻገሩ ፥ የባህሩንም ሞገዶች (አዚረቶች) እንደ ምድር ፀጥ አደረጓቸው ።

ደግሞ ባህታዊ ሲፀልይ ወገቡን በሰቅ (ቀበቶ) እንደሚታጠቅ እንደግይነጋገር የባህታዊው ምሳሌ የሆነው የኢያሪኮ ባህር በአባ ኤዎስጣቴዎስ አፅፍ ተአምር ተሰራበት ፤ እንደዘካርያስም ዝም አለ በማለት ደራሲው የአባ ኤዎስጣቴዎስን ተአምር አድራጊ ነት በቅኔያቸው ምስጢር አብራርተዋል ።

174 ዋዜማ

ዘገዝሙ (ደብተራ)

የዋሃን ደቂቀ ኖኅ
ለዐዲው ማይ ደክሙ በእስተዳልዎ ሐመረ ፤
እሰመ ኖኅ ጽንዐ መሐላሁ ምስለ ማይ ገብረ ።
በሳዒ ሰብእሰ ጥበበ እመ እምነዳይ ተምህረ
ጸሳሎተ ሐመር ዘኖኅ ላዕለ ማይ ገብረ
ከመ ይዕዱ ዘእሳት ባሕረ ።

ት ር ጉ ም

የዋሆች የኖህ ልጆች
ውሃን ለመሻገር መርከብ በማዘጋጀት ደከሙ ፤
ኖህ የመሀላውን ጥናት ከውሃ ጋር አድርጓልና ።
በላኤ ሰብእ ግን ጥበብን ከድሃ ቢማር
የእሳትን ባህር ይሻገር ዘንድ የኖህን
መርከብ ጥላ በውሃ ላይ እደረገ ።

ም ስ ጢ ር

ኖህ ከነቤተ ሰቦቹ ከጥፋት ውሃ ለመዳን በቅድሚያ መርከብን በመስራት ተዘጋጀ ። በላኤ ሰብእ ግን መርከብን ሳይሰራ በውሃ ላይ በሆነው በመርከቢቱ ማርያም ጥላ ብቻ የእሳት ባህርን ተሻገረ ማለት በቅድስት ማርየም ስም ለአንድ በሽተኛ ባጠጣው ውሃ ምክንያት ወደኩነኔ ቦታ ከመውረድ ዳነ ማለት ነው ።

175 ዋዜማ

ዘተክለ ጽዮን (አለቃ)

ኢየሱስ ገሊላዊ
ኀበ ገሊላዊ ዮሐንስ ወኀበ ዮርዳኖስ ሐረ
ውእቱ እንዘ በተጠምቆ ኢየኀሥሥ ክብረ ፤
ጊዮርጊስሰ ኢይኀሥሥ ዮሐንስሃ ወባሕረ
ዮሀንስሃ ረሰየ ርእሶ ምቁረ ፡
ወከሣዶ ዮርዳኖስ ገብረ ።

ት ር ጉ ም

የገሊላ ሰው ኢየሱስ
እርሱ በመጠመቅ ክብርን ሳይሻ ወደ ዮርዳኖስና
ወደገሊላ ሰው ዮሀንስ ሄደ ፤
ጊዮርጊስ ግን ባህርና ዮሀንስን
እንዳይሻ የተቆረጠ ራሱን የሀንስን እደረገ ፡
አንገቱንም ዮርዳኖስን አደረገ ።

ም ስ ጢ ር

ኢየሱስ በመጠመቅ ላይክብር ነገር ፡ ወደአጥማቂ ዮሀንስና ወደመጠመቂያው ዮርዳኖስ የሄደ ሲሆን የልዳ ሰማእት ጊዮርጊስ ግን ራሱን ቻለ ፤ ይህንም ጊዮርጊስ አንገቱን በወንጀለኞች ሰይፍ ሲቆረጥ የፈሰሰው ውሃ ያስረዳል በማለት ደራሲው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

176 ዋዜማ

ኢዮብ ሕሙመ ሥጋ
እመ ኅቡአ ከሠተ ወዘተከሥተ ሰወረ
ጸቃውዐ ደዌ በልሳን አምረረ ፤

ሊቀ ምርፋቅሰ ካልአ ገብረ መርዓዊ ዘከብረ
ደዌ ኢዮብ ወይነ ጥዒሞ አንከረ
ወአካለ በረከተ ገብረ ።

ት ር ጉ ም

የስጋ ህመምተኛ/ ኢዮብ
ድብቁን ቢገልጥ የተገለጠውንም ቢሰውር
የማር ወለላ/ ደዌን በአንደበት አመረረ ፤
ሌላው የመቀመጫ አለቃ የከበረ ገብረ መርአዊ ግን
የኢዮብ በሽታ/ ወይንን ቀምሶ አደነቀ ፡
አካል/ በረከትንም (ብርካቱ) አደረገ ።

ም ስ ጢ ር

አንዳንድ ህመምተኛ ሰው «ምንህን ነው የሚያምህ ? » ሲሉት ግልጡን ሰውሮ ስውሩንም ገልጦ ይናገራል ፤ መብሉንና መጠጡ ም ቀምሶ «መረረኝ» ይላል ። እንዲሁም ኢዮብ የውስጥ አካሉ በላይ ፡ የላይ አካሉ በውስጥ እስኪሆን ድረስ በመታመሙ የተወ ለደባትን ቀን እስከመርገም ደረሰ ። ግን ኢየሱስ ያደረገውን የተ አምር ወይንን ቀምሶ የመቀመጫው አለቃ እንዳደነቀ ገብረ ክር ስቶስ የተባለው መናኝ ፃድቅ በሽታውን በፈቃዱ ተቀበለ ፡ አካ ሉንም በሽታው ቆራረጠው ይላሉ ባለቅኔው ።

177 ሥላሴ

ዘከብቱ (ዐቃቤ ሰዓት)

ሀገረ ጽዕቅተ ፍና
እንበለ አሐቲ ምክያደ እግር
ዘኢታገምር አእጋረ ክልኤተ ሶበ እምርኁቅ ነጸረ ፡
ነገረነ ዕዝራ እሙነ ነገረ ።
ወእምነ ዛቲ ሀገር በአፍአ ከመ ኢይኩን ኅዱረ

ተክለ ሃይማኖት በዘአእመረ ፡
እምአእጋሪሁ አሐተ መተረ ፡
በካልእታ ለበዊእ ሀገረ ።

ትርጉም

መንገዲ የምታስጨንቅ
ከአንዲት እግር መርገጫ ሌላ
ሁለት እግሮችን የማትችል አገርን ከሩቅ ባየ ጊዜ
የታመነ ነገርን እዝራ ነገረን ።
ከዚችም አገር በውጭ (በዳሪ) እንዳያድር
ተክለ ሃይማኖት ባወቀ ነንዘብ ፡
ከእግሮቹ አንዲቱን ቆረጠ
በሁለተኛይቱ አገርን ለመግባት ።

ምስጢር

እዝራ « ካንዲት እግር ርግጫ በቀር ሁለት እግሮችን የማትችል መንገዲ ጠባብ አገርን አየሁ» ማለቱን ዓድቅ ተክለ ሃይማኖት ስላወቁ ፡ ከዚች አገር ውጭ እንዳያድሩ አንዲቱን እግር ጥለው በሁለተኛይቱ እግር ብቻ ወደዚች አገር ለመግባት አሰቡ በማለት የፃድቁ አንዲቱ እግራቸው በቁመት ብዛት መሰበሯንና በሁለተኛይቱ እግር ብቻ ቆመው መፀለያቸውን ባለቅኔው ገልጠዋል ።

178 ሥላሴ

ርእስ ደብረ ብርሃን
እግረ ኮነ ውስተ ቤትኪ
ወእንዘ ኢይሰርቅ ምንተ ጥሪተ ሐሰት ነውረ
እደ ጽዋዔሁ ድኅሪተ ተአስረ ፡
ወለተ ነጋሢ ዮሐንስ ነጋሢ ዘአውረሰኪ መንበረ
ዝሰ ግፍዕ እመ ተገብረ

አዕይንት ዶስምዓ ዙሉ ነገረ ፡
ወአእዛን ይርአያ አድባረ ።

ትርጉም

ንጉስ ዘፋንን ያወረሰሽ
የንጉስ የሀንስ ልጅ !
ደብረ ብርሃን/ ራስ በቤትሽ ውስጥ እግር ሆነ ፡
የውሸት/ ጥሪት ነወጥንም
ምንም ሳይሰርቅ ጥሪወ/እጅ ወደሁዋላ ተሰረ ፡
ይህ ግፍ ግን በተደረገ ጊዜ
ነገርን ሁሉ አይኖች ይስሙ ፡
ጆሮዎችም ተራሮችን ሁሉ ይዩ ።

ምስጢር

ሰው ተዘቅዝቆ ሲሰቀል ራሱ በእግሩ ቦታ እንደሚውል ፡ የነገደሩ የአፄ የሀንስ ሴት ልጅ ከፍተኛወን የነገደሩን ደብረ ብርሃንን አዋረዱት ። ምክንያቱም ወንጀለኛ እጁን የፊጥኝ እንደሚታሰር ፡ ነውር የሌለበትን የዚህን ደብር ጥሪ በቤታቸው ግብዣ ክነገዩር አድባራት በሁዋላ አደረጉት ። ይህም በየል ብጆሮዎች እንደማየትና በአይኖች እንደመስማት ይቆጠራል በማለት ባለቅኔው ቅሬታቸውን ገልጠዋል ።

179 ሥላሴ

አስተብፅዑ ነፍስተ ዓሣ
ኢየሱስ ወጴጥሮስ ወሩፋኤል ፡
ባሕረ ጥብርያዶስ አኮኑ እመ ኢየሱስ ወፈረ
በጎዳጥ ዓሣ አጽንበ ማኅበረ ።

ወእምከርሠ ዓግ አውዕአ ጸባሕተ ቈጣር ዲናረ
መሠግር ጴጥሮስ አመ አሥግረ
ሩፋኤልኒ ሥራየ በዘአአመረ
በሐሞቱ አሕየወ ዕውረ ።

ት ር ጉ ም

ኢየሱስና ጴጥሮስ
ሩፋኤልም የአሳ ብልትን እደነቁ ፤
በጥብርያዶስ ባህር ኢየሱስ በተሰግራ ጊዜ
በትንሽ አሳ ማህበሩን አጥግቧልና ፥
አሳ አስጋሪ/ጴጥሮስም በአሰገረ ጊዜ ከአሳው ሆድ
የቄሳር ግብር ዲናርን (ብርን) አውጥቷልና ፥
ሩፋኤልም ስራይን (መድሃኒትን) በአወቀ ገንዘብ (በማወቁ)
በአሳው አሞት እውርን አድኗልና ።

ም ስ ጢ ር

ሶስት ተቀራማቾች (ስጋ የሚካፈሉ ሰዎች) ያረዱት ሙክት የሰባ ሲሆንና ስጋው ሲበረክት ያመሰግናሉ ፤ እንዲሁም ሶስቱ ኢየሱስና ጴጥሮስ ሩፋኤልም ተአምር የሰሩበት አንድ አሳ ሲሆን አሳው ለኢየሱሳ በረከተለት ፥ ለጴጥሮስም የንጉስ ግብር አስገኘለት ፤ ለመል አክ ሩፋኤልም ለእውር አይን መድሃኒት ሆነለት በማለት ባለቅኔው ለምግብ እንዲሆን ከተሰገረ አሳ የተለያየ ጥቅም መግኘቱን በቅኔያቸው ምስጢር ያስገነዝባሉ ።

180 መወድስ

ኵሉ ፍጥረት ወዕፀወ ሐቅል
በሥርዐተ አምላክ ይቀውም ወኢያንቀለቅል ድኅረ
እንበለ አዳም ወሔዋን እስ አምጽኡ ኀሳረ

መንገለ ኀሠሡ ለርእሶሙ ክብረ ፤
እስመ ዕፀ ከርሜል ኢተዘከረ
ከመ ዕፀ ቈድሮስ ይኩን ደሊወ ርእሱ ኀበ አእመረ
አዳምሰ ወሔዋን እንዘ ይመክሩ ምክረ
ለከዊነ አምላክ ተባደሩ በበሊዐ በለስ ዘተመትረ ፤
በበለስኒ ኢንፍታሕ አመ በልዕዎ ኀቡረ
ብልውኒ እንዘ ይብል አምጣነ በለስ ኢተናገረ

ት ር ጉ ም

ለራሳቸው ክብርን ከፈለጉ ዘንድ
መ ከራን ካመጡ ከአዳምና ከሄዋን በቀር
ፍጥረት ሁሉ የዱር እንጨቶችም ጭምር
በአምላክ ስርአት ይቆማል
ወደ ሁዋላም አይናወጥም ፥
ራሱን መ መዘንን ካወቀ ዘንድ
የቸፍርግ እንጨት የዋንዛ እንጨትን ሊሆን አላሰበምና ።
አዳምና ሄዋን ግን ምክርን ሲ ሰ ክሩ
የተቆረጠ በለስን በመ ብላት አምላክን ለመ ሆን ተቀዳደሙ ፤
በበለስም እንፍረድ ፥ በእንድነት በበሉት ጊዜ
ብሉኝ ሲል በለስ አልተናገረምና ።

ም ስ ጢ ር

ፍጥረቱ ሁሉ እንጨትም ሳይቀር በተፈጥሮ ህግ ፀንቶ ሲኖር እንደ ገና ባለአእምሮ ሆነው የተፈጠሩት አዳምና ሄዋን በበለስ እንጨት ላይ የተሰራላቸውን ህግ አልጠበቁም ። እነርሱ ሰው እንደመሆናቸው መጠን ካላወቁ የበለስ እንጨት ምን ያድርጋቸው እርሱ ብሉኝ አላላቸው ! እነርሱ በጎዛ እጃቸው የአምላክነት ምክንያት ይሆነናል ብለው በሉት እንጂ ይላሉ ባለቅኔው ።

181 መወድስ

ዘምትኩ ዕውር (ዘደብረ ወርቅ)

ቦ ጻድቃን ውሉደ ቤትከ
እለ መነኑ ዓለመ ወእለ ዔሉ አድባረ
እንዘ የኀሥሡ ዮም ሰማያዊተ ሀገረ
እስከነ ቀነዩ ሥጋሆሙ ገብረ
ወልቡናሆሙ ማእምረ
ለተቀንዎ እምላከ ዘኢያኀጸርከ አእጋረ !
ንሕነሰ እለ ጻሕፍነ ሀኬተ ልቡና ጠማረ
አምረርነ ቃላቲከ ሐሊበ ወመዓረ
እንዘ ተድላ ዓለም ነኀሥሥ ፤ ወእንዘ ንትሜነይ ክብረ
ሞት ይወስደነ ወያወርደነ መቃብረ ።

ት ር ጉ ም

ለመቸንከር እግሮችህን ያላሳጠርህ
አምላክ ! ስጋቸው/አገልጋይንና አዋቂ ልባቸውን
እስከገዙ ድረስ ፥ ሰማያዊት አገርን
እየፈለጉ አለምን የናቁና
ተራሮችን የዞሩ
የድቃን/የቤትህ ልጆች አሉ ፤
ደብዳቤ/የልብን ስንፍና የፃፍን እኛ ግን
ወተትና ማር/ቃሉችህን እመረርን
የአለምን ደስታ ስንሻ ፤ ክብርንም ስንመኝ
ሞት ይወስደናል ፤ መደመቃብርም ያወርደናል ።

ም ስ ጢ ር

የቤተ ሰሪ ልጆች አሮጌውን ቤት ለግደስ እንጨትና አረግ ፍለጋ ዱር ለዱር ተራራ ለተራራ ይሄዳሉ ። እንዲሁም የእግዚአብሄርን መንግስት የሚሹ የድቃን ይሆን አለም ትተው ሜካ ጥሰው

ዳሞ ለብሰው ይኖራሉ ። ጌቶች አገልጋይን እንደሚገዙ እጥቂውን ም እንደሚያስሩት ፥ መናኞችም ሲጋቸውን አሸንፈው የልባቸውን አሳብ ወስነው አምላካቸውን ያገለግሉታል ።

ሰውነቱን ለግዝናናት የፈለገ ሰው እግሮቹን እንደሚዘረጋ ፥ ኢየሱስ ክርስቶስም በመስቀል ላይ ሲሰቀል ሁለቱ እግሮቹ ትክክል ሆነው በእንድ የብረት ችንካር ተቸነከሩ ። አንዳንድ ወረቀት ፀሀፊዎች ጉበ ሲሹ « ግሩን አምርረው ወተቱን እጥቁረው » ይናገራሉ። በወዲያ የእግዚአብሄርን በወዲህ የአለምን እንከተላለን የሚሉ ክህናትም « የሞቴን መስቀል ያልተሸከመ ሊያገለግለኝ አይችልም» የተባለውን የክርስቶስን ትእዛዝ ስላልፈፀሙ ሰነፉ ። ከዚህም ሌላ ባሰበው ቀርቶ ባላሰበው የሚውል አለሙን የሚሻ ሰው ከአለሙም ከነፍሱም ሳይሆን ፤ ሞት ይነጥቀውና አፈር ይሆናል ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

182 መወድስ

ዘዘገየ (ሊቀ ጥሩን)

እግዝእተ ዮሐንስ ሰይፍ መጋቢተ ዙሉ
ለሥጋ ግዙፍ እመ ገብረቶ ጽቡረ
ተዐርቆተ ሥጋ ወዕፅም ኢተዘከረ
ቶማስ ወዓሊ ዘተቀንየ ገብረ ፤
በመዐዛ ደም አምጣነ ሰከረ
ጽዋዐ ዚአሁ ለሞት እስከነ ይጥዕም ድኅረ ።
ቶማስሂ እንተ ከማሁ ጎልቀተ ዓለም ነጸረ
ለዘሞተ ሰብእናሁ ኢነሠሠ መቃብረ ፤
እስከነ ተፈነወ ንስር እንተ የዐውድ አድባረ
ያስተጋብእ ዝርዋነ አእዳወ ወእጋረ ።

ትርጉም

ሁሉን የምትመግብ የዮሀንስ እመቤት/ሰይፍ
ደንዳና (ጮማ) ስጋን ሞቃ ብታደርገው
አገልጋይ ሆኖ የተገዛ ቶማስ/ሉሌ

የስጋና የአጥንት መራቆትን አላሰበም ፥
የርሱ የሞትን ፅዋ
ሁዋላ እስኪቀምስ ድረስ በደም ሽታ ሰክሯልና ።
እንደርሱ የአለምን ግለቅ የተመለከተ ቶማስም
ብትኖች እጆችንና እግሮችን ይሰበስብ ዘንድ
ተራሮችን የሚዞር ንስር እስከተላከ ድረስ
ለሞተ ሰው/ሰውነቱ መቃብርን አልፈለገም ።

ም ስ ጢ ር

ያካባቢዋን ሰው ሁሉ ጠርታ ግብግ የምትጋብዝ ሴት ወይ ዘር ጮማውን ስጋ እንደጭቃ ታደርገዋለች ፥ ትረፈርፈዋለች ። እንዲሁም የወይዘሮይቱ ምሳሌ የሆነች መጥምቁ ዮሀንስን የቆረጠችው የወንጀለኛ ሰይፍ የዮሀንስን ስጋ ደም ብቻ አደረገችው ። ደግሞ ዳረጎቱ እስኪሰጠው ድረስ በጠላ ሽታ የሰከረ አገልጋይ የአካሉን መራቆት እንደማያስብ እንዲሁም የሀንደኬው ሀዋርያ ቶማስ የስጋውን ቁርበት መራቆት በሰይፍ ተገፎ ስጋው ተንበልጥጦና አጥንቱ ገጠ ምልምል ግንዱን ታየ ከዚህም በሁዋላ ሞተ ።

ከዚህም ሌላ በጦር ሜዳ የሚዋጋ አርበኛ ሰው የሞተበትን ጓዱን ለመቅበር አመቺ ጊዜና ቦታ እንደማያገኝ ፥ እንዲሁም የመርአስ አገር ሰማእት ቶማስ በሰይፍ ተቆራርጦ ስላለቀ በመቃብር የሚቀበር ሙሉ አካል አልቀረውም ። በተጨማሪም አሞራ በመሬት የወደቀ ስጋ ለማንሳት እንደሚዞር ፥ ክንፍ አውጥቶ የበረረ የመጥምቁ የዮሀንስ ራስ በመጨረሻ እንደ እጆቹና እግሮቹ በመሬት ተቀበረ ይላሉ ባለቅኔው ።

183 መወድስ

ወይን ተነብዮ ምሥጢረ መንቅሔ ሕሊና
ቀዳሕተ ምሳሌ አብዝጉ ወተመሰሉ ስኩረ ፤
መስብክተ አሐዱ በእብን አምጣነ አሐዱ ሰበረ

ወአንበረ በዋሕድና
ጌዴዎን ሊቀ ምርፋቆሙ አሳተ ወፀምረ ፥
ወስኩረ ምሥጢር ዘካርያስ
መልዕልተ ነዳዲ እሳት አምጣነ ግየ ደመረ ፥
ዘኮነሂ ኢሳይያስ ለግብረ እሱ መምህረ
ጣዕዋ ምስለ አንበሳ በሐብለ ምሳሌ አስተፃመረ ፤
ባሕቱ ዕሜይ ወአሮን አመ ተማልሑ በትረ
ወጺዎ ኖኅተ ቤቱ ሕዝቅኤል ተሰወረ ።

ት ር ጉ ም

አሳብን አነቃቂ የሆነ የትንቢትን ወይን/ምስጢር
የምሳሌ ቀጅዎች አበዙ የሰከረንም መሰሉ ፤
አንዱ ያንዱን ጋን በድንጋይ ሰብሯልና
የድግስ ቤት አለቃቸው/ጌዴዎንም
እሳትና ግምጃን በአንድነት አኑሯልና ፥
የምስጢር ሰካራም /ዘካርያስም
በሚነድ እሳት ላይ ውሃን ጨምሯልና ፥
ለነርሱ ስራ መምህር የሆነ ኢሳይያስም
ጥጃን ከአንበሳ ጋር በምሳሌ/ገመድ አጣምሯልና ፤
ነገር ግን እሴይና አሮን በትርን በተግዘዙ ጊዜ
የቤቱን ደጃፍ (በራፍ) ዘግቶ ሀዝቅኤል ተሸሸገ ።

ም ስ ጢ ር

የወይን መጠጥ ልብን ያነቃቃል ፥ እርሱንም ያበዙ ጠጭዎች ይሰክራሉ ። እንዲሁም የጠጭዎቹ ምሳሌዎች ነቢያት በመንፈስ ትንቢት (በትንቢት መንፈስ) ተናገሩ ። ከሰከሩትም አንዱ ገንቦይ ቱን በድንጋይ ሲሰብር ሌላው ልብሱን በእሳት ላይ እንደሚጥለው የባለድንጋዩ ምሳሌ ዳንኤል ክርስቶስን በድንጋይ አምሳል አይቶ ተነባ። የባለገንቦው ምሳሌም የሆነው ነቢይ ኤልሳእ ሲሆን በኤልሳእ ገንቦ የተመሰለችው ቅድስት ማርያም ሆነች ። ሌላው ሰካራም ደግሞ

ጥጃይቱን ከውሻው ጋር እንደሚያስራትና በውሻው ስም ሊጠራት እን
ደሚሞክር ፣ ከነቢያትም ማርያምን አንዱ በጥጃ ሊመስላት ሌላው
ደግሞ ወልድን በአንበሳ መሰለው ። እንዲሁም ከሰካራሞቹ
ሁለቱ በትርን ሲግዘዙ ከነርሱ የተሻለው ደጃፉን ዘግቶ እንደሚደ
በቅ ፣ በአሮን በትርና በእሴይ ቁጥቋጦ ስር የተመሰለች ማርያምን
ህዝቅኤል በቤት ደጃፍ መስሎ ትንቢት ተናገረ ማለት በቅኔው
ተመስጥሯል ።

184 መወድስ

ዘመንግሥቱ (መሪጌታ)

ሑሉ ይትራዳእ በበከሂሎቱ
ሐራሲ ማርቆስ እንዘ ይፀምድ አሥዋረ
አኮኑ ታዴዎስ ለእምጽአ ዘርዕ ሐረ
ወማርቆስ በጊዜ ፍሬሁ ስብከተ ሰፈረ ፣
ወዲዲሞስ ተአዛዚ
መሥነቅቶ አምጽአ ፣ ወአፈ መሥነቅት አቄረ ።
ቶማስሂ ደኃራዊ ዘኪያሆሙ ነጸረ
አምጽአ አእዱገ ወአስፈፈዳተ እንኩርኩረ ፤
ማእረረ ሥቃይ እስከነ የኅልቅ ምዕረ
አምጣነ አልቦ ዘይነውም እንበለ ዘቦአ መቃብረ ።

ትርጉም

ሁሉ በየችሎታው ይራዳል ፤
አራሽ ማርቆስ በሬዎችን ሲጠምድ
ታዴዎስ ዘር ለማምጣት ሂዷልና
ማርቆስም በፍሬው ጊዜ ስብከትን ሰፍሯልና ፣
ታዛዥ ቶማስም (ሀዋርያው)
አቅማዳውን አምጥቶ የአቅማዳውን አፍ ቋጥሯልና ።
እነሱን ያየ ሁሉ ኖሮለት ቶማስም (ሰማእቱ)

እሀዮቹን አመጣና ቅርጫቶቹን አገለባበጠ ፤
እዝመራ/ስቃይ በፍፁም እስኪያልቅ ድረስ
መቃብር ከገባ በቀር የሚተኛ የለምና ።

ምስጢር

በግብርና ስራ ጊዜ መተጋገዝ (መረዳዳት) አለ ። አንዱ በሬዎ
ችን ሲጠምድ ሌላው ዘርን ያመጣል ፣ እንዲሁም የበሬ ጠማጅ
ምሳሌ ማርቆስ በበሬዎች ተጎተተ ። የዘር አምጪው ምሳሌ ታዴዎስ
ስንዴን ዘርቶ በአንድ ቀን እደረሰው ። ደግሞ እህሉ ሲበራይ
(ሲወቃ) አንዱ ምርቱን ሲሰፍር ሌላው አቅማዳን እንደሚሰበ
ስብ የእህል ሰፋሪው ምሳሌ ማርቆስ የምርት ምሳሌ ስብከተ ወን
ጌልን አካሂደ ። የአቅማዳ ሰብሳቢው ምሳሌ የቶማስ ሀዋርያ ቁር
በትም አቅማዳ ተወጣ ።

ከዚህም ሌላ አሽከሩ አህያ ካመጣ በሁዋላ ምርቱ በቅርጫት
እየተሰበሰበ በአቅማዳ ተከቶ እንደሚጫን ፣ የአህያ ሰብሳቢው
ምሳሌ የመርአስ ሰማእት ቶማስ ወንጌልን ሲሰብክ በቅርጫት
ውስጥ ሆኖ በአህያ ተጭኖ ተጓዘ ። እስከ ህይወቱ ፍፃሜም ወንጌ
ልን መስበኩን አልተወም ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

185 መወድስ

ተውላጠ ምክረ ሰብእ ብዙኀ ለዘየሐትቶ
እመኒ ለጽድቅ ወለእበሳ ዘገብረ ፤
እስመ ሞተ ጻድቅ ያዕቆብ በምኅፃበ እግር ተገብረ ።
ወቅድመ አባግዕ ምኅፃበ እድ
ላቲይውተ ርእሱ ያዕቆብ አንበረ ፣
እስመ ውሳጤ እብን ተሣረረ
ሕይውተ አዳም ኤርምያስ በመልዕልተ እብን ዘተቀብረ ።
እመኒ በኤርምያስ ንስሓ ዮናስ አእመረ
እብን ዘቀተለ ወርቀ ወብሩረ
እንዘ እምላዕለ ደብር ይወርድ ፡ ወእንዘ የወርግ ደብረ
አበሰ በሐልዮ አእዳወ ወአእጋረ ።

ት ር ጉ ም

የሰው ምክር ለውጥ ለሚመረምረው ብዙ ነው
ለፅድቅም ለበደልም ላደረገው ፤
የፃድቅ ያእቆብ ሞት በእግር ማጠቢያ ተደርጓልና ።
በበጎቹ ፊትም የእጅ መታጠቢያን
ለራሱ ህይወት ያእቆብ አስቀመጠ ፤
በድንጋይ ላይ የተቀበረ
የኤርምያስ አዳም ህይወት በድንጋዩ ውስጥ ተመስርቷልና።
በኤርምያስም የዮናስን ንስሃ ቢያውቅ
ብርና ወርቅን የገደለ ድንጋይ
ከተራራ ላይ ሲወርድ ወዳተራራም ሲወጣ
እጆችንና እግሮችን በማሰብ በደለ ።

ም ስ ጢ ር

በዚህ አለም ውስጥ የሚሰራው ስራ (ፅድቅም ሃጢአትም ሲሆን) ልዩ ልዩ ነው ። አንዱ ነገር ለአንዱ ምክንያተ ሞት (የሞት ምክንያት) ይሆንበታል ። ከዚህም የተነሳ ህዋርያው ያእቆብ በእንጨት ገበታ ተገደለ ። የይስሀቅ ልጅ ያእቆብ ግን በበጎች ውሃ መጠጫ ገንዳ ምክንያት በላባ ቤት መወደድንና መመረቅን አገኘ ፤ እንዲሁም ወደ አዳም ለሞት የተወረወረው ድንጋይ የህይወት ድንኳን ሆነለት ። በተጨማሪም ነፍስ የገደለ ሰው እንደሚፀፀት ከተራራ ላይ ወርዶ የብርንና የወርቅን ምስል ቀጥቅጦ ሲያጠፋ ነቢይ ዳንኤል ያየው ድንጋይ ከነቢይ ኤርምያስ ፅሁፍ ጋር በኤፍራጥስ ባህር እንደ ዮናስ በመውደቁ የባቢሎንን ውድቀት አሳየ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል።

ታ ሪ ክ

ህዋርያው ያእቆብ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አብሮ በማደግ « እጉሁ ለእግዚእነ (የጌታችን ወንድም) » የተሰኘ የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ ነው ። ክእለታት በእንደኛው ወንጌልን በጉባኤ ሲሰ

ብክ ፡ አንድ እይሁዳዊ ቀንቶ በእጅ መታጠቢያ ገዘታ ራሱን መት ቶት ገድሎታል ። ከገድሉ ጥናትም የተነሳ እግሩ እንደ ዝሆን እግር ተድበልብሎ ነበር ።

የይስሀቅ ልጅ ያእቆብ ከወንድሙ ከኤሳው ጋር ተጣልቶ ወደ አጎቱ ወደላባ አገር ኮበለለ ። እዚያ ሲደርስ በጎች በሚጠጡበት በድንጋይ በተገጠመ ጉድጓድ ዳር አረፈ ፤ የበጎች እረኞች መጥተው ሲያከቱ የጉድጓዱን አፍ መግጠሚያ ያነሱትና በጎቹን ውሃ ያጠጧ ቸዋል ። ያጎቱ የላባ ልጅ ራሄልም ወዲያውኑ ከበጎቿ ጋር መጣች ፤ ለበጎችዋና ለሌሎቹም በጎች ያእቆብ መግጠሚያውን አንስቶ ከጉድ ጓዱ ውሃ በገበታ አመጣላቸው ። በዚህ ምክንያት ወደላባ ቤት ገብቶ በደህና ለመኖርና ሁለቱን ሴቶች ልጆቹን ለማግባት ቻለ (ዘፍጥ. 29—30) ።

አዳም እፀ በለስን በልቶ ከገነት በወጣ ጊዜ በበደሉ ተፀፅቶ አዘነ ፤ ከሄዋን ጋር በባህር ውስጥ ገብቶ ዘጠና ዘጠኝ ቀን እንዳ ለቀሰ ለመቶ አንድ ቀን ሲቀረው ያው ከገነት ያወጣቸው ሰይጣን በግታለል ከባህር አወጣቸው ። ካወጣቸውም በሁዋላ ድንጋይ እን ሰቶ ጫነባቸው ። ድንጋይቱ ግን በአዳምና በሄዋን ራስ ላይ ተደነ ኮነች (ድንኳን ሆነች) (ገድለ አዳም) ።

ነቢይ ኤርምያስ በተቃዋሚዎቹ ጅራፍ ሊገረፍ ሲል ፡ ድንጋይ እሱን ተመስሎ እርሱን ሸፍኖ ቆመና በርሱ ፈንታ ተገርፎለታል ይባላል ። ነቢይ ኤርምያስ በባቢሎን ላይ ሲተነባ «የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ሰፊው የባቢሎን ቅጥር ፈፅሞ ይፈርሳል በሮቿም በእሳት ይቃጠላሉ ፤ አህዛብም ይወድቃሉ ባቢሎን ባድማ ትሆናለች » በማ ለት ፤ በባቢሎን ላይ የሚመጣውን ክፉውን ነገር ሁሉ በመፅ ሀፍ የፈው ብሎ ስርያን ሲያዝዘው « ይህን መፅሃፍ ለህዝቡ አን ብበህ ከፈፀምህ በሁዋላ ድንጋይን እሰርበትና በኤፍራጥስ ወንዝ ጣለው » ብሎት ስርያም የታዘዘውን አደርጓል (ኤር.51፡59 — 64)።

ዘወርቅ አገኘሁ ተክሌ (አለቃ)

እመ ተአንገደ ዮሴፍ ዘምስለ ሰሎሚ
ጎበ እለ ግዕድ አልቦሙ ወኢይሁቡ ድራረ
ሕሊና ሰሎሚ ተደመ ፡ ወልበ ዮሴፍ አንከረ ፤
ረኃብ ቃል ነደ እሳት
እስመ ውስተ ከርሣ ለድንግል ጎደረ ፡
ወለዝሉፉ አስተፃመረ
ብእሴ ዘይምን ውብእሲተ ፅግም አእጋረ ።
ድምፀ ማይሂ ንጉሠ ግብጽ አመ ጎይለ ልሳን አሰረ
ተግብረ በገሊላ ውስተ ብሔረ ግብጽ ዘኢቲገብረ ፤
ማየ ገሊላ ጽሙዕ ለእመ በወይን ሰከረ
ኢይርአይ ሙስናሁ አምጣነ ማየ ግብጽ ተሰወረ ።

ትርጉም

ማእድ በሌላቸውና ራት በማይሰጡ
ሰዎች ዘንድ ዮሴፍ ከሰሎሚ ጋር እንግዳ በሆነ ጊዜ
የሰሎሚ ልብ ተደነቀ ፡ የዮሴፍ ልብም አደነቀ ፤
የእሳት ነዲድ የሆነ ራብ ቃል
በድንግል ሆድ ውስጥ አድሯልና ፡
ለሁልጊዜም አጣምሯልና
የቀኝ ወንድና የግራ ሴት እግሮችን ።
የውሃ ጥም/ የግብፅ ንጉስም የምላስን ሃይል ባሰረ ጊዜ
በግብፅ አገር ያልተደረገ በገሊላ ተደረገ ፤
የገሊላ ውሃ / የተጠማ ሰው በጠጅ ቢሰክር
ጥፋቱን (ውርደቱን) እንዳያይ የግብፅ ውሃ ተሸሽጓልና ።

ምስጢር

የሚበሉትና ለእንግዳ የሚያበሉት በሌላቸው ሰዎች ቤት ያደሩ እንግዶች ይደነቃሉ ። እንዲሁም ዮሴፍና ሰሎሚ ከቅድስት ማርያምና ከልጅዋ ጋር ወደግብፅ አገር ያለስንቅ ተሰደዱ ። ደግሞ ቃል የሚባል ወልድ በድንግሊቱ ሆድ እንደተፀነሰ እንዲሁም ራብ በድንግል ማርያም ሆድ ጠና ። ከዚህም ጋር ክርስቶስ በጋብቻ ህግ ባልንና ሚስትን እንደአጣመራቸው በራብ ጊዜ የቀኝ እግርና የግራ እግር ተሻረቡ (ተፋተሱ) ። ከዚህም ሌላ የግብፅ ንጉስ ፈርኦን ዮሴፍን ባሰረው ጊዜ ግሩም የሆነ (የሚያስደንቅ) ህልም እንዳየ የስደት ውሃ ጥም የስደተኞቹን ምላስ እደረቀው ፤ በግብፅ ያልሆነ የህፃናትም እልቂት በገሊላ ተደረገ ። በተጨማሪም ተጠምቶ የዋለ ሰውን እንደጠማው የጠጣው ወይን እንደሚያሰክረው በቃና ዘገሊላ በተደረገው ሰርግ ውሃው ወይን ሆነ ። ያም ሰው የስካሩን ውርደት እንዳያይ ፊቱን እንደሚያዞር ፤ በእነ ዮሴፍ ስደት ጊዜ በግብፅ በረሃ የሚጠጣ ውሃ ታጣ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

ታሪክ

የአምላክ እናት ድንግል ማርያም በቤተ ልሄም አምላክን በድንግልና ወልዳ ሳለች ሰይጣን ልጅዋን ለማስገደል ተነኮለባት ፤ ወደገሊላ ንጉስ ሄሮድስ ሄዶ ነገር ሰራባት ። «ለአንተም ለእኔም የማይበጅ ንጉስ በሀገርህ በቤተልሄም ተወልዷል ፡ ይህን ጊዜ እርሱን ካልገደልኸው መንግስትህን ይቀማሃል » አለው ። ስለዚህም «ህፃኑን ሊገድሉት ይሹታልና ህፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ ብሎ መልአክ ለዮሴፍ ነገረው። ዮሴፍም ህፃኑን ከነእናቱ ፡ ሰሎሚንም ይዞ በሌሊት ወጣና ወደግብፅ ተሰደደ ። በዚያ ጊዜ ድንግል ማርያም ጫካ ለጫካ በመሄድ እያለቀሰች በራብና በጥም በእሾህና በእንቅፋት ተሰቃየች ። እነርሱም ሄሮድስ እስኪሞት ድረስ ሶስት አመት ከስድስት ወር በግብፅ ኖሩ (ማቴ.2፡1—23)።

187 መወድስ

ዘአፈ ወርቅ ዘውዴ (አለቃ)

ግሥጻን አጎው ኢታስተሐፅቡ
ተግሣጸ ቃልየ ዘንተ ፣ ወኢታምስልዎ ዕጦሥታረ ፤
እመ ለጊዜሁ መሪር እስመ ያስተፈሥሕ ድኅረ ፣
ምሳሌ ዝኒ ከመ ታምእሩ
ነጽሩ በዐይነ ልቡና ሶረርተ መሪረ ፤
እስመ እንዘ ለአፍ ምንዳቤሁ
መድኀኒተ ከርሥ ውእቱ ፣ ወያስተፈሥሕ ጽዑረ ።
በጽድቅሰ ገሥጾ አርከ ኢይከውነኒ ነውረ ፣
እግዚአብሔር እስመ ገሠጾ ለኢዮብ ዘአፍቀረ ፣
ወያጠይቅሙ ኢዮብ ዘልሳንየ ነገረ
ምረረ ሕማሙ አስተማሰለ ሐሊበ ወመሣረ ።

ትርጉም

የተገሰፃችሁ ወንድሞች ! ይህን
የቃሌን ተግሳፅ አትሰቀቁ ፣ እሬትንም አታስመስሉት ፤
ለጊዜው መራራ ቢሆን በሁዋላ ያስደስታልና ።
የዚህንም ምሳሌ ታውቁ ዘንድ
በልብ አይን መራራ ኮሶን ተመልከቱ ፤
ለአፍ ጉፍናኔው (ጎምዛዛ) ሲሆን
የሆድ ፈውስ ነውና ፣ ተጨናቂንም ያስደስታልና ።
በእውነትስ ወዳጅን መገሰፅ ነውርን አይሆንብኝም ፤
እግዚአብሄር የወደደውን ኢዮብን ገስያታልና ፣
ኢዮብም ያንደበቴን ነገር ያስረዳችሁ ዘንድ
የደዌውን ጉፍናኔ ወተትንና ማርን አስመስሎታልና ።

ምስጢር

የሬት ዝልግልግ (ወለላ) ቢጠጡት ምላስንና ከንፈርን ከመ ጎምዘዝ በቀር ጥቅም አይሰጥም ። በሌላ በኩል ሬት የመዳኒትነት ጠባይ አለው ቢባልም እንደ ኮሶ የተፈተነ አይደለም ። መምህር ተማሪዎቹን እንደ አባትነቱ ቢገስፃቸው ግን የኮሶ መጠጥ የአፍ ጉፍናኔ ሲሆን ፣ የሆድ ተባይ በሽታን ገድሎ እንደሚያወጣው ሁሉ የመምህር ተግሳፅም የተማሮችን ውስልትና በለጋው ነቅሎ ይጥ ለዋል ። የኮሶ መጠጥ ለጊዜው ቢጎፈንንም በሁዋላ እንደሚያስደስት የመምህር አባታዊ ተግሳፅም ለጊዜው ቢያሰቅቅም ተማሪዎችን እንደ ታረመ እህልና እንደ ተኮተኮተ ተክል ፍሬያማዎች ያደርጋቸዋል ።

የመምህርም ወዳጅን በእውነት መገሰፅ አያስነውርም ። ምክን ያቱም እግዚአብሄር የሚወደው ኢዮብን በደዌና በሀብት ጥፋት ሲገስፀው ቢታገስ ወዳጅነቱ ነጥሯልና ። ወተትና ማርም ጣፋጮች እንደሆኑ ኢዮብ አምላኩ የገሰፀውን (የዳረገውን) የደዌውን ስቃይ እንደመልካም ስጦታ ቆጠረው ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

ታሪክ

ብዙዎች ተማሪዎች በአንድ መምህር ትምህርት ቤት ተሰብስ በው ሲማሩ ሁሉም ሙሉ በሙሉ አመለ ወርቅ ሊሆኑ አይች ሉም ። አንዳንዶቹ « ሲመትሩላት ትንሢና ቢወቅሩ አይፈጭ » ሲሆኑ አንዳንዶቹ « ለብልህ አይነግሩ ለአንበሳ አያመትሩና በአይን አውቃ » ይሆናሉ ። ከዚህም የተነሳ ባለቅኔው በተማሪዎቻቸው መካከል ያሉትን ወስላቶች ተማሪዎች ለማስጠንቀቅ ያህል « ሾላ በደፈናው » የሆነ ተግሳፃዊ ምክርን በማህበር ሲሰጡ « ያደረገች ውን ታስታውቅ ከደረቷ ትታጠቅ» እንዲሉ ከወስላቶቹ ተማሪዎች የቅርታ እንጉርጉሮ ይሰማ ጀመር ። ከዚህም አያይዞ እንደ ትምህ ርቱ ስርአትና ህግ « ባለተራ ግስ ተቀበል» በማለት መምህሩ ቢያዙ እምምታው በረከተ ። ስለዚህ መምህሩ ይህን ስለተግሳፅ ጠቃሚ ነት የሚያስረዳ ቅኔ ለተማሪዎቻቸው ዘርፈዋል ።

188 ሕንጺሃ

ሕንጺሃ ለባሕረ ኤርትራ ተመዝበረ
እስመ በውስቴታ ጣኔያስ ተገብረ ።

ት ር ጉ ም

የኤርትራ ሀንፃዋ ፈረሰ ፤
በውስጢ ፈርኦን ተደርጓልና ።

ም ስ ጢ ር

አንድ አጓጉል የሆነ (ያልተጠረበ) ድንጋይ ያለበት ህንፃ በአጓጉሉ ድንጋይ አቀማመጥ ምክንያት እንደሚፈርስ፥ የኤርትራ ባህር ተከፍሎላቸው እስራኤል በደህና ሲሻገሩ ግብፃውያን እነፈርኦን ሰጠሙበት ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

189 ዕጣነ ሞገር

ዘተክሉ (መምህር፥ ዘዋሽራ)

እግዚአ ውላጤ ክረምት
አመተ ሁከት ዘኮነት ደመና ለምንት እንተ አንበረ ?
አመ ተአዘዘት ትቅዳሕ ማየ አስተፍሥሖ ፍጡረ
እንበለ ነጐርጓር ይእቲ እስመ ኢተሐውር ባሕረ ፤
ወይእቲ በአጽልሞ ገጽ ዘትትመየጥ ድኅረ ።

አሠረ ንጉሥ

ቅኑየ ሐጋይ ይብሰት በጥንቃቄ ምክረ ቃለ ነቢይ እንተ አእመረ
ለእግዚአ ተግሣጽ ክረምት መዓቱ እስከነ ኅልፈተ ገብረ ፤
ውእቱ እስመ ውስተ ቤት ተሰወረ ።

ት ር ጉ ም

የመለወጥ ጌታ / ክረምት
የእውከት አገልጋይ የሆነች ደመናን ለምን ነው ያስቀመጠ ?
ፍጡርን የሚያስደስት ውሃ እንድትቀዳ በታዘዘች ጊዜ
እርሷ ያለማንጎራጎር ወደወንዝ አትሄድምና ።
እርሷም ፊት በማጥቆር ወደሁዋላ የምትመለስ ናትና ።

አሰረ ንጉስ

የበጋ ተገዥ /ድርቅ በጥንቃቄ የነቢይን ቃል ምክር ያወቀ ነው ፤
የተግሳፅ ጌታ/ ክረምት ቁጣው እስካለፈ ድረስ
እሱ ከቤት ውስጥ ተደብቋልና ።

ም ስ ጢ ር

ውሃ ቅጂ ስትባል ያለማጎመትመት (ያለማንጎራጎር) የማትሄድና ፊቷን የምታጠቁር አገልጋይን ያየ ሰው ጌታዋን « ይህችን እውከተኛ ለምን ነው ያናርህት ? » ይለዋል ። እንዲሁም የአገልጋይቱ ምሳሌ የክረምት ደመና ወደውቅያኖስ ባህር ሄዳ ውሃን ጠልቃ በነፋስ ወደ ልጋዝነት (ተሸካሚነት) ወደላይ ስትወጣ ጉር ምርምታ ይሆናል ፤ የሰማይም ገፅ ይጠቁራል ።

አንድ አስቸጋሪ ነገር የተፈጠረበት ሰው የሚፈራው ነገር እስኪያልፍ ድረስ በቤት ውስጥ ተደብቆ የለም እንደሚያስኝ የበጋም ድርቅ የክረምት ዝናብ እስኪያልቅ ድረስ በቤት ውስጥ እንጂ በውጭ አይገኝም ይላሉ ባለቅኔው ።

190 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ይቤልዎ ሕዝብ ስቡረ ዕፅም ለሰማዕተ ልዳ በግብሩ ፤
እስመ የአንም ሐዊረ መልበሰ በእእዳዊሁ ወእግሩ ።

ት ር ጉ ም

ህዝቦች በስራው የልዳን ሰማእት አጥንተ ሰባራ አሉት ፤
ልብሱ / መሄድን በእጆቹና በእግሩ ይሰራልና ።

ም ስ ጢ ር

ሸማኔ በድሮ ዘመን አላዋቂዎች ዘንድ አጥንተ ሰባራ እንደ ሚባል ፣ የልዳ ሰማእት ጊዮርጊስን ወንጀለኞች በእጆቹና በእግ ሮቹ እንደከብት የእንብርክክ አስሄዱት ፤ አጥንቶቹንም አደቀቁ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

191 ዘአምላኪየ

አናሚ አምላክ ዘኢይትዐወቅ ሀገሩ
አነመ ልብሰ ተቀንዎ በእዱ ወእግሩ ፤
አዳም ወሔዋን ደቂቁ እስመ በተዐርቆ ነበሩ ።

ት ር ጉ ም

አገሩ የማይታወቅ ሸማኔ / አምላክ
በእጁና በእግሩ ልብስ / መቸንከርን ሰራ ፤
አዳምና ሄዋን / ልጆቹ በመራቆት ተቀምጠዋልና (ይኖራሉና) ።

ም ስ ጢ ር

የትውልድ ቦታው ያልታወቀ ሸማኔ ሸማን በእጆቹና በእግ ሮቹ ለተራቆቱት ልጆቹ እንደሚሰራ ፣ ባህርዩ የማይመረመር አም ላክ ለአዳምና ለሄዋን ብሉ እጆቹንና እግሮቹን በችንካር ተቸነከረ ። ልጆች ከልብስ እንደተራቆቱ አዳምና ሄዋን ከእግዚአብሄር ልጅ ነት ወጡ (ተለዩ) ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

192 ዋዜማ

ዘተክለ ጽዮን (አለቃ)

ዐደወ በላኤ ሰብእ
በንስቲት ማይ ጎበ ሰማያዊት ሀገሩ
ምስአ ፈለገ እሳት ፤ እስመ ማይ ሐመሩ ።
አመኒ አዝማድ ሞተ በላዔ ሰብእ አእመሩ
እስመ በላዔ ሰብእ ለሰብእ መቃብሩ
ጎበ አይቴ መቃብረ ገብሩ ?

ት ር ጉ ም

በላኤ ሰብእ በጥቂት
ውሃ ወደሰማይ አገሩ የመላ
የእሳት ባህርን ተሻግረ ፤ ውሃ መርከቡ ነውና ።
ዘመዶችም የበላኤ ሰብእ ሞትን ባወቁ ጊዜ
በላኤ ሰብእ የሰው መቃብሩ ነውና
መቃብሩን የት አደረጉ ?

ም ስ ጢ ር

ሰው ሁሉ ለልማዱ ባህርን የሚሻገረው በመርከብ ሲሆን በላኤ ሰብእ (ሰው በላተኛ) ውሃን ለድሃው ማጠጣቱ እንደመር ከብ ሆኖለት የእሳት ባህርን በውሃ ተሻግሮ ገነት ገባ ። ደግሞ እያንዳንዱ ሰው ሲሞት በመሬት ይቀበራል ፤ በላኤ ሰብእ ግን ራሱ መቃብር ስለሆነ በሞተ ጊዜ ዘመዶቹ መቃብር ሊፈልጉ ለት አይችሉም ። በላኤ ሰብእ ባእዶችን ሰዎች ብቻ ሳይሆን ሚስ ቱንና ልጆቹንም ስለበላ «መቃብር በመቃብር እንዴት ይቀበራል» በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

193 ዋዜማ

ዘወብተ ሚካኤል (አለቃ)

ቀርነ መድኃኒትነ ዮርዳኖስ
አንሥአ ለነ እምሀገረ ዳዊት ገብሩ
አብ ተክለ ሃይማኖት ዘኢዮር ማኅደሩ ፡
እስመ ከመ አዘዘ ውእቱ ዘእንበለ ነቢብ ተፈጥሩ
ዕውራን ኪሩቤል ዘኢይትናገሩ
ብርሃናተ ዐበይተ ይጹሩ ።

ት ር ጉ ም

ኢዮር (ሰማይ) ማደሪያው የሆነ
አባት /ተክለ ሃይማኖት የመዳኛችን መምሪያ ዮርዳኖስን
ከአገልጋይ ዳዊት አገር አነሳልን (አመጣልን)፡
የማይናገሩ ኪሩቤል እውሮች ታሳላቆች
ብርሃኖችን ይሸከሙ ዘንድ
እርሱ እንዳዘዘ ያለመናገር ተፈጥረዋልና ።

ም ስ ጢ ር

« እግዚአብሄር የመዳኛችንን መምሪያ ከዳዊት ወገን አነሳልን » ብሎ ነቢዩ ዘካርያስ እንደተናገረ ፡ ከመላእክት ጋር አመሰገኑ የሚባሉ ፃድቅ ተክለ ሃይማኖት ውሃውን ፈዋሽ አደረጉት ፡ ደግሞ ኪሩቤል የአምላክን ዙፋን ሊሸከሙ እንደተፈጠሩ ሁሉ እውሮች ሰዎች በፀበሉ ተጠምቀው ዐይኖቻቸው በሩላቸው ይላሉ ባለቅኔው።

194 ሥላሴ

ለኀሊፍተ ፍና
ቀርነ ግብጽ ፈርዖን ወሠራዊቱ
ብዙኀ ስንቀ አበሳ እለ በርእሶሙ ጸሩ
ሚካኤል እንዘ ቅድሜሆሙ ኀበ መስየ ምድሩ ፡
ኤርትራ ዘመድ አሐቲ እንተ ኪያሃ አፍቀሩ
ከመ ፍና ምሴት ኢይሑሩ
በእንቀጸ ቤታ ማዕበል እምድኅረ ነበሩ ፡
ትቤሎሙ ኀድሩ ኀድሩ

ት ር ጉ ም

መንገድ / የግብፅ ነጋሪትን
የሄዱ ብዙ ስንቅ / አበሳን
በራሳቸው የተሸከሙ ፈርኦንና ሰራዊቱ
ሚካኤል በፊታቸው ሲሆን ምድሩ ከመሸ ዘንድ ፡
እርስዋን / የወደዷት እንዲት ዘመድ /ኤርትራ
የምሽት መንገድን እንዳይሄዱ
በቤትዋ/ ማእበል ደጇ ከተቀመጡ በዋሁላ
እደሩ እደሩ አለቻቸው ።

ም ስ ጢ ር

ስንቃቸውን ተሸክመው የሚጓዙ መንገደኞች ከነርሱ አንዱ እፊት እፊታቸው በመሄድ ሲመራቸው ፡ ቀኑ በመሸባቸው ጊዜ ጎራ ብለው የጠየቋት ዘመዳቸው ሴት « በምሽት አትሄዱ ፡ እደሩ» ትላቸዋለች ። እንዲሁም የመንገድኞቹ ምሳሌ ፈርኦንና ሰራዊቱ መንገድን እንደመሄድ ነጋሪትን አስነሰሙ አዋጅ አስነገሩ ። ስንቅን እንደመሸከም አበሳን (በደልን) አበዙ ። ከመንገደኞች አንዱ መንገድ እንደሚመራቸው ፡ ቅዱስ ሚካኤልም በእስራኤል ፊት

ብርሃን ሲያሳይ በግብፃውያን ፊት ደመና ጋረደባቸው ። የዘመድ ሴት ምሳሌ የሆነች የኤርትራ ባህርም የመንገደኞች ምሳሌ የሆኑ ፈርኦንና ሰራዊቱን የደጅ ምሳሌ በሆነው ማእበል አሰጠመቻቸው ይላሉ ባለቅኔው ።

195 መወድስ

ዘንብረ ሥላሴ (ንቡረ እድ)

በአናቅጺሃ ለደብር ወለተ ጽዮን
ስብሐተ ምኒልክ ንጉሥ ይስብኩ ወይንግሩ
ደቂቀ ደብረ ጎይል አእላፍ ዘበተዋሕዶ ነበሩ
ዘልፈ ይተግሁ ።
ወእንበለ ነፍስ አምላከ አእመሩ
አእባነ መርዓ ዘተዐሠሩ ፤
እስመ እንበለ አፍ ወይን በስብሐተ ራጉኤል ሰክሩ ።
ይትጎደግሂ ውስተ ፍኖት ለእግረ ትንቢት አሠሩ
እድግት ወዕዋላ ውስተ እግዚአሙ ይነብሩ ፤
ባሕቱ እሉ ሠናየ እንዘ ይገብሩ
ጎያላን በእከዮሙ ለምንት ይዜነሩ ?

ት ር ጉ ም

በፅዮን ልጅ/ ደብር በሮች
የንጉስ ምኒልክ ምስጋናን ይነግሩና ይሰብኩ ዘንድ
በአንድነት የሚኖሩ ብዙዎች የደብረ ሀይል ልጆች
ዘወትር ይተጋሉ ።
የተጠሩ (የተጋበዙ) የሰርግ ድንጋዮችም
ያለነፍስ አምላክን አወቁ ፤
ያለወይን/አፍ በራጉኤል ምስጋና ሰከረዋልና ።
የትንቢት/ እግር ኮቴም በመንገድ ውስጥ ይቀረፅ ዘንድ

አሀያና ውርንጭዋ በጌታቸው (ቁጥር ስር) ይናራሉ ፤
ነገር ግን እሊህ መልካምን ሲያደርጉ (መልካም ስራ ሲሰሩ)
ብርቱዎች በክፋታቸው ለምን ይኮራሉ ?

ም ስ ጢ ር

አንድነታቸውን ለማጠንከር የሚጣጣሩ ተባባሪ ሰዎች የመጣውን በህብረት ምስጋና ተቀብለውና የሚሄደውንም ሸኝተው ይኖራሉ ። እንዲሁም ከእንጦጦ ማርያም ተነራብቶ የተቋቋመው የራጉኤል ደብር ካህናት በፍቅር አንድነት ይኖራሉ ፤ ለእዬ ምኒልክም ግንባር ቀደም ናቸው ።

ደግሞ ወይን የጠጡ የሰርግ በአል እድምተኞች ቢሰክሩም አእምሯቸውን ፍፁም እንደማይስቱ ሀይወት የሌላቸው ድንጋዮች እንደ መልእክ ራጉኤል ኢየሱስን አውቀው አመሰገኑት ። ከዚህም ሌላ መንገደኛ ሲሄድ የእግሩ ርግጫ በጫማው ልክ በመንገድ ላይ እንደሚቀረፅ ፣ በተነገረው ትንቢት መሰረት አሀያና ውርንጫዋ ኢየሱስን በመንገድ ተሸከሙት ። ይህ ሲፈፀም ያዩ አይሁድ ግን አይተው እንዳላዩ ሆኑ ይላሉ ባለቅኔው ።

196 መወድስ

ዘተስሙ (መምህር ፡ ዘጥበራ)

እንግዳ ዓለም እምአምሮ ርእሱ
ወእመ ከመ ነግድ መጽአ ኢየአምሮ ለግብሩ ፤
ለጠይቆ ዝኒ ነገር መንገለ ዳዊት ይሑሩ
ጠቢባን እለ በአእምሮ ወጥበብ ተነክሩ ፤
አምጣነ ጎደረ ውስተ አፍአ
ጠቢበ ውሳጤ ዳዊት እምውሳጣዊት ምሥጢሩ ።
እይሁድሂ በምሳሌ ሶበ ግብሮሙ ተምህሩ

እኩያን ዐቀብተ ወይን ጽድቀ ተናገሩ ፤
መጠነ በሕያው ክርስቶስ ሰማዕተ ሐሰት አቅጸሩ
ለሐምየ ርእሶሙ በጽሚት እስመ እምርእሶሙ ተሰወሩ ።

ት ር ጉ ም

አለም ራሱን ከማወቅ እንግዳ ነው ፥
እንደ እንግዳ ቢመጣም ስራውን አያውቀውም ፤
ይህንም ነገር ለመረዳት በአእምሮና በጥበብ
የተለዩ ጥበበኞች ወደ ዳዊት ይሂዱ ፤
የውስጥ ጥበበኛ ዳዊት
ከውስጠኛይቱ ምስጢሩ በውጭ አድራልና ።
አይሁድም በምሳሌ ስራቸውን በተግሩ ጊዜ
ክፉዎች የወይን ጠባቆች እውነትን ተናገሩ ፤
በሀያው ክርስቶስ የአሰት ምስክሮችን በዋጁ መጠን
በቀስታ ራሳቸውን ለማግት ከራሳቸው ተደብቀዋልና ።

ም ስ ጢ ር

ዘመድ አዝማድ በሌለበት የባእድ አገር እየተዘዋወረ የሚነግድ የጥንት ነጋዴ ከቤት ውጭ እንደሚያድር ፥ ንጉስ ዳዊት በአርዮ ሚስት የፈፀመው ሃጢአት በምሳሌ ቢነገረው አላዋቂ ሆነ ። እንዲ ሁም አይሁድ የገዛ ስራቸው በወይን ጠባቆች ምሳሌ ቢነገራቸው ስራቸውን ባለማወቃቸው ራሳቸውን ቢያሳሙም ፤ በክርስቶስ ላይ የአሰት ምስክሮችን በዋጁበት (በገዙበት) ልክ ራሳቸውን ባለማወቅ በራሳቸው ላይ በፈረዱት ፍርድ እውነተኞች ሆኑ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

ታ ሪ ክ

ዳዊት በአርዮ ሚስት የፈፀመው ሃጢአት እንዳይገለጥበት አፍሮ አርዮን አስገድሎታል ። በዚህ የተነሳ ነቢዩ ናታን በአርዮ ላይ የፈ ፀመውን የራሱን ግፍ (ሃጢአት) በምሳሌ ቢነግረው ፈፃሚው ሌላ

ሰው መስሎት ሞት ፈርዷል (2 ሳሙ. 12 ፥ 1—13) ። አይሁድም የራ ሳቸውን ክፉ ስራ ክርስቶስ በወይን ጠባቂዎች ምሳሌ ሲነግራቸው ወይን ጠባቂዎች ሌሎች መስለዋቸው በራሳቸው ላይ ቅጣትን ፈር ደዋል (ማቴ. 21 ፥ 33—41) ።

197 ሥላሴ

ዘዶቀ እስጢፋ

አጋግ ይቤ
«ከመዝኑ ሞት መሪር»
በጊዜ ረገዞ ሳሙኤል መምህር ።
ወሰራቂ ንግሥት አነ ደቀ እስጢፋ ጎሱር ፤
አንበሳ እስክንድር !
እዓለ አንበሳ እንዘ ትዋሕር
እምእርአይከ ተጎጠኒ ምድር ።

ት ር ጉ ም

አጋግ አለ
« ሞት እንደዚህ መራራ ነውን ? »
መምህር ሳሙኤል በወጋው ጊዜ ።
ንግስትን የሰረቀሁ ወራዳ እኔ ደቀ እስጢፋም
አንበሳ እስክንድር !
የአንበሳ ደቦል የሆንህ አንተ ስታገሳ
ከማይህ ምድር ትዋጠኝ ።

ም ስ ጢ ር

ኮሶ ጠጥቶ የማያውቅ ሰው ኮሶ ቀምሶ ምረቱ ሲያንገሸግሸው «ለካ ኮሶ እንደዚህ መራራ ኖሯልን ? » ብሎ እንደሚገረም ሁሉ አጋግም ሳሙኤል በጦር ወግቶ ሲገድለው የሞትን መራራነት ተረ ድቷል ። ደቀ እስጢፋም እዬ እስክንድርን እንስሳን እንደሚሰብር

አንበሳ በመቁጠርና ራሱንም እንደ እንስሳ በመገመት ሞቱን እንደ አጋጣ አሟሟት ቆጥሮታል ። ከዚህም የተነሳ የአዬ እስክንድርን አይን ከግየት ምድር ተከፍታ ብትውጠው ወዲል ።

198 መወድስ

ዘአካለ ወልድ (ምሥር)

ሐጸ ቶማስ መንፈቀ ፍጸሜ ፣
ወኢተፈጸመ ምንተ ትርብዕተ አእዳው ወእጋር ፤
እስከ ውኂዘ ደም ኮነ ሣልስተ እደሃ ለባሕር ፣
እስመ ቆመ ሰይፍ ሊቀ ካህናት
ይርአይ ማኅለቅቶ ለቶማስ ነገር ።
ወአዝማደ ቶማስ ኢሐለዩ
ዐስበ ከራይያን ዕደው ወሜጠ ስፋሕ መቃብር ።
ወአብዝኀ ሕብረ መልክእ ተክለ ሃይማኖት ማእረር ፤
አምጣነ ኪሩብ ገጸ ሰብእ ወዮሐንስ ገጸ ንስር ፤
እመኒ ሀሎ በምእት አካለ ቶማስ ምቱር
ወያዕቆብ ዘሠላሳ ግማደ አካል ፍሬ ምድር ።

ት ር ጉ ም

ቶማስ/የጭራሽ እኩሌታ ጎደለ ፣
የእጆችና የእግሮች አራትነትም ምንም አልተፈፀመም ፤
የደመ ፈሳሽ የባህር ሲሶ እስኪሆን ድረስ
የቶማስን ነገር ፍፃሜ
ይመለከት ዘንድ የካህናት አለቃ/ሰይፍ ቆሟልና ፤
የቶማስ ዘመዶችም የቆፋሪዎች
ወንዶችን ዋጋና የሰፊ መቃብርን ዋጋ አላሰቡምና ።
አዝመራ/ተክለ ሃይማኖትም የመልክ አይነትን

በሰው ፊት ኪሩብና በአሞራ ፊት ዮሀንስ ልክ አበዛ ፤
ምንም የታጨደ የቶማስ አካል/ባለመቶ መስፈሪያ ቢኖር ፤
ባለሰላሳ የአካል ቁራጭ የምድር ፍሬ/ያእቆብም ቢኖር ።

ም ስ ጢ ር

አንድ ነገር ፈሳሽ ወይም ጠጣር መላልሶ ቢሰፍሩት ስፍሩ ይቀንሳል ፤ እንዲሁም የመርአስ ሰማእት ቶማስ በጠላቶች ሰይፍ ሲቆራረጥ ጊዜ የእጁና የእግሩ አራትነት ቀረ ። ደግሞ ከሶስት አንድ የሆነው ክፍያ ሲሶ እንደሚባል የቶማስ ደም የባህር ውሃ ሶስትያ ሆነ ። የተከሳሽ ወይም የከሳሽ ዘመድ የነገሩን ፍፃሜ እየተጠባበቀ በአደባባይ እንደሚቆም ፣ የከሀዲዎች ሰይፍም ቶማስን ጨርሶ እስኪ ቆርጠው አልተገታም ። ስለዚህም ቶማስ በመቆራረጥ ካለቀ የሙት ወገኖች ለመቃብር ቆፋሪዎችና ለመቃብር የሚሰጡት (የሚከፍሉት) ገንዘብ የቶማስን ዘመዶች አያሳስባቸውም ።

ከዚህም ሌላ እገሌ በነእገሌ ምርት ልክ አመረተ እንደሚባል አቡነ ተክለ ሃይማኖትም በመልክ በኪሩብና በመጥምቅ ዮሀንስ አይነት ክንፍ አወጡ ። ከዚህም በላይ መቶ ዳውላና ሰላሳ ሜን አምራቾች እንዳሉም የቶማስ መቆረጥ በአካላቱ ልክ ሆነ ፤ ያእቆብም እግሩን ተቆረጠ በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

199 መወድስ

ዘክፍለ ዮሐንስ

ሶሎ ይትነጣእ እመ ጎሠሥዎ ፣
ወእመ ኢፈቀድከ አይ ዘይትወሀበነ ግብር
እምነ ፍተ ቃኅም ንኡስ እስከ ነጥበ ግይ ቁሪር ።
ዝሰ ይጽንሐነ
ሀልው አግዓዚ በሰማይ ወምድር
እንበለ ምክርከ ሠርዌ ምክር

እድምዖ መቃብር ኢንክል ወረኪበ ሞት ወሰነ ጸዕር ፤
እስመ ጎጥአ ዘይቀትሎ አመ ተባጽሕዎ ፀር
ሳኦል ዘተውህቦ ሀብተ አክሊለ ወርቅ ወመንበር ።
ወአመ ተመከረ ኢዮብ በዕጸበ ደዌ መሪር
ተመነየ መቃብረ ወኢረከቦ ለመቃብር ።

ት ር ጉ ም

ከፈለጉት ሁሉ ይታጣል ፡
አንተስ ካልፈቀድህ የሚሰጠን ስራ ምንድን ነው ?
ከጉንዳን ትንሽ ቁራሽ እስከ ቀዝቃዛ የውሃ ጠብታ ድረስ ።
ይህስ ይቆየንና
በምድርና በሰማይ የምትኖር ጌታ ሆይ !
የምክር ምሰሶ (መወሰኛ) ከሆነ ምክርህ በቀር
መቃብርን ማግኘትን አንችልም ፡ የጭንቅ ወሰን የሆነ
ሞትን ማግኘትም አንችልም ፤
ዙፋንና የወርቅ አክሊል ሀብት የተሰጠው ሳኦል
ጠላቶች በተገናኙት ጊዜ የሚገድለው እጥቷልና ።
ኢዮብም በመራራ ህማም ጭንቅ በተፈተነ ጊዜ
መቃብርን ተመኘና መቃብርን አላገኘውምና ።

ም ስ ጢ ር

የዚህ ቅኔ ምስጢር ማንኛውም ነገር መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን ፡ ያለ እግዚአብሄር ፈቃድ እንደማይሆን ያመለክታል ። ይኸውም ሳኦልን ጠላቶቹ በድንገት በደረሱበት ጊዜ ጋሻ ጃግሬውን እባክህ ግደለኝ አለው ። ጋሻ ጃግሬውም ሳኦልን ሊገድለው አልፈለገም ፤ ስለዚህ ሳኦል በሎሌው እጅ መሞትን አላገኘም ። እንዲሁም ኢዮብ በቁስለ ስጋ አንገብግቦት (በቁስል በሽታ በመቃጠል) ከመ ሰቃየት ይልቅ ሞትን ቢመኝ አልሆነለትም በማለት ሰው የፈለገውን በጊዜው ሊያገኝ እንደማይችል ባለቅኔው አረጋግጠዋል ።

200 መወድስ

ዘከብቱ (ወቃቤ ሰዓት)

እፎ ንሬኢ ገጸ ሠሣዕና
እለ በከንቱ ፈጸምነ ነሶሳወ ክልኤ አእጋር ?
እስመ ጸድቀተነ ንኅብ በጣዕመ ዚአሃ መዓር ።
ወኢነባብያን ምሳሌያት
ለገሥጾትነ ተንሥኡ እምድር ፤
አምጣነ ለከንቱ ኢትትባደር
ሐዋርያዊት ዕፅ ማኅደረ ብእሲ በሊሐ ምክር ።
ወይግበር ከመ ገብርዎ ሞሠርተ ሐሢን ግቡር
በሑረት ወበግብአት እንበለ ረባሕ ኢየሐውር ፤
ወየዋህ ለርእሱ ጠቢብ በወርኅ ማእረር
አቅድሞተ ዘርዕ እንዘ አልቦቱ ምስለ እለ ዘርዑ የአርር ።

ት ር ጉ ም

የሁለት እግሮች ምልልስን በከንቱ የፈፀምን እኛ
የሆሳእናን ፊት እንዴት እናያለን ?
ንብ በማሯ ጥፍጥና በልጣናለችና ።
የማይናገሩ ምሳሌዎችም
እኛን ለመገሰፅ ከምድር ተነሱ ፤
የምክረ ፈጣን ሰው
ማደሪያ የሆነች የሸማኔ መወርወሪያ ለከንቱ
አትቀዳደምምና ።
የተሰራ የብረት መጋዝም እንዳደረጉት ያደርግ ዘንድ
በመሄድና በመመለስ ያለጥቅም አይሄድምና ፤
ለራሱ ጥበበኛ ገር ሰውም በአዝመራ ወራት
ዘር ማስቀደም ሳይኖርበት ከዘሩት ጋር ይለቅማልና ።

ጌታቸው ለሰራ ያዘዛቸው አሽከሮች የታዘዙትን ስራ ሳይሰሩ ጌታቸው ሲመጣባቸው ፊቱን እንዴት እንደሚያዩት ይጨንቃቸዋል ። እንዲሁም የአምላክን ትእዛዝ ያልፈፀሙ ክርስቲያኖች ክርስቶስ ዳግመኛ በሚመጣበት ጊዜ ከእኔ ፊት ወግዱ ይባላሉ ።

ደግሞ ጌታቸው ያዘዛቸውን የሰሩ አሽከሮች ያልሰሩትን ሰነፎች እንደሚያስወቅሏቸው ከኤዛን ፍጥረቶች ንብ በምትሰራው ማር ከሰው ተሻለች ። እንዲሁም የሸማኔ መወርወሪያ በምታመላል ሰውና ከድሩ ጋር በምታዋህደው ማግ ከሰነፍ ሰው ትበልጣለች ። መጋዝም ወደፊትና ወደሁዋላ ሲመግዙበት በሚፈፅመው ምገዛ ከሰነፎች ሰዎች ይሻላል ። ገር ሰውም ምንም ሳይዘራ ከዘሩት ጋር ቢማርም እንኳን ብልጥ ነን ከሚሉት ሰነፎች ይልቅ አዋቂ ነው ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

201 መወድስ

ዘከብቱ (ዐቃቤ ሰዓት)

ምንት ውእቱ ፍድፋዴ ዚአሃ
ለምክሐ ጠቢባን ጥበብ ? እስመ በጥበብ ወምክር
ኢይጸወዱ ጸሊም ወኢይነውኅ ጎጺር ፤
ወለአብድ ዘይጸንሕም ከልኤቱ አፅራር
ሞት ወመቃብር
ይጸንሕም ከማሁ ለጠቢብ ወግእምር ።
ከመሰ ኢንሰጠም በዕመቀ ብሂል ባሕር
ታኅሥር የውሃት ወጥበብ ታከብር
እንዘ ርግብ የዋህ በዓለ አክናፍ ወእግር
የሐውር በእንግድዓ ጠቢብ አርዌ ምድር ።

የጥበበኞች መመኪያ የሆነች
የጥበብ ብልጫ ምንድር ነው ? በጥበብና በምክር
ጥቁር አይነጣምና አጭርም አይረዝምምና ፤
ሰነፍን የሚጠብቁት ሁለት ጠላቶች/
ሞትና መቃብርም
ጥበበኛውንና አዋቂውን እንደርሱ (እንደሰነፉ)
ይጠብቁታልና ።
የዋህነት ታኅሳቁላለች (ታዋርዳለች) ጥበብም
ታከብራለች በማለት/ባህር ጥልቅ እንዳንሰጥም ግን
የዋህ ርግብ ባለእግርና ክንፎች ስትሆን
ብልሃተኛ እባብ በደረት ይሄዳል ።

ም ስ ጢ ር

የዚህ ቅኔ ፍሬ አሳቡ ጥበበኞች በጥበባቸው የሚመኩባት ከሆነችና ጥበባቸውም ከየዋህነት ብልጫ ካላት ፣ ጥቁሩን ነጭ ፣ አጭሩን ረዥም ማድረግ ባልተሳናትም ነበር ። ጥበበኞችም እንደሰነፎች ፍጻሜያቸው ሞትና መቃብር ባልሆነም ነበር ። በመሆኑም የዋህነትም ርግብን ሲጠቅማት ፣ ጥበበኛነት እባብን በደረት ከመሄድ እንዳላዳነው በመግለጥ ባለቅኔው የትምክህተኞችን ጥበብ አኮስሰዋል ።

202 መወድስ

ዘአይቹህ (መጋቢ ፣ ዘደብረ ወርት)

ንጹሓን በቀል ንኩን ፤ እምከመ ተሠርዐ
መሥዋዕተ ሕማም ሰብእ እስመ ለጌሠም ኢየኀድር ፣
ወዘከመ አጋግ ኮነ ተጸውዖ ኵሉ ፍጡር
መብልዕ እንዘ በእፉሁ ውስተ ሞት መሪር ።
ወእንዘ ይረውጹ ክልኤሆሙ

በዓለ ፈረስ ረኃብ ወደዌ ቀሲለ እግር ፣
ለረኃብ ይቀድሞ ጊዜ ምሀርካ ሰብእ በግብር
ደዌ ውስተ ዓለም በክነፈ ነፋስ ዘይሰርር ፤
ወከመ ዕራቃ ኢትኩን ገራህተ ዓለም መንበር
አንግሥ ምሕረተከ አምላከ ሙሴ ወአልዓዛር ።

ት ር ጉ ም

ከበቀል ንፁሃን እንሁን ፤ ከተሰራ
የሀግም መስዋእት/ ሰው ለነገ አያድርምና ፤
መብል በአፋ ውስጥ ሳለ ወደ መራራ ሞት
የፍጡር ሁሉ መጠራትም እንደ አጋግ ሆኗልና ።
ባለፈረስ/ ራብና
በሽታ/ እግረ ቀላል ሁለታቸው ሲሮጡም ፣
ወደአለም በነፋስ/ ክንፍ የሚበር በሽታ
በሰው ምርኮ ጊዜ በግድ ራብን ይቀድመዋል ፤
የአለም እርሻ/ ወንበርም ባዶዋን እንዳትሆን
የሙሴና የአልዓር አምላክ! ይቅርታህን አንግስ ።

ም ስ ጢ ር

የቁርባን መስዋእት ለነገ እንደማያድር እያንዳንዱ ህመምተኛ በአንድ ቀን የሚሞት ሆነ ። አጋግንም ነቢይ ሳሙኤል በጦር ሲወጋው ሞቱ መራራ እንደሆነ የህመምተኛው ውጋት አሰቃቂ ሆነ ። ወደንጉስ በአስቸኳይ የተጠራ ሹምም የነረሰውን ሳይውጠው እንደሚሮጥ መቅሰፍቱ አጣዳፊ ነው ። ባለፈረስና ባለሰረገላም ሲሮጡ ባለፈረሱን ባለሰረገላው (ባለመኪናው) እንደሚቀድመው የነፋስ በሽታ ከራቡ በፊት ሆነ ። አለምም ባዶዋን እንዳትቀርና እርሻ መን በርም (ዙፋን) ጦም እንዳታድር ዘር መንግስት ,እንደሚዘራባት አምላክ ሆይ ! ይቅርታህን አድርግልን በማለት ባለቅኔው የነፋስ በሽታና የክፉ ቀንን አሰቃቂ ገፅታ በቅኔያቸው ተርከዋል ።

203 መወድስ

እግዚአብሔር አንተን በመበደል ጊዜ
የሚያሀለኝ የለም እኔን ከፈጠርኸው ሁሉ ፍጡር ፤
እመስላለሁና መቼም ይሁዳ ወንድሜን በግብር
ምንም ብበልጠው በጥበብ በነውር
ካባቴ ከነዌ ጋር
የተካከልሁ ነኝ እኔም ወርቅና ብርን በማፍቀር ።
እንብላ እንብላ ሲሉ ሰምች ስጋ መልከኛው ቢቀር
ቆርጠው የሄዱ ብዙ ናቸው እኔን ጨልሞኝ ስድበረበር ፤
ከነጋም ወዲያ እንዳልሄድ እሊያ በሄዱበት አገር
ይጠብቀኛል ከሁዋላዬ የሁሉ ጠላት መቃብር ።

ት ር ጉ ም

ይህ ቅኔ በእማርኛ ቋንቋ የተደረሰ ስለሆነ መተርጎም አላስፈለገም ። ስለዚህ የሰምና ወርቁ ምስጢር ብቻ እንደሚከተለው ይነገራል።

ም ስ ጢ ር

አንዳንድ ብልጥ የግለሰብ ተቀጣሪ «ጌታዬ ሆይ ! የእኔን ያህል ያገለገለ አሽከር የለህም ። ግን ያገልግሎቴን ዋጋ አላገኘሁም» በማለት ለቀጣሪው አገልግሎቱን ይዘረዝራል ። እንዲሁም አንድ ተነሳሂ (ተፀየች) ባለቅኔ እግዚአብሄርን በመለማመጥ ፣ የራሳቸውን ሀጢአት ከፍ የሌላውን ሀጢአት ዝቅ በማድረግ ተቀኝተዋል ። ራሳቸውንም ከይሁዳ ጋር አነፃፅረዋል ። ምክንያቱም ይሁዳ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ሲሆን ክርስቶስን ለገንዘብ ብሎ እንዳሰቀለው ሁሉ ፣ የክርስቶስን ህግ በገንዘብ ፍቅር ማፍረስ በባለቅኔው እምነት ክርስቶስን እንደመስቀል ስለሆነ ነው ። ሀብታምንም ሀብታም እንደሚወዳደረው ገንዘብን በመውደድ ባለቅኔው ለድሀ አልአዛር ያልራራ ኒዌን እንደሚወዳደሩ አረጋግጠዋል።

ከዚህም ሌላ ስጋ ለመብላት የጓጉ ሰዎች የስጋ መልከኛው ያቀረበላቸውን ብርንዶ ስጋ እየቆረጡ ይበሉና በየቤታቸው ይሄዳሉ። እንዲሁም የአለም ሰዎች እንብላ እንጠጣ ሲሉ ፣ በግግኘት ላይ ግጣት እንዳለ አስበው አለምን የናቁ መናኞች በቁጥር አይወሰኑም (ብዙ ናቸው)።በጨለማ የሚሄድ ሰው እንደሚድበረበር (እንደሚደናበር) እንዲሁም ተፀፃቹ ባለቅኔ ሀጢአታቸው ቀናውን መንገድ ጋርዶባቸው በአለም ይልከሰከሳሉ ። ቀኑ በመሸቱ ጉዞውን ያቋረጠ የጥንት ነጋዴ ሲነጋ እንኳን እንዳይገዝ ሽፍቶች በሸረሃ ውስጥ ሸም ቀው ይጠብቁታል ። እንዲሁም ተፀፃቹ ባለቅኔ ልጣቸው የተራሰና መቃብራቸው የተማሰ ደካማ በመሆናቸው ይህን አለም ንቀው ወደ ገዳም ለመሄድ አለመቻላቸውን በቅኔያቸው ገልጠዋል።

203 ሀ ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘእንግዳ (መምህር ፣ ዘዲግ)

ጊዮርጊስ ካህን መፍቀሬ ማኅሌት ተመትሮ
ርእሶ አጽነነ ለጸዊረ መጥባሕት ከበሮ ።

ት ር ጉ ም

ማህሌት/ መቆረጥን የወደደ ካህን/ ጊዮርጊስ
ከበሮ/ ሰይፍን ለመሸከም ራሱን አዘነበለ ።

ም ስ ጢ ር

ማህሌትን የሚወድ ካህን ከበሮን በአንገቱ ለማንገት ራሱን ዘንበል እንደሚያደርግ ሁሉ ፣ ጊዮርጊስ በሰይፍ በተቆረጠ ጊዜ ራሱ ወደቀ ይላሉ ባለቅኔው ።

104 ዘአምላኪየ

በቀራንዮ ተገብረ ዘያስተዓጽብ ልሂቀ ፤
እንዘ ደም አልቦ በኮከብ ዘወድቀ
ዘኢወድቀ ወርኅ እምጣነ በደም ተጠምቀ ።

ት ር ጉ ም

ሽግግሌን የሚያስደንቅ በቀራንዮ ተደረገ ፤
በወደቀ/ኮከብ ደም ሳይኖር
ያልወደቀ/ጨረቃ በደም ተጠምቋልና (ጠልቋልና) ።

ም ስ ጢ ር

መድማት የሚገባው የወደቀው ሰው ሳይደማ ያልወደቀው ደምቶ ቢገኝ እንደሚያስደንቅ ፣ ክርስቶስ በቀራንዮ በተሰቀለ ጊዜ በምድር የወደቀው (የረገፈው) ኮከብ እያለ ያልወደቀው ጨረቃ ደም መምሰሉ የሚያስደንቅ መሆኑን ደራሲው በቅኔያቸው ምስጢር አመልክተዋል ።

205 መወድስ

ዘድንቆ ግርቆስ

ሎሱ ይትነደግ እመ ጎደግዎ ።
ለጠይቆ ዝኒ ነገር እምሐልዮ መንበር ምጡቅ
ኢያሱ ጎደገ ተድላ መንበሩ ዘወርቅ ፤
ወከዊኖተ ነግድ በበብሔሩ
ኢያስተዓጸበ ያዕቆብ ልሂቅ
በእንጸረ አብርሃም ወይስሐቅ ።

ትሩፋን እሰብ ንሕነ ኅለፍተ ፍና እንበለ ሥጋቅ
ለጽድቅ ኢንዘከረ ወኢትዘከረነ ጽድቅ ፤
እስመ ጊዜ ብዕልነ ንትዔበይ ወጊዜ ንዲትነ ንሰርቅ ።
ትካዝነሂ ካልእ እምትካዘ ጳውሎስ ሊቅ፤
እስመ ዘኢየኅልቅ መሰለነ ንብረተ ዓለም ዘየኅልቅ ።

ት ር ጉ ም

ከተውት ሁሉ ይተዋል ።
ይህንም ነገር ለመረዳት የመጠቀ ዙፋንን ከመመኘት የተነሳ
ኢያሱ የወርቅ ዙፋኑን ምኾት ተወ ፤
በያኅሩ እንግዳ መሆንንም
በአብርሃምና በይስሀቅ አንፃር
ሽማግሌ ያእቆብ አሳደነቀም ።
ግን የእነዚህ ቅሪቶች ያለስንቅ መንገድን ሂያጆች እኛ
እውነትን አናስባትም፤ እውነትም አታስበንም ፤
በብልፅግናችን ጊዜ እንታበያለንና ፣ በችግራችንም ጊዜ እን
ሰርቃለንና
አሳባችንም ከሊቅ ጳውሎስ አሳብ ሌላ ነው፤
የሚያልቅ የለለም ንብረት የማያልቅ መስሎናልና።

ም ስ ጢ ር

በአለም ከሚያጓጉ ነገሮች ሁሉ ዋናው የመንግስትን ዙፋን ምኾት መተው ሲሆን ፣ ቆራጥነት ካለ ሊፈፀም ይችላል ። ይህም ዙፋ
ናቸውን በተዉ በነአድያም ሰገድ ኢያሱ ታውቋል ። ያእቆብም ያኅሩን ምኾት ከእንግድነቱ አገር መኑላላት ጋር ሲያመዛዝነው እንግድነቱ ብርቅና ድንቅ ሊሆንበት አልቻለም ። ምክንያቱም ከአያቱ አብርሃ
ምና ከአባቱ ከይስሀቅ የወረደ ልምድ ስለሆነ ነው ።

በግግኘቱም በግጣቱም የግናውቅበት «የእሳት ልጅ አመድ» እኛ አለና! ስናገኝ ስንታበይ ፣ ስናጣም ስንሰርቅና መንገዳችንንም ያለስንቅ ስንሄድ ተስፋ ቢሶች ነን ። ለመንገድ የሚበቃውን ስንቅ

ሳያዘጋጅ ወደሩቅ አገር እንደሚሄድ መንገደኛ በዚህ አለም ሀብታ
ችን መንግስተ ሰማይን አንዋጅበትም፤ ለዚህ አለም እንጂ ለወዲያ
ኛው አለም እንደ ቅዱስ ጳውሎስ አንጨነቅም ይላሉ ባለቅኔው ።

206 መወድስ

ዘተዋነይ

ቦኑ ተአምር ከመይትቀነይ
ለበረድ በረድ ወመብረቅ ለመብረቅ ?
ለምንት ውእቱ ተቀንዮትከ በወርቅ
ዕሩቅ ብእሲ ለብእሲ ዕሩቅ
ዓለመ ሕይወቱ ዘየኅልቅ
ወሰማየ ዐፅሙ ይትከደን ደመና መቃብር ዕሙቅ ?
በኢዮር እንዘ ሀሎ እምላከ ኢዮር ምጡቅ
ዘይፈትሕ በጎጥእ ወይፈትሕ ለጻድቅ ፤
አምጣነ ጽጌ ዓለም ሠርፀ መይልዋን አዕጹቅ
ጽባሐ ይሠርፅ ወሠርከ ይወድቅ ።

ት ር ጉ ም

ራቁት ሰው (ባዶ ሰው)
በረዶ ለበረዶ መብረቅም ለመብረቅ
እንደሚገዙ ታውቃለህን ?
በሃጢአተኛው የሚፈርድበት ለፃድቁም የሚፈርድለት
የመጠቀ የኢዮር (ሰማይ) አምላክ በኢዮር ሳለ
የህይወቱ አመት ለሚያልቅ
አጥንቱ /ሰማይም ጥልቅ መቃብር/ ደመናን
ለሚለብስ ለራቁት ሰው
በወርቅ መገዛትህ ለምንድን ነው ?
የግብዞች /ሚፎች ፅንስ የሆነ አበባ/ አለም
ጥዋት ይበቅላልና ፣ ማታም ይረግፋልና ።

ም ስ ጢ ር

በረዶ ሲባል ሁሉም በፀሀይ ሙቀት ስለሚሟሟና መብረቅ ሲባል ሁሉም አየር ወለድ ስለሆነና አንዱ ካንዱ የሚበልጥበት ምክንያት ስለሌለው ሰውም ሲባል ሁሉም አላፊና ጠፊ ስለሆነ ፣ እያንዳንዱ ሰው ሰርቶ ማግኘት እንጂ ከሁሉ በላይ የሆነ አምላክ እያለ አንዱ ላንዱ የገንዘብ ተጎዥ መሆን የለበትም ። ምክንያቱም አለም ጥቂት ታይታ ማታ እንደምትረግፍ አበባ ናትና በማለት የቅኔ አባት ተዋነይ አመስጥሯል ።

207 ዕዝል ዕጣነ ሞገር

ፀሐየ ሰማይ ያውሂ ሀገረ መርቁ ርኁቅ
እንዘ ቅርብቶ ደደከ ኢያመውቅ ፤
ዝኒ ሕንጻ ምሳሌ ፀሐየ አሞንዮስ ሊቅ
ከመ ኢያንቀልቅል በጥዩቅ ፣
ለዐይነ ሄሮድስ ቅሩብ እንዘ ውእቱ ረቂቅ
ለዘርኅቁ ነገሥተ ጽባሕ ተማህደ በጽድቅ ።

ት ር ጉ ም

የሰማይ ፀሀይ ፣ የቀረበችው ደጋን ሳያሞቅ
ሩቅ የቆላ አገርን ያሞቃል ፣
ይህም የምሳሌ ህንፃ ለሊቅ አሞንዮስ ፀሀይ
በተረዳ ነገር እንዳይናወጥ ፣
ለቅርብ ሄሮድስ አይን ረቂቅ ሲሆን
ለራቁ የምስራቅ ነገስታት በእውነት ተገለጠ ።

ም ስ ጢ ር

ፀሀይ አቅራቢያውን ደጋን (ተራራ ኮረብታውን) ሳያሞቅ የራቀውን በረሃ እንደሚያግለው ሁሉ ፣ ፀሀይ የተባለው የአሞንዮስ ጌታ ክርስቶስም በአቅራቢያው ላለው ለሄሮድስ ሳይገኝለት ከሩቅ አገር ለመጡት ለሰብአ ሰገል መታየቱን ባለቅኔው ያስገንዝባሉ ።

ታ ሪ ክ

ኢየሱስ በቤተ ልሄም ከድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ የጥበብ ሰዎች ሶስት ነገስታት ከምስራቅ አገር መጡና በክብት በረት ለተወለደው ህፃን ሰገዱለት ። ወርቅና ከርቤ እጣን ገበሩ ለትና በሌላ መንገድ ወደአገራቸው ተመለሱ ። የገሊላ ንጉስ ሄሮድስ ግን በቤተ ልሄም የተወለደውን ህፃን ክርስቶስን ሊያገኘው አልቻለም (ማቴ. 2) ።

208 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ዘገብረ መድኀን (አለቃ ፣ ዘአሰቦት)

እነግር አነ ሰገብረ ሚካኤል ጽድቆ ፤
እስመ ገብረ መድኀን አነ ወመኑ ይከልአኒ ተጠምቆ ?

ት ር ጉ ም

እኔ የገብረ ሚካኤልን እውነቱን እናገራለሁ ፣
እኔ ገብረ መድህን ነኝና ፣ መጠመቅንስ ማን ይከለክለኛል።

ም ስ ጢ ር

በመጠመቅ (ክርስትና ሲነሱ) ገብረ መድህን መባል ስርአት እንደመሆኑ ፣ ገብረ መድህን የተባሉት መምህር ተጠምቆ ከተባሉ መምህር ጋር በሙያ አንድ መሆናቸውን በቅኔያቸው ምስጢር ያስገነዝባሉ ።

ታ ሪ ክ

አለቃ ገብረ መድህን ፣ አለቃ ገብረ ሚካኤልና መምህር ተጠምቆ የትምህርት ቤትም የሙያም ጓደኞች ናቸው ። ከአለታት በአንዱ ቀን ሶስቱም አብረው ምስጢራዊ ጨዋታን ሲጨዋወቱ አለቃ ገብረ መድህን ስለሁለቱ ጓዶቻቸው ይህን ቅኔ ዘረፉ ይባላል ።

209 ሥላሴ

ዓለመ ሥጋነ
ዐባይ ባሕር ዘርኢከዋ
ድምርት ይእቲ በእሳተ ብዙኀ ተጽዕቆ ፡
ወእለ ውስቴታ ዘነሥኡ መሰንቆ ።
ወለብእሲሃ ጥበብ ዘወይነ መንሱት አውደቆ
አልቦ ረድኤት ዘይሰውቆ ፡
ወእኅቱ ፍጽምት ደማስቆ
ታስቆቅዎ ሐቂፋ ደቂቆ ።

ት ር ጉ ም

ያየሁዋት ትልቅ
ባህር / የሲጋችን አለም
በብዙ መጨነቅ እሳት የተዶለች ናት ፡
በውስጧ ያሉትም መሰንቆ እንደያዙ የተሞሉ ናቸው።
ጥፋት /የወይን ጠጅ የጣለው ጥበብ/ ባሏንም
የሚደግፈው ረዳት የለም ፡
ፍፁም እህቱ ደማስቆም
ልጆቹን አቅፋ ታለቅስለታለች ።

ም ስ ጢ ር

ሀዋርያው ዮሀንስ በራእዩ «ከእሳት ጋር የተቀየጠች ባህርን አየሁ» ባለው አንፃር የእሳት ባህር ምሳሌ የሆነችው ይህች የሲጋ ችን አለም በጭንቀት የሚኖሩባት ናት ። የሚኖሩባትም ሰዎች አነ ሰኝ ላብዛው ጠበበኝ ላስፋው በማለት አሳብ የተዋጡ ናቸው ። ደግሞ በወይን ጠጅ የሰከረ ሰው ባልሆነ ቦታ ሲወድቅ ፡ የሚያነሳው እንደማያገኝ የአለምም ጥበብ ከጥፋት አያድንም ። ከዚህም ሌላ

ለሞተ ሰው እህቱ ልጆቹን አቅፋ እንደምታለቅስለት የአለምና የወ ዳጆቿ ምሳሌ በእሳት የተቃጠለችው ደማስቆ መሆኗን ባለቅኔው አስረድተዋል ።

210 መወድስ

አትሮንስ ረኃብ ሰሎሞን ድንግለ ኢያሱ
አቤሜሌክ ግፍዕ ኤርምያስ ዘአልሀቆ
አዕረገ ብኪ እግረ ተሣልቆ ፡
ለገጽኪ ፈሪሳዊ
ዮሐንስ ተሰዶ አኮኑ አጥመቆ ።
ወተመሥጠ ልቡናኪ
በዘልቡና ይመሥጥ ድምፀ ሰቆቃው መሰንቆ ።
ረኃብኂ አምላኩሙ ለሰብአ ብዙኀ ናፍቆ
ለቃዴስ ልቡናኪ በግብጽ ያድለቀልቆ ፡
ወእንዘ ይዘርዕ ነግሀ ዘርዐ ልቡና ተጽዕቆ
ለእብን መልዕልቴሃ ቦ ዘይወድቆ ።

ት ር ጉ ም

የሰሎሞን / ራብ ዙፋን / የኢያሱ ድንግል !
ኤርምያስ ያሳደገው አቤሜሌክ / ግፍ
ዝብብት / እግርን አወጣብሽ ፡
የፋሬስ ወገን / ፈትሽን
ዮሀንስ / መሰደድ አጥምቆታልና ፡
ልብን በሚመስጥ
በልቅሶ / መሰንቆ ድምፅም ልብሽ ተመስጧልና ።
የብዙ ጥርጥር ሰዎች አምላክ / ራብም
በረሃ / ልብሽን በግብፅ ያናውጠዋል ፡
የልብ ዘር / መጨነቅንም በጠዋት ሲዘራ
በድንጋይ ላይ የወደቀ ዘር አለ ።

ለሰሎሞን በተዘጋጀለት በዳዊት ዙፋን ላይ የሚቀመጥ እግ
ሩን እንደሚዘረጋባት ፣ በራብም የተሰቃየች ቅድስት ማርያምን መገ
ፋት መዘባበቻ አደረጋት ። ደግሞ አባት ልጁን ተጠብቦ ተጨንቆ
እንደሚያሳድግ ነቢይ ኤርምያስም ግፍ ተቀብሏል ።

ዮሀንስ ፈሪሳዊውን በውሃ እንዳጠመቀው መሰደድ የማርያምን
ፊት በእንባ አጠበው ። ከዚህም በላይ የመሰንቆ ድምፅ ልብን እን
ደሚመስጥ የልቅሶ ብዛት የማርያምን አእምሮ ሲያናውጠው ራብም
የማርያምን ልብ አደከመው ። ዘርም በገበሬ እጅ ሲዘራ በድንጋይ
ላይ የሚወድቅ ፍንጣሪ እንዳለ መጨነቅም ማርያምን እንቅፋት
አስመታት ይላሉ ባለቅኔው ።

211 ዋዜማ

ዘእርአያ ወረታ (አቶ)

መላእክተ ሰማይ ለመታብር
በከመ ሕገ ላእክ ዮሴፍ አማሕፀንም ዐቂበ
እንበለ ሩካቤ ኪያሃ መዝገበ ፤
ዳዊትሰ ዘመዳ አመ በመታብር ተረክበ
አንሰ ዕፄ ብሂለ በከመ ነበበ
እምከልእዎ ጎቤሃ ቀሪበ ።

ት ር ጉ ም

የሰማይ መላእክት መታብርን
እንደ መላክተኛ ዮሴፍ ህግ ያለግንኙት እርሷ
ሳጥንን መጠበቅን አማጠኑት (አደራ አሉት) ፤
ዘመዷ ዳዊት ግን በመታብር ቢገኝ
«እኔ ትል ነኝ» ማለትን እንደተናገረ
ወደርሷ መቅረብን በከለከሉት ነበር ።

እነዘካርያስ ብላቴናይቱን ማርያምን ጠብቅ ብለው ዮሴፍን
እንደአማጠኑትና እርሱም ያለ ሩካቤ (ያለግንኙነት) በንፅህና ጠብቆ
እንዳስረከባቸው ፣ መታብርም የተቀበረችበትን ቅድስት ማርያምን
እንደ ሌሎቹ ሙታን አላፈረሳትም ፣ አላበሰበሳትም ። የስጋ ዘመዷ
ዳዊትም « እኔ ትል ነኝ » ብሎ በማረጋገጥ ትልነቱን ካመነበት
በስመ ዘመድ እርሱን ወደበድኗ ማቅረብ አይገባም በማለት ደራ
ሲው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

212 ሥላሴ

ዘኢላይያስ (አቡቶ)

በለሰ ገነት
ለአዳም ወሔዋን መቲሮቶሙ
መንከረ ልደት አምላክ መንገሌሆሙ ሰሐበ ፤
ወገብርኤልሃ ዜናዌ ቀጸበ ።
እንተ ከመዝሰ ግብር እምከመ ለአዳም ተውህበ
ወረከበት ሔዋን ዘኢተረክበ ፣
ካዕበ ይስሐብ ጎቤሆሙ አበ
ለበለስ ይምትርዎ ካዕበ ።

ት ር ጉ ም

የገነት በለስን
የአዳምና የሄዋን መቁረጣቸው
ልደቱ የተደነቀ አምላክን ወደነርሱ ሳበ ፤
ዝነኛ ገብርኤልንም ወደነርሱ ጠቀሰ ።
እንደዚህስ ያለው ስራ ለአዳም ከተሰጠ
ሄዋንም ያልተገኘውን ካገኘች ፣
አብን ዳግመኛ ወደነርሱ ይስብ ዘንድ
በለስን ሁለተኛ (ዳግመኛ) ይቁረጡት ።

ም ስ ጢ ር

ቤተ ሰሪ አረግ እንደሚመዝ የአዳምና የሄዋን በለስን መብላት ሰማያዊው እግዚአብሄር ወልድን ሰው ለመሆን አደረሰው ። ደግሞ አንድ ጓድ ጓደኛውን በእጁ እንደሚጠቅሰው ፣ የአዳምና የሄዋን በለስን መብላት ገብርኤል የተባለውን መልአክ የወልድን መፀነስና መወለድ ለቅድስት ማርያም እንዲያበስር አደረገው ።

ከዚህም ሌላ መጠጥ ሲደጋግሙት እንደሚያረካ በለስን ቆርጦ መብላት ወልድን የስጋ ዘመዳችን ካደረገልን ፣ አዳምና ሄዋን ዳግመኛ በለስን ቆርጠው ቢበሉት አብም እንደ ወልድ በስጋ ይዘመዳን ነበር ይላሉ ባለቅኔው ።

213 ሥላሴ

ወልድ ፈደለ ዐርብ
ላዕሌሁ ለዕፀ አመ ተሰፍሐ
ሕማማተ ሥጋ ደቂቅ ከመ ኪያሁ ያንብቡ
ሣዕረ ቀኖተ ሐፂን ነሢአሙ ቀርቡ ፤
ለመምህሮሙ ትጉህ ይሁዳ እንተ ፈድፈደ ጥበቡ
ሠላሳ ብሩር አምጣነ አስቡ ።
ወጽሕፈተ ዝንቱ ፈደል በማይ ጎፀቡ ፤
እስመ ሐረ ውስተ ደይን ምስካቡ ።

ት ር ጉ ም

የአርብ ፈደል/ ወልድ
በእንጨት ላይ በተዘረጋ ጊዜ
የስጋ ህማሞች / ልጆች እርሱን ያነቡ ዘንድ
የብረት ችንካር / ሳርን ይዘው ቀረቡ ፤
ጥበቡ የበዛ የትጉ መምህራቸው ይሁዳ

ደመወዙ ሰላሳ ብር ነውና ።
የዚህንም ፈደል ዕህፈት በውሃ አጠቡ ፤
ወደ ቅጣት / መኝታው ሄዷልና ።

ም ስ ጢ ር

የህፃናት መማሪያ ፈደል በእንጨት ላይ ተዘርግቶ ልጆች በሳር እየነኩ እንደሚቆጥሩት ፣ ወልድ አርብ ቀን በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ ፣ በችንካር ተቸነከረ ፣ የስጋ መከራንም ተቀበለ ። የልጆቹም መምህር በሰላሳ ብር እንደሚቀጠር ይሁዳ ወልድን ለሰላሳ ብር ሸጠው ። መምህሩ ከክፍሉ ሲወጣ ትንንሾቹ ልጆች ፈደሉን በውሃ እንደሚያጥቡት ከወልድ ጎንም ውሃ ፈሰሰ ። ይሁዳም ወደቅጣት ቦታ ወረደ በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

214 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ረቢ ሰገደ በመንፈቀ ሌሊት ለረቢ ፤
አኮኑ አጽባዕት እምነ አጽባዕት የዐቢ ።

ት ር ጉ ም

መምህር በእኩለ ሌሊት ለመምህር ሰገደ ፤
ከጣት ጣት ይበልጣልና ።

ም ስ ጢ ር

ከጣት ጣት እንደሚበልጥ ፣ ከመምህር መምህር ስለሚበልጥ ከላቀው መምህር ዝቅተኛው መምህር ጠይቆ ይረዳል ። እንዲሁም የአይሁድ አለቃ ኒቆዲሞስ በኢየሱስ አምኖ ፣ አምላክነቱን መስክሮ ሌሊት ለኢየሱስ መስገዱን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

ረቢ የተባለው የአይሁድ አለቃ ኒቆዲሞስ ነው ። እርሱም ቀ
ቀን በአሪቱ ህግ ከአይሁድ ጋር እየመከረ ሌሊት ሌሊት ወደክር
ቱስ እየሄደ ይሰግድለት ነበር ። ሁለተኛው ረቢ ኒቆዲሞስ የሰ
ለት ኢየሱስ ነው ። በዚህም ኢየሱስ ኒቆዲሞስን « ከውሃና ከመ
ፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ወደ እግዚአብሄር መንግስት ሊገባ አ
ችልም» ቢለው ፣ ኒቆዲሞስ «ዳግመኛ ወደእናት ሆድ መግባት እ
ዴት ይቻላል ?» ብሏል (ዮሀ. 3) ።

215 ዋዜማ

መንበረ ኪሩባዌ
ለእመ በቅብዐት ወረሰ ፍሬ ክርሥኪ ዕፀብ ፣
ዘቤተ ድንጋሌ ማርያም ርግብ !
እስመ ከማሁ ኮልነ ሱቱፋነ ቅብዐት ሕዝብ
እስፍንተ ያገምር መንበሩ ለአብ
ወእስፍንተ ይጸውር ኪሩብ ።

ት ር ጉ ም

የኪሩብን ዙፋን
የሚያስደንቅ ሆድሽ ፍሬ በመቀባት ቢወርስ ፣
የድንጋሌ ቤት ልጅ ማርያም ርግብ !
ሁላችን እንደርሱው የቅባቱ ተሳታፊዎች ህዝብ ነንና
የአብ ዙፋኑ ስንትን ሰው ይችላል ?
ኪሩብስ ስንቱን ይሸከማል ?

ም ስ ጢ ር

አንድ ወንበር ወይም አንድ ዙፋን ከአንድ ተቀቢ ሹም ሌ
አይዝም ። ስለዚህ ከቅድስት ማርያም በስጋ የተወለደ እግዚአብሄ
ወልድ በመንፈስ ቅዱስ ቅባት የከበረ ከሆነ ፣ ክርስቲያኖች ሁ

በውሃ ተጠምቀው በሚያገኙት በመንፈስ ቅዱስ ልጅነት የወልድ
ግብረ አበሮች መሆናቸው ነውና ፡ ኪሩብ የተሸከመው አንዱ ዙፋን
ይህን ሁሉ አምላክ ሊችል ነው ወይ ? በማለት ባለቅኔው «ወልድ
በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ከበረ» የሚሉ ወገኖችን በቅኔያቸው ምስ
ጢር ገስፀዋል ።

216 መወድስ

ዘጎይለ ሥላሴ (አለቃ)

ኦ ዓለም ኢይደልወከ
በጎልቀተ ብሉይ ልብስከ ትግበር ጎዘነ ልብ ፣
አኮኑ መሀበ እግዚአብሔር ቅሩብ
ክልኤቱ ጽላት ድኅረ ተሰብሩ
ጽላተ ክልኤተ ለሙሴ መክብብ ፡
ወወሀበ ለኢዮብ
ድኅረ ጎልቀተ ብዕል ብዕለ እንተ አልቦቱ ሐሳብ ።
ልብከሰ እመ አእመረ ጣዕመ ሕተታ ሐሊብ
ጎዘን ይደልወከ በጎልቀተ ዕድሜ ወይኒ ከብካብ ፡
እስመ ከመ ይትረከብ ልብስ ድኅረ ጎልቀተ ልብስ ዕፀብ
ዕድሜ እምድኅረ ጎልቀ ዕድሜ ኢይትረከብ ።

ት ር ጉ ም

አለም ሆይ ለአሮጌ
ልብስህ ማለቅ የልብ አዘንን ታደርግ ዘንድ አይገባህም ፣
ሁለቱ ፅላቶች ከተሰበሩ በሁዋላ
ሁለት ፅላትን ለሹም ሙሴ
ቅርብ እግዚአብሄር ሰጥቷልና ፡
ከብልፅግና እልቀት በሁዋላም
ቁጥር የሌለው ብልፅግናን ለኢዮብ ሰጥቷልና ።
ልብህስ የምርምር / ወተት ጣእምን ቢያውቅ

ለሰርግ ወይን ጠጅ / እድሜ እልቀት አዘን ይገባሃል ፤
ከድንቅ ልብስ እልቀት በሁዋላ ልብስ እንዲገኝ
እድሜ ካለቀ በሁዋላ እድሜ አይገኝምና ።

ም ስ ጢ ር

ባለፀጋ ልብሱ ቢያረጅና ቢያልቅ ምን አለብሳለሁ እንደማይል ሁለት ፅላቶች የተሰበሩበት ሙሴ ሌሎች ሁለት ፅላቶችን አግኝ ቷል ። ገንዘብም ቢያልቅ ገንዘብ ያለው ሰው ምን አበላለሁ እንደ ማይል ሀብቱ ያለቀበት አዮብ ሀብቱ እጥፍ ሆኖለታል ። ይህ ሁሉ መገኘቱ ሀይወት ባያልቅ ስለሆነ ሀይወት ካለቀ መተኪያ ስለሌ ለው ፤ ከልብስና ከገንዘብ ይልቅ ለህይወት ግሰብ ይበልጣል በማ ለት ባለቅኔው የህይወትን ክቡርነት ያስረዳሉ ።

217 ዋዜማ

ዘተክለ ጽዮን (አለታ)

ወላዴ ሶምሶን ረዓይታዊ
በቃለ አፍአዊ ትሕዝብት ለመልአከ ሰማይ ነበቦ ፤
በሐቅል ምስለ ብእሲቱ አኮኑ ረከቦ
ጸጋ ዘአብሰ በፍቅር ድኅረ ለመልአከ ሰሐቦ
ምስለ ብእሲቱ ፅንስት እምተሐዘቦ ፤
አስሙ ከንፍ ለወልዱ ተውህቦ ።

ት ር ጉ ም

የረአይት ወገን የሶምሶን አባት
በላይ መድላ ጥርጣሬ ቃል የሰማይ መልአክን ተናገረው ፤
ከሚሽቱ ጋር በዱር አግኙቱታልና ።
ፀጋ ዘአብ ግን በፍቅር መልአክን ከሳበው በሁዋላ
ከፀነሸች ሚስቱ ጋር በተጠራጠረው ነበር ፤
ከንፍ ለልጁ ተሰጥቶታልና ።

ም ስ ጢ ር

አንድ ሰው ከሚስቱ ጋር በጫካ ውስጥ ሲያወራ ያገኘውን ሌላ ሰው ባልጠለቀ (በቀል በሌለው) ጥርጥር ቃል ያነጋግረዋል ፤ ምክ ንያቱም ልጁ አባቱን እንጂ ሰውየውን ስላልመሰለ ነው ። እንዲሁም የሶምሶን አባት ሚስቱን ሲያበስር (የምስራች ሲነግር) በዱር ያገኘ ውን መልአክ በሌላ ሁኔታ እንዳይገምተው የልጁ መልክ መልአ ክን አልመሰለም ።

ነገር ግን ከሴትየይቱ ጋር ሲያወራ በዱር የተገኘወን ሰው መስሎ ልጁ ሲወለድ ባለየው ሰውየውን በፍፁም እንደሚጠረጥ ረው ፤ የፀጋ ዘአብ ልጅ ተክለ ሃይማኖት በክንፍ መልአክን መስሎ በመገኘቱ በአባቱ በኩል ያጠራጥር እንደነበር በማመልከት ቅኔው ተመስጥሯል ።

218 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ዘቴዎድሮስ (መልአክ ፀሐይ)

ግርያም ዘኢትፈርህ ሐሜት
ፍርፋራተ ጎብስት ሰአለት በፍና እንዘ ትጸውር ጎብስተ።

ት ር ጉ ም

አሜት የማትፈራ ግርያም
እንጀራ ተሸክማ የእንጀራን ፍርፋሪ በመንገድ ለመነች።

ም ስ ጢ ር

ያልተቆረሰ እንጀራ አያላት ቁራሽ እንጀራ የምትለምን ለማኝ «አሜትን አትፈራም ? » ይባላል ። በእንግሩም ቅድስት ግርያም ከአ ገሯ ወደምድረ ግብፅ በተሰደደች ጊዜ ሀብስት የተባለ ልጅዋን ይዛ እንጀራ መለመንን በመግለጥ እርሷም ልጅዋም ነውር የሌለባቸው መሆኑን ባለቅኔው አስገንዝበዋል ።

219 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘምንደስይል (ደብተራ)

ሙሴ ኢትጎድግ መቃብረከ ክሡት ፤
እስመ እንተ ጴጥሮስ ቤት ኢይከውነከ ቤተ ።

ት ር ጉ ም

ሙሴ የተከፈተ መቃብርህን አትትው ፤
የጴጥሮስ ቤት ቤት አይሆንህምና ።

ም ስ ጢ ር

«የሰው ቤት ቤት ላይሆን ቤትህን አትልቀቅ» እንዲሉ ሙሴ ከሞተ በሁዋላ በአካለ ነፍስ ወደ ደብረ ታቦር መምጣቱንና ተመልሶ መሄዱን ፥ ጴጥሮስም «ለሙሴና ለኤልያስ አንዳንድ ቤትን እንስራ» ካለ በሁዋላ ቤቱ እለመሰራቱን ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

220 ዘአምላኪየ

ዘኮነ (መምህር)

ዕቡየ ልቡና መሰልከ ወኢመሰልከ ትሑተ
ቴዎድሮስ ብእሴ ቅሕትና ዘትሰመይ አንተ ፤
እስከ አንፍከ በዐውድ እስመ ትለብስ ቀናቱ ።

ት ር ጉ ም

የትህትና ሰው የምትባል ቴዎድሮስ ! አንተ የልብ ቅንዒ ትኖን መሰልህ ትሁትን ግን አልመሰልህም ፤
እስከ አፍንጫህ ድረስ በአደባባይ ችንካር/ ልብስን ትለብሳለህና ።

ም ስ ጢ ር

አንዳንድ ሰው «እገሌ ትሁት ነው» እየተባለ ሲመሰገን ከኖረ በሁዋላ ከእለታት አንድ ቀን ልብሱን አፍንጫው ላይ አድርጎ በአደባባይ ትእቢተኛ መስሉ ይታያል ። እንዲሁም የክርስቶስ ሰማእት ቴዎድሮስ ለጣኦት አልሰግድም ፥ ለከሀዲ አልገዛም በማለቱ መላ ሰውነቱን አፍንጫው ላይቀር በችንካሮች ተቸነከረ ይላሉ ባለቅኔው።

221 ዋዜማ

ዘተክሌ (መምህር ፥ ዘዋሽራ)

ቶማስ መምህረ ሕግ
እንተ ወሀብዎ ሕዝብ ጽዋዐ ሞቱ ምትረተ
ተወክፈ ሰፈሐ እጻዋ ክልኡተ ፥
ካልኡሰ ሉቃስ ዘኢትምህረ ሥርዐተ
በዋሕድ እድ ተወክፈ ዘንተ ፥
እስመ ገብረ ምስለ ላሕም ጎድረተ ።

ት ር ጉ ም

የህግ መምህር ቶማስ
ህዝብ የሰጡት የሞቱ ዕዋ መቆረጥን
ሁለት እጆቹን ዘርግቶ ተቀበለ ፥
ስርአትን ያልተማረ ሁለተኛው ሉቃስ ግን
ይህን በአንድ እጅ ተቀበለ ፥
ከላም ጋር አዳርጎ እደርጓልና ።

ም ስ ጢ ር

ያባቶችን ስርአት ያወቀ ልጅ ዳረጎቱን በሁለት እጆቹ እንዲ ተባል ቶማስ ሁለት እጆቹን በሰይፍ ተቆረጠ ፥ ያባቶችን ስርአት ያልተማረ የከብቶች እረኛ ግን ዳረጎቱን በአንድ እጁ እንደሚቀበል

ነፀ ላህም (ላም ፌት) የሚባል ሉቃስ አንዱን እጁን ተሰየፈ በማ
ለት ባለትኔው የሰማእቱ ቶማስንና የሀዋርያው ሉቃስን ስቃይ ልዩ
ነት በመተንተን ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ፡

222 ሥላሴ

እዝርዕተ ምድርነ
ያደንኑ ታሕተ ሶበ ፈረዩ ፤
ፍሬ ይስሕብ አኮኑ መንገለ ታሕቱ አዝርዕተ ።
ወዘከመ እሱ እኁልቍ እስፍንት ?
አሐቲሰ ዕፅ ባሕቲታ ከመ ታግብአ መሬተ
ወከመ ያዕርጋ ሰማያተ
ሰሐበት ዕፅ ታሕተ ታሕተ ፤
ወፍሬሃ ሰሐባ መልዕልተ ።

ት ጉ ር ም

የመሬት ዝሪቶቻችን
ባፈሩ ጊዜ ወደታች ያዘነብላሉ ፤
ፍሬ ዘሮችን ወደታቹ (ወደስሩ) ይስባልና ።
እንደነዚህ ያሉትንም ስንቱን እቆጥራለሁ ?
አንዲት እንጨት ግን ብቻዋን ወደመሬት ታግባው ዘንድ
ወደሰማዮችም እርሷን ያወጣት ዘንድ
እንጨት ፍሬዋን ወደታች ወደታች ሳበች ፤
ፍሬዋም ወደላይ ሳባት ።

ም ስ ጢ ር

የምድር ዝሪቶች (አዝርእት) ባፈሩ ጊዜ ራሳቸውን ወደምድር ዘንበል ማድረጋቸው ልማድ ሲሆን አንድ በቀል እንጨት ያለል ማድ ሰራች በማለት ፤ ለአባቷና ለእናቷ አንድ የሆነችና እፅ የተ ባለች ቅድስት ማርያምን የፍሬ ምሳሌ የሆነ ወልድ ከሰማይ ወደ ምድር ወርዶ ከርሷ ተወልዶ ወደ ሰማይ አወጣት ይላሉ ባለቅኔው ።

223 ሥላሴ

ልሕቱተ ኤልሣዕ
ጥንቁቀ አንብር ዘካርያስ ፡
ወነጺረከ ተወከፍ አእዛኒሃ ከልኤተ
እሰ ኢተሰብሩ በአእባን ግብተ ፤
ለእመ ይቤሉከ አምጽእ ሥላሴ እስመ ኢትረክብ እንተ
ለእመ ቱዐርግ ሰማያተ ፡
ወለእመ ትወርድ ካዕበ ታሕተ ታሕተ
ዘከማሃ ሐዳሰ ልሕቱተ ።

ት ር ጉ ም

ዘካርያስ የኤልሳእ
ገንቦን በጥንቃቄ አስቀምጥ ፡
ድንገት በድንጋዮች ያልተሰበሩትን
ሁለት ጀሮዎችዋንም እይተህ ተቀበል ፤
ስላሴ አምጣ ቢሉህ አንተ አታገኝምና
ወደ ሰማዮች ብትወጣ ፡
ሁለተኛም ወደታች ወደ ታች ብትወርድ
እንደሷ አዲስ ገንቦን (አታገኝምና) ።

ም ስ ጢ ር

ጥሩ የሆነች ገንቦን የሚዋስ ሰው ሁለንተናዋን አይቶ መረከ ብና በጥንቃቄ ማኖር አለበት ። በዘመነ አሪት የቤተ መቅደስ አስ ተዳዳሪ የሆነ ዘካርያስም የኤልሳእ ገንቦ ምሳሌ የሆነችውን የሶስት አመት ብላቴና ማርያምን ከወላጆቿ ሲረከባት ፡ ሁለት ነገሮች መናና ወይን ለርሷ ከሰማይ መውረዳቸውንና አርሷም በሁለት ነገሮች (በስጋና በአሳብ) ድንግል መሆኗን በመግለጥ በገንቦና በሁ ለት ህብርነት ቅኔው ተመስጥሯል ።

224 ዘይእዜ

ዘዐምደ ሚካኤል (አለቃ)

ኢይበቁዕ ወልድ ለወላዲሁ ፣
አምጣነ ለሞቱ ወለደ አርዌ ገሞራ ነልኤተ ፣
ወደቂቅ ዘልህቁ በአጥባቲሁ ፡
ቀተልዎ ለአርዌ ገዳም ዘወለደ ምእተ ።
በወሊድሂ ብዙኀ እመ ኢረከቡ በቍዔተ
ዘወለዱ ሰብአ ወመላእክተ
ሐና ትበቍዕ በወሊዶታ እሐተ ።
ዘወለዱ ሰብአ ወመላእክተ

ት ር ጉ ም

ልጅ ለወላጁ አይጠቅምም ፣
የገሞራ አውሬ ለሞቱ ሁለት ወልዷልና ፣
በጡቶቹ ያደጉ ልጆቹም
መቶን የወለደ የዱር አውሬን ገድለውታልና ።
ሰውንና መላእክትን የወለዱም
ብዙ በመውለድ ጥቅምን ባያገኙ
አንዲትን በመውለዷ ሀና ትጠቅማለች ።
ሰውንና መላእክትን የወለዱም

ም ስ ጢ ር

የገሞራ አውሬን (እባብን) ልጆቿ ገድለዋት ይወለዳሉ ። ሀና ግን አንዲት ልጅ ብቻ ወልዳ ፡ ፎካሪ « ብዙ ቢወለድ ብዙ ነው ጉዱ የእገሌ ልጅ ይበቃል አንዱ » እንዳለው ብዙ ከወለዱት ይበልጥ ተከበረች በማለት ባለቅኔው መጠቀም ወይም አለመጠቀም ብዙ ወይም ጥቂት በመውለድ አለመሆኑን ያስረዳሉ ።

225 መወድስ

መዓተ ሥላሴ ዘኮነ አረጋዌ ዕድሜ
ድኅረ እግየ አይኅ ወፅአ እመ ኢክህለ ቍረተ
በምድረ ገሞራ ተረክበ እንዘ ይስሕን እሳተ ፤
ወእመ ተጸውዐ ለበሊዕ
ውስተ ቤተ ሎጥ ዘቀርበ ምሕረተ
እመ ለስሐ ጣዕመ ዝንቱ
ለተወክፎ ጼው ሰአለ ወአግኅፀነ ብእሲተ ።
መዓትሂ አረጋዊ በጊዜ ሰአለ ዘንተ
ብዙኀ ያኅዝን ወያቴክዝ ዓለማተ ፤
እምድኅረ ውእቱ ፈትሐ በምድረ ሰናዖር ቤተ
ቅድመ ሎጥ ጸላኢሁ እስመ ተዋረደ ወተትሕተ ።

ት ር ጉ ም

የእድሜ ሽማግሌ የሆነ የሰላሴ ቁጣ
ከጥፋት ውሃ ከወጣ በሁዋላ ቅዝቃዜን ባይችል
እሳትን እየሞቀ በገሞራ ምድር ተገኘ ፤
በሎጥ ቤት ውስጥ የቀረበ
ምህረትንም ለመብላት በተጠራ ጊዜ
የዚሁ ጣም ቢያልጥ (አልጫ ቢሆን)
ጨው ለመቀበል ለምኖ ቤትን አማጠነ ።
ሽማግሌ ቁጣም ይህን በለመነ ጊዜ
ብዙውን ያሳዝናል ፡ አለሞችንም ያስተከዛል ፤
እሱ በሰናኦር ምድር ቤት ከፈታ በሁዋላ
በጠላቱ ሎጥ ፊት ተዋርዷልና ።

ም ስ ጢ ር

ገላውን የታጠበ ሽማግሌ ከመታጠቢያ ቤት ሲወጣ የተሰማውን ቅዝቃዜ ለማስወገድ እሳት እንደሚሞቅ ፡ የስላሴ ቁጣ በሰብአ ትካት የጥፋት ውሃን ካዘነበ በሁዋላ በገሞራና በሰዶም እሳትን አዘ ነበ ። ደግሞ ለግብጣ የተጠራ ሽማግሌ ምግቡ ጨው ሲያንሰው ተጨማሪ ጨው እንደሚጠይቅ ፡ የስላሴ ቁጣም ለሎጥ ይቅርታን ሲያደርግ የሎጥን ሚስት የጨው ሀውልት አደረገ ። ከዚህም ሌላ ሽማግሌ ቤት ሲፈታ እንደሚዋረድ የስላሴ ቁጣ በሰናአር ምድር የተሰራውን ህንፃ ማፍረሱንና መመዝበሩን ፡ ቋንቋውንም መለወ ጡን ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

226 መወድስ

ደቀ አስጢፋ ጻድቅ አመ አስክንድር
በመንፈስ ቅዱስ ነበበ ሐሳባተ ነቢይ ቅኔያተ
እምቅኔያቲሁ ለያሬድ እንበለ ያትርፍ አሐተ ።
ወከመ ኢይጎድሩ ውስተ አፍአ
ለቅኔያቲሁ ሐነጸ አብያተ
ሰብዓ ወሰማኒተ ፡
ወጠፈረ እሎን አብያት እስካነ ይእዜ ኢተነስተ ።
ሐዊራስ ወመንክራ ዘተጋብኡ ድርገተ
ዘምስለ ብሑር ወእስክንድር አስተጋብኡ መንክራተ
መንክራተሂ መተሩ ወተመሰሉ መጥባሕተ ፡
ለመጥባሕት እስመ ልማዱ ከፈለ ዋሕድ አርባዕተ ።

ት ር ጉ ም

እውነተኛ ደቀ አስጢፋ በእስክንድር ጊዜ
በመንፈስ ቅዱስ የነቢይ አሳቦች ቅኔያትን ተናገረ ፡
ከያሬድ ቅኔዎች አንዲቱን ሳያስቀር ።
በውጭም እንዳያድሩ

ሰባ ስምንት ቤቶችን
ለቅኔዎች ሰራ ፤
የእሊህም ቤቶች ባጥ (ጣሪያ) እስከዛሬ አልፈረሰም ።
ከብሑርና ከእስክንድር ጋር በአንድነት የተሰበሰቡ
ሀዊራና መንክራ ግን አስደናቂዎችን ሰበሰቡ ፡
አስደናቂዎችንም ከፈሉ ሰይፍንም መሰሉ ፤
ለሰይፍ አንዱን ለአራት መክፈል ልማዱ ነውና ።

ም ስ ጢ ር

እውነተኛ ሰው ምስክርነት ሲጠራ በዳኛው ፊት እውነቱን ይመሰክራል ። ከሚያውቃቸውም ነገሮች ምንም አያስቀርም ። እን ዲሁም ደቀ አስጠፋ የነቢያትን አሳብ አጉልቶ የያሬድን ቅኔዎች አደመቀ ፡ ምንም አላጎደለም ።

አንዳንድ አባት ልጆች በቤት እጦት እንዳይቸገሩ በቁጥራቸው ቤቶችን ሰርቶ እንደሚያስረክባቸው ሁሉ እንዲሁም ደቀ አስጢፋ ቅኔዎችን በሰባ ስምንት ቤቶች ከፍሎ ተቀኘ ። የእነዚህም አቅ ዋም እስከባለቅኔው ዘመን ድረስ ፀንቶ ቆየ ።

ከዚህም ሌላ ሽማግሌዎች የሚች ልጆችን ሰብስበው ሀብቱን እንደሚያካፍሏቸው ሀዊራና መንክራ እስክንድርና ብሑር የተባሉ የደቀ አስጢፋ ደቀ መዛሙርት አስደናቂዎችን የዜማ ድርሰቶች በእየተሰማሚዎቻቸው ዘመናትና በአላት አዘጋጁዋቸው ። የስጋ መልከኛም ስጋውን በየብልቱ እንደሚያወጣው ድጓውን ለአራት ከፈሉት በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

227 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘወልደ ጊዮርጊስ (መምህር ፡ ዘራጉኤል)

ባሕታዊ ኢትክሥት ምስጢረ አዕይንት ክልኤቱ ፤
ቀሊል ያፍ እስመ ያወፅአ በከንቱ ።

ባህታዊ ! የሁለቱ አይኖች ምስጢርን አትግለጥ ፣
ቀላል ወፍ በከንቱ ያወጣዋልና ።

ም ስ ጢ ር

ለቀላል ሰው ምስጢር ቢነግሩት ለማንም እንደሚያወጣው ፣ የገብረ መንፈስ ቅዱስን አይን የዱር ወፍ አወጣው ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

228 ዋዜማ

ለሥጋ ድንግል ደጋራዊ
መኑ ይነግር በይነ ሰማያዊ ልደቱ ?
እምድር እስመ ተአተተ መቃብር ሕይወቱ ።
በልማደ ሲኦል ይብል ዕፄ መቃብር ባሕቱ
ተውህቦ ሥጋ ለሀጕል ይምሥጠኒ ዝንቱ
ሰማያዊ ደመና በከንቱ ።

ት ር ጉ ም

ለሁዋለኛው የድንግል ስጋ
ስለሰማያዊ ልደቱ ማን ያወራል ?
ህይወቱ መቃብር ከምድር ተወግዷልና ።
ነገር ግን በሲኦል ልማድ የመቃብር ትል
እርሱ የሰማይ ደመና በከንቱ ለጥፋት ይነጥቀኝ ዘንድ
ስጋ ተሰጠው ይላል ።

ም ስ ጢ ር

ለወልድ የማይመረመር ሰማያዊ ልደት እንዳለው የድንግል ማርያም ስጋ ከመቃብር ተነስቶ ወደሰማይ መውጣቱን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ።

እንዲሁም ዲያብሎስ ነፍሳትን እንደተነጠቀ የመቃብር ትልም የማርያምን ስጋ በደመና አጣ በማለት ባለቅኔው የቅድስት ማርያምን ስጋ በመቃብር መፍረስና መበስበስ ያላገኙት መሆኑን በቅኔ ያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

229 ዋዜማ

ዘሣህሌ ወልደ ተክሉ

እምአብርሃም መጋቤ ሕግ
ሲሳየ ዕለት ጎሠሠ አጋዕዝተ ሙሴ ሠለስቱ ፤
ጎዳጥ ሲሳየ ዕለት እስመ ፈውስ ውእቱ ።
ውስተ ቤተ ሙሴሰ ኪራም ዘኢየጎልቅ ንብረቱ
ኢጎሠሠ መና ብዙኅ ከመ ኢይሙቱ ፤
አበዊነ እስመ ጎልቁ ቦቱ ።

ት ር ጉ ም

ከህግ መጋቢ /አብርሃም
ሶስቱ የሙሴ ጌቶች የእለት ምግብን ፈለጉ ፤
ጥቂት የእለት ምግብ መድሃኒት ነውና ።
ንብረቱ በማያልቅ በሙሴ / ኪራም ቤት ውስጥ ግን
እንዳይሞቱ ብዙ መናን አልፈለጉም ፤
አባቶቻችን አልቀውበታልና ።

ም ስ ጢ ር

መንገደኞች ካለው ሰው ቤት የእለት ምግብን ፈልገው በራብ ከመሞት እንደሚድኑ ስላሴም በአብርሃም ቤት በሉ ። ከዚህም ሌላ መንገደኞች በሚጠረጥሩት ሰው ቤት ምንም ነገር እንደማይቀምሱ ፣ ስላሴም ከሙሴ መና አለመቅመሳቸው እስራኤል ስለሞቱ በት ነው ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

ታሪክ

ስላሴ በአብርሃም ቤት ገብተው በእንግዶች አምሳል የቀረበ ላቸውን ተቀብለዋል ። እስራኤል አርባ ዘመን ሲጓዙ መና ከሰማይ እየወረደላቸው ተመግበዋል ፤ ከእነርሱም ብዙዎቹ እየታመሙ እንደቅጠል ረግፈው እንደሻሸ ተነጥፈው በዱር ቀርተዋል ይባላል። (ዘፍጥ.18 ። ዘፀአ. 16 ፣ 13—36) ።

230 ዋዜማ

ፈሪሳውያን ወብእሲት
ምክንያተ ዕልው ሄሮድስ ወሄሮድያዳ ክልኤቱ ፤
ብዙኃን እስመ በአሐቲ ዘመዊ እምጥንቱ ።
እመሰ ይትረከብ ሠራዔ ሕግጋት እሎንቱ
ሰብዑ አንስት እምኮና ለሰብዐቱ ፤
ወአሐቲ ለዋሕድ ዝንቱ ።

ትርጉም

ፈሪሳውያንና ሴት
የሁለቱ የወንጀለኛው ሄሮድስና የሄሮድያዳ ምክንያት ናቸው ፤
ብዙዎች ባንዲቱ ከመጀመርያ በድለዋልና
እነኚህን ሀጎች ሰሪ ቢገኝ ግን
ሰባቱ ሴቶች ለሰባቱ ወንዶች በሆኑ ነበር ፤
አንዲቱም ለዚህ ለአንዱ በሆነች ነበር ።

ምስጢር

ባለቅኔው የፈሪሳውያንና ያንዲት ዝሙት አዳሪ ሴት ስራ ከሄሮድስና ከሄሮድያዳ ስራ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን በቅኔያቸው ገልጠዋል ።

231 ዋዜማ

ዘገብረ ሚካኤል ዕሙር (ዘሰላሴ)

ነጸረ ሰማዕተ ልዳ
ተቅዋመ ሥቃይ ዘመነ ዘአዕጹቂሃ ሰብዐቱ
እንዘ በውስቴታ ነበልባል የኀቱ ።
ወጐልቈ ሰብዐቱ አክራም ዘወሰናሙ ዕረፍቱ
በነበ ዕብራዊ መጥባሕት ፍጹም ውእቱ ፤
ወዐሥር በነቢነ ሞቱ ።

ትርጉም

የልዳ ሰማእት (ጊዮርጊስ)
ጫፎቿ ሰባት የሆኑ የስቃይ መቅረዝ ዘመንን አየ ፤
በውስጧ ነበልባሉ ሲበራ ።
እረፍቱ (ሞቱ) የወሰናቸው የሰባቱ ዘመኖች ቁጥርም
በእብራዊ ሰይፍ ዘንድ ፍፁም ነው ፤
አስርም በእኛ ዘንድ ሞቱ ነው ።

ምስጢር

ዘካርያስ ጫፎቿ ሰባት በሆኑ መቅረዞች ላይ ሰባት መብራት ሲበራ እንዳየ ፡ የልዳ ሰማእት ቅዱስ ጊዮርጊስም ሰባት እመት በእሳት መሰቃየቱን ቅኔው ያስረዳል ።

ደግሞ በኢትዮጵያውያን ዘንድ አስር ቁጥር፡ ሰባት ቁጥርም በእብራውያን ዘንድ ፍፁም (መጨረሻ ፡ሙሉ) እንደሆነ፡ የጊዮርጊስ የሰባት አሙት ስቃይ መጨረሻው ሞት መሆኑን ባለቅኔው ይገልጣሉ ።

232 ሥላሴ

ሞተ ከመ አንስት
በስባረ ማሕረጽ አቤሜሌክ
ፍዳ ሞተት ቅድመ ለዘምሪ በኩናተ ሐራ ብእሲቱ ።
ተዋልጦ ገድል ኢናንክር ባሕቱ
ሞተ ሰይፈ ዕደው ተወክፈ ወልደ ጕልቈ አክራም ሠለስቱ
በሐሊብ ሞት እንዘ ድልወቱ ፤
ወእንዘ ወሬዛ ጎያል ከመ ሥርዐቱ
ለሚሣራ በሐሊብ ሞቱ ።

ት ር ጉ ም

በመጀመሪያ የዘምሪ
ሚስት በወታደር ጦር
ስለሞተች ብድራት አቤሜሌክ በወፍጮ ስባሪ እንደሴት
ሞተ ፤
ነገር ግን የገድል መለያየትን እንዳናደንቅ
በወተት መሞት ተገቢው ሲሆን የሰስት አመት ልጅ
የወንዶች ሰይፍ አሟሟትን ተቀበለ (ሞተ) ፤
እንደ ስርአቱም ብርቱ ጎረምሳ ሲሆን
የሲሳራ ሞቱ በወተት ሆነ ።

ም ስ ጢ ር

የዚህ የቅኔ ምስጢር ሰው በታሰበው ቀርቶ ባልታሰበ ምክን
ያት የሚሞት መሆኑን ከታሪክ ማስረጃ በማቅረብ ያስገነዝባል ።

ታ ሪ ክ

አቤሜሌክ የጌዴዎን ልጅ ነው ። አባቱ ጌዴዎን ከሞተ
በሁዋላ በሹመት ሽሚያ ሰባቱን ወንድሞቹን በግፍ ገደላቸውና የእግ
ዚአብሄርን ህግ አፈረሰ ። ጠላቶች ተነሱበትና በሴኬምና በቴቤስ

ሲዋጋ ያገሪቱ ሰዎች የሸሹበትን የቴቤስን ግንብ በእሳት ለማቃ
ጠል ወደቴቤስ ግንብ በቀረበ ጊዜ ፣ አንዲት ሴት የወፍጮ መጅ
በራሱ ላይ ጣለችበትና አናቱን ፈጠፈጠችው ። እርሱም ሲያጣጥር
ጋሻ ጃግሬውን ጠራና «ሴት ገደለችው እንዳይባል በሰይፍህ ውጋኝ»
አለው ። ጎልማሳውም ሰይፉን መዝዞ ወጋውና ሞተ (መሳ. 8፣
31 ፤ 9) ።

ዘምሪና ክስቢ በሳሙኤል ጦር ተወግተው ሙተዋል ። ምክን
ያቱም በደብተራ አሪት ሲዘሙቱ ስለተገኙ ነው (1 ነገስ.16 ፣ 9—
20) ። ናኦድ ከሞተ በሁዋላ እስራኤል አምላካቸውን በደሉና በኢያ
ቢስ እጅ ጣላቸው ፤ ሰራዊቱም አለቀ ። እስራኤል ወደ እግዚአ
ብሄር ጮሁ ። የእስራኤል ነቢይት ዲቦራ ባርቅን አስጠርታ አስነ
ሳችላቸውና ከርሱ ጋር ወደ ሲሳራ ዘመተች ። ባርቅም ገጠማቸውና
የኢያቢስ ሰራዊት አለቁ ፣ ጥቂቶችም ሸሹ ። ሲሳራም ሸሽቶ በሄ
ቤር ሚስት በኢያኤል ቤት ገብቶ ሳለ ለውሃ ጥሙ ማብረጃ ጫጌ
ሙሉ (ማለቢያ ሙሉ) አጓት ሰጠችው ፤ ያን ቸልሶ (ጨልጦ) ብር
ድ ብርድ አለውና ተኛ ። በዚያን ጊዜ ኢያኤል የድንኳን ካስማ
በጀሮው ቸከለችበት (ቀበቀበችበት) ፤ እርሱም ወዲያውኑ ሞተ
(መሳ. 4 ፣ 17—22 ፤ 9 ፣ 1—57 ፤ 4 ፣ 1—24) ።

233 ሥላሴ

ዘእንግዳ ዳንኤል (አለታ)

ገቦ ወልድ እንተ ገሠሠ
ውኅበ መቃብር እንተ ሮጸ
ትንሣኤ እግዚእነ አምኑ በሥጋ ። ነገረ ትንሣኤ ባሕቱ
ጊዜ ቶማስ ወተክለ አሚን እምተርፈ በከንቱ ፤
ኀበ መቃብር ኢይረድ በእግሩ ተክለ ሃይማኖት ዝንቱ
አምጣነ ሐንካስ በፍናቱ ፣
ወርግዘተ ገቦ ኢይግሥሥ በአጽባዕቱ ።
አጸብዕ ለቶማስ አልቦቱ ።

ት ር ጉ ም

የወልድን ጎን የዳሰሰውና
ወደ መቃብር የሮጠው
የጌታችንን መነሳት በስጋ አመኑ ። ነገር ግን የትንሳኤ
ነገር
በተከለ ሃይማኖትና በቶማስ ጊዜ በከንቱ በቀረ ነበር ፤
ይኸው ተክለ ሃይማኖት በእግሩ ወደመቃብሩ እንዳይሮጥ
በመንገዱ አንካሳ ነውና ፣
የጎን መወጋትንም በጣቶቹ እንዳይዳስስ
ለቶማስ ጣቶች የሉትምና ።

ም ስ ጢ ር

ባለቅኔው የተክለ ሃይማኖት አንዱ እግራቸው በመሰበሩና የቶ
ማስ እጅም በመቆረጡ መሮጥና መዳሰስ እንደማይሳኩላቸው በግ
ረጋገጥ ፣ ካልተሮጠና ካልተዳሰሰም ማመን እንደማይቻል በመግለጥ
ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

ታ ሪ ክ

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን መቃብር በተነሳ ጊዜ የቀሩት ሀዋ
ርያት ትንሳኤውን ሲያዩ ቶማስ ያን ጊዜ ባለመኖሩ ትንሳኤውን
አላየም ፤ ስለዚህም ጓደኞቹ ቢነግሩት « በጦር የተወጋውን ጎኑንና
በችንካር የተቸነከረውን እጁንና እግሩን ካላየሁ አላምንም » አላ
ቸው ። በዚህ ምክንያት ከሙታን የተነሳ ክርስቶስ ሀዋርያት በተሰ
በሰቡበት በዝግ ቤት እንደ አምላክነቱ ገብቶ « ሰላም ለሁላችሁ»
አላቸውና « ቶማስን ና ! አይተህ ተረዳ » አለው ። እርሱም
በጦር የተወጋውን ጎኑንና በችንካር የተቸነከረውን እጁን ዳስሶ
አምኗል ይባላል (ዮሀ.20 ፣ 26) ።

ዮሀንስና ጴጥሮስ ሴቶች የነገሯቸውን የክርስቶስን መነሳት
ለመረዳት ወደመቃብሩ ሲሮጡ ፣ ጴጥሮስን ዮሀንስ ቀደመው ።
ሆኖም ሁለቱም ትንሳኤውን አምነዋል (ዮሀ- 20 ፣ 3-7) ።

234 ሥላሴ

ሀለዉ ወኢሀለዉ
ክልኤቱ ዕፀው ነባብያን
ዘኢይቀድሞሙ ሥርው ወኢተድኅሩ እሙንቱ
እንዘ ፀአቶሙ ለእሉ እምዝንቱ ።
ወምስጢሮሙ ለሥርው ወለአዕጹቅ ክልኤቱ
እመ ሐታትያን የሐትቱ
ዕፀ-ብኪ ዕፀ-ብ ውእቱ ፤
ወካልእ ትርጓሜ አልቦቱ ።

ት ር ጉ ም

ስር የማይቀድማቸው
እነርሱም ወደሁዋላ ያላሉ
ሁለቱ ተናጋሪዎች እንጨቶች አሉ ? የሉም ?
የእነዚሁ አመጣጣቸው ከዚሁ ሲሆን ፤
የስርና የሁለቱን ጫፎች ምስጢርም
መርማሪዎች ቢመረምሩ
እፀ-ብ ድንቅ እኮ ነው ፤
ሌላም ትርጓሜ የለውም ።

ም ስ ጢ ር

በስር የተመሰለው ወላጅና አስራጊ የሆነው አብ ፣ በሁለቱ
እንጨቶች የተመሰሉ በባህርይ የወለደውን ወልድንና ያሰረፀውን
መንፈስ ቅዱስን በመኖር አይቀድማቸውም ፣ አይበልጣቸውም ።

እንዲሁም የስላሴ መኖር በምርምር እንደማይገኝና ነገራቸውም (ስለአብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የሚነገረው ነገር) በዕፁብ ድንቅ እንደሚወሰን በመግለጥ ባለቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር የስላሴን አለመታወቅ ያስረዳሉ ።

235 ሥላሴ

ዘዘዮሐንስ (አለቃ)

ሀብተ ፈውስ ጊዜ ተገብረ
እምረኪብ ኢኮነ ውሂበ ፈውስ ፤
ተክለ ሃይማኖት ዘጎየአ አሐደ እምአእጋሪሁ ክልኤቱ
እግረ አምጣነ ወሀበ እንዘ እግር አልቦቱ ።
እመሰ ውሂብ ለዙሉ እምረኪበ ክብር ውእቱ
የሀበነ ክንፈ ለሰብአ ቤቱ ፤
በረከተ አብ ወወልድ እስመ ድልወቱ
ጎበ ሐረ ከመ ንሑር ቦቱ ።

ትርጉም

የማዳን ሀብት በተደረገ ጊዜ
ማዳንን መስጠት ከማግኘት የተነሳ አይደለም ፤
ከሁለት እግሮቹ አንዱን ያጣ ተክለ ሃይማኖት
እግር ሳይኖረው እግርን ሰጥቷልና ።
ለሁሉ መስጠት ግን ክብር ከማግኘት የተነሳ ከሆነ
ለቤቱ ሰዎች ክንፍን ይስጠን ፤
የአብና የወልድ በረከት ተገቢው ነውና
ወደ ሄደበት እንሄድበት ዘንድ ።

ምስጢር

ተክለ ሃይማኖት ራሳቸው አንድ እግር ሲሆኑ እንካሶችን ማዳናቸው መስጠት በቸርነት እንጂ በማግኘት ብቻ እንዳይደለ ያስረዳል ።

ደግሞም ሀብታም ለሌለው መስጠት እንደሚገባው አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ባለስድስት ክንፍ ከሆኑ ፥ ለአገልጋዮቻቸው ፀጋ ቸውን ማደል ይችላሉ በማለት ባለቅኔው ተመኝተዋል ።

236 ዘይእዜ

ነገረ ደብረ ታቦር ድኅረ ጎልቀ
ወተፈጸመ እምአብ ለአማኑኤል ልደቱ ፥
ኤልያስ ግባእ በኢተድኅሮ
መንገለ ገነት ዘነበርከ ቦቱ ፤
ወእመ ሰሐበከ ለከ ለሙሴ ተዛውዖቱ
እስኩ ኢትሑር ለበዊአ ቤቱ ፤
እስመ ቤተ ሙሴ ርኁቅ ወመቃብረ ምድር ውእቱ ።
እስኩ ኢትሑር ለበዊአ ቤቱ ፤

ትርጉም

የደብረ ታቦር ነገር ካለቀና
የአማኑኤል ከአብ መወለዱም ከተፈፀመ በሁዋላ ፥
ኤልያስ ! ወደነበርህበት ገነት ወደሁዋላ ያለማለት ግባ ፤
አንተንም የሙሴ ጭዋታው ቢስብህ
እስቲ ወደ ቤቱ ለመግባት አትሂድ ፤
የሙሴ ቤት ሩቅ ነውና ፤ የምድርም መቃብር ነውና ።
እስቲ ወደቤቱ ለመግባት አትሂድ ፤

ምስጢር

ተሟጋች ሰው ነገሩን ሲፈፅም ወደቤቱ እንደሚገባ ፥ ክርስ ቶስ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን ከገለጠ በሁዋላ ነቢይ ኤልያስ ወደነበረበት ገነት መግባቱን ቅኔው ያመለክታል ።

እንዲሁም ባለንገር (ቀጠሮ ያለው ሰው) በመንገድ ወደሌላ ቤት ንራ ብሎ በጨዋታ እንደማይታለል ፡ ነቢይ ኤልያስ አለመሞቱንና አለመቀበሩን እንደመሲም አለመሆኑን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

237 ዘይእዜ

ዘተከሉ (መምህር ፡ ዘዋሽራ)

እፎኑመ አብ ለአርዳኢከ
ቀባዕኩሙ ስመ ዘመዐዛ ጸድቅ አልቦቱ?
አኮኑ ያዕቆብ ወዮሐንስ
እለ ጸውዖሙ ለክብካብ ልደቱ
ቃለ ነጐድጓድከ ፈርሁ ደቂቀ ነጐድጓድ እንዘ እሙንቱ ።
መነገረ ፍርሃት ኢይቄም በስምዐ ክልኤቱ
ተዐቅፈ ጴጥሮስ እንዘ ዕቅፍተ እግር ውእቱ ።
መነገረ ፍርሃት ኢይቄም በስምዐ ክልኤቱ

ት ር ጉ ም

አባት!ተማሮችን የእውነት
ሽታ የሌለበት ስምን እንዴት ቀባኻቸው?
ለሰርግ ልደቱ
የጠራቸው ዮሀንስና ያእቆብ
እነርሱ የነጎድጓድ ልጆች ሲሆኑ የነጎድጓድህ ቃልን ፈር ተዋልና ።
የፍርሃት ነገርም በሁለቱ ምስክርነት እንዳይፀና
ጴጥሮስ የእግር እንቅፋት ሲሆን (እርሱ) ተደናቀፈ ።
የፍርሃት ነገርም በሁለቱ ምስክርነት እንዳይፀና

ም ስ ጢ ር

«አያወዛው ተቀብቶ» እንዲሉ እግዚአብሄር ሀዋርያትን (ያእቆብና ዮሀንስን) የነጎድጓድ ልጆች ማለቱ ተግባራዊ አልሆነም ። ምክንያቱም በደብረታቦር ከደመና በሰሙት ድምፅ መውደቃቸው የነጎድጓድ ልጆች ባይሆኑ ነው እንጂ የነጎድጓድ ልጆች ቢሆኑ ኖሮማ እንኳን መውደቅ ድንጋጤም ባልተሰማቸው ነበር ይላሉ ባለቅኔው ።

238 መወድስ

ኢይበቍዖ ለሰብእ ንብረተ ሀገሩ፡
ለዘብሔሮ ጎደገ ዮሴፍ ባሕቲቱ
እስመ እኰነኖ ንጉሥ መልዕልተ ኵሉ ጥራቱ ።
ይኄይሶ እንከ ብሔረ ባዕድ
ንሕነ ደቂቀ ሐተታ ኢንበል ባሕቱ ፤
እስመ አንገሥዎ ሰብአ ቤቱ
ለንጉሥ ሰሎሞን ዘኢይሰዐር መንግሥቱ ።
ነቢርሰ በበሀገሩ ኢያደልዎ በከንቱ ፡
ናቡቴ እስመ ተቀትለ በዐጸደ ወይን ወላዲቱ።
ወእመ በጥበብ ጐየ ውስተ ሰማያት ሰብዐቱ
ኤልያስ ምስለ ዕዝራ ይነብር በሕይወቱ ።

ት ር ጉ ም

ያገሩ ኑሮ ሰውን አይጠቅመውም፤
አገሩን የለቀቀ ብቸኛ ዮሴፍን
ንጉስ በንብረቱ ሁሉ ላይ ሾሞታልና ።
እኛ የምርምር ልጆች ግን
እንግዲያስ የባእድ አገር ይሻላል እንበል ፤
መንግስቱ የማይሻር
ሰሎሞን ንጉስን ቤተሰቦቹ አንግሰውታልና ።

በያገሩ መቀመጥ ግን በከንቱ አይገባም፤
በእናቱ የወይን ቦታ ናቡቴ ተገድሏልና፥
ወደሰባቱ ሰማዮችም በጥበብ በሸሸ ጊዜ
ኤልያስ ከእዝራ ጋር በሀይወት ይኖራልና።

ም ስ ጢ ር

«ነቢይ በአገሩ አይከብርም »ከተባለው አንፃር ባገር መኖር ለሁሉም ስለማይጠቅም፡«የሰው አገሩ ምግባሩ» በተባለው መሰረት በአገር ከመኖር ይልቅ በባእድ አገር መኖር መልካም መሆኑን ባለ ቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር አረጋግጠዋል ።

ታ ሪ ክ

ናቡቴ ጥሩ የወይን ቦታ ነበረው ። የእስራኤል ንጉስ አክአብ የናቡቴን የወይን ቦታ ወደደ።በሌላ የወይን ቦታም እንዲለውጠው አክአብ ናቡቴን ጠየቀ ። ናቡቴ የወይን ቦታውን ለመለወጥ ፈቃደኛ አልሆነም ። በዚህም ምክንያት የንጉሱ የአክአብ ሚስት አስገደለች ውና አክአብ የናቡቴን የወይን ቦታ ወረሰ (1 ነገስ.20፡17) ።

239 መወድስ

ዘተከለጽዮን (አለቃ)

ዳዊት ሐሰወ ትንቢተ ዳዊት ፤
አምጣነ ዕፄ ተስምየ ዕፄ እንዘ አልቦቱ ።
ገብረ ክርስቶስ ይፈጽም ትንቢተ ዳዊት ባሕቱ
ውእቱ ዕፄ ወሥጋ ውእቱ ፤
ወኤፈርሀ ድኅረ ሞቱ
እምነ ዕፄ ወነድ ፤ አምጣነ በዙሉ ሕይወቱ
ዕፄሁ ዘኢይነውም ወኢይጠፍእ እሳቱ

ነፍሳተ እልዓዛር ሕማማት ጠፈረ ሥጋሁ እስከ ነሡቱ ።
ወእመ ጎደጋ በነውር ለተድላ ዓለም ብእሲቱ
መጽሐፈ ሕማማት ጎዳጋቲሃ ጸሐፈ በእጽባዕቱ ።

ት ር ጉ ም

ዳዊት የዳዊት ትንቢትን ዋሸ፤
ትል ሳይኖረው ትል ተብሏልና ።
ገብረ ክርስቶስ ግን የዳዊት ትንቢትን ይፈፅም ዘንድ
ስጋ ሲሆን ትል ሆነ ፤
ከሞቱም በሁዋላ ከትልና
ከእሳት አልፈራም ፤ በህይወቱ ሁሉ
ትሉ አይተኛምና ፤ እሳቱ አይጠፋምና
ነፍሶች/የአልአዛር ህመሞች የስጋ ጣራውን እስካፈረሱ
ድረስ ።
የአለም ደስታ ሚስቱንም በነውር በፈታት ጊዜ
የህማሞች ፍቾች መፅሀፍን በጣቱ ፃፈ ።

ም ስ ጢ ር

ዳዊት «እኔ ትል ነኝ» ያለው በርሱ ሳይፀድቅ « ትል ነኝ » ያላ ለው ገብረ ክርስቶስ ትል ሆነ ። በዚያውም ላይ ከሞት በሁዋላ አለ የሚባለውን ገሃነመ እሳትን እንዳይፈራ ትሉ የማያንቀላፋና እሳቱ የማይጠፋ ገሃነመ እሳትን አካሉ ሆነ ። ነፍሶችም ጣሪያን እንደሚ ያፈርሱት ህማሞችም የገብረ ክርስቶስን ስጋ አፈራረሱት ። በተ ጨማሪም ባል ሚስቱን በነውር ፈትቶ የፍችዋን ፅሁፍ እንደሚሰጣት ፣ ገብረ ክርስቶስም የዚህ አለምን ምኞት ትቶ የስቃይ እንግልትን መረጠ በማለት ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

240 መወድስ

ዘተከለ ጽዮን (አለቃ)

ሞተ ዘካርያስ አብ በአፍቅሮ ወልዱ
ወሞተ የዋህ አቤል በአፍቅሮ ብእሲት ከንቱ ፤
አፍቅሮ ብእሲት ወወልድ እስመ ቅታሌ ነፍስ ውእቱ ።
በይነ ምንት ዳዕሙ ለዮሐንስ ሞቱ?
በገዳም እንዘ አልቦቱ
ብእሲት ወወልድ እስመ ውስተ ገዳም ንብረቱ ።
ወልድሰ ወብእሲት እመ ይትረከቡ ሎቱ
እምድኅነ ከመ ሙሴ ወከመ ዳዊት በእሎንቱ፤
አፍቅሮተ ብእሲት ወወልድ ከመ ኢንእመን ባሕቱ
ሞተ ሰናክሬም በውሉዱ ወሀጕለ ሶምሶን በብእሲቱ ።

ት ር ጉ ም

የአባት ዘካርያስ ሞት ልጅን በመውደድ ነው ፣
የየዋህ አቤል ሞትም ከንቱ ሴትን በመውደድ ነው ፤
ሴትንና ልጅን መውደድ ነፍስን ገዳይ ነውና ።
የዮሀንስ ሞት ግን በምን ምክንያት ነው ?
ሴትና ልጅ
በዱር ሳይኖሩት ኑሮው በዱር ውስጥ ነውና ።
ሚስትና ልጅስ ቢገኙለት ኖሮ
እንደ ዳዊትና እንደሙሴ በነዚሁ በዳነ ነበር ፤
ሴትና ልጅን መውደድን እንዳናምን ግን
የሰናክሬም ሞት በልጆቹ ነው ፣ የሶምሶንም ጥፋት (ሞት)
በሚስቱ ነው ።

ም ስ ጢ ር

ይህ ቅኔ ሴትና ልጅ አስገዳይም አዳኝም መሆናቸውን ከገለጠ በሁዋላ ፣ በተለይ በሴትና በልጅ አማካይነት የሚመጣውን መዘዝ አደ ገኛነት በምሳሌ ያስገነዝባል።

ታ ሪ ክ

ሰናክሬም የይሁዳ ንጉስ ሀዝቅያስን ለመውጋት በዘመተ ጊዜ ፣ የሀ ዝቅያስ ረዳት መልአክ ሰራዊቱን በሰፈሩበት ቦታ ፈጅቶበት ወደ አገሩ ከተመለሰ በሁዋላ ሁለቱ ልጆቹ ሶርሶርና አድራሜሌክ በጣኦት ቤት ሲሰግድ የገደሉት የአሶር ንጉስ ነው ።

ሶምሶን ከሳሙኤል በስተቀር መሳፍንት ከተባሉት የእስራኤል አዳኞችና ፈራጆች የመጨረሻው ነበረ ። አባቱ የዳን ነገድ ስሙ ማኑሄ ነበረ፤ እናቱ መካን ነበረች ። ልጃቸው ሶምሶን ከልደቱ ጀምሮ ከሚያሰክር መጠጥ ፣ ጠጉሩን ከመቆረጥና ሬሳም ከመንካት የተከለ ከለ ናዝራዊ ነበረ ።

በዘመኑ ፍልስጥኤማውያን አጎዳንዶቹን የእስራኤል ከተሞች ወስደው ይመኩባቸው ጀመር። እስራኤላውያን ግን ሊዋጓቸው አል ደፈሩም ። ከዚህም የተነሳ ሶምሶን በተሰጠው ልዩ ብርታትና ሃይል ይቃወማቸው ነበር እንጂ እንደ ሌሎቹ የእስራኤል መሪዎች ሰራ ዊት ሰብስቦ አልተዋጋም ። አስቀድሞ በፍልስጥኤማውያን ላይ የጠብ መነሻ ምክንያትን በመፈለግ እንዲት ፍልስጥኤማዊት ሴት አገባ ። በእርሷም ምክንያት በተጣሉ ጊዜ አዝመራቸውን አቃጠለ ብዙ ፍልስጥኤማውያንንም ገደለ ። ወገኖቹ የይሁዳ ሰዎች ፍልስጥኤማው ያንን ፈርተው አሳልፈው ሊሰጡት ተስማሙ ። ሶምሶን ግን በአሀያ መንጋጋ ከጠላቶቹ አንድ ሽህ ሰው ገደለ። ለ20 አመት ያህል የእ ስራኤልን ህዝብ አስተዳደረ ።

አንድ ጊዜ ጠላቶቹ በጋዛ ከተማ ሊይዙት ሲጠባበቁት የከተ ማይቱን በር መዝጊያ ነቅሎ አመለጠ ። ነገር ግን በመጨረሻው ራሱን ካለመግዛቱ የተነሳ ደሊላ የተባለች ሴት ናዝራዊነቱን እስኪ

ገልጥሳት ድረስ ከነዘንዘቸው በሁዋላ ለፍልስጥኤማውያን አሳልፋ ሰጠ
ችው ። እነርሱም አይኑን አሳውረው በጋዛ አሰሩት ። አምላካቸው
ዳጎንን ሊያመሰግኑ በተሰበሰቡ ጊዜ ሶምሶንን አስመጥተው ተዘባበ
ቱበት ። እርሱም «ነፍስየ ትሣእ ምስለ ኤሎፍላውያን (ነፍሴ ከኢሎ
ፍላውያን ጋር ትውጣ)»በማለት የቤቱን ምሰሶዎች ገፋ ። ቤቱ ሲወ
ድቅ በውስጡ የነበሩት መኳንንትና ከፍልስጥኤማውያን አያሌ ሽህ
ሰዎች ተገደሉ ፤ ሶምሶንም አብሯቸው ሞተ(መሳ. 13 ፡ 14 ፡ 15 ፡ 16)።

241 መወድስ

ዘአፈወርቅ ዘውዴ (አለቃ)

እመቦ ሐይው እምድኅረ ተከፍሎ
ከመ ጊዮርጊስ በሰይፍ ዘተከፍለ ለዐሠርቱ
ዙሉ ባዕል በጐልቄ ቤቱ ወርስቱ
እምተከፍለ በፈቃዱ
ይንበሩ ክፍላተ አካሉ በርስቱ ወቤቱ፤
አስመ እንዘ መሬት ለሐራሲሁ፤
ወእንዘ ለመንግሥት አብያት ብእሲ ወብእሲቱ
ዘእንበለ ጸብእ ተፋለጡ መንገለ መካናት ክልኤቱ ።
ወበጽሐ በባዕል ለረድእ ፍኖተ መሐደምቱ ፤
አስመ ረድእ ፍኖት ዘርእየ ተዝካረ ላዕሉ ወታሕቱ
ፈቀደ ኀበ ክልኤ ይትከፈል በፍኖቱ ።

ት ር ጉ ም

በሰይፍ ለአስር እንደተከፈለ
እንደ ጊዮርጊስ ከመከፈል በሁዋላ በሀይወት መኖር ቢኖር
ባለፀጋ ሁሉ በቤቱና በርስቱ ቁጥር
በፈቃዱ በተከፈለ ነበር
የአካሉ ክፋዮች በርስቱና በቤቱ ይኖሩ ዘንድ፤
መሬት ለአራሹ ሲባልና

ቤቶች ለመንግስት ሲባሉ ፣ ባልና ሚስቱ
ያለጠብ ወደሁለት ቦታ ተለያይተዋልና ።
የመንገድ ተማሪ ተረትም በባለፀጋ ደረሰ፤
የላይና የታች ተዝካርን ያየ የመንገድ ተማሪ
በመንገዱ ወደሁለት ቦታዎች ሊከፈል ወዷልና ።

ም ስ ጢ ር

ቅዱስ ጊዮርጊስ በሰይፍ ስለት ለአስር ከተከፈለ በሁዋላ ሀያው
ሰው ሆኖ ክርስቶስን ለአህዛብ ሊሰብክ ቻለ እንደሚባል ፣ የዘመናችን
ባለፀጎች ከአካላቸው መከፈል በሁዋላ በሀይወት መኖር ቢቻላቸው
በመሬት ለአራሹና ትርፍ ቤቶችን ለመንግስት ባደረገው አዋጅ ጊዜ
አካላቸውን በገዛ እጆቻቸው በመቆራረጥ በርስታቸውና በቤቶቻቸው
ቁጥር ለማከፋፈል በሞከሩ ነበር ይላሉ ባለቅኔው ። በዚያን ጊዜ ሀብ
ታሞች ሁሉ እንደገበታ ውሃ ከመዋለላቸው የተነሳ ባልና ሚስቱ በው
ስጠ ስምምነት ተፋቱ። ወንዱ በአንድ ቤትና ቦታ ፣ ቤቲቱ በሌላው
ቤትና ቦታ የሚኖሩ ሆኑ ። በዚህም ምክንያት ሳይፋቱ በተፋቱት ባልና
ሚስት በሁለት በተለያዩ ስፍራዎች ድል ያለ ተዝካር መኖሩን ያወቀ
መንገደኛ ተማሪ የሁሉንም ቦታ ተዝካር መብላት እንዲችል «ምነው
ዛሬስ ሁለት ሰው በሆንሁ » አለ የሚባለው ተረት ተፈፀመባቸው
ይላሉ ባለቅኔው።

242 ዕዝል ክብር ይእቲ

ዘወልደ ሥላሴ (አለቃ)

ውስተ ቤተ መቅደስ ትፈትል ሜላተ ወርቅ ዘእምላዕለ
አይሁድ እንመቱ
ወለተ እስራኤል ተሠይጦ እንተ ለዮሴፍ ፍኅርቱ ፤
አስመ ልብሰ ሞትከ ኅልቀ እምነ ትንሣኤ ርፍአቱ
ዓለመ እሳት ቀኖተ ዘአኀዝከ በአእዳዊከ ክልኤቱ !

ት ር ጉ ም

የእሳት አለም ችንካርን በሁለት እጅችህ የያዝህ (ክርስቶስ)!
ለዮሴፍ እፎኛ የሆነች የእስራኤል ልጅ መሸጥ ስራው
ከአይሁድ በላይ
የሆነ የወርቅ ግምጃን በቤተ መቅደስ ውስጥ ትፈትላለች፤
ከመነሳት ስፈቱ ጀምሮ ልብስህ ሞት አልቋልና ።

ም ስ ጢ ር

ቅድስት ማርያም በቤተ መቅደስ ወርቅንና ሀርን ፈተለች እን ደሚባል የክርስቶስም መሸጥ በወርቅ መሆኑን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ። እንዲሁም የሀሩ ስራ ከላይ መሆኑ የመሸጡም ነገር በአ ይሁድ መፈፀሙን ያሳያል ። ቅድስት ማርያምም የዮሴፍ እፎኛ እን ደተባለች የክርስቶስ በወርቅ መሸጥ ከእርሱ በፊት በያእቆብ ልጅ ፣ በዮሴፍም መፈፀሙን ቅኔው ያስረዳል ።

ልብስም ከስፈቱ እንደሚያልቅ ክርስቶስ ከመቃብር በመነሳቱ ሞት ጠፋ ። አለምንም በመሀል እጁ እንደያዘ የአለም ምሳሌ በሆነ በብረት ችንካር መሀል እጁን ተቸንከረ በማለት ባለቅኔው አመስጥ ረዋል ።

243 ዕዝል ክብር ይእቲ

ዘተክለ ጽዮን (አለቃ)

በአፍቅሮ ብእሲት ወወይን ሞተ ናቡቴ ወለኦርዮ ቅትለቱ
ሞተ ወልድሰ የዋህ እንበለ ክልኤሆን በከንቱ ።
እንበለ ከልኤሆን ሞተ ከመ ኢንበል ባሕቱ
ቤተ እስራኤል ጎሩይ ዐጸደ ወይኑ ወቤተ ክርስቲያን መር ዓቱ ።

ት ር ጉ ም

የናቡቴ ሞት ወይንን በመውደድ ነው የኦርዮ ሞት ደግሞ
ሴትን በመውደድ ነው ፤
የየዋህ ወልድ ሞት ግን ያለ ሁለቱ እንዲያው በከንቱ ነው ።
ነገር ግን ያለሁለቱ ሞተ እንዳንል
የተመረጠ የእስራኤል ወገን የወይኑ ቦታ ነው ቤተ ክር ስቲያንም ሙሽራው ናት ።

ም ስ ጢ ር

የኦርዮ ሞት በሚስቱ በቤርሳቤህ ምክንያት ነው ፤ የናቡቴም ሞት በወይኑ ቦታ ፍቅር ነው ። የክርስቶስ ሞት ግን በአዲስ ኪዳን እርሱን በባለወይንና በወንድ ሙሽራ ሲመስል ፣ በወይን ቦታና በሴት ሙሽራ ለሚመስላቸው ለእስራኤልና ለቤተ ክርስቲያን መሆኑን ባለ ቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

244 ዋዜማ

በዘመነ ወንጌል ዓለመ ፍዳ
ብዙኃን ሕዝብ አግብርቱ ዘእኩ መዋቲ
በወርቅ መርዓተ ይሁዳ ተባእሱ ባቲ ፤
እምነ ካልኣት እንስት አምጣነ ወላድ ይእቲ
ጽዋዐ ሕይወተ እስከነ ታሰቲ
ውስተ ቤቱ ለብእሲ ሐታቲ ።

ት ር ጉ ም

በመከራ አለም/ ወንጌል ዘመን
ሚች ያይደለ የጌታ አነልጋዮች /ህዝቦች
በይሁዳ ሙሽራ/ወርቅ ተጣሉባት ፤

ከሴሎች ሴቶች ይልቅ ወላድ ናቅሩ ፡
በቶመራማሪ ሰው ቤት ውስጥ
መጠጥዋ ህይወትን እስክታጠጣ ።

ም ስ ጢ ር

ወላድ የሆነች መልከ መልካም ሰትን ለማግባት ብዙዎች እን ደሚሻሙባት የክርስቶስ አገልጋዮች በወርቅ ትርፍ ተመሰገኑ ፡ መብ ልና መጠጥ በሴቲቱ እጅ እንደሚዘጋጅ ዕድቅም በወርቅ ትርፍ እንደታወቀ ባለቅኔው አመስጥረዋል።

245 ዕዝል ጉባኤ ቃና

እመቤ በሰዶም ተክለ አልፋ እሞተ ነዳጁ እሳት
በምንት እምድኅነ? አኮኑ በዓለ ክልኤ ገጻት ።

ት ር ጉ ም

ተክለ አልፋ በሰዶም ቢኖር ከነዳጅ እሳት ሞት
በምን በዳነ ነበር ? ባለሁለት ፊት ነውና ።

ም ስ ጢ ር

የሰዶምን ጥፋት ወደሁዋላ ዞሮ ማየት አጥፊ ከሆነ ፡ በፊታቸውም በሁዋላቸውም አይኖች ነበሩዋቸው የሚባል ዓይቅ ተክለ አልፋ በሰ ዶም ጥፋት ጊዜ ቢኖሩ እንደሎጥ ሚስት መሆን ያገኛቸው እንደነበር በመግለጥ በቅኔው ተመስጥሯል ።

246 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ዘከፍለ ዮሐንስ

ዮም ዕለተ ብዙኅ ትፍሥሕት ፡
እስመ በደብረ ታቦር ቆመ ፈጣሪ ወበደብረ ብርሃን ዳዊት።

ት ር ጉ ም

ዛሬ የብዙ ደስታ ቀን ነው ፤
ፈጣሪ በደብረ ታቦር ቆሟልና ፡ በደብረ ብርሃንም ዳዊት (ቋሟልና) ።

ም ስ ጢ ር

ባለቅኔው የጎንደር ንጉስ አፄ ዳዊት ያሰሩት ደብረ ብርሃንንና ክርስቶስ አምላክነቱን ገለጠበት የሚባለውን ደብረ ታቦርን በማነ ፃፀር ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

247 ዋዜማ

ናጽድቅ ዜና ሕሳዊ
ለእርባዕቱ ኪሩቤል ይደልዎሙ ፍርሃት ፤
በሰማይ ኦኮኑ ተአዘዘ ሞት።
ወሕሰወ ኮነ ፍትሐ ጎያሳን ነገሥት ፤
ዘእሰረ ጴጥሮስ ሲቀ ካህናት
እስመ ፈትሐ ካልኤ ዕርገት ።

ት ር ጉ ም

ያሰት ወሬን እናፀድቅ ዘንድ
ለአራቱ ኪሩቤል ፍራት ይገባቸዋል፤
ሞት በሰማይ ታዟልና ።
የሃይለኞች ነገስታት ፍርድም አሰት ሆነ፤
የካህናት አለቃ ጴጥሮስ ያሰረውን
ሌላው ካህን/ እርገት ፈቷልና ።

መልአክን ሞት አያስፈራውም ማለት ውሸት ነው። ይህን እንደ ውነት አድርገው በሰማይ ሞት ታዘዘ በማለት ፥ ሰማይ በትባለች በቅድስት ማርያም ሞት ስለተፈረደባት በሰማይ ያሉትን መላእክ ትንም ሞት እንደሚያስጋቸው ባለቅኔው አመልክተዋል ።

በተጨማሪም ሀዋርያት በመንፈሳዊ ስልጣን «ያሰሩት በሰማ ይም የታሰረ ይሆናል» ማለት አሰት መሆኑን ቅዱስ ጴጥሮስ ያሰ ረው (የገነዘው) የቅድስት ማርያም ስጋ መግነዙን ፈትቶ ወደ ሰማይ ወጣ በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

248 ዋዜማ

ዘገብረ ማርያም (ቁሰ ገበዝ)

ዐባይ ወረሓብ
አካለ ቴዎድሮስ ባሕር ፤ ወለሥጎ ሥቃይ ፍጥረት
ዘይትሐወስ ህየ አልቦቱ መሥፈርት ።
ወእንዘ እሳቱ ይነድድ ምስለ በረዱ ቀኖት
በእቶን እሳት ዘወድቀ ቴዎድሮስ ናእት
አጽገቦሙ ለጎምሳ ወምእት ።

ት ር ጉ ም

የቴዎድሮስ አካል/ ባህር
ታላቅና ሰፊ ናት ፤ በዚያ የሚንቀሳቀስ
የፍጥረት አይነትም ስፍር ቁጥር የለውም ።
ከበረዶ/ ችንካርም ጋር እሳቱ ሲነድ
በእሳት ምጣድ ላይ የወደቀ ቴዎድሮስ/ ዳቦ
መቶ አምሳውን (ሰዎች) አጠገባቸው ።

ትልቅና ሰፊ በሆነች ባህር ውስጥ ብዙ ተንቀሳቃሾች እንዳሉ በሰማእት ቴዎድሮስ አካል የተደረገው ስቃይ ብዙ መሆኑን ቅኔው ይገልጣል ። ከዚህም ሌላ ነቢይ ሙሴ እሳቱ ከበረዶው ጋር ሲነድ እንዳየ ቴዎድሮስ በእሳትና በችንካር ስቃይ መቀበሉን ያሳያል ። በተጨማሪም ቂጣ (ርሚጠ) በእሳት እንደሚጣልና ብዙ ሰዎችን እን ደሚያጠግብ በእሳት የተሰቃየው ቴዎድሮስ በመቶ ሃምሳ ችንካ ሮች ተቸንከረ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

249 ሥላሴ

ዘሲናዳ (ጴሐፈ ትእዛዝ ፥ ዘጉንደር)

ሩፋኤል በቤትከ
ጎብስተ ርኑባን እመ በላዕከ
ኢተረክበ ጎይል ዘይቤ እምአብያጺከ ጎይላት
ሐሜት ዝንቱ ወዝንቱ ጎፍረት ፤
እመሰ ላዕሌከ ኢሀሎ በዘከመዝ ሐሜት
አንጻረ በካፋ በኵረ ነገሥት
ድግምኬ በሊዐ ጎብስት
ውስተ ዛቲ ቤትከ እምርት ።

ት ር ጉ ም

ሩፋኤል በቤትህ
የራብተኞች እንጀራን በበላህ ጊዜ
«ይህ አሜት ነው ይህም ሀፍረት ነው » የሚል
ሀይል ከጓደኞችህ መላእክት አልተገኘም ።
እንደዚህ ያለ አሜት በአንተ ላይ ከሌለ ግን
በነገስታት አለቃ በበካፋ አንፃር (ፊት)
በዚያችው በታወቀች ቤትህ ውስጥ
እንጀራ መብላትን ድገማ ።

ም ስ ጢ ር

አይነ ስውር የነበረ ጦቢትን ሩፋኤል የተባለው መልአክ በሰው አምሳል መርዳቱን አስታውሰው ፥ እንደዚሁም በጎንደር ከተማ ሩፋኤል አዬ በካፋን የሚረዳቸው መሆኑን ባለቅኔው አመስ ጥረዋል ።

ታ ሪ ክ

መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ጦቢትን በሰው አምሳል እየረዳው ሰባት አመት ኑሯል ። ይኸው ጦቢት የሞተ ሰው ሳያስቀብር እህልና ውሃ አይቀምስም ነበር ። አንድ ቀን በግንብ ተጠግቶ ሙት ሲያስቀ ብር አንዲት ወፍ በአይኑ ውስጥ ኮሰችበትና በዚህ የተነሳ አይኑ ጠፋ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል የአሳ አሞት አይኑን ቀብቶ አዳነው ይባላል ። በዚሁ መልአክ ስምም በጎንደር ከተማ የተሰራች ቤተ ክርስቲያን አለች ። «ዛቲ ቤትክ» የተባለችው በጎንደር ከተማ ያለ ችው ይችው የሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ናት (ስንክ.ጳጉሜ 3 ቀን) ።

250 ሥላሴ

ዘሐይመት (ወይዘሮ)

ለወድሶትክ
ናሁ አብጸሕኩ ዐቅመ ውርዛዌ
እንዘ ብእሲት እነ እምጎይለ ውርዛዌ ድክምት
ዳዊት ጸዋሚ እመርገም ጎብስት ፤
ለዳዊትኒ አቡክ ነጋሢ መሠረተ ዅሉ መንግሥት
በፈለገ ዔላ ፈለገ ቅስት
አመ ተወርዘወ ቅድመ በወሬዛ ጌት
ወደሳሁ ከማየ አንስት ።

ት ር ጉ ም

ከመርገም /እንጀራ
ፁዋሚ ዳዊት ! ከጉርምስና / ሃይል
የደከምሁ እኔ ሴት ስሆን እንተን ለማመስገን
እነሆ የጉልምስናን ልክ (አካለ መጠን) አደረስሁ ፤
የመንግስት ሁሉ መሰረት የሆነ ነጋሽ አባትህ ዳዊትንም
የክርክር ወንዝ በሆነ በኤላ ወንዝ
ቀድሞ በጌት ጎልማሳ ባየለ ጊዜ
እንደእኔ ሴቶች አመሰገኑት ።

ም ስ ጢ ር

ትንሽቱ ስታድግ አካለ መጠን እንደምታደርስ ፥ ወይዘሮ ሀይ መት የጎንደር ንጉስ ዳዊትን ለማመስገን የቅኔ ችሎታ ማግኘታቸው ንና ፁዋሚም ሰው ከመብል ተከልክሎ እንደሚውል ፤ አዬ ዳዊት ከህ ዝብ ርግማን የራቀ መሆኑን ዳዊት ጎልያድን ገድሎ በተመለሰ ጊዜ «ዳዊት እልፍ ገዳይ ሳአል ሺህ ገዳይ» እያሉ የእስራኤል ንጉስ ዳዊ ትን በአመሰገኑት ሴቶች አንፃር ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

251 ሥላሴ

ዘጉሹ አራት ዐይና

ኢያድጎነ ንዴተ ሥጋ
ተዋሕዶተ ቃል ምስለ ሥጋነ
አመ ሐተትነ በልብ እንበለ ማኅየዊ ቅብዐት ፥
ወኢይኩን በዐውደ ሮምያ በይነገ ሁከት ፥
ይክልኑ በእግር ተሐውሶ ኅበ ፍኖተ ላዕል ወታሕት
ነፍስ ዘአልቦ ሥጋ ምውት ?
ወጽልመተኑ ያሴስል እምዐይን ማኅቶት
ዘላዕሌሁ ኢሀለወ ዘይት ?

ትርጉም

በልብ በመረመርን ጊዜ
ያለአዳኝ ቅብአት ከስጋችን ጋር
የቃል መዋሃድ የስጋችንን ችግር አላደነም ፤
ስለዚህም በሮምያ አደባባይ ሁክት (ብጥብጥ) እንዳይሆን ፤
ነፍስ የሌለው የሙት ስጋ ወደላይና ወደታች መንገድ
በእግር መንቀሳቀስ ይችላልን ?
በላዩ ላይ ዘይት የሌለበት መብራትስ
ጨለማን ከአይን ያስወግዳልን ?

ምስጢር

በስጋ የተሰራ ወጥ ያለቅቤ እንደማይጥም የእግዚአብሄር ቃል ከስጋችን ጋር መዋሀዱ መንፈስ ቅዱስን ያለመቀበል አይከብርም ይላሉ ባለቅኔው ። ከዚህም በተጨማሪ ነፍስ የሌለው በድን (ሬሳ) እንደማይንቀሳቀስና የዘይት ቅባት የሌለው መብራት ጨለማን እንደ ማያርቅ ፤ መንፈስ ቅዱስን ያለመቀበል ክብር የለም በማለት ባለቅኔው «ወልድ በቅብዐተ መንፈስ ቅዱስ ከበረ » እያሉ የሚሰብኩትን እምነታቸውን በቅኔያቸው ምስጢር አብራርተዋል ።

252 ሥላሴ

ቀድሐ በላኤ ሰብእ
ማየ ነዳያን በእደዉ
ድኅረ ኀልቀ ሰብእ መብልዉ ለኀፅበተ ጌጋይ ርስሐት
እንዘ ይብል «እምድኅረ በሊዕ ይደሉ ኀፅበት»
ዘይቀድሕ ማየ ብእሲ እመ አልቦቱ በቤት ።
ወትቤ ድንግል በጽላሎት
ኀዳጥ ማይ ቃለ መጻሕፍት ፤
ይበቍዖ ለጻድቅ መድሎት ።

ትርጉም

በላኤ ሰብእ ሰው / ምግቡ
ካለቀ በሁዋላ በደል/እድፍን
ለመታጠብ የችግረኞች ውሃን በእጁ ቀዳ ፤
«ከመብል በሁዋላ መታጠብ ይገባል» እያለ
ውሃ የሚቀዳ ሰው ከቤት ባይኖረው ።
ድንግልም በጥላ አለች
ጥቂት የመፃህፍት ቃል / ውሃ
ለፃድቅ / ሚዛን ይበቃዋል (አለች) ።

ምስጢር

በላተኛ በልቶ ካበቃ በሁዋላ እጁን በውሃ እንደሚታጠብ ፤ በላኤ ሰብእ ሰባ ስምንት ሰው በልቶ እፍኝ ውሃን ለአንድ በኽለተኛ በማጠቱ ምክንያት ሀጢአቱ ተሰረየለት ይላሉ ባለቅኔው ። በተጨማሪም ለብልሀ ጥቂት ምክር እንደሚበቃው የሰባ ስምንት ሰዎችን ነፍሳት ሚዛን እፍኝ ውሃ መዘነው በማለት ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

253 መወድስ

በእግረ ሰሎሞን ፍትሕ እመ ተለዐልን
ደብረ ሐተታ ነጊረ ነገረ ዘሉቃስ መጻሕፍት
ተሰምዮተ ሉቃስ ላሕም እምኢደለዎ እምጥንት
እንዘቦ በውስተ ልዳ
በዓለ ሐሊብ ጊዮርጊስ ሰማዕት ።
ወለጊዮርጊስ እምኢደለዎ
አውርዶተ ሐሊብ ጽዋዕ እምነ ክሣዱ አረፍት
ሣዕረ ከመ እንስሳ ዘተሴሰየ በቤት
ማትያስ እንዘ ሀሎ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ።
ባሕቱ በለዐ ሣዕር ለሰማዕተ ልዳ ድልወት ፤
በከርሠ እንስሳት እስመ ተረክበ አመ ኀሠሥዎ መንክራት።

ት ር ጉ ም

የሉቃስ መዕሀፍች ነገርን መናገር /
የምርምር ተራራን በሰሎሞን እግር / ፍርድ ብንወጣ
የሉቃስ ላም መባል ከጥንት ባልተገባው ነበር ፡
ባለወተት ሰማእት
ጊዮርጊስ በልዳ ውስጥ እያለ ።
ከአንገቱ / ግድግዳ ወተት /
ዕዋን ማውረድም ለጊዮርጊስ ባልተገባው ነበር ፡
ሳርንም እንደ እንስሳ በቤት የበላ
ማትያስ በሰማያዊት ኢየሩሳሌም እያለ ።
ነገር ግን ሳርን መብላት ለልዳ ሰማእት ተገቢ ነው ፡
ታምራቶች በፈለጉት ጊዜ በእንስሳት ሆድ ተገኝቷልና ።

ም ስ ጢ ር

ሉቃስ ገፀ ላህም (ላም ፊት) ሲባል ያልሰጠውን ወተት በላም ስም ያልተጠራ ጊዮርጊስ ሰጠ ። እንደ እንስሳት ሳር የበላ ማትያስም ወተት ካላስገኘ ፡ ሳር መብላት የሚገባው ወተት የሰጠ ጊዮርጊስ ነው በማለት ባለቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር የሰማእታትን ተጋድሎ አብራርተዋል ።

254 መወድስ

አፍቅሮ ብእሲት ሠናይ ለሰብእ ሐተታ
ወአኮ ሠናይ አፍቅሮ ዚአሃ ለብእሲት ፡
አኮኑ አምሠጠ እመሥገርት ሳአል ሞት
በጥበበ ሜልኮል ብእሲቱ
ዘሰበረ ላሕመ አሉፍላዊ አንበሳ ዳዊት ።
ወበሐሳኒቱ ለኢዮዓስ
ኢዮዓስ ድኅነ እምኀልቀት ደቂቅ ወሕፃናት ፡

ኢይደቅ በበዘመኑ ነገረ ምሳሌ አረፍ
አምጣነ ዮሐንስ ተደለወ በዘማ አርቃድዮስ ለኅልፈት ።
ወከልኡሂ ዮሐንስ ሥርወ ዘከርያስ ዘይት
ትመልሐ በእዴሃ ለሄሮድያዳ ገሊላዊት ።

ት ር ጉ ም

ለምርምር ሰዎች ሴትን ማፍቀር መልካም ነው ፡
ሴትንም ማፍቀር መልካም አይደለም ፤
የኢሉፍላዊ ላምን የሰበረ አንበሳ / ዳዊት
በሚስቱ ሜልኮል ጥበብ
ከሳአል ወጥመድ / ሞት አመልጧልና ።
ኢዮአስም በሞግዚቱ
ከህፃናት እልቂት ዳነ ፤
የምሳሌ ነገር ግድግዳ በየዘመኑ እንዳይወድቅ
ዮሀንስ በአርቃዶዎስ ዘማ ለሞት ተዘጋጅቷልና ።
የዘካርያስ ዘይት ስር ሌላው ዮሀንስም
በገሊላ ሴት ሄሮድያዳ እጅ ተነቀለ ።

ም ስ ጢ ር

የሴት ፍቅር በአንድ በኩል መልካም ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ጎጂ መሆኑን በሴት በተጠቀሙና በተጎዱ ሰዎች ማስረጃነት የቅኔው ደራሲ ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

ታ ሪ ክ

ዳዊት ጎልያድ የተባለውን ፍልስጥኤማዊ በወንጭፍ ድንጋይ ገደለ ። ይህንን ጀብዱ በመስራቱ በህዝቡ ዘንድ ተወዳጅነትን አተረፈ ። ነገር ግን በዚሁ መጠን ንጉስ ሳአል ምቀኛ ሆነበትና ዳዊትን ሊገድለው ፈለገ ። ሚስቱ የሳአል ልጅ ሜልኮል ግን እጅግ በጣም ትወደው ስለነበር ከሳአል ሸሽቶ እንዲያመልጥ ረዳችው (1. ሳሙ. 17 ፡ 45—51 ፤ 19 ፡ 11—17) ።

የንጉስ አካዝያስ እናት ጎቶልያ ልጅዋ እንደሞት ስላወቀች የመንግስትን ዘር ሁሉ አጠፋች ። በዚያን ጊዜ የኢዮአስ አሳዳጊ የሆነች የአካዝያስ እህት ዮሳቤት የአካዝያስ ልጅ የሆነ ኢዮአስን ከንጉስ እልፍኝ ወሰደችው ፤ እንዳይገደልም ከጎቶልያ አዳነችው (2 ነገ ፡ 11 ፡ 1—3) ።

ዮሀንስ አፈ ወርቅ የአንያኪያና የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ነው። በቅድማያ አለማዊውን ትምህርት ካጠናቀቀ በሁዋላ ወደ መንፈሳዊው ትመልሶ ደጋግ ድርሳናትን ደርሷል ። በሰው ፊት ሳያዳላና ንጉስና ንግስትን ሳይፈራ ሁሉንም በእኩልነት ተመልክቶ በእውነት ይገስፅ ነበር ። የንጉስ አርቃድዮስ ሚስት ንግስት አውዶክስያ ያንዲት መበለት የወይን ቦታ ቀምታ ባለቦታይቱን መበለት ስላስለቀሰቻት የወሰደችባትን ቦታ እንድትመልስላት ቢመክራትና ቢገስፃት አልሰማ አለች ። ስለዚህ ከቤተ ክርስቲያን እንድትለይ ቢያወግዛት እንደ ዲዮቅልጥያኖስ «አብያተ ክርስቲያናትን ዘግቼ አብያተ ጣኦታትን እከፍታለሁ» በማለት አንገራግራና አስፈራርታ ዮሀንስ አፈ ወርቅን አሰደደችው ። ስለዚህም በዚያው በጥሰደደበት በአክራጥያ ደሴት ወንጌል ሲሰብክና ክርስቶስን ሲያሳምን አርፏል (ስንክ. ግንቦት 12)።

255 መወድስ

ኢየወርፍ ልብ እምተምኔት ሥጋ
እመኒ ይረክብ መንግሥት ዕብራዊ ዳዊት ፤
እስመ እመ ርኁቅ ፍኖቱ ፍና ሰማያት
ኢይዌስንዎ ምስፍና ወሀብት ፡
ወከመ ይሠዕዎ ነቢያት
ለምሳሌሁ በግዕ እኁዘ ክልኤቱ አቅርንት ።
አዳምሂ ለእመ ነግሠ ፈልዕልተ ኵሉ ፍጥረት
መንግሥቶ ለፈጣሪሁ ተመነየ በገነት ፤
ወከዊነ አምላክ ፈቀደ ልቡና ሔዋን ብእሲት
ኵሉ ለእመ ሞተ አምጣነ ልቡና ኢይመውት ።

ት ር ጉ ም

የእብራዊ ዳዊት መንግስትን
በያገኝ እንኳ ልብ ከሰጋዊ ምኞት ኢያርፍም ፤
የራቀ መንገዱ የሰማዮች መንገድ ቢሆን
ግዛትና ሀብት ኢይወስኑትምና ፡
ነቢያትም ሁለቱ ቃንዶችን
የያዘ በግ/ ምሳሌውን ይሰውት ዘንድ ነውና ።
አዳምም በፍጥረት ሁሉ ላይ ቢነግስ
የፈጣሪው መንግስትን በገነት ትመኝ ፤
እምላክ መሆንንም የሴት ሄዋን ልብ ወደደ
ሁሉም ቢሞት ልቡና አይሞትምና ።

ም ስ ጢ ር

ሰው ንጉሰ ነገስት ቢሆንና ቢበለፅግም እንኳን ምኞቱ በአፍንጫ እንደሚመላለስ አስትንፋስ የማያቋርጥና በእርጅናም ጊዜ የማይቆም መሆኑን ባለቅኔው ከአዳምና ከሄዋን አድራጎት ጋር በማነፃፀር አመስጥረዋል ።

256 መወድስ

ጸላእኩ ሰብአ እምነ ርእስየ
ዘትርጓሜሁ በቀል መዘንባቡ ሐሰት ፤
እስመ እምልሳኑ ለሰብእ ዘይበልዖ መሬት
ለፈ ትሕትና ወለፈ ትዕቢት
ይወፅኡ ለሰብከት ፡
እንዘ በላዕሌሁ ይሄሉ እንተ ኢይትርፍ ሞት ።
ልብየሂ ለእመ ጌሠ መንግለ ሐተታ ኅጎት
ባቲ ዘትጋብአ ጥበባተ ሰሎሞን ጽጌያት ፡
ዕሩያን ኮኑ በሳምናዊ ሰዓት
ሰብእ በዐመፃ ወእግዚአብሔር በምሕረት ።

ትርጉም

ትርጓሜው በቀል ንባቡም
አሰት የሆነ ሰውን ከራሴ ጀምሬ ጠላሁ ፡
መሬት ከሚበላው ሰው አንደበት
በወዲያ ትህትና በወዲህ ትእቢት
ለማስተማር (ለስብከት) ይወሳሉና
የማይቀር ሞት በላዩ ላይ እያለ ።
ልቤም የሰሎሞን ጥበቦች / አበቦች
ወደትሰበሰቡባት ነጎት / ምርምር ቢገሰግስ
በስምንተኛው ሽህ አንድ ሆኑ
ሰው በበያል እግዚአብሄርም በምህረት ።

ምስጢር

ለአንድ መፅሀፍ ንባብና ትርጓሜ እንዳሉት ሰው በቁምና በአሰት ተመርዘል ። ሁለት ጓዶችም በአንድነት እንደሚወጡና እንደሚገቡ በሰው አንደበት ትእቢትና ትህትና መነገራቸው ፡ በስምንተኛው ሽህ ሰው ሞት እንዳለበት አለማሰቡን ያመለክታል በማለት ባለቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

257 መወድስ

ኢተገፋሂ ያስቆቁ ፍዳ ተገፋሂ ፡
ወጽድቁ ኤልያስ ወሕኑጸ ደብር ቤት ፡
አምጣነ አጎዘ ይብኪ ዘኢተገፍዐ እሳት
እንዘቦ ደቂቅ ዘገፍዕዎ
መገብተ ዚአሃ ለባቢሎን ቅሥት
ወበምድረ ነፋስ ኢተክዕወ
ዘያደነግፅ ልቡና ጽዋዐ ምሳሌ እሳት ።
አመ በጽሐ ተባርዮ መንግሥት አዝርዕት ጸባሕት

ገራህት በዘትሰጠ እስመ ይበክዩ ደመናት ፡
ወትጸርሕ ሰውዋ በዘተቀስፉ አንስት
ወበዘተጸፍዉ መላትሕ ያስቆቅዋ አዕይንት ።

ትርጉም

ያልተገፋው በተገፋው ብድራት ያለቅሳል ፡
እመነቱም ኤልያስና በተራራ ላይ የተሰራ ቤት ናቸው ፤
የርሷ የባቢሎን ከርከር ሹማምንት የሆኑ ፡
የበደሉ ልጆች ሳሉ
ያልተገፋ እሳት ያለቅስ ጀምሯልና ፡
ልብን የሚያስደንግጥ የምሳሌ
ፅዋ / መአትም በነፋስ ምድር አልፈሰሰም ።
የእዝርእት / ገባሮች መንግስት መለዋወጥ (ፍርርቅ) በደረሰ ጊዜ
እርሻ በትቀደደ ደመናዎች ያለቅሳሉና ፡
ሴቶችም በተገረፉ ጅራፍ ትጮሃለችና
ጉንጮችም በተጠፈጠፉ አይኖች ያለቅሳሉና ።

ምስጢር

«የምጣዱ ሳለ የአንቅቡ ትንጣጣ» እንደሚባለው የተበደለው ሳለ የበደለው እንደሚያለቅስ ፡ ሶስቱ ልጆች (እናንያ ፡ አዛርያና ሚሳኤል) በወሰጡ የተጣሉበት እሳት እንደውሃ ቀዘቀዘ ። ከዚህም አንፃር ባለቅኔው መሬት ሲታረስ በግረሻ መወጋቱንና ደመናዎች ዝናብን ማዝነባቸውን ፡ ጀርባም በተገረፈ ጅራፍ መጮሁዋንና ጉንጮችም በተመቱ አይኖች ማንባታቸውን በመጥቀስ ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

258 መወድስ

ዘውብሸት (ቁሰ ገበዝ ፣ ዘብኾና)

ኦ አብርሃም መድኀኔ ዓለም
ትእንገዱ ብከ እናግደ ሐዊን ቅንዋት ፤
ወእመ በገጽከ ቀርበ ትጸፍያት ገጽ ጎብስት
ነበረ በጥቃ ነቦከ እንግዳ ኩናት ፤
ወላእከ ትእዛዝ ገቦ ዚአከ
ጽሩየ ማየ አቅረበ ለጎፅበት ።
ይትሐነጽሂ ለአረጋዊ ሕንጻ ቤትከ ስቅለት
በሐብል ተመጠነ ዘባንከ መሠረት ፤
ወእመ ይጠፍእ ብከ ብርሃነ ፀሐይ ማኅቶት
ዕለተ ሞትከ አረጋዊ ነበረ በጽልመት ።

ት ር ጉ ም

መድሀኔ አለም / አብርሃም ሆይ !
የብረት እንግዶች / ችንካሮች እንግዶች ሆኑብህ ፤
የፊት መጠፍጠፍ / እንጀራም በፊትህ በቀረበ ጊዜ
ጦር / እንግዳ በጎንህ አጠገብ ተቀመጠ ፤
የትእዛዝ መላክተኛ / ያንት ጎንዎ
ለእጥበት ጥሩ ውሃን አቀረበ ።
የቤትህ ስቅለት / ህንፃዎ ለሽማግሌ ይሰራ ዘንድ
መሰረት / ጀርባህ በገሠድ ተለካ ፤
የፀሀይ ብርሃን / መጎረጉም በጠፋብህ ጊዜ
የሞትህ ቀን / ሽማግሌ በጨለማ ተቀመጠ ።

ም ስ ጢ ር

አብርሃምን እንግዶች እንዳቀማመጡት መድሀኔ አለምን ችን
ካሮች ወጉት ። ማእድ በቀረበ ጊዜ እንግዳ ከባለቤቱ ጎን እንደሚ
ቀመጣ ክርስቶስም ፊቱን በጥፊ ተመታ ፣ ጎኑንም በጦር ተወጋ፤ አሽ

ከርም የጌታውን እጅ ላማስታጠብ ውሃ እንደሚያቀርብ ክክርስቶስ
ጎን ውሃ ፈለቀ ። ቤተሰቦም መሬቱን በገመድ እንደሚለካ የክርስ
ቶስ ጀርባም በገመድ ጅራፍ ተገረፈ ። ከዚህም ሌላ መብራቱ የጠ
ፋበት ሽማግሌ በጨለማ እንደሚቀመጥ ክርስቶስ የተሰቀለበት ቀን
ጨለማ ሆነ በማለት ባለቅኔው በክርስቶስ ስቅላት ምክንያት ተፈ
ፀሙ የሚባሉትን ተአምሮች በመዘርዘር በቅኔያቸው አመስጥረዋል።

259 መወድስ

ጣዕዋ ንዑስ መድኀኔ ዓለም
ዘአሰረከ እግረከ ናላዌ እንስሳ ቀኖት
አድያመ ዮርዳኖስ አፉከ እንተ አልቦቱ ሐሰት
ያደ ነዋ ዮሐንስ ሐሞት ፤
ወአጸብዓኪ ነቢያት
ቀዳሚ ጸሐፉ ቃላተ ብሉይ አሪት ።
ጎዳጠሂ ኢትፈርሆ ላብእሲሃ ኩናት
ርብቃ ገቦ ዚአከ መንታ ዘወለደት ፤
ወመትረት ሞተ በለሰ አሐቲ ገኔት
ሔዋን ስቅለትከ ዘበዕለተ ዐርብ ተፈጥረት ።

ት ር ጉ ም

የክብቶች ጠባቂ ችንካር እግርህን ያሰረህ
ትንሽ ጥጃ / መድሃኔ አለም !
ኦሰት የሌለበት የዮርዳኖስ ዙሪያ / አፍህን
እነሆ አሞት / ዮሀንስ ዞረ ፤
ነቢያት/ ጣቶችህም
የብሉይ ቃላትን በመጀመሪያ ፃፉ ።
መንታን የወለደች ያንተ ጎን/ ርብቃም
ችንካር/ባልዋን ጥቂት አትፈራውም ፤
በእርብ ቀን የተፈጠረች ስቅለትህ / ሄዋንም
ያንዲት ገነት በለስ/ሞትን ቆረጠች።

ም ስ ጢ ር

የክብቶች እረኛ የጥጃውን እግር እንደሚያስረው የመድሃኔ አለ
ምን እግር ቸንካር ወጋው ። ዮሀንስ መጥምቅም የዮርዳናስን አካባቢ
እንደዞረ በክርስቶስ ጉረሮ አሞት ወረደ፤ ነቢያትም የአሪት ቃላትን
እንደፃፉ የክርስቶስ ጣቶች በአሪት«እጆቼንና እግሮቼን ቸንከሩኝ»
ተብሎ የተነገረው ቃል መፈፀሚያ ሆኑ ። ከዚህም ሌላ ርብቃ ይስ
ሀቅን እንዳገባችና መንታ እንደወለደች ፣ የክርስቶስ ጎን በጦር መወ
ጋቱንና ደምንና ውሃን በመንታነት ማፍለቁን የቅኔው ምስጢር ያስ
ረዳል ። ሄዋንም አርብ ቀን ተፈጥራ የኖረችበት የገነት በለስን እንደ
ቆረጠች የክርስቶስ ስቅላት ሞትን አጠፋች ይላሉ ባለቅኔው ።

260 መወድስ

ግፋዕ ይሬኢ ሀጕለ ገፋዒሁ ፤
እስመ በገፋዒ ትረውጽ ሀጕለ ተገፋዒ ንግሥት
እንዘ በፀጋማ ሕማም ወበየማና ሕይወት ፣
ዝኒ ኢይኩን ቃለ ሕሳቄ
ተሠግረ ነዋ ወበጽሐ ለሞት
ሐማ ገፋዔ ጥንት
ለመርዶክዮስ ወይጠል በዘረበቦ መሥገርት ።
ጽሩየኒ ግየ ዘለፋ በምክረ ዐመፃ ቀሱት
ዘቀድሑ ለሶስና ሰትዩ ረበናት፤
አኪጦፈልኒ ዘሐረ በምክረ ዐመፃ ፍናት
ወድቀ ውስተ ግብ ዘከረየ ለዳዊት ።

ት ር ጉ ም

የተገፋ የገፈውን ጥፋት ያያል፤
በግራዋ ህማም ፣ በቀኟም ህይወት ሳሉ
የተገፈ ጥፋት/ንግስት በገፈ ትሮጣለችና ፣
ይህም የአሰት ቃል እንዳይሆን

የመጀመሪያ ገፈ የሆነ ህማ
እነሆ ለመርዶክዮስ / ፈቆ
በዘረጋው ወጥመድ ተጠመደና (ተያዘና) ለሞት ደረሰ ።
የጠራ ውሀ/ስድብንም በበደል ምክር/እንስራ
ለሶስና የቀዱትን መምህራን ጠጡ፤
በበደል ምክር/መንገድ የሄደ አኪጦፈልም
ለዳዊት በቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ወደቀ።

ም ስ ጢ ር

ባለቅኔው ንግስት በቀኝና በግራዋ ታጅባ እንደምትሄድ ለተገ
ፈው የታሰበችው ጥፋት ለገፈው መከራ ፣ ለተገፈው ግን ህይወት
ሆነች በማለት ቅኔያቸውን አመሰጥረዋል።

ታ ሪ ክ

ሀማ የፋርስ ንጉስ አርጤክስስ ከፍ ከፍ ያደረገው የአይሁድ
ጠላት ነበር ። አይሁድን ለማጥፋት ፣ እስራኤላዊው መርዶክዮስንም
ለማሰቀል አሰበ ። ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው መስቀል ራሱ ተሰቀለ
(አስቴ.3፤1—15፤5፤9—14) ።

ሶስና እስራኤላዊት ሴት ናት ። ባሏ ከሞተባት በሁዋላ ሌላ ወንድ
ሳታገባ በፆምና በፀሎት ተጠምዳ እግዚአብሄርን በንፅህና እያገለገ
ለች ትኖር ነበር። በዘመኗ የነበሩ የህዝብ አሰተኞች መምህራን ለዝ
ሙት ተግባር ጠይቀዋት ብታሳፍራቸው « የዝሙት ስራ ስትሰራ
አገኘናት» ብለው ወንጀሏት ። እንደሙሴ ህግ ሞት ከተፈረደባት
በሁዋላ በነቢዩ ዳንኤል መንፈሳዊ ብልሃት ንፅህናዋ ተገለጠላት ። ያሳ
ጧት (ስምዋን ያጠፉት) ረበናትም (የአይሁድ መምህራን) አሰተኛ
ስራ ታወቀ ። ከዚህም በሁዋላ ትሙት በቃ የፈረደባት የገዛ አባቷ ከነ
ህዝቡ አገነናት አሳቃት ይባላል (መፅሀፈ ሶስና)።

አኪጦፈል የእስራኤል ንጉስ ዳዊት አማካሪ ነበር ። አቤሴሎም
በአባቱ በዳዊት ላይ ባደመ ጊዜ አኪጦፈል በአድማው ተባበረው ።
ነገር ግን «ዳዊትን በፍጥነት እናሳድደው» የሚል ምክሩን አቤሴ
ሎም ሳይቀበለው በመቅረቱ አኪጦፈል ወደ ቤቱ ተመልሶ በገዛ
እጁ ታንቆ ሞተ (2.ሳሙ.17 ፣ 1—23) ።

261 መወድስ

ምውታን ቀስቱ ቀበረ በውሳጤ ከርሡ ፣
ወኢጎሠሠ መግነዘ እስመ መግነዙ ጎብስት
በሳዔ ሥጋሁ ለሰብእ ። ወበእንተዝ ሥርዐት
እንግዳ ነገረ ለማርያም
እንግር ላቲ በዘየም ዕለት፤
አኮኑ እንበለ ጥንት
መቃብረ ሙታን አዕረገት ማርያም ውስተ ገነት ።
ወኢተርፉ በውስቴቱ እለ ተቀብሩ ነፍሳት፤
እስመ ንጹሬ ዐይን ኢይተርፍ እንዘ የሐውሩ አዕይንት፡
ወእመ ሰራቂ ወሰደ መዛግብተ አዕናቅ ዐበይት
አዕናቅኑ ኢይተርፉ እንዘ የሐውሩ መዛግብት።

ት ር ጉ ም

በላኤ ሰብእ በቀስቱ የሞቱትን በሆዱ ውስጥ
ቀበረ ፣ መገነዣንም አልፈለገም ፤
መገነዣው እንጀራ ነውና ። ስለዚህም ስርአት
እንግዳ ነገርን ለማርያም
በዛሬ ቀን እናገርላታለሁ፤
ያለ ጥንት(ያለልማድ)
የሙታን መቃብርን ማርያም ወደ ገነት አውጥታለችና።
የተቀበሩ ነፍሶችም በውስጡ አልቀሩም፤
የአይን መመልከት (ምልከታ) አይኖች ሲሄዱ አይቀርምና
ሌባም የታላላቅ እንቁዎች ሳጥኖችን በወሰደ ጊዜ
ሳጥኖች ሲሄዱ እንቁዎች አይቀሩምና።

ም ስ ጢ ር

በሽብር ጊዜ የሞተውን ሰው ዘመዶቹ ሳይገንዙ እንደሚቀብሩት በላኤሰብእ ሰዎችን በቀስቱ እየወጋ በላ ካሉ በሁዋላ ፤ ባለቅኔው ቅድስት ማርያም የሰዎች ስጋ የተከማቸበትን ሰው(በላኤ ሰብእን) ወደ ገነት እንዲገባ በማድረጓ ፣ መቃብርን እንዳሳረገች ቆጥረው በአይኖችና በሳጥኖች አንፃር ቅኔያቸውን አመስጥረዋል።

262 መወድስ

ጸናጽለ ብሩር ከንፈ ወምቅዋመ ቀርን
በንዋየ ጸጋ አጥረየ ለግብረ ቀኖና ግጎሌት
መዘምር ካህን ተክለ ሃይማኖት
ዘመልአ በልብሱ መዐዛ ስብሐት፤
ወግብረ ቀኖና ከመ ይግበር
ደንጊያ ተንሥአ በመንፈቀ እግሩ ሌሊት ።
ካዕበሂ ለእመ ጎጥአ እምሕዋሳቲሁ ዐበይት
ዶርሆ ሰኰና እግር ዘያነቅሆ ጊዜ ጸሎት፤
ግሩመ ዙሉ ሌሊተ ፍና ሰማያት
መጠነ በስድስቱ አክናፈ ኪሩቤል ከዋክብት።

ት ር ጉ ም

መአዛ / ምስጋና በልብሱ የሞላ ዘማሪ
ካህን / ተክለ ሃይማኖት የብር ፀናፅል / ክንፍንና
የቀንድ መቋሚያን በፀጋ / ገንዘብ
ለቀኖና (ያም) ስራ / ማህሌት ገዛ ።
የቀኖና ስራንም ይሰራ ዘንድ
ደንግጦ በእግሩ / ሌሊት እኩሌታ (አጋማሽ) ተነሳ።
ሁለተኛም ከታላላቅ ሰውነቶቹ በፀሎት ጊዜ

የሚያነቃው የእግር ሽሆና /ደሮን ቢያጣ ፥
የሁሉ አስፈሪ የሰማዮች መንገድ / ሌሊትን
በስድስቱ የኪሩቤል ክንፎች/ ኮከቦች ለካ ።

ም ስ ጢ ር

ደብተራ የብር ፀናፅልንና የቀንድ መቋሚያን ለማህሌት ስራ በገንዘቡ እንደሚገዛ ፃድቅ ተክለ ሃይማኖት የፀጋ ክንፍ አበቀሉ ፥ የቀንድ እግርን በተሰበረው እግራቸው ተኩ ይላሉ ባለቅኔው ።

ካህንም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በእኩለ ሌሊት እንደ ሚነሳ ተክለ ሃይማኖት ባንድ እግር መቆማቸውን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ። ከዚህም ሌላ የሌሊት መንገደኛ የከዋክብትን መውጣ ት ተጠባብቆ በከዋክብት ብርሃን እያየ እንደሚሄድ ፥ የተክለ ሃይ ማኖትም አንድ እግራቸው ቢሰበር በስድስት የፀጋ ክንፎች ወደ ሰማይ አረጉ በማለት ባለቅኔው ለተክለ ሃይማኖት ተፈፅሟል የሚባ ለውን ተአምር በቅኔያቸው ምስጢር ያስረዳሉ ።

263 መወድስ

ዘአፈ ወርቅ ዘውዴ (አለቃ)

ተበቃሊሁ ለሰብአ ንዋየ እዴሁ ፤
እስመ በዓለ ወርቅ ወርቅ ተፈትነ በእሳት ፥
ወአመ በምድርነ ከብዶ ቅንየተ ሮሜ ክረምት
ለኵሉ ርኩብ ማየ መከራ
እስከ ጎርየ በዓለ ንዋይ ተጽናሰ እምሀብት
ወእስከ ኢክህለት ትትከበት
ንዋየ ቅድስት ሀገር እንተ መልዕልተ ደብር ተሐንጸት።
ወእምላዕል ዘይዘንም ወዘይነቅዕ እምታሕት
ማየ አይኅ አማዕበለነ በመዓልት ወበሌሊት ፤
ወእማየ አይኅ ንድኅን ኢትጹረነ ታቦት
ታቦትን አራራት ለርእሳ ኢረከበት ።

ት ር ጉ ም

ሰውን የሚበቀለው የእጁ ገንዘብ (የገዛ ገንዘቡ) ነው፤
ባለ ወርቅ / ወርቅ በእሳት ተፈትኗልና ፥
የሮም አገዛዝ / ክረምትም በምድራችን በከበደ ጊዜ
ፈተና / ውሃ ለሁሉ ግኝ ነውና (ይገኛልና)
ባለገንዘብ ከሀብት ይልቅ ችግርን እስከ መረጠ ድረስ ፥
በደብር ላይ የታነፀች
የተለየች (የከበረች) ታቦት እቃም ልትደበቅ እስካልቻ
ለች ድረስ ፤
ከላይም የሚዘንብና ከታች የሚፈልቅ (የሚመነጭ)
የጥፋት ውሃ
በቀንና በሌሊት አጥለቅልቆናልና
ከጥፋት ውሃም እንድን ዘንድ ታቦት እንዳትሸከመን
ታቦታችን አራራትን ለራሷ አላገኘችምና ።

ም ስ ጢ ር

በጠብመንጃው ቃታ ያነረሰው ጥይት ተባርቆ ባለጠብመ ንጃውን እንደሚመታው ሁሉ ባለወርቅና ብር ደክሞ በላቡ ባፈ ራው በገዛ ገንዘቡ ተሰቃየ ። ወርቅም በእሳት እንደሚፈተን ባለብር በእሳት በጋለ ብረት ምጣድ ተጠበሰ ።

ክረምትም በምድር ላይ እንደሚከብድ የሮም ፋሽስት አገዛዝ በኢትዮጵያ ላይ አለወጉ ሆነ ። ክረምትም በከበደ ጊዜ ውሃ በየ ደጁ ለሁሉ እንደሚገኝ በሮም አገዛዝ ጥናትም መከራ ለሁሉም ደረ ሰው ። ክረምት ሲከብድ ፀሀይ እንደሚፈለግ ፥ በኢጣልያ አገዛዝ ሽፍታውም ባንዳውም ባለገንዘቡን ሲያሰቃዩት ባለፀጋው « ምነው ድሃ በሆንሁ » እስከማለት ደረሰ ።

በተራራ ላይ የተሰሩች መንደር ከአይን እንደማትሰወር በየደብሩ በቤተ ክርስቲያን የተኖረው የታቦት እቃ ሁሉ ተበረበረ (ተዘረፈ)።

በኖህ ዘመን ከላይ የዘነበውና ከምድር የመነጨው የጥፋት ውሃ የቀድሞ ሰዎችን በቀንና በሌሊት እንዳሰጠማቸው በኢጣልያ ወረራ ጊዜ በቀን ባንዳዎች ፡ ሽፍቶችም በሌሊት ህዝቡን ደበደቡ ት ። የጥፋት ውሃ ከላይ ወደ ምድር እንደዘነበና ከምድርም ወደላይ እንደፈላ ከአውሮፕላን ላይ ቦምብ ወደህዝቡ ተጣለና ምድሩን አደ ባለቀው ፡ የላዩን በታች የታቹን በላይ አደረገው ፤ ስለዚህም ሌት ም ቀንም መባነን ሆነ ።

ኖህ ከእነቤተሰቦቹ በታቦት (በመርከብ) ወስጥ ገብቶ ከጥ ፋት ውሃ እንደዳነ ፡ የኢትዮጵያ ህዝብ በቤተ ክርስቲያን ታቦት ከኢጣልያ አደጋ እንዳያመልጥ የቤተ መቅደስ ታቦት ለራሷ መጠ ጊያ ደብርን አሳገኘችም ። ምክንያቱም ደብሩ (ቤተ ክርስቲያኑ) ከአውሮፕላን ላይ በሚወረወር ቦምብ ከመደብደብ አላመለጠምና ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

ታሪክ

ይህ ቅኔ የተደረሰው ከጎጃም አድባራት መካከል አንዱ በሆ ነው በደብረ ገነት ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን ነው ። ዘመኑ 1931 አ.ም. ሲሆን ፡ ምክንያቱ ጠላት ከ1928 አ.ም. ጀምሮ በኢትዮ ጵያ ህዝብ ላይ ስለፈፀመው ግፍ ነው ። በዚያ ዘመን ስለሀብት መኖር ጭምጭምታ የተሰማበት ሰው ሁሉ ቀን ቀን በኢጣልያ ፋሽ ስት ባንዳ ሲደበደብና ሲሰቃይ ይውላል ። ሌሊት ሌሊት ደግሞ በሽፍቶች የቀበርኽውን ብር አምጣ እየተባለ የፊጥኝ ከወጋግራ ጋር ታስሮ ይገረፋል ፤ በእሳት በጋለ ብረት ምጣድ ላይ ተቀምጦ ይጠበሳል ። ያን ጊዜ ያልተሰቃየ ከስንት አንድ ነው ፤ በቤቱ የሚ ውል አልነበረም።መላው ቤተሰብ በጫካና በዋሻ ውሎ ማታ ጨለማ ለብሶ እቤቱ ገብቶ ሴቶቹ እሳት ሲያጢያጢሱና ገና እህል ሳይቀ ምሱ ሽፍታ በየቤቱ ከች ይልባቸዋል ። በአርበኞች ሰፈር አካባቢ የነበሩት ቤተ መቅደሶች ከአውሮፕላን ላይ ቦምብ ተጣለባቸው ። የታቦት እቃ ቤቶችና መቅደሶችም ፈረበሩ ። የየደብሩ ህዝብ በሙሉ በባለሳንጃ ፈረሰኞች ፋሽስቶችና ባንዳዎች እየተከበበ መሳ ሪያው ቀርቶ ቀለሀ የተገኘበት ይረሽን ነበር ።

264 መወድስ

ዘውብሸት (መምህር)

ለዐፅመ ልዳዊ ሰማዕት እግዚአ ተገፍያ
ይስቅልዎ መጽኡ አይሁድ ነፋሳት ፡
ወዝርዋነ ምድር ኮኑ ሕዋሳቲሁ አርድእት ፤
ለሞት አምጣነ አብጽሖ ይሁዳ መጥባሕት ።
ወአመ ተምዑ አጋዕዝት
ሕንጻ ሥጋሁ ሰናያር በነፋሰ ዐውሎ ተመዝበረት ።
ፈረየትሂ ለለዕለቱ አስካለ ምትረት
ክሣደ ጊዮርጊስ ዕፀ ከርካዕ ጎበ ሙሐዘ ማይ ዘበቈለት፤
አመኒ ደወየ በዙረ ተጋድሎ ሰማዕት
መጽኡ ለጠይቆ አዝማደ ጳውሎስ አክሊላት ።

ትርጉም

የመገፋት ጌታ / የልዳ ሰማእት አጥንትን
ይሰቅሉት ዘንድ ነፋሶች / አይሁድ መጡ ፤
ተማሮች/ ሰውነቶቹም የምድር ብትኖች ሆኑ (ተበተኑ) ፤
ይሁዳ / ሰይፍ ለሞት አድርሶታልና ።
ጌቶችም (ስላሴ) በተቆጡ ጊዜ
የስጋው / ሰናአር ህንፃ በአውሎ ነፋስ ፈረሰች ።
በውሃ መውረጃ የበቀለች የጊዮርጊስ
አንገት / የሎሚ እንጨትም ፍሬ/ መቆረጥን በየቀኑ አፈ
ራች ፤
የመጋደል አለቃ / ሰማእትም በታመመ ጊዜ
የጳውሎስ ዘመዶች / አክሊሎች ለመጠየቅ መጡ ።

ምስጢር

ክርስቶስን አይሁድ እንደሰቀሉት የጊዮርጊስንም አጥንት ነፋሶች ወሰዱት ። እንዲሁም ክርስቶስ ሲያዝ ሀዋርያት እንደተበ ተኑ የጊዮርጊስ ሀዋሳት (የአካሉ ክፍሎች) ደቀው ተበተኑ ።

ከዚህም ሌላ ስላሴ በተቆጡ ጊዜ የሰናኦር ህንፃ እንደፈራረ ሰች የጊዮርጊስ አካል በነፋስ ተበተነች ። በውሃ መፍሰሻም-የበቀ ለች የሎሚ እንጨት በየጊዜው ፍሬን እንደምታፈራ የጊዮርጊስ አን ገት በመቆረጥ ውሃ አፈሰሰች ። የታመመውን ሰውም ዘመዶቹ ሊጠይቁት እንደሚመጡ ፣ መከራ ለተቀበለ ጊዮርጊስ ሰባት አክ ሊሎች ወረዱለት በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

265 ዑልክሙ

ዘመርሻ (መጋቢ ፡ ዘዲማ ጊዮርጊስ)

ልበ አስራኤል ሰረቀ በከናፍሪሁ
አቤሴሎም አብን ማኅበረ ደቂቅ ወሕፃናት
አስመ ለአሉ ይእቲ መንግሥተ ሰማይ ስብሐት ።
ወፈለሰ አመካኑ
አስራኤል እንተ አንገሥዎ አርምሞ ዳዊት ፤
ወአምይሁዳ ዘተረስዐት
ተናግሮ አይሁድ ትእማር ዘለፋ አስራኤል ጸሐፍት ።
ይቤሎሙሂ ሦፃዕና ለአእባነ ደብር ጎለፍት
ኢትበሉ ለጌሠም ቅዳሴ ምግበ ዕለት ፤
ወለሦፃዕና ይብልዎ ጎበስተ ሕይወት
ንብላዕ ወንስተይ ወጌሠመ ንመውት ፤
እንዘ ዮም ሰብአ አምጣነ ጌሠም መሬት ።
ንብላ ወንስተይ ወጌሠመ ንመውት ፤

ትርጉም

የእሽከሮችና የህፃናት ተባባሪ
ድንጋይ / አቤሴሎም የእስራኤልን ልብ በከንፈሮቹ አስኮ በለለ ፤
መንግስተ ሰማይ / ምስጋና ለእነርሱ ናትና ።
እስራኤል ያነገሱት
ዳዊት / ዝምታም ከቦታው ተሰደደ ፤
የእስራኤል ፀሀፊዎች ስድብ
የሆነች የአይሁድ መናገር/ ትእማርም ከይሁዳ የተረሳች ናት ።
ሆሳእናም የተራራ ድንጋዮች / መንገዶደኞችን የእለት ምግብ/ምስጋናን ለነገ ይሁን አትበሉ አላቸው ፤
(እነርሱም) ሆሳእናን የህይወት እንጀራን
«እንብላና እንጠጣ ፡ ነገም እንሞታለን » ይሉታል ፤
«ዛሬ ሰው ስንሆን ነገ መሬት ነንና » ።
«እንብላና እንጠጣ ነገም እንሞታለን» ይሉታል ፤

ምስጢር

ያባቱን ዙፋን ለመንጠቅ ከትንንሾችና ከትልልቆች ጋር የመ ከረ የእስራኤል ንጉስ ዳዊት ልጅ አቤሴሎም በንግግሩ የእስራኤ ልን ልብ እንዳስኮበለለ የሆሳእና ድንጋይ እንደልጆች አመሰገነ ፤ በምስጋናውም ህዝቡን አስገረመ ። አይሁድ ገንዘብ ያደረጉት ዝም ታም ከድንጋይና ከህፃናት ጠፋ ፤ የተረሳች ትእማርም የእስራኤል መሰደቢያ እንደሆነች ፡ ይሁዳ የተዋት እውነትን መናገር የእስራ ኤል መነቀፊያ ሆነች በማለት የቅኔው ደራሲ የቅኔያቸውን ምስ ጢር አራቀዋል ። ከዚህም ሌላ ክርስቶስ ሀዋርያትን « ለነገ አት በሉ» እንዳላቸው የድንጋዮችም ማመስገን ያንድ ቀን ብቻ ሆኖ መቅረቱን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

266 ሚበዝኑ

ዘተክለ ጽዮን (አለቃ)

ሐሜተ ክልኤቱ አኀው
ዘኢፈርሀ ወልድ በልዐ በተከብቶ
ሥጋ ጥዑመ እንዘ የዐጹ ኖኅቶ ፤
ወፍሉጠ ሞት ኮነ ባሕቲቶ ዘበልዐ እስመ ይመውት ባሕቲቶ ።

ት ር ጉ ም

የሁለቱ ወንድሞቹን አሜት
ያልፈራ ወልድ በሩን ዘግቶ
በመደበቅ ጣፋጭ ስጋን በላ ፤
በሞትም ልዩን ሆነ «ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታልና።»

ም ስ ጢ ር

የባልጀሮችን አሜት ያልፈራ ሰው ደጃፉን ዘግቶ ስጋን እንደ ሚበላ ከሶስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ በቦታ ሳይለይ በተለየ አካሉ የማርያምን ስጋ ለበሰ ፤ በድን ግልናም ተወለደ ። « ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል » እንዲሉም ወልድ በለበሰው ስጋ ሲሞት ፥ አብና መንፈስ ቅዱስ ስጋን ባለመልበሳቸው በሞት አልተሳተፉትም (እንደ ወልድ አልሞቱም) በማለት ባለቅኔው የወልድን ሰው መሆንና መሞት ያስገነዝባሉ ።

267 ግእዝ ጉባኤ ቃና

በካፋ ኢትርሳዕ ዘተዋነይነ ክልኤነ ፤
እንዘ አበ አብርሃም አንተ ወብእሲተ አብርሃም አነ ።

ት ር ጉ ም

በካፋ ! ሁለታችን የተጫወትነውን አትርሳ ፤
አንተ የአብርሃም አባት (ታራ) ስትሆን እኔም የአብርሃም ሚስት (ሳራ) ስሆን ።

ም ስ ጢ ር

ሁለት ጓዶች ሲጨዋወቱ ቆይተው ሲሰነባበቱ አንዱ ለሁለ ተኛው «ያን የተባባልነውን እንዳትረሳ» ይለዋል ። በዚህም አንባር አፄ በካፋ በልጅነታቸው ከአንድ ጓደኛቸው ጋር በትምህርት ቤት ሲማሩና አፍአ ወጥተው (ተቀምጠው) ሳሉ «እኔ ብነግስ አንተንም ሾሜና ሽልሜ አልቅሃለሁ» የሚል የልጅነት ተምኔታዊ ተስፋ ለዚሁ ጓደኛቸው ሰጥተው ነበር ። እፄ በካፋ በምኞታቸው መሰረት ለመን ግስት በቁ ። ያም ተማሪ ምሁር ሆኖ ወደ ንጉሱ (አፄ በካፋ) ቀርቦ ያን በአፍአ የተጨዋወቱትን የልጅነታቸውን ነገር በዚህ ቅኔ አማ ካይነት አስታወሳቸው እና ያሉትን ፈፀሙለት ይባላል ።

268 ዋዜማ

ዘነይሉ (ዘመቀሉ)

ጽዮን ኢየአምሮ
መሰግላዊ አጽሎን እንተ ያሰግድ አእባነ ፥
ሶበ ሰትየ በቀርነ ኢሎፍሊ መዓተኪ ወይነ
ልብሰ ከዊኖቱ አምላከ እስመ ጎደገ ፍጡነ ፥
ወእንዘ ለሕዝቡ ይብሎሙ መድኀኒት አነ
መድኀኒተ ለርእሱ ኢኮነ ።

ት ር ጉ ም

ፅዮን ድንጋዮችን
የሚያሰግድ የጠንቋይ ወገን/አጽሎን አያውቅም ፥
መአትሽ/ወይንን በኢሎፍሊ/ዋንጫ በጠጣ ጊዜ

ልብስ/አምላክ መሆኑን ፈጥኖ ጥሏልና ፣
ለወገኖቹም መድሀኒት ነኝ ሲላቸው
ለራሱ መድሀኒትን አልሆነምና ።

ም ስ ጢ ር

ህዝቡን የሚያሰግድ ጠንቋይ በወይን (ቢና) ሰክሮ ልብሱን ጥሎ ሲታይ ፡ «አዋቂው ለራሱ አላወቀም ለሌሎቹ መድሃኒት ነኝ ሲል ራሱን አላዳነም» ይባላል ። እንዲሁም በእንፃሩ ከድንጋይ የተ ሰራ የኢሎፍሊ ጣኦት አጽሎን ከታቦተ ፅዮን ላይ ወድቆ ሲሰባበር አምላክ አለመሆኑ ተገለጠ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

ታ ሪ ክ

ዳጎን (አጽሎን) በፍልስጥኤም ፣ በሶርያና በመስጴጦምያ አገሮች ከሚመለኩ ጣኦቶች አንዱ ነበረ ። ይህ ጣኦት ልዩ መልክ ያለው ሆኖ ከወገቡ በላይ ያለው የአካሉ ቅርፅ ሰው ፣ ከወገቡ በታች አሳ ይመስል ነበር ።

በዘመነ መሳፍንት መጨረሻ ላይ ፍልስጥኤማውያን (ኢሎ ፍላውያን) እስራኤላውያንን በጦርነት አሸንፈው የእግዚአብሄርን ታቦት ፅዮንን በዳጎን ቤተ ቢያኖሯት የጣኦቱ ምስል ወቆድ ተሰበረ ይባላል (መሳ . 16 ፣ 21—30) ።

269 መወድስ

ዘተክለ ጽዮን (አለቃ)

በሰሚዐ ቃሉ ለሳውል ቢጸ ኤርምያስ
ሠለስተ አክራመ ኢነትገ አንብዕነ ፣
ለዝኒ ብካይ ሀገረ ሳውል ኢኮነ
ነግደ ወፈላሴ ፤
እስመ ሰብእ ቤቱ ለብካይ ንሕነ ፣

ቀዳሚ ኀበ ለመድነ
በላዕለ ትካዝ ትካዘ ወበላዕለ ኀዘን ኀዘነ ።
ሶበሂ ተዘከርናሃ ለደብረ ሊባኖስ እምነ
ሀየ ውስተ አፍላጋ ነበርነ ወበከይነ ፣
እስመ ማየ ዕድሜነ ኀልቀ ከመ ንዘረው ዙልነ
መንፈቅነ በምዕራብ ወበውስተ ምሥራቅ መንፈቅነ ።

ት ር ጉ ም

የኤርምያስ ጓደኛ የሆነ የሳውልን (የጳውሎስን) ቃል
በመስማት ሶስት ዘመን እንባችን አልጎደለም (አላቋረጠም)፣
ለዚህም ልቅሶ/የጳውሎስ አገር እንግዳና
ፈላሻን አልሆንም ፣
የልቅሶ ቤተ ሰቦች ነንና ፣
በትካዜ ላይ ትካዜን
በአዘንም ላይ አዘንን ቀድሞ ከለመድን ዘንድ ።
እናታችን/ ደብረሊባኖስንም በአሰብናት ጊዜ
በዚያ በወንዞች ተቀመጥንና አለቀስን ፤
እኩላችን በምእራብ እኩላችንም በምስራቅ ሁላችን
እንድንበተን ውሃ/እድሜያችን አልቋልና ።

ም ስ ጢ ር

አለቃ ተክለ ፅዮን በሃይማኖት ምክንያት እየተከሰሱ ተጉላል ተዋል ። በሁዋላም ከነጓደኞቻቸው ከኢትዮጵያ ውጭ ተሰደው ሄደዋል። ቅዱስ ጳውሎስ «ሶስት አመት ሙሉ እንባየ አላቋረጠም» እንዳለ አለቃ ተክለ ፅዮንም በኢትዮጳያ ሳሉ በሃይማኖት ምክንያት እየተ ከሰሱ የተጉላሉትን መጉላላትና ያዘኑትን አዘን ያነቡትንም እንባ አስታውሰው በውጭ አገር ሳሉ በደብረ ሊባኖስ ትዝታ መመሰጣ ቸውን በቅኔያቸው ምስጢር ቀርፀዋል ። በተጨማሪም ውሃ ወርዶ ወርዶ እንደሚያልቅ እድሜያቸው በስደትና በስቃይ ማለቁን ቤተ ሰብም አሳዳሪውን እንደሚለምደውና እንደማይፈራው ፣ እርሳቸውም በአገራቸው የለመዱትን መከራና ስቃይ በውጭም አገር የማይሰ ቀቁት መሆናቸውን በማመልከት ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

270 መወድስ

ለመኑ ሐለየ እግዚአብሔር
ተድላ ዓለማት ዓለመ እምድኅረ ፈጠረ ለነ?
አኮኑ ኀድግዎ ወመንንዎ ይብለነ ፡
ወቦኑ ለእንስሳት
ዘከረ ለሊሁ ወሐለየ ብነ ?
ቅድመ ኢሳይያስ ነቢይነ
ውስተ አእምሮ አግን አምጣነ እንስሳት ይኄይሱነ ።
ዓለምሂ ለእመ ተርፈ ኢያኅዝነነ
አምጣነ ኅሳር ወቅጥቃጤ ፍኖተ ሰናክሬም ዓለምነ ፤
ወመፍትው እግዚእ ዓለመ ከመ ያኅድገነ
አምጣነ ለሊሁ መቅድመ ዅሉ ዓለምነ ወርስትነ ።

ት ር ጉ ም

እግዚአብሄር ለግን አሰበ ?
የአለምን ደስታ/ አለም ለእኛ ከፈጠረ በውዋላ
«ተውትና ናቁት ይለናልና»
በእውኑ (በእውነቱ) ለእንስሶች
አስታወሰና አሰበን ?
በነቢያችን ኢሳይያስ ፊት
በእውነተኛ እውቀት እንስሶች ይበልጡናልና ።
አለምም ቢቀር አያሳዝነንም
የሰናክሬም መንገድ/አለማችን አሳርና ቅጥቅጣት ነውና ፤
ጌታም አለምን ያስተወን ዘንድ ተገቢ ነው
«ኃርሱው ከሁሉ በፊት አለማችንና ርስታችን ነውና» ።

ም ስ ጢ ር

«እንዳያማህ ጥራው ፡ እንዳይበላ ግፋው» እንደሚባለው አንዳንድ ሰው ሙሉ ተስፋ ከሰጠ በሁዋላ ወደሁዋላ ይላል (የሰጠውን ተስፋ ሳይፈፅም ይቀራል) ። እንዲሁም እግዚአብሄር ይህን አለም ለሰዎች መጠቀሚያ አድርጎ ከፈጠረ በሁዋላ ሰዎች አለሙን እንዲተውት ያዝዛል ። ነቢዩ ኢሳይያስ «አህያ ጋጡን አወቀ ፡ ላምም የጌታውን ቤት አወቀ ፡ እስራኤል ግን አላወቁኝም ፡ አልተረዱኝም» እንዳለ በተፈጥሮው ከእንስሳት የበለጠ ሰው በእንቢተኛነቱ ከእንስሳት ስላነሰ እግዚአብሄር አለሙን ለእንስሶች ብቻ መጠቀሚያ ሊያደርገው አሰበን ? በማለት ደራሲው ራሳቸውን ጠይቀዋል ። በተጨማሪም ከተባያማ እርሻ ተባይ የሌለበት እርሻ እንደሚመረጥ ይህ ብዙ ችግር ያለበት አለም ቢቀር የማያልፍ አለምና ርስታችን ራሱ አምላካችን ስለሆነ በርሱ እንኖራለን በማለት ባለቅኔው እምነታቸውን በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

271 መወድስ

ዘደለለ (መሪጌታ ፡ ዘዋሸራ)

መሥዋዕተ መድኀኒት ሰይፍ ለእመ ተሥዐ
በደሙ ቤዘወ ሕያዋነ ወሙታነ ፤
እስመ በደሙ አብጠለ ዘሞተ ይስሐቅ ሥልጣነ
ድኅረ ልብሰ ሥጋ ወኮነ ከማነ ፡
ንሕነሂ ዘኢሀሎነ
ተዋሕዶተ በግብጽ ዘሥላሴሁ ኢርኢነ ።
ሞተ ሰይፍሂ በርስተ ሥጋ ዘኢነጸርነ ነጸርነ ፡
ለቃል እንቲአሁ ለሥጋ አምጣነ ኮነ ።
ወሥኑ ለሰይፍ ወርነ ሰማያት ከደነ
በሰማይ እስመ ፈጠረ ጽልመተ ወብርሃነ ።

ት ር ጉ ም

የመዳኛ መስዋእት/ ሰይፍ ቢሰዋ
ህያዋንንና ሙታንን በደሙ አዳነ ፤
ስጋ ከለበሰና እንደኛ ከሆነ በሁዋላ
የይስሀቅ ሞት/ ስልጣንን በደሙ አጥፍቷልና ፥
የሌለን እኛም
በግብፅ የሶስትነቱ ምስጢር አንድነትን አላየንም ።
በስጋ ርስት ግን ያላየነውን የሰይፍ ሞት አየን ፤
ለቃል የሆነው ለስጋ ሆኗልና ።
የሰይፍም ውበቱ የሰማየት ጨረቃን ከደነ (አለበሰ) ፤
ጨለማንና ብርሃንን በሰማይ ፈጥሯልና ።

ም ስ ጢ ር

አብርሃም ልጁን ይስሀቅን ለእግዚአብሄር ሊሰዋበት የቃጣው ሰይፍ ደም ተቀብቶ በመገኘቱ ይስሀቅ ከመሰዋት ዳነ ። ክርስቶስ ስጋን ለብሶ እንደእኛ ሰው እንደሆነ የአብርሃም ሰይፍ የሰማያዊ በግ አንገትን በይስሀቅ ፈንታ ቆረጠ ። የእግዚአብሄር ቃል ርስት (እምላ ክነት) የስጋ ገንዘብ እንደሆነ ይስሀቅ እንዳይሰዋ ከሰማይ ቃል ተሰማ። ብርሃንም ሰማይን እንደሚያደምቀው በአብርሃም ሰይፍ የታየ ደም በሰማይ ጨረቃ ታየ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

272 ሕንጺሃ

እንከ ቀራንዮ ኢይበጽሕ እግዚእነ ፤
እስመ ቀራንዮ ምድረ ደም ኮነ ።

ት ር ጉ ም

እንግዲህ ጌታችን ቀራንዮ አይደርስም ፤
ቀራንዮ የደም ምድር ሆኗልና ።

ም ስ ጢ ር

ደመኛ ያለው ሰው ደም ወደፈሰሰበት ቦታ መሄድ ያስፈራ ዋል ፤ እንዲሁም ደሙ በቀራንዮ የፈሰሰ ክርስቶስ በዚያ እንደሞተ አለመቅረቱና ከመቃብር መነሳቱ በቅኔው ተመስጥሯል ።

327 መወድስ

ዘነሩይ (አለቃ)

ሞተ ፍጡራን ተምህረ ገቢረ ትሕትና
እንቃዕዲዎ ኢይርአይ ገጸ አረጋዊ በዐይኑ ፤
ባሕቱ ይብለን ውስተ ደብረ ዳሞ መካኑ ።
እንበለ ውእቱ አረጋዊ
ሥጋ ሰብእ ለቢሶ ዘሞአኒ መኑ
ንንግር ወንዜኑ ፤
ከመ ከመ ሊቁ ኤልያስ ለአረጋዊ መጠኑ ።
ለሕያውኒ ገብረ ክርስቶስ ላእካነ ምስጢር ኮኑ
ካህናተ ሰማይ ሕማማት መንበረ ሥጋሁ ዘየዐጥኑ ፤
ወእምሐዋርያት ገድላት እሰ ተአመኑ
ዮሐንስ ዕዜ ሥጋ ዘረፈቀ ውስተ ሕፅኑ ።

ት ር ጉ ም

ቀና ብሎ የሸማግሌ ፊትን በአይኑ
እንዳያይ የፍጡራን ሞት የትህትና ስራን ተማረ ፤
ነገር ግን በደብረ ዳሞ ቦታው ውስጥ
ያለዚያ አረጋዊ
«የሰው ስጋ ለብሶ ያሸነፈኝ ማን ነው ?» ይለናል ፤
የአረጋዊ መጠኑ
እንደ ሊቁ / ኤልያስ እንደሆነ እንናገርና እናወራ ዘንድ።
ስጋ / መንበሩን (ዙፋኑን) የሚያጥኑ ህማሞች / የሰማይ
ካህናትም ።

ለሀያው አምላክ/ገብረ ክርስቶስ የምስጢር መላክተኞች ሆኑ።
ከታመኑ ከሀዋርያት / ገድሎችም
የስጋ ትል / የሀንስ በጭኑ የተቀመጠ ነው ።

ም ስ ጢ ር

ትሁት የሆነ ልጅ የሽማግሌን ፊት ቀና ብሎ ማየት አይደፍርም ። እንዲሁም የስጋ ሞት የደብረ ዳሞ ገዳም አበምኔት የነበሩ አቡነ አረጋዊን አላገኛቸውም ። ስለዚህም ዲያብሎስ «ስጋ ለብሶ ያሸነፈኝ ይህ ማን ነው?» እንዳለ ሞትም ስጋ የለበሰውን ሁሉ ሲያሸንፍ አቡነ አረጋዊን አላሸነፈም ፤ የደቀ መዝሙር መጠኑ እንደ መምህሩ መጠን እንደሆነ አቡነ አረጋዊ እንደ ነቢይ ኤልያስ በሀይወት ይኖራሉ ። የሰማይ ካህናትም የአምላክን ዙፋን እንደሚያጥኑ ህግሞች የገብረ ክርስቶስን ስጋ በሉት ። ከሀዋርያትም አንዱ ዮሀንስ በክርስቶስ አጠገብ እንደተቀመጠ ትል በገብረ ክርስቶስ አካል ላይ ተርመሰመሰ ይላሉ ባለቅኔው ።

274 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ትቤ አራት እቤርተ ዓለም ማሳኒ
መፃጉዕ ወልድየ ከመ ጾርኩከ ጹረኒ ።

ት ር ጉ ም

የሚጠፉ አለም ባልቴት/ አልጋ
«መፃጉእ ልጄ ! እንደተሸከምሁህ ተሸከመኝ» አለች ።

ም ስ ጢ ር

ጡረተኛ ባልቴት በእግሯ መሄድ ሲሳናት የሚጦራትን ልጅዋን «ልጄ ሆይ እንግዲህ አዝዬ እንዳሳደግሁህ እዘልኝ እንጂ ምን ይደረጋል» ትለዋለች ። እንደዚሁም ሁሉ የባልቴቲቱ ምሳሌ አልጋን ሰላሳ ስምንት አመት የተኛባት በሽተኛ ድኖ ተሸክሟት ወደቤቱ መሄዱን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

275 ዘአምላኪየ

ውስተ ደብረ ምስጢር ታቦር እመ ትሬኢ ደመና
ኢይምሰልከ ሙሴ ዘይወርድ መና ፤
ደመና ታቦር ፍሉጥ አኮኑ እምደመና ደብርከ ሲና ።

ት ር ጉ ም

በምስጢር ተራራ ታቦር ደመናን ብታይ
ሙሴ ! መና የሚወርድ አይምሰልህ ፤
ሲና ከተባለ ተራራህ ደመና የታቦር ደመና የተለየ ነውና ።

ም ስ ጢ ር

ቀድሞ በደብረ ሲና የታየው ደመና ለእነሙሴ የሰማይ መናን የሚያዘንብላቸው ሲሆን ፡ በደብረ ታቦር በሙሴና በኤልያስ በሀዋርያትም ፊት የታየው ደመና «ይህ ልጄ ነውና እርሱን ስሙት» የሚል የወልድን ነገር የሚያሰማ በመሆኑ ባለቅኔው ሙሴን ደመና ባየ ቁጥር መና ይወርድልኛል እያለ የሚጓጓ አስመስለው ተቀኝ ተዋል ።

276 ሥላሴ

ዘበትረ ጊዮርጊስ (እጨጌ)

በዘመን ቀዳማዊ
አመ ምግበ ሙሴ ወሚካኤል
አሠረ ቀዳሚ ኢቀጽአ ዘአሪቶሙ ሰኩና ፤
ወኢያፍለጠሙ በካልእ ፍና ፤
በምግበ ገብርኤልሰ ክረምተ ቃሉ ደመና

ሶበ ዘበጠ ዝናመ ዜና
መሬት አገየ አምላክና
ወአምላክ ፈረየ ሰብእና

ት ር ጉ ም

በቀድሞ ዘመን
በሙሴና በሚካኤል ሹመት ጊዜ
የአሪታቸው ተረከዝ የመጀመሪያ ዱካን (ፍለጋን) አል
ቀረፀም ፣
በሌላ መንገድም አልለያቸውም ፤
በገብርኤል ሹመት / የቃሉ ደመና ከረምት ግን
ዝናብ / ወሬ በመታ (በጣለ) ጊዜ
መሬት አምላክነትን አበበ ፣
አምላክም ሰው መሆንን አፈራ ።

ም ስ ጢ ር

ሙሴና ሚካኤል እስራኤልን እየመሩ በመገቡበት (በአስተዳ ደሩበት) ዘመን አንበሳ የእግሩ ርግጫ ዱካን (ፍለጋን) እንደሚያ ጠፋ የሙሴ ሁኔታ በሚካኤል ፣ የሚካኤልም ሁኔታ በሙሴ አልተ መለከተም ነበር ። በገብርኤል ቃል ምግብና (ማገልገል) ጊዜ ግን በከረምት ደመና ጠል የረካ የመሬት ተክል አበባን እንደሚያብ ብና ዝሪቱም (ሰብሉ) እንደሚያፈራ ከመሬት የተፈጠረው ሰው አምላክነትን ፣ አምላክም ሰው መሆንን ተገናዘቡ (ገንዘብ አደረጉ) ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

277 ሥላሴ

ዘእንግዳ ወርት ጎይሱ (አለቃ)

በቀለ ቀዳማዊ
በአፍአ አጥፍኡ እማእከሎሙ
አርዌ ምድር ወቶማስ ክልኤቱ ዘተባእሱ በዜና ፣

ወሞእዎ ዓዲ ለእኩይ ሕሊና ፤
ላዕለ አርዌ ምድር ቶማስ እደዩ ከመ ኢያንሥእ በፍና
አእዳው ለቶማስ እስመ ኢኮና ፣
ወኢይዕቀብ አርዌ አእጋረ ጊዜ ጽሙና
ኢሀለዎ ለቶማስ ሰኩና ።

ት ር ጉ ም

በወሬ የተጣሉ
ሁለቱ ቶማስና የምድር እባብ
የቀድሞ በቀልን (ቂምን) በመካከላቸው አጠፉ ፣
ዳግመኛም «ክፉ አሳብን አሸንፉ» ፤
በምድር እባብ ላይ ቶማስ እጁን በመንገድ እንዳያነሳ
እጆቹ ለቶማስ አልሆኑምና ፣
እባብም እግሮችን በድካም ጊዜ እንዳይጠብት (እንዳይ
ነድፍ)
ለቶማስ ተረከዝ የለውምና ።

ም ስ ጢ ር

በመሬት ተጣልተው የኖሩ ሁለት ሰዎች ሲታረቁ «እንተም በእገሌ ይዞታ የሚያገባህ የለም ፣ እንተም ደግሞ ከእገሌ ይዞታ ምንም የለህ ፤ ስለዚህ ቂም በቀላችሁን ተዉ» ይባላሉ ። እንዲሁም አዳም የእባብን ራስ በበትር እንዲቀጠቅጥና እባብም ተረከዙን እን ዲነድፈው በተደረገው መሰረት በሰውና በእባብ መካከል ያለው ቅራኔ በቶማስ ሁኔታ ለእባብ ጠፋለት ። ቶማስ እባቡን በእጁ በትር እንዳይቀጠቅጠው እጆች የሉትም ፣ እባብ ደግሞ እግሩን እንዳይነ ድፈው የቶማስ እግሮቹ ተቆርጠዋል ። ስለዚህ «ሲስኑ ይሰለቡ» እንዲሉ ባለመቻላቸው ብቻ ከአንገት በላይ ቶማስና እባብ ተስማሙ ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

278 መወድስ

እልቦ ለሰብእ እንተ ይፈድዮ
ሀየንተ ሠናይ ሠናየ እንበለ እኪት ወሙስና ፤
ወምሳሌ ዝንቱ ነገር ከመ ኢይትርፍ በዜና
ድኅረ ተከለሱ በብሩህ ደመና
እስራኤል መገብተ ሲና
እስመ ላዕለ ክርስቶስ መከሩ ሀየንተ ዘበልዉ መና ።
ሠናያትሰ ለሠናያን እመ በፍትሐ ጽድቅ ኮና
ላሕም ፍዳ ጸግሁ እምጸግበ ወይነ ቃና ።
ወለሳምናዊት ዘመን እመ ይበጽሕ መጠና
ፍቅር ቀጸላ ርእስ ተኅድፈ በሰኰና ።

ት ር ጉ ም

ከክፋትና ከጥፋት በቀር ለሰው
በመልካም ፈንታ መልካምን የሚከፍለው (የሚመልስ ለት) የለም ፤
የዚህም ነገር ምሳሌ በወሬ እንዳይቀር
በብሩህ ደመና ከተጋረዱ በሁዋላ
የሲና መጋቢዎች እስራኤል
መና ስለበሉ ፈንታ በክርስቶስ ላይ መክረዋልና ።
መልካሞችስ ለመልካሞች በእውነት ፍርድ ቢሆኑ
ላም በድካሙ ብድራት (ፈንታ) የቃና ወይንን በጠገበ ነበርና ።
የስምንተኛዋ ዘመንም ልኳ ቢደርስ
የራስ መሸፈኛ/ ፍቅር በእግር ተረከዝ ተጣለ ።

ም ስ ጢ ር

የበጎ አድራጎት ብድራት በጎ አድራጎት ሲሆን«እህል ላበደረ አፈር» እንዲሉ ፥ የበጎ አድራጊው ክፍያ ክፉ ስራ ሆነ ። እስራኤል

አምላካቸው ደመና ጋርዶ የሰማይ መና እየመገበ ከጠላቶቻቸው ጭቆና ቢያወጣቸው «በደጋ ቢሆን ነው እንጂ በበረሃ ቢሆን የሰማይ መናን ማዝነብና የአለት ውሃን ማፍለቅ አይቻለውም ነበር» አሉ ። በተጨማሪም መልካም ስራ ለሰሪው ቢሆን ፥ በብርድ ቀን በትንፋሹ ያሟሟቀው እንስሳ ስለበጎ አድራጎቱ የወይን መጠጥ ሊታደል (ሊጋበዝ) ይገባው ነበር ። ግን አልተደረገም ። ይህ ሁሉ የሆነው የራስ ባርኔጣ በነፋስ እንደሚወድቅ ፥ በስምንተኛው ሺህ ፍቅር ቢጠፋ ነው በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

279 ዋዜማ

መራጒተ ሞት አወፈዮ
ለፀሐይ ብሩህ እደ ኤርምያስ መድኅን
ከመ ንስማዕ ውስተ መቃብሩ ድምፀ ኤልሳዕ ቀርን ።
ወበሳድሳይ ወርኀ ድኅረ ፅንሰ ዮሐንስ ዐይን
ኀበ አሐቲ ሀገር ገጸ ዕውራን
ተፈነወ ገብርኤል ብርሃን

ት ር ጉ ም

የኤልሳአ ነጋሪት ድምፅን
በመቃብር ውስጥ እንሰማ ዘንድ ለበራ
ፀሀይ/ የኤርምያስ እጅ አዳኝ የሞት መክፈቻዎችን ሰጠው።
ከዮሀንስ ፅንስ/ አይን በሁዋላም በስድስተኛው ወር
ወደአንዲት አገር/ የእውሮች ፊት
ገብርኤል/ ብርሃን ተላከ ።

ም ስ ጢ ር

ለኤርምያስ መራሁትን (መክፈቻ ቁልፎችን) እንደሰጠው አዳኝ ጌታ ለፀሀይ የሞትን መክፈቻ ሰጠው ማለት ፀሀይ የክርስቶስን እርቃን ለመሸፈን ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ ጨለመ ማለት

ነው ። ቅዱስ ገብርኤልም ኤልሳቤጥ በፀነሰች በስድስተኛው ወር
ወደገሊላ ሄዶ ማርያምን «በድንግልና ትወልጃለሽ» ብሎ እንዳበሰ
ራት ለንጊኖስ የተባለ አንድ አይና ወታደር የክርስቶስን ጎን በጦር
ቢወጋው የደሙ ፍንጣቂ የነካው እውሩ አይኑ በራለት ማለት በቅ
ኔው ተመስጥሯል ።

280 ሥላሴ

ዘክብቱ (ወታቢ ሰዓት)

መንግሥተ ሰማይ
ጎቤሁ ለጴጥሮስ እንዘ ቅርብት
ኢነጸረ ጴጥሮስ ኪያሃ ተሥዕሎተ መልክአ ብርሃን
እስከ ተፈጸመ በታቦር ማሕፀን ፤
ከመሰ ኢንበል እመ ይቀርብ መካን
ነጽሮ ቅሩበ ኢይሰአን ፡
ቀራንብት ለዐይን እንዘ ቅሩባን
ቀራንብተ ኢይኔጽር ዐይን ።

ት ር ጉ ም

መንግስተ ሰማይ
ወደጴጥሮስ የቀረበች ስትሆን
የመልክ ብርሃን መሳል በታቦር ማህፀን
እስከ ተፈፀመ ድረስ ጴጥሮስ እሷን አላየም ፤
ቦታ ቢቀርብ ቅርብ ማየት
አይሳንም እንዳንል ግን ፡
ቅንድቦች ለአይን ቅርቦች ሲሆኑ
ቅንድቦችን አይን አያይም ።

ሰዎች በፍቅር ቅርበት እንጂ በቦታ ቅርበት ሊጠያየቁና ሊተያ
ያዩ አይችሉም ። እንዲሁም ቅዱስ ጴጥሮስ የመንግስተ ሰማይ መክ
ፈቻ የተሰጠው ሲሆን ዝጎን ከፍቶ ሊገባባት አልቻለም ። የአካል
ቅርፅ በማህፀን እንደሚፈፀም ጴጥሮስም የመንግስተ ሰማይ በር
አርአያን በደብረ ታቦር አየ እንጂ ፡ በቦታ መቅረብማ ማየት
ከተቻለ አይኖች ቅንድቦችን ያዩ ነበር በማለት ቅኔው ተመስጥሯል።

281 ሥላሴ

ዘገብረ ሥላሴ (መምህር)

አእላፍ የሐምይዎ
ለኪሩብ ካህን እንዘ ንጹሕ
ከመ እምኔሁ ተወልደ በሥጋ ተክለ ሃይማኖት መድኀን
ለውእቱ እስመ ይመስሎ በመልክአ ወሥን ።
ወትእምርተ ዝንቱ ተረክበ በጎበ ተክለ አብ ሕፃን
እመንገለ ፀጋም ወየማን ፡
ወከመ ኪሩብ ቀሲስ በሊሐ ልሳን ፤
ወመጠኑ ዘኪሩብ መጠን ።

ት ር ጉ ም

አዳኝ ተክለ ሃይማኖት
በስጋ ከርሱ እንደተወለደ
ንፁህ ሲሆን ኪሩብ ካህንን ወገኖች ያሙታል ፤
በመልክና በደም ግባት እርሱን ይመስለዋልና ።
የዚህ ምልክትም በስተግራና በስተቀኝ በኩል
በተክለ ሃይማኖት ህፃን ዘንድ ተገኝቷልና ፡
እንደ ኪሩብ ቄስም አንደበተ ርቱእ ነውና ፤
ልኩም የኪሩብ ልክ ነውና ።

እንዳንድ ካህን ንፁህ ሆኖ ሳለ ወገናቹ ካህናት « የእገሌ ልጅ የርሱ ዲቃላ ነው በመልኩም በደም ግባቱም ፣ በእነጋገሩም በቁመቱም ይመስለዋል ፤ ይህ ቀረህ አይባልም » እያሉ ያሙታል ። እንዲሁም ፃድቃን የህፃኑ ምሳሌ የሆነውን ፃድቅ ተክለ ሃይማኖትን መልአክ ሳይሆን እንደ መልአክ ያዩታል ። ምክንያቱም ኪሩብ እንደሚባለው መልአክ በግራና በቀኝ ክንፎች ስላሉትና እንደኪሩብም አመስጋኝ ስለሆነ ነው በማለት ባለቅኔው ያስረዳሉ ።

282 ሥላሴ

ዘመን ጎዳጌ ሁሉ ፣
ወመንሥኤ ሁሉ ድኅረ ድቀት ፤
ተዋልጦ ንዴት ወብዕል ባሕቱ እንዘ ይሬኢ በዐይን
ባዕል በብዝኀ መዝገቡ ዘአልቦ ወሰን
ትምክህተ ልቡና ኢይግበር ፣ ወበንዴቱ ምኑን
ነዳይ ኢይብኪ ወኢይኅዝን ፤
አምጣነ ዘመን ያቴሕት ቤተ ብዑላን ፣
ወነዳየ ያነሥእ ዘመን ።

ትርጉም

ሁሉን የሚጥል ዘመን ነው ፣
ከውድቀት በሁዋላም ሁሉን አንሽ ዘመን ነው ፤
ነገር ግን የችግርና የሀብት መለዋወጥን በአይን ሲያይ
ባለፀጋ ወሰን በሌለው ሳጥን ብዛት
የልቡና ትምክህትን አያድርግ ፣ በተናቀ ችግሩም
ድሃ አያልቅስ አይዘንም ፤
የባለፀጎች ቤትን ዘመን ያዋርዳልና ፣
ድሃንም ዘመን ያነሳልና ።

ሽማግሎች ሲመርቁ « ዘመን ይስጥልኝ » ይላሉ ። አዝር እትና አትክልት የማበብ ፣ የማፍራትና የመድረቅ ጊዜ እንዳላቸው ለልማትና ለጥፋትም ጊዜ አላቸው ። ስለዚህ ነው ባለቅኔው «የሚጥልም ፣ የሚያነሳም ዘመን ነው» ማለታቸው ። ማጣትና ማግኘት እንደዘበኞች ሲፈራረቁ ስለሚኖሩ ፣ ባለፀጋው በሀብቱ ሊተማመንና ድሃውም በማጣቱ ተስፋ ሊቆርጥ አይገባውም ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

283 መወድስ

ዘጎይሌ (አለቃ)

ማየ ዮርዳኖስ ተስዕረ እግዕርገ ጣዕሙ ፤
እንዘ ቤተ ክብካብ የሐውር አምጣነ ሰክረ በወይን
ወምርዐተ ገብረ በዘሊቀ ምርፋቅ ልሳን ፣
ወእንበለ መጠን ለእመ ሰክረ
ወድቀ በላዕለ ስድስቱ መሳብክት ዘእብን ፤
እእላፈ እስራኤል ጣዕማተ ወይን
አምጣነ በማይ ፈተነ ሕያወ ባሕርይ ጌዴዎን ።
ማይሂ ለእመ ሞተ ማእከለ መሳብክት ሁሎን
በወይን ጎዚቦሙ ቀበርዎ ጽሙዓን ፤
ወለፍትሐተ ማይ ሖረ ወይነ ቤተ ቃና ካህን
መዝሙረ ጣዕሙ ከመ ያንብቡ ሰብእ ቤተ ቃና መዘምራን።

ትርጉም

የዮርዳኖስ ውሃ /ካህን ከጣሙ/ ማእረግ ተሻረ ፣
ወደ ሰርግ ቤት ሄዶ በጠጅ ሰክሯልና
በመቀመጫ አለቃ እንደበትም መዳራትን አድርጓልና ፣
ያለመጠንም ቢሰክር
በስድስቱ የድንጋይ ጋኖች ላይ ወድቋልና ፣

የእስራኤል ጦረኞች የወይን ጣሞችን
አምላክ/ ጌዴዎን በውሃ ስለፈተነ ።
ውሃም በሁላቸው ጋኖች መካከል ቢሞት
የተጠሙ ሰዎች በወይን ጠጅ አጥበው ቀበሩት ፤
የቃና ቤት ሰዎች /መዘምራንም መዝሙር/ ጣሙን
ያነቡ ዘንድ የቃና ቤት ወይን/ካህን ለውሃ ፍታት ሄደ ።

ም ስ ጢ ር

በሰርግ ቤት ወይን ጠጥቶና ሰክሮ ሲዳራና በየድንጋዩ ላይ እየ
ወደቀ የተገኘ ካህን ከስልጣኑ ይሻራል ። እንዲሁም የካህኑ ምሳሌ
በስድስቱ የድንጋይ ጋኖች የተሞላው ውሃ ወደ ወይንነት ስለተ
ለወጠ የውሃነቱ ጣም ቀረ ። ጌዴዎን የተባለው የእስራኤል መስ
ፍን የእስራኤልን ጦረኞች በዮርዳኖስ ውሃ እንደፈተናቸውና ንቁ
ዎቹን በዚህ ፈተና ለማወቅ እንደቻለ ክርስቶስ የውሃን ጣም
የወይን ጣም አደረገው ። የሞተውንም በድን በውሃና በቅጠል እን
ደሚያጥቡት የጋኑ ውሃ ወደ ወይንነት ተለውጠላቸው የተጠሙ
ሰዎች ጠጡት ።

ደብተራዎች ዳዊት እየደገሙ የሞተውን ሰው እንደሚፈቱት
የቃና ሰርግ ቤት ሰዎችም ወይኑን ሲጠጡት ጣሙን አደነቁ ማለት
በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

284 መወድስ

እስፍንተ ቀተልኪ ወኢቀተሉኪ
ንግሥተ ኀጣውእ ቅንአት ወለተ ቃየል ሕፃን
ወፍጎርተ ልሂቅ ኤሳው ዘሚበተ ርእሱ ተስናን ?
አኮኑ ፈጠርኪ በአጎዊሁ
ጽልመተ ቅትለቱ ለዮሴፍ ብርሃን ፤
ወእመ ሰምዐኪ ባዕዳን
ዐቃቤ አዘቅት አንበሩ ለአስካለ ኤርምያስ ወይን ፤
ዓዲ ኀበ ጸመው በሥርዐትኪ ክዱን

ክብረ ህላዌሁ ለማያዊት እንዘ ይትናገሩ አእባን ፣
ኀጠተ መና ፍትሕ ሰፈርኪ በመስፈርተ አይሁድ ልሳን
ተአስሮ አእዳው ለሥጣዕና ወተፈትሖ አእዳው ለበርባን ።

ት ር ጉ ም

የህፃን /ቃየል ልጅ የሆንሽ የሃጢአቶች ንግስት/ ቅንአት
የራሱ ሽበት ጠብ የሆነ የሸማግሌ /ኤሳውም እሎኛ የሆንሽ
ስንትን ገደልሽ ? አንችን አልገደሉሽም እንጂ ፤
የዮሴፍ/ ብርሃን
መገደል/ ጨለማን በወንድሞቹ ፈጥረሻልና ፣
ባእዶችም ቢሰሙሽ
ለኤርምያስ ወይን ፍሬ ምንጭ ጠባቂን አኑረዋልና (አስ
ቀምጠዋልና) ፤
ዳግመኛ ም በሽፍን ስርአትሽ ከደከሙ ዘንድ
የሰማያዊት ኑሮውን ክብር ድንጋዮች ሲናገሩ ፣
የእጆች መታሰር ለሆሳእና የእጆች መፈታት ደግሞ ለበር
ባን እንዲሆኑ
የፍርድ /መና ቅንጣትን በአይሁድ መስፈሪያ አንደበት
ሰፍረሻልና ።

ም ስ ጢ ር

እሎኛዋ የበዛ ልጃገረድ እሎኛዎችዋን ታጋድላለች ። እንዲ
ሁም በሀጢአቶች ላይ የሰለጠንችና ጠበኛ ኤሳውን ያገበረችው
(በወንድሙ በያእቆብ ላይ በጠላትነት እንዲነሳ ያደረገችው) የቃ
የል ቅናት ብዙዎችን ስታጋድላቸው ትኖራለች ፤ እርሱዋን ግን
ያሸነፋት የለም ። ቃየል አቤልን ፣ ኤሳው ያእቆብን ፣ ዮሴፍንም ወን
ድሞቹ እንዲበቀሉ አደረገች ።

ደግሞ ለወይን ፍሬ ጠባቂ እንደሚደረግለት ቅናት ኤርምያስን
በኩስ አዘቅት ውስጥ አስጣለች ፤ ግኡዛን (የማይናገሩ የሴትና የወ
ንድ ምልክት የሌላቸው) ፍጥረቶች ድንጋዮች እንኳ ለክርስቶስ ምስ

ጋና አቀረቡ ። ለእስራኤል የወረደ መና በመስፈሪያ እንደተሰፈረ የአይሁድ አንደበት ክርስቶስን ከማመስገን በቅናት ተከለከለ ። ቅናት መታሰርን ለክርስቶስ ፣ ከእስራት መፈታትንም ለወንጀለኛው በርባን እንዲፈረድ አደረገች በማለት ባለቅኔው የቅናትን አስከፊ ገፅታ በቅኔያቸው ምስጢር አመልክተዋል ።

285 ዕዝል ዕጣነ ሞገር

ዘድንቁ (አለቃ)

ዘራዔ ንባብ ይሰመይ ተክለ ሃይማኖት መድኅን ፤
አምጣነ ኮሞ ቃለ ለበሃማን
ወተክዕወ ዲበ ልብሱ ደመ ገጸ አቤል ወይን ፤
ወብዕለ ኪሩቤል ይሜንን
እምነ ብዑሳን ኪሩቤል ዘኮለንታሆሙ ዐይን ፤
ተክለ አብ ለውሂበ ዐይን በውኑድ ምእመን ።

አሠረ ንጉሥ

መክሊተ ዕድሜ ተለቃሕ እምኤልያስ በመድሎተ
ዕዝራ ሐሚን
ከመ ሕዝብከ ይሑሩ መንገለ ፀጋም ወይምን
ምኒልክ ሳሙኤል አኃዜ ቀርን ፤
አምጣነ አንገሥኮ ለሳኦል ፍሥሓ ዘመን ፣
ወቀተልኮ ለአጋግ ኅዘን ።

ት ር ጉ ም

አዳኝ ተክለ ሃይማኖት ነገር አባካኝ ይባላል ፤
ለዲዳዎች ቃልን (ንግግርን) ሆኗቸዋልና
በልብሱም ላይ የአቤል ፊት ወይን /ደም ፈሷልና ፣
ሁለንተናቸው አይን ከሆነ
ከኪሩቤል/ ባለፀጎች ይልቅ አይንን ለመስጠት
በጥቂት የታመነ ተክለ አብ የኪሩቤልን ሀብትም ንቋልና ።

እሰረ ንጉስ

ቀንድ (ስልጣን) ያዥ ምኒልክ/ ሳሙኤል ! ህዝብህ
ወደ ግራና ወደ ቀኝ እንዲሄዱ
በእዝራ/ ብረት ሚዛን ከኤልያስ
እድሜ /መክሊትን (ገንዘብን) ተበደር ፤
የዘመን ደስታ /ሳኦልን እንግሰኽዋልና
አጋግ/ አዘንንም ገድልኽዋልና ።

ም ስ ጢ ር

ላገኘው ሁሉ የልቡን የሚያወራ ሰው ወሬኛ ይባላል ። በእንፃሩም የድቅ ተክለ ሃይማኖት በተወለዱ በሶስተኛው ቀን በአምላካዊ ተአምራት ተናገሩ ፣ በሁዋላም ዲዳዎችን አናገሩ ። በልብስም ላይ ሽቱ እንደሚርከፈከፍበት ልብሳቸው እንደ አቤል ደም ተናገረ ። ባለፀጋም የሌላውን ባለፀጋ ሀብት እንደሚንቅበት ፣ ሁሉንተናቸው አይን ብቻ ከሆነ ከኪሩቤል ይልቅ ተክለ ሃይማኖት በሁለት አይኖች ያዩዋቸውን የአውር አይኖች አበሩ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

ከዚህም ሌላ አንድ ሰው ከሌላው ባለፀጋ በብረት ሚዛን የተመዘነ ወርቅ እንደሚበደርና ቤተሰቦቹን እንደሚያስተዳድር ፣ « ምኒልክ ከኤልያስ እድሜን በእዝራ ሚዛን ተበደር » ማለት እንደ ኤልያስና እንደ እዝራ ሀያው ሆነህ ኑር ፤ ግዛትህም በነጋሪትህ ይሰፋፋ ማለት ነው ። ሳሙኤልም አጋግን ገድሎ ሳኦልን እንዳነገሰው ፣ «እኔ ምኒልክ ! ያዘነውን ሁሉ በዘመንህ ደስተኛ አደረግኸው» በማለት ባለቅኔው ለምኒልክ ዘመነ መንግስት ያላቸውን አክብሮት በአድናቆት ገልጠዋል ።

286 ሥላሴ

ዘአስክንድር (አፄ)

ምንት አገበረክ
ቍንፅለ ገዳም አንተ ቤተ አንበሳ በዊአ ?
ኢትሰምዕኑ ጥሕረቶ በአፍአ ?

እስመ እምኀቤየሰ ተጋንዮትከ ጠፍአ
አንበሳ በኀይሉ እምድኅረ ሞአ ፤
ኀድገሰ ዘለከ ብፅዐ
ጽንሖ ለእሳት ከሞነከ ብርዐ ።

ት ር ጉ ም

አንተ የዳዳም (የዱር) ቀበሮ ፤
ወደ አንበሳ ቤት ለመግባት ምን አስገደደህ? (አስደፈረህ ?)
በውጭ አጪጪሁን አልሰማህምን ?
አንበሳ በሀይሉ ካሸነፈ በሁዋላ
ከኔስ መለማመጥህ ጠፋ እኮ ፤
እንግዲህ ወዲህስ ያለህን ምስጋና ተውና
ብር (ገለባ) ሆነህ እሳትን ቆየው ።

ም ስ ጢ ር

ቀበሮው በአንበሳ ቤት ገብቶ ከተገኘ አንበሳው ይሰባብረዋል። እንዲሁም ደቀ እስጢፋ በቀበሮው ሲመሰል አፄ እስክንድር የአንበሳው ምሳሌ ሆነዋል ። ምክንያቱም ደቀ እስጢፋ የአፄ እስክንድር ባለሟልና ጓደኛ ሲሆን በንግስቲቱ ታምታልና ። ከዚህም ሌላ እሳት የበላው ገለባ ድራሹ እንደሚጠፋም ደቀ እስጢፋ እምነቱን በማጉደሉ የነፍስ ጉዳት ጭምር ይፈረድበታል ማለት በቅኔው ተመስጥሯል።

287 መወድስ

በዐጸደ ረኃብ ያንሶሱ እግረ ተዋርዶ
አምጣነ ዳዊት አተወ መቅደሰ ውሳጤ ወአፍአ ፤
ለአዕርነ መሥዋዕት ጥዑም እንተ ለካህናት ተሠርዐ
ወሰሎሞን ጥቀ እንዘ ባዕል
እምአግብርተ ቤቱ ሰአለ መብልዐ ፤
በአምሳለ ነዳይ አልዓዛር
እስመ ተወክፈ ረኃበ እምዘርዐ ዳዊት ዘመጽአ ።
ረኃብሂ ምውተ ነፍስ እመ በሥጋ ተንሥአ

ሰማዒ እዝነ ሕፃን ነገረ ኂቆዲሞስ ኢያጽምዐ ፤
በግዕተ ዮርዳኖስ ብእሲተ ለእመ ረኃብ ሥዐ
ሕፃን እምድኅረ ልህቀ ውስተ ከርሠ እሙ አምጣነ ገብአ።

ት ር ጉ ም

የመዋረድ እግር በራብ /ቦታ ይመላለሳል ፤
ለካህናት የተሰራ ጣፋጭ መስዋእትን ለማሳረግ
ዳዊት በውጭና በውስጥ መቅደስ ገብቷልና ፥
ሰሎሞንም በጣም ባለፀጋ ሲሆን
ከቤቱ አገልጋዮች መብልን ለምኗልና ፥
በድሃ አልአዛር አምሳል
ከዳዊት ዘር የመጣ ራብን ስለተቀበለ ።
የነፍስ ሟች/ ራብም በስጋ ቢነሳ
ሰሚ የህፃን ጆሮ የኂቆዲሞስ ነገርን አላዳመጠም ፤
የዮርዳኖስ በግ/ሴትን ራብ ቢሰዋ
ህፃን ካደገ በሁዋላ በእናቱ ሆድ ውስጥ ገብቷልና ።

ም ስ ጢ ር

አንድ እረፍት የፈለገ ሰው በአትክልት መካከል እየተመላለሰ ንፁህ አየር ተቀብሎ እቤቱ እንደሚገባ ሁሉ ውርደት በራብ ምክ ያት ይመጣል ። ራብ ዳዊትን ለርሱ የማይገባውንና ለካህናት የሚገ ባውን መስዋእት እስከ መብላት አደረሰው ። በጣም የበለፀገ ሰሎሞ ንን እንኳን ድንገተኛው ራብ ከቤቱ አገልጋዮች መብልን አስለመ ነው ። ኂቆዲሞስ «ህፃን ካደገ በሁዋላ ወደእናቱ ሆድ ሊገባ አይች ልም » ያለው ነገር ታበለና ራብ የጠናባት እናት ልጇዋን በላች ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

ታ ሪ ክ

ሰሎሞን አንበሳ ወደብ (መፅዳጃ ቤት) ወጥቶ ሲመለስ ሌላ እርሱን ተመስሎ በዙፋኑ ስለተቀመጠበት የእልፍኝ አሽከሩ ከበር መልሶት በገዛ ከተማው ሶስት ቀን ያህል ለምኗል ይባላል ። ይህም

የሆነበት ምክንያት ከእለታቱ በአንዱ ቀን ሰሎሞን አንድ የራበው ድሃ ሲለምን አይቶ «ምንድን ነው?» ብሎ ጠየቀ ። ቤተሰቦቹም የተራበ ለማኝ ነው አሉት ። እርሱም « ራብ ምንድነው?» ብሎ ጠይቆ ነበርና እንዲቀምሰው እግዚአብሄር ይህን ችግር እንዲደርስበት አደረገ ተብሎ ይተረካል ።

288 መወድስ

በይነ ምንት ጎፍሩ ነቢያተ ሕግ ?
አምጣነ እምዓለም ተጎጥኡ ድኅረ ጸውዎ እግዚአ
እንዘ ይረድኦሙ ኤልሳዕ በነሢአ ልሕዙት ዘመጽአ ።
ወይኤዝዝ ዮሴፍ መገብተ ቤቱ
ለእስተዳልዎ ሠናየ ጽዋዐ ፤
ወከመ ያሠኒ ቤተ መርዓ
ምስለ መሰንቆሁ ዳዊት እማእከሎሙ ተንሥአ ።
በዓሎሙሂ ትንቢተ ሕግ ለእመ ኮነ ርቱዐ
ኢጎጥኡ ለተጠብሖ ላሕመ ወበግዐ ፤
ለተግይጦ ላሕም ሄኖክ አምጣነ እምገዳም ወፅአ
ወበይነ በግው ኢሳይያስ ቃለ ኢያውሥአ ።

ት ር ጉ ም

የህግ ነቢያት ስለምን አፈሩ ?
ገንቦን በመያዝ የመጣ ኤልሳእ እየረዳቸው
ጌታን ከጠሩ በሁዋላ ከአለም ታጥተዋልና ።
ዮሴፍም የቤቱን መጋቢዎች መልካም
መጠጫን ለማዘጋጀት ያዝዛል ፤
የሙሽራ ቤትንም ያሳምር ዘንድ
ዳዊት ከመሰንቆው ጋር ከመሃላቸው ተነሳ ።
በአላቸው/ የህግ ትንቢትም የተቃና ቢሆን
ለመታረድ በግና ላምን አላጡም ፤
ሄኖክ ላምን ለመግዛት ከገዳም (ከጫካ) መጥቷልና
ስለበጉም ኢሳይያስ ቃልን አልመለሰምና ።

ም ስ ጢ ር

ያላቅማቸው ጌታ ሰውን ለማብዣ የጠሩ ጋባዦች በተጠሪው ፊት ቀርበው ለመጋበዝ ያፍሩና ውጭ ለውጭ ይላሉ ። ስለወልድ ወደዚህ አለም መምጣት ሲግልዱና ሲተነቡ የኖሩ ነቢያትም ወልድ ስጋን በለበሰበት ዘመን አልተገኙም በሞት ተለዩ ። ደግሞ በድግስ ቀን የደጋሹ ረዳት መጠጡን በገንቦ እንደሚያቀርብ ነቢይ ኤልሳእ ቅድስት ማርያምን በገንቦ መስሎ ተናገረ ። ሌላውም የጠላ መጠጫ እቃ ለማዘጋጀት ቤተሰቦቹን እንደሚያዝ እርሱዋ (ማርያም) በዮሴፍ ዕዋ ተመሰለች ። የሰርግ ቤትንም ለማድመቅ ከተጋባዦች መካከል አንዱ እንደሚነሳና በመሰንቆ እንደሚዘፍን በዳዊት መሰንቆም ድንግሊቱ ተመሰለች ። ደጋሾች ሀብት ያላቸው ከሆኑ ለድግሱ የሚታረድ በሬና በግ እንደሚገዙ ትንቢታዊ ምሳሌም ልዩ ልዩ በመሆኑ ፣ ክርስቶስ በኢሳይያስ ትንቢት በሚታረዱ በሬና በግ ተመሰለ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

289 ዕዝል ክብር ይእቲ

ሚካኤል ጎዘንካ ለርጉባን መጠነ ዓመታት አርብዓ ፤
ወበተአዝዞ ከረይከ መቃብረ ሙሴ ጎቡአ ።
ባዕልሰ ይትፈሣሕ ሶበ ዜና ረታብ ሰምዐ ፤
ወመቃብረ ይከሪ ለወርቁ እንዘ በድነ ቢጹ በአፍአ ።

ት ር ጉ ም

ሚካኤል ! ለተራቡ አርባ አመታት ያህል አዘንህ ፤
በመታዘዝም ድብቅ የሙሴ መቃብርን ቆፈርህ ።
ባለፀጋ ግን የራብን ወሬ በሰማ ጊዜ ይደሰታል ፤
የጓደኛው በድንም በውጭ ሳለ ለወርቁ መቃብርን ይቆፍራል ።

ም ስ ጢ ር

ቅዱስ ሚካኤል እስራኤልን በሙሴ አማካይነት ከግብፅ አውጥቶ እየመራቸውና መናን እየመገባቸው አርባ ዘመን ሙሉ አብሯቸው እንደተጓዘ ፣ አንዳንድ ርሀሩህ ሰው ብዙ ጊዜ ራብተኞችን ሲያበላና ሲያጠጣ የሞተውንም ወሰንተኛ (የሌላ አገር ሰው) ሲቀ ብር ይኖራል ። ሌላው ጨካኝ ግን ዘመኑ የራብ ዘመን ሲሆንለት ብርን ለማፈስ ይደሰታል ፤ ድሃውም በራብ ሞቶ በድኑ በውጭ ወድቆ እያየ ፣ የሞተውን ድሃ በመቅበር ፈንታ ወርቁን በመሬት ውስጥ ይቀብራል በማለት ባለቅኔው የባለፀጎችን ጭካኔ በቅኔያቸው ምስጢር አመልክተዋል ።

290 መወድስ

ገሠጽኮ ለዮናስ በቀስታመ ባሕር
ጎበ ኢዘርዐ ስብከተ ጎጠተ ቃሉ ዘራዊ
በምድረ ነነዌ ፀርከ በገራሀተ እዝና ሰማዒ ፣
ወበቃለ ረኃብ ተዛለፍኮ
ለዘኢጎዘነ ኤልያስ ቀናኢ
በእሳተ ረኃብ እንዘ ያውዒ
ዙሉ ገጻመ ቤተ አክዓብ ገፋዒ ፤
አኮኑ አምላከ ፍቅር ! እንዘ ነደ እሳት በላዒ
ትቄርር ከመ ማይ ድንጋፄ ጎጥአን ሶበ ትራኢ ፣
ለገብርከኒ ዓለም በበትረ መከራ በቋዒ
ተግሣጸ ውሉድ ትጌሥጾ ወኢትራእዮ ከመ ጸላኢ ።

ት ር ጉ ም

በጠላትህ /ነነዌ ምድር ሰሚ
ጆሮዋ/ እርሻ የዘራ ቃሉ ቅንጣት/ ስብከትን
ካልዘራ ዘንድ ዮናስን በዱላ /ባህር ቀጣኸው ፣
ገፊ የሆነ የአክአብ

ወገን /ጫካውን ሁሉ
በእሳት /ራብ ሲያቃጥል
ያላዘነ ቀናተኛ ኤልያስንም በቃል/ ራብ ዘለፍኸው ፤
የፍቅር አምላክ ! አቃጣይ የእሳት ነዲድ ስትሆን
የሀጢአተኞችን ድንጋጤ ስታይ እንደውሃ ትቀዘቅዛለህና፣
አገልጋይህ/ አለምንም በጠቃሚ መከራ /በትር
የልጆችን ቅጣት ትቀጣዋለህና እንደጠላትም አታየውምና።

ም ስ ጢ ር

እርሻ አርሶ ዘር እንዲዘራ ያዘዘው አንደኛው ልጁ ትእዛዙን ሳይፈፅም ሲቀር አባቱ ተቆጥቶ በሽመል ይመታዋል ፤ ደግሞ በሬዎቹን ውሃ እንዲያጠጣቸው ያዘዘው ሌላው ልጁ የታዘዘውን ሳይፈፅም ሲቀርና እንኩቶም ሲያነኩት የጫካውን ሳር ሲያቃጥለው በቁጣ ቃል ይዘልፈዋል ።

እንዲሁም በአንፃሩ ዘር ያልዘራው ልጅ ምሳሌ የሆነው ነቢይ ዮናስ ነነዌን አልሰብክም በማለቱ በባህር ውስጥ እንዲሰጥምና በአሳ አንበሪ ሆድ እንዲዋጥ አደረግኸው ። በሬዎችን ያላጠጣው ልጅ ምሳሌ የሆነውን ነቢይ ኤልያስንም እስራኤልን በራብ ስላ ንገበገባቸውና ስላላዘነላቸው እንደህዝቡ እንዲራብና እንዲጠማ ምግቡን አስቀረህበት የሚጠግበትንም ምንጭ አደረቅህበት ። በቁጣ የተናደደውን ያህል ልጆቹ ይቅርታ እየጠየቁ ሲቅለበለቡ በት አባት ከቁጣው እንደሚበርድ ፣ በሀጢአተኞች ድንጋጤ ጊዜ መአትህን በምህረት ቁጣህን በትእግስት ትመልሳለህ ማለት በቅ ኔው ተመስጥሮበታል ።

291 ሥላሴ

ፍናዊነ ብዙኃት
በከመ ብዙኃት አህጉሪነ ፤
ባሕቱ በጽዮን እመ ይከውን ጉባኤ

አህጉር ክልኤቱ ወፍናው ክልኤ ።
ወጊዜ ምሳሓ ለጽዮን ከመ ኢንሕሚ ጸዋዔ
ሶሉ ይጼዋዕ ጊዜ ትንግኤ ፤
ባሕቱ ይከውን በዝንጋዔ
ኢበላኢ ዘትካት በላዔ ።

ት ር ጉ ም

አገሮቻችን ብዙ እንደሆኑ
መንገዶቻችን ብዙዎች ናቸው ፤
ነገር ግን በፅዮን ስብሰባ ቢሆን
አገሮች ሁለት ናቸው ፤ መንገዶችም ሁለት ናቸው ።
በፅዮን ምሳም ጊዜ ጠሪን እንዳናማ
ለትንሳኤ ጊዜ ሁሉ ይጠራል ፤
ነገር ግን በመርሳት የቀድሞ
ተራቢ በላተኛ ይሆናል ።

ም ስ ጢ ር

በዚህ አለም አገሮችና መንገዶቻቸው ብዙዎች ናቸው ። ለወዲ ያኛው አለም (ለእለተ ምፅአት) ጉባኤ ግን ሰፊ ቦታና መንገድ የሉ ትም ቦታዎቹም መንግስተ ሰማይና ገሃነም ብቻ ናቸው ፡ መንገ ዶችም ህይወትና ሞት ብቻ ይሆናሉ ። የሞተው ሰው ሁሉ መን ገድ መንገዱን ለመሄድ ቢነሳ የበላው እንዳልበላ ፤ ያልበላውም እንደበላ ይሆናል በማለት ፤ ቀድሞ በድሃና በሃብታም መካከል ይታይ የነበረው ልዩነት ከሞት በሁዋላ የሚስተካከል መሆኑን ባለ ቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

292 ሥላሴ

ሰሚዕየ ኢይሰምዓ
ለመንግሥተ ሰማይ መዝሙረ ዕንቍ
ዘአውታሪሃ ሕማም ወድኅንፃሃ ተገፍዖ ፤

እስመ ተድላ ሥጋ ለሥጋየ ሞአ ፡
ባሕቱ ጴጥሮስ ብእሴ ብዙኅ ተበፅዖ
አፍቀረ ሞተ ዘይጸልእ ፡
ወእንዘ ለድምፃ ጳውሎስ ያጸምዖ
ኢያእመረ ከመ ሰይፍ በልዖ ።

ት ር ጉ ም

አውታሯ መከራ
መቃኛዋም መገፋት የሆነ
መንግስተ ሰማይ/ የእንቁ መዝሙርን ሰምቼ አልሰማትም፡
የስጋ ምኞት ስጋየን አሸንፎታልና ፡
ነገር ግን ጴጥሮስ/ የብዙ ምስጋና ሰው
የሚጠላው ሞትን ወደደ ፤
ጳውሎስም ድምፁዋን ሲሰማ
ሰይፍ እንደበላው አላወቀም ።

ም ስ ጢ ር

አሳቡ ወደሌላ የተሰማራበት ሰው እያለ እንደሌለ ስለሚሆን ሌላው የሚጫወተውን ነገር ልብ አይለውም ። እንዲሁም የዚህ አለም ተድላና ደስታ ያሸነፈው አለማዊ መንግስተ ሰማይን ለመ ውረስ የሚያስችለውን ስራ ከመስራት ወደሁዋላ ይላል ። አሳቡ የተሰ በሰበለት ሰው ግን ጓደኛው የሚነግረውን ከመጀመሪያ እስከ መጨ ረሻ ልብ እንደሚል ፡ በመንግስተ ሰማይ ፍቅር የተነደፈ ጴጥ ሮስ በህይወት ኖሮ ከመንግስተ ሰማይ ውጪ ከመሆን ስለርሷ መሞትን መረጠ ። እንዲሁም ጳውሎስ ስለርሷ (መንግስተ ሰማይ) በሰይፍ መቆረጡን ከመቆረጥ አልቆጠረውም ይላሉ ባለቅኔው ።

293 መወድስ

ዘደስታ (ሙሀር ዋሸራ)

ኢወለጠ ብነ ጣዕመ ርኅራኄከ
ምረረ ልሳን ወአፍ ሐሞት ዘትበልዖ ፤
እስመ ለመሪር ሐሞት ጣዕመ ቃልከ አጥፍአ
ምሕረትከ እምድኅረ አዕበዮ ለዮሴፍ ተገፍዖ ።
ወአመ ግፍዕከ ይረድኦ
ለጸላኢከ ቀኖት ውስተ እዴከ አግብአ ።
አሠነይከሂ ሕብረ ገጽከ በመጽሔተ አይሁድ ተጸፍዖ
ለክሂል ነውረ ዚአከ እመኒ ኢይከልኦ ፤
ወእምርእስከ ኢውኅዘ ዘተቀባዕከ ተኰርዖ
ፀሐይ አምጣነ አልቦ እንዘ ለርእስከ ትትቀብዖ ።

ት ር ጉ ም

የምላስና የአፍ ምረት
የሆነ የበላኸው አሞት የርሀራሄህን ጣም አልለወጠብንም ፤
ምህረትህ ዮሴፍ/ መገፋትን ከፍ ካደረገው በሁዋላ
መራራ አሞትን የቃልህ ጥፍጥና (ጣም) አጥፍቶታልና ።
ግፍህም ቢረዳው
ጠላትህ ችንካርን በእጅህ ጣለው ።
መቻል/ ነውርህን ምንም ባይከለክለው የፊትህን መልክ
በአይሁድ መስታወት/ ጥፊ መመታት አሳመርህ ፤
የተቀባኸው ቅቤ/ መመታትም ከራስህ አልፈሰሰም
ራስህን ስትቀባው ፀሀይ የለምና ።

ም ስ ጢ ር

በብዙው ወተት ጠብታ ውሃ ቢቀላቀልበት የወተቱን ጣም ሊለውጠው አይችልም ። እንዲሁም ክርስቶስን አይሁድ መራራ አሞትን ቢያጠጡትም «አባት ፤ ይቅር በላቸው ፤ በግያውቁት ይሰ

ራሱና» ብሎ ለሰቃዮች ይቅርታን በመለመን ለሰው መራራቱን አልተወም ፤ በደሉንም በይቅርታው ሸፈነው ። የግፅ ንጉስም ዮሴፍን ከፍ ከፍ እንዳደረገው እንዲሁም የክርስቶስ ይቅርታው መገፋትን እንዲታገስ አደረገው ። መገፋትም ጠላትን በተገፊው እጅ እንደሚጥለው ፣ ክርስቶስም መገፋቱን መታገሱ እጆቹን በች ንካር እንዲቸነከር አደረገው ።

ፊትንም በመስታወት ተመልክቶ መልክን እንደማሳመር የክ ርስቶስም ፊቱ በአይሁድ እጅ ተፀፋ (በጥፊ ተመታ) ። የሰው ፊትም ምንም በመስታወት ቢታይ ጥንቱን በተፈጥሮው ያለበት ሳካ (ጉድ ለት) አይወገድም ። እንዲሁም ክርስቶስ ምንም በከሃዲው እጅ ቢጠ ፈጠፍ ችሎታውን በብስጭት አልቀነሰውም ። ፀሀይን ደመና በጋ ረደው ጊዜ ቅቤ የተቀባ ሰው ቅቤው ከራሱ ኢይፈስበትም ። ክርስ ቶስም በመስቀል ላይ ሳለ ራሱን በዘንግ ተመታ ፤ ፀሀይም የክር ስቶስን እርቃኑን ለመሸፈን ጨለመ በግለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

294 ሕንጺሃ

ዘደስታ (አለቃ ፣ ዘጋይንት)

የሐንስ መኑ ከማከ ?
እስመ በሰማይ ወበምድር ሀሎከ ።

ት ር ጉ ም

ዮሀንስ እንደአንተ ያለ ማነው ?
በሰማይና በምድር አለህና ።

ም ስ ጢ ር

አንድ ሰው በዚህም በዚያም ስሉጥ (ሁለ ገብ) ሲሆን «እንደ አንተ የተመቸው ማን አለ ? በሁሉም አለህበት » ይባላል ። በአን የሩም «ከሴቶች ከተወለዱ ልጆች ዮሀንስን የሚበልጠው የለም »

በተባለው መሰረት መጥምቁ ዮሀንስ በክርስቶስ ምክንያት አንገቱን ተቆርጦ ፡ ራሱ በክንፍ ወደሰማይ ሲወጣ ከአንገቱ በታች በምድር ላይ ቀረ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

295 ዘአምላኪየ

ፀሐይ ወወርኅ ነዳያነ ሥጋ ተሀወኩ
ሶበ ሞተ ብዑስ ኵለንታ ለሄኖክ አምላኩ ፤
አምጣነ እምዝኩ ልብሰሙ ወሲሳዮሙ እምዝኩ ።

ት ር ጉ ም

የሁለንተና (በሁሉም) ባለፀጋ/ የሄኖክ አምላኩ
በሞተ ጊዜ ፀሀይና ጨረቃ/ የስጋ ድሆች ታወኩ ፤
ልብሳቸው ከርሱ ነውና ምግባቸውም ከርሱው ነውና ።

ም ስ ጢ ር

በልብስ ፡ በጉርስ የሚረዳቸው ባለፀጋ ሲሞት ድሆች በልቅሶው ይብላላሉ (ይተራመሳሉ) ። በእንፃሩም ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ሲሞት ፀሀይ ጨለመ ፡ ጨረቃም ደም ሆነ ፤ ተፈጥሯቸውና ፍርርጀቃቸውም በርሱ ስልጣን መሆኑ ታወቀ ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

296 ዋዜማ

ዘአይቴሀ (መጋቢ ፡ ዘደብረ ወርቅ)

ኢተሐውር ማዕቀብ አልፋ
በምክረ ረሲዓን ዕወው ፤ አምጣነ ለዕዝራ ሐሰውኩ ፤
ወለባሕር ዘእንበለ ጸብእ ፍኖተ ረሰይኩ ፤

እስከነይቤ አጽፍከ ዘበአምሳለ ንስር ፈነውኩ
አይቴኑ ባቢሎን ኢያሪኮ ?
ወአይቴኑ ዳንኤል ተሀውኩ ?

ት ር ጉ ም

ማእቀበ አልፋ (ኤዎስጣቴዎስ) !
በዝንጉዎች እንጨቶች ምክር አትሄድም ፤ አዝራን አስ ተባብለኸዋልና ፡
ባህርንም ያለጠብ መንገድ አድርገኸዋልና ፤
በአሞራ አምሳል የላክኸው አጥፍህ
ባቢሎን/ ኢያሪኮ ወዴት ነው ?
ዳንኤል/ መታወክስ ወዴት ነው ? እስኪል ድረስ ።

ም ስ ጢ ር

ብልህ ሰው በግብዞች እንደማይታለልና ወደክፉ አድራጎት እንደማይሄድ ሁሉ ማእቀበ አልፋ የተባሉት አባ ኤዎስጣቴዎስ የአዝራ ሱቱኤልን ምሳሌ አላፀደቁለትም ።

አዝራ ሱቱኤል « እንጨቶች ተሰብስበው ባህርን በጦርነት ድል ነስተን ቦታውን እንውረስውና ግዛታችንን እናስፋፋ ፤ የባህር ማእበሎችም በበኩላቸው ተሰበሰቡና የምድረ በዳ እንጨቶችን ነቃቅለን ቦታቸውን ለራሳችን እናስፋፋው ብለው በእንጨቶች መከሩባቸው ። እሳት በድንገት ተነስቶ እንጨቶቹን በላቸው ፤ የባህር ማእበሎችንም የአሸዋ ግድብ አስቀራቸው ። ስለዚህም የሁሉም ምክር ከንቱ ሆነ» ብሎ ነበርና አባ ኤዎስጣቴዎስ እንደ እንጨቶች የኢያሪኮን ባህር ማእበል ለማስለቀቅ ሳይፈልጉ በሰላም ተሻገሩ ።

ደግሞ ነቢይ እንባቆም «ባቢሎን ወዴት ነው ? ዳንኤልስ ወዴት ነው? » ብሎ ቅዱስ ሚካኤልን እንደጠየቀው ሁሉ ፤ እንደ ንስር አሞራ ያከነፈፈ (በሁለት ወገን የተዘረጋ) የኤዎስጣቴዎስ

አፅፍ (ከቆዳ የተሰራ ካባ መሳይ ልብስ) ኢያሪኮን እንደሌለ እደ ረገው ፣ መታወክን አጠፋ 1 በባህር መታወክ መስጠምንም አስቀረ በግለት ቅኔው ተመስጥሯል (እዝ. 2 ፣ 13) ።

ታሪክ

እንባቆም የተባለው ነቢይ በኢየሩሳሌም ይሁዳ ለእህል አሜጆች ምሳቸውን ይዞ ሲሄድ ፣ ሚካኤል የተባለው መልአክ «ይህን ምሳ በባቢሎን ላለው ለዳንኤል ውሰድ» አለው ። በዚህ ጊዜ « ባቢሎን ወዴት ነው ? ዳንኤልስ ወዴት ነው ? እወስድለት ዘንድ» በማለት ጠየቀው ። ስለዚህ ሚካኤል በራሱ ጠጉር አንጠልጥሎ ወሰደውና ዳንኤል ወዳለበት ቦታ አደረሰው ። በዚያም ዳንኤል ምሳውን ተመግቦ ሲያበቃ ከተረፈው ምግብ ጋር መልሶ ወደመጣበት አድርሶታል (ዳን 12 ፣ 1—2 ። ድርሳነ ሚካኤል ግንቦት 12) ።

በክርስትና ማእቀበ እግዚእ (ማእቀበ አልፋ) በተፀውኦ ስማቸው ኤዎስጣቴዎስ የተባሉት ኢትዮጵያዊ ፃድቅ የክርስቶስ ምእና የስነ ህይወት ልጅ ናቸው ። በትውልድ ስፍራቸው በሀማሴን ተምረው የቅዱሳት መፃህፍት መምህር ለመሆን በቅተዋል ።

አባ ኤዎስጣቴዎስ የእናታቸው ታላቅ ወንድም አባ ዘካርያስ ከነበሩበት ገዳም ገብተው ስርአተ ምንኩስናን ፈፅመዋል ። ዲቁናና ቅስና ተቀብለው ሲያገለግሉ በትምህርታቸውና በትሩፋታቸው የገዳሙ መነኮሳት ያደንቋቸው ነበር። ስለቀዳሚት ሰንበትና ስለእሁድ ሰንበት እኩልነት አስተምረዋል ።

እኒህ ፃድቅ በኢትዮጵያ ስለሁለቱ ሰንበታት (ቅዳሜና እሁድ) አከባበር ክርክር ስለተነሳ ወደ እስክንድርያው ፓትርያርክ ወደአባ ብንያሚን ሁለተኛ (1327—1338) ሄደዋል ። ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም ወርደው ቅዱሳት መካናትን ተሳልመው ወደ አርማንያ ጉዟቸውን ቀጥለዋል። የኢያሪኮ ባህር መርከበኞች እርሳቸውንና ደቀ መዝሙሮቻቸውን እናሻግርም ስላሉ ፃድቁ የለበሱትን አፅፍ በባህሩ ላይ ዘርግተው ከነደቀ መዝሙሮቻቸው ተሳፈሩ ። ከመካከላቸውም አንድ ደቀ መዝሙር ብቻ ሲሰጥም የቀሩት በደህና ተሻግረው ወደ አርማንያ ገብተዋል ።

አባ ኤዎስጣቴዎስ በአርማንያው ሊቀ ጳጳሳት ፈቃድ በአርማንያ የወንጌል ስራቸውን ቀጥለው በስብከታቸውና በሰሩት ተአምር አህዛብን ወደ ክርስትና መልሰዋል ። እኒህ ኢትዮጵዊ ፃድቅ በአርማንያ እንዳሉ አርፈው በክብር መቀበራቸው ተዕፍል (ስንክ. መስከረም 18) ።

297 ሥላሴ

ዘተክለ ሃይማኖት (አቢቶ)

ክራማተ ዕሥራ
ሐሰወ ኖኅ ነቢየ ጊዜ ፡
ወትትገፈታዕ በነድ በላኂ ማዕደ መወልጥ ነነዌ
ጽድቀ ብሂሎቱ ለዮናስ ሕሳዊ ።
ከመ ትኩኑ አምላነ ባሕቱ ሀለወክሙ ህላዌ
ዘደቤ ዕቢረ ወአረጋዌ
እስመ ኮነ ሥጋ አምላነ ማሕየዊ ፡
ኢሐሰወ ነቢይነ አርዌ ።

ትርጉም

ሃያ ዘመንን
የጊዜ ነቢይ ኖህ አበለ ፡
የለዋጯ ማእድ ነነዌ በእሳት ትገለባበጣለች
የዮናስ የማለቱ እውነትም ውሸት ሆነ ።
ነገር ግን ባልቴትንና ሽማግሌን አምላክ
ትሆኑ ዘንድ ህልውና አላችሁ
ያለ ነቢያችን አውራ አላበለም ፡
ስጋ አዳኝ አምላክን ሆኗልና ።

ምስጢር

አምላክ የጥፋት ውሃን ይመቱ ሃያ ዘመን እንደሚያዘንብ ለወዳጁ ለኖህ ነግሮት ነበር ። ኖህም ይህንን ለህዝቡ አስረድቶ

ሳለ የጥፋቱ ውሃ መቶው ዘመን ሲሞላ ዘነበ ። ለህዝቡ የተናገረው መቶ ሃያ ዘመን አልሆነም ። ስለዚህ ናህ ሃያ ዘመንን አበለ ተብሏል ።

እንዲሁም ነቢይ ዮናስ «ታላቅ አገር ነነዌ እስከ ሶስት ቀን ድረስ በሰማይ እሳት ትገለባበጣለች » ብሎ ለከተማይቱ ህዝብ ሰብኮ ነበር ። ግን ህዝቡ ከእነንጉሱ ንስሃ ገብተው ስለያሙና ስለፀ ለዩ የሰማይ እሳት በአየር ታይቶ ተመልሶላቸዋል ፤ ስለዚህም ዮናስ አባይ መስሎ ተገኝቷል ። እባብ አልዋሸም ማለት ግን «እፀ በለስን ብትበሉ አምላክ ትሆናላችሁ» በማለት የተናገረው ከአዳምና ከሄዋን ዘር ከቅድስት ማርያም የተገኘ ስጋ በመለኮት ተዋህዶ አምላክ ሆነ መባሉ እንደሆነ ባለቅኔው ያስገነዝባሉ ።

298 መወድስ

በመስፈርተ ሰሎሞን ነሥአ ሥንቀ ኢተዐውቆ
ገብረ መርዓዊ ዘሠምረ ሐዊረ ሥቃያት ፍናው ፤
እስመ በደዌ ተስብረ ሥነ መልክኡ ግጎው ፣
ዳንኤል ልቡናሁ
እንዘ ለተሀውኮ አንበላ ምጥው ።
ወለሥጋሁ ፈትለ ሜላት
ተካፈልዋ ሰረቅት ዕዒያት በመዳልው ።
ጎበሂ ተረክበ ትዕግሥተ ዕዒ ልብው
የዋሃን አጸብጺሁ አምለኩ በዕፀው ፤
ወእኮ ምኑን በጎቤሆሙ ለእፅይንቲሁ አበው
ሐና ዘወለደቶ ሳሙኤል ሰቆቃው ።

ት ር ጉ ም

ሲቃዮች/ መንገዶችን መሄድ የወደደ ገብረ መርአዊ
ስንቅ /አለመታወቅን በሰሎሞን መስፈሪያ ወሰደ ፤
የመልኩ ውበት/ ብርሌ በደዌ (በህማም) ተሰብሯልና
ዳንኤል/ ልቡ

ለመታወክ/ አንበሳ የተሰጠ ሲሆን ።
የሀር ፈትል /ስጋውንም
ሌቦች /ትሎች በሚዛን ተካፈሏት ።
የልበኛ/ ትል ትእግስትም ከተገኘ ዘንድ
የዋሆች /ጣቶቹ በእንጨቶች አመለኩ ፤
ሀና የወለደችው ሳሙኤል ሰቆቃውም (ለቅሶም)
በአባቶች/ አይኖች ዘንድ የተናቀ አይደለም ።

ም ስ ጢ ር

ሊሄድ የተዘጋጀ ድሃ መንገደኛ ተበድሮ መስፈሪያ ሙሉ እህል ስንቁን ይዞ ይሄዳል ፤ እንዲሁም ገብረ ክርስቶስ የተባለው መናኝ ከአባቱ ቤት ምኞት ይልቅ ስለ ክርስቶስ መንግስት የስጋ መከራ መቀበልን ወደደ ።

ብርጭቆም በድንጋይ እንደሚሰበር የገብረ ክርስቶስ የወጣት ነቱ መልክ ውበት በደዌ ስጋ (በስጋ ደዌ) ተለወጠ ።

ነቢይ ዳንኤል በጉድጓድ ተጥሎ ለአንበሳ እንደተሰጠ የገብረ ክርስቶስም ልቡና በክርስቶስ ፍቅር በመነሳሳት ጨከነ ፤ ሌቦችም የልብስ ፈትልን ቀምተው እንደሚካፈሉት የደዌ ስጋ ትሎችም የገብረ ክርስቶስን ስጋ በሉት ።

የዋሆች ሰዎች በእንጨቶች እንዳመለኩ ትል ከተፈጠረ ዘንድ የገብረ ክርስቶስ ጣቶች እንደ እንጨቶች ያረቁ ተቆራረጡ ። መክና የኖረች ሀና የወለደችው ሳሙኤልም በእስራኤል ዘንድ የከበረ እንደ ሆነ የድንግል ማርያም እናት ሀና ያለቀሰችውን ልቅሶ የገብረ ክርስቶስ አይኖች አለቀሱ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

የሰሎሞንን መስፈሪያ ባለቅኔው የጠቀሱበት ምክንያትም ሰሎሞን በገዛ ቤተ መንግስቱ እንግዳ ሆኗል ስለሚባል ገብረ ክርስቶስ ከታመመ በሁዋላ በቤተ ሰቦቹ ዘንድ አለመታወቁን ለማነፃፀር ነው ።

299 ዘአምላኪየ

ይቤ ሐሊብ ብእሴ ብዙኅ ትካዜ
ጸም ጸላኤ ዚአየ ይመውት ማእዜ ፤
አምጣነ ግዱፈ ኮንኩ ወኢተራድአኒ ጊዜ ።

ት ር ጉ ም

ወተት/ የብዙ ትካዜ ሰው
ያም /የእኔ ጠላት መቼ ይሞታል ? አለ ፤
የወደቅሁ ሆኛለሁና ጊዜም አልተራዳኝምና ።

ም ስ ጢ ር

አዘን የበዛበት ሰው « ጠላቴ መቼ ይሞታል? እኔ መቼም ወድቄአለሁ ፤ ጊዜም አልተራዳኝም» ይላል ። እንዲሁም በአቢይ ያም (በኩዳዴ) ወራት ወተት መመገብ አልተፈቀደም ፤ ስለዚህም በሰው ሆድ አልገባም ይላሉ ባለቅኔው ።

300 መወድስ

ዘጉራይ (አለቃ)

ሰብዓ አዝማነ አርድኦተ ብካይ
እምሕዝበ ዘመኑ ዮሐንስ ለሰብከተ ጎዘን ጎረየ ፤
ወማእከለ ጎዘን ፍኖቱ ለእመ ጸምአ ብካየ
እምነ ሳምራዊት ዕለተ ዐርብ
ሰአለ ዐይነ ወንጌላዊ ከመ ይስተይ ማየ ፤
ሕዋሳቲሁ ሐዋርያት
እስመ ሀገረ ሞት ቦኡ ለተግይጦ ሲሳየ ።

ተጋብኡሂ ገጸቲሁ ማእከለ አዕይንት ዝየ
ላዕለ ዕፅ ከመ ይስቅሉ ሕሊና ዘኢጌገየ ፤
ወውስተ መልክኡ መብልዕ ሐሞተ ምሳሌ ወደየ ፤
በሕለተ ወይን ትርጓሜሁ ሰትየ ስሙ እስመ አበየ ።

ት ር ጉ ም

ሰባ ዘመኖች/ የልቅሶ ተማሮችን
ዮሀንስ ከዘመኑ ህዝቦች ለሰብከት /አዘን መረጠ ፤
በአዘን መንገዱ መሃልም ልቅሶን ቢጠማ
ከሳምራዊት/ የአርብ ቀን
የወንጌላዊ ዮሀንስ አይን ይጠጣ ዘንድ ውሃን ለመነ ፤
ሰውነቶቹ/ ሀዋርያት
ምግብን ለመግዛት ወደአገር ሞት ገብተዋልና።
ያልበደለ አሳብን በእንጨት ላይ ይሰቅሉ ዘንድ
ፊቶችም በአይኖች መካከል በዚህ ተሰበሰቡ ፤
በመልኩ/ ምግብም ውስጥ የምሳሌ ሀሞትን ጨመረ ፤
በወይን በትር/ ትርጓሜው ስሙን መጠጣት እምቢ ብሏልና።

ም ስ ጢ ር

ክርስቶስ ለወንጌል ስብከት ስላ ተማሪዎችን ከሕዝቡ መካከል እንደመረጠ ዮሀንስ ወልደ ነጎድጓድ ከመላው ዘመኑ (ከእድሜው) ሰባውን ዘመናት በልቅሶ አሳለፋቸው ። ደግሞ ክርስቶስ በመንገድ ተጠምቶ ከሳምራዊት ሴትዮ (ከሰማርያ ሴት) ውሃን እንደ ለመነ ፤ የዮሀንስም አይኖች ከአርብ መከራ የተነሳ (ክርስቶስ በእለተ አርብ የተቀበለውን ስቃይ እያስታወሰ) እያነቡ እንደ ውሃ ሚሙ ። ክርስቶስም ውሃን ከሳምራዊት የለመነው ደቀ መዛሙርቱ ምግብን ለመግዛት ወደመንደር በገቡ ጊዜ እንደሆነ ፤ የዮሀንስም ሰውነቶች ክርስቶስ ስጋውን በሀብስት አምሳያ ሰጥቶ መሞቱን በማሰብ ደከሙ ።

አይሁድም ያልበደለ ክርስቶስን በእንጨት ላይ ለመስቀል በህዝቡ መካከል እንደተሰበሰቡ የዮሀንስም ገፆች (ፊቶች) በአይኖቹ መካከል ተሰረንዱ ፡ አሳቡም ክርስቶስ ወደ ተሰቀለበት መስቀል ሆነ ይላሉ ባለቅኔው ።

በክርስቶስ መብል አሞት እንደ ጨመሩበትና እርሱም ትንሽ ቀምሶ እንደተወው የዮሀንስ መልክ የአሞት ምሳሌ ሆነ ፡ ፊቱ ጭፍግግ አለ ፡ ጠቆረ ፡ የስሙም ትርጓሜ ደስታ ሲሆን በስሙ ትርጓሜ መሰረት አልተደሰተም ማለት ብቅኔው ተመስጥሮበታል ።

301 መወድስ

ዘውብሽት (ቁሰ ገበዝ ፡ ዘብቸና)

አ ድንግል ካልእተ ምናሴ
ጎበ ዮርዳኖስ ወረደ ዐይንኪ ዘደወየ ፡
እስመ ሠረገላ ዘነድ ሠረገላሁ አርአየ
ዐይንኪ መልአከ ደመና ዘይቀድኅ ማየ ፡
ወእግርኪ ሐዋርያ ፡
ተመግሮተ እብን ይትወከፍ ትንቢተ ኤርምያስ ተነበየ ።
ዮሐንስሃ ዐይነ ዚአኪ እምሐዋርያት ዐብየ ፡
እምጣነ ይፈክር ብካያተ ሐዲስ ወብሉየ
ወታለ ዐዋዲ ዐይንኪ ዘምስለ እግዚኡ ዐረየ ፡
እስመ ያስተባረ በአምሳሉ ክረምተ ወሐጋየ ።

ት ር ጉ ም

የምናሴ ሁለተኛይቱ ድንግል ሆይ !
የታመመ አይንሽ ወደ ዮርዳኖስ ወረደ ፡
ውሃን የሚቀዳ የደመና መልአክ/ አይንሽ
የእሳት ሰረገላ የሆነ ሰረገላውን አሳይቷልና ፡
ሀዋርያ እግርሽም
በድንጋይ መወገርን ይቀበል ዘንድ የኤርምያስ ትንቢትን ተንብቷልና ።

የእንቺ አይን የሀንስም ከሀዋርያት ከፍ አለ ፡
ብሉይንና ሀዲስ ልቅሶዎችን ይተረጉማልና ፡
የሀንስ አይንሽም ከጌታው ጋር ተስተካከለ ፡
ክረምትና ቢጋን በአምሳያው ያፈራረቃልና ።

ም ስ ጢ ር

አንዲት ሴት ከንደኛዋ ሙያ እንደምታጠና ድንግል ማር ያም እንደ ምናሴ አለቀሰች ። እስራኤላዊ በሽተኛም ወደ ዮርዳኖስ ውሃ እየወረደ እንደሚታጠብ የድንግሊቱ (ማርያም) አይን ውሃ ሆነ ። ሀዋርያም ሲሰብክ በድንጋይ እንደተወገረ የድንግልም እግር እንደ ኤርምያስ በድንጋይ ተወገረ (ተመታ) ።

የሀንስም «ከሴቶች ልጆች ይበልጣል» እንደተባለ የቅድስት ማርያም አይንም ከሀዋርያት ይበልጥ አለቀሰ ። የሀንስ ብሉይንና ሀዲስን እንደ ተረጎመ የማርያም አይን በደረቀው እንባ ላይ አዲሱን እንባ አነባ ። አምላክም ክረምትንና ቢጋን እንደሚያፈራርቅ የማርያም አይን እንባውን እንደክረምት ዝናብ አዥጎደጎደው ፡ የወረደውንም እንባ እንደቢጋ መፈት አደረቀው ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

302 መወድስ

እፈርሀ አንሰ ወእርዕድ
እምነ ኀምስቱ ግብራት እለ ሀለዉ ምስሌየ ፡
አሐዱ በሞት እንዘ ትወፅእ ነፍስየ
ወካልኡ እንዘ መቃብረ ትውርድ ሥጋየ
ወሣልስ ለአምላኪየ
እንዘ ቅድመ ገጹ እቀውም ይርዕዱ አባላትየ ፡
ወራብዕ ፍትሐ ህየኔ እንዘ ትሰምዕ እዝንየ

ወጎምስ መንገለ ደይን እንዘ ይወስዱኒ አፅራርየ ፤
ወዝ ኵሉ ነገር እምይኩን ብየ
ከዊኖተ ግይ እምጎየሰኒ በማሕፀን እም ወላዲትየ ።

ት ር ጉ ም

ከእኔ ጋር ካሉት ከአምስቱ
ስራዎች የተነሳ እፈራና እንቀጠቀጣለሁ ፤
እንደኛው ነፍሴ በሞት ስትወጣ ይሆናልና
ሁለተኛም ወደመቃብር ስጋየ ስትወርድ ይሆናልና
ሶስተኛም በአምላኬ ፊት
ስቆም ሰውነቶቼ ይንቀጠቀጣሉና ፤
አራተኛም የኩነኔ ፍርድን ጅርዬ ስትሰማ ነውና
አምስተኛው ወደ መከራ ጠላቶቼ ሲወስዱኝ ነውና ፤
ይህም ሁሉ ነገር ከሚሆንብኝስ
በወለደችኝ እናቴ ማህፀን ውሃ መሆን በተሻለኝ ነበር ።

ም ስ ጢ ር

አንድ እንግዳ ሰው «ለአገሩ እንግዳ ፣ ለሰው ባዳ» ሆኖ የሀገሩን ልማድና ጠባይ ሲጠይቅ ፣ «በዚህ ብትሄድ ሽፍታ ይቀማሃል በዚያም ብትሄድ ሌባ ያስፈራሃል» ሲሉት ይሸበራል ።

እንዲሁም ህግንና ስርአትን ጠብቆ እንዲኖር የተፈጠረ ሰው ሀጉን ጥሶ ፣ ትእዛዙን አፍርሶ ፣ እንደስድ አደግ መረን ሲሄድ ከኖረ እነዚህ ከአንድ እስከ አምስት የተገለጡት ነገሮች ከሞት በሁዋላ ያሰጉታል ። ስለዚህ እነዚህን ተዘክሮ (አስታውሶ) ከሞት በፊት ስህተትን በግንዛቤ አርሞ ፣ በደልን በንስሃ አስተስርዮ (አቃልሎ) መቆየት ይገባዋል ። ይህ ካልሆነ ግን ለሰው ጥንቱን አለመፈጠር ይሻለው ነበር ማለት በቅኔው ተገልጧል ።

303 ሥላሴ

ዘዘወልዱ (አለታ)

አርካ ኬቱ ሁንዱማ ጨብሴ
ሌንጫ ጎፍታኮ ኢጆሌ ሌንጫ ፤
አሁንም የእውነት ግሩም አንበሳ የአንበሳ ኮርማ የቢያ
በከንድህ ሰበርኽው የሁሉን ሶማያ ።
ዱጉማ ጎፍታኮ ዱጉማ አሲ መና ኬቲ ገበያ
ሀሬ ጉደቴ ፈርዳን ፉለያ
ማሎ ማሎ ጎፍታ ኪያ !
መና ፈርዳ ፉደቴ አሀያ ።

ት ር ጉ ም

አንበሳ የአንበሳ ልጅ
ጌታየ ! ክንድህ ሁሉን ሰበረች ፤
አሁንም የእውነት አስፈሪ አንበሳ የአገር የአንበሳ ኮርማ (አንተ)
የሁሉን በትር በክንድህ ሰበርኽው ።
እውነት ጌታዬ እውነት ከዚህ ገበያ/ ቤትህ
እንደ አይጠ መጎጥ ፈረሶች ሲናቁ አህያ ከፍ ከፍ ተደረገች ፤
ምነው ምነው የእኔ ጌታ !
የፈረስን ቤት አህያ ወሰደች ።

ም ስ ጢ ር

አንበሳ በጉልበቱ ሃይል ሁሉን እንደሚሰብር አዩ ምኒልክ ሁሉንም አልፈው ነገሱ ። ደግሞ ጡንቻው በጣም የጠነከረ ሰው ዘንጉን ሲሰብቀው እንደሚያነቅጨው ምኒልክ የባላባቶቹን ምኞት አከሸፉት ።

ከአሀያም በግንኛውም ረገድ ፈረስ እንደሚበልጥ የታወቀ ሲሆን ፈረሱን ትቶ አሀያይቱን ቀሚስ ግልበስ ወግ እንዳይደለ ፣ እንዲሁም ጨዋ ሳለ ሌላውን ማላቅ አይገባዎትም የማለት ምስጋናም ወቀሳም በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

304 መወድስ

ዙተክሉ (መምህር ፣ ዘዋሽራ)

ጉባኤ ዕዒያት ኮነት ሥጋ አካልከ ፤
እመ ዕዒያት ዘኢዮብ ሊቃውንተ ንጉሥ ኬንያ
ዛቲ ሥጋከ እስመ ይእቲ ኂቅያ
ወምድረ ኂቅያ አካልከ ነያ ፣
ተመትሮ ማዕበለ ደም
እንተ ኢፈርሀ ልብከ ገብረ መርዓዊ ናትያ !
ቅርብትሂ ለተመትሮ ምድረ ቢታንያ
ኢየሩሳሌም እደ ዚአከ ማኅደረ ሕማም ሐዋርያ ፤
ወበበርእሶን ደመ እንዘ ይበክያ
ደናግለ ምትረት አጻብዒከ ገይሠ መቃብር አሌለያ ።

ት ር ጉ ም

የአካልህ ሲጋ የትሎች መሰብሰቢያ ሆነች ፤
የኢዮብ ትሎች የብልህ ንጉስ ሊቃውንት ቢሆኑ
ይህች ስጋህ ኂቅያ ናትና
አካልህም የኂቅያ ምድር ናትና ፣
መቆረጥ/ የደም ማእበልን
ልብህ ያልፈራ ዋናተኛ / ገብረ መርአዊ !
የህማም / ሀዋርያ ማደሪያ የሆነች ያንተ
እጅ ኢየሩሳሌም ለመቆረጥ / የቢታንያ ምድር ቅርብ ናት፤

በየራሳቸውም ደምን እያለቀሱ
የመቆረጥ ደናግል/ ጣቶችሀ ወደ መቃብር ለመገስገስ
ግለዱ ።

ም ስ ጢ ር

ኂቅያ በ325 አ.ም. አርዮስን ለማውገዝ በሮሙ ንጉስ ቆስ ጠንጢኖስ ትእዛዝ ለተጠሩ ሊቃውንት (ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጳሳት) መሰብሰቢያ እንደሆነች የገብረ ክርስቶስ አካልም የስጋ ደዌ ትሎችን አፈራች ። ደግሞ የወንዝን ማእበል የዋናተኛ ልብ እንደማይፈራ የገብረ ክርስቶስም ልብ ደም ብቻ የሚያደርግ ደዌን አልተሰቀቀውም። ሀዋርያ የሰበከባት ኢየሩሳሌም ለቢታንያ ቅርብ እንደሆነች ሀማሙ ያደረባት የገብረ ክርስቶስ እጅ ለመቆረጥ ሆነች ።

ሌቶችም (እነመግደላዊት ማርያም) እያለቀሱ ወደ ክርስቶስ መቃብር በማለዳ እንደሄዱ የገብረ መርአዊ ጣቶች በደም ጠልቀው ወደመቃብር ወረዱ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

305 መወድስ

ሚካኤል ሰዐር ምክረ አሕዛብ
እለ መከሩ ውኀብሩ በርስትከ ኢትዮጵያ ፤
ከመ ርስተ ባዕዳን ኮነት ርስተ ጴጥሮስ ሮምያ
ኢትኩን ለባዕዳን
ብሔረ አግዓዚ ሀገርከ ነያ ፣
እስመ ሰብእ ጽርእ ወእንጾኪያ
በልብሰ አባግዕ መጽኡ ወእንተ ውስጦሙ ሐራውያ ።
አራምሂ እንተ ኢጸግበ ምህርካ ጥቃሁ ሶርያ
ወኤፍራም ለደዌሁ በመጽሔተ አካዝ እንተ ርእያ
በኢየሩሳሌም መከሩ ወተመነዩ ንዋያ ፤
እንዘ ርእሰ አራም ደማስቆ ወኤፍራም ሰማርያ ።

ት ር ጉ ም

ሚካኤል ! በርስትህ/ ኢትዮጵያ
ያበሩና የመከሩ የአህዛብን ምክር ሻር ፤
የጴጥሮስ ርስት/ ሮምያ የባእዶች ርስት እንደሆነች
አገርህ የሆነች
የእግአዝያን አገር ኢትዮጵያ ለባእዶች እንዳትሆን ፤
የፅርአና የአንያኪያ ሰዎች
ውስጣቸው እሪያ ሲሆን በበጎች ልብስ (እንደ በግ ፀጉር
ለስልሰው) መጥተዋልና ።
የሶርያን ምርኩም ያልጠገበ አራምና
ደዌውን በአካዝ መስታወት ያየ ኤፍሬም
በኢየሩሳሌም መክረዋልና ገንዘቧንም ተመኝተዋልና ፤
የአራም ራስ ደማስቆ ሲሆንና ኤፍሬም ሰማርያ ሲሆን ።

ም ስ ጢ ር

ጠላቶች ተሰብስበው በሌላው ላይ ሲመክሩ የሰማ ወዳጅ «እነእገሌን እወቅባቸው ፥ ውስጣቸው ርኩስ ሲሆን ቅዱስ መስለው መጥተዋል ። እገሌ ፥ እገሌና እገሌ በሞኝነት ተታለው በእገሌና በእገሌ ርስቶቻቸውን እንደተነቀሉ አንተም ይህችን መሳይ ርስትህን በእነዚህ አታላዮች ትነጠቃለህ» በማለት እንደ ሚያስጠነቅቀው ሁሉ ፤ ቅዱስ ሚካኤል ! ኢትዮጵያን በስጋዊውም በመንፈሳዊውም ከማይመስሏት ጠላቶችዋ ጠብቅልን ምክራቸውንም ለውጠው ይላሉ ባለቅኔው ።

ጴጥሮስ በሮምያ የመሰረተው ባህል በሌሎች ባህል እንደተለወጠ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ባህል በማይመስሏት ሰዎች ባህል እንዳይለወጥ አድርግልን ። በጉዳዩ ቸል እንዳትልም ይሄውና ! የፅርአና የአንያኪያ ሰዎች ርኩስ ባህላቸውን በኢትዮጵያውያን ባህል ሸፍነው መጥተውልሃል ። በዚህም አይነት ተንኮል ከአሁን በፊት የአራምና የኤፍሬም ልጆች ኢየሩሳሌምን ለመውረር አቅደው ነበር በማለት ፀሎታዊና ጥቆማዊ ምስጢር በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

306 መወድስ

ዘከፍለ ዮሐንስ (ዘንጎደር)

እምከዊነ ካህን ይጌይስ ከዊነ ኖላዊ ፥
ወነለ እንስሳ ትትበደር እምቤተ መቅደስ ዐባይ ።
እስመ ቤተ መቅደስ ኮነት ቤተ ፈያታይ ፥
ወበላዕለ ኖሎት ኢሀለወ
በላዕለ ካህናት ዘሀሎ እከይ ፤
ትእምርተ ዝኒ ከመ ንርአይ
በነለ እንስሳ ሠረቀ ዘኢየዐርብ ፀሐይ ፥
ወኖሎት ተዛውዑ ምስለ ሐራ ልዑል ሰማይ ።
ዓዲ እምቅድመ ዝንቱ እመካነ ኖሎት ወመራዕይ
ከመ ተጸውዑ ደምፀ እግረ ቃለ ዜና ሠናይ
ወልደ እንበረም ለምስፍና ወለቅብዐ መንግሥት ወልደ
ዕሤይ ።

ት ር ጉ ም

ካህን ከመሆን እረኛ መሆን ይሻላል ፥
የእንስሶች በረትም ከታላቅ ቤተ መቅደስ ትመረጣለች።
ቤተ መቅደስ የሽፍታ ቤት ሆናለችና ፥
በካህናት ላይ ያለ
ክፋትም በእረኞች ላይ የለምና ፤
የዚህንም ምልክት እናይ ዘንድ
የማይጠልቅ (የማይጨልም) ፀሀይ በእንስሳ በረት ወጣ ፥
እረኞችም ከከፍተኛ ሰማይ ጌታ መላእክት ጋር አብረው
ተጫወቱ ።
ዳግመኛም ከዚህ በፊት ከእረኞችና ከመንጎች ቦታ
የእንበረም ልጅ (ሙሴ) ለመስፍንነት የእሴይም
ልጅ (ዳዊት) ለመንግስት ቅባት እንደተጠሩ የመል
ካም ወሬ ኩቴ ተሰማ ።

ም ስ ጢ ር

«እናትና አባት ብዙ ይወልዳሉ ፣ ሙያውንና ግብሩን አይተው አንዱን ይወዳሉ» እንዲሉ መወደድና መላቅ ከስራ መበጀት የተ ነሳ ነው ። እረኞች ከብቶቻቸውን ከማሰማራትና እርስ በርስ ከመ ጫወት በቀር ሌላ ተንኮል አለማሰባቸውን ለጊዜው በጨዋ ታም ቢጣሉ ወዲያውኑ መስማማታቸውን ፣ ከቅንነታቸውም የተ ነሳ ክርስቶስ በእንስሶቻቸው በረት ሲወለድ እነርሱ ከመላ ክት ጋር ማመስገናቸውን በማመልከት ባለቅኔው ከካህንነት እረኝ ነት ከቤተ መቅደስ በረት ይሻላል ይላሉ ።

ደግሞ ክርስቶስ ስለቤተ መቅደስ ሲናገር «ቤቴስ የፀሎት ቤት ነበር ! እናንተ ግን የቀማኞችና የሌቦች ቦታ አደረጋችሁት » እንዳለ እውነት ሊነገርባትና ሊሰራባት የተመሰረተችው ቤተ መቅ ደስ ማታለያና መቀሰሚ ስትሆን የከብቶች በረት ግን የክርስቶስ መወለጃና የመላእክት ማመስገኛ መሆኗን ገልጠዋል ።

ጥንቱንም ሙሴ ለመስፍንነት የእሴይ ልጅ ዳዊትም ለመንግ ስት የተመረጡት ከበጎችና ከእረኞች መካከል እንጂ ከቤተ መቅ ደስና ከካህናት መካከል አለመሆኑን ጠቅሰው ታላቁ ሊቅ ክፍለ ዮሀንስ በአስራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረውን የካህናትን ማህበራዊ ግንኙነት በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

307 መወድስ

ዘንባዜ (አለቃ)

ቦ ሕሰው ስመ ተጸውዖ ፤
እስመ ቦ በባሕር ወላዲተ ማይ ዘትሰመይ
እንዘ ኢትወልድ ማየ ጸሊመ ባሕርይ ፣
ወእንዘ አሐደ ኢይኬንን
ደክመ በጸዊረ ስም ማልኮስ ሀካይ ፤

ወእንዘ በብርሃን ኢይትረአይ
ሀለመ ቄሣር በተሰምዮ ብሩህ ፀሐይ ።
ለድንግልሰ ትርጓሜ ስማ በበንባቡ ዕሩይ ፤
ለእመ ፈለገ ንሰምያ አምጣነ ወልዳ ዕንቄ ባሕርይ ፣
ወለእመ ንብላ ዙልነ ገራሀተ ሠሉስ ወባይ
ከርዳድ ዘኢሀለዎ ፍሬሃ ፍሬ ሥርናይ ።

ት ር ጉ ም

የተዋሸ የተፀውአ ስም አለ ፤
ባህርዩ የጠቆረ ውሃን ሳትወልድ
የውሃ እናት የምትባል በባህር አለችና ፣
አንድም ሳይገዛ
ስምን በመሸከም ሰነፍ ማልኮስ ደክሟልና ፣
በብርሃንም ሳይታይ
ብሩህ ፀሀይን በመባል ቄሳር ኖሯልና ።
የድንግል ግን የስሟ ትርጓሜ በየንባቡ ትከክል ነው ፤
ወንዝ ብንላት ልጅዋ እንቆ ባህርይ (የእንቁ እንቁ) ነውና
ሁላችን የታላቅ ማክሰኞ እርሻ ብንላትም
ፍሬዋ እንክርዳድ የሌለው የስንዴ ፍሬ ነውና ።

ም ስ ጢ ር

ያለበቂ ሙያ የሚመሰገን ሰው መኖሩ የውሃ እናት በምትባ ለው በውሃ ውስጥ በምትኖር ተንቀሳቃሽ ፣ የስሙ ትርጓሜ ንጉስ በሆነ በእይሁድ ሊቀ ካህናት በቀያፋ አገልጋይ በማልኮስና በሮም ንጉስ በቄሳር ስሞች የተረዳ ነው ። የቅድስት ማርያም የስሟ አጠ ራር ግን በተግባራዊ ምሳሌ የተመሰረተ መሆኑ በወንዝነቷ እን ቁን ወለደች ። በእርሻነቷም የስንዴ ፍሬን አስገኘች ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

308 ዕዝል ዕጣነ ሞገር

ዘድንቆ ማርቆስ

በደመ ሰብዓ ናሎት እንዘ እዴከ ሚሩይ
ሚካኤል ለከ ንጽሐ ባሕርይ ፤
ከመ ትድምርተ ሠሌዕ ምስለ ዘማ ገፋዒተ ሕግ ብሉይ
ቅድስና ኤርምያስ ይሰመይ ፡
ወዘሰበረ ሕዝቅያስ ነጋሢ መዓጹተ ወርቅ ጽሩይ
ምስለ ዘአግበረ ሰሎሞን ዕሩይ ።

አሠረ ንጉሥ

ለዘአልቦቱ ጎዮእ ንስሓ ወኢይትፈወስ ድውይ ፡
ለነዳይኒ እምዮም ሳኒታ ዘኢይኄይሶ ሲሳይ
እንዘ ያውዕዮ ፍቅረ ንዋይ
እንበለ ዘተፈትነ ሞት ሥራየ ሰማይ
ለሠለስቱ አልቦሙ ሥራይ ።

ትርጉም

በሰባ እረኞች ደም እጅህ ያለለ (የጠለቀ) ሲሆን
ሚካኤል ! የባህርይ ንፅህና አለህ ፤
ከብሉይ ህግ ገፊ ዘማ ጋር የሆሴእ ግንኙት
የኤርምያስ ቅድስና እንደሚባል ሁሉ ፡
የጥሩ ወርቅ መዝጊያዎችን የሰበረ ንጉስ ህዝቅያስም
ከአሰራው ከሰሎሞን ጋር ትክክል እንደሆነ ።

አሰረ ንጉስ

ፀፀት ለሌለው ሀጢአተኛና ለማይፈወስ በሽተኛ ፡
የገንዘብ ፍቅር እያቃጠለው ከዛሬ ነገም
ምግብ ለማይሻለው ችግረኛ

ከተፈተነ ሞት የሰማይ መድሀኒት በቀር
ለሶስቱ ሌላ መድሀኒት የላቸውም ።

ምስጢር

አንዳንድ ሰው ክፉ ሳለ መልካም ሰሪ መስሎ ይኖራል ። እን ዲሁም ቅዱስ ሚካኤል በእነሰናክሬም ዘንድ ነፍሰ ገዳይ ሲሆን ከእዳው ንፁህ ሆኖ በቅዱስነት ይመሰገናል ። ነቢይ ሆሴእም በትንቢታዊ ምሳሌ ከዘማ ጋር መገናኘቱ እንደ ነቢይ ኤርምያስ ቅድስና እንጂ እንደ ዘማዊ ግንኙት አልሆነበትም ። የእስራኤል ንጉስ ህዝቅያስም የእስራኤል ንጉስ ሰሎሞን ያሰራው ቤተ መቅ ደስ መዝጊያዎች የተለበጡበትን ወርቅ ልጦ (ቀርፎ) ለአሶር ንጉስ ሰናክሬም ቢገብር ይህ አድራጎት ከአሰሪው ከሰሎሞን አድራጎት አላነሰበትም ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

ከዚህም ሌላ መድሀኒት የማያሻለው በሽተኛ ከሞት በቀር ሌላ የሚፈውሰው እንደሌለ ፡ እየሰራ ሁልጊዜ ለሚችገር ሰውም ከሞት በቀር ችግሩን የሚያቃልልለት የለም ይላሉ ባለቅኔው ።

309 መወድስ

ዘተከለ ሃይማኖት ነጮ

አሐደ ዕለተ እምተፈጸምነ
ለፍጥረትከ አምላክ ለእመ አምላከ ትሬስዮ ፤
ወትእምርተ ዝኒ ነገር ሶበ ለነጥበ ግይ ቀነዮ
ኤልያስ ዘፍዳ ሰበኑ ለኤልሣዕ ፈደዮ
ለፍጥረተ ዚአከ ተሐየዮ ፤
እስመ ለፍጥረትከ ዕፅ በእሳተ ረኃብ አውዐዮ ፡
ዳዊትሂ ዘተሠርገወ መንግሥተ ሳኦል ሎግዮ
ግፍዐ ሳኦል ተዘከረ ወጸንዐ በኦርዮ ፡
ሚካኤልኒ ርኅሩኅ ዘጽጋበ ምሕረት ከረዮ
ለሙሴ ኢተራኅርኅ እንዘ ውስተ መሬት ይወድዮ ።

ት ር ጉ ም

አምላክ ፤ ፍጥረትህን አምላክ
ብታደርገው አንድ ቀን በተፈፀምን (ባለቅን) ነበር ።
ለዚህም ነገር ምልክት የውሃን ጠብታ በገዛ ጊዜ
የመጠምጠሚያውን ክፍያ ለኤልሳእ የከፈለው ኤልያስ
ፍጥረትህን ቸል አለው ፤
ፍጥረትህ/ እንጨትን በእሳት/ ራብ አቃጥሎታልና ፤
የሳኦል መንግስት/ በፍታን የተሸለመ ዳዊትም
የሳኦል ግፍን አስቧልና በእርዮም ጠንቷልና ፤
ምህረት/ ጥጋብ ያቀናጣው ርህሩህ ሚካኤልም
በመሬት ውስጥ ሲጨምረው ለሙሴ አልራራምና ።

ም ስ ጢ ር

«የጠገበ ለተራበ ፥ የለበሰ ለታረዘ አያዝኑም» እንደተባለው ሁሉ ኤልያስ እንጨትን በእሳት እንደማቃጠል ፍጥረቱን ሁሉ (እስራኤልን) በራብ አንገበገበው ። ነጭ ሀርንም እንደመልበስ የሳኦልን መንግስት የያዘ ዳዊት ሳኦል የሰራበትን ግፍ አልረሳም ፤ አገልጋዩ የሆነ አርዮንም ሚስቱን በደፈራት ላይ (የእርዮን ሚስት መድፈሩ አንሶት) አስገደለው ።

መልአክ ሚካኤል ስንኳ ወርቅን እንደመቅበር ሙሴን ከእነ ነፍሱ (በህይወቱ) ሲቀብረው አላዘነለትም ። ስለዚህ በባለቅኔው ግምት ፍጡር ለአንድ ቀን እንኳን የአምላክነትን ስልጣን ቢያገኝ እንደፈጣሪው ሊታገስ አይችልም ነበር ማለት ነው ።

ታ ሪ ክ

መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል በናባው ተራራ ሙሴን በህይወቱ ቀብሮታል ፤ ይህም የተደረገበት ምክንያት እስራኤል ሙሴን በጣም ስለሚወዱትና ስለሚያከብሩት መቃብሩን እንዳያመልኩት ለመሰወር ነው ይባላል (ዘዳግ. 34 ፥ 1—8) ።

310 ዘአምላኪየ

ደመና ዮሐንስ አድያመ ዮርዳኖስ ፆደ ፥
ወሰበከ ለወይነ ዕብራስዲ ንስሓ በረደ ፤
አምጣነ በማይ ያጠምቅ አዝርዕተ ገራህት ውሉዶ ።

ት ር ጉ ም

ደመና/ የሀንስ የዮርዳኖስን አውራጃ ዞረ ፥
ለእብራስዲ ወይንም ንስሀ/ በረድን ሰበከ ፤
የእርሻ ዘሮች/ ልጆችን በውሃ ያጠምቃልና ።

ም ስ ጢ ር

የዘካርያስ ልጅ የሀንስ የዮርዳኖስን አውራጃ እየዞረ ህዝቡን በውሃ ያጠምቅ እንደነበረ ፥ የከረምት ደመና የእህል ዘሮችን በዝናብ ውሃ ሊያበቅል ውሃን ከውቅያኖስ ጠልቆ ወደሰማይ ወጣ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

311 ሥላሴ

ዘድንቆ ማርቆስ

መጠንከ ገብረ ሕይወት
ዘመደ መላእክት ተሰምዮትከ ፥
ምስለ ጸድቃነ ምድርሰ ከመ ኢትኩን ዘመደ
ሕርመተ መብልዕ ረሰይከ ባዕደ ፤
ውስተ ምኔተ ገድል ይፈጽም አኮኑ ቀኖና ፍጹማን ከቡዶ
በበእልፍ አልፈ እመ ሰገዶ
ለመብልዕ ምድራዊ ዘኢተዋረደ
ኢረከብነ እምጸድቃን አሐዶ ።

ትርጉም

ገብረ ሀይወት! የመላእክት
ዘመድ መባልህ ልክህ ነው ፡
ከምድር ፃድቃን ጋር ግን ዘመድን እንዳትሆን
የመብል ትውታን (መብልን መተው) ባእድን አደረግህ ፡
በገድል ገዳም ውስጥ የከበደ የፍፁሞች ቀኖናን ይፈፅም
ዘንድ
እልፍ ጊዜ እልፍን ቢሰግድ
ለምድር መብል ያልተዋረደ (ፃድቅ)
ከፃድቃን አንድ እንኳን አላገኘንምና ።

ምስጢር

አንድ ሰው ዝምድናውን ቆጥሮ የትውልድ አረጉን መዞ ለተ
ወላጁ ሲያስረዳ ተወላጁ « ዝምድናችን እውነት ነው ፤ እንደ አንተ
ዘርዝሮ ዝምድናችንን ያስረዳኝ የለም » ይለዋል ። በእንፃሩም ገብረ
መንፈስ ቅዱስ በተፈጥሯቸው ሰው ሲሆኑ በግብራቸው እንደ መል
አክ ሆኑ ፤ ከሰው ወገን ፃድቃንም ቢሆኑ በእህልና ውሃ ያልኖረ
የለም ። እቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ግን በፅኑ ተጋድሎ ሲኖሩ የእ
ህልና ውሃ ከጃሎት(ፍላጎት)ጠፍቶላቸው ፤ አምላካቸውን ማመስገ
ንን ብቻ እንደ እህልና ውሃ ተመግበው ኖሩ ስለሚባል መልአክ
መባል ይገባቸዋል ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

312 ዘይእዜ

በንባብ ይትዐወቅ ገጸ ሕሳቄ ፤
እሰመ እመ ይቤ እሰግድ ለእግዚ ድንግል ሰጊደ
ሄሮድስ ጸድቀ አፍአ
በቀቲለ እሉ ሕፃናት ተግህደ ።
ወእመ ረበናት ገብሩ መጽሐፈ ሙሴ ዘኢፈቀደ

ፍትሐ ሞተ ብእሲት ቍር ለእመ ወረደ
በጎሚሠ ዕፀው ዳንኤል ሐሰተ ረበናት እንደደ ።
ፍትሐ ሞተ ብእሲት ቍር ለእመ ወረደ

ትርጉም

የውሸት ፊት በንግግር ይታወቃል ፤
ለድንግል ሀፃን ስግደትን እሰግዳለሁ ቢል
የውሸ እውነተኛ ሄሮድስ
እነዚህን ሀፃናት በመግደል ተገልጧልና ።
መምህሮችም የሙሴ መፅሀፍ ያልፈቀደውን ባደረጉ ጊዜ
የሴት ሞት ፍርድ / ብርድ ቢወርድ
ዳንኤል እንጨቶችን በመፈለግ የመምህሮችን እሰት
እነደደ ።
የሴት ሞት ፍርድ / ብርድ ቢወርድ

ምስጢር

« ተከናንቦ ቢተኙ ገልጦ የሚያይ አምላክ አለ » እንዲሉ
አንድ የተከናነበ ሰው ክንንቡ ሲገለጥ ፊቱ እንደሚታይ ፤ የውሸ
ታም ነገርም በእውነት መሳይ ቃል ቢሸፈን በፍፃሜው ይገለጣል።
በመሆኑም አካል በልብስ እንደሚሸፈን ፤ « እሰግድለታለሁ » በግ
ለት የማርያም ሀፃን (ክርስቶስ) ግድያን የደበቀ ሄሮድስ « አሳድ
ጋቸዋለሁ » ብሎ የሰበሰባቸውን ሀፃናት በመግደሉ ተንኮለኛነቱ
ታወቀበት ።

እንዲሁም ብርድ በሆነ ጊዜ እንጨቶችን በእሳት አንድዶ እን
ደመሞቅ የዝሙት ስራቸውን በሶስና ሊፈፅሙ አስበው ባይሳካላ
ቸው ፤ ከነውር የነፃችውን ሶስናን በነውረኛ ስም የሞት ፍርድ ያስ
ፈረዱባት ረበናት (መምህራኑ አይሁድ) ተንኮል በዳንኤል ጥበብ
ተከሰተ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

313 መወድስ

ዘልሳነ ወርቅ (አለታ)

አልቦ በምድር ምልእተ ፍጥረት
እንተ ኢይትዋረድ ሰብእ ክቡር በዘወለደ ፤
እንዘ ወልደ ንጉሥ ውእቱ ገብረ መርዓዊ ዘክሕደ
ክቡራን አዝማዲሁ
በቤተ አቡሁ እስመ ኮነ ባዕደ ፤
መድኀረ ዝንቱ አስተዋረደ
አባሁ ንጉሠ እንተ የወቢ ፈድፋደ ።
ይትርፍሰ ነገረ ዝንቱ ከመ ተነግረ ገሃደ
በልደተ ዮሐንስ ወንጌላዊ ዘካርያስ ተዋረደ ፤
ወበልደቱ ለዮሴፍ አናግደ ጸዊር ክቡደ
ዘይትዌከፍ በሀገሩ ያዕቆብ ተአንገደ ።

ት ር ጉ ም

ፍጥረትን በተመላች ምድር
የከበረ በወለደው የማይዋረድ ሰው የለም ፤
የከበሩ ዘመዶችን የካደ ገብረ ክርስቶስ
የንጉስ ልጅ ሲሆን
በአባቱ ቤት ባእድን ሆኗልና ፤
ከዚህ በሁዋላም እጅግ
የገነነ ንጉስ አባቱን አዋርዷልና ።
የዚህስ ነገር እንደተነገረ ይቅርና
በወንጌላዊ ዮሀንስ ልደት ዘካርያስ ተዋረደ ፤
በዮሴፍም መወለድ ከባድን የመሸከም እንግዶችን
በአገሩ የሚቀበል ያእቆብ እንግዳ ሆነ ።

ም ስ ጢ ር

ገብረ ክርስቶስ በገዛ ፈቃዱ የንጉስ አባቱን ቤት ትቶ በመ ሄዱ መፃተኛ መሆኑንና ያእቆብ በችግር መሰደዱን ፤ ዘካርያስም በልጁ በዮሀንስ ምክንያት አንገቱን በሰይፍ መቆረጡን በማስረዳት በሰው ልጆች ላይ የሚሆነውን የማጣትንና የማግኘትን ፍርርቅ የሚ ያሳይ ምስጢር በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

314 መወድስ

ዘአካለ ወልድ (መምህር)

አኮ ቀሊል ለዘይጸውሮ
እብነ አድማስ ረኃብ እንተ ይሰብር ክሣደ ፤
ወከመ ኢቀሊል ለጸር አጠየቀነ ገሃደ
ኤልያስ ሐመልማለ ከርሡ በረኃብ ዘነደ ፤
አድባረ ብካይ አመ ያደ
እስመ በዐይኑ ነጸረ እንተ ብእሲት እደ ።
ረኃብሂ ሐፂነ ከርሥ እመ ኢኮነ ክቡደ
ለፈርያን ጸላኢሁ በከተማ በትሩ እምኢሰገደ ፤
ወእምሀገሩ ከነዓን እምኢተሰደ
ያዕቆብ በሀገሩ ብዙኃ ዘለመደ ።

ት ር ጉ ም

አንገትን የሚሰብር የአድማስ
ድንጋይ /ራብ ለሚሸከመው ቀላል አይደለም ፤
ሆዱ/ ቅጠል በራብ /እሳት የነደደ ኤልያስም
ለሸክም ቀላል እንዳይደለ በግልፅ አስረዳን ፤
የልቅሶ ተራራዎችን በዞረ ጊዜ
የሴትን እጅ በአይኑ አይቷልና ።
ራብ/ የሆድ ብረትም ከባድን ባይሆን ኖሮ

ለጠላቱ ፈርአን በበትሩ ጫፍ ባልሰገደ ነበርና ፤
በአገሩ ብዙን የለመደ ያእቆብም
ከአገሩ ከነአን ባልተሰደደ ነበርና ።

ም ስ ጢ ር

የድንጋይ ሸክም አንገትን እንደሚጫነው (እንደሚከብደው) ሁሉ ራብ አንገትን ያስደፋል ። ቅጠልም በእሳት እንደሚቃጠል የሌ ልያስም ሆድ በራብ ተሞረሞረ ። ተራራዎችንም እንደመዞር ኤል ያስ ተርቦ ልቅሶን አበዛ ፤ በእይኑም የሴትዮቱን ስጦታ ከጀለ ። ድንጋይንም ከክብደቱ የተነሳ ብርቱ ሰው እንኳ ሊሸከመው እን ግይችል ያእቆብ ከራብ ፅናት የተነሳ ወደግብፅ ተሰደደ ፤ ለፈርአንም ተገዛ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

315 ዋዜማ

ዘገብሬ (አለቃ)

በይነ ምንት ኢተሐዘባ
ለእግዚእኁረያ ንጽሕት ልበ ጸጋዘአብ አሐዱ ?
ገጸ ሰብእ ወገጸ መልአክ እስመ ነሥአ ወልዱ ፤
ግብረ ተሐዝቦሰ ይግበር በከመ ኤፍሬም ዘመዱ
መላእክተ ሰማይ ምድረ ማእዜ ወረዱ ?
ወማእዜ ሕገ ሰብእ ለመዱ ?

ት ር ጉ ም

የአንድ ፀጋዘአብ ልብ
እግዚአሀረያን ለምን አልጠረጠራትም ?
ልጁ የመላእክትንና የሰውን ፊት ይዚልና ፤
ግን እንደ ኤፍሬም ዘመዱ ይጠራጠር ዘንድ
የሰማይ መላእክት ወደምድር መቼ ወረዱ ?
የሰውንስ ህግ መቼ ለመዱ ?

ም ስ ጢ ር

አንዳንድ የዋህ ወንድ ሚስቱ ሌላውን ወንድ አስመስላ ብት ወልድም አይጠራጠርም ። እንዲሁም ፀጋዘአብ የተባለው የእቡን ተክለ ሃይማኖት አባት ልጁ ተክለ ሃይማኖት እንደ መላእክት ከንፈ ፀጋ (የፀጋ ከንፍ) ቢኖራቸውም ሚስቱ እግዚአሀረያን አልጠረ ጠራትም ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

316 መወድስ

ዘተክለ ጽዮን (አለቃ)

ሚ ይበዝኅ ኀዘነ እምየ
እምኀዘነ ያዕቆብ አብ ወኀዘነ ዳዊት አሐዱ !
እመኒ ትካት ባሕረ ሰቆቃው ወረዱ
ያዕቆብ እምጣነ ረከበ ልብሰ ዮሴፍ ወልዱ ፣
ወርእሰ ወልዱ አቤሴሎም
ዳዊት ርእየ ቅቡዐ ሰቆቃው ናርዱ ።
ለእምየሰ ሶበ ኀለፍት ዜና ሞትየ ወሰዱ
ዜና ሕይወትየ ለጠይቆ እንዘ ኀቤሆሙ ታንቀዐዱ
እፎኑ እምየ ባሕረ ሰቆቃው ተዐዱ !
ልብስየ ወርእሰየ እምጣነ ላቲ ኢይትገህዱ ።

ት ር ጉ ም

ከአባት ያእቆብ አዘንና
ከአንዱ ዳዊት አዘን የእናቴ አዘን ምን ይበዛ !
ምንም ቀድሞ ባህር/ ልቅሶን ቢወርዱ
ያእቆብ የልጁ ዮሴፍ ልብስን አግኝቷልና ፤
ሰቆቃው/ ሽቱን የተቀባ
ዳዊትም የልጁ አቤሴሎምን ራስ አይቷልና ።

ግን የህይወቴን ወሬ ለመጠየቅ ወደነርሱ ስታንጋጥጥ
መንገደኞች የሞቴን ወሬ (መርዶ) ለእናቴ በወሰዱ ጊዜ
እናቴ እንዴት ብላ ባህር/ ልቅሶን ትሻገር ይሆን!
ልብሴና ራሴ አይገለጡላትምና (አይታይዋትምና) ።

ም ስ ጢ ር

ያእቆብ በልጁ በዮሴፍ መጥፋት ዳዊትም በልጁ በአቤ
ሴሎም ሞት ቢያዝኑና ቢያለቅሱ፣ ያእቆብ የዮሴፍ ልብስን በማግ
ኘቱ ዳዊትም የአቤሴሎምን ራስ በማየቱ ልጆቻችን እንዴት
ሆነው ይሆን? በማለት ከመጨነቅ አረፉ ።

የዚህ ቅኔ ባለቤት የአለቃ ተክለ ፅዮን እናት ግን አለቃ ተክለ
ፅዮን ወደውጭ አገር ሄደው በዚያው ስለሞቱና አንድ የሆነ ማስታ
ወሻ እንኳን ስላልተላከላቸው፣ አዘናቸውና ልቅሷቸው ከያእቆብና
ከዳዊት አዘንና ልቅሶ የበለጠ ከመሆኑም በላይ ፀፀቱ እስከ እለተ
ሞታቸው ድረስ የማያቋርጥ መሆኑን ባለቅኔው በቅኔያቸው ምስ
ጢር ገልጠዋል ።

317 መወድስ

ዘጴያ (አባ፣ ዘአዘዘ)

መካነ ሰብዐቱ ሀብታት ደብረ ሊባኖስ
ዘውስቴትኪ ይምዕዝ ተክለ ሃይማኖት ናርዱ!
ዓለመ መንኖ ዓለመ መንከራትኪ ይዑዱ
ውሉዳ ለጢሮስ ቀናእያን
እለ እምትካት ሐሜተ ለመዱ
ላእሌኪ ተካየዱ
ንዋያተኪ ይንሥኡ ወጥሪተኪ ይሂዱ ።
ባሕቱ ሰዓተ ፀብዕ ቅድመ ወልድኪ አሐዱ

አሐደ ኢይከውኑ ባሕረ ተጋብአ አመ ነገዱ ፤
ለመጽሐፍኒ ቀላይ ዘባሕረ ትርጓሜ ሞገዱ
ይቀውሙ ውስተ ጽንፉ ወውስተ ዕመቁ ኢይወርዱ ።

ት ር ጉ ም

ሽቱ/ ተክለ ሃይማኖት በውስጥሽ የሚሸት
የሰባት ሀብቶች ቦታ ደብረ ሊባኖስ !
አድናቆትሽ አለምን የመናቅ አለምን ይዞሩ ዘንድ
ከጥንት አሜትን የለመዱ
ቀናተኞች የጢሮስ ልጆች በእንቺ ላይ
ቃል ኪዳን ተጋቡ
ገንዘቦችሽን ይወስዱ ዘንድ ጥሪትሽንም ይቀሙ ዘንድ።
ነገር ግን በጠብ ስአት በአንድ ልጅሽ ፊት
ወደ ባህር /መሰብሰብ በሄዱ ጊዜ አንድ አይሆኑም ፤
የትርጓሜ ቃል አዟሪቱ በሆነ ወንዝ/ መፅሀፍ ዳርም
ይቆማሉ ወደ ጥልቀቱ አይወርዱም እንጂ ።

ም ስ ጢ ር

ሽቱ በብልቃጡ ውስጥ እንደሚሸት ሁሉ ተክለሃይማኖት
በደብረ ሊባኖስ ይከበራሉ ። የተቻላቸውም አዋቂዎች አለምን
እንደሚዞሩ በደብረ ሊባኖስ አለምን የመናቅ አድናቆቶች አሉ ።

አሜተኞችም እገሌ እንደዚህ ነው እገሊትም እንዲህ ናት በማ
ለት የሰውን ክብር እንደሚገፉ ፣ የሃይማኖት ተቃራኒዎች የጢ
ሮስ ልጆች ስምሽን ሊያጠፉና ክብርሽን ሊያዋርዱ በቅናት ተነ
ሱብሽ ።

ግን « ሴባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል» እንዲሉ አሜተኛ ለል
ማዱ ቢያማም ምንም ለማድረግ እንደማይችል እነዚህም አይመክ

ቱም ። ዋና የማያውቅ ሰው በወንዝ አጠገብ ቆሞ ዳር ለዳር እንደሚ
ያገበግብና ወደባህሩ ጥልቅ እንደማይገባ ሁሉ ፥ በመሰብሰብ ቢመ
ክሩም የመፅሀፉን ቃል ንባቡን እንጂ ውስጠ ምስጢሩን አያውቁ
ትምና ይረታሉ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

318 መወድስ

ዘኪዳነ ወልድ (አለቃ)

ማሕፀነ ድንግል ሐዳስ አስተዐረዮሙ
ለባሕርየ ሥጋ ቄሪር ወለባሕርየ ቃል ነዳዲ ፥
እንዘ ሥጋ አዳም ይብዕል ወእንዘ ቃለ አብ ይነዲ
ሶበ ደምፀ ወተሰምዐ
ቃለ ሰማያዊ ገብርኤል ዐዋዲ ።
ወአልቦ እንበለ ወልድ
ፍዳ አረጋዊ አዳም ዘያጥብእ ወይፈዲ ።
ኢጎለፈሂ ወኢፈለሰ በአሠረ ተውላጥ ነጋዲ
ተሰምዮተ አብ መንገለ ወልድ ወተሰምዮተ ወልድ ጎበ
ወላዲ ፤
ወእምህላዌ አብ ወወልድ ዘኢይቀርብ ሀያዲ
አልቦ ዘይቀድም ወአልቦ ዘይጐነዲ ።

ት ር ጉ ም

የሰማያዊው ገብርኤል ዘዋሪ ቃል
ከደመና በተሰማ ጊዜ የአዳም ስጋ ሲበለፅግና
የአብ ቃል ሲቸገር ፥ የድንግል ማህፀን
ቀዝቃዛ የስጋ ባህርይንና
ነዳጅ የቃል ባህርይን አስተካክላቸው ።
ነገር ግን ከወልድ በቀር
የአረጋዊ አዳም ብድርን የሚመልስና የሚከፍል የለም።

በለውጥ/ ነጋዴ ፈለግም አብ መባል
ወደ ወልድ ፥ ወልድ መባልም ወደ አብ ፈልሶ አላለፈም፤
ቀማኛ ከማይቀርበው ከአብና ከወልድ ህልውናም
የሚቀድም የለም ፥ የሚዘገይም የለም ።

ም ስ ጢ ር

እውነተኛ ዳኛ ድህውንና ባለፀጋውን እንደሚያስተካክላቸው
የድንግል ማርያም ማህፀን የቃልን ባህርይ ከስጋው ባህርይ ጋር
አዋሃደው ፤ የእውነተኛውን ዳኛ ፍርድንም ወሸን (ጎሽ) እያለ የሚ
ያመሰግን ሰው ቃል እንደሚሰማ ቅዱስ ገብርኤል ማርያምን
በቃሉ አበሰራት ።

ደግሞ ደግ ልጅ የአባቱን እዳ ጨርሶ ይከፍላል ። እንዲሁም
አዳም ህግን ጥሶ በፈፀመው በደል እግዚአብሄር ወልድ በለበሰው
ስጋ በመስቀል ተሰቅሎ ካሰለት ፤ ሲክስም እርዳታ ለማግኘት
ወደዘመድና ወደወዳጅ እንዳልሄደ አብ በወልድ ስም አይጠራም ፤
ወልድም በአብ ስም አይጠራም ።

ሁለት ወንድማማቾችም ተጠባብቀው ጎን ለጎን እንደሚሄዱ
ሁሉ አብ ከወልድ አይቀድምም ወልድም ከአብ አያንስም ይላሉ
ባለቅኔው ።

319 ዘይእዜ

ዘአካለ ወልድ (መምህር)

ክርስቶስ መካሕ እምድኅረ ኀፀበ
በፈለገ ወይን ግዮን ልብሰ አቡሁ ይሁዳ ፥
አጸዕደወ ልብሰ ላፅለ ታቦር
በፀሐይ ልብሰ ወላዲቱ ዘጉብሩ እንግዳ ፤
ወብዕለ ባሕርዩ አርአየ በወርኀ ንዲቱ ማኅተመ ፍዳ

ቀይሕ ፈረስ ልብሰ ከለሜዳ
ወካልእ ልብስ ፈረሰ ታቦር ጸዐዳ
ቀይሕ ፈረስ ልብሰ ከለሜዳ ።

ትርጉም

ተመኪ ክርስቶስ በወይን ወንዝ
ግዮን የአባቱ/ይሁዳ ልብስን ካጠበ ብሁዋላ ፣
አይነቱ እንግዳ በሆነ
በእናቱ ልብስ ፀሀይ በታቦር ልብስን አነጣ ፤
ቀይ ፈረስ / የከለሜዳ ልብስና ሌላ ነጭ የታቦር ፈረስ/
ልብስም
የፍዳ መጨረሻ በሆነ በችግሩ ወራት
የባህርዩን ብልፅግና (ክብሩን) አሳየ ።
የፍዳ መጨረሻ በሆነ በችግሩ ወራት

ምስጢር

ልብስ አጣቢ ልጅ በወንዝ ውሃ አጥቦ ያነጣውን ያባቱን ልብስ በፀሀይ እንደሚያደርቅ ክርስቶስ ከይሁዳ ወገን (ከማርያም) ሰብአዊ ባህርይን ባህርይ አድርጎ በነሳው (በወሰደው) ስጋ በደብረ ታቦር የመለኮቱን ባህርይ ገለጠበት ። የሀብታም ሰው ብልፅግናም በፈራሱና በበቅሎው እንደሚታወቅ ክርስቶስም «በሰውነቱ ቀይ በመለኮቱ ነጭ » መባሉ ትህትናውንና ክብሩን ይገልጣሉ በማለት ባለቅኔው የክርስቶስን እምላክነት በቅኔያቸው ምስጢር ያስረዳሉ ።

320 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ይቤ ዮሐንስ መምህረ ብዙኃን ውሉድ
አክብሮ ሰንበት ሰይፍ በእንብሮ እግር ወእድ ።

ትርጉም

ብዙ የሆኑ ልጆች መምህር ዮሀንስ
ሰይፍ/ ሰንበትን ማክበር እጅንና እግርን በማሳረፍ ነው
አለ ።

ምስጢር

የልጆች መምህር ሲመክር « ሰንበትን ማክበር እጅንና እግርን በማሳረፍ ነው » ይላል ፤ እንዲሁም ክርስቶስን ያጠመቀ ዮሀንስ አንገቱን በሰይፍ ሲቆረጥ ራሱ በክንፍ ወደላይ ወጣ ፤ ከአንገቱ በታች ያለ አካሉ እጆቹና እግሮቹ በመሬት ወደቁ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

321 ሥላሴ

ዘካሣ (ቁሰገበዝ)

ሱርስተ ወዕብራይስጠ
ኢትትናገር ላእክ ልብሰ ባሕታዊ
መኑ ከልአከ ለነቢበ ሰብዓ በፍቅድ
እስመ አንተ ሥርግወ ዘሙሴ ወአሮን ኤፉድ ።
ቶማስሰ መምህር ዘንብሎ እምነ አእላፍ ውሉድ
በከናፍሪሁ ጽጌ በረድ
ነበበ የውጣ በማእከለ ዐውድ ፤
ወዳግመ ተርጕማ ለዮድ ።

ትርጉም

የባህታዊ ልብስ መልእክተኛ
ሰባን (ቋንቋ) በቁጥር ለመናገር
ሱርስትና እብራይስጥን እንዳትናገር ማን ከለከለህ ?

የሙሴንና የአሮንን የክህነት ልብስ የተሸለምህ ነህና ።
ከአእላፍ (ከብዙዎች) ምርጥ የምንለው መምህር ቶማስ ግን
የበረዶ አበባ በሆኑ ክንፈሮቹ
የውጣን በአደባባይ መካከል ተናገረ ፤
ዮድንም ዳግመኛ ተረጎማት ።

ም ስ ጢ ር

ከጌታ ልብስን የተሸለመ መልእክተኛ ሸለሚውን አመስግኖ ሲወጣ የቅርብ ጓደኛው የቀረ ነገር እያስታወሰ «ለምን እንደዚህ ሳትል ቀረህ» ይለዋል ። እንዲሁም የተከለ ሃይማኖት ልብስ እን ደለባሹ ፃድቅ ከአመሰገነ ዘንድ ፥ ከሆነ አይቀር ሰባ ሁለት ቋን ቋን እንደሀዋርያት ሊናገር በቻለ ነበር ። የእነአሮን ልብስም የሚ ንሸሸ ድምፅ ያለው ሻሁራ ያለበት እንደነበረ የተከለ ሃይማኖት ልብስ ቅዱስ ቅዱስ . . . የሚል ድምፅ አሰማ ይላሉ ባለቅኔው ።

ደግሞ አንድ መምህር እያነበበ እንደሚተረጉም ቶማስ የውጣ ንና ዮድን አነበበና ተረጎመ ማለት ፥ የግሪክ ፊደል የውጣ ቅፅ ልና እዝል የሌለባት ወጥ እንደሆነችና የእብራይስጥ ፊደል ዮድም እንድ ወጥ እንደ ሆነች እርሱም ሀሳቱን ሁሉ በከሀዲዎች ሰይፍ ተቆርጦ ምልምል ግንዱን ቀረ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

322 መወድስ

አልቦ ዘመድ ጊዜ ተዋርዶ
ወያክውን ባዕደ ጊዜ ተዋርዶ ዘመድ ፥
እመሰ ይትሌዐል በንብረተ ሥጋ ማዕድ
ጥቀ ዘመድ ወጥቀ ነገድ
ባዕድ ይዘመድ
እምኀበ አልቦ ነገድ ወእምኀበ አልቦ ትውልድ ።
ሶበሂ ተሰአልዎ ለሐዋርያ አይሁድ

ጎደገ ፈጣሪሁ ወቅመ ምስለ ባዕድ ፤
ዘመድሰ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ
እስመ ኢተፈልጠ ምስለ እሙ እስከ መቃብረ ይወርድ ።

ት ር ጉ ም

በመዋረድ ጊዜ ዘመድ የለም ፥
ዘመድም በመዋረድ ጊዜ ባእድን ይሆናል ፤
የሰጋ ንብረት በሆነ ማእድ ከፍ ባለ ጊዜ ግን
እንኳን ዘመድ ፥ እንኳን ወገንና
ነገድ ከሌለበትና
ትውልድ ከሌለበት መጥቶ ባእድ ይዘመዳል ።
አይሁድም ሀዋርያን (ጴጥሮስን) በጠየቁት ጊዜ
ፈጣሪውን ተወና ከባእድ ጋር ቆመ ፤
ዘመድስ ዮሀንስ ወልደ ነጎድጓድ ነው
ወደ መቃብር እስኪወርድ ድረስ ከእናቱ ጋር አልተለ
የምና ።

ም ስ ጢ ር

ሾላ በአፈራ ጊዜ ወፎች በቅርንጫፎቹ ፥ ሀፃናትም በስሩ እንደሚሰበሰቡ ሁሉ እንድ ሰው ሀብት ባገኘና በተሾመ ጊዜ ዘመዱ ባእዱ አፋሽ አጎንባሹ ሁሉ ያገለግለዋል ፤ እጅብ እጅብ ያደርገዋል። በተሻረና በደኸየ ጊዜ ግን እንኳን ባእዱ ዘመዱ ይርቀዋል ። እንደዚ ሁም ሁሉ ክርስቶስ አርብ ሊሰቀል ሀሙስ ማታ ተይዞ ሳለ ፥ ተማ ሪው ጴጥሮስ « ኢየሱስን ታውቀዋለህን ? » ተብሎ ቢጠየቅ አላ ውቀውም ብሎ መምህሩን ካደና ከአይሁድ ሰዎች ጋር እሳቱን ይሞቅ ጀመር ።

አንዳንድ መንፈሰ ጠንካራ ወዳጅ ግን በማግኘቱና በደ ስታው ጊዜ የተጠጋውን ወዳጁን በችግሩና በመከራውም ጊዜ አይለ የውም ። ዮሀንስ ወልደ ነጎድጓድም ቀድሞ በባለሟልነት በክርስቶስ አጠገብ እንደተቀመጠ በመስቀልም ስር ሳይለየው ዋለ የክርስቶስንም እናቱን በአደራ ቃል ተቀበለ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

323 መወድስ

ዘአድግሱ (ንቡረ እድ)

ሆሣዕና ዳዊት ወዐለ ውስተ ቤተ መርዓ
እንዘ በአእባን ጎለይት ስብሐታቲሁ ያስተዋድድ
በጊዜ ቅዳሴ ማእረር ለእመ ይነውም አብድ ፡
ወገፍትዐ ማዕዳቲሆሙ በጎብዕት እድ፤
እስመ ኢተጎርዩ ለማዕድ
ሕዝበ ምናሴ ወኤፍሬም ውስተ ቤተ ዳዊት ዘይትፈቀድ ።
ባሕቱ እመ ገፍትዐ ማዕደ ዕልዋን አይሁድ
ኢተከልዉ አእዱግ ውስተ ቤተ ምስላል ወምስጋድ ፤
አሣዕነ እእጋር ጥቀ እምአእጋረ ሙሴ ፀግድ
እንዘ ክሉአን በደብረ ሲና መካነ መብረቅ ወነጐድጓድ ።

ት ር ጉ ም

በምስጋና /አዝመራ ጊዜ ሰነፍ ቢተኛ
የዳዊት ሆሳእና በሙሽራ ቤት ውስጥ
በዘፋኞች /ድንጋዮች ምስጋናዎቹን እያስማማ ዋለ ፡
በተደበቀች እጅም ድርድራቸውን ገለበጠ ፤
የምናሴና የኤፍሬም ወገኖች
በሚወደድ በዳዊት ቤት ውስጥ ለማእድ አልተመረጡምና።
ነገር ግን የወንጀለኞች አይሁድ ግእድን ቢገለብጥ
የእግሮቹ ጫማዎች እንኳን የመብረቅና የነጎድጓድ ቦታ
በሆነ በደብረ ሲና ከአገልጋይ ሙሴ እግሮች የተከለከሉ
ሲሆኑ እሀዮች በመለመኛና በመስገጃ ቤት ውስጥ አልተ
ከለከሉም ።

ም ስ ጢ ር

ሙሽራ ጫጉላው ውስጥ በዘፋኞች ሚዜዎቹ እየተመሰገነ ሲደ
ስት ዘፈን የማያውቀው ዝም ይላል ። እንዲሁም የዳዊት ሆሳእና
የተባለ ክርስቶስን የተፈጥሮ እውቀት የሌላቸው ድንጋዮች ሲያመሰግ
ኑት የተፈጥሮ እውቀት ያላቸው አይሁድ በዝምታ ድንጋይ ሆኑ ።
ደግሞ ልጆች እንጂ ሽማግሌዎችና ባልቴቶች ወደ ሙሽሮቹ ጫጉላ
ለመግባት እንደማይሯሯጡ የአይሁድ የሽቀጣቸው ድርድር ሲመነ
ቃቀርና እነርሱም ከመቅደስ ቦታ ሲባረሩ ሆሳእና (ክርስቶስ)የተቀ
መጠባቸው አህዮች ወደቤተ መቅደስ ገቡ ። ለልማዱም ያገቡት ጎልማ
ሶች እንኳን ቢሆኑ ወደ ጫጉላ ቤት መግባት እንደሚያፍሩ ፡
ሙሴ በደብረ ሲና ወደ እሳቱና ነበልባሉ ከእነጫማው በቀረበ ጊዜ
የእግሩ ጫማዎች እንዲወልቁ ተደረገ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

324 መወድስ

ዘውብሽት (ቁሰ ገበዝ ፡ ዘብኖና)

ማርያም አነ እንተ እዜከሮ
ለመከራኪ ኤርምያስ ዘተረስዐ በጎበ አብድ ፤
አምጣነ በጽሐኒ ሌተ በብሔረ ባዕድ
ለኪ ዘበጽሐኪ
ብዝኀ ጸዊሮቱ ለንዑስ ወልድ ፡
ወአድባረ ገዳም አዐውድ
እንዘ አኀሥሥ ከማኪ ሲሳየ ዕለት ዋሕድ ።
እቅዳሕሂ ማየ አንብዕ በዘዚአኪ ልግድ
ልሕኵተ ረኃብ ጸዊርየ ዕመቀ ዮርዳኖስ እወርድ ፤
ወቀሪቦትየ ፈርሁ መባልዕተ ሥጋ አዝግድ ፤
ለዘየአምሩኒ መባልዕት እስመ ኮንኩ ከመ ነግድ ።

ት ር ጉ ም

ማርያም! በሰነፍ ዘንድ
የተረሳ መከራሽ /ኤርምያስን የማስበው ነኝ (አስበዋለሁ) ።
ለአንች የደረሰሽ ትንሽ ልጅን
የመሸከም ብዛት
ለእኔም በባእድ አገር ደርሶኛልና ፣
እንደአንቺም የአንድ
ቀን ምግብን እየፈለግሁ የደን ተራሮችን እዞር ነበርና ።
በአንቺ ልማድም እንባ/ ውሃን እቀዳ ዘንድ
ራብ /ጎንቦን ተሸክሜ ወደ ዮርዳኖስ ጥልቀት እወርዳ
ለሁ ፤
የስጋ መብሎች / ዘመዶችም መቅረቤን ፈሩ ፤
ለሚያውቁኝ መብሎች እንደ እንግዳ ሆኛለሁና ።

ም ስ ጢ ር

«ያለብሽ አለብኝ አዘንን የፈተነ (የቀመሰ) አዘንን ያውቃል» እንዲሉ ፣ ባለቅኔው እንደ ቅድስት ማርያም ከአንዱ ወደሌላው በመሰደድ በመራባቸውና በመጠማታቸው አንፃር የማርያምን መጉላላትና መሰቃየት አስታውሰዋል ። ውሃን ለመቅዳት ጎንቦ ተሸክሞ ወደ ወንዝ እንደመውረድም ከመራብ የተነሳ ባለቅኔው እንባቸውን አዥጎድጉደዋል (ዱብ ዱብ አድርገዋል) ። ተስህቦ (ወረርሽኝ) የያዘውንም ሰው ዘመዶቹ ለመቅረብ እንደሚፈሩት ቀድሞ የለመዱት መብል መጠጥ በችግራቸው ጊዜ አልተገኘላቸውም።

ነቢዩ ኤርምያስም በኩስ ጓድጓድ ተጥሎ ሳለ የሚያስታውሰው እንደታጣ የማርያምን መራብና መጠማት በስደታ ወቅት ያወቀላት የለም በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

325 መወድስ

ዘሙሽት (ቋሰ ገበዝ ፡ ዘጣቸና)

ግፋዕ ዐይንኪ በርተሎሜዎስ
ውስተ ባሕር ወደቀ በዘአሪታዊ ልማድ ፡
አምጣነ ጎየሉ ብኪ ብካያትኪ አይሁድ ።
ውኃልቀ በከዊነ ማይ ዐይንኪ በረድ ፡
በላዕለ ሰልሞን ዐውደ ግብጽ
አኮኑ ውእቱ ኢየዐርፍ ለወረድ ።
ዳዊትሂ ጽንዐ ረኃብ አመ ተምዐ በዐውድ
ናባል ልቡናኪ ወዐለ በረዓድ ፡
ወአመ ተመልሐ ብኪ ሰይፈ ነበልባል ወነድ
ሐርጌ ዘደማስቆ ፡ ወሐርጌ ዘገለዓድ ።

ት ር ጉ ም

የተገፋ በርተሎሜዎስ አይንሽ
በአሪት ሰው ልማድ በባህር ውስጥ ወደቀ ፡
አይሁድ ለቅሶዎችሽ በርትተውብሻልና ።
በረድ አይንሽም ውሃን በመሆን አለቀ ፡
በግብፅ አደባባይ ደጋ ላይ
እርሱ (እንባ) ለመውረድ አያርፍምና ።
የራብ ጥናት ዳዊትም በአደባባይ በተቆጣ ጊዜ
ልብሽ ናባል በመንቀጥቀጥ ዋለ ፡
የእሳትና የነበልባሉ ሰይፍም በተመዘዘብሽ ጊዜ
የደማስቆ ጌደር ሆንሽ ፡ የገለአድም ጌደር ነሽ ።

ም ስ ጢ ር

ሀዋርያው በርተሎሜዎስ የክርስቶን ወንጌል ሲሰብክ አይሁድ ባሰቀዩት ጊዜ በባህር ውስጥ እንደተጣለ የቅድስት ማርያም አይን

በስደት ጊዜ መከራ በዛበት እንባውን እነባው ። በረዶም በጮቄ ላይ (በቅዝቃዛ ቦታ) እየወረደ እንደሚሟሟ የማርያም አይን እን ባን በማንባት ብዛት ተሰረንደ (ወደ ውስጥ ገባ) ጎደንደ ።

ዳዊትም በተቆጣ ጊዜ ናባል በድንጋጤ እንደተንቀጠቀጠ ፣ በማርያምም ራብ በፀና ጊዜ ልቧ ተንሰፈሰፈ ። ከዚህም ሌላ ሰይፍ የተመዘዘባት ጊዶር እንደምትበረግግ የሄሮድስ ሰይፍ በልጅዋ የተመዘ ዘባት ማርያም ወደግብፅ ሽሽች በማለት ባለቅኔው በማርያም የደረሰውን መከራና ስቃይ በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

ታ ሪ ክ

በእስራኤል አገር ቀርሜሎስ በሚባል ቦታ የሚኖር ናባል የሚ የል ባለፀጋ ነበር ። ሚስቱም አቤግያ ትባላለች ። ዳዊት ከሳኦል ሸሽቶ በሽፍትነት በዱር ሳለ ለሰራዊቱ ምግብ እንዲልክለት ወደ ናባል መልእክተኞችን ላከ ። ናባል ግን ለዳዊት የንቀት መልስ ላከ ለት ። ዳዊትም በናባል አድራጎት ተቆጥቶ ናባልና ቤተሰቡን ለመበቀል ከነሰራዊቱ ወደ ቀርሜሎስ ሲሄድ የናባል ሚስት አቤ ግያ ዳዊት የጠየቀውን ሁሉ አስጭና ከመንገድ ተቀበለችው። ዳዊ ትም አቤግያ የሰጠችውን ተቀብሎ ተመለሰ ። አቤግያ ዳዊትን ከነ ሰራዊቱ አስተናግዳ እንደተመለሰች ለናባል የዳዊትን መምጣት ብት ነግረው ደንግጦ ሞቷል (1ሳሙ. 25፡2—23) ።

326 መወድስ

ዘገብረ መድሀን (መምህር ፣ ዘማኅደረ ማርያም)

በሊሕ እግርኪ ለክኒወ ደም ፤
እስመ ገራህተ ደም ውእቱ ርስተ አቡኪ ተሰዶ ።
ወእመ ተጐለቈ ብኪ መጥባሕተ ሄሮድስ ተዘምዶ
አብርሃም ክሣደ ወልድኪ ለይስሐቅ ወለዶ ፤
እስመ ሰፍሐ መከየዶ
ዲበ ኤዶምያስ ግብጽ ቅርብት ለአንድዶ

ዘመንበረ ወርቅ ማርያም ወዘሠረገላ ተዋሕዶ !
ወመራሔ ፍናት ሰናኩኪ ለያዕቆብ ተካየዶ ፤
እስመ ይብል ዮሴፍ ጸሐፈ መልእክት ተፈቅዶ
የአርር አሜከላ ዘዘርዐ ተዋርዶ ።

ት ር ጉ ም

የወርቅ ወንበርና የተዋሀዶ ሰረገላ
የሆንሽ ማርያም ! «እግርሽ ደምን ለማፍሰስ ፈጣን ነው»
የአባትሽ ርስት መሰደድ የደም እርሻ ነውና ።
የሄሮድስ ሰይፍ ዝምድናም በተቆጠረብሽ ጊዜ
አብርሃም የልጅሽ/ አንገት
ይስሀቅን ወለደው ፤ ለማንደድ በቀረበች
በግብፅ/ ኤዶምያስ ላይ መሄጃውን (እግሩን) ዘርግታልና ።
መንገድ መሪ/ ተረከዝሽም ያእቆብን ቃል ኪዳን ተጋባው ፤
የመልእክት ፀሀፊ ውዴታ (መፈቀድ) ዮሴፍ
« መዋረድን የዘራ እሾሀን ይለቅማል» ይላልና ።

ም ስ ጢ ር

የጨካኝ እግር የሰውን ደም ለማፍሰስ እንደሚፋጠን የቅድስት ማርያም እግር በስደቷ ጊዜ በእንቅፋትና በእሾህ ደግ ። ደግሞ አንዳንዱ ርስት የደም መፋሰሻ እንደሚሆን በእንቅፋት መድ ማትን ያመጣው መሰደድ ነው ። ቤትውልድም አቆጣጠር አብ ርሃም ይስሀቅን ወለደው እንደሚባል ፣ የቅድስት ማርያም የል ጁዋ አንገት እንደ ይስሀቅ ሳይታረድ ቀረ ፤ ምክንያቱም እግር በአልጋ ላይ እንደሚዘረጋ ልጅዋ ወደግብፅ ስለተሰደደ ነው ። አምላክም ያእቆብን በመንገድ ድንጋይ እንደተካየደው (ቃል ኪዳን እንደተጋባው) የክርስቶስን ህይወት ለማዳን የተሰደደች የማርያምን እግር ድንጋይ ገረፈጠው ።

ጳውሎስም «ብዙ የዘራ ብዙ ያገኛል » እንዳለው አብሯት የተሰደደው ዮሴፍ እንደርሷ ውርደትን ተቀበለ ፣ በእሚከላም (በእሾህ) ተወጋ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

327 ዘይእዜ

ያስተጋብእ ቶማስ መስተገብር
ማእረረ ገድሉ ብዙኅ በአስተጋብአ አእዳኅ ፣
እስመ እክል ገድሉ እምልአት ኢነትገ ፣
ምስለ መኑሂ በገድል ጸማ ቅዱሳን ኢተዛወገ ፤
በርእይ ደቂቀ ወአእሩገ
እስመ ጕንደ ዕፅ ይፀውር ወድርዓተ ልብ ኀደገ ።
በርእይ ደቂቀ ወአእሩገ

ትርጉም

ገበሬ / ቶማስ አህዮችን
በመሰብሰብ ብዙ አዝመራ / ገድሉን ይሰበስባል ፣
እህል / ገድሉ ከሙላቱ አልጎደለምና ፡
ከማንም ጋር በቅዱሳን ድካም ገድል አልተጎራበተም ፤
ሽማግሌችና ልጆችን በማየት
የእንጨትን ግንድ ይሸከማልና ፣ የልብ ጭካኔንም ትታልና።
ሽማግሌችና ልጆችን በማየት

ምስጢር

ገበሬ አህዮችን ሰብስቦ ምርቱን እንደሚጭን የክርስቶስ ሰማእት ቶማስ የተቀበለው መቆረጥ ለአህዮቹም ተረፋቸው ። ደግሞ ይሄው ገበሬ ልጆችና ሽማግሌች ወላጆችን በማየት (የትጉህ ሰዎችን ምሳሌ በመከተል) ጌጥ ሳይሻ ለቤቱ ግንድ እየተሸ ከመ እንደሚኖር ከሰማእታትም መካከል እንደ ሰማእቱ ቶማስ

የተሰቃየ የለም ። ምንም እንኳን አስራ አራት አልፍ የገሊላ ሀገ ናት በክርስቶስ ምክንያት አንገት አንገታቸውን ቢቆረጡና የቀ ደሙ ነቢያትም ቢሰቃዩ ክርሱ አካላት አንዱ አልቀረለትምና የሰማእቱ ቶማስ ስቃይ ከሁሉም ስቃይ ይበልጣል ይላሉ ባለቅኔው ።

328 ሚበዝኁ

እመ እኅተ ሙሴ ነቢይ
እብነ ቢታንያ ዘበጠት ከበሮ ስብሐት በእብራይስጢ
ተክለ ሃይማኖት ይብል ተመየጢ ተመየጢ
ሰላመ ሰጣዊት ልብስየ
ወይነ መላእክት ስብሐተ ውስተ አፉኪ ትሱጢ ።

ትርጉም

የነቢይ ሙሴ እህት
የቢታንያ ድንጋይ ምስጋና / ከበሮን በእብራይስጥ ብት መታ
ተክለ ሃይማኖት ሰላመ ሰጣዊት (በጣም የተዋብሽ) ልብሴ !
የመላእክት ወይን / ምስጋናን
ከአፍሽ ትጨምሪ ዘንድ ተመለሺ ተመለሺ አለ ።

ምስጢር

የሙሴ እህት ማርያም በእብራይስጥ ቋንቋ ከበሮን እየመታች የእግዚአብሄርን ምስጋና እንደዘመረች የቢታንያ ድንጋይ በሰብ አዊ ልሳን የአምላክን ምስጋና ተናገረች ። እንዲሁም አዝማሪት ስትዘፍን አዳማጪዋ «እስኪ መለስ በይና ከወይኑ ተጎንጪ» እን ደሚላት የአቡነ ተክለ ሃይማኖትም ልብስ እንደቢታንያ ድንጋይ ምስጋናን አመሰገነች በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

329 መወድስ

ሩፋኤል መልአክ ቀስታመ በካፋ
ለመቅደስከ ዐባይ ዘተሣረረት በየውጣ
አንበሳ ነነዌ ድቀት ኢይመሥጣ ፡
ወዕንቄ ቢረሌ ኢይከውን ሜጣ ፤
አዕግዲሃ እስመ ተለብጣ
አፍአሃ መብረቀ ወነጐድጓደ በውስጣ
ግብጽኒ በለሰ ግብጽ ዘኢተአምር ተውላጣ
ታሕመለምል ለበረድ ወትፈሪ ለአንበጣ ፤
ወለሰግርያ ሜላት ዘወልዶ አዴር ሠጠጣ
ሆሴዕ በፈረሱ እምይእዜ ኢይመይጣ ።

ት ር ጉ ም

የበካፋ በሎታ (ዱላ) መልአክ ሩፋኤል !
በየውጣ የተሰራች ታላቅ መቅደስህን
የነነዌ አንበሳ መውደቅ አይነጥቃትም ፡
ብርሌ የሚባል እንቁም ዋጋዋ አይሆንም ፤
በውጭዋ መብረቅን
በውስጧም ነጎድጓድን አምዶቿ ተለብጠዋልና ።
ለውጪን የማታውቅ የግብፅ በለስ/ ግብፅም
ለበረድ ትለመልማለች ለአንበጣም ታፈራለች ፤
የአዴር ልጅ የቀደዳት የሀር ልብስ/ ሰግርያንም
ሆሴእ በፈረሱ ከእንግዲህ አይመልሳትም ።

ም ስ ጢ ር

ይህ ቀረሽ የማትባል መልከ መልካም ሴት ወደር የለሽ (ማጫሽ) ትባላለች ። ባለፀጋ ሰው እንኳን ማጫዋን ሊከፍል አይችልም ፤ የላይ ካባዋና የውስጥ ቀሚሷ ወርቀ ዘቦ ናቸውና ። እንዲሁም ምሳሌዋ የሆ

ነችው በጎንደር ከተማ አጼ በካፋ ያሳነፁዋት የሩፋኤል ቤተ መቅደስ ስራዋ ስለተዋጣላት ምንጊዜም መውደቅ አያገኛትም መሰልም የላትም ። አምዶቿ መብረቅ ይመስላሉ ፤ የዝግሬውንም ድምፅ እንደ ነጎድጓድ ታስተጋባለች ።

ደግሞ በለስ ለምልማና አፍርታ በረዶ እንደሚጨፈጭፋትና አንበጣ እንደሚበላት ግብፅን አምላክ ስለ እነሙሴ በበረዶና በአንበጣ ቀጣት ። የሀር ልብስንም ልጅ ጨርሶ ከቀደደው በሁዋላ ዳግመኛ መስፋት እንደሚያስቸግር የሶርያ ንጉስ ወልደ አዴር የዘረፋት ሰግርያን ሆሴእ መልሶ ሊያቋቁማት አልቻለም ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

330 ዋዜማ

አልዐሉ አዕይንቲሁ
ለተክለ ሃይማኖት ዮሴፍ እኅወ ኪሩቤል አብያጽ
ይምጽኡ ማያተ ጸጋሁ ተንባላት እምግብጽ ፤
አምጣነ ልብሱ ካልእ መርድኤ መትከፍ ወገጽ
በደሮ ለመልአክ ጴጥሮስ እንዘ ይረውጽ
ኀበ ሀሎ ዘተቀብረ ድምፅ ።

ት ር ጉ ም

የፀጋው ውሃዎች/ ማላጆች
ከግብፅ ይመጡ ዘንድ የኪሩቤል ጓደኞች ወንድም የሆነ
የተክለ ሃይማኖት/ ዮሴፍ አይኖችን ከፍ አደረጉ ፤
ልዩ ልብሱ/ የትከሻና የፊት ተማሪ
የተቀበረ ድምፅ ወደአለበት እየሮጠ
ጴጥሮስ/ መልአክን ቀድሞታልና ።

ም ስ ጢ ር

ውሃዎች በመጣያ ገደል (ከረጅም ገደል) ላይ ሲፈሱ ከፍተኛ ድምፅ ይሰማል ። እንዲሁም የፀጋው ሀይሎች እንደኪሩቤል በክንፍ የሚበር ተክለ ሃይማኖት አይኖች ሰማያዊውን ምስጢር እንዲያዩ አደረጉ ። ጴጥሮስንም ሌላው ተማሪ ዮሀንስ የክርስቶስን መቃብር ለማየት እንደቀደመው የተክለ ሃይማኖት ልብስ ከመልአክ የበለጠ አመሰገነ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

ታ ሪ ክ

የያእቆብ ልጅ ዮሴፍ በግብፅ አገር ሳለ የሸጡት ወንድሞቹ በራብ ምክንያት እሱ ካለበት አገር (ግብፅ) እህል ለመሸመት ሄደው ወደርሱ ገቡ ። ቃል በቃል ሲያነጋግራቸው ሁላችንም የአንድ ሰው ልጆች ነን ፤ አንዱን ታናሽ ወንድማችንን ግን አውሬ በልቶታል ብለውታል (ዘፍጥ . 46—47) ።

331 ሥላሴ

ቁሣር ጊዜ ልደቱ
ከርሠ ወላዲቱ ሠጠቀ ከመ ይሠጥቆ ለዕፅ ፣
ወውስተ ሥጣቁ ይበውእ ስርዋጽ ፤
ክርስቶስሰ አምላክ አምላካ ለግብጽ
እንዘ እምልአቱ ኢያሐጽጽ ፣
ወዕለ እምጎቱም አንቀጽ
ከመ ሀፍ ይወዕእ እምገጽ ።

ት ር ጉ ም

እንጨትን እንደሚሰነጥቅ
በስንጣቂውም ውስጥ ሽብልቅ እንደሚገባ ፣ በልደቱ ጊዜ
ቁሳር የእናቱን ሆድ ቀደደ ፤
የግብፅ አምላኳ አምላክ ክርስቶስ ግን

ከሙላቱ ሳይነድል ፣
ወዝ (ላብ) ከፊት እንዲወጣ
ከተዘጋ በር ወጣ ።

ም ስ ጢ ር

እንጨትን በምሳር እንደመሰንጠቅና ስንጣቂውን በሽብልቅ እንደመለየት ቁሳር ሲወለድ የእናቱን ሆድ ቀዶ እንደወጣው አወጣጥ ሳይሆን ክርስቶስ በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና ተወለደ ይላሉ ባለቅኔው ።

332 መወድስ

ገሠጻ ዮሐንስ ገሠጻ ልቡና
ከመ ትትመሀር ጥበበ ለእንተ ገሠጸቶ ቢጽ ፤
ጸድቃነ አፍአሰ ንሕነ እለ ናደሉ ለገጽ
ንጌሥጽ ካልአነ
እንዘ ለርእስነ አልቦቱ ተግሣጽ
ወካልአ ንዔምጽ ።
ምሳሌ ዝኒ ነገር እመ በልቡና ናስተሐይጽ
ለበሊሕ አፈ መላጺ ዘአካለ እብን ልሙጽ
መቅረጸ ሥዕርት ይሬስዮ እንዘ ለሊሁ ኢይቀርጽ ፤
ወማየ ሰሊሆም ይጹር እንተ አንበርዎ ዕፅ
ያሠርፅ ካልአነ እንዘ ለሊሁ ኢይሠርፅ ።

ት ር ጉ ም

ልቡናው የተገሰፀ ዮሀንስ
የገሰፀችውን ጓድ ጥበብን እንድትማር ገሰፃት ፤
ለፊት የምናደላ የውጭ እውነኞች እኛ ግን
ለራሳችን ግሳፄ

ሳይኖረው ሌሎችን እንቆጣለን
ሌላውንም እንበድላለን ።
የዚህን ነገር ምሳሌም በልብ ብንመለከት
ልሙጥ የሆነ የድንጋይ አካል እርሱ ሳይቀርፅ
የተባ (ስለታም) የምላጭ አፍን የራስ ጠጉር መላጫ ያደ
ርገዋል ፤
የመስኖ ውሃንም እንዲሸከም (እንዲይዝ) ያስቀመጡት
ድንጋይ
እርሱ ሳይበቅል ሌሎችን ያበቅላል ።

ም ስ ጢ ር

ልሙጥ የሆነ ለሆቴ (ብረት መሳያ) ድንጋይ እርሱ ራሱ ሌላ ውን ሳይቆርጥ ምላጭን በመሳል የራስ ጠጉርን እንዲላጭ እንደ ሚያደርገውና የውሀ ገንዳም እርሱ ራሱ በውሃ ሳይለመልም ፣ ሌሎ ቹን አትክልት እንደሚያበቅልና እንደሚያለመልም ፤ አንዳንዱ ሰው ለራሱ ሳይመክርና ሳይገሰፅ ሌላውን ልምከርና ልገሰፅ ይላል ። ይሁን እንጂ «ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም» እንዲሉ እንዲህ አይነቱ ሰው ምንም ለራሱ ባያውቅ ፣ ምክሩና ተግሳፁ መልካሞች ከሆኑ ሌሎቹን ሊጠቅሚቸው ይችላሉ ። መጥምቁ ዮሀንስ ግን በቅ ድሚያ ራሱን ገስፆና ቀጥቶ ሲያበቃ ምክሩን ያልተቀበለች የፊ ጥልቅ ውስጥ አሰጠማት በማለት ቅኔው ተመስጥሯል ።

333 መወድስ

ዘለግ ጎይሉ (አለቃ)

መዝገበ ተግሣጽ አንበሩ በይነ ውሉደሙ
አበወ ሥጋ ዘሠምሩ መዐዛ ፍቅሮሙ ዕፅ
ከመ ኢይትዐጸው ቦሙ ሕይወተ ውሉድ እንቀጽ ፤

ወበበገጸሙ ይከዕዉ
ትብዐ ተግሀሎ ከመ ይብራህ ገጽ ።
ባሕቱ ድኅረ ዘመን
መወልጠ ሥርዐት አብ እመ ጎቤሆሙ ይሔውጽ
ለመዝገበ ልግድ ቀበርዎ ውስተ ቀራንዮ ምርዋጽ ፤
እስመ አብ ዘወለዶ በእንተ ወልዱ ኢይጌሥጽ ፣
ወእንዘ ፍቅሩ ምሉእ እመስፈርተ ይስሐቅ ቢጽ
በግዐ ለቤዛሁ እምጉንደ መስቀል ኢያሠርፅ ።

ት ር ጉ ም

የፍቅራቸው እንጨት መአዛን የወደዱ
የስጋ አባቶች የልጆች ህይወት /በር እንዳይዘጋባቸው
መዝገብ/ ግሰፃን ለልጆቻቸው አኖሩ ፤
ፊትም እንዲበራ
ይቅርታ/ ቅቤን በየፊታቸው ያፈሳሉ ።
ነገር ግን ከዘመን በኦዋላ
ስርአትን ለዋጭ አባት ወደርሳቸው ቢጎበኝ (ቢመለከት)
ልግድ/ መዝገብን በመሮጫ/ ቀራንዮ ውስጥ ቀበሩት ፤
የወለደው አባት ስለልጁ አይቆጣምና ፣
ፍቅሩም ከጓደኛ ይሳሀቅ መስፈሪያ ይልቅ የሞላ ሲሆን
በግን ለቤዛው ከመስቀል ግንድ አያወጣምና ።

ም ስ ጢ ር

ልጆቻቸው በህይወት እንዲያድጉላቸው የልጆቻቸውን ፍቅር እንደ እንጨት መአዛ ያደረጉ የስጋ አባቶች ሀብት በጥንቃቄ ይቀ መጣል ። ልጆቻቸውን ይገስፁዋቸዋል ለጥፋታቸውም ይቅርታ ያደ ርጉላቸዋል ። እግዚአብሄር አብ ግን ስርአትን በስርአት በመለወጥ የወላጆች ልግድን ተወው ። በልጁ በእግዚአብሄር ወልድ ላይ ስለተ ፈፀመው የጭካኔ ድርጊት አልተቆረቆረም ። ጭራሹንም ስለልጁ

ህይወት በአባትና በልጅ ልማድ አልተጨነቀም ። እንደ ይስሀቅም ጊዜ ለልጁ ቤዛ በግን ከልጁ መስቀል ስር አላስገኝም ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

334 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘካሣ (ቁሰ ገበዝ)

ምዕመናን ለቅብዕ ብእሴ ነቢብ አእላፈ
ሎቱ አርምሙ ወኢተሀብም አፈ ።

ትርጉም

አማኞች ! ብዙ ለሚናገር ሰው/ ቅቤ
ዝም በሉለት አፍም አትስጡት ።

ምስጢር

ነገረኛን ሰው የሚያሸንፈው ዝምታ እንጂ ብዙ መናገር አይደለም ። በአንፃሩም አማኞች ለቅቤ አፍ አትስጡት በማለት በያም ጊዜ አፋችሁ ቅቤ አይቅመስ ብለው ባለቅኔው ያመኞችን በቅኔያቸው ምስጢር አስጠንቅቀዋል ።

335 ዘይእዜ

ዘሰማ ጎይሉ (አለቃ)

ነጸረ ጴጥሮስ ያፈ ሰማይ
እንበለ ማእረር ወዘርዕ ለአሠንዮ ጽርሕ ትሩፍ ፤
እስመ እንበለ ዘርዕ ወማእረር
ለምጽላለ ርእሳ ዘትጸሙ ያፍ ።
ወአመ ይሰምዕ ቃለ እምነ ደመና ልብሰ መትከፍ

ተዘክረ ታቦር በዓለ መጽሐፍ
ድንጋጌ ለጴጥሮስ ከመ ደዌሁ ዘዘልፍ ።
ተዘክረ ታቦር በዓለ መጽሐፍ

ትርጉም

ጴጥሮስ ያለዘርና አዝመራ
ትርፍ ቤትን ለማሳመር የሰማይ ወፍን ተመለከተ ፤
ወፍ ያለዘርና አዝመራ
ለራሷ ማረፊያ የምትጥር ናትና ።
ከትክሻ ልብስ/ ደመና ቃልን በሰማ ጊዜም
ባለ መፅሀፍ/ ታቦር አስታወሰ
ድንጋጤ የጴጥሮስ የዘወትር በሽታው እንደሆነ ።
ባለመፅሀፍ/ ታቦር አስታወሰ

ምስጢር

ክርስቶስ «ወፎች ሳይዘሩና ሳይማርሩ እንዲመገቡ ተመልከቱ» ያለውን ጴጥሮስ በደብረ ታቦር አፀደቀ ፤ ምክንያቱም ወፎች ያለ ዘርና ያለአዝመራ እንደሚመገቡ ፣ እርሱም ለቤት ስራ የሚያስፈልጉት ነገሮች ሳይኖሩ «ሶስት ቤቶችን ሰርተን በዚህ ብንኖር መልካም ነው» ብሏልና ። በዚህም ላይ የደመና ነጎድጓድን ሰምቶ የደነገጠ መፅሀፍን መርማሪ ሰው ድንጋጤ በሽታ እንደሆነ ያስታውሳል ፤ እንዲሁም የወልድ ልብስ እንደበረዶ በሆነበት (በነጣ በት) በደብረ ታቦር ጴጥሮስን ድንጋጤ እንደ በሽታ እንዳስተኛው ነተገረ ማለት ጭምር በቅኔው ተመስጥሯልታል ።

336 መወድስ

አ አብዳን ሰብአ ገላትያ
ዘገፋዕናክሙ ምንት ሰብአ ደብረ ምጥማቅ አእላፍ ?
ንቃወ ምዝባሬ ካልእ ዘጥቅመ ሰናያር ያፍ
ለቤተ መቅደስነ ትንግርዋ

ዘበጽሐ እግረ ሠራፊሃ እስከ ጽንፍ እምጽንፍ ፣
ወእስከ አድማስ ዮኀልፍ ፤
ባሕቱ ይመትር ዘለፋክሙ እንበለ ሰይፍ ።
ንሔውጽኂ ዘለፋክሙ በመሳክወ ልብ ወአፍ
ወአኀው ዮሴፍ መጻሕፍተ ለዘለፋክሙ ንጽሕፍ ፤
እስመ እንዘቦ ሕያወ እሞተ ሥጋ ግዙፍ
ሞተ ዮሴፍ አኀዊሁ ነገርዎ ለዮሴፍ ።

ት ር ጉ ም

ሰነፎች የገላትያ ሰዎች ሆይ !
እግር/ ስራዋ ከዳር እስከ ዳር ለደረሰና እስከ አድማስ ለአለፈ
የሰናኦር / ወፍ ሀንፃ ሁለተኛ የሆነ መፍረስ/ ጩኸትን
ለቤተ መቅደሳችን ትነግርዋት ዘንድ
ብዙዎች የደብረ ምጥማቅ ሰዎች የበይልናችሁ
በደል ምንድንው ነው ?
ነገር ግን ስድባችሁ ያለ ሰይፍ ይቆርጣል ።
ስድባችሁንም በልብና በአፍ / መስኩቶች እንጎበኛለን
የዮሴፍ ወንድሞች / መፃህፍትንም ለስድባችሁ እንፅፋለን፤
ከደነደነ የስጋ ሞት ደህና ሳለ
የዮሴፍ ሞትን ወንድሞቹ ለዮሴፍ ነግረውታልና ።

ም ስ ጢ ር

የወፍ ጩኸት በንጋት እንደሚሰማ ነቃፊዎች የሰናኦር ሀንፃ መፍረስን በደብረ ምጥማቅ ቤተ ክርስቲያን አወሩባት ። እግርም ከዳር እስከ ዳር እንደሚሄድ የደብረ ምጥማቅ ዝናዋ በሁሉ ተሰምቷል ፤ ሰይፍም አካልን እንደሚቆርጥ የነቃፊዎች ስድብ ያበሳጫል ። በመስኩትም ብቅ ብሎ እንደማየት ስድባቸው በሀሊና ሲታሰብና በአፍ ሲነገር በተግባራቸው ከዮሴፍ ወንድሞች ጋር መነፃፀር አላቸው (ይነፃፀራሉ) ። ዮሴፍ ወንድሞቹን በባእድ አገር(በምድረ ግብፅ) እንደ ባእድ ሆኖ ስለትውልዳቸው ቢጠይቃቸው አንዱ ታናሽ ወን

ድማችን ሞቷል ብለው የራሱን ለራሱ (ለዮሴፍ) እንዳረዱት ፣ ወሬኞችም የደብረ ምጥማቅ ቤተ ክርስቲያን ደህና ስትሆን እንደ ፈረሰች ቆጠሯት ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

337 መወድስ

ዘእለ ወርቅ ዘውዱ (አለቃ)

በሶስት ወር ከረምት ዝናብ የዳኘነት ፍርድ
ግበል ወሰደው ምድሩን አጥረገረገው ሰውም ሳይተርፍ
ልግመኛው ቅጥረኛ በሬ ጠምዶ ሲጉነፈነፍ ።
እሪትና ወንጌል ቢለፈልፉም
ግንም አልረዳቸውም በብዙው መለፈፍ ፤
ሁሉም ለእራሱ ይጥራልና
ጥሪት እየያዘ ሊሸሽ ልክ የሌለው ግበል ሲጎርፍ ።
ቆረቆንዳውም አልተቆረጠም ገና በጭቅጭቁ ሲረግፍ
ዘንጋዳ የተባለው ሰነፍ ምርት ሆኖ በመነጠፍ ፤
ድንጋይ ለቃሚ ሲቀጥር የወፍ ቅጥረኛው ሰነፍ
አይወርድምና ከራሱ ላይ መአት የሆነ ግማት ወፍ ።

ም ስ ጢ ር

ከሰኔ 26 እስከ መስከረም 25 ቀን ያለው ሶስት ወር ክረምት ይባላል ። ክረምት ሲበረታ የሚዘንበው ዝናብ ጎርፍ ፣ የማእበል መከላከያ ግድብ ያልተደረገለትን መሬት እየሸረሸረ ይወስደዋል ። አንዳንድ ጊዜም ሰውንም እንስሳውንም ጭምር ያጥረግርገዋል ። እንዲሁም በሶስት ወር ክረምት የተመሰሉት ሶስት ዳኞች የአድልዎ ፍርድ ድሃውን መሬቱን አስነጥቆ ከመኖሪያ ቀበሌው አሰደደው ። ልግመኛው አራሽ በሬ ጠምዶ እንደሚጉነፈነፍና ለመሬቱ የማእበል መከላከያ ግድብ እንደማያደርግለት ጉቦኛው ዳኛ ያለምጣል ፤ ጉቦ ካልበላ አይሰቅም ያልሰጠውንም ይጠምደዋል ።

የከረምቱ ማእበል በወሰዳቸው እቃና ሰው ላይ ደለል ሲደልልባቸው (ሲጭንባቸው) የጮሁ ሰዎችን ሰምቶ ችግራቸውን የሚረዳላቸው አይገኝም ። እንዲሁም በአሪትም በወንጌልም መማለጃን መቀበልና ፍርድን ማጣመም እንዳይኖር ቢነገርም ትእዛዙን የሚጠብቀው አልተገኘም ፤ ድሃውን ሃብታም በገንዘብ ተዳለለበት ። ዳኞችም ምስክሮችም በገንዘብ እየተደለሉ አዳፍኔ ሆኑ ። ማእበሉም ከወንዙ ድንጋግ (ወሰን) አልፎ እንደሚነርፍ እብለት በዛ ።

ዘንጋዳ የሚባለው ያገዳ እህል አበባውን አርግፎ ለጋ ፍሬ ሲደመድም ጭቅጭቅ ጨቅጭቋል ይባላል ። ቃሉ ከወቀሳ ነገር ጋር ይሞካሻል ። በዚህ አተረጓጎም ግን ለጋ ፍሬን ያዘ ነፍስ አዋለ ማለት ነው ። ይሁን እንጂ በወርቁ በኩል የሙግትን ነገር ይዟል። ዘንጋዳ ሲባልም በሰም በኩል የአገዳ እህል ሲሆን ፥ በወርቁ በኩል ዘንጋ ፥ ዳ ፥ እንደማለት ሁለት ቃላት ይሆንና የቸልታን ፍች ይሰጣል ። ሰነፍ ምርት ማለትም በሰም በኩል ከደቃቁ ገለባው ጨርሶ ያልጠራው ፊስ (ርጋፊ) ሲሆን በወርቅ በኩል የሰነፍ ሰው ስራ ይሆናል።

በመነጠፍ ማለት ደሞ በሰም በኩል ከአፈር ጋር መቀላቀል ሲሆን በወርቅ በኩል የተረሳው መዝገብ ከመዛግብት ውስጥ መቀበሩን ያወሳል ። የዘንጋዳው ፍሬ ጨርሶ ከረገፈ ራሱ ቆረቆንዳ ይሆንና በግጭድ እንደፍሬያማው ሳይቆረጥ እንደሚቀር በሌሎቹ መዛግብት ውስጥ የተቀበረው የድሃው ሰው ጉዳይ በግጭቅጭቅና በሙግት እንዳለ ሳይወሰን ቀረ ። «ወፍ ጠባቂ ለወፍ ጠባቂነት ቢቀጠር ፥ ድንጋይ ለቃሚ (አቀባይ) ቀጠረ» እንዲሉ ወፍ ጠባቂው ጠጠር አቀባዩን ሲያዝዝ የጠጠሩ ቅጥረኛ ጠጠሩን እስኪያቀብለው ወፉ የዘንጋዳውን ፍሬ ያወልበዋል (ይጨርሰዋል) ። ከመዝገብ ቤት ሰራተኛ ራስ ላይ የማይወርድ አሜትም የበላዮችን (የባላስልጣኖችን) ቁጣ ሲያመጣና አንዱ በሌላው ሲያመካኝ የመንግስት አደራ አልተጠበቀም ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

የባለቅኔዎች አጫጭር የህይወት ታሪክ

(የሚቀጥሉት የባለ ቅኔ ሊቃውንት አጫጭር ታሪኮች ባብዛኛው ከ«መፅሀፈ ቅኔ፡ ዝክረ ሊቃውንት» እንዲሁም ከ«የቀድሞ ቅኔዎች ከነትርጓሜአቸው» የተቀሰሱ ናቸው ። ሰፋ ያለውን ታሪክ ከእነዚሁ መፃህፍት መመልከት ይቻላል ።)

ሀይለ ስላሴ (መልአከ ሀይል)

መልአከ ሀይል ሀይለ ስላሴ ወልደ ሀና በሸዋ ክ/ሀገር በደብረ ብርሃን ስላሴ በ1870 አ.ም. ተወለዱ ። በሸዋ በመሎና በጎጃም አድባራትና ገዳማት ከነበሩ ሊቃውንት ዜማ ፥ ቅኔና የመፃህፍት ትርጓሜ ተምረዋል ።

መልአከ ሀይል ሀይለ ስላሴ ትምህርታቸውን ጨርሰው ከተመለሱ በሁዋላም በአዲስ አበባ ከተማ እንጦጦ ራጉኤልን በድብትርና አገልግለዋል ። ብሉያትም በተተረጎሙ ጊዜ ከሌሎች ሊቃውንት ጋር ሆነው ሲራክንና ሰሎሞንን ተርጉመዋል ። ከዚህም ጋር አንደኛ የመካነ ህይወት ገብረ መንፈስ ቅዱስን ደብር በአለቅነት ሁለተኛ እንጦጦ ራጉኤልን መልአከ ሀይል ሆነው አስተዳድረዋል ። መንፈሳዊ ጉባኤም ሲቋቋም በአባልነትና በመንፈሳዊ ዳኝነት አገልግለዋል ።

መልአከ ሀይል ሀይለ ስላሴ በተወለዱ በ85 አመታቸው በ1955 አርፈው በመካነ ህይወት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

ሀይሌ ጉልቤ (አጋፋሪ)

አጋፋሪ ሀይሌ ጉልቤ የሸዋ ክፍለ ሀገር ተወላጅ ናቸው ። አዲስ አበባ በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ስላሴ መጀመሪያ በደብተርነት ሁዋላም አጋፋሪ ተብለው አገልግለዋል ። በቅኔ ሙያቸው የተመሰገኑ ነበሩ ።

ለማ ሀይሉ (አለቃ)

አለቃ ለማ ሀይሉ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት መጨረሻ በመቄት (ላስታ) በአገረ ገነት ኪዳነ ምህረት አጥቢያ ተወለዱ ። አለቃ ለማ በላስታ ፣ በጎንደር በጎጃምና በሸዋ እየተዘዋወሩ ዜማ ቅኔና መፃህፍት ትርጓሜ አጥንተዋል ።

አለቃ ለማ በ1883 አ.ም. የአዲስ አበባ መንበረ ፀባኦት ቅድስ ስላሴ የሀዲስ መምህር ሆነው ተሾመዋል ። ከ1906 አ.ም. ጀምሮ በሀረር በአደሬ ጢቆ መካነ ስላሴ ደብር የሀዲስና የሃይማኖተ አበውን ትርጓሜ እያስተማሩ አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። ከዚህም ሌላ በአዲስ አበባ የቀጨኔ መድሃኔ አለምና በሀረር የጢቆ መካነ ስላሴ አድባራትን በአለቅነት አስተዳድረዋል ።

አለቃ ለማ የመፅሀፈ ቁርሎስን አንድምታ ትርጓሜና የሀዲስ ኪዳንን ነጠላ ትርጓሜ አዘጋጅተዋል ። ለቅዱሳት መፃህፍት ትርጉም ስራም ከተመደቡት ሊቃውንት አንዱ በመሆን ሃይማኖተ አበውን ተርጉመዋል ።

አለቃ ለማ በተወለዱ በ99 አመታቸው በአዲስ አበባ ከተማ ጥር 14 ቀን በ1959 አ.ም. ከዚህ አለም ተለዩ ።

መርሻ ሀይሉ (መጋቢ ፡ ዘዲማ ጊዮርጊስ)

መጋቢ መርሻ ሀይሉ በጎጃም ክ/ ሀገር በታላቁ ገዳም ዲማ ጊዮርጊስ በ1840 አ.ም. ተወለዱ ። ፀዋትወ ዜማ (የዜማ አይነቶች) ና የመፃህፍት ትርጓሜን በዚያው በገዳሙ ከሚገኙት ሊቃውንት ተምረዋል ። ቅኔም አለቃ ተክለ ጽዮን ዲማ በነበሩበት ዘመን ከርሳቸው ተምረው በቅኔ አዋቂነት የተመሰገኑ ሆነዋል ።

እኒህ ሊቅ የዲማ ጊዮርጊስ መጋቢ ሆነው አገልግለዋል ። በ1888 አ.ም. ለጉዳይ አዲስ አበባ እንደመጡ በድንገት ታመው ስላረፉ በአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

መርአዊ (አለቃ)

አለቃ መርአዊ በወሎ ክፍለ ሀገር ግሸን ደብረ ከርቤ ተወል ደዋል ። የቁም ዜማ ፣ ያቋቋምና የቅኔ ባለሙያ ነበሩ ። በንጉስ ሚካኤል ጊዜ የተንታ ሚካኤል ደብተራ ሆነው አገልግለዋል ። በተለ ያየ ጊዜም የደሴ ተክለ ሃይማኖት ደብርና የመቅደላ ቤተ ክርስቲያን አለቃ ሆነው ሰርተዋል ።

መኮንን ሰሎሞን (አለቃ)

አለቃ መኮንን ሰሎሞን ከአቶ ሰሎሞን ግፋ ወሰንና ከወ/ሮ ግብረጃ መንገሻ ሸዋ በደብረ ሊባኖስ አካባቢ በ1871 ተወልደዋል ። በተወለዱበት ቀበሌ ንባብና ቅኔ ተምረዋል ። ከዚህ በሁዋላ ቦሩ ሜዳ ስላሴ ሄደው ከመምህር ወልደ ሚካኤል ሀዲስና ሊቅ አጥንተዋል ።

አለቃ መኮንን ሰለሞን በደብረ ሊባኖስ ገዳም ትርጓሜ መፃ ህፍት እያስተማሩ ኖረዋል ። በዚህም ጊዜ ገድለ ተክለ ሃይማኖትን

ድርሳነ ማህየዊንና ሰአታትን ተርጉመው በግእዝና በአማርኛ አሳትመ ዋል።በተጨማሪም መፅሀፈ ሀዊን ከግእዝ ወደ አማርርኛ ተርጉመዋል።

አለቃ መኮንን ሰሎሞን የአራተግርያምን አለቅነት ተሾመው መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ሳያቋርጡ አርፈው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተቀብረዋል ።

ስመኝ (መሪጌታ)

መሪጌታ ስመኝ በጎጃም ክፍለ ሀገር በእርባብ ወረዳ ጠለዛሞ ግርያም ተወለዱ ። በጎጃም አድባራትና ገዳማት ከነበሩ መም ህራን ፀዋትወ ዜማና ቅኔ ተምረዋል ። የተመሰገኑ ቅኔ አዋቂ ነበሩ። እኒህ ምሁር በጠለዛሞ ግርያም ደብር ተቀምጠው ለረጅም አመ ታት ድጓ ያስተምሩ ነበር ። ከጉባኤያቸውም ብዙ ደቀ መዛሙርት ተምረው ለመምህርነት በቅተዋል ። ድጓ ሲያስተምሩም ዜማውን ብቻ ሳይሆን የንባቡንም ከየት መጣ ጭምር ይነግሩ ነበር ይባላል።

ቀስሙ (መምህር)

መምህር ቀስሙ በጎጃም ክ/ ሀገር በዋሽራ ግርያም ተወለዱ ። በዚያው በትውልድ አገራቸው ተምረው መሀፅፈ መነኮሳትና ቅኔ ሲያስተምሩ ኖረዋል ። ከጉባኤያቸውም ብዙ ሊቃውንትን በትም ህርት ወልደዋል ። ጉባኤያቸውን ሳይፈቱ የዋሸራን ገዳም በመም ህርነት ሲያስተዳድሩ ኖረው በሞት ተለይተዋል ።

በዛብህ ወንድም (አለቃ)

አለቃ በዛብህ ወንድም በጎንደር ክ/ሀገር እስቴ ወረዳ በመ ካነ ኢየሱስ አካባቢ በ1870 አ.ም. ግድም ተወልደዋል ። በመካነ ኢየሱስ ደብር ሀዲስ ካጠኑ በሁዋላ ድባና ቅዱስ ሚካኤል ሄደው

ከመምህር ወልደ ሚካኤል ፍትሀ ነገስት ተምረዋል ። ወደ ሽዋ መጥተው ከአለቃ ወልደ ጊዮርጊስ መፅሀፈ ሊቃውንት ቀፅለዋል ።

አለቃ በዛብህ ወንድም በጎንደር ክ/ሀገር ሊቀ ካህናትና የደ ብረ ታቦር መድሀኔ አለም አለቃ ሆነዋል ። ከዚያም በሁዋላ ወደአዲስ አበባ መጥተው የማህደረ ስብሀት ልደታ አለቃ ሆነው ርስትም ቦታም ተቀብለዋል ። በቦታቸው ላይ የመድሀኔ አለምን ቤተ ክር ስቲያን አሰርተው ንብረታቸውን አውርሰው ሲኖሩ ሰኔ 28 ቀን በ1956 አ.ም. አረፉ ።

ተክለ ሃይማኖት (አቤቶ)

አቤቶ ተክለ ሃይማኖት በጎንደር በበየዳ ኢየሱስ ደብር በ1635 አ.ም. ተወለዱ ። የአቤቶ ተክለ ሃይማኖት አባት እንድርያስ የአፄ ሱስንዮስ ዘመድ ነበር ይባላል ።

አቤቶ ተክለ ሃይማኖት የአራቱን ጉባኤ የባህረ ሀሳብና የቅኔ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በሁዋላ ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ ኖረዋል ።

ተክለ ፅዮን (አለቃ)

አለቃ ተክለ ፅዮን በሸዋ ክ/ሀገር በአንኮበር ወረዳ ሀር አምባ በሚባል ቀበሌ በ1820 አ.ም. ተወለዱ ። በአንኮበር ከተማ ከአ ለቃ ወልደ ስላሴ ትርጓሜ መፃህፍት ተምረዋል ። ወደ ጎጃም ተሻ ግረው ሞጣ ጊዮርጊስ በተባለው በስመ ጥሩው ደብር ከአራት አይና ጎሹ የብሉያትን ትርጓሜ አጥንተዋል ። ብሉይና ቅኔ አዋቂ ነበሩ ።

አለቃ ተክለ ፅዮን በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ብሉይና ቅኔ ማስተ ማር ጀመሩ ። ከዚያም ወደሸዋ ተመልሰው በአንኮበር ከተማ የማ ስተማር ስራቸውን ቀጥለዋል ።

በ1870 አ.ም. ግንቦት 21 ቀን በወሎ ክፍለ ሀገር ቦሩ ሚዳ ስላሴ በአፄ ዮሀንስ ዘመን ከተደረገው የሃይማኖት ክርክር በሁዋላ አለቃ ተክለ ፅዮን ወደኢየሩሳሌም ተሰደው ሄደው ሀዳር 29 ቀን በ1881 አ.ም. አርፈው ከዚያው ተቀብረዋል ።

ተክሌ (መምህር ፡ ዘዋሸራ)

መምህር ተክሌ በጎጃም ክ/ሀገር ዋሸራ ግርያም ተወልደዋል ። ዜማ ፡ ቅኔና መፃሀፍት ትርጓሜ ተምረዋል ። በጣም የተመሰገኑ የቅኔ መምህር ነበሩ ። በዚህም ምክንያት ከዜማና ከመፃሀፍት ትር ጓሜ ሙያቸው ይልቅ የቅኔ ትምህርት ጉባኤያቸው ሰፍቶ ብዙ ሊቃ ውንትን አውጥተዋል ። እስከሞቱም ድረስ ከጉባኤ አልተለዩም ። መምህር ተክሌ በ98 አመታቸው አርፈው በሀገራቸው ዋሸራ ግር ያም ተቀብረዋል ።

ተገኘ (መልአከ ፀሀይ)

መልአከ ፀሀይ ተገኘ በጎጃም ክፍለ ሀገር በብቸና አውራጃ በደባይ ጥላትግን ወረዳ ወንዳሳ ቁስቋም ተወለዱ።ከአለቃ ሸዬ ወልደ ጊዮርጊስ ተምረዋል ። ቅኔና መፅሀፍ አዋቂና ተመራማሪ ሊቅ ነበሩ ።

መልአከ ፀሀይ ተገኘ ደብረ ማርቆስ ሲተከልና ሲደበር ጀምሮ ሊቀ ጠበብት ሆነው አቅንተዋል ። የቤተ ክርስቲያኑን ጥላንም ራሳቸው አውጥተው አናጢዎቹን እየመሩ አሰርተዋል ይባላል ።

መልአከ ፀሐይ ተገኘ በምርምርና ፈጠራ ስራቸው 1ኛ/ በኢ ትዮጵያ የሚገኙ መፃሀፍትን ዝርዝርና የሚገኙበትንም ቦታ የሚ ያመለክት ፡ 2ኛ/ በኢትዮጵያ የነበሩ ሊቃውንትና ደጋግ ሰዎችን የህ ይወት ታሪክ ፡ 3ኛ/ የሊቃውንቱን ቅኔ ፡ ሳኛ/ የኢትዮጵያን ታሪክና የሰንደቅ አላማን ከብር የሚያስረዱ መፃህፍትንና ሌላም ብዙ አይ ነት ፅሁፍ አዘጋጅተው ነበረ ይባላል ።

እኒህ ሊቅ ከ1929 እስከ 1930 አ.ም. ባለው ጊዜ አርፈው በዚያው ደከመው ባቀኑት በደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተቀ ብረዋል ።

ንጉሴ ይመር (አለቃ)

አለቃ ንጉሴ ይመር በጎጃም ክፍለ ሀገር ዲማ ጊዮርጊስ ተወ ለዱ ። በዚያው በትውልድ ቦታቸው ዜማ ከመሪጌታ ደርሰህ ፡ቅኔ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ፡ መፅሀፍም ከመምህር እንግዳ እሸት ተምረዋል ። የሰአሊነት ሙያ ስለነበራቸው አለቃ ንጉሴ በጎንደር ክፍለ ሀገር ኮስተት ዮሀንስ ፡ አጋጥ ፅዮን ፡ ጓሳጥ ሀናና ሽምላኮ ጊዮ ርጊስ የሚባሉ አብያተ ክርስቲያንን ስለዋል ። ወደሸዋም መጥተው ደንዲ የምትባልለዋን ደብር ተሾመው ገበዝም አለቃም እየሆኑ አስ ተዳድረዋል ። በወሎ ክ/ሀገር በደሴ ከተማ የዳኝነት ስራ ሰርተዋል ። ከፋሽስት ወረራም በሁዋላ አጋምና ጊዮርጊስን አለቅነት ተሾመዋል ።

አለቃ ንጉሴ በትምህርት ሚኒስቴር ባስተማሪነት ተመድበው ሲሰሩ ቆይተው በ1948 አ.ም. አርፈው በደጀን ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

አካለ ወልድ (መምህር)

መምህር አካለ ወልድ በሸዋ ክፍለ ሀገር ተወልደው ጎንደር ከመምህር ሀሊብ ተምረዋል ። በወሎ ክፍለ ሀገር በሚገኘው ቦሩ ሚዳ ስላሴ ገዳም ተቀምጠው አራቱን ጉባኤያት ያስተምሩ ነበር ። በቅኔም እጅግ የተመሰገኑ ሊቅ ናቸው ። ከሊቅነታቸው የተነሳ አፄ ቴዎድሮስ መምህር አካለ ወልድን «ይዋጓል እንደ ገብርዬ ይማ ሯል እንደ አካልዬ» ብለው አመስግነዋቸዋል ይባላል ። እኒህ ሊቅ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ንግስት ዘውዲቱ ዘመን ከጉባኤ ሳይለዩ ኖረው ሀዳር 29 ቀን በ1912 አ.ም. አርፈው ባስተማሩበት ገዳም ቦሩ ሚዳ ስላሴ ተቀብረዋል ።

አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)

መልአከ ብርሃን አድማሱ በጎጃም ክፍለ ሀገር በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ነሀሴ 1 ቀን በ1985 አ.ም. ተወለዱ ።

መልአከ ብርሃን አድማሱ በጎጃም ከአለቃ ገብረ ኤልያስና ከአለቃ ገብረ ማርያም ብሉይና ቅኔ ፡ በሸዋ ከካቢው መምህር ወልደ ስላሴ ብሉይ ፡ በወሎ ከደሴው መልአከ ገነት አፈወርቅና ከቦሩ ሜዳ ስላሴው ሊቅ ከመምህር አካለ ወልድ ሀዲሳትንና መፃ ፍተ ሊቃውንትን አጥንተው በዲማ ጊዮርጊሰ ገዳም መፅሀፍና ቅኔ አስተምረዋል ።

መልአከ ብርሃን አድማሱ የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ትም ህርት ቤት መጋቤ ምስጢር ፡ የብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀ ጠበ ብትና መልአከ ብርሃን ፡ በቤተ ክህነትም የመንፈሳዊ ጉባኤ መማክ ርት አባል ፡ የታሪክና የድርሰት ክፍል ሀላፊና የሊቃውንት ጉባኤ ሊቀ መንበር ሆነው አገልግለዋል ።

መልአከ ብርሃን 1ኛ ኮኩሀ ሃይማኖት ፡ 2ኛ መድሎተ አሚን፡ 3ኛ መፅሀፈ ቅኔ ዝክረ ሊቃውንት ፡ 4ኛ የበገና መዝሙር የተ ባሉ መፃሀፍትን አዘጋጅተው አሳትመዋል ።

እረሀ ሊቅ በአዲስ አበባ ከተማ ሀምሌ 24 ቀን በ1962 አ.ም. በሞት ተለዩ ።

አድማሱ ጌትዬ (ንቡረ እድ)

ንቡረ እድ አድማሱ ጌትዬ በሸዋ ክፍለ ሀገር ሀር አምባ በሚ ባል ስፍራ ተወለዱ ። በዚሁ በተወለዱበት ክፍለ ሀገር ተምረው የተመሰገኑ ሊቅ ሆነዋል ።

በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት የካህናት ባልደረባ ሆነው ሰር ተዋል ። ከዚያም በሁዋላ ንቡረ እድ አድማሱ መልአከ ገነት ተብለው

አራዳ ጊዮርጊስን አለቅነት ተሾመዋል ። ንቡረ እድም ሆነው አዲስ አለም ማርያምን ሲያስተዳድሩ ሰኔ 9 ቀን በ1921 አ.ም. አርፈዋል ።

አፈወርቅ ዘውዴ (አለቃ)

አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ በወሎ ክፍለ ሀገር በአማራ ሳይንትና ቦረና አውራጃ መጋቢት 15 ቀን በ1909 አ.ም. ተወለዱ ።

አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ በወሎ ፡ በጎጃምና በጎንደር አድባራትና ገዳማት ከነበሩ ሊቃውንት ዜማ ቅኔና የመፃሀፍት ትርጓሜ አጥ ንተዋል ።

አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ የቅኔ መምህርነት ሙያቸውን ካደላ ደሉ በሁዋላ በጎጃም ፡ በወሎና በአዲስ አበባ 36 አመታት አስተም ረው ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። በተጨማሪም በወሎ የደብረ ከርቤ ጊዮርጊስ አለቃ ሆነው 22 አመታት አገልግለዋል ።

አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ ለግእዝ መማሪያ የሚሆኑ መፃሀፍ ትን በሰባት ደረጃ መድበው አዘጋጅተዋል ። የመጀመሪያው መፅ ሀፍ «ፀያሄ ፍኖት» በሚል ርእስ በ1958 አ.ም. ታትሟል ።

እረሀ አረጋዊ አባት የግእዝ ቅኔ ሊቅ አሁንም በመንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን እያስተማሩ በኮንትራት ተቀጥረው በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ በግእዝ ቅኔና መፃሀፍት አንድምታ ትርጓሜ ክፍል ቅኔያትን በመተርጎም ፡ በማመሰጠርና በመተረክ ይሰራሉ ። ቅኔዎቻቸውም በቁጥር 187 ፡ 241 ፡ 263 እና 337 ይገኛሉ ።

እንግዳሸት (መምህር)

መምህር እንግዳሸት በጎጃም ክፍለ ሀገር ዲማ ጊዮርጊስ ተወ ለዱ ። በዚያው በተወለዱበት ገዳም ተምረው የሀዲስ የሊቅና የቅኔ መምህር ለመሆን በቅተዋል ።

መምህር እንግዳሸት በቅኔ ሙያቸው እጅግ የተመሰገኑ ከመ ሆናቸውም በላይ የቅኔ ዘረፋና ነጠቃ ስጦታ እንደነበራቸው ይነ ገራል ። ቅኔም ሆነ የመፃሀፍት ትርጓሜ በሚያስተምሩ ጊዜ ለደቀ መዝሙሮቻቸው ምስጢሩን አብራርተው ያስተምሩ ነበር ይባላል ።

መምህር እንግዳሸት የዲማ ጊዮርጊስን ገዳም መጀመሪያ በግ ብዝና ቀጥሎም በመምህርነት ሲያስተዳድሩ ኖረው ጥቅምት 25 በ1923 አ.ም. አርፈዋል ።

እንግዳ ደስታ (አለቃ)

አለቃ እንግዳ ደስታ በጎንደር ከተማ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ተወለዱ ። ንባብና ዜማ በጎንደር ከተማ ከተማሩ በዋሁላ ወደ ጎጃም ሄደው በዲማ ጊዮርጊስ ቅኔ ከመምህር ተጠምቆ ተማሩ ። ቁም ፅህፈትና ቅኔ አዋቂ ነበሩ ። አለቃ እንግዳ ደርቡሽ ጎንደርን በወረረ ጊዜ ወደእንግሊዝ አገር ሄደው እንግሊዝኛ ተምረው አስ ተርጓሚ ሆነዋል ።

አለቃ እንግዳ ደስታ እንግዳ ዳንኤል ተብለው ይጠሩ ነበር ። በእንግሊዝ አገር 24 አመት ከኖሩ በሁዋላ ወዳገራቸው ተመልሰው በጎንደር ክፍለ ሀገር መጀመሪያ ፋሲለደስን በሁዋላ አጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤልን በአለቅነት አስተዳድረዋል ።

አለቃ እንግዳ በ1914 አ.ም. በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተቀ ጥረው መፃህፍትን ከእንግሊዝኛ ወደአማርኛ ከአማርኛ ወደ እንግ ሊዝኛ በመተርጎም ሲያገለግሉ ኖረው በ1934 አ.ም. አርፈዋል ።

እንግዳ ወርቅ ሀይሉ (አለቃ)

አለቃ እንግዳ ወርቅ ሀይሉ በጎንደር ከተማ በዘመነ መሳፍንት ተወለዱ ። በተወለዱበት ከተማ ተምረው የሀዲስና የቅኔ ባለሙያ ለመሆን ችለዋል ።

አለቃ እንግዳ ወርቅ ሀይሉ መጀመሪያ ጎንደር ኤዎስጣቴዎ ስን ፣ ሁዋላም ጎንደር መድሀኔ አለምን አለቅነት ተሾመው ሲያገለ ግሉ በ1906 አ.ም. ሀምሌ 12 ቀን አርፈዋል ።

ከብቴ (አቃቤ ሰአት)

አቃቤ ሰአት ከብቴ የታወቁት የጎንደር ሊቃውንት የመም ህር ኤስድሮስና የመምህር መልከ ፄዲቅ ደቀ መዝሙር ነበሩ ። የአ ራቱ ጉባኤ (ብሉይ ፣ ሀዲስ ፣ መጽሀፈ ሊቃውንትና መፅሀፈ መነ ኮሳት)ና የአቡሻህር ሊቅ ናቸው ። ከዚህም ጋር በፀዋትወ ዜማና በቅኔ እውቀታቸው እጅግ ተመስግነውበታል ።

እኒህ ሊቅ በጎንደር ከተማ በደብረ ምጥማቅና በግምጃ ቤት ማርያም ተቀምጠው እያስተማሩ አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተ ዋል ። የታወቁት ሊቅ አለቃ ወልደ አብም የእርሳቸው ደቀ መዝ ሙር እንደሆኑ ይነገራል ። በተጨማሪም እኒህ ሊቅ አቃቤ ሰአት (ሰአት ጠባቂ በዚህ ጊዜ ውጡ ፣ በዚህ ጊዜ ግቡ የሚል የአፄ ዳኛ) ሆነው አገልግለዋል ። የአቃቤ ሰአት ከብቴ የመምህርነትና የሹመት ዘመን ከመናኔ መንግስት ተክለ ሃይማኖት እስከ ፈፃሚ መንግስት ተክለ ጊዮርጊስ ዘመነ መንግስት ነበር ይባላል ።

ካሳ (ቄሰ ገበዝ)

ቄሰ ገበዝ ካሳ በጎጃም ክ/ሀገር በይልማናና በዴንሳ አውራጃ በጎንጅ ቴዎድሮስ ደብር ተወልደዋል ። በዚሁ በተወለዱበት ደብር ከነበሩ ሊቃውንት ተምረው የተመሰገኑ የብሉይና የቅኔ መምህር ሆነው ተመርቀዋል ።

ቄሰ ገበዝ ካሳ ከአፄ ዮሀንስ እስከ ንግስት ዘውዲቱ ዘመነ መንግስት የጎንጅ ቴዎድሮስ የብሉያትና የቅኔ መምህር ሆነው አያሌ ደቀ መዛሙርትን አስተምረው በመምህርነት መርቀዋል ።

በተጨማሪም የደብሩ ቄሰ ገበዝ ሆነው አገልግለዋል ። ቄሰ ገበዝ ካሳ ከቅኔያቸው ክብደት የተነሳ እቡይ የሚባል ቅፅል እንደተሰጣ ቸው ይተረካል ።

ክፍለ ዮሀንስ

ታላቁ ሊቅ ክፍለ ዮሀንስ መጀመሪያ በጎጃም ክፍለ ሀገር በመ ተከል አውራጃ ውስጥ በሚገኘው በጋሾላ ገዳም ቶምረዋል ። ቀጥ ሎም በጎንደር ከተማ አራቱን ጉባኤ ፡ ቅኔና ዜማ አጥንተዋል ።

ክፍለ ዮሀንስ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በሁዋላ አራቱን ጉባ ኤና ቅኔ እያስተማሩ በተማሩበት ከተማ በጎንደር ደብረ ብርሃን ስላሴ ብዙ ዘመን ኖረዋል ። እኒህ ሊቅ ብዙ ሊቃውንትን በትም ህርት ወልደዋል ። የመምህርነት ዘመናቸውም ከአድያም ሰገድ ኢያሱ እስከ አፄ በካፋ ዘመነ መንግስት መጨረሻ እንደነበር ይተ ረካል ። ክፍለ ዮሀንስ በቅኔያቸው እጅግ ከተመሰገኑት ሊቃውንት አንዱ ናቸው ።

ወልደ ማርያም ሀብቴ (አለቃ)

አለቃ ወልደ ማርያም ሀብቴ በሸዋ ክፍለ ሀገር በደብረ ሲና አው ራጃ በሾተል አምባ በአታ ሰኔ 21 ቀን በ1879 አ.ም. ተወልደዋል።

በሸዋ በወሎና በጎንደር ክፍላተ ሀገር ከነበሩ መምህራን ፀዋ ትወ ዜማና ቅኔ ተምረው የዝማሬ መዋስእትና የአቋቋም መምህር ለመሆን በቅተዋል ።

አለቃ ወልደ ማርያም ሀብቴ በሸዋ ክፍለ ሀገር በመናገሻ ማር ቆስ ተቀምጠው ዝማሬ ፡ መዋስእትና አቋቋም እየነገሩ በግብዝናና በልቅና ደብሩን ሰላሳ አንድ አመት አስተዳድረዋል ።

ወልደ ዮሀንስ (መልአከ ብርሃን)

መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሀንስ በሸዋ ክፍለ ሀገር ተወለዱ ። በጎጃም ክፍለ ሀገር በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ከአለቃ ተክለ ፅዮን ቅኔ ከመምህር ገብረ ሀይወት የመፃህፍት ትርጓሜ ተማሩ ። ወደሸዋም ተመልሰው ከአለቃ ገብረ ኢየሱስ የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ አጥንተዋል ።

መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሀንስ የመፃህፍትን ትርጓሜ አስተ ምረው አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። ከደቀ መዛሙርታ ቸውም መካከል ሊቁ ገብረ ክርስቶስ አንዱ ናቸው ። በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ፍትሀ ነገስት አውጭ ሆነው አገልግለዋል ።

ወልደ ገብርኤል (ራስ)

ራስ ወልደ ገብርኤል በትግራይ ክፍለ ሀገር በኢጋሜ አውራጃ የተወለዱ የደጃች ሰባጋዲስ ልጅ ናቸው ። በራስ ስኡል ሚካኤል ቤት አድገዋል ። በዚሁ ጊዜ ቅኔ ከነአግባቡና የመፃህፍተ ሊቃ ውንትን ትርጓሜ ተምረዋል ። ራስ ወልደ ገብርኤል የተመሰገኑ ቅኔ አዋቂ ነበሩ ።

ወልደ ጊዮርጊስ (አለቃ)

አለቃ ወልደ ጊዮርጊስ በሸዋ ክፍለ ሀገር ተወለዱ ። በጎንደ ርና በጎጃም አድባራት ከነበሩ ሊቃውንት ተምረዋል ። በንጉስ ተክ ለ ሃይማኖት ዘመን በጎጃም ክፍለ ሀገር የገወራ ቁስቋምን በአለ ቅነት እያስተዳደሩ የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ያስተምሩ ነበር ። በብዙዎች በጎጃም አድባራት ሪም ተተክለው ስማቸው ሽዬ ወልደ ጊዮርጊስ እየተባለ ተዕፈል ።

አለቃ ወልደ ጊዮርጊስ ንጉስ ተክለ ሃይማኖት ከሞቱ በሁዋላ አዲስ አበባ የአራዳ ጊዮርጊስ አለቃ ሆነው በማስተዳደር ላይ እን ዳሉ በ1899 አ.ም. አርፈዋል ።

ወልደ ጊ| ሀ| ማርያም (መምህር)

መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ሀ ማርያም ሸዋ በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ሚጣቅ አማኑኤል ወረዳ ድዋይ ሚካኤል በ1848 አ.ም. ተወለዱ ። በሚጣቅ አማኑኤል ደብር ግብረ ዲቁና ተምረው ሲያ ገለግሉ ከቆዩ በሁዋላ በጎንደር ከመምህር ወልደ አብ ወልደ ሚካ ኤል ሀዲስ አጥንተዋል ።

ከዚህ በሁዋላ ወደሸዋ ተመልሰው በሚጣቅ አማኑኤል ደብር ማስ ተማር ጀምረዋል ። ወደአዲስ አበባም መጥተው በእንጦጦ ራጉኤል ደብር ሀዲስ እያስተማሩ ኖሩ ። ከዚያም ወደመናገሻ ቅዱስ ጊዮ ርጊስ ተዛውረው የማስተማር ስራቸውን ቀጥለዋል ። ከደቀ መዛሙ ርታቸውም መካከል አንዱ ብላቴን ጌታ ሀሩይ ወ ስላሴ ነበሩ ።

መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ሀ/ ማርያም ከጉባኤ ሳይለዩ በ1931 አ.ም. ወደ ደብረ ሊባኖስ ሄደው መአረገ ምንኩስና ተቀብለው ሲኖሩ በ90 አመታቸው መስከረም 29 ቀን በ1939 አ.ም. አርፈዋል ።

ወርቅ አገኘሁ ተክሌ (አለቃ)

አለቃ ወርቅአገኘሁ ተክሌ በሸዋ ክፍለ ሀገር ወግዳ ወራና ፈንጣጣ በምትባል ቦታ በ1873 አ.ም. ተወለዱ ። በሸዋ ክፍለ ገር አድባራትና ገዳማት ከነበሩ መምህራን ቅኔ ተምረው በመ ምህርነት ተመርቀዋል ። ከዚህ በሁዋላ አለቃ ወርቅ አገኘሁ በአባ ታቸው ወንበር ተተክተው በማስተማር ከጉባኤ ሳይለዩ ኖረው በተወለዱ በ86 አመታቸው ታህሳስ 19 ቀን በ1959 አ.ም. አረፉ ።

ውብሸት (ቄሰ ገበዝ)

ቄሰ ገበዝ ውብሸት በጎጃም ክፍለ ሀገር በብቸና አውራጃ በብቸና ጊዮርጊስ ደብር ተወለዱ ። በትውልድ ቦታቸው ንባብና ፀዋትወ ዜማ ተማሩ ። ከዚያም በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ከነበ ሩት መምህር ተጠምቆ ብሉይና ቅኔ ተምረው በመምህርነት ተመ ርቀዋል ። እንዲሁም በዚሁ ገዳም የፍትሀ ነገስትን ትርጓሜ አጥንተዋል ።

እኒህ ሊቅ በብቸና ጊዮርጊስ ደብር ብሉይ ፍትሀ ነገስትና ቅኔ እያስተማሩ ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። በተለይም እጅግ የሚመሰገኑበት የቅኔ ሙያቸው ብዙ ፍሬ አስገኝቷል ። በተጨ ማሪም በቄስ ገበዝነት ደብሩን ለረጅም አመታት አገልግለዋል ።

መምህር ውብሸት ከማስተማር ስራቸው ሳይለዩ ኖረው ጥቅምት 13 ቀን በ1942 አ.ም. አርፈው ባገለገሉበት ደብር በብቸና ጊዮርጊስ ተቀብረዋል ።

ዘገየ (ሊቀ ሀሩያን)

ሊቀ ሀሩያን ዘገየ በጎጃም ክፍለ ሀገር በባሶ ሊበን ወረዳ በየ ውሽ ቅዱስ ሚካኤል ደብር ከአባታቸው ከአቶ ገብረ ስላሴ ሀይሉና ከእናታቸው ከወ ሮ ውዲቱ ሀይሉ በ1864 አ.ም. ተወለዱ ።

በተወለዱበት ክፍለ ሀገር በሚገኘው ደብር በጎንጅ ቴዎድ ሮስ መፃህፍት ቅኔና አገባብ ተምረዋል ። የግእዝን ሰዋስው አካሄድ በቅያቸው የተረጎሙ ተመራማሪና ቅኔ ፈጣሪ ሊቅ ነበሩ ። የዋድላንም አገባብና እርባ ቅምር ከሚጫው ሊቅ ከማእበል ወልደ ሀይወት አጥንተዋል ።

እኒህ ሊቅ በጎጃም ክ ሀገር በደብረ መዊእ ገዳም ለረጅም አመታት ቅኔ ከነአገባቡ በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍ ርተዋል ። ከቀደ መዛሙርታቸውም አንዱ አለቃ ቃለ ማእነቅ የመና ገሻ ማርያም የቅኔ መምህር ናቸው ።

ሊቀ ሀሩያን ዘገየ ገብረ ስላሴ ለብዙ ዘመናት በትጋትና በቅን ነት ሲያስተምሩ ኖረው በ1932 አ. ም. አርፈዋል ። (ታሪኩ የልጅ ልጃቸው መሪጌታ በላይ መኮንን ካቀረቡት በምህፃር የቀረበ ነው።)

ዝማነህ (ደብተራ)

ደብተራ ዝማነህ በሸዋ ክፍለ ሀገር ተወልደዋል ። በአዲስ አበባ ከተማ አራዳ ጊዮርጊስ ሲተከል ጀምሮ በደብተርነት ሲያገ ግሉ ኖረዋል ። ደብተራ ዝማነህ ጥሩ ቅኔ አዋቂ ነበሩ ።

ይትባረክ ቂርቆስ (መሪጌታ)

መሪጌታ ይትባረክ ቂርቆስ በጎጃም ክፍለ ሀገር በብቸና አውራጃ በደብረ ፅሙና ተወልደዋል ። በተወለዱበት በደብረ ፅሙ ናና በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ተምረው በድጓና በቅኔ መምህር ነት ተመርቀዋል። ከዚህም ሌላ መርሀ እውር ፣ ቀመረ አረብ (ባህረ ሀሳብ) አዋቂ ነበሩ ። እኒህ ሊቅ መሪጌታ ያሬድ ቂርቆስም እየተ ባለ ይጠራሉ

መሪጌታ ይትባረክ ቂርቆስ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በሁዋላ ጎጃም በደብረ ፅሙና በወይባ ደብርና በእነብሴ ፣ ወሎ በአማራ ሳይ ንት ፣ ሸዋ በአራተ ማርያም ደብር ቅኔ አስተምረዋል ። ከዚያም በሁዋላ እንደገና ወደ ተወለዱበት ደብረ ፅሙና ተመልሰው በማ ስተማር ላይ እንዳሉ በ1946 አ.ም. አርፈዋል ።

ደለለ (መሪጌታ)

መሪጌታ ደለለ በጎጃም ክፍለ ሀገር ዋሸራ ማርያም ተወለዱ ። ከስመ ጥሩው መምህር ተክሌ ዘዋሸራ ቅኔ ከነአገባቡና ከነእርባ ቅምሩ ተምረዋል ። የመምህራቸውን ወንበር ተረክበው ሲያስተምሩ እያሌ ደቀ መዛሙርትን አውጥተዋል ። መሪጌታ ደለለ ፍሬያማ የሆነ የማስተማር ስራቸውን በማከናወን ላይ እርፈው ተምረው ባስ ተማሩበት ዋሸራ ማርያም ተቀብረዋል ።

ደመረ (ግራጌታ)

ግራ ጌታ ደመረ ትውልዳቸው በሸዋ ክፍለ ሀገር ነው ። በአ ዲስ አበባ ከተማ በአራዳ ጊዮርጊስ ደብር ቅኔ ሲያስተምሩ ኖረው አርፈዋል ።

ደስታ (አለቃ)

ጋይንቴ ደስታ ትውልዳቸው በጎንደር ክፍለ ሀገር ጋይንት ነው ። የብሉይና የቅኔ መምህር ነበሩ ። ይህንኑ ሙያቸውን እያስተ ማሩ በሀረር ከተማ ይኖሩ እንደነበር ይነገራል ። ጋይንቴ ደስታ በቅኔ ሙያቸው እጅግ የተመሰገኑ ናቸው ።

ድንቄ (አለቃ)

አለቃ ድንቄ በሸዋ ክ/ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ በጅ ሩና ወግዳ ወረዳ ሶምሳ በሚባል ቦታ ተወለዱ ።

የንባብ ትምህርትና መዝሙረ ዳዊትን ከፈፀሙ በሁዋላ ተጉለት ሄደው ተጉለቴ ዜማ ፣ ቅኔ ሰላሌ ከአለቃ ዘዮሀንስ ፣ ሀዲስ ካለቃ ሀሩይ ተምረዋል ። የብሉያቱንም ትርጓሜ ዘልቀውታል ።

አለቃ ድንቁ የቅኔ ሙያቸውን ካስፋፉ በሁዋላ ጉባኤ ዘርግተው እያስተማሩ ብዙ ደቀ መዛሙርትን አውጥተዋል ። ከ1898 አ.ም. ጀምሮ በእንጦጦ ራጉኤል ደብር ቅኔ እያስተማሩ ኖረዋል ።

አለቃ ድንቁ በእንጦጦ ራጉኤል ደብር መጀመሪያ ርእሰ ደብር በሁዋላም ሊቀ ጠበብት ሆነው አገልግለዋል ። በመጨረሻም የመጋ በረ ብርሃን ወጨፌ ማርያም አለቃ ሆነው በመሪጌትነትም እያገለገሉ ሳለ ታህሳስ 26 ቀን በ1934 አ.ም. አርፈው በዚሁ ደብር ተቀብረዋል።

ድንቆ ማርቆስ

ድንቆ ማርቆስ በጎንደር ክ ሀገር ተወለዱ ። መጀመሪያ በጎን ደር ከተማ ደብረ ብርሃን ስላሴ አራቱን ጉባኤያት ባህረ ሀሳብና ቅኔ ያስተምሩ ነበር ይባላል ። በዚሁም ላይ በጎንደር የደብረ ብርሃን ስላሴ አለቃ ሆነው አገልግለዋል ። ታላቁ ሊቅ ክፍለ ዮሀንስም ከእ ርሳቸው እንደተማሩ ይነገራል ።

ገብረ መስቀል (መምህር)

መምህር ገብረ መስቀል በትግራይ ክ ሀገር በእንደርታ አው ራጃ በደብረ ገሊላ ተወለዱ ። በተንቤን ውስጥ እንዳ ማርያም ቆራር በተባለው ገዳም እየተማሩ አደገዋል ። በጎጃምና በዋድላ ደላንታ እየተዘዋወሩ ከሊቃውንቱ ቅኔና አባባብ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ።

መምህር ገብረ መስቀል በትግራይ ክፍለ ሀገር ቤተ ዮሀንስ በተባለው ደብር ለብዙ አመታት ቅኔ በማስተማር አያሌ ደቀ መዛ ሙርትን ካበረከቱ በሁዋላ በ1935 አ.ም. አርፈዋል ።

ገብረ መድህን (አለቃ)

አለቃ ገብረ መድህን የትግራይ ክፍለ ሀገር ተወላጅ ናቸው ። በዚያው በትግራይ ንባብና ዜማ ካጠኑ በሁዋላ በጎንደር ክፍለ ሀገር አድቋም በጎጃም ክፍለ ሀገር ቅኔ ተምረው በመምህርነት ተመር ቀዋል ። ቀጥሎም ከወልደ አብ ወልደ ሚካኤል ደቀ መዝሙር ከቡ ልጌ አለቃ ወልደ አግኑኤል ሀዲሱን እጥንተዋል ። ከዚያም ከማን መልሶህ ወልደ ስላሴ የመፃህፍት ሊቃውንትን ትርጓሜ ቀፅለዋል ።

አለቃ ገብረ መድህን ትምህርታቸውን ጨርሰው ደብረ ሊባ ኖስ ተቀምጠው ሲያስተምሩ ተመርጠው መጀመሪያ ደብረ ብር ሃን ስላሴን ፣ በሁዋላም አራዳ ጊዮርጊስን አለቅነት ተሾመዋል ። በሀረ ርጌ ክፍለ ሀገርም መጀመሪያ አደሬ ጢቆ ስላሴን ፣ በሁዋላም የአሰ ቦትን ገዳም እንደገና አቅንተው አስተዳድረዋል ።

አለቃ ገብረ መድህን የአስተዳደርና የማስተማር ስራቸውን ሳያቋርጡ መስከረም 4 ቀን በ1918 አ.ም. አርፈው በአሰቦት ገዳም ተቀብረዋል ።

ገብረ መድህን (ግራጌታ)

ግራ ጌታ ገብረ መድህን ትውልዳቸው በሸዋ ክ/ሀገር ነው ። የንባብና የዜማ ትምህርታቸውን በትውልድ ስፍራቸው ካጠናቀቁ በሁዋላ ወደ ጎጃም ተሻግረው በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ቅኔ ከአለቃ ተክለ ፅዮን ተምረዋል ።

ግራጌታ ገብረ መድህን በአዲስ አበባ መንበረ ፀባኦት ቅድ ስት ስላሴ ሲተከል ጀምሮ የደብሩ የቅኔ መምህር ሆነው ተሾመው ለብዙ አመታት ሲያገለግሉ ከቆዩ በሁዋላ አርፈዋል ።

ገብረ ሥላሴ ክንፉ (መምህር)

መምህር ገብረ ስላሴ ክንፉ ትውልዳቸው በወለጋ ክፍለ ሀገር ነው ። ቅኔና መፅሀፈ ሊቃውንት በጎጃም ክፍለ ሀገር በየገወራ ግር ያም ደብር ከአለቃ ሸዩ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ ብሉይና ቅኔ በደብረ ግር ቆስ ከመምህር ሰረገላ ብርሃን ፣ አገባብና እርባ ቅምር በደብረ ገነት ኤልያስ ከሊቀ ጠበብት አይቸሀ ፣ የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትር ጓሜ በደንበጫ ሚካኤል ከመልአከ ሰላም ገብረ ግርያም (ቡሬ ገብረ ግርያም) ተምረዋል ። በተጨማሪም የፀዋትወ ዜማና የሀዲስ መም ህር ሆነው ተመርቀዋል ።

መምህር ገብረ ስላሴ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በሁዋላ እየተ ማሩ ባደጉበት በየገወራ ግርያም ደብር ሀዲስና ቅኔ ማስተማር ጀመሩ ። ከዚህም በሁዋላ በደብረ ገነት ኤልያስ ተቀምጠው ቅኔ ከነ አገባቡ ፣ ብሉይ ሀዲስና ፍትሀ ነገስት እያስተማሩ ብዙ መምህራ ንን መርቀው ሾመዋል ።

መምህር ገብረ ስላሴ በቅኔያቸው ከሚደነቁት ሊቃውንት አንዱ ናቸው ። እኒህ ሊቅ ከማስተማርና ምስጢረ መፃህፍትን ከመመር መር ሳይለዩ በ1938 አ.ም. አርፈው በደብረ ገነት ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

ገብረ ስላሴ (ንቡረ እድ)

ንቡረ እድ ገብረ ስላሴ በሸዋ ክፍለ ሀገር በደብረ ብርሃን ከተማ በ1837 አ.ም. ተወልደዋል ። በአንኮበር ከተማ ዜማና ቅኔ እየተ ማሩ አድገዋል ።

ንቡረ እድ ገብረ ስላሴ ከ1860 አ.ም. ጀምሮ ፀሀፈ ትእዛዝ ሆነው ሰርተዋል ። በ1900 አ.ም. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የፅሀፈት

ሚኒስቴር ሆነው ተሾመዋል ። እንጦጦ ራጉኤል ሲተከል ጀምሮ እስ ተዳዳሪ ሆነው አገልግለዋል ። በ1920 አ.ም. የአዲስ አለም ማርያም ንቡረ እድ ሆነዋል ።

ንቡረ እድ ገብረ ስላሴ ጠቃሚ የሆነ አገልግሎታቸውን ሲያ በረከቱ ኖረው በ1905 አ.ም. ጥቅምት 27 ቀን አርፈው በደብረ ሀይል እንጦጦ ራጉኤል ተቀብረዋል ።

ገብረ ዋህድ ህሼ (አለቃ)

አለቃ ገብረ ዋህድ ህሼ በትግራይ ክፍለ ሀገር በእንደርታ አውራጃ ገረአልታ ልዩ ስሙ አባ ሰላማ በተባለ ቦታ ተወለዱ ። ቅኔ ፣ ዜማና ትርጓሜ መፃህፍት አዋቂ ነበሩ ።

አለቃ ገብረ ዋህድ በቤተ ክህነት የሊቃውንት ጉባኤ አባል ሆነው ሲሰሩ ቆይተው ታህሳስ 4 ቀን በ1961 አ.ም. አርፈው በአዲስ አበባ በመካነ ህይወት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

ጎሹ አራት አይና

አራት አይና ጎሹ በጎጃም ክ/ ሀገር ተወለዱ ። በታወቀው ደብር ሞጣ ጊዮርጊስ ተምረው የአራቱ ጉባኤ መምህር ሆነው ተመርቀ ዋል ። አራቱን ጉባኤ ያጠናቀቁ ሊቅ በመሆናቸው «አራት አይና» የሚል ቅፅል ተሰጥቷቸዋል ።

አራት አይና ጎሹ በተማሩበት ደብር ጉባኤ ዘርግተው አለ ቅነቱንም ደርበው የታወቁ ሊቃውንት እነመምህር ሰው አገኘ ሁን ፣ እነአለቃ ገብረ ኤልያስን ፣ እነመምህር ፀበሉን ፣ እነአለቃ ተክለ ፅዮንን ፣ እነአለቃ ስነ ጊዮርጊስን ፣ እነ መምህር ክፍለ ጊዮር ጊስንና ሌሎችንም ብዙ ሊቃውንት አስተምረው የብሉያት ትር ጓሜ መምህር አድርገው መርቀዋል ።

አራት አይና ጎሹ በዘመናቸው እጅግ የታወቁና የተመሰገኑ የትርጓሜ መፃህፍትና የቅኔ ሊቅ ነበሩ ። እኒህ ሊቅ ከሚወዱት ጉባኤ ሳይለዩ ጥር 29 ቀን በ1861 ዓ.ም. አርፈው የውሽ ሚካኤል በተባለው ደብር ተቀብረዋል ።

ጥበቡ ገሜ (መምህር)

አለቃ ጥበቡ ገሜ በሸዋ ክፍለ ሀገር በሰላሌ አውራጃ በጎህ ፅዮን ከተማ ሰኔ 10 ቀን በ1873 ዓ.ም ተወለዱ ።

ጎህ ፅዮን ከነበሩት ከአባ ገብረ ማርያም ዘንድ እስከ ግብረ ዲቁና ያለውን ትምህርት ተምረዋል ። ከዚያም ወደ ጎጃም ተሻግረው በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ቅኔ ከነአገባቡ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ፣ የብሉይን ትርጓሜ ከመልአከ ገነት ክፍሌና ከመምህር ገብረ ኤልያስ በሞጣና በደብረ ማርቆስ አድባራት ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ በየጁና በሰቆጣ ከነበሩ ሊቃውንት የቅኔና የመፃህፍት ትርጓሜ ትምህርት ሙያቸውን አደላድለዋል ።

አለቃ ጥበቡ ገሜ በወሎና በሸዋ በሚገኙ ገዳማትና አድባራት አያሌ አመታት አስተምረው ብዙ የቅኔ መምህራንን መርቀው አውጥተዋል ።

እኒህ ሊቅ 37 ዓመታት ባስተማሩበት በሸዋ በሰላሌ አውራጃ በሚገኘው በስሬ መድሃኔ አለም ደብር በተወለዱ በ91 አመታቸው አርፈው ሀምሌ 27 ቀን በ1964 አ.ም. ተቀብረዋል ። (ታሪኩ ለአርባ ቀን መታሰቢያቸው ከታተመው ፅሁፍ በምህፃር የቀረበ ነው ።)

ፈንታ ገብርየ (መልአከ ብርሃን)

መልአከ ብርሃን ፈንታ ገብርየ በጎጃም ክፍለ ሀገር በጎዛምን ወረዳ ዝግባ አቦ ተወልደዋል ። አባትና እናታቸው በልጅነታቸው

ስለሞቱባቸው ከፊደል እስከዳዊት ድጋም ያለውን በንጉስ ተክለ ሃይማት ግቢ ተማሩ ። ከዚያም ዜማ ቤት ገብተው ፀዋትወ ዜማ ፣ ቅኔ ከመምህር ሰረገላ ብርሃን ፣ ብሉያቱን ከአለቃ ገብረ ኤልያስ ፣ ሊቃውንቱን ከአለቃ ወልደ ጊዮርጊስ አጠኑ ። ፅህፈት ፣ ድጉሰት ስእል መሳልና ሀረግ መንደፍም ይችሉ ነበር ።

መልአከ ብርሃን ፈንታ ገብርየ በአለቅነት አጋምና ጊዮርጊስን መልአከ ብርሃን ሆነው ብቸና ጊዮርጊስን አስተዳድረዋል ።

እኒህ ሊቅ ሚያዝያ 27 ቀን በ1935 አ.ም. አርፈው በደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

ፈንቴ (መሪጌታ)

መሪጌታ ፈንቴ ዋሴ ትውልዳቸው በጎጃም ክፍለ ሀገር በዋሸራ ማርያም ገዳም ነው ። ከታላቁ ሊቅ ከመምህር ተክሌ ዘዋሸራ የቅኔ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በሁዋላ ወደአቸፈር ሄደው ከመምህር ገሰሰ የጎዳና ቅኔ እውቀታቸውን አደላድለዋል ።

መሪጌታ ፈንቴ ተወልደው በተማሩበት በዋሸራ ማርያም ገዳም አስተምረው ብዙ የቅኔ መምህራንን መርቀው ሾመዋል ። እኒህ አረጋዊ ምሁር ከጉባኤ ሳይለዩ ለብዙ ዘመናት ከኖሩ በሁዋላ ሀምሌ 25 ቀን በ1955 አ.ም. በ71 አመታቸው አርፈው በዚያው በዋሸራ ማርያም ተቀብረዋል ።

ባለቅኔዎቹ

በፈይል ተራ

(የቅኔዎቻቸው ቁጥሮች ከስሞቻቸው ጋር ሰፍረዋል ። ከስማቸው በፊት የኮከብ ምልክት የተደረገባቸው የህይወት ታሪካቸው ባጭሩ ተፅፎላቸዋል) ።

ተ. ቁ.	ሙሉ ስም
*1	ሀይለ ስላሴ (መልአከ ሀይል) ፡ 284 ፡ 216
*2	ሀይሉ (አጋፋሪ) ፡ 139
3	ሀይሉ (ዘመቀሌ) ፡ 268
4	ሀይሌ (አለቃ) ፡ 283
5	ሀይመት (ወይዘሮ) ፡ 250
6	ህሩይ (አለቃ) ፡ 273 ፡ 299
*7	ለማ ሀይሉ (አለቃ) ፡ 73 ፡ 88 ፡ 128 ፡ 333 ፡ 335
8	ልሳነ ወርቅ (አለቃ) ፡ 313
*9	መርሻ (መጋቢ ፡ ዘዲማ ጊዮርጊስ) ፡ 79 ፡ 265
*10	መርአዊ (አለቃ ፡ ዘተንታ) ፡ 120
11	መንግስቱ (መሪጌታ) ፡ 85 ፡ 87 ፡ 184
*12	መኮንን ሰሎሞን (አለቃ) ፡ 75
13	ምስራቅ (አለቃ ፡ ዘኤልሻማ) ፡ 65
14	ምትኩ እውር (ዘደብረ ወርቅ) ፡ 181
15	ምትኩ (መጋቢ) ፡ 108
16	ምንደስይል (ደብተራ) ፡ 143 ፡ 219
17	ሲኖዳ (ፀሀፌ ትእዛዝ ፡ ዘጎንደር) ፡ 249
18	ሳህሌ ወልደ ተክሌ (አለቃ) ፡ 228
*19	ስመኝ (መሪጌታ ፡ ዘጠላዘሞ) ፡ 37 ፡ 58 ፡ 60

*20 ቀስሙ (መምህር ፡ ዘዋሽራ) ፡ 196
21 ቂያ (አባ ፡ ዘአዘዞ) ፡ 317
22 በትረ ጊዮርጊስ (እጨጌ) ፡ 276
*23 በዛብህ ወንድም (አለቃ) ፡ 38 ፡ 162
24 ባቱኤል ፡ 165
25 ተሰማ (አለቃ) ፡ 91
26 ተስፋ (አባ ፡ ዘደብረ ሊባኖስ) ፡ 144
*27 ተክለ ሃይማኖት (ነጮ) ፡ 309
28 ተክለ ሃይማኖት (አቤቶ) ፡ 362 ፡ 297
29 ተክለ ጊዮርጊስ ፡ 83
*30 ተክለ ፅዮን (አለቃ) ፡ 95 ፡ 131 ፡ 158 ፡ 175 ፡ 192 ፡ 217 ፡ 238 ፡ 240 ፡ 243 ፡ 266 ፡ 269 ፡ 316
*31 ተክሉ (መምህር ፡ ዘዋሽራ) 14 ፡ 33 ፡ 34 ፡ 69 ፡ 189 ፡ 221 ፡ 237 ፡ 304
32 ተዋንይ ፡ 206
*33 ተጎኘ (መልአከ ፀሀይ) ፡ 115
34 ቴዎድሮስ (መልአከ ፀሀይ) ፡ 216
35 ንጉሴ ይመር (አለቃ ፡ ዘዲማ) ፡ 53 ፡ 56
36 አለሙ (መጋቢ ፡ ዘጎንጅ) ፡ 62
37 አምደ ሚካኤል (አለቃ) ፡ 51 ፡ 224
38 አርአያ ወረታ (አቶ) ፡ 211
39 አበበ (አለቃ ፡ ዘሀመረ ኖህ ጎንደር) ፡ 35
40 አበበ መሸሻ (መረጌታ ፡ ዘደብረ ወርቅ) ፡ 137
41 አባተ (መረጌታ) ፡ 10
42 አብርሀ (አፈ ንቡረ እድ ፡ ዘአክሱም) ፡ 160
*43 አካለ ወልድ (መምህር) ፡ 198 ፡ 314 ፡ 319
44 አያቼህ (መጋቢ ፡ ዘደብረ ወርቅ) ፡ 202 ፡ 296
*45 አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን) ፡ 1 ፡ 9 ፡ 12 ፡ 13 ፡ 54 ፡ 97 ፡ 118 ፡ 119 ፡ 130 ፡ 115 ፡ 138

*46 አድማሱ (ንቡረ እድ) ፡ 72 ፡ 89 ፡ 323
*47 አፈ ወርቅ ዘውዴ (አለቃ) ፡ 187 ፡ 241 ፡ 263 ፡ 338
48 እስክንድር (አፂ) ፡ 283
*49 እንግዳሸት (መምህር ፡ ዘዲማ) ፡ 233 /ሀ
*50 እንግዳ ዳንኤል (አለቃ) ፡ 132 ፡ 233
*51 እንግዳ ወርቅ ሀይሉ (አለቃ) ፡ 64 ፡ 277
*52 ከብቴ (አቃቤ ሰአት) ፡ 8 ፡ 177 ፡ 201 ፡ 270
53 ኪዳነ ወልድ (አለቃ) ፡ 318
*54 ካሳ (ቄስ ገበዝ) ፡ 321 ፡ 334
55 ካሳ (መምህር) ፡ 220
*56 ክፍለ ዮሀንስ (ዘጎንደር) ፡ 199 ፡ 25 ፡ 306
57 ወልደ ግርያም ሀብቴ (አለቃ) ፡ 68
58 ወልደ ግርያም ጉታ (መምህር) ፡ 48
59 ወልደ ግርያም (መምህር ፡ ዘዲማ) ፡ 109
60 ወልደ ሥላሴ (አለቃ) ፡ 242
61 ወልደ ያሬድ (አለቃ ፡) ፡ 102
*62 ወልደ ዮሀንስ (መልአከ ብርሃን) ፡ 113
*63 ወልደ ጉብርኤል (ራስ) ፡ 106 ፡ 112 ፡ 157
*64 ወልደ ጊዮርጊስ (አለቃ ሸዋ) ፡ 74
*65 ወልደ ጊዮርጊስ (መምህር ፡ ዘራጉኤል) ፡ 5 ፡ 227
*66 ወርቅ አገኘሁ ተክሉ (አለቃ) ፡ 187
*67 ውብሸት (ቄስ ገበዝ ፡ ዘብቸና ጊዮርጊስ) ፡ 20 ፡ 28 ፡ 264 ፡ 300 ፡ 324 ፡ 325
68 ዘወልዴ (አለቃ) ፡ 303
69 ዘዮሀንስ (አለቃ) ፡ 117 ፡ 121 ፡ 136 ፡ 235
*70 ዘገየ (ሊቀ ህሩያን) 161 ፡ 182
*71 ዝግንህ (ደብተራ ፡ ዘንጉተ ፅጌ) ፡ 11 ፡ 133
*72 ይትባረክ ቂርቆስ (መሪጌታ) ፡ 20 ፡ 59
73 ይኩኖ አምላክ (አቶ) ፡ 101

74 ይግዛው (አለቃ ፡ ዘደብረ ወርቅ) ፡ 164
*75 ዮፍታሄ ንጉሴ (ቀኝ ጌታ) ፡ 61
*76 ደለለ (መሪጌታ ፡ ዘዋሸራ) ፡ 271
77 ደመረ (ግራጌታ ፡ ዘገንተ ፅጌ) ፡ 110
78 ደስታ (አለቃ ፡ ዘተድባበ ማርያም) 23 ፡ 92
79 ደስታ (መምህር ፡ ዘዋሸራ) ፡ 293
*80 ደስታ (አለቃ) ፡ 294
81 ደቀ እስጢፋ ፡ 197
82 ዳኜ (አለቃ ፡ ዘራጉኤል) ፡ 103
*83 ድንቄ (አለቃ) ፡ 285
*84 ድንቆ ማርቆስ ፡ 205 ፡ 308 ፡ 311
85 ጀምበሬ (መሪጌታ) ፡ 41
*86 ገብረ መስቀል (መምህር) ፡ 22
87 ገብረ መድህን (መምህር) ፡ 153
*88 ገብረ መድህን (አለቃ ፡ ዘአሰቦት) ፡ 27 ፡ 207
89 ገብረ መድህን (አለቃ ፡ ዘሌሙን ሰላሌ) ፡ 111
*90 ገብረ መድህን (ግራጌታ) ፡ 57
91 ገብረ መድህን (መምህር ፡ ዘማህደረ ማርያም) ፡ 326
92 ገብረ ሚካኤል እውር (ዘሰላሌ) ፡ 231
93 ገብረ ማርያም (ቄስ ገበዝ) ፡ 248
*94 ገብረ ስላሴ ክንፉ (መምህር ፤ ዘኤልያስ) ፡ 70 ፡ 86 ፡ 105 ፡ 155 ፡ 163 ፡ 170 ፡ 281
*95 ገብረ ስላሴ ፡ (ንቡረ እድ) 195
96 ገብረ ኢያሱስ (መምህር) ፡ 4
*97 ገብረ ዋህድ ህሼ (አለቃ) ፡ 142
98 ገብረ ጊዮርጊስ (መምህር) ፡ 29
99 ገብረ ፃድቅ (መሪጌታ ፡ ዘፍቼ ጊዮርጊስ) ፡ 24
100 ገብሬ (አለቃ ፡ ዘደብረ ሊባኖስ) ፡ 315
101 ገዝሙ (ደብተራ) ፡ 174

102 ጌቴ ገሞራው ፡ 151
*103 ጎሹ አራት አይና ፡ 251
104 ጎበዜ (አለቃ) ፡ 307
105 ጥበቡ (መሪጌታ) ፡ 52
*106 ጥበቡ ገሚ (መምህር) ፡ 141 ፡ 147
107 ጫልቲ ሀይሉ (አባ) ፡ 166
*108 ፈንታ ገብርየ (መልአከ ብርሃን) ፡ 6
109 ፈንታየ (አለቃ) ፡ 127
*110 ፈንቴ (መሪጌታ) ፡ 15

ከዚህ መፅሀፍ ቅርብ ዝምድና ያላቸው መፃህፍት ዝርዝር

መፅሀፈ ቅኔ ፡

ከፀሓፂን ጊታ ሠናይ ወልደ ስላሴ ፡ አዲስ አበባ 1918 ፡

መፅሀፈ ቅኔ ፡ ዝክረ ሊቃውንት

ከመልአክ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ፡ አዲስ አበባ 1963 ፡

ንባብ ወትርጓሜ ዘቅኔያት ፡ አእማደ ምስጢራት ፡

ከመምህር ይሬይስ መርቱ ፡ አዲስ አበባ 1960 ፡

የቀድሞ ቅኔዎች ከነትርጓሜአቸው ፡

ከአለቃ ይኩኖ አምላክ ንብረ ስላሴ ፡ አዲስ አበባ 1959 ፡

ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት ፡

ከሊቀ ስልጣናት ሀብተ ጣርያም መርቅነህ ፡ አዲስ አበባ 1963 ፡

መፅሀፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ፡

ከመንግስቱ ለማ ፡ አዲስ አበባ 1959 ፡

መፅሀፈ ሰዋስው ፡

ከአለቃ ታየ ፡ ምንኩሱ 1889 ፡